የደሪሲፍዳ



ተፀተዋ

በአበባው ተክሌ

እንደ መነሻ

ሐሚልተን በሚኰሰኩሰው አገጩ ፊቴን እየሞረደኝ ስለ ነበረ 'መልካም ወስፋት' ብዬ በማሾፍ ላይ እንዳለሁ፥ ስልኩ ጮኸና አነሣሁት። የደወለልኝ የጽሑፍ ሥራዎቼን የሚያሳትምልኝ ወኪሌ ፋበር ነበር።

«ደህና አደርሽ የእኔ ቆንጆ?» ሲል ሞቅ ያለ ሰላምታ ሰጠኝና፥ «ዛሬ ወደ አራቱ ሰዓት ገደማ ላይ ከዚያ ከሰውዬ ጋር ቀጠሮ አለን። መቼም እንዳልረሳሺው እርግጠኛ ነኝ» አለኝ። የፋበር አነጋገር ሁል ጊዜ ይህን ይመስል ነበር።

«አልረሳሁትም» አልኩት። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፥ዘንግቼው ነበር። የማይሳካ ነገር ከወዲሁ በደመ ነፍሴ ስለ ሚታወቀኝ መርሳቱን ነበር የምመርጠው።

ለአራት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ፥ በባየንደር አሳታሚ ድርጅት ሕንፃ መግቢያ ላይ እንድንገናኝ ፋበር ከነገረኝ በኋላ ስልኩን ዘጋ። ሐሚል ተን፥ በራ ራሱን ከትራሱ ላይ ቀና በማድረግ ትኩር ብሎ ይመለከተኝ ነበር።

«ማን ነው የደወለልኝ?» ሲልም ጠየቀኝ።

«ሚስትህ ናት፤ እናም ላውንድሪ የገባውን ልብስ ማውጣቱን እንዳትረሳ ነው የምትልህ» አልኩት።

በድንጋጤ ፊቱ ዐመድ መሰለ። ስቀልድበት እንደ ነበረ ወዲያውኑ አልነቃብኝም። ሐሚልተን ነገሮችን ቶሎ ለመረዳት ፍጥነት ከሌላቸው ሰዎች የሚደመር ነው። ከእኔ ጋር አንሶላ ለመጋፈፍ የፈቀድኩለት በርሱነቱ ተማርኬ ሳይሆን፥ ባብሮ አደጌ ጓደኛዬ በላውራ ካደረብኝ ቅናት የተነሣ ብቻ ነበር። የሐሚልተን ሚስት የሆነችውና ለፕላስቲክ ቀዶ ጥገና ሆስፒታል ከገባች ውላ ያደረችው ጓደኛዬ ላውራ ቆንጆ ሽንቃጣ ቁመና ያላት ልጅ ናት። የእኔ ቅርፅ ደግሞ ይበልጥ ወደ ወንዳወንድነቱ የሚያመዝን ነበር።

ያለ ማጋነን ግዙፍ ነኝ ባልልም ፥ ቁመቴ ከአንድ ሜትር ከሰባ አምስት ሴንቲሜትር በላይ ነው ። ሐሚልተንና ላውራ ግን አጭር የሚባሉ ናቸው ። የሁለቱም ቁመት ከእኔ በዐሥራ አምስት ሴንቲ ሜትር ያህል ያንሳል ። ታዲያ እንደ መሰሎቼ ረጃጅም ሴቶች ሁሉ ፥ እኔም የአጫጭር ወንዶችን ስሜት የመቀስቀስ ኃይል ነበረኝ ። ጡቶቼ እንደ ላውራ ያኮጠኮጡ አይደሉም ፤ ጸጉሬንም እንደርሷ በማሳደግ ምትክ አሳጥሬ ነበር የምቆረጠው ። እንደ ዐይኔ ብሌኖች ጸጉሬም ቡናማ ቀለም አለው ።

ዕድሜዬ ሐያ ስምንት ዓመት ሲሆን ፥ የተወለድኩት በፔሩ ዋና ከተማ ሌማ ውስጥ ነው ። በሦስት ዓመት ከእኔ የምታንሰዋ ጓደኛዬ ላውራ ግን ፥ የተወለደችው በፈረንሳይ ዋና ከተማ ፓሪስ ነበረ ።

አባቴ በመኪና አደጋ ሲሞት የሐያ ሁለት ዓመት ልጅ ነበርኩ ። እናቴም ለጥቂት ወራት ብትታገሥም ፥ ከእኔ በሁለት ዓመት የሚበል ጠውንና የስፔን ተወላጅ የሆነውን ጅዋንን አግብታ ኮስት ዲ ሶሎ ወደ ተባለች የወደብ ከተማ ሔዳለች ። የእናቴ ስም ማቲልዳ ይባላል ። ለገና በዓል ካርድ ከምንለዋወጥ በስተቀር ተጠያይቀን አናውቅም ።

አንድም ጊዜ ባል አላገባሁም ፤ በጋብቻ መኖርም አልፈልግም ። ሆኖም ግን ፥ ደስ ካለኝ ወንድ ጋር ስሜቴን አረካለሁ ። ከሴቶች ይልቅ የወንድ ጓደኞች ብዙ አሉኝ ። እርግጠኛ ነኝ ፥ ስለኔ ለማወቅ ከላይ የጠቀስኩት በቂ መሰለኝ ። እስካሁን ድረስ እንደሚሰማኝ ምንም የፈጸምኩት ወንጀል የለም ። ግን የኒውዮርክ ፖሊሶችና የማንሐተን ወረዳ ዓቃቤ ሕግ የሚሉት ሌላ ነው ። ፍትሕን የምጠብቀው ከእነ ባቢዎች ብቻ ይሆናል ።

በደራሲነት ዓለም ውስጥ

ስሜ በየጊዜው ይቀያየራል ። አንዴ ቻክ ቶርንዳይክ ፥ በሌላ ጊዜ ማይክ ካንትሪል ነው ። ቢዩክ ዊልያምና ፖት ስላውት የሆነበትም ወቅት አለ ። የእግዚአብሔር ያለህ! ስሜ ፎርድ የሆነበትም ጊዜ ነበረ ። ሁሉም የፈጠራ ስሞች ናቸው ፤ እውነተኛ ስሜ ግን ጄኒ ሼን ነው ። ልብ ሰቀል የሆኑ የስለላና የወንጀል ምርመራ ጽሑፎቼን የሚያሳትም ልኝ የባይንደር አሳታሚ ድርጅት ባለቤት እንደ መከረኝ ፥ ብዙ ጊዜ መጽሐፍ የሚገዙ ደንበኞች የጸሐፊው ስም የሴት ከመሆን ይልቅ የወንድ ስም ቢሆን እንደሚመርጡና ፥ ለዚያውም የጉልበተኛና የጮበዝ ወንድ ስም መሆን ስለሚኖርበት ፥ እኔም በዚሁ መሠረት በተለያዩ የወንድ ስሞች ተጠቅሜአለሁ ።

ለዚህ አሳታሚ ድርጅት የመጀመሪያ መጽሐፌን ለሽያጭ ሳቀርብ ፣ የተጠቀምኩበት ስም ቻክ ቶርንዳይክን ነው ። በኋላ ግን እኔ ማይክ ፣ ቢዩክ ፣ ፓትን የመሳሰሉ ስሞች መጠቀም ጀመርኩ ። መጽሐፍ ለመጻፍ ችግር የለብኝም ። የምጽፋቸው መጽሐፎች በአብዛኛው ስለ ፍቅርና ስለ ወንጀለኞች የሚያወሱ በመሆናቸው ብዙ አንባቢ አላቸው ። ከመጽሐፎቼ ሁለቱ በፊልም ተቀርፀው ወደ ሙቶ ሺ ብር አግኝቻለሁ ፤ ዕድለኛ መሆኔን ዐውቃለሁ ። ማንኛውም ሰው ራሱን ለማስተዳደርና ለመመገብ ያስተምራል ፤ መኪና ይጠግናል ወ.ዘ.ተ. ጸሐፊም እንደዚሁ ይጽፋል ። በሚያገኘው ገቢ የራሱን ኑሮ ያሻሽላል ። እኔም ይህንኑ ተከትያለሁ ። መጻፍ እወዳለሁ ፤ ብዙ ሰዎች ደግሞ ማንበብ ይወዳሉ ።

ስለ ዘረፋ ፣ ጠለፋና ወሲብ የመሳሰሉትን ስለ ምጽፍና በአሁኑ ጊዜም ሰዎች ይህንን ማንበብ ስለሚወዱ ፣ በእነኝህ ርዕሶች ላይ መጻፌን እቀጥላለሁ ።

በቅርቡ በቻክ ቶርንዳይክ ስም የጻፍኩትን፣ «በቁርስ ሰዓት የተፈጸመ ግድያ» የሚለውን መጽሐፌን ረቂቅ ለአሳታሚው ድርጅት ልኬ ነበረ ። ከሦስት ሳምንታት ዝምታ በኋላ ፣ የአሳታሚው ድርጅት ሥራ አስኪያጅ እኔና ወኪሌን ሶልን ለማነጋገር እንደሚፈልጉ ፣ በጸሐፊያቸው በኩል መልዕክት ደረሰን ። በቀጠሮ ሰዓትም እኔና ወኪሌ ወደ ድርጅቱ መሥሪያ ቤት አመራን ።

የባይንደር አሳታሚ ድርጅት ሕንፃ በታይምስ አደባባይ የሚገኝ ሲሆን፣ ለውይይታችን የተመረጠው አዳራሽ የእርታዕያኑ ክፍል ነበረ።

የአሳታሚው ድርጅት ኃላፊ አልዶና ዋናው አርታዒ ሲመን ሁለታችን ወደ ነበርንበት ቦታ መጥተው ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ቁጭ አሉ ።

አልዶ ወፍራም ቶስካኖ ሲጋራ ማጨስ የሚወድ ደረተ ሰፊ ነው ። የሕትመት ሥራውን የጀመረው በወጣትነቱ ጊዜ ስለ ነበረና በሥራው ብዙ ዓመታትን ያሳለፈ በመሆኑ፣የዐዋቂነትና ብልጣብልጥነት መልክ ይታይበታል ።

ሥራውን ሲጀምር የቀጠራት ጸሐፊው አሁንም አብራው ትሠራ ለች ። በዚህም ብዙ ሐሜት ይወራበታል ።

ሲመን በሥነ-ጽሑፍ የዶክትሬት ዲግሪውን ከጀርመን ያገኘ በመሆኑ ፣ለአሳታሚው ድርጅት የሚቀርቡትን መጻሕፍት የሚገመግም ዋናው አርታዒ ነው ።

ሲመን፡ «ይህ ረቂቅ» አለ ወደ እኔ ጽሑፍ እያመለከተና ለመን ካት እየተጠየፈ ። «ተቀባይነት የለውም።»

«ቆይ እንጂ !» አለ ወኪሌ ሶል በዚህ ባልታሰበ ዱብ ዕዳ በመደናገጥ ፡ «እዚህ የተሰበሰብነው ስሕተቶችን ለማረምና ከመጽሐፉ ውስጥ መውጣት ያለባቸውን አውጥተን ለማስተካከል መስሎኝ !»

«በጠቅሳላው ተቀባይነት የለውም !» ሲል አርታዒው ሲመን ያለማመንታት ደገመ ።

«አልዶ ! መጽሐፉን አንብበኸዋል?» አለ ሶል፡ በንዴት ወደ ዋናው ኃላፊ እያየ ። አልዶ በራሱ የአምንታ ምልክት አሳየ ።

«እና? !»
«አይረባም !! »

ሲመን ከተቀመጠበት በመነሣት፡ «የመጽሐፉ ይዘት ከእውነት የራቀና ብዙ የሚጐድለው ነው» በማለት ተናገረ ።

መጽሐፌ ይህን ያህል መጥፎ የሆነ ስላልመሰለኝ ፡ «በጥቅል ከመነጋገር ይልቅ በምን፡በምን ነጥቦች ላይ ስሕተት እንዳለው ለይተህ ልትነግረኝ ትችላለህ ሲመን?» አልኩት ።

«ደስ ይለኛል ! ለምሳሌ በገጽ ሃምሳ አራት ላይ ልጅትዋ በታክሲ ሔደች ፤ ምክንያቱም ዝናብ ስለ ነበረ ነው ሲል ፡ ከሁለት ገጽ በፊት ግን ቀኑ ፀሐያማ እንደ ሆነና ምንም ደመና እንደማይታይ ገልጸሻል ። በገጽ ሃምሳ ሁለት ላይ ደግሞ፡ ጨረቃዋ ሐብሐብ በመምሰል በሰማይ ላይ ተሰቅላለች ብለሻል ። ይህስ ! ምን ማለት ነው ? ከእውነት ውጪ ! በገጽ . . . »

«በቃ ! ቢቃ ! የመሰለህን የመከራከሪያ ነጥቦች አዘጋጅተሃል !»

«የመሰለህን ነጥቦች?!» አለ በቁጣ እመለካከት። «በገጽ ሁለት መቶ ዐሥራ አንድ ሌባው የባንኩን ዘበኛ በጠመንጃ ተኩሶ ሲመታው ድምፁ «ካቻው !» አለ ስትይም ገልጸሻል ። ለመሆኑ ከመቼ ወዲህ ነው የጠመንጃ ድምፅ «ካቻው» የሚለው? ማለት ያለብሽ «ብው !» ወይም «ድው !» ወይም «ደፍ ! እንጂ !»

ውስጥ አንጀቴ አረረ ፡ እንባዬ መጣ ፡ ሲመን እንድበሳጭ እንደ ፈለገ ገባኝና ራሴን ተቆጣጠርኩት ።

በሁላችንም ዘንድ ጸጥታ ሰፈነ ። አልዶ በረኽሙ ተነፈሰና በሲጋራ ወደ ሶልና ሲመን እያመለከተ፡ «አንድ ጊዜ ውጭ ጠብቁኝ ፡ ከጂኒ ጋር በግል ልነጋገር» አለ ።

ሁለቱም ከክፍሉ ሲወጡ ከቦርሳዬ ሲጋራ አወጣሁ ። አልዶ ለኮሰልኝ ። ለመጣቅ እየሞከርኩ፣ «ሲመን እንደሚጠላኝ ዐውቃለሁ» አልኩት ።

«ሲመን አይጠላሽም ፤ እንዲያውም ያከብርሻል ።»

«ያከብርሻል?»

«አንቺ . . . የተዋጣልሽ ጸሐፊ ነሽ » አለኝ ።

«ከሆነ !» አልኩት ቀስ በቀስ ራሴን እየተቆጣጠርኩ። «ታዲያ እኔ ሲመን መጽሐፍ ለመጻፍ እንደሚፈልግ አላውቅም ። አድራጐቱ ሁሉ በእኔ ላይ ቅናት እንዳደረበት ሰው ነው» አልኩት በምሬት[።

«ማንኛውም አርታዒ መጻፍ ይፈልጋል ። አርታዒያን ባለ ሙያዎች ስለ ሆኑ ብቻ በቀላሉ ወጥ ሥራዎችን መድረስ እንችላለን ሲሉ ያምናሉ ። ግን የሚሳካላቸው ጥቂቶቹ ናቸው ። ሲመን ይህ ፍላጐት ያለው ቢሆንም ፣ በመጽሐፍሽ ላይ ያቀረበው ትችት ትክክል አይደለም አያሰኝም » አሉና በቶርን ዳይክ ስም ወደ አዘጋጀሁት ረቂቅ ጽሑፍ እያመለከተ ፣ «ይህ ጽሑፍሽ ተራ ስለ ሆነ አላትመውም » ሲል አከለበት ።

«በዚህ ዓይነት ከድርጅትህ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ሊቋረጥ ነው ። ሌላ ጽሑፍ የማዘጋጅ አይመስለኝም » አልኩት በንዴት ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ።

«ጄኒ . . .ከዚህ አሳታሚ ድርጅት ብዙ ገንዘብ አፍርተሽበታል!»

«ትክክል . . .ድርጅቱም በኔ ብዙ አትርፎብኛል !»

«ልክ ነሽ» አለ ራሱን ከፍ ዝቅ እያደረገ ። «የምጠላው . . . የ ድርጅቱና ያንቺ ግንኙነት ወደ መቋረጥ በመድረሱ ነው ። በውላችን መሠረት መጽሐፍሽን በሌላ አሳታሚ ድርጅት ማሳተም ትችያለሽ ። ግን ይህ እንዲሆን ትፈልጊያለሽ ?»

ጥያቄው አስደንግጦኝ የያዝኩትን ሲጋራ በማጥፋት ሌላ አቀጣጠልኩ ።

«ብዙ ታጨሺያለሽ !» አለኝ እንደ መታዘብ ብሎ ።

«አንተም ብዙ ትበሳለህ» ስል መልሼለት ፣«አልዶ ! ምን ማድረግ እንደሚገባኝ አላወቅኩም ። ለማንኛውም ስለ ጽሑፉ አስብበታለሁ» አልኩት ።

«ጂኒ ፣ የዚህም ሆነ ያለፉት ሁለት መጽሐፎችሽ ጉድለት ምን እንደሆነ ብነግርሽ ትቀየሚያለሽ?»

«አልቀየምም!» አልኩት ። ውስጥ ውስጡን ግን ስዋሽ ነበር ።

«ጂኒ ፣ የልብወለድ ሥራ በሕልም የሚታይ ሳይሆን የገሃዱ ዓለም ነጸብራቅ ነው ።»

«ጥሩ በዚህ አባባልህ እስማማለሁ» ስል ነገር ግን ፣ እጇን በመ ጨበጥ «ቆዩ አስጨርሺኝ» ብሎ አቋረጠኝ ።

«የልብወለድ፣ የፈጠራ ሥራ በርግጥ ሕልም ነው። ነገር ግን ፣ አንድ አንባቢ ከማንኛውም የመጽሐፍ መሸጫ ሱቅ ገብቶ የሚፈልገው መጽ ሐፍ ፣ ከእውነኛው ዓለም የሌለ ፣ ተራና ተአማኒነት የጐደለው ሳይ ሆን በእውነተኛው ዓለም ሊያጋጥም የሚችል ታሪክ መሆን አለበት ። አዎ ! የልብወለድ ሥራ የደራሲው ምናባዊ ምጥቀት ውጤት መሆ ኑን እኔም ሆንኩ አንቺ እናውቀዋለን፤ ሆኖም አንባቢው ማመን ያለበት የደራሲው የፈጠራ ሥራ መሆኑን ሳይሆን ደራሲው ፣ ትክክለኛ የሆኑ ድርጊቶችን ለአንባቢው በሚገባ ቋንቋ እንደገለጸ መሆኑን መረዳት እንዲችል ማድረግ ይኖርበታል ። ይህ ሳይሆን በጥቂቱ የተዛባ ወይም ባጠቃላይ ከእውነተኛው ዓለም የራቀ ጽሑፍ ቢያቀርብ ፣ ደራሲው በአንባብያን ዘንድ እምነት እንዳያገኝ ያደርገዋል ።»

«እና እኔም እንደዚሁ እምነት አጥቻለሁ ማለት ነው ? »

አልዶ የሲጋራውን ዐመድ በትዝብት እያራገፈ ፣ «አዎን፣ ከእው ነት እየራቅሽ ነው ። በመሆኑም ጠቅላላው የመጽሐፉ ይዘት ኢተ አማኒ ነው ። ቢታተምም አንባቢዎች ከእውነት እየራቅሽ መሔድ ሽን ይረዱታል ።»

«እሺ ! ምን ትመክረኛለህ?»

«ማድረግ ያለብሽ ፖሊሶችን አነጋግሪ ፣ ከነሱም ጋር ማታ ማታ ሮንድ አብረሽ ውጭ ። ይህን እኔ ላመቻችልሽ እችላለሁ ። እንዲሁም የታሰሩ ወይም ያልታሰሩ አደገኛ ወንጀለኞችን ለማነጋገር ሞክሪ ። የሥነ ልቦና መጻሕፍትን ፣ የጥርድ ቤት ውሳኔዎችን አንብቢ ። የምመክርሽ ፣ ራስሽን ከሕልም ዓለም አውጥተሽ እግርሽንና አእም ሮሽን በተጨባጩ ዓለም ላይ አሳርፊ ።»

«ይህን ዐረፍተ ነገርህን በመጽሐፌ ውስጥ ብጠቀምበት ፣ ሲመን በቀይ ቀለም ይከበዋል » አልኩት ፣ የሲመን እኔን ጠምዶ መያዝ እየታየኝ ።

«ሲመን እንደሚመቀኝሽ እድርገሽ ሁል ጊዜ አትጠርጥሪ ። ይልቁንስ ያልኩሽን ምክር ተጠቀሚበት ። በትንሽ ጥረት ከዚህ በፊት ታስደስቺያቸው የነበሩትን አንባቢያን ይበልጥ መማረክ ትችያለሽ ።»

«እና ! መጽሐፉም ይሸጣል ?»

«ይሸጣል ! ጂኒ ይህ ድርጅት አትራፊ ነው ። አይደለም እንዴ? እናም እንደ መከርኩሽ ከጸፍሽ እናተርፋለን ።»

ጥ ን ስ ስ

ከሶል ጋር ከአሳታሚ ድርጅቱ ሕንፃ ወጣን ። በንዴት ራሴን የም ስት መስሎት እጁን ጠበቅ አድርጎ ያዘኝና ታክሲ ውስጥ ገብተን ጉዞአችንን ቀጠልን ።

«የኔ ቆንጆ! ቡና ቤት ሔደን ትንሽ መጠጥ ቢጤና ምግብ ብንቀምስ ?»

«ጥሩ ነው ። ግን ሒሳቡን ለሁለት እንካፈላለን» አልኩት ።

በዚህ ተስማማን ። «ለመሆኑ ከአልዶ ጋር ምን ተነጋገራችሁ?» አለኝ ሶል በጉዞ ላይ እንዳለን። «አብረን ከነበርንበት ጊዜ ከተናገረው የተለየ አይደለም ። መጽሐፉን እንደማያትመውና ከፈለግሁም ሌላ ማተሚያ ቤት ልወስደው እንደምችል ነው የነገረጸልኝ ።»

«እሺ እንግዲህ. . .» አለ በታክሲው መስኮት ወደ ውጭ እየ ተመለከተ ፥ «ቡና ቤቱ ስለደረሰን እየበላንና እየጠጣን እንነጋገራለን» አለኝ ።

ክፍት ሆኖ ባገኘነው ወንበር ላይ በመቀመጥ ምግብና መጠጥ አዘዝን ። ወሬአችን ግን በመጠኑ ሆነ ።

ሶል በቡና ቤቱ ውስጥ ያሉትን አብዛኛዎቹን ሰዎች ስለሚያ ውቃቸው በአንገቱ ሰላምታ ተለዋወጠ ።

«ብዙ ሰዎች ታውቃለህ» አልኩት ።

«ልክ ነሽ የኔ ቆንጆ ፥ እንድ የሕትመት ወኪል ብዙ ሰው ማወቅ አለበት » አለኝ ።

«ይህም ከሆነ፥ ይህን ጽሑፍ ለሌላ አሳታሚ ድርጅት ለመ ስጠት ችግር የለማ ?»

«አዎ ! ብዙ ቦታ አለ . . . . . »

«ሶል ! መጽሐፉን አንብበኸዋል?»

«አዎ አንብቤዋለሁ ።»

«ከዳር እስከ ዳር?»

«እይው. . . . አዳምጪኝ ። ምናልባት ሁሉንም አይደለም ። ሥራሽን ዐውቀዋለሁ ። ምን ያህል ባለሙያ እንደሆንሽ ማለቴ ነው . . . .»

«ከመጽሐፌ ምን ያህሉን አንብበሃል?»

«አ ! በትክክል አላስታውሰውም ፤ ምናልባት የመጀመሪያውን ሃምሳ ገጽና የመጨረሻውን ሃምሳ ገጽ ...»

«እሺ ፥ ስለ መጽሐፉ ምን ታስባለህ! እውነቱን ንገረኝ ።»

«ጄኒ ! እውነት መነጋገር አለብን ። ይህ መጽሐፍ ከበፊቶቹ በደረጃው ዝቅ ያለ ነው ።»

ሣቅሁኝ ።

ወዲያው ምግብ ቀረበልን ፤ አስተናጋጁ እስኪሔድ ጠበቅኩና፡ «እሺ ቀጥል ። ምንድነው የመጽሐፉ ስሕተት?»

አንድ ወኪል ውክልናውን እንዳያጣ ማድረግ የሚገባውን ጥንቃቄ በማድረግ መናገር ጀመረ ። ፊቱን ሳየው እውነት እንደሚነግረኝ ተረዳሁ ።

«ይቅርታ አድርጊልኝ እንጂ ፥ መጽሐፉን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንብቤዋለሁ ። እና ጄኒ አዳምጪኝ ፥ ሰዎች የወንጀልና የስለላ መጽሐፎችን ለምን እንደሚያነቡ ታውቂያለሽ? አቀራረባቸው ጥራት ስላለው ነው ።»

«ጥራት?» አልኩት ደገምኩና ያለውን ለማረጋገጥ።

«ማለቴ በአንድ ቦታ የተወሰኑ ሰዎችን አስቀምጪና ለአንድ ወንጀል አዘጋጂአቸው ። ለወንጀሉ ፅቅድ ይነድፉሉ ፤ ሥራ ላይ ያውሉታል ፤ ይህም የመጨረሻው ይሆናል ።»

«ለምን? ይያዛሉ ወይም ይሞታሉ እንጂ» አልኩት ።

«በግድ ይህ መሆን የለበትም ። አምልጠውና ራሳቸውን ደብቀው በሌላ አካባቢ ጥሩ ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ ። እንዲህ ዐይነት መጽሐፎች ደስ ይላሉ ። ለምንድነው ደስ የሚሉት? ታውቂያለሽ?»

«አላውቅም ! ለምንድነው?»

«ምክንያቱም ፥ መጨረሻው አሳዛኝ ከመሆኑም ጥራት ሲኖረው ስለሚችልና አንባብያንም በዚህ እንዲያልቅ ስለሚፈልጉት ነው ። ማንኛውም ሰው በተጨባጭ ዓለም የማይገኘውን ለማየት ይፈልጋል ። ማለቴ ወንጀለኛው በፖሊስ በመያዙ ወይም በመሞቱ የሚደሰት አንባቢ የለም ። ዋናው ቁም ነገር ደስ የሚል መጨረሻ ሊኖረው ይገባል። በአንቺ መጽሐፍ የመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ 'ሁለቱ ወንጀለኞች ተገደሉ ፥ አንዱ ተያዘ ፥ አንዱ ራሱን ገደለ ፥ አንዱ የት እንደ ገባ አይታወቅም' ብሎ በእንጥልጥል ይተወዋል ። በመሆኑም መጨረሻው ምን እንደ ሆነ የማይታወቅ ግራ የሚያጋባ ነው ። የኔ ቆንጆ መጽሐፉ ያለቀ ሳይሆን በመኻል የቆመ ነው ።»

ሶል የሚነግረኝን በማብሰልሰል ምግቤን መመገብ ጀመርኩ ። አሳታሚው ድርጅትም ፥ ከእውነትነት ጋር መጣጣም አለበት ነው ያለኝ ። እንደ ሁለቱም አባባል በሕይወታችን ውስጥ «እውነት» የሚባል ነገር በትክክል አለ?

«አስብበታለሁ» አልኩት ።

መጠጣችንን ጠጥተን ወጣን ። ሶል ታክሲ አሳፍሮኝ ተለያየን ። ታክሲ ውስጥ እንዳለሁ ረቂቅ ጽሑፌን መቀመጫው ላይ ልተወውና ከኔ በኋላ የሚሳፈር ሰው እግኝቶት እያነበበ ትንሽ ይጣቅበት ብዬ አሰብኩ ። በኋላ ግን ሐሳቤን ለወጥኩና ይዤው ወረድኩ ።

እቤቴ ስገባ ስልኩ ይጮኻል ። ምናልባት አልዶ ሐሳቡን ቀይሮ መጽሐፉን ለማተም ፈቃደኛ ሆኖ ይሆናል በሚል በመንደርደር አነሣሁት ። ግን የደወለልኝ እርሱ አልነበረም ። ጓደኛዬ ላውራ ሆስፒታል የምትቆይ መሆኑን የተረዳው ባልዋ ዛሬም አብረን እንድናድር ለመጠየቅ ነበር የደወለልኝ ። «ድራሽህ ይጥፋ !» ብዬ ስልኩን ዘጋሁበት ። መኖሪያ ቤቴ አንድ ሳሎን ፥ ሁለት የመኝታ ክፍል ፥ አንድ ማድ ቤትና የመታጠቢያ ቤት ያለው ሲሆን ፥ አንዱን የመኝታ ክፍል እንደ መጻፊያ ክፍል የምጠቀምበት ነው ። ጫማዬን አውልቄ በተሽከርካሪውና ምቹ ወንበሬ ላይ ቁጭ በማለት ጽሑፌን ማንበብ ጀመርኩ ።

ለወትሮው ብዙውን ጊዜ የጸፍኩትን ደግሜ አላነብም ። ዝም ብዬ ታይፕ አደርግና ለወኪሉ ልኬ የገንዘብ ቼክ ይደርሰኛል ። እንዲታተም የምልከውን መጽሐፍ ርዕስ አሳታሚው ድርጅት ቢቀይረው እንኳ ግድ አልነበረኝም ። የመጽሐፉን ሽፋን በፈለጉት ዐይነት ቢያደርጉትም አይሰማኝም። የሚታተመው መጽሐፍ ቅጂ ብዛትና ሽያጭ

ምንያህል እንደ ሆነ አልከታተልም። ይህ ሁሉ ተሰምቶኝ አያውቅም ። ይህ ግን ፣ የአንድ ጸሐፊ ደካማ ጐን ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ ። የረቂቁን ዐሥር ገጽ ያህል እንኳን ማንበብ አልቻልኩም፤ አሁን ግን ሳነበው የሴላ ሰው እንጂ የራሴ ጽሑፍ አልመስለኝ አለ ። በሕይወቴ እስከ ዛሬ በራሴ አፍሬ አላውቅም ። በጣም መጥፎ ጽሑፍ ነበር ። የሰዎቹ ገጸ ባሕሪም እንደ ነገረኝ ፣ ታሪኩ ለራሴም አጣቀኝ ።

ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ እንደ ገና ማንበብ ቀጠልኩና ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ እንደ ጨረስኩ ፣ ጭምድድ አድርጌ ከቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጣልኩትና ወደ ማደቤት ገብቼ ፣ ጠርሙስ ወይን ጠጅ ይዤ ወንበሬ ላይ ዐረፍ በማለት መጠጣቱን ተያያዝኩት ።

ቀደም ሲል የጻፍኳቸው መጽሐፎች ገበያ ያገኙልኝ በአጋጣሚ መሆኑን ተረዳሁት ። እንዲያውም ራሴን ስለ መሐንዲስነት ምንም ዕውቀት ሳይኖረው፣ ሰዎች ቤት ሲሠሩ ስላየ ብቻ ቤት ለመሥራት፣ እን ደሞከረ ሰው አድርጌ ቆጠርኩት። ሰዎች የጻፉትን በማየትና በማንበብ ብቻ እኔም ለመጻፍ ሞከርኩ ። እነ አልዶ የነገሩኝ እውነት ነው ። ከእውነተኛው ዓለም ራሴን አግልያለሁ ። አንባቢዎች ምን እንደ ሚፈልጉ ማወቅ አልቻልኩም። ይሁን እንጂ፣ አሁንም ከመጻፍ የሚ ያግደኝ አይኖርም እያልኩ ይህን ሳወጣና ሳወርድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች አልፈው ኖሮ ረኃብ ሲሞረሙረኝ ተሰማኝ ። ወደ ዲክ ፍላሚንግ ስልክ ደውዬ፡«ዲክ ረበሽኩህ መሰለኝ?» አልኩት ።

«አይ አልረበሽኝም ። ደህና ነሽ ጆኒ?» አለኝ ።

«ደህናስ አይደለሁም ። ለማንኛውም ራት በልተሃል?» ስል ጠየቅኩት ።

«አልበላሁም ። ገና እያዘጋጀሁ ነው ፣ ትንሽ ያሣማ ሥጋ አለኝ» አለ ።

«ከአንተ የተሻለ እኔጋ አለ ። መምጣት ትችላለህ?»

«አሁኑኑ እመጣለሁ ።» ከዲክ ጋር ያስተዋወቀኝ ሶል ነበር ። ዲክ የሕፃናት መጽሐፎችን መጻፍ የሚወድ ነው ። በቁመቱ ከኔ ትንሽ ከፍ የሚል ቢሆንም በጣም ቀጭን ነው ። ጥሩ ጓደኞች ሆነናል ። እምብዛም ደስተኛ አይደለም ። የልጆች መጽሐፍ ስለሚጽፍ ነው መሰለኝ አልፎ አልፎ ልጅ የሚያስመስሉት ሁኔታዎች ይታዩበታል ። ስለ ቤተሰቡ ታሪክ ብዙም አያወራም ። ከናቱም ፣ ከእህቱም ጋር እንደ ኖረና ከአሐዮ ግዛት እንደ መጣ ብቻ ነው የነገረኝ ። የተለያዩ ሦስት ቋንቋዎች መናገር ይችላል ። እንደዚሁም ፒያኖና ጊታር የመ

ሚወት ችሎታ ያለው ሲሆን፥ ብዙ ጊዜ ምግብ ማዘጋጀት ይወዳል ። የዲክ መኖሪያ ቤት ከኔ ብዙም አይርቅም ። አልፎ አልፎ እንጠያየቃለን ። ሆኖም አንዳችን አንዳችን ቤት ለመሔድ በቅድሚያ በስልክ ተነጋግረን ከተስማማን በኋላ ነው ።

ዲክ ወዲያው መጣና ምግቡን እኔ ላዘጋጅ ብሎኝ አዘጋጅቶ መመገብ እንደ ጀመርን ፥ ልክ እንደ ከዚህ በፊቱ በትግሮቹ ተመስጦ በየመኻሉም ጥያቄዎችን ሲጠይቀኝ ቆየና ሁለታችንም ቡናችንን ፉት እያልን ብራንዲ በመያዝ ወደ ሳሎን ገብተን ገን ለገን ተቀመጥን ። አዋዋሉን ዘርዝሬ ካጫወትኩት በኋላ ፥

«መጥፎ ቀን አጋጥሞሻል » ሲል በመቆርቆር ዓይነት ተናገረ ።

«አዎ !» አልኩት በምሬት ።

«ታዲያ ምን ለማድረግ አስበሻል?»

«አላወቅሁም ፥ አዲስ መጽሐፍ ጀምሬ ወደ መቶ ገጽ ደርሻለሁ ። ይህንንም ሳነበው ካለፈው ያልተሻለ ነው ። አልዶና ሶል ስለ ነገሩኝ የአጻጸፍ ቴክኒክ ምን ይሰማሃል?»

«እንደዚህ ዓይነት መጽሐፎችን ማንበብ እንደማልወድ ታውቂያለሽ ። ግን እነሱ ያሉት ትክክል ይመስለኛል ። ምናልባትም ስሕተትሽን አፍረጥርጠው ነግረውሽ ይሆናል ። አንቺ ራስሽስ መጥፎ ነው ብለሽ አምነሻል?»

«ዲክ . . . አንብቤዋለሁ ። የጻፍኩትም የማይረባ ነው ። ስለ ዚህም ጥየዋለሁ ።»

«እሺ ፥ ግን ያ መጽሐፍሽ መጥፎ ስለ ሆነ፥ ሌላ መጻፍሽን ማቋረጥ የለብሽም ። ቶሎ ብለሽ አዲስ መጽሐፍ ለመጻፍ ሞክሪ ።»

«ሶልም ያለኝ ይህንኑ ነው ። ግን አልዶ ከእውነት ርቀሻል ብሎኛል ። እንዴት ብዬ ነው ይህን የማሻሽለው? ምን ማድረግ እንዳለብኝ አልገባኝም ። አብረኸኝ ታድራለህ?» ስል በድንገት ጠየቅኩት ።

«በደስታ !!» አለ ምንም ሳያመነታ ። ከዚያም ፥—

«ጄኒ! ለዐሥራ አምስት ዓመታት ያህል በጐልማሶች ለጐልማሶች የተጻፉ መጽሐፎችን ማንበብ ትቻለሁ ። ከሕፃናት መጻሕፍት ግን ደስታ አገኛለሁ ። ልጆች አዳዲስ ነገሮችን ፥ ትልልቆችም ወንጀል ነክ ልብወለዶችን ማንበብ ይወዳሉ ። ለምን መሰለሽ፣ ማንኛውም ሰው በአሁኑ ጊዜ ስለ ራሱ የግል ተግባር ምን እንደሚል ታው-

ቂያለሽ? 'አሰልቺ ነው፣ የማያረካ ነው!' ነው የሚልሽ። ለዚህም ነው አንባቢያን ራሳቸውን ለማታለል ሲሉ ፣ ልብወለድ ማንበብ የሚወዱት ።»

«እሺ ! እንግዲህ እንተኛ ።»

«ቆይ ፣ ብራንዲ ይገቡ ልምጣ ።»

«ጥሩ ነው ።»

ዲክ ራሱን ደረቴ ላይ አድርጎ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው ። እኔ ግን አልዶ ፣ ሶልና ዲክ ያሉኝን እያብሰለሰልኩ እንቅልፍ አል ወስድሽ አለኝ ። ሴቶች ብዙ ጊዜ ወንዶች ስለ ነገሩዋቸው ጉዳይ አላስፈላጊ ጭንቀት ውስጥ ለምን ይገባሉ? ወዲያው ቀስ ብዬ ከአል ጋው በመነሣት በውስጥ ልብሴ ወደ መጻፊያ ክፍሌ ሔጄ ወንበሩ ላይ ቁጭ አልኩ ።

ለምን ያህል ጊዜ ቁጭ እንዳልኩ አላስታውሰውም ። በሩ ተከ ፍቶ ዲክ ራቁቱን ሆኖ ዐይኑን እያሻሸ ያዛጋል ።

«ዲክ ! ቁጭ በልና አዳምጠኝ ።»
«ስንት ሰዓት ነው?»

«ምን ዐውቄ? ከጥዋቱ ሁለት ወይም ሦስት ሰዓት ይሆናል ። ብቻ ቁጭ በልና አዳምጠኝ ።»

እንቅልፉን ለማስወገድ ራሱን እያወዛወዘ አጠገቤ ከነበረው ወንበር ላይ ቁጭ አለ ፣ «እሺ በደንብ ነቅቻለሁ ፣ ምንድነው የምት ነግሪኝ?»

ያመነጨሁትን ሐሳቤን ነገርኩትና በመሣቅ፣«ግን እንዴት ነው ከዕውነት ጋር የማቀራርበው? እንዴት ነው ከዕውነተኛ ሕይወት ጋር የማገናኘው?» ስል ጠየቅኩት ።

በመገረም ተመልከቶኝ፣ «ይህን ከፈጸምሽ ትያዥና ለሐያ ዓመት እስር ቤት ትማቅቂያለሽ» አለኝ ።

«እኔ ወንጀል አልሠራም ፣ ወንጀል እንዴት እንደሚሠራ ዕቅድ ለማውጣት ሲሆን ፣ በመጨረሻ ደረጃ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ለማ ቋረጥ ነው ። በዚህም የዋናው ወንጀል መደምደሚያ ምን ሊሆን እንደ ሚችል እራሱ ወንጀሉ ይመራናል ።

«በርግጥ በዚህ ልምድ ውስጥ ለማለፍ ጥርሃቱ ፣ ችግሩ ፣ አደገ ኛነቱ ወለል ብሎ ይታየኛል ። ሆኖም ልምዱን ማግኘት መቻል

አለብኝ ። ከዚህ በፊት ዝም ብዬ መጻፍ እንጂ፣ ስለምጽፈው ጉዳይ ምንም ዕውቀት አልነበረኝም ። በዚህ ሐሳቤ ከተመራሁ ግን ከፍተኛው የወንጀል ጸሐፊ ለመሆን እችላለሁ ።»

በረኽሙ ተነፈሰና ትኩር ብሎ ተመልከቶኝ፣ «የዚህ ዓይነት የወንበዴ ቡድን ልታቋቁሚ ነው?» ሲልም ጠየቀኝ ።

«አዎ» አልኩት በራሴ ጭምር ምልክት እያሳየሁት። «በወንጀል ሥራ ልምድ ያላቸውን ሰዎች የሚያካትት ቡድን ።»

«እነዚህን የመሰሉ ሰዎች እንዴት ልታገኚአቸው ትችያለሽ?»

«ዲክ ! ዋናው ነጥብ ይሄ ነው ። የወንበዴውን ቡድን እንዴት ማሰባሰብ እንደሚቻል? ማንን ማናገር እንዳለብኝና እንዴት እንደ ማገኝ ሁሉ ማወቅ አለብኝ ። በተጨማሪም ሽጉጥ ያስፈልገኛል ።»

«ጄኒ ! ከልብሽ ነው እንዴ ?»

«እውነቴን ነው ።»

«ደህና ሽጉጥ ማግኘቱ አስቸጋሪ አይደለም ። ግን የምትቀጥሪ ያቸው ወንጀለኞች ለዘረፋ የተዘጋጁ እንጂ፣ መጽሐፍ ለመጻፍ ብቻ ስትይ የተጠቀምሽባቸው መሆኑን ሲረዱት እንዲህ በቀላሉ የሚለቁሽ ይመስልሻል?»

«ግዴለህም በቀላሉ እወጣዋለሁ ። ጽሑፌን ልጨርስ ስቃረብ ፣ ደመወዛቸውን በቅድሚያ ብከፍላቸውና ብጠፋባቸው ምንም አይሉም ። መረዳት ያለብህ ወንጀለኞች ትንሽ ጥቅም ካገኙ ብዙም የሚጨነቁና የሚያስቡ አይደሉም። ወጣም ወረደ ይህ ሐሳብ እንጂ፣ እንዴት በሥራ ላይ እንደሚውል ገና አልተዘጋጀሁበትም።ምን አሰብክ?»

ዲክ ፣ «በሕይወትሽ ላይ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ሳትገነዘቢ የቀረሽ አይመስለኝም?» አለ ።

«ዐውቃለሁ ። አደጋም መኖር አለበት ። ይህ ካልሆነ ፣ ጽሑፌ እንዴት እውነተኛነት ይኖረዋል ። ስለ አደጋም መማር እፈልጋለሁ ። ሐሳቤም ከዚህ የመነጨ ነው ። የት ልትሔድ ነው? ልትተኛ?» አልኩት መንቀሳቀሱን አይቼ ። ወደ በሩ እያመራ አንገቱን አዙሮ «መጣሁ!» አለኝ ። ወዲያው የብራንዲ ጠርሙስና ሁለት መለኪያ ይዞ ተመለሰና ሁለቱንም ቀድቶ አንዱን ለኔ ሰጠኝ ።

«ጄኒ በዚህ ሐሳብሽ እኔም አለሁበት ።»

«ምን?» በማለት ማመን አቅቶኝ ጠየቅኩት ።

«እኔም የመጀመሪያው የወንበዴ ቡድን አባል መሆን እፈል ጋለሁ ።»

«እብድ ነህ?» አልኩት በመገረም ።

«ካንች የበለጠ እብድ አይደለሁም ። ተስማማሽ?» አለኝ ረጋ ብሎ ።

እውነቱን መሆኑን ለማረጋገጥ ትኩር ብዬ አየሁት ። «ዲክ ! ወደ ስሕተት ውስጥ የምመራህ አልመሰለኝም? ሙከራህ ምናልባት እንደ ጉልበተኛ ወንዶች ፥ ደካማ ሴቶችን ከመጥፎና አደገኛ ወንዶች የመ ከላከል ዓይነት እርዳታ ይሆን እንዴ?»

«ጉልበተኛ እመስላለሁ? አእምሮሽን ተጠቀሚበት ፥ ስለ መሣ ሪያ ፥ ጩቤ ወይም ድብድብ የማውቀው ነገር የለም ።»

«ታዲያ ለምን?»

«ለዝናውና ለአደጋው ስል ።»

«ለአደጋውና ለዝናው ስንል እንጠጣ!» አልኩት ሣቅ ብዬ ።

ፅቅድ አነዳደፍ

በማግሥቱ ፥ ምሽት ላይ ራቴን ከጓደኛዬ ከሳውራና ከባለቤትዋ ከሐሚልተን ጋር በልቼ እንደ ጨረስኩ ፥ ቤቱ በመመለስ ዲክ ከመም ጣቱ በፊት ስለ ፅቅዳችን ለመወያየት የሚያስፈልገንን ወረቀት ፥ እርሳስ እንዲሁም መጠጥ አዘጋጀሁ ። አልዶ ከነገረኝ ሌላ ስለ ጸሐ ፊዎችም አንብቤአለሁ ። ከወንጀል ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሁሉ በአንድ ላይ ከጋዜጦች በማሰባሰብ ጠርዣቸዋለሁ ። ከነኝህም ብዙ ውጤት የሚገኝበትንና ለአነስተኛ አደጋ የሚያጋልጠውን የወንጀል ዓይነት ለመለየት ጥረት አድርጌአለሁ ።

ዲክ መጥቶ ባገኘው ወንበር ላይ እንደ ተቀመጠ የዘመኑ የወን ጀል ዓይነቶችን በየዘርፋቸው መለየት ጀመርን ። በግድያ ፥ በዘረፋና ጠለፋ በመሳሰሉት ላይ ውይይት አደረግን ። ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች የሠሩትን ድብቅ ወንጀል በማወቅ ለሕዝብ ከማጋለጥ በፊት እያስፈራሩ መደለያ ገንዘብ መቀበልንም እንዳማራጭ አየነው ። ይህ ግን፥ ከፍተኛ ችሎታ የሚጠይቅ ስለ ሆነ ተውነው። የሰው ጠለ ፋም ደስ የማይል ሆነ ። አይሮፕላን ጠለፋም አያዋጣም ። ይህን ሁሉ ዓይነት ወንጀል ስንተው የቀረን የቤት ሰበራና በመዛሪያ የተደራጀ ዘረፋ ማካሔድ ብቻ ሆነ ።

መጠጥ ደገምንና በሁለቱም ላይ ተከፋፍለን ጋዜጦችን ማንበብ ጀመርን ። የተለያዩ ቢሮዎች ፣ መጋዘኖች ፣ ባንኮች ፣ የጦር መሣሪያ የጫኑ መኪኖችና ሆቴሎች ከዚህ በፊት እንዴት እንደ ተዘረፉ ተመለከትን ። ሆኖም የባንክና የጦር መሣሪያ የጫነ መኪና ዘረፋ ጥበቃው ከፍተኛ ስለ ሆነ ተውነው ።

የግለሰብ ቤት ዘረፋም የሚያሳትፈው አንድና ሁለት ሰው እንጂ ከዚያ በላይ ባለመሆኑ ይህም ለመጽሐፌ በቂ ገጸ ባሕርያትን ስለማያስገኝልኝ መተው አስፈላጊ ሆነ ።

ከፍተኛ ሆቴል ግን ፣ ጥሩ ሊሆን ይችላል ብለን አሰብን ። ሆቴል ቤትን ለመዘረፍ ከሆቴል ሠራተኞች ተባባሪ ያስፈልገናል ። ይህም በካዝና ውስጥ የተቀመጠውን ገንዘብ ልክ ማወቅ አለብን ። በተጨማሪም፣ ምን ያህሉ የሆቴል ሠራተኞች በዚህ ዓይነት ዘረፋ ተሳታፊ ለመሆን ፈቃደኛ መሆናቸውን ማጥናት ሊኖርብን ነው ። «ባለፉት ዓመታት አምስት ትላልቅ ሆቴሎች በመዘረፋቸው ምክንያት ፖሊሶች በሆቴል ቤት ውስጥ ሠራተኛ በመምሰል ይቆጣጠራሉ» አለ ዲክ ። ስለዚህ እንደገና ጋዜጦች ማገላበጥ ጀመርን ።

«ዲክ ይህ ታሪክ ስምን ያህል ጊዜ የሚቆይ ነው?» ሲል ጠየቅኝ።

«ግሩ ቢል እስከ ሦስት ዓመት ። ግን ለምን ጠየቅኸኝ?»

«እንዲያው ገርሞኝ ነው ።»

በጸጥታ ንባባችንን ቀጠልን ።

«የሚያስደንቅ ነው!» አለ ዲክ ።

«ምኑ?»

«ሌሎችን ተያቸውና እስቲ ስለ ጌጣጌጥ ሱቅ ፈልጊ ። በአብዛኛው አልማዝ ስለሚያስቀምጡ ሱቆች» ሲል ሐሳብ አመነጨ ።

መጠጡ እንደገና ተቀድቶ ጥናታችንን ጀመርን ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ፣ በየሀገሩ ውስጥ በተፈጸሙ የከፍተኛ የጌጣጌጥ ሱቅ ዘረፋዎች ላይ የቀረበ በርካታ ሪፖርት አወጣንና ዲክ በተሻሉት ዘረፋዎች ላይ ጥናቱን አተኮረ ።

«አሁን ምን እያደረክ ነው?» አልኩት ጥቂት እንደ ቆየን ።

«ከመቶ ሺ ብር በታች የሚገመት ንብረት ያላቸውን ሱቆች ለይቼ እያወጣሁ... ዐሥራ አራት የጌጣጌጥ ሱቆች በሦስት ዓመት ውስጥ እያንዳንዳቸው ከመቶ ሺ ብር የበለጠ ንብረት ተዘርፈዋል ።

የመጨረሻውም ዘረፋ ቀደም ሲል የተዶረጉትን ዘረፋዎች ተመሳሳይ ዘዴዎች የተከተለ ነው ። ከዐሥራ አራቱ ዝርፊያዎች ሁለቱ እዚህ ኒውዮርክ የተከናወኑ ሲሆን፣ ዐሥራ ሁለቱ በተለያዩ ከተሞች ነው ። ከሁሉም የሚገርመው ግን፣ ከነዚህ ሁሉ ዝርፊያዎች አንዱ ብቻ ነው በክትትል የተደረሰበት» አለኝ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ ።

«ምናልባት የወንጀሉን ውጤት ሳታነብ ቀርተህ ይሆናል ። ትላልቅ ዘረፋ ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ርዕስ ሆኖ በጋዜጣ ይወጣል ። ግን እንበል ከዓመት በኋላ ሌቦቹ ቢያዙ ጋዜጦች በጥቂቱ ነካ ነካ አድርገው ነው የሚያልፉት ።»

«ሊሆን ይችላል» አለ በመጠራጠር ። «ነገር ግን፣ አሁን የማነ ባቸው አብዛኞቹ ዘረፋዎች እስካሁን ምንም ውጤት ሳይ ያልተደረሰ ባቸው ናቸው ።»

«እስቲ ልያው» አልኩና ጋዜጦቹን አነበብኩ ። ብዙዎቹ ዘረ ፋዎች ሱቆቹ ለሥራ ክፍት በሆኑበት በጠራራ ፀሐይ መሣሪያ ባነገቱ ሰዎች የተከናወኑ ናቸው ። ሦስቱ ብቻ በጨለማ የተፈጸሙ ናቸው ። ከዚህ የተረዳነው ሱቆች ሌሊት የሚጠበቁት ከሰውም በተጨማሪ በኤሌክትሪክ በሚሠራ የማስጠንቀቂያ ደወል ጭምር እንደ ነበረ ነው ። ለዚህም ነው በቀን የተዶረጉት ዘረፋዎች ሊሳኩ የቻሉት ።

ሁለታችንም ተያየንና ፈገግ አልን ።

«በቀን ሲዘርፉ ከዐይናቸው በስተቀር ፊታቸውን በጨርቅ ይሸፍናሉ?» አለኝ ።

«ልክ ነህ፤ ብዙውን ጊዜ የሚያያቸውን ሰው ለማሳሳት ፣ ፊታ ቸውን ይሸፍናሉ ወይም አርቲፊሻል ጺም ያደርጋሉ ። የሚያያቸውን ሰው ግራ ለማጋባት አልባሌ ልብስም ይለብሳሉ ።»

እንደ ገና ተያየንና መጠጥ ደገምን ።

«እንዴት ይመስልሻል?»

«ለኔ ጥሩ መስሎኛል ። አንተስ?»

«እኔም ጥሩ መሰለኝ ። ጂኒ ! ሱቆቹን ከዘረፍን በኋላ ጌጣ ጌጡን ሸጠን እንዴት ገንዘብ እናገኛለን?»

«ሁለት መንገድ አለ ። አንደኛው ለፖሊሶች ተባባሪ ያልሆኑ ሰዎችን አጥንተን እንሸጣለን ። ሌላው ገንዘብ ማግኛ ዘዴ፣ ሱቆች ኢንሹራንስ ስላላቸው የተሰረቁትን ንብረቶች ለኢንሹራንስ መሸጥ

ነው ። ገባህ? ኢንሹራንሶች ለጠፋው ንብረት መቶ በመቶ ለባለሱቆች ከመክፈል ለሌቦች የተወሰነ ገንዘብ መክፈል ሳያዋጣቸው አይቀ ርም ። ፖሊሶችና የሕግ ሰዎች ይህን ውል ይቃወማሉ ። ግን ምንም ማድረግ አይችሉም ። በርግጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። ዋናው ቁም ነገር እንዴት እንደሚዘረፍ ማቀድና ለመጽሐፍ በሚያመች መንገድ ለማዘጋጀት እንጂ ፣ ለመዝረፍ ፍላጐት ስለሌለን ይህ አያስ ጨንቅም ።»

«ልክ ነሽ» አለ በራሴ ላይ አሻግሮ ግድግዳውን እያየ ። «አዎ! አንዘርፍም » ሲልም የተናገርኩትን ደገመው ።

በጊጣጌጥ ዘረፋው ተስማምተን ለመጽሐፋችን ዓላማ ተፈጸሚ ነት ጥሩ ውጤት የሚያስገኝልንና ተስማሚ የሚሆንልንን ሱቅ ማማ ረጥ ጀመርን ።

«በጣም ከፍተኛ የሆኑትን ሱቆች በቀን ለመዝረፍ ከፍተኛ የሰው ኃይል ያስፈልገናል ። አነስተኞችን ብንዘርፍ ለምንቀጥራ ቸው ሌቦች ድርሻ እንኳን የሚሸፍኑ ስለማይሆኑ ፣ በመካከለኛ ሱቆች ዘረፋ ላይ ማተኮር ይኖርብናል ።»

«አዎ ! ከሰባትና ከስምንት ሰው በላይ ሠራተኛ የሌላቸውን ቢሆን ፣ በተጨማሪም አንድ መግቢያ በር ብቻ ያለውን ሱቅ ብናገኝ ጥሩ ነው ።»

«ይሁን ። ግን ውድ ንብረት የያዘ ሱቅ ፣ ለምሳሌ ወርቅ ፣ አል ማዝና ዕንቁ. . . አዎ ! እንዲያውም የማስጠንቀቂያ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች ቢኖሩም፣ በቀላሉ ልናጠፋቸው የምንችለው ዓይነት»

«ልክ ነህ ! ከአንድ የታጠቀ ዘበኛ በላይ የሌለው ሱቅ ደግሞ ይበልጥ የተሻለ ይሆናል» በማለት በማስታወሻየ መጻፍ ጀመርኩ ። «ምን ያህል ሰዎች ያስፈልጉን ይመስልሃል?»

«እኔና አንችን ጨምሮ ሌሎች ሦስት ሰዎች ብናገኝ ። ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ጋጋታ ነው ።»

« ከዘረፋው በኋላም ሆነ በፊት ውጪውን የሚቆጣጠርና ሰን ወጣም ይዞን ሊሔድ የሚችል አንድ ሾፌር ያስፈልገናል እኮ !»

«ተጨማሪ አራተኛ ሰውነ ምናልባት የሱቁ ስፋትና ጥበት የሰ ውን ቁጥር ሊወስነው ይችላል ። ስለዚህ ጄኒ ፣ አመቺ ሱቅ መም ረጡ ያንች ሥራ ይሆናል ። ቅዳሜና እሑድ፣ እንዲሁም ከሥራ በኋላ ልረዳሽ እችላለሁ ። ነገር ግን ኃላፊነቱ በሙሉ ያንች ነው ።»

«ከየት ብጀምር ይሻላል ?»

«ብዙ ሕዝብ የሚበዛበት አምስተኛው ጐዳና ስለሆነ ከዚያ ብትጀምሪ ?»

«የከተማውን ግማሽ መዞር ሊኖርብኝ ነው ?»

«ረዥም መንገድ መጓዝሽ አልቀረም ።»

«መጓዙ ለኔ ይጠቅመኛል ። በዚህም ላይ አሥቂኝ ነው ።» በዚሁ ከዲክ ጋር ተስማምተን ከተለያየን በኋላ ፡ ዕቃዎቼን አነሣሥቼና አደዳድቼ እንደገና ተቀምጬ በማስታወሻዬ የጻፍኩትን ማንበብ ጀመርኩ ። እስካሁን ከዲክ ጋር የተነጋገርንባቸውን ሁሉ በማስታወሻዬ ባለመያዜ ቅር አለኝ ። መዝግቤው ቢሆን ኖሮ ለወደፊቱ አዲሱ መጽሐፌ ጠቃሚ በሆነ ነበር ።

«አልዶ! ቆይ ታየኛለህ!» ብዬ በመጮህ የኤሌክትሪክ ታይፔን ተያያዝኩት ። ለመግቢያ ምዕራፌም፡ «እንዴት ተጀመረ» የሚለውን ርእስ አደረኩ ።

መልማመድ ጀመርኩኝ

ዝርዝር የየወቅቱን እንቅስቃሴዎቼንና ያጋጠሙኝን ገጠመኞች ለዲክ እንደማልነግር ወሰንኩ ። ይህም ምናልባት ከነገርኩት ፍር ሃት ሊገባው ይችላል በሚል ሥጋት ነው ። ለሁለት ሳምንታት ያህል በዋና ዋና መንገዶች ላይ መዘዋወር ጀመርኩ ። ኪሎ ሜትር ቆጣሪ እግሬ ላይ ታስሮልኝ ቢሆን ኑሮ በቀን ምን ያህል እንደ ተጓዝኩ ባውቀው ደስ ባለኝ ነበር ።

በተዘዋወርኩባቸው ቦታዎች ሁሉ አየሩ ቀዝቃዛ በመሆኑ የሱፍ ካቦርቴን ደርቤ ነበር ። ፖሊሶችም ሆኑ የጌጣጌጥ ባለ ሱቆች በተደ ጋጋሚ ቢያዩኝም ፡ ከአለባበሴ ጀምሮ እስከ አካሐዴ ድረስ ሊያስጠረ ጥረኝ የሚችል ፍንጭ አይገኙብኝም ።

ላልወድ በግድ ፖሊሶችንና ዘበኞችን እንደ መደበኛ ጠላቶቼ ተመለከትኳቸው ። የመኪናና የሰው ብዛት ለዕቅዴ ተፈጻሚነት አመቺ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን በደንብ አጠናሁ ።

የአየሩ ጠባይም ሲለዋወጥ እንደሚጠቅመኝ ተረዳሁ ። ከፀሐያማ ቀን ይልቅ ጨፍጋግ ያለ የደመና ቀን ለዘረፋ የተሻለ አማራጭ ሆኖ አገኘሁት ።

ስለ ዓለም ፣ ስለ ሕይወትና ሕብረተሰብ የነበረኝ ሐሳብና እም ነት ሁሉ እየተለወጠ መጣ ። የራሴን ምግብ እንኳን ተወት አደረ ኩት ። የምበላው ምግብ አልጥም አለኝ ። ሌላው ቀርቶ የወሲብ አስ ፈላጊነት እየተረሳኝ ሔደ ። ዋናው ሐሳቤ በዘረፋው ዕቅድ ላይ ብቻ ሆነ ። ሁልጊዜ ከጧቱ አራት ሰዓት ሆስፒታል የምሔድ ወይም የቤት ዕቃ ለመግዛት እንደሚወጣ ሰው መስዬ ወዲያና ወዲህ ስል እውላለሁ ።

መዘዋወሬ የትኛው የጌጣጌጥ ሱቅ ለዘረፋ አመቺ እንደሚሆን በየሱቆቹ በማልፍበት በጥቂት ደቂቃ ውስጥ የመለየት ችሎታ አስ ገኝቶልኛል ።

በመጀመሪያ ሳምንት በመኪና ለማምለጥ እንዲቻል አካባቢው መኪና የሚበዛበት፣ ግን ማቆም የማይቻልበትና በፍጥነት የሚነዳበት ሥፍራ ሊሆን እንደሚገባው ተረዳሁ ።

ብዙውን ጊዜ በየሱቆቹ እየገባሁ ቀለበትና ሐብል እየጠየቅሁ እወጣለሁ ። የገዛሁት ግን የለም ። ይህም ምን ያህል ንብረት እንዳ ላቸው ፣ የአጠባበቃቸው ሁኔታ ምን እንደሚመስልና የሠራተኞች ብዛት ስንት እንደሆነ ፣ ጌጣጌጡ ውጭ ብቻ የሚቀመጡ ወይም ሌላ ማስቀመጫ እንዳላቸው ለማወቅ ረድቶኛል ።

አንዳንድ ዘመናዊና ከፍተኛ ንብረት ያላቸውን ሱቆች በተደ ጋጋሚ የተመለከትኳቸው ቢሆንም ፣ ብዙውን ጊዜ በራቸውን ይዘ ጋሉ ። የሚከፈቱት በሀብታምነታቸው ለሚታወቁ ደንበኞቻቸው ብቻ በመሆኑ ለዘረፋ አመቺ አይደሉም ።

ሌሎች ሱቆችም ፣ ጌጣጌጣቸውን የሚደረድሩ ቢሆንም ዋጋቸ ውን አይለጥፉም ። የሚለጥፉ ቢኖሩም ከውጭ የሚታዩ አይደሉም ። ይህም ጥራት ያላቸው ጌጣጌጦች የሚሸጡ ነጋዴዎችን መለያ መሆኑ ነው ።

ከፍተኛ ንብረት ያላቸው መሆኑን ለማወቅ የሱቆች ስፋት ወሳኝ አይደለም ። አንዳንዶቹ የእንግዳ ማረፊያ ወንበር ብቻ ያላቸው ሲሆን ፣ ደንበኞች የሚፈልጉትን ጌጣጌጥ ዓይነት ብቻ ሲጠየቁ ከው ስጠኛው ክፍል አውጥተው ያሳያሉ እንጂ ፣ የሚደረደር ጌጣጌጥ አያ ስቀምጡም ። የገዥውን ዐይን ካልማረከ ያመጡትን መልሰው ሌላ ለማምጣት ስለሚሔዱ ለዘረፋ አመቺ አይደሉም ።

ሌላው የተረዳሁት ብዙዎቹ ሱቆች መሣሪያ የያዙ ዘበኞች ሲኖ ሩዋቸው ፣ ከውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞችም አነስተኛ በእጅ የሚያዝ ሬዲዮ አላቸው ። እነዚህ ሬዲዮኖች በአካባቢው ከሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ጋር ለመነጋገር የሚረዱ ናቸው ።

በአብዛኛዎቹ ሱቆች አነስተኛ ድምፅ ያላቸው የኤሌክትሪክ ማስጠንቀቂያዎች በግድግዳዎች ላይ ይታያሉ ። ሠራተኞቹ እነዚህን በግልጽ የሚታዩ ማስጠንቀቂያዎች እንዳይነኩ ዘራፊዎቹ ትኩረት በሚያደርጉበት ወቅት በቀላሉ በድብቅ መልእክት ለማስተላለፍ የሚረዱ ሌሎች ሥውር መሣሪያዎች መኖራቸውን አጤንሁ ።

ከፍተኛ ንብረት የሚቀመጥባቸው ካዝናዎች ይህ አስጠንቃቂ መሣሪያ ያላቸው ቢሆንም ፣ ቀን ቀን እንዳይሠሩ ያላቅቋቸውና ማታ ሲወጡ እንደገና ያገናኙዋቸዋል ።

በሁለተኛው ሳምንት መጨረሻ፣ ወኪሉ ሶልፋበር ወደ ምሽቱ ገደማ ስልክ ደውሎ ፣ «ባለፉት ሦስት ቀናት ደውዬ እጣሁሽ ። የት ሐደሽ ነው የኔ ቆንጆ?» አለኝ ።

«ወጣ ብዬ ነው » ስል መለስኩለት ።

«ምን ለማድረግ ?»

«ለጥናት ።»

«እዲስ ጽሑፍ ጀመርሽ እንዴ ! የኔ ቆንጆ ?»

«ጥሩና እውነተኛነት የሚኖረው» አልኩት ።

«ደስ የሚል ዜና ነው ። አስታውሽ ውሸት የማይኖርበት ንጹሕና ወደ እውነትነት የተጠጋ ይሁን ።»

«እሞክራለሁ» ብዬ ስልኩን ዘጋሁና ፣ ባለፉት ሳምንታት ያከናወንኳቸውን ተግባራት በምመዘግብበት ማስታወሻዬ ላይ የየዕለቱን ድርጊት አሰፈርኩኝ ።

☆ ☆ ☆

ከመኖሪያ ቤቱ ትንሽ ራቅ ብሎ በባለቤቱ በሼዝ ሞሪስ ስም የሚጠራ ምግብ ቤት አለ ። ባለቤቱ ሞሪስ ቀደም ሲል በተለያየ የውን ብድና ሥራዎች የተሳተፈ ሲሆን ፣ የምግብ ቤት ባለቤት ከሆነ ጀምሮ ግን፣ ይህንን ትቶ የምግብ ቤቱን ሥራ እያካሔደ በተጨማሪ ባለጉዳዮችንም ያገናኛል ። የሱ ዓይነት ምግብ ቤቶች በከተማው ወደ መቶ የሚጠጉ ሲሆን ፣ የሞሪስም አንድ መቶ አንደኛው ሳይሆን አይቀርም ። ብዙውን ጊዜ ምግብ ቤቱ በሰው የሚሞላ በመሆኑና መቀመጫም ስለማይገኝ፣ በየኮሪደሩ ቆመው የሚዝናኑት ብዙ ናቸው ። ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ ግን፣ መቀመጫ የሚገኝበትና የአካባቢው ሰዎች እንደልብ የሚሆኑበት ነው ። ባለቤቱ ሞሪስ በስፖርት ፣ በ

ዚቃና በቁማር ጨዋታ ችሎታ ያለው ፣ በሰዎች መኻከል የሚነሣ አለመግባባትን የሚፈታ ፣ የሚናገራቸው ሁሉ እንደ ሕግ ተወስደው የሚፈጸሙ በመሆናቸው በአካባቢው ታዋቂ ነው ።

ምግብ ቤቱ ጭር የሚልበትን ሰዓት ጠብቄ ሞሪስን በግል ለማ ነጋገር ገባሁኝ ።

«አ! ጆኒ! እንደምን አለሽ? ካየሁሽ ብዙ ጊዜ ሆነኝ ። ደህና ነሽ ወይ?» ሲል ሞቅ ባለ ሰላምታ ተቀበለኝ ።

«ሞሪስ! ምን ብዬ እንድነግርህ ነው? ይልቅስ ብራንዲ ለሁለ ታችንም ቅዳ!» በማለት እንደ ተናደድኩ አስመስዬ ተናገርኩ ።

ብዙ ጊዜ የምትጠጭው ቪኖ እንጂ ብራንዲ አልነበረም ፣ ዛሬ ምን ነካሽ? ችግር አለ?»

«ትላንት ማታ ሌቦች ሊዘርፉኝ ሞክረው ስለ ነበር፣ የዛ ድንጋጤ አሁንም አልለቀቀኝም » አልኩትና እንዲያምነኝ እጄን ማንቀጥ ቀጥ ጀመርኩ ።

«የውሻ ልጆች ! በዚህ ወር ውስጥ አንቺ ሦስተኛ ሰው መሆ ንሽ ነው ። ለመሆኑ ጐዱሽ ?»

«አይ አልተጐዳሁም ። አመለጥኩ ።»

«እና ፣ ምንም አልሆንሽማ ?»

«ምንም አልሆንኩም ። ብቻ ቦርሳዬን ወሰዱት ። ከመቶ ብር በላይ ነበረበት ። ደግነቱ የባንክ ደብተሬን አልወሰዱብኝም ። ዕድ ለኛ ነኝ ።»

«መልካቸውን ትለያቸዋለሽ ?»

«እንዴት ልበልህ ? ጭቤ የያዙ ጐረምሶች ናቸው ።»

«ቅማላሞች !» በማለት አዲስ የመጣውን ሰው ሊያስተናግድ ሔዶ ሲመለስ «እና ፖሊሶች ምን አሉሽ ?» አለኝ ።

«ፖሊሶች !» አልኩት በመገረም ። «ቃሌን ተቀበሉኝ ። ምን ማድረግ ይችላሉ? በአሁኑ ጊዜ በኒውዮርክ ከተማ በቀን ከመቶ በላይ ተመሳሳይ ዝርፊያዎች ይካሔዳሉ ። ሞሪስ ! መጥተው ቦርሳዬን ለመ ንጠቅ ሲሞክሩና ጩቤ ሲያሳዩኝ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ። ሽጉጥ ኖሮኝ ቢሆን ኖሮ አንዱን ደረቱን ባልኩት ነበር ።»

«እውነተኛና ንጹሕ ያገራቱ ዜጐች መሣሪያ መያዝ አልቻሉም ። በአሁኑ ጊዜ ሌቦች ባለመሣሪያ ናቸው !» አለኝና ትከዝ አለ ።

ዐይን ዐይኑን እየተመለከትኩ «ሞሪስ ! ሁለተኛ መዘረፍ አል ፈልግም ። ሊዘርፉኝ ቢፈልጉም በሰላም መሆን የለበትም ። ስለዚህ መሣሪያ ከየት ማግኘት እንደምችል ታውቃለህ?»

ድንግጥ ብሎ ፣ «የኔ ልጅ ! ይህን ማድረግ የለብሽም ። ሊዘ ርፍሽ የመጣውን አስቀድመሽ ብትገድይ በሕግ ተጠያቂ መሆንሽን ታውቂያለሽ ?»

«ግድ የለኝም !» አልኩት በንዴት አነጋገር ። «ራሴን መከ ላከል መቻል አለብኝ ። ምናልባት በሚቀጥለው ጊዜ ሊዘርፈኝ የሚ መጣው ፣ ከገዢፊያውም አልፎ ሊደፍረኝ ይፈልግ ይሆናል ። ሞሪስ እባክህ መሣሪያ እንዳገኝ እርዳኝ ።»

እንደ ገና አዲስ የመጣውን ሰው ሊያስተናግድ ፈጐ ተመለሰና ጠጋ አለኝ ። እኔም ተጠጋሁት ። «ሰሚ !» አለኝ በመንሾካሾክ ፣ «ስሕተት ውስጥ ልትወድቂ ትችያለሽ ፣ ማለቴ ተኩሰሽ ብትስች በጩቤ ትወጊያለሽ ፤ ባለመሣሪያም ከሆነ ተኩሶ ይገድልሻል ። ማንን ልትወቅሽ ነው ?»

«ሰድሌን ለመሞከር ፈቃደኛ ነኝ ።»

«ለመሆኑ መሣሪያ እንዴት መጠቀም እንዳለብሽ ታውቂያለሽ?»

«እማራለሁ ። መደገንና ምላጩን መሳብ አይደለም እንዴ !»

«ነገሩ እንደዛ ነው ። በትክክል ቆርጠሽ ከተነሣሽ ላገኝልሽ እሞክራለሁ ።»

«ዋጋው ስንት ይሆናል ?»

«ከአምስት መቶ ብር በላይ ይሆናል ። ቢሆንም እንደ መሣሪ ያው ዓይነት ይለያያል ። ለማንኛውም ከሚሸጠው ሰውዬ ጋር እንዳ ገናኝሽ መቼ እንገናኝ? እንዳያውም ነገ ማታ ብቅ በይ ወይም ደው ይልኝ ፣ ባልኖር መልእክት እተዋለሁ ። ግን የምርሽን ነው ?»

«ሙሉ በሙሉ !» አልኩት ኮስተር ብዬ ።

«እሺ የሚቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እሞክራለሁ ።»

☆ ☆ ☆

ለዘረፋ አመቺ የሆኑ ሦስት ሱቆችን መርጫለሁ ። ዲክ እነዚህን ሱቆች እንዲያይ አደረኩ ። የመጀመሪያው ሱቅ በምሥራቅ አምስ

ተኛው መንገድ በሃምሳ አራተኛውና በሃምሳ አምስተኛው ጐዳና መካከል ይገኛል ። ሱቁ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ ነው ። አንድ ትልቅ መግቢያ በር ፣ ሦስት ሠራተኞች ፣ አንድ ኃላፊና ሁለት የታጠቁ ዘበኞች አሉት ። የጌጣ ጌጥ ማስቀመጫው ጠንካራ የብረት መዝጊያ ባለው ሌላ ክፍል ውስጥ ተቀምጧል ፤ መዝጊያው የሚከፈተው በመሸጫ ሰዓት ብቻ ነው ።

ሱቁን ከመንገድ ባሻገር ቆመን ተመለከትን ፤ ከዚያም መንገዱን ተሻግረንና በሱቁ በር አልፈን በመስኮት የተደረደሩትን ጌጣ ጌጦች በጣታችን እያመለከትን ካየን በኋላ ወደ ውስጥ ገባን ። ሠራተኞቹ ሥራ በዝቶባቸው ወዲያ ወዲህ ይላሉ ። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ክፍሉን በደንብ ለመመልከት ቻልን ። የምንገዛ በመምሰል በእጃችን ጌጣጌጦችን እያመለከትን 'ይህ ጥሩ ነው ያኛው ይሻላል' ተባባልን ።

ከሱቁ እንደ ወጣንም የዲክን እጅ በመያዝ ወደ ሌላው ስፍራ ጉዞ ጀመርን ።

«እሺ ! ስለ ሱቁ ምን ታስባለህ ?»

ዲክ በመጠራጠር፡ «እንጃ! ብዙ ጌጣጌጥ አለ። ቢሆንም ለዘረፋ በቂ አልመሰለኝም ። ግን ውድ ጌጣጌጥ ዓዳ አስቀምጠው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ያየነው አንድ ውድ የጌጥ ሐብል አራት ሺ ብር የሚያወጣ ነው ። ስለዚህ ይህ ሱቅ የሚሆን አልመሰለኝም » አለኝ ።

«እሺ የሚቀጥለው ከመናፈሻው ጥቂት አለፍ ብሎ በስተደቡብ የሚገኘው ነው» አልኩትና ወደዚያው አመራን ።

ሁለተኛው ሱቅ በጣም ሰፊ ሆኖ ዩኒፎርም የለበሰ ዘበኛ ፣ ስድስት ሠራተኞች ፣ ገንዘብ ተቀባይ ፣ ኃላፊና አንድ በዕድሜዋ የገፋች ከተቀመጠችበት ሳትንቀሳቀስ ዝም ብላ ገበያተኞችን የምትመለከት ሴት አለች ። በበሩ መግቢያና በስተግራ ግድግዳ ላይ ሁለት ትናንሽ ፎቶግራፍ የሚያነሡ ካሜራዎች ተሰቅለዋል ። ከውስጠኛው ክፍል እነዚህ ካሜራዎች የሚያስተላልፉትን ምስል የሚከታተሉ ሰዎች ሳይኖሩ አይቀሩም ።

ከሱቁ ውስጥ እንደ ገባን የበረዶ ሽራፊ የምታክል ትንሽ አልማዝ ጠየቅን ። ዋጋው ዐሥራ ስምንት ሺ መሆኑ ተነገረን ። የተሻለና ዋጋ የሚቀንስ እንዳለ ሠራተኛውን ጠየቅነው ። እርሱም አልማዙን ከፈለግነው ኃላፊውን በግል ብናነጋግረው ሊቀንስልን ስለሚችል ትንሽ እንድንጠብቀው ነገረን ። ኃላፊው ከሌሎች ደንበኞች ጋር

እየተነጋገረ ስለ ነበረ መቆየት አንችልም ፡ ቀጠሮ አለብን ብለን ወጣን ።

ለአጭር ጊዜ ሱቁ በር በመቆም ሰላማዊ ሰው መሆናችንን እንዲ ያዩ በማለት ሲጋራ አውጥተን ለኩስንና መንገዳችንን ቀጠልን ።

«ይሄኛውስ እንዴት ነው ዲክ?»

«ይሄ ከፍተኛ ገንዘብ አለው ። ኃላፊው ለሴትየዋ ሲያሳያት የነበረውን ዕንቁ አይተሻል?»

«አዎ አይቻለሁ ። ከሃምሳ ሺ ብር በላይ የሚያወጣ ሳይሆን አይቀርም ። ጌጣጌጡን የሚያስቀምጡት የት ይሆን? ምናልባት ጓዳ ውስጥ ይሆን? እላይኛው ወይም እታችኛው ክፍል ሊሆን ይችላል ። ያሳሰበኝ የት እንዳለ ሳይሆን የካሜራዎቹ ነው ።»

«ሦስተኛውን ሱቅ እንይና በኋላ እንወያይበታለን ።»

የመጨረሻው አማራጭ ሱቅ በሃምሳ አምስተኛው መንገድ በማድቦን ጐዳና በስተምዕራብ የሚገኘው ነው ። በዚህ አካባቢ የተ ጨናነቀ ትራፊክ ያለበትና ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚያስወጡ መንገዶች ያሉ መሆናቸውን ልብ አላልኩም ነበር ። ሱቁን ከውጭ ሲያዩት የሚስብ አይደለም ። ከሱቁ መስኮት በላይ ‘ሰዓትና ጌጣጌጥ እንገዛለን ፣ እንሸጣለን ፡ እናድሳለን’ የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል ።

ዲክ ፊቱን ወደኔ ዞር አድርጎ ፡ «ምንድነው ይሄ? የሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫ ነው እንዴ ?» አለኝ ።

«ገዛም ብለህ ተመልከት» አልኩትና ወደ ሱቁ ገባን ። የሱቁ ስም ፡ «ብንደንበርግና ልጆቹ» ነው ። እንደ ዘመናዊዎቹ ሱቆች ያሸ በረቀ አይደለም ። በሱቁ ውስጥ ለገበያተኞች የተዘጋጁ ትናንሽ ወን በሮች አሉ ። ከነዚህ ወንበሮች ለየት ያለ ትልቅ ወንበር አለ ። ሦስት ወጣት ሠራተኞች ፡ አንድ ኃላፊ ያለው ሲሆን እንደ ሌላው ሱቅ የቴሌቪዥን ካሜራዎች የለውም ። በየግድግዳዎቹ ላይ በምስጢር አስጠንቃቂ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች መጠመዳቸው ይታያል ፤ የታ ጠቀ ዘበኛ ግን የለውም ። ለማታ ጥበቃ የሚያመች የሚዘረጋ ብረት መዝጊያ አለው ። ሱቁ ጸጥታ የሰፈነበት ነው ።

ሦስቱም ሠራተኞች በሥራ ተጠምደዋል ። ኃላፊው እራሱ መጥቶ በአንገቱ ጭምር ሰላምታ እየሰጠ ፡ «እንደምን ዋላችሁ ፡ ምን ልታዘዝ ?» አለን ።

«ከውጪ የተለጠፈውን ማስታወቂያ አይቼ ነው ። ከወርቅ የተሠራ የኪስ ሰዓት አለኝ !» እጆቹን በመዘርጋትና አንዱን

ትከሻውን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ፥ «ምን ያህል ዕድሜ አለው ?» ሲል ጠየቀኝ ።

«ምን ያህል ዕድሜ እንዳለው በእውነቱ አላውቅም» አልኩት ። የእውነቴን ነው ።

«አምጪውና ልየው» አለኝ ።

«እሺ አሁን ስለ አልያዝኩት ፥ ሌላ ጊዜ አመጣዋለሁ ።»

«ጌጣጌጦችን ተዟዙረን ማየት ይቻላል?» አለና ዲክ ጠየቀው ፥ ፈገግ በማለት ። «ይቻላል» ሲል መለሰለት ።

ብዙም መቆየት አስፈላጊ አልነበረም ። ሁሉንም ማየት ቻልን ። አንዱ ሠራተኛ አንድ ጌጥ ለአንድ ሰውዬ እያሳየ ዋጋውን ሁለት መቶ ሰማንያ ሺ ብር ሲል ሰማነው ።

ወዲያው ከሱቁ ወጣንና ተያይዘን ወደ ቡና ቤት ገባን ።

«ጄኒ! ሱቁ በጌጣጌጥ የተሞላ ነው ። ይሄ ምርጫችን መሆን አለበት » አለ ዲክ እየተፍነከነከ ። እጇን በጠረጴዛው ሥር አሳልፌ እጁን ጨበጥ አድርጌ ፥ «ይህን በማለትህ ደስ ብሎኛል ። የመጀመሪያ ምርጫየም ይሄ ሱቅ ነው ። ለዕቅዳችንም አመቺ ነው » አልኩት እኔም ፈገግ ብዬ ።

«ምንም ጥርጥር የለውም ! አንድ በርና ስድስት ሠራተኞች ! ያውም ጓዳ ሁለት ሠራተኞች ሊኖሩ ይችላሉ ብዬ ነው !»

«በተጨማሪ ለመግዛት የሚመጡ ደንበኞች ሊኖሩ ይችላሉ» አልኩት ። ሻያችንን አቅርቦልን አስተናጋጁ እስክሚሔድ ዝም ተባ ባልን ። ዲክ ራሱን በመነቅነቅ ፥ «እውነት ለመናገር በጣም ጥሩ ነው ! የቴሌቪዥን ካሜራና የታጠቀ ዘበኛ የሌለው ፥ የጌጥ ማስቀመጫ ሣጥኑም ክፍት የሚሆን. . . .»

«ግን እኮ አስጠንቃቂ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎች አሉት » አልኩት ።

«ዐውቃለሁ ፤ ግን ከሁለት መቶ ሺ ብር በላይ የሚገመት አንድ ጌጥ ባለው ሱቅ ውስጥ ጥበቃው በቂ አይደለም ።»

«አሁን የሚያከራክረን አይሆንም ። ግን ከሌሎቹ ይልቅ ምርጫችን ይህ ሱቅ ስለ ሆነ ፥ በየጊዜው ስለ ሱቁ ጥናት ማድረግ ነው ። ይኸው ቡና ቤት ለጥናታችን አመቺ ነው ። እዚህ ሆኖ ሱቁ መቼ እንደሚከፈትና እንደሚዘጋ ፥ ምን ያህል ሠራተኞች እንዳሉትና

የመሳሰሉትን እከታተላለሁ ። እንዲሁም ለኃላፊው አለኝ ያልኩት ንም ሰዓት አምጥቼ ሱቁን በደንብ አየዋለሁ ።»

«እና የምር ልትሸጭውን?»

«ብሸጠው ምናለበት? እንዳውም ለዕቅዳችን ማስፈጸሚያ የገን ዘብ ድጋፍ አገኘን ማለት ነው » አልኩት ። ሁለታችንም ተሣሣቅን ።

ከልባችን ተደሰትን ። ሆኖም በውስጣችን ዘረፋውን እንደማን ፈጽመው ገብቶናል ።

ሞሪስ ስልክ ደውሎ ፣ መሣሪያ ከሚሸጠው ሰውየ ጋር ስለ ተነጋገረ ፣ እሑድ ማታ አራት ሰዓት ላይ እንድገኝ ነገረኝ ።

«ከልብሽ መሣሪያውን የምትፈልጊ ከሆነ ልክ በሰዓቱ ተገኚ ። ሰውየው ሰዓት አክባሪ ነው ።»

«ሰዓት አክባሪ?» አልኩት ።

«የዘወትር ጠባዩ ነው ።»

☆ ☆ ☆

እሑድ ማታ በተባለው ሰዓት ሼዝ ሞሪስ ቡና ቤት ደርሼ በቀጥታ ሞሪስ ወደ ቆመበት ሒድኩኝ። በሹክሹክታ «ማድ ቤት አጠገብ ወደ ተቀመጠው ሰውዬ ጋ ሒጂ» አለኝ ።

ቀስ ብየ ፊቴን በማዞር ወደ ተነገረኝ ቦታ ተመለከትኩ ። ዐይኔን ማመን አልቻልኩም ።

ገርሞኝ ወደ ሞሪስ ፊቴን አዙሬ ፣ «እዚያ ሽማግሌ ጋ?» አልኩት ሞሪስ ፈገግ ብሎ ፣ ስሙ 'አጐት ሳም' ነው ። ዝም ብለሽ ሒደሽ 'አጐት ሳም' በይው» አለኝ ።

እንዳለኝ ወደ ሽማግሌው ሒጄ፣ «እንደምን አመሸህ አጐት ሳም፣ ጄኒ ሼን እባላለሁ» አልኩት ። በፈገግታ ከመቀመጫው ተነሥቶ ከተጨባበጥን በኋላ ወንበር ሰቦልኝ ተቀመጥኩ ። «የኔ ወይዘሮ ! ስም መጥራቱ አስፈላጊ አይደለም ። ቅር ይልሻል ?» አለኝ በለስላሳ አነጋገር ።

መልስ ሳልመልስለት፣ «ቡና ይምጣልን» አልኩት ። ወዲያውኑ በጆ ምልክት አስተናጋጁን ጠርቶ ቡና ለሁለታችንም አዘዘ ።

«እሺ እንግዲህ ተገናኘን» አለኝ ።

የሽማግሌው ቁመት መካከለኛ ሲሆን፣ ዐይኖቹ ትክ ብለው ሲያዩ

ያሸብራሉ ። ጸጉሩን ሙሉ በሙሉ ሽበት ወሮታል ። አለባበሱ ግን እንደ ጐረምሳ ነው ።

«የኔ ወይዘሮ! ባለፈው በደረሰብሽ ችግር በጣም ነው ያዘንኩት» አለ ፣ የቀረበልንን ቡና እየቀዳ ።

ግራ በመጋባት ተመለከትኩትና ፣ ለሞሪስ የነገርኩት ውሸት ትዝ ብሎኝ ፣ «እንደሚመስለኝ ማንኛውም ሰው ራሱን ለመከላከል መጣሩ አዲስ ነገር አይደለም» አልኩት ።

«አዎ አዲስ አይደለም ። በኛ ዘመን ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል ። በአሁኑ በናንተ የሥልጣኔ ዘመን ሰላማዊ ሰው ከቤቱ ወጥቶ የማይመለስበት ጊዜ ላይ ደረስን ። ዘመኑ ያፈራቸው ወንጀለኞች ንጹሕ ሰዎችን ቀን በቀን በየአደባባዩ ሲዘርፉ ሀይ! የሚላቸው ጠፋ ። አያ ሳዝንም ?»

መልስ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ ዝም አልኩት ። በመቀጠል «አሳዛኝ ነው ። ማንኛውም ሰው ያለው አማራጭ ራሱን በራሱ መከላከል ነው » አለ ።

«አዎ ! እኔም ራሴን መከላከል አለብኝ» አልኩት ።
«በደንብ እንጂ ! ራስሽን መከላከል አለብሽ ። ምን ዐይነት መሣሪያ ነው የምትፈልጊው ?»

ስለ መሣሪያው በዚህ ቡና ቤት ውስጥ የምንወያይ አልመሰለኝም ነበር ። ግን ይህ የለመደውና መደበኛ ሥራው ስለሆነ ፣ ከኔ በበለጠ ስለዚህ ጉዳይ የት ማድረግ እንዳለበት ስለሚያውቅ አልተጨነኩም ።

«አጐት ሳም ! እውነቱን ለመናገር ስለ መሣሪያ ያለኝ ዕውቀት እነስተኛ ስለ ሆነ ካንተ ምክር እሻለሁ » አልኩት ።

«ልክ ነሽ ፣ የኔ ወይዘሮ !» አለ ዐይኑን አፍጥጦ ። «የባለሙያ ምክር መጠየቅሽ ዐዋቂ ሰው ነሽ ። በዚህ ሥራ የብዙ ዓመት ልምድ ያካበትኩ ስለ ሆነ ፣ ልምዴን ለማካፈል ደስተኛ ነኝ ። የተወሰኑትን የሽጉጦች ዓይነት ልጠቁምሽ?»

«እሺ !»

«ብዙ ጊዜ ስለ ሽጉጥ ጉዳይ ሲነሣ ፣ ሴቶች በጌጥ ያሸበረቀና እጅም ላይ የማይከብደውን ይመርጣሉ ። ነገር ግን የመሣሪያው ማጌጥና ለእጅ መቅለል የመምረጫ ዋነኛ ነጥብ መሆን የለበትም ። ዋና ውና አስፈላጊው የመሣሪያው ውጤትና አስተማማኝነቱ ነው ።»

«የምትለው ትክክል ሊሆን ይችላል ። ለኔ ምን ዓይነት መጣሪያ ነው የሚያስፈልገኝ?»

«አንቺ የኔዋ ወይዘሮ ! ቁመናሽና የአካል ጥንካሬሽ ሲታይ ፣ ለሌሎቹ የአካል ጥንካሬ ለሚጐድላቸው ሴቶች የምመርጥላቸው ዓይነት ሳይሆን ፣ ባንቺ እጅ ላይ ትንሽ ከበድ የሚል መሣሪያ ነው ። ክብደት ማለትም አስተማማኝ ውጤት ማግኘት ማለት ነው ። በተጨማሪም መትረየስ ሽጉጦችን እመርጣለሁ ። በቀላሉ ጥይት ለማጉረስና በአንድ ጊዜም ብዙ ለመተኮስ የሚያስችልና በቦርሳሽ ይዘሽ በፈለግሽው ጊዜ ቶሎ ለማውጣት አመቺ ነው ።»

በመገረም ፣ «ቀደም ሲል ያሰብክበት ትመስላለህ» አልኩት ።

ወደ መሬት በማቀርቀር ፣ «የደንበኞቼን ፍላጐት ለማርካት ካለኝ የብዙ ጊዜ ልምድ አኳያ ብዙ እጥራለሁ ። አንቺ መሣሪያውን ለፈለግሽበት ጉዳይ ፣ ረዥም ርቀት የሚመታ መሣሪያ አያስፈልግሽም ። መሣሪያውን የምትጠቀሚበት ለመዘረፍ የሚጠጋሽን ሰው በመሆኑ ለቅርበት ነው የሚያስፈልግሽ ማለቴ ነው ።»

«አዎ! ብዙ ማለም የማያስፈልግበት ርቀት ።»

«በትክክል! እንግዲህ መትረየስ ሽጉጥ ብትወስጂ መልካም ይሆናል ። ስለዚህ ፣ የሚገኙትን ዓይነቶች ላማርጥሽ» አለኝና ትንሽ መጽሐፍ ከኪሱ አውጥቶ እፊቴ አስቀመጠልኝ ።

መጽሐፉን መሣሪያ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ያወጡት ሲሆን ፣ በየገጹ የመሣሪያው ሥዕል፣ ስምና ክብደት፣ የሚገመርሰው ጥይትና የርቀት መጠኑ ወ.ዘ.ተ ተጽፎበታል ። የመሣሪያውም ዋጋ በእጅ ጽሑፍ ከሥሩ ተጽፏል ።

የምፈልገው መሣሪያ ያለበትን ገጽ አጥፌ መጽሐፉን መልሼ «ይሄኛውን አልኩት» በእጄ እያሳየሁት ።

አየና ፣ «ይሄን አልመርጥልሽም ፤ ለሴትም የሚሆን አይደለም ፣ ዋጋው ቀላል ይሆን ይሆናል ። መሣሪያው ግን ለጦር ሜዳ የሚያገለግል ነው » አለኝ ።

መጽሐፉን ዝም ብዬ በመቀበል ፣ የቀሩትን ገጾች ተመልከቼ ሌላ መሣሪያ መርጬ አሳየሁትና ፣ «ዋጋው ማውጣት ከምፈልገው በላይ ነው ። መሣሪያው ግን ጥሩ መሰለኝ» አልኩት መጽሐፉን እየመለስኩ ።

በመደሰት ጠረጴዛውን በእጁ እየመታ፣«በጣም ጥሩ ምርጫ ነው። አውቶማቲክ ብሬታ! የኔ ወይዘሮ ጥሩ ምርጫ ነው፤የዚህ ዓይነት መሣ

ሪያ ከፋብሪካ የወጣ አመጣልሻለሁ ። በጣም ጥሩ ነው » አለ ፊቱ ፈገግታ ተላበሰ ።

«አዎ! ተጨማሪ ጥይት ያስፈልገኛል ።»

«የተወሰነ ገንዘብ ከጨመርሽ እስከ ሦስት መቶ ጥይት ላገኝልሽ እችላለሁ ።»

«ጥሩ ነው !» አልኩት ።

«የኔ ወይዘሮ መሣሪያውን በሙሉ ልብሽ ወደሽዋል ?»

«አንተ ጥሩ ነው ብለህ እስከ መረጥክልኝ ድረስ አዎ ወድጀዋለሁ ።»

«እኔ መርጨልሻለሁ ። ሌላው ጥቅሙ ደግሞ ካላስፈለገሽ በማንኛውም ጊዜ መመለስ ይቻላል ። የቆየበትን ጊዜ ዋጋ ብቻ ቀንሰን በደስታ ገንዘብሽን እንሰጥሻለን ።»

«እስቲ ለማንኛውም ሒሳቡን እናስላው » በማለት መጽሐፉን ኪሱ ከተተና ወረቀት አውጥቶ ቁጥሮችን ደማመረና ፡ «ከሦስት መቶ ጥይት ጋር አምስት መቶ ሃምሳ ብር ነው ፡ ይሰማሻል ?» አለኝ ።

«ጥሩ ነው ይሁን ። ስለ ገንዘብ አከፋፈሉና መሣሪያውን የት እንደምታገኘው የራሴ ዘዴ አለኝ ። ይህም ሦስተኛ ሰው ሊያስጨምረን ነው ። ሞሪስን ታምኛዋለሽ ?»

«አዎ አምነዋለሁ ።»

«በጣም ጥሩ! ገንዘቡን መቼ መክፈል ትችያለሽ ?»

ትንሽ አሰብኩና፡ «የሞሪስ ቡና ቤት ነገ ከሰዓት በኋላ እንደ ተከፈተ ገንዘቡን ማምጣት እችላለሁ» አልኩት ።

«ጥሩ ነው ።»

«እና ገንዘቡን ለሞሪስ ስሰጥ ሽጉጡን ወዲያው አገኛለሁ ?»

«አይደለም !» አለ በመቸኮል መልክ ። ሞሪስን በዝርዝር ጉዳዮች እንዲሳተፍ አልፈልግም ። ነገ በስድስት ሰዓት ገንዘቡን ለሞሪስ ስትሰጭው ፖስታ ይሰጥሻል ። በፖስታው ውስጥ ቁልፍና አድራሻ ታገኛለሽ ። ወዲያው በተሰጠሽ አድራሻ መሠረት የዕቃና የሠንድ ማስቀመጫ ጣቢያ ሔደሽ በያዝሽው ቁጥር መሠረት የምታገኝውን ሣጥን ከፍተሽ መሣሪያሽን ታገኛለሽ ። ቁልፉን ለሞሪስ ትመልሺ ያለሽ ። ስምንት ሰዓት ካለፈ የሚዘጋ ስለሆነ በሰዓት መገኘት አለ ብሽ ።»

«ግድየለም ፤ አድራሻውና ቁልፉ እንደ ደረሰኝ ወደ ጣቢያው እሔዳለሁ» አልኩኝ ። ከሁኔታዬም ጥርጣሬ እንደ ገባኝ ተረድቶ ፥

«ጭንቀትሽ ፥ ሔጂ መሣሪያውን ባጣውን ወይም ቁልፉ የሌለ ቢሆን የሚል ነው ። አይደለም?»

«አዎ ! አጐት ሳም ።»

«ለሰው ልጅ ትልቁ ቁም ነገር እምነት ነው ። እመኚኝ ።»

ሀይኑን ትክ ብየ ተመለከትኩና፣ «አምንሃለሁ አጐት ሳም» አልኩት ።

«እግዜር ይባርክሽ የኔ ወይዘሮ» በማለት እጇን ስሞ ተለያየን ።

በማግሥቱ ማታ ከዲክ ጋር እቤት ቁጭ ብለን ስለ መሣሪያው አጠቃቀም የተዳፈውን መመሪያ አነበብኩ ፤ ጥይት ሳላጐርስ ባዶውን ሽጉጥ እንሥቼ ወደ ግድግዳው አስምሩና ድምፁ ማስማት ያለበት ጩኸት «ካቻው» ሳይሆን «ብው» የሚል መሆን አለበት አልኩ ።

ዝግጅቱን ቀጠልኩኝ

«እንግዲህ ለሥራችን የሚያስፈልጉ ተባባሪ ሰዎችን ማግኘት አለብን ። ቢሆንም እዚህ ቤት ሰብስቤ ዘረፋውን እንዴት እንደ ምናካፈል ፥ ምን ያህል እንደምከፍላቸው መነጋገር አልፈልግም ። በተቻለ መጠን ማንነቴን እንዲያውቁ አልሻም » ስል ዲክ አማከርኩት ።

«አባባልሽ ገብቶኛል ። ሴላ ቦታ ሔደሽ ብትነጋገሪና ስምም ብትለውጪ ይሻላል እንበል ፥ ያሰብሽው ከተሳካልሽ በኋላ ፥ ከሌቦቹ አንዱ መንገድ ላይ ቢያገኝሽስ ?»

«ይህ ከሆነ ፥ የስም ለውጥ ብቻ ሳይሆን ራሴንም መለወጥ አስብኝ ማለት ነው ። ዕቅዳችን ከተሳካ በኋላ፡ ወደ ጀኒ ሼን ተለውጬ መንገድ ላይ እንኳን ቢያገኙኝ አያውቁኝም ። ይህን ማድረግ አልችልም? . . . ይቻላል አርቴፊሻል ጸጉር ፥ የተለየ ልብስ . . . የተለየ አካሔድና አነጋገር ማለት ነው ። ገባህ ?»

«ይሄን ሁሉ ለመፈጸም ያስቸግራል ። ለዚያውስ አንቺ ተዋናይ አይደለሽ ?»

«ለምን አልሆንም፣ ሴቶች ሁሉ ተዋናይ ናቸው ። ይህ ካልሆነ

እንዴት በወንዱ ዓለም መኖር ቻልን? እውነቱን ልንገርህ ፥ ራሴን ለመለወጥ እሞክራለሁ ፤ ታየኝና አያዋጣም ካልከኝ ሌላ መንገድ እሞክራለሁ ።»

«ጥሩ ፈሳጊ ነው ። ለአዲሷ ሴትዮ አዲስ ቤት የመፈለጉ ጉዳይስ?»

«ይሄ ደረጃ በደረጃ የሚሆን ነው ። መጀመሪያ የአዲስ ሴት ቅርፅ ፥ ስምና ታሪክ ካዘጋጀን በኋላ ቤት እንፈልጋለን ።»

«ጂኒ ! ይህ ብዙ ገንዘብ ያስወጣሻል ።»

«አያስወጣም ። ቢያስወጣም ከሚታሰመው መጽሐፌ የሚ ታሰብ ይሆናል ።»

በስድስተኛው ጐዳና አጠገብ ከናይለን የተሠሩ የሴት ልብስ ከሚሸጡ ሱቆች ወደ አንደኛው ገባ ፥ ሻጭዋን ሴትዮ ፥ «እንደምን አደርሽ ፥— እንደምታይው ጡቴ ትንሽ ስለ ሆነ ትልቅ አድርጎ የሚያሳይ የጡት መያዣ እፈልጋለሁ » አልኩዋት ።

«እጥፍ ነው የምትፈልጊው ወይስ ነጠላ?» ስትል ጠየቀችኝ ።

«ነጠላው ቢሆን. . .»

«ስንት ቁጥር ይሆንሻል ?»

«ሠላሳ አራት ቁጥር ይብቃኛል ።»

«ድርብ ይሻልሻል ፤ ለአንቺ ቁጥር ተስማሚ ነው ። ግቢና ሞክሪው» ብላኝ ወደ መልበሻ ክፍል ገባሁና ለካሁት ።

«ሌላ ሴት አስመሰለሽ ። ጥሩ ነው ?» አለችኝ ። በዋጋ ተስማ ምቼ ገዛሁ ።

ከዚያው ሱቅ የተለያዩ ልብሶችን ገዛሁ ። ሌላ ሱቅ በመሔድ ወደ ቡናኒት ቀለም የሚያደላ አርቲፊሻል ጸጉር ፥ ሊፕስቲክና ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ ገዛሁ ። ጫማውን ስሞክረው ለመራመድ አስ ቸጋሪ መስሎ ታየኝ ።

ለአንድ ሳምንት ማታ ፥ ማታ እያደረኩ መንገድ ላይ መለማመድ ጀመርኩ ። አካሔዱን በደንብ ስለ ለመድኩ ፥ እንግዲህ የቀረኝ የመ ጨረሻውን ፈተና ማለፍ ነው ።

ዲክ ቤት ስልክ ደወልኩና ጠራሁት ። ወዲያው ወደ መንገድ ወጣሁ ፥ ስወጣ ዘበኛው ቢያየኝም ሊለየኝ አልቻለም ። ዲክ በሦስ ተኛው ጐዳና እንደሚመጣ ስለማውቅ ፥ ሲጋራየን እያጨስኩ ጠበቅ ሁት ። በአጠገቤ ሲያልፍ ፥ «ትንሽ መጫወት ትፈልጋለህ?» አልኩት

በተለማመድኩት አዲስ የድምፅ ቅላፄ ።

«ሌላ ጊዜ ይሻላል አመሰግናለሁ» ብሎኝ መንገዱን ከቀጠለ በኋላ ተመለሰ ።

«ሐሳብህን ቀየርክ ?»

ማመን እያቃተው ራሱን ነቀነቀና ፥ «አሺ ጄኔ አሸንፈሽኛል» አለ ።

ለአንድ ወር ያህል ጌጣጌጥ መሸጫው ሱቅ ፊት ለፊት በሚገኘው ቡና ቤት እየተቀመጥኩ ፥ የሠራተኞችን የመግቢያና የመውጫ ሰዓት ፥ እንዲሁም የሠራተኞችን ስም ባላውቅም አንድ ፥ ሁለት ፥ ሦስት ብዬ ቁጥር ሰጥቼ በመሠየም አቋማቸውን እየለየሁ መዘገብኩ ። ሰባተኛው አንድ ጥቁር ሽማግሌ እንደ ዘበኛና ተላላኪ ሆኖ የሚያገለግል መኖሩንም አረጋገጥኩ ።

አልፎ አልፎም በራሴ መኪና እየሆንኩ ሱቁን ከውጭ መመልከት ጀመርኩ ። የኔ መኪና በየጊዜው ከታየች ስለሚያስጠረጥር የዲክን ቮልስ ዋገን ተጠቀምኩ ።

የሱቅ ሠራተኞች ለሦስት ሩብ ጉዳይ ጀምሮ እስከ ሦስት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራቸው ይገባሉ ። ለገበያ የሚከፈተው አራት ሰዓት ላይ ነው ። አንዱ ሰዓት ማታ ከተዶረደሩበት የተነሡትን ጌጦች መልሰው የሚያስቀምጡበት ሰዓት መሆኑ ነው ። ለምሳ ከሠለት ሠራተኞች በስተቀር የሚወጣ የለም ። እዛው ሱቅ ውስጥ ሳንድዊች ይበላሉ ።

ሱቁ ዐሥራ አንድ ሰዓት ካለፈ በኋላ ይዘጋል ። ዐሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ የሱቁ ኃላፊና ሠራተኛ ቁጥር ሦስት አንድ ላይ ይወጣሉ ። ሠራተኛው አንድ እጁን ኪሱ ወስጥ ከቶ ስለሚሑድመጣሪያ የያዘ ይመስላል ። ሁለቱ አብረው ባንክ ቤት በመሑድ ፖስታ ገቢ ያደርጋሉ ። ፖስታው የየቀኑ ሽያጭ ቼክ የያዘ ሳይሆን አይቀርም ። ከዚያም ተለያይተው በየፊናቸው ይሔዳሉ ።

ሱቁን በተቻለ መጠን በደንብ ለማጥናት ከመሞከሬም ሌላ፥ የሱቁ ደን በኞች መካከለኛ ዕድሜ ያላቸውና ሽማግሌዎች መሆናቸውን ዐውቄአለሁ ። እንዲሁም በርካታ የሆኑና በተለያየ ዕድሜ ውስጥ ያሉ በየመስኩቱ የሚመለከቱም አሉበት ።

አንዳንድ ጊዜ ግን፥ ለየት ያሉ ደንበኞች ይመጣሉ ፤ የሰውነታቸው አፃም ሪፖርተኛ የሚያስመስላቸው ፥ በአለባበሳቸውም ማራኪ

የሆኑ ወጣቶች ከእጃቸው ጋር በሰንሰለት የተያያዘ ቦርሳ ይዘው ይገ ባሉ ። ለዲክ ነግሬው ጌጣ ጌጥ አሻሻጭ ደላሎች ሊሆኑ ይችላሉ ብሎኛል ።

የዚህ ሱቅ እውነተኛ ባለቤት ማን ሊሆን እንደሚችል እኔና ዲክ ብዙ ተነጋገርን ። ጊዜ ሊፈጅብን ሆነና እንጂ፣ በተለያየ መንገድ ማወቅ እንችል ነበር ። ግን ተውነው ። ብናውቀውስ ምን ለውጥ ያመጣል ።

አለማወቃችን ግን ትልቁ ስሕተት ! ! !

በሁለተኛው ሳምንት ከአያቴ በስጦታ ያገኘሁትን የወርቅ ሰዓት በመያዝ ወደ ሱቁ ሒድኩኝ ። ቁጥር አንድ ብዬ ሥያሜ ያወጣሁለት ሠራተኛ ምን እንደምፈልግ ጠየቀኝ ።

«የሱቁን ኃላፊ ነበር ።»

«ሚስተር ጀርቪስን ነው ? ትንሽ ጠብቂው ሥራ ላይ ስለ ሆነ ነው» ብሎኝ ወንበር አመጣልኝና ተቀመጥኩ ።

ወዲያው ደንበኞችን ለማስተናገድ ትቶኝ ሲሒድ ፣ ይህ አጋጣሚ ሱቁን በደንብ ለማየት አስቻለኝ ።

ኃላፊው ከጓዳ ቦርሳ ከያዘ ወጣት ጋር ወጣ ፤ የወጣቱ እጅ ከቦር ሳው ጋር በሰንሰለት ተያይዟል ። እበር ድረስ ሽኝቶት ሲመለስ በሠ ራተኞቹና በሱ መኻል አንድ ምልክት ተሰጣጥተው መሰለኝ ፣ በቀጥታ ወደኔ መጣ ። ከተነጋገርን ከወር በላይ ይሆናል ። ግን ቶሎ እንዴት ሊያውቀኝ እንደቻለ ገረመኝ ። ይህንኑ ነገርኩት ።

«አንድ ጊዜ ያየሁትን ሰው አልረሳም ። ያውም እንደ አንቺ ያለ ቆንጆ!» ሰዓቱን ከቦርሳየ አውጥቼ ሰጠሁት ። «አንድ ጊዜ ጠብቂኝ ለባለሙያዎች ላሳየው» ብሎኝ ወደ ጓዳ ይዞት ገባ ።

ለአምስት ደቂቃ ያህል ስለ ሱቁ ሳወጣና ሳወርድ ሚስተር ጀር ቪስ ተመልሶ ለሰዓቱና ለሰንሰለቱ ሁለት መቶ ብር ለመክፈል ፈቃ ደኛ መሆኑን ገለጸልኝና ባልስማማ ግን ፣ ለሌላ ገዥ እንደሚሸጥልኝና ከሽያጩ ስድሳ አምስት ከመቶ ሊደርሰኝ እንደሚችል ነገረኝ ።

«አይ ግድየለም፤ ሁለት መቶ ብር ይበቃኛል» አልኩት ።

«በጣም ጥሩ፣ ገንዘብሽን መውሰድ ትችያለሽ» ብሎኝ ለገንዘብ ቤት በተዘጋጀው ክፍል ገብቶ ፣ ስለ መሸጥሽ መተማመኛ ብትፈር ሚልን ስለ አለኝ፣ በደረሰኝ ላይ ፈርሜ ገንዘቡን ተቀበልኩ ።

እስከ መውጫው በር ድረስ ሸኘኝና ፥ ሲጨብጠኝ እጇን ይዞ ለትንሽ ጊዜ ቆየ ። በዚሁ ተለያየን ።

ይህንኑ ለዲክ ስነግረው በጭንቀት ተመለከተኝ ። «ምንድነው ያስጨነቀህ ?»

«ሁለት ነገሮች ። አንደኛው ለምን የገዛሽበትን ደረሰኝ አልጠየቀሽም? ሁለተኛ ያን የሚያህል ንብረት እያላቸው ካንቺ ለምን አሮጌ ሰዓት ይገዛሉ ?» አለ ዲክ ግንባሩን ቋጥሮ ።

«ባክህ ተወው ! የለበስኩት ልብስ ውድ በመሆኑ አያስጠረጥረኝም ።»

«ልብሱንስ ሠርቀሽ ብትሆኝ ?»

«ምናልባት ሰዓቱ የቆየ በመሆኑ ፊልገውት ሊሆን ይችላል ።»

«በእውነት ይህ እምነትሽ ነው ?»

«አይደለም !»

«ታዲያ ለምን ያገለገለ ዕቃ ይገዛሉ ?»

«ምናውቄ ?» ስለው ግራ በመጋባት ተመለከተኝ ።

አዲሱን አርቴፊሻል ጸጉሬንና ልብሴን ለብሼ ከዲክ ጋር ቤት ስንዝናና አለባበሴ ጥሩ መሆኑን ገለጸልኝ ። አንድ ቀን ማታ ከቤቴ አዲሱን አለባበስ ለብሼ ልወጣ ስል በአጋጣሚ ከጐረቤት ጋር ልን ገጣጠም ነበር ። ቶሎ ብዬ ወደ ቤቴ ተመልሼ ገባሁ ። ዘበኞቹ ግን ስድስተኛ ፎቅ ያሉ ወንደላጤዎች የቀጠሩዋት ሴተኛ አዳሪ እየመሰልኳቸው ነው መሰለኝ ዝም ይሉኛል ።»

«ለወደፊቱ አዲሱን ቤትሽን ሲታገኝ ይህን ቤት ምን ልታደር ጊው ነው ?» አለኝ ዲክ ።

«አልፎ አልፎ እየመጣሁ እቀመጥበታለሁ ። ሆኖም በዚህ አለ ባበሴ ቀን መምጣት የለብኝም ።»

«ይሄ ችግር አይደለም ፤ ወደ ድሮ ቤትሽ መምጣት ስትፈልጊ መኪናሽ ውስጥ ሆነሽ አርቴፊሻልሽን አወላልቀሽ መምጣት ነው ። ወደ አዲሱ ቤትሽ ስትሔጂ ደግሞ ፥ አርቴፊሻልሽን ማድረግ ነው ። ቀላል አይደለም ?»

«ጥሩ ሐሳብ ነው ። ሌላው ችግር የመኪና ነው የኔ መኪና በቀላሉ የምትታወቅ ናት ።»

«ለምን የኔን ቮልስ ዋገን አትጠቀሚም ?»

«ያንተም ጥሩ አይደለም ፤ ሌላ መኪና መከራየት አለብኝ ።»

ስሜ ቢያ ፍላንደር እንዲሆን ተስማማንና በተቻለ መጠን ያለ ውን የቢያ ታሪክ ለማንም እንደማልናገር ወሰንን ። አስገዳጅ ሁኔታ ከመጣ ግን፡ መናገር ስላለብኝ የቢያን ታሪክ በዚህ መልክ አዘጋጀሁት።

ቤትሪስ ፍላንደር ፡ ኢንዲያና ግዛት ውስጥ ቴሪ ሀውቲ በተባለ ቀበሌ ተወለደች ። እናትና አባትዋ ትልቅ ከሆነች በኋላ ሞተዋል ። አንድ ያገባች እህትና ባሕር ኃይል የሚሠራ ወንድም አላት ። የሁለ ተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቃ በሒሳብ ሙያ የስድስት ወር ኮርስ ተከታትላለች ። በቡና ቤት ተቀጥራ ብዙ ገንዘብ ማግኘት እንደ ጀመ ረች ባል አግብታ ነበር ። ያገባችው ባልዋ ከየሱቁ እንዴት አነስተኛ ዕቃዎችን መስረቅ እንደሚቻል አስተምሯታል ። ሆኖም በልታወቀ ምክንያት ባልዋ ጠፍቷል ። በዚህ ምክንያት ድሮ ወደ ነበረችበት ኑሮ ተመልሳ ቡና ቤቶች ውስጥ በአሻሻጭነት እየተቀጠረች ሠርታለች ። ለአንድ ዓመት ያህል የቡና ቤት ሥራዋን ትታ በየጉራንጉሩ ውስጥ በሚዘጋጅ ፓርቲ መገኘት በመጀመርዋ፡ የተለያየ ሙያ ካላቸው ሌቦች ጋር መወዳጀት ቻለች ። ለሁለት ዓመት ያህል ዳኒ ከሚባል ሰው ጋር አብራ ኑራለች ። የዳኒ ልዩ ችሎታ ጌጣጌጥ ዘረፋ ሲሆን ፡ አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር ዘረፋውን የሚፈጽመው ብቻውን ነው ። ለቢያም የዘረፋውን ዘዴ ያስተማራት ቢሆንም አብረው ዘርፈው አያ ውቁም ። ከዘረፋው በሚያገኙት ገቢ ጥሩ ኑሮ ኖረው ነበር ። አንድ ቀን ዳኒ የጌጣጌጥ ሱቅ ሊዘርፍ ሲሞክር ስለ ተገደለ፡ ቤትሪስ ሸሽታ ያለ ሥራ በኒውዮርክ ማንሐተን ተቀመጠች ። ገንዘብዋ በየቀኑ እያ ለቀ በመሆኑ የሚስማማትን ሥራ በመፈለግ ላይ ትገኛለች ። ይህ ነው እንግዲህ ቢያን በመሆን የሚኖረኝ ታሪክ ። በአዲሱ ስብእናዬም አዲስ ሚና መጫወት ጀመርኩ ።

☆ ☆ ☆

የተከራየሁትን ፎርድ መኪና በምዕራብ ሰማንያ ሰባተኛው መን ገድ ላይ አቁሜ በሮቹን ቆለፍኩና ከዲክ ጋር በእግራችን ወደ ኩሎም በስ ጐዳና ሔድን ። በቢያ ፍላንደርነቴ በለበስኩት በአዲሱ አለባበስ በዚህ መንገድ ካሉት ሴቶች የተሻልኩ ነበርኩ ። ሆኖም ዞር ብሎ ያስተዋለኝ የለም ። በየመንገዱ ዳርቻ ቁጭ ብለው አልኮል የሚጠጡ ሰዎች ሞልተዋል ። ባለቤት የሌላቸው ውሾች ፡ ድመቶች ፡ አካለ ጐደሎ ለማኞች ፡ እብዶች ፡ ሰካራሞች የሐሺሽ ሱሰኞች የተሰባሰቡ በት ሰፈር ነው ። የተሻለ አልቤርጎ ፍለጋ ብዙ ዞርን ፤ እንዴት እን

ደዚህ ባለው ሠፈር ሰው ይኖራል' ተባባልን ። መልሱ ግን አማራጭ ስለሌላቸው ነው ። አንድ የተሻለ ቤት አግኝተን ብንጠይቅ የሴትኛ አዳሪዎች ማደሪያ መሆኑ ተነገረን ። ወደ ከሰዓት በኋላ ላይ በምዕራብ ዘጠና አራተኛው መንገድ አጠገብ አንድ አልቤርጎ አየን ። በአካባቢው ሽንት የሚሸትና ቆሻሻም የሚጣልበት በመሆኑ ከመሸተት አልፎ ዐይን ያቃጥላል ። ወደ አልቤርጎ ማከራያው ክፍል ስንገባ ፣ አስተናጋጁ ከባንኩኒው አጠገብ ተቀምጦ ጋዜጣ እያነበበ ሬዲዮ ያዳምጣል ። ንባቡን በማቋረጡ እየተናደደ ከእግር እስከ ራሳችን ተመልከቶ ፣ «ለአምስት ቀን ሠላሳ ብር ፣ ለወር መቶ ብር» አለን ጮክ ብሎ ።

«የግል መታጠቢያ ቤት አለው ?»

በንቀት እየተመለከተኝ ፣ «እንደዚያ ከሆነ የምትፈልጊው በላምንት ዐርባ ፣ ለወር አንድ መቶ ሠላሳ ብር» አለኝ ።

«ክፍሉን ማየት እንፈልግ ነበር» አለ ዲክ ።

ቁልፉን ከተንጠለጠለበት አንሥቶ በመወርወር ፣ «ቍጥር ሰባት መቶ ሦስት ! ፎጣና አንሶላ በየሳምንቱ ይለወጣል!» አለ አሁንም በሚጮህ ድምፅ ።

ደረጃውን መውጣት ስንጀምር እላይኛው ክፍል አንድ ሴት ትጮኻለች ፤ ሌላኛው ክፍል የሙዚቃ ድምፅ ይሰማል ።

እተባለው ክፍል ደረስን ፤ በጣም ጠባብ ነው ። አንድ መኝታ ክፍል ፣ ቁም ሣጥን ፣ ትንሽ ጠረጴዛና ሁለት ወንበር አለው ። ያልጋው ፍራሽ ቆሻሻ ነው ። የመታጠቢያ ቤቱ በር በተደጋጋሚ ለብዙ ጊዜ ቀለም የተቀባ በመሆኑ አይዘጋም ። የመታጠቢያ ቧንቧዎቹ ያረጁ ፣ የሽንት ቤቱ መቀመጫ የተሰነጣጠቀ ነው ።

«ይቅርብሽ !» አለኝ ዲክ ።
«ሌላ ቦታ እንይ እንዴ ?»

«ጂኒ እንደዚህ ዓይነት ቦታ ከምትኖሪ ጠቅላላው ጉዳይ ቢቀር ይሻላል ።»

«ጂኒ አይደለሁም ቢያ ነኝ ! ከእንግዲህ ማቋረጥ አልችልም ። ደግሞም ከእንደዚህ ዓይነቱ ቦታ ነው እውነተኛ ታሪክ ያዘሉ ገጸ ባሕርያትን የማገኘው » አልኩት ።

«ወደ ሐኪም ቤት ሔደሽ ብትመረመሪ ጥሩ ነው» ብሎኝ ወደ አስተናጋጅ ተመለስን ። እኔ ግን ክፍሉ የተስማማኝ መሆኑን ገለጽኩለት ።

«የአንድ ሳምንት ቅድሚያ ትከፍያለሽ ። ክፍሉ ውስጥ ምግብ ማብሰል ፣ የወንድ ጓደኛ ይዞ መምጣት ፣ ጭፈራና ሐሺሽ ማጨስ አይቻልም» አለኝ ። ይህ ሕጉ ቢሆንም እንደማይሠራበት ዐውቄ አለሁ ።

ሆኖም ሰውየው በአለባበሴ ሊጠረጥረኝ ባለመቻሉ ደስ አለኝ ። የሳምንት ሒሳብ ሰጠሁትና ደረሰኝ ስጠይቀው ፣ አፈጠጠብኝ ። እኔም መልሼ ሳፈጥበት ፣ ደረሰኝ ሰጠኝና ቢያ ፍላንደር በሚል ተመዘገብኩ ።

ከዲክ ጋር ከመለያየታችን በፊት ፊሊትና ሳሙና ገዝቼ መጠጥ ለመጠጣት ባቅራቢያው ወደሚገኘው ቡና ቤት ጐራ አልን ። ከዚያም የገዛሁትን ዕቃ ወደ ተከራየሁት ክፍል አስገባሁት ። ሰዓቱ ወደ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ስለ ነበር ፣ ዲክ ከመሔዱ በፊት እንደ ገና በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ምግብ ቤት ለመሔድ ከክፍል ወጥተን ደረጃውን ስንወርድ ከአንድ ዕድሜው ከሠላሳ አምስት ከማይበልጥ ፣ ደህና አቋም ካለው ጐረቤቴ ከሆነ ሰው ጋር ተገናኘን ። ፈገግታ እያ ሳየን «እለፉ» አለንና ፣ «እንኳን ወደዚህ ሆቴል በደህና መጣችሁ ። ስሜ ጀክ ዳንሆ ይባላል ። የምኖረው በክፍል ሰባት መዶ አምስት ነው ። የምረዳችሁ ነገር ካለ ለመርዳት ዝግጁ ስለሆንኩ ፣ በማንኛውም ሰዓት በሬን አንኳኩ » ሲል ተባባሪነቱን ገለጸልን ።

«እናመሰግናለን ! ራት ለመብላት የምንወጣ ስለሆነ ፣ የትኛው ምግብ ቤት እንደሚሻለን ልትነግረን ትችላለህ ?» አለ ዲክ ።

«ጥሩ ምግብ ቤት እንኳን በአካባቢው የለም ! ካሉት ምግብ ቤቶች የተሻለው ቶም ምግብ ቤት ስለ ሆነ ወደዚያው ብትሔዱ» አለ ፈገግታውን ለኔ እያሳየኝ ።

«አመሰግናለሁ» አልኩት ረጋ ብዬ ።

ደረጃውን እንደ ወረድን ፣ «ችግር የማይፈጥር ጐረቤት ሲገኝ ጥሩ ነው ። ደስተኛና ጥሩ ሰው ይመስላል» አለኝ ዲክ በቅናት በሚ መስል አነጋገር ።

ራታችንን ከበላን በኋላ ፣ ቮድካና ብራንዲ ገዝቼ ያለ ምንም ንግግር ወደ አልቤርጎ ተመለስን ። ስንገባ ፣ ሦስት ወንዶችና ሴቶች ተቀምጠው ይጫወቱት የነበረውን ጨዋታ አቋርጠው እኛን ማየት ጀመሩ ። ዝም ብለን ደረጃውን መውጣት ቀጠልን ። ስንመለከት አሁንም ዝም ብለው ይመለከቱናል ።

«እርግጠኛ ነሽ ፣ እዚህ ቦታ ማደር ትፈልጊያለሽ ?»

«እምን» አልኩት ፤ ውስጡን ግን ስዋሽ ነበር ።

«መልካም ዕድል ። ሐሳብሽን መቀየር ከፈለግሽ ስልክ ደውይ ልኝ» ብሎ ስሞኝ ሲሔድ ዝም ብዬ ቆምኩ ፤

ከተቀመጡት አንድዋ ሴትዮ ፥ «ምነው ጥሎሽ ሔደ?» አለችኝ በመጠጥ አንደበት ። ትከሻየን ነቅንቄ፥ «በዚህ ሥራ ውስጥ ገበያ እን ዳንዴ ይገኛል ወይም ይጠፋል» አልኳት ። ሴቶችም ወንዶችም ተሣ ሣቁ ። ዝም ብዬ ወደ ክፍሌ አመራሁ ፥ ቅድም ዘግቼው የሔድኩት ክፍል ተከፍቷል ። ስገባ ፥ አልጋ አንጣፊዋ አልጋ እያነጠፈች ነበር ። ዞር ብላ አየችኝና ፥ «አዳምጪኝ ቆንጂት! ይህን የገማ ሥፍራ የምቆ ጣጠረው እኔ ብቻዬን ነው ። ረዳት እንዲጨመርልኝ ባለቤቱን ጠየ ቅሁ ። እርሱ ግን ዘጋኝ ። ተከራዮች ይሄ ለምን እንደዚህ ሆነ? ይሄን አርጊ ፥ እያሉ ሲጮሁብኝ ይውላሉ» በማለት ወሬዋን ልትቀጥል ስትል ሁለት ብር አውጥቼ ሰጠሁዋት ። «እግዚአብሔር ይባርክሽ ቆንጂት ፥ የሚያስፈልግሽ ነገር ካለ ጠይቂኝ ። ሳንቺ የተለየ እንክብ ካቤ አደርግልሻለሁ» ብላኝ በዐይንዋ ጠቅሳኝ ከክፍሉ ወጣች ።

በሩን ዘጋሁና ጫማየን አውልቄ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩኝ ። ንጹሕ አየር ለማግኘት ከብዙ ትግል በኋላ፥ መስኮቱን ከፍቼ የገዛሁትን ፊሊት መታጠቢያ ቤትና መኝታ ቤት ረጨሁት ።

እዚህ ሁሉ ጣጣ ውስጥ ገብቼ የምሠራው ለራሴ አስገረ መኝ ። ሁሉንም ነገር ትቼ ወደ ቤቴ ለመሔድ አሰብኩ ። ግን ይህ ሐሳብ አሁን አልነበረም መታሰብ የነበረበት ።

የገዛሁትን መጠጥ ከፍቼ ለመጠጣት ብርጭቆ ብፈልግ አጣሁ ። በሩን ከፈትኩና አንገቴን አውጥቼ ባይ ኮሪደሩ ጭር ያለ ነው ። ወጣ ሁና ቍጥር ሰባት መቶ አምስትን አንኳኳሁ ።

በንዴት «ማነው !» አለ ።

«ክፍል ሰባት መቶ ሦስት የምገኘው አዲሱ ጐረቤትህ ነኝ» አልኩት ። የበሩ ቁልፍ እየተንቃጨለ በሩ ተከፈተ ።

«ታዲያስ ! የሚገርም ነው ፥ አሁን ስለአንቺ ሳስብ ነበር» አለኝ በሩን ይዞ እንደ ቆመ ።

«ስማ ! መጠጥ መጠጣት ፈልጌ ብርጭቆ አጣሁ ፥ አንተጋ ይኖ ራል ብየ ነው ። አለህ ?»

በፈገግታ እየተመለከተኝ ፥ «አለኝ ። ባለቤትሽ እንድትጠጪ ይፈቅድልሻል ?» ሲል ጠየቀኝ ።

«ባለቤቴ አይደለም» አልኩት ።

«ፍቅረኛሽ ነው ?»

«እንዲሁ ጓደኛዬ ነው ፣ አሁን ከኔ ጋር የለም ። ብርጭቆ አለህ?»

ጭንቀቱ ወዲያው ለቀቀውና ፣ «ክፍሉን ለብቻሽ ነዋ የያዝሽው? በእውነት አላወቅሁም ነበር ። ግቢ! ብርጭቆ አለኝ አጥቤ ልስጥሽ» አለኝ ።

«አትቸገር እኔ አጥበዋለሁ ።»
«ምንም ችግር የለም ፣ ግቢ» አለኝ ፈገግታ እያሳየኝ ።
በሩን በግማሽ ከፈት አድርጌ በመተው እያመናታሁ ገባሁ ።

ዞር ብሎም ሳያየኝ በቀጥታ ወደ መታጠቢያ ክፍሉ ገብቶ ብር ጭቆዎችን ማጠብ ጀመረ ። ክፍሉ ከኔ ክፍል የበለጠ ንጹሕና ትንሽ ቴሌቪዥንና ማቀዝቀዣ ያለው ነው ። ብርጭቆውን እየወለወለ ከመ ታጠቢያ ክፍሉ ሲወጣ ፣ «በረዶስ ያስፈልግሻል ?» አለኝ ።

«አዎ ያስፈልገኛል ።»
«እንቺ የኔን ስም ታውቂያለሽ፤እኔ ግን ያንችን ስም አላውቅም»
«ቤትሪስ ፍላንደር እባላለሁ ፣ ስታሳጥረው ቢያ !» አልኩት ።

ወደ ማቀዝቀዣው ፈጌዶ በረዶ ሲያወጣ ጐንበስ ሲል በደንብ ተመለከትኩት ። ብዙም ቆንጆ የሚባል ሳይሆን ደህና ነው ። ጠን ካራ እንደሆነ ያስታውቃል ። አለባበሱም የሚያምር ነው ። የድም ፁም አወጣጥ እንደ ሙዚቃ ደስ የሚል ነበረ ።

በረዶውን ብርጭቆ ውስጥ እየሞላ ፣«ከየት ነው የመጣሽው?» አለኝ ።

«ከእዚህ፣ ከእዚያም፣ ከማንኛውም ቦታ» አልኩት ።
«ያው እንደ እኔው ነሽ !» አለኝ ።
«ሥራህ ምንድነው ?»

«ይህንንም ያንንም» አለኝና፣ «በረዶውና ብርጭቆውን አዘጋጅ ቼልሻለሁ» በማለት ተመለከተኝ ።

«ቮድካና ብራንዲ አለኝ መጠጣት ትፈልጋለህ ?»
«እኔስ አትጠይቂኝ ይሆናል እያልኩ ሳስብ ነበር ። ምን አልሽ?»
«ቮድካ በብዛት አለኝ» አልኩት ።
«ይስማማኛል ጥሩ ነው ።»

«ያንተ ከፍል ከኔ የተሻለ ምቹ ስለ ሆነ መጠጡን እዚህ አም

ጥቼ እንጠጣ» ብየው መጠጡን ይገፎ ተመለስኩ ።

«ኒውዮርክ የገባሽው ዛሬ ነው ?»
«ትንሽ ቀናት ቆይቻለሁ»
«ካንቺ ጋር የነበረው ሰውዬ ምንድን ነው ?»
ፈገግ በማለት ፡ «እዚህ ለመምጣት የረዳኝ የጓደኛዬ ጓደኛ ነው ።»
«ከኒውዮርክ በፊት የት ነበርሽ ?»
«ቺካጐ ነበርኩ ። አንተስ ?»
«እኔ ሚያሚ ነበርኩ ። ዕድሌ አበረረኝና ወደዚህ አመጣኝ»
«አሁን ምን እየሠራህ ነው ?»

«ዕድሌን እየተጠባበቅሁ ነው ። ምናልባት አንቺ ዕድሌን ታቃ ኚልኝ ይሆናል ።»

«መጠጡን ቅዳልኝና ስለ ዕድልህ እንጠጣ ።»

ዝም ብለን መጠጣት ጀመርን ። ትኩር ብሎ ሲመለከተኝ ቆየና ፤ «ለመሳደብ አይደለም ፤ ቡና ቤት ትሠሪ ነበር ?» ሲል ጠየቀኝ ።

«ስድብ አይደለም ። ከሁለት ዓመት በፊት እሠራ ነበር ።»
«ፍቅር ይዞሽ ሥራሽን ተውሽው ?» አለኝ በሽሙጥ ።

«ልክ ነህ ።»

«በመጨረሻም ተለያያችሁ ?»

«አዎን! ዳግመኛ አንገናኝም ሞቷል» አልኩት ።
«አዝናለሁ»

ትከሻየን በመነቅነቅ ፡ «ሞት አዲስ ነገር አይደለም የተለመደ ነው » አልኩት ።

«ኒውዮርክ የመጣሽው የድሮ ሥራሽን ለመጀመር ነው ?»
«ሁለተኛ አልመለስበትም ። ለተወሰነ ጊዜ ዝም ብዬ እቀመጥና ዕድሌን እሞክራለሁ ።»

«እም !» አለ አፉን በመግጠም ። «ምናልባት አብረን ዕድላ ችንን እንሞክራለን ።»

«እንዴት ?»
«አንዳንድ ጊዜ ብቸኛ ከመሆን ሁለት መሆን የተሻለ ዕድል ይኖረዋል ።»

«ልክ ነው ። በአእምሮህ ያሰብከው አለ ?»

«እስካሁን ምንም የለም ፣ ለወደፊቱ አስብበታለሁ ማለቴ ነው ።»

«ምናልባት» አልኩት በማሰብ ። «ለሚሰጥህ ሥራ ምን ያህል ዝግጁ ነህ ?»

ቢገረምም ፣ መገረሙን ሳያሳየኝ ፣ «እንደ ሥራው ዓይነት ዝግጁ ነኝ » አለኝ ።

ስለ ሕገ ወጥ ድርጊት እንደምንነጋገር ሁለታችንም ተግባብ ተናል ።

«አንድ ጉዳይ አለኝ ፣ ግን በሐሳብ ደረጃ ነው ። ሥራ ላይ ሊውል ይችላል ። ስለዚህ እርዳታ ያስፈልገኛል ።»

ለብዙ ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና ፣ «ዕርዳታ . . . ዕርዳታ ትፈልጊያ ለሽ ? የጉልበት እርዳታ ማለትሽ ነው ?»

በአዎንታ ራሴን ቀና አደረኩ ።

«በደንብ ስትዘጋጂ ትነግሪኛለሽ ።»

«እሺ» አልኩና ፤ «ለበረዶው ብከፍልህ ይከፋሃል ?» አልኩት ።

«አይከፋኝም ። ስለ ክፍያው ግን አመሰግናለሁ!»

ከጃክ ጋር መጫወት ከባድ አልነበረም ። ስለ አለፈው ሕይወቱም መነጋገር ይቻል ነበር ፤ ግን ተውኩት ።

«ጃክ ! አግብተሃል»

«አዎ ! አሁንም አለኝ ። ቁማር ሳይሳካልኝ ሲቀር ጊዜ ጥላኝ ሔደች»

«ከመጋባታችሁ በፊት ቁማር እንደምትጫወት ታውቅ ነበር»?

«ነግሬአታለሁ ። ልደብቃት የሞከርኩበት ጊዜ የለም ። አስተ ወዋለሁ ብላ የምታስብ ይመስለኝ ነበረ ። የአንቺስ የሞተው ፣ የዱሮ ፍቅረኛሽ ምን ይሠራ ነበር ?»

ትንሽ አሰብኩና ፣ ከዚያም ልንገረውና ከቀፈፈው አሁኑኑ ልወቅ በማለት ፣ «በዘረፋ የተሠማራ ነበር አልኩት . .» አልገረመውም ።

«በምን ዓይነት ዘረፋ ?»

«በጌጣጌጥ ነው ። ብዙውን ጊዜ ለብቻው ነው የሚዘርፈው ፣ ደህና ይሳካለት ነበር ። መጨረሻው ግን አላማረም ?»

«አዎ ! ዘረፋ ሁል ጊዜ መጨረሻው አያምርም ። እንዴት ሊሞት ቻለ ?»

«የጌጣጌጡ ባለቤት ገደለው።»

«መሣሪያ አልያዘም ነበር ?»

«መያዝ ይዟል ። ግን ሰውየው ከሱ በላይ ፈጣን ስለ ነበረ ቀደመው»

«አብረሽ ነበርሽ ?»

«አልነበርኩም ። ሆቴል ሆኜ ሻንጣየንና የአውሮፕላን ትኬቴን እዘጋጅቼ እጠብቀው ነበር ። ሲዘገይ ችግር እንዳለ ገባኝ ። እንደ ዕቅዳችን ተሳፍሬ መጣሁ ። ጃክ ! እርግጠኛ ነኝ ይሄን ሁሉ መናገሬስሕተት ነው ። አምኛ ነው አደራ !»

«ያልሽውን ሁሉ አልሰማሁም እርሺው ።»

«እሺ እንርሳው !»

«መጠጥ ልጨምርልሽ ?»

«እሺ» ብየው ፥ ለሁለታችንም ቀድዶ መጠጣት ጀመርን ።

«ፍቅረኛሽን ትወጂው ነበር ?» አለኝ እጄን ይዞ ።

«ሰውየው ደህና ነበር ፥ ግን ማፍቀር ምንድነው ?»

«እኔና አንች ተመሳሳይ ባሕሪ አለን ። አብረን እንደር?»

«እሺ» ብየው ወደ መኝታ ክፍሉ ከነብርጭቆዬ ገብቼ አልጋው ላይ ቁጭ አልኩ ። ትራሱን ደገፍ ስል ሽጉጥ እንዳለ ታወቀኝ ። የምገምተው ነበር ።

እሱድ ጧት ተነሥቼ በቀዝቃዛ ውኃ ሰውነቴን ታጥቤ ፥ ብርጭቆና አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ገዛዛሁና ተመለስኩ ። የሚያስፈልገኝን ዕቃ ሁሉ ከመደበኛው ቤቴ ማምጣት እችል ነበር ። ግን ጂኒነቴ ሊያሳውቅብኝ ስለሚችል ተውኩት ። በተከራየሁት ፎርድ መኪና ወንበር ሥር መታወቂያየን ፥ መንጃ ፈቃዴን የደበቅሁት ስለሆነ ማንም ሊያገኘው አይችልም ። አልጋ አንጣፊዋም በሌለሁበት ክፍሌ ውስጥ ገብታ ብትፈትሽ እንኳ ስለ ጂኒነቴ ምንም የምታውቀው አይኖርም ።

የተከራየሁትን መኪና እየነዳሁ ሞር ወደ አለ ቦታ ሔጄ መኪና ውስጥ ልብሴን አወላልቄ ቀየርሁና ወደ መደበኛ ቤቴ ሔድኩ ። እቤቴ

እንደ ደረስኩ እንደ ገና በሙቅ ውኃ ታጥቤ ጥሩ ቁርስ አዘጋጅቼ በላሁ ።

ለጓደኛዬ ላውራ ስልክ ደውዬ ስለ ጤናዋ ትንሽ ከተነጋገርን በኋላ፣ «ሰተወሰኑ ሳምንታት እንዳትፈልጊኝ» አልኳት ።

«ለምን ነው» አለችኝ ።

«አዲስ መጽሐፍ ለመጻፍ ጥናት ላይ ስለሆንኩኝ አንዳንድ ቦታ ዎችን እጐበኛለሁ ። ስመለስ እደውልልሻለሁ» ብዬ ተሰናብቼአት ስልኩን ዘጋሁ ።

በቅርብ ለማውቃቸው የቅርብ ጓደኞቼም ስልክ ደውዬ ለጥናት ወደ ሌላ ቦታ እንደም ሔድ ነገርኳቸው ።

ለዲክም ፣ አልፎ አልፎ ወደ ድሮው ቤት ፖስታ ለመሰብሰብና የቤት ኪራይ ሰመክፈል እንደምመላለስ ነገርኩት ። ይህ እውነት ቢሆንም ፣ ዋናው ወደዚያ ቤት የምመጣውም ከዲክ ደብቄ የየቀኑን ድርጊቶች በምመዘግብበት ማስታወሻዬ ላይ ለማስፈር ነው ።

በማስታወሻዬ ላይ በየጊዜው የገጠመኝን በአዲሱ ሰፈር ከጃክ ጋር የተነጋገርናቸውን ሁሉ አንድ ሳላስቀር ጻፍኩት ። በዚህ ጽሑፍ ላይ ጃክን 'ጥቁር ጃክ' ብዬ መዘገብኩት ። ይህም የሰውየውን ጉል በተኝነትና አደገኝነት ለመግለጽ ነው ።

ጽሑፌን ለሦስት ሰዓት ያህል ከጻፍኩ በኋላ፣ በመሳቢያ ውስጥ አስገብቼ ቆለፍኩና ለናቴ ደብዳቤ ጽፌ ወደ ቢያ ለመቀየር የሚያስ ፈልጉኝን ልብሶች ይዤ ከመኖሪያ ቤቱ ወጣሁ ።

ራሴን ቶሎ ወደ ጀኒነት ከመለወጥ ይልቅ፣ ወደ ቢያነት ለመ ለወጥ የማደርገው ጥረት አስቸጋሪ ሆኖ አገኘሁት ። መኪናየ ውስጥ ሆኜ ቢያ የሚያስመስለኝን ጸጉርና ልብስ ስለብስና የከንፈር ቀለም ስቀባባ ከኔ አለፍ ብሎ በቆመ መኪና ውስጥ ያሉ ወጣቶች ተገርመው ያዩኛል ። ደንታም አልሰጠኝ ። ቶሎ ለዋወጥኩና ወደ አዲሱ ኑሮዬ ተመለስኩ ።

እክፍሉ ገብቼ ትንሽ እንደ ቆየሁ በሩ ተንኳኳ ። ከፈትኩት ፣ ጃክ ነበር ። «አሁን ብርጭቆ ስለ ገዛሁ አልረብሽህም » አልኩት ።

«እርቦኛል ፣ ለምን ወጥተን አንበላም ?» አለኝ ።

ከአልቤርጎው ወጥተን ትንሽ ከሔድን በኋላ፣ ፓርቶሪካን ተው ላጆች ምግብ ቤት ገባን ። ከውጭ የሚመጣውን ሰው በደንብ ልናይ ከምንችልበት ቦታ ቁጭ አልንና መጠጥ አዘዝን ። አስተናጋጅዋ

ከመሐዱዋ በፊት እጅዋን ያዝ አድርጎ «የጐድን ጥብስ ብንበላስ ?» አለኝ ። ተስማማሁ ። ሁለት አድርጊው ብሎአት ልታመጣልን ሐደች ።

ሆቴሉን በዐይኔ ቃኘሁት ። ከምግብ ቤት ይልቅ መጠጥ ቤት ቢሉት ይሻላል ። ግማሹ ይጠጣል ፥ ያጨሳል ፥ ግማሹ ይበላል ። አብዛኛው በቴሌቪዥን የእግር ኳስ ጨዋታ ይመለከታል ። ጫጫታው ከመጠን በላይ ነው ።

«የምትጠብቀው ሰው አለህ መሰለኝ ?» አልኩት ።
«ጐበዝ! እንዴት ዐወቅሽ? አዎ የምጠብቀው ሰው አለኝ» አለ ።
«እኔ ባለሁበት ማነጋገር ካልፈለግህ መሐድ እችላለሁ ።»

«አይሆንም ። ብዙም አያቆየን፥ ሰሁለት ደቂቃ ብቻ ነው የምን ነጋገረው ፤ አንቺ ዝም ብለሽ ባለሽበት ቆይ ።»

'ለምሳ እንሒድ ያለኝ ለቀጠሮው አስፈላጊ ሆኝ ይሆን ወይስ ሊጠቀምብኝ ነው' እያልኩ አብሰለሰል ጀመር ። ትኩር ብዬ ባየው ዐይኑን ወደ መግቢያው በር ተክሎ የሚገባውን ሰው ይመለከታል ። ጥሩ ወሬ የሚጠብቅ አይመስልም ፤ ጭንቀት ይታይበታል ።

ከመቀመጫው ተነሥቶ ወደ በሩ ሔደና ከአንድ አጭር ሰው ጋር ተገናኘ ። ሰውዬው በፊገግታ የተሞላ ነው ። ግን የሽሙጥ እንጂ የደስታ አይደለም ። ለትንሽ ደቂቃ ራሳቸውን ገጥመው ሲንሾካሾኩ ቆዩና ተለያዩ ።

ተመልሶ መጥቶ ጥብሳችን ቀርቦልን መመገብ ስንጀምር ፥ «ያ ጓደኛህ ሁል ጊዜ ፊገግታ የማይለየው ደስተኛ ይመስላል ?» አልኩት ።

«አዎ ስዎችም እንደዛ ይሉታል ።»
«የቅርብ ጓደኛህ ነው ?»
«ይህን ያህል አይደለም ።»
«ሥራው ምንድን ነው ?»

ዝም ብሎ አጥንቱን ጋጋጠና ሲጨርስ እጁን በወረቀት ጠራርጎ፥ «እስማይሊንግ ነው፣ . . . እስማይሊ ሌባ ነው » አለኝ ።

«ዕዳ አለብህ እንዴ ?» ብየ ጠየቅሁት በግምት ።
ራሱን በአዎንታ በመነቅነቅ ፥ «ወደ አምስት ሺ ብር» አለኝ ።
«ካልመለስክ ምን ይመጣብሃል ?»
«በቀላሉ ሁለቱንም ጉልበቶቼን ያደቃቸዋል»
«ከከፋስ ?»

«ከምድረ ገጽ መጥፋት ፥ መሞት ማለት ነው ። እንደዚህ ዓይ ነት ስምምነት ሞክረሽ ታውቂያለሽ ?»

«አላውቅም» አልኩት ራሴን በመነቅነቅ ።

«አትጨነቂ ስቀልድ ነው ። በቀላሉ ከዚህ ችግር እወጣለሁ ።»

«ገዛም ብለህ መጥፋት አትችልም ?»

«አልችልም ። በቀላሉ ያገኙኛል ። እንደነሱ አባባል መሸሽ ይቻላል ፤ መደበቅ ግን አይቻልም ።»

«ለአምስት ሺ ብር ብለው ይህን ያደርጋሉ ?»

«ዋናው ብሩ አይደለም ። ዛሬ ለትንሹ ጉዳይ ገዛም ካሉ በዚህ ተለምዶ ነገ ከፍተኛ ብር እንዲወሰድባቸው ስለማይፈልጉ ለትንሹ ቶሎ መፍትሔ ይፈልጋሉ ። አንድ ሥራ አለኝ ስትይ ነበር ። እንዴት ነው ?»

የምግጠውን አጥንት ቁጭ አደረኩት ። ትክ ብሎ ይመለከተኛል ፤ የመጓጓት ስሜት አይታይበትም ።

«አዎ ሥራ አለኝ ። ጥሩ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ ።»

«ምን ያህል የሚያስገኝ ይሆናል ?»

«በጣም ብዙ ! ያንተ አምስት ሺ ብርማ ምን አላት ? ይኸ የሚ ዛቅበት ነው »

«አሁን በምን ደረጃ ላይ እንዳለሽ ንገሪኝ ?»

«ከጓደኛዬ ጋር ተነጋግረን ስን ስማማበት እነግርህ ይሆናል።»

«ከዚያ ከቀጫጫ ጋር ? ለምን እሱን መረጥሽ ?»

«ዕዳ አለብኝ» አልኩት በሚገባው አነጋገር ።

«ጥሩ ! ተነጋገሩበትና እንገናኝ ።»

«ጥብስህን ብላና ጨርስ ። መጠጥ እኔ ልጋብዝህ ።»

«እሺ !»

«ዛሬ ከኔ ጋር አታድርም» አልኩት ዐይኑን እያየሁ ።

ትከሻውን ነቀነቀና ፥ «ቢያ አለቃዬ ስለ ሆንሽ እንደ ፈለግሽ » አለኝ ።

እኔም በአለቃነቴ አመንኩበት ።

የደራሲ ሥራ ብቸኛ ያደርጋል ። ውሎውና ሐሳቡ ከባዶ ወረቀትና ከጽሕፈት መኪና ጋር ብቻ ይሆናል ። ለቲያትርና ለሲኒማ የሚጻፍ ድርሰት ትንሽ ከመሆኑም በላይ በቡድን የሚሠራ ነው ። የደራሲ ሥራና የጣሣሚ ሥራ ግን የተለየ ነው ። ለተወሰኑ ዓመታት በዚህ ሥራ የሚቆይ ሰው ስለ ጽሑፍ ብቻ የሚያስብ በመሆኑ ከዓለም የተገለለ ነው ። ለሱ ዓለሙ መጻፍ ብቻ ይሆናል ።

አሁን ግን ፣ ራሴን በሁለት ሕይወት የማየው በመሆኑ ደስተኛ ነኝ ።

እንደ ጂኒ ደራሲ ነኝ ፣ እንደ ቢያ ደግሞ መኻል ከተማውን ለመዝረፍ ላይ ታች እላለሁ ። እንዲህ በመሆኑም የእንቅስቃሴዬን እያንዳንዱን ደቂቃ ወደድኩት ።

አንድ ቀን ሰኞ ለመዝረፍ የተዘጋጀነውን ሱቅ እንደ ገና አጠናሁት ። የሠራተኞች መግቢያና መውጫ ሰዓት ከበፊቱ የተለየ አልነበረም ።

ዲክም በአካባቢው በመዘዋወር የፖሊስ መኪና ወይም በእግሩ ወዲያና ወዲህ የሚል የፖሊስ ሮንድ በአካባቢው አለመኖሩን አረጋገጠ ።

ለመጨረሻ ጊዜ፡ በሱቁ ሚስተር ጄርቪስ ከእጁ ጋር በሰንሰለት የተያያዘ ቦርሳ የያዘ ወጣት ጋር ተጨባብጦ ሲለያይ አየሁት ። ወጣቱን ትንሽ እንደ ተከተልኩት ጥቁር ማርቼዲስ ውስጥ የጓላ በር ተከፍቶለት ገብቶ መንገዱን ቀጠለ ። እኔም ክትትሌን አቋርጬ ወደ መደበኛ ቤቴ ሐጄ የዕለቱን እንቅስቃሴ በማስታወሻዬ ላይ ካሰፈርኩ በኋላ ሰውነቴን ተጣጥቤ ወደ ከተማ ወጣሁ ። ጉዞዬ ጄርቪስና ያ ቁጥር ሦስት የምለው ሰውዬ ወደሚለያዩበት ቦታ ነበር ። ሁለቱም ፖስታውን ባንክ አስገብተው ቆመው ሲያወሩ ልጠጋቸው ብዬ የመኪናውን መንገድ ማቋረጥ ስጀምር ፣ የመኪና ጥሩንባና የጮማ መንሸራተት ጩኸት ተደበላለቀ ። ባለመኪናዎቹም አንገታቸውን በመስኮት በማውጣት ስድብ አወረዱብኝ ። ዝም ብዬ አቋርጬ ስሔድ ፣ ጄርቪስና ሰውየው ተለያይተው ጄርቪስ ወደ እኔ ሲመጣ ተመለከትኩት ። እኔም አንገቴን አቀርቅሬ ወደሱ ሔድኩኝ ።

ፀወይዘሪት ጂኒ ! እንደምን አለሽ? ምን ዐይነት ጥሩ አጋጣሚ ነው አለኝ ።

ግራ በመጋባት ዐይነት፣ «እንደምን አለህ ሚስተር ጄርቪስ ። መገናኘታችን ደስ ብሎኛል ። ሥራ ጨርሰህ ነው ?» አልኩት ።

«አዎ ! እንደ ቸኮልሽ ልዩ ፕሮግራም ያለሽ ትመስያለሽ? ወዴት እየሔድሽ ነው ?»

«ጥሩ ምሽት ለማሳለፍ በመተማመን ፣ ወደ አንድ ቦታ እየሔድኩ ነው ።»

የምንነጋገረው እግረኛ የሚበዛበትን መንገድ ዘግተን ስለ ነበረ ጄርቪስ እጄን ይዞ ወደ ዳር አወጣኝ ።

«ባጋጣሚ ስለ አገኘሁሽ እንዴት ደስ ብሎኛል መሰለሽ ። ብዙ ጊዜ የት አገኛታለሁ እያልኩ እሰብ ነበር ።»

የአነጋገሩ ዘይቤ ጣሊያናዊ ሲያስመስለው ፣ ጠንካራ ሰውነትና ቀጥ ያለ አቋም አለው ። ቁመቱ አጠር ያለ ነው ። እንደዚህ ጠጋ ብዬ ሳስተውለው የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው ። ዕድሜውም ወደ ዐርባ አምስት ገደማ እንደሚደርስ ገመትኩ ። ከዐሥር ዓመት በፊት ሴት አሳዳጅ ሳይሆን አይቀርም ። የደስ ደስ ያለው የወንድ ፊት ነው ያለው ። ዐይኖቹ ትናንሽና ሰማያዊ ሲሆኑ ትኩር ብሎ ሲመለከት ያስጨንቃሉ ።

«ጊዜ ካለሽ አንድ ቦታ ቁጭ ብለን ትንሽ ብናወራ ?»

ግራ እንደ ተጋባ ሰው ፣ «ምን አልክ ?» አልኩትና ፣ «ይቻላል የቀጠሮየ ሰዓት ገና ነው ። ለትንሽ ጊዜ ያህል መጫወት እንችላለን» ብዬው ወደ ቡና ቤት ሔድን ።

ቡና ቤት ቁጭ ብለን መጠጥ አዘዝን ። ከደንበኛ ጠጪ ጋር መሆኔን ያወቅሁት በኋላ ነው ። እኔ አንዱን መለኪያ ብራንዲ ሳልጨርስ ፣ እሱ ሦስቱን መለኪያ ማርቲኒ ጨልጦታል ።

ጨዋታ ዐዋቂና አሥቂኝ ነው ። ሲጋራ ባወጣሁ ቁጥር ለመለኮስ ያለው ፍጥነት ያስደንቃል ።

ስለ አለባበሴ ፣ ጥሩነት ስለ ሱቁ ደንበኞች ሲያወራልኝ ቆየ ። ሆነ ብዬ ስለ ሥራው ብዙ እንዲያወራልኝ ገፋፋሁት ፤ ምንም ሳያስብና ሳይጨነቅ የአልማዝና የዕንቁ ዋጋ እንዴት እንደናረ ፣ ዋጋቸው እንዴት እንደሚተመን ፣ የሚቆረጡት የት እንደሆነና ፣ ሱቃቸውም በዓመት ምን ያህል ትርፍ እንደሚያገኝ ነገረኝ ።

እኔም «የተወሰኑ አልማዞች አሉኝ ፣ ለመሸጥ እንዴት ነው የምችለው፣ ዋጋ እንዲጨምሩ ቢቆረጡ ይሻል ይሆን ?» ስል ሆነ ብዬ ጠየቅኩት ።

«የግድ አስፈላጊ አይደለም ። የአልማዙ ታሪካዊነት ዋጋውን ከፍ ሊያደርገው ይችላል ፣ ወይም ዐይነቱ ሊያስወድደው ይችላል ። ሆኖም መቆራረጡ እንደልብ ይዞ የትም ለመሔድ ያስችላል ፤ ለመሸጥም ያመቻል ። ሌላው በአሁኑ ጊዜ የተለመደው ከፍተኛ ዋጋ ያለውን አልማዝ እንደ ትንሽ ነገር በተራ ሐብል ላይ ማንጠልጠል ሲሆን፣ ለጥንቃቄ ጥሩ ነው ።»

ጥቂት ዝም ዝም ከተባባልን በኋላ ፣

«እራት አብረሽኝ ልትበይ ትችያለሽ ?» አለኝ ።

በድንገት በመጠየቁ ደንግጬ ፣ «አይ አይሆንም፣ ቀጠሮ አለኝ» አልኩት ።

«ዐውቃለሁ ! ለሌላ ጊዜ ብጠይቅሽስ ?» አለኝና ትኩር ብሎ ተመለከተኝ ።

«ትችላለህ ደውልልኝ ፤ የስልክ ቁጥሬም በሰጠኋችሁ ደረሰኝ ላይ የተመዘገበ ነው » አልኩት ፈገግ ብዬ ።

ለስለስ ብሎ ፣ «ዐውቃለሁ» አለኝ ። ታክሲም ላሳፍርሽ ብሎኝ ነበር ፤ አስፈላጊ እንዳልሆነ ነግሬው ተጨባብጠን ወደ በሩ አመራሁ ። ከመውጣቴ በፊት ዞር ብዬ ስመለከተው ያየኛል ። እጁን በማወዛወዝ «ደህና አምሺ» አለኝ ። አጸፋውን መልሼ ወደ ቤቴ አመራሁ ።

ዲክና ጃክን አስተዋወቅኋቸው

ፋንጮ ቡና ቤት በጓሮ በኩል እኔ ፣ ዲክና ጃክ መናፈሻ ውስጥ ቁጭ ብለን እንወያይ ነበር ። ሁለቱም ቅናት ስለያዛቸው እኔን ለመብላት ያፈጠጡ ውሾች መስለዋል ።

«ከየት ነበር መጣሁ ያልከው ?» አለና ጃክ ዲክን ጠየቀው ።

«የትም ነበርኩ አላልኩም ። አስፈላጊ ነው እንዴ? ይህን ያህል ለማወቅ ካስፈለገህ ግን ፣ ካንሳስ ኩተማ ነበርኩ» አለው ዲክ ፊቱ እንደ ተቋጠረ ።

«ምን ትሠራ ነበር ?»

«ማንም የሚሠራውን ሥራ እሠራ ነበር» አለ ዲክ ። መልሱ ጃክን ያረካው አይመስልም ።

«ከንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር መሥራት አልፈልግም ። ከጀርባዬ የምተማመንባቸውና ጠንካራ ሰዎችን እፈልጋለሁ » አለ ጃክ ።

«ይሀን በማለትህ በጣም ደስ ይለኛል ። ለዕቅዳችን መሳካት ብቃት ያለህ አይመስለኝም ቢያ እንሒድ» አለ ዲክ በማፌዝ ።

«ድንጋይ ራሶች ! ዝም በሉና ቁጭ በሉ ! ለዚህ ጉዳይ ሁለ ታችሁ አብራችሁ እንድትሠሩና እንድትስማሙ ለማድረግ ጊዜ የለ ኝም ። ከፊለጋችሁ የማዛችሁን ሥሩ ፣ አለዛ ተዉት ። የምትፈልጉ ወይም የማትፈልጉ መሆኑን አሁኑኑ ንገሩኝ፣ በአስቸኳይ ሌላ ሰው እንድፈልግ» አልኩ ። ሁለቱም ለጥቂት ጊዜ ተያዩና ፣

ዲክ ፡ «እኔ አብሬሽ ለመሥራት እስማማለሁ» አለ ።

ጃክም «ሥራን በሚመለከት ብቻ ከሆነ እኔም እስማማለሁ» አለ።

«ጥሩ እንግዲህ ለዚህ ሥራ ኃላፊው እኔ ነኝ ። ግን ሁላችንም አብረን እንሠራለን ። ውድቀት ከመጣ ለሁላችንም ነው ። ስለዚህ ተግባብተን በቡድን መሥራት አለብን» አልኩና ስለ ብንደንበርግና ልጅቱ ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ ማወቅ የሚኖርበትን ሁሉ ለጃክ ነገርኩት።

በተመስጦ እያዳመጠኝ አልፎ አልፎ በመነሳሳ ፡ ስለ ፖሊሶች ፡ ስለ ማስጠንቀቂያ የኤሌክትሪክ መሣሪያዎችና ስለ ተጠመዱ ቴሌ ቪዥኖች ጠየቀኝ ። ለጥያቄዎቹ ሁሉ ደረጃ በደረጃ መልስ ሰጠሁ ። በዕቅዱ በጣም የተገረመበት ይሁን እንጂ ፡ መደነቁን በቃላት ሊገል ጽልኝ አልፈለገም ።

«መቼ ተግባራዊ ሊሆን ታስቧል ?» ሲል ጥያቄ አነሣ ።

የገና በዓል ከመድረሱ ሁለት ሳምንት በፊት ፡ ሱቁ ተከፍቶ ገበያተኞች መግባት ከመጀመራቸው በፊት ፡ በጥዋት መፈጸም አለ በት» አለ ዲክ ።

«ሰባት ሠራተኞች እንዳሉ ገልጸችሁልኛል ። ሦስታችን ብቻ ይሀን ለመፈጸም በጣም ያስቸግረናል ። የግዴታ ሌሎች ሰዎች መጨ መር አለብን ።»

«ልክ ነህ ፤ ሁለት ወይም ሦስት ሰው መቅጠር ይኖርብናል » አልኩት ።

«በገንዘብ ሲገመት ምን ያህል ንብረት አለበት ?»

«ከሚሊዮን በላይ ይሆናል ። አሁን ይሄ አያሳስበንም ። እንዴት እንደ ምናደርግ ማቀድና የምንቀጥራቸውን ሰዎች መፈለግ ነው ።»

«በከፍያው ላይስ ምን አስበሻል ?»

«ለምንቀጥራቸው ሰዎች ደህና እንከፍላቸዋለን ። ከዛ በኋላ የተረፈውን ዐርባ ኪሎዉ ለኔ፡ቀሪው ሠላሳ ሠላሳ ከሎዉ ለሁለታችሁ።»

«እሺ ! አሁን ከኔ ይሆናል አይሆንም የሚል መልስ የምትጠብቁ አይመስለኝም ።»

«ለምን? ከዚህ የበለጠ ምን ጥሩ ዕድል ይገኛል» አለ ዲክ ።

«ለማነው ጥሩ የሚሆነው? አንገቴን ዝም ብዬ ገመድ ውስጥ አልከትም ። መጀመሪያ ቦታውን ልየው ፡ በዚህ ዓይነት ሥራ ውስጥ የሚሰማማኝንና የማይስማማኝን የማውቀው እኔ ነኝ ።»

«ለምሳሌ?» አልኩት ።

«ለምሳሌ ጥዋት ደንበኞች የሚበዙ መሆኑን ፡ ፖሊሶች ይዘዋወሩ እንደ ሆነ ፤ እናንተ የማታውቁት የማስጠንቀቂያ ኤሌክትሪክ መሣሪያ ኖሮ በሩን በኤሌክትሪክ ሊዘጉ ወይም ላይዘጉ የሚችሉ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አለብኝ ። ለተወሰነ ቀን ልየውና ከዚያ በኋላ አቋሜን እገልጽላችኋለሁ ።»

እኔና ዲክ ተያየንና ፡ «በቅርብ ቀን ውስጥ የምትወስን ከሆነ እስማማለሁ ። ሥራውን ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆንክ ቶሎ ከውሳኔ ላይ ድረስ ። እንደ እኔ ከሆነ በቀላሉ የሚፈጸም ነው » ስለው ፡

ጃክ በመገረም ተመልከቶኝ ፡ «እንደምትይው ጥሩ ሆኖ ካገኘሁት እንቀጥላለን ። ሱቁን አይቶ ለመወሰን ከሦስት ቀን በላይ አይፈጅብኝም ። ለሥራችን ተባባሪ የሚሆኑ ጠንካራ ሰዎችንም ስለማውቅ ብቁ የሆኑትን መምረጥ እችላለሁ » አለኝ ።

«ጥሩ በሦስት ቀን የምትወስን ከሆነ ዐርብ ዕለት ማታ ለምን እኔ ክፍል ተገናኝተን አንነጋገርም ?»

«ካንች ክፍል የኔ ክፍል የተሻለና ለሦስታችን መቀመጫ የሚሆን ወንበር ስለ አለ የኔ ይሻላል ። ለመጠጣችንም በረዶ እንደ ልብ ማቅረብ እችላለሁ ።»

የሌቦች አለቃ መሆን ብዙ ገንዘብ ያስወጣል ! የጠጡትን መጠጥ ሒሳብ እኔው ከፍየ ወጣን ።

ዲክን ታክሲ ለማሳፈር ስንሸኘው ፡ «ለመሆኑ የት ሠፈር ነው የምትኖረው ?» ብሎ ጃክ ጠየቀው ።

«አንድ የማይረባ ሆቴል ውስጥ ነው የምኖረው ። ጉዳያችን መስመር ከያዘ ለቅቄ እናንተ አልቤርጎ አልጋ እይዛለሁ ።»

«ወደፊት ማድረግ የሚገባንን እናደርጋለ» አለን ። ዲክን ታክሲ ስናሳፍረው ሁለታችንን ለብቻችን ጥሎን በመሔዱ ደስ አላ ለውም ።

ወደ አልቤርጎአችን ስንመለስ፥ መንገዱ ሁሉ በሴተኛ አዳሪዎ ችና በደላሎቻቸው ተሞልቶአል ።

«ለመሆኑ ይህን ሰውዬ ምን ያህል ታምኝዋለሽ?» አለኝ ጃክ ።

«አንተን የማምንህን ያህል አምነዋለሁ ።»

«ግን ክፉ ነገር ቢያጋጥም ፥ የሚጋፈጥ አይመስለኝም ።»

«ይጋፈጣል ! ወንድ ነው ። የሚተጣጠፍ ወረቀት መሰለህ ?»

«ካመንሽበት ጥሩ ነው ።»

ጃክ ክፍል ገባንና ጫማችንን አውልቀን ወንበር ላይ ተቀመጥን ።

«ጃክ ! ለመሆኑ ከየት ነው የመጣኸው ?»

«እውነቱን ለማወቅ ትፈልጊያለሽ ፥ ትውልዴ የአየርሽና የአሜሪካ ነው ። የተወለድኩበትም ቦታ ስተን ነው ። እህቴ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ናት ፤ ሁለት ወንድሞቼ ቄሶች ናቸው ፥ ብዙ ዘመዶቼ ፖሊ ሶች ሲሆኑ አባቴ የፖለቲካ ሰው ነው ።»

«ከቤተሰብህ መካከል ወድቀህ ተልከስክሰህ የቀረህ አንተ ብቻ ነህ ?»

«ከውዳቂም ውዳቂ እንጂ ! ከልክስክስም ልክስክስ !»

«ወደ ቤተሰብህ ለመመለስ ታስባለህ? ትጠይቃቸዋለህ ?»

«በተመቸኝ ጊዜ እጠይቃቸዋለሁ ። በድግስና በደስታ ይቀበሉ ኛል ። ስለ ሥራዬ ምንም አይጠይቁኝም ። ከፍተኛ ሥራ የምሠራ ይመስላቸዋል ። አብሬአቸው ለመኖር ግን አላስብም ።»

«አሁንም ከፍተኛ ሥራ ላይ ነው ያለኸው ። በተለይ የዐርብ ማታው አቋምህ ይወስነዋል ። ምናልባት ሊሆን ይችላል ። እስቲ እናያለን ።»

«ዛሬ አብረን እንደር» አልኩት ።

«እሺ !»

የኒውዮርክን የምሥራቅ ክፍል የሚያሳይ ካርታ ገዝቼ፥ ያሉትን ቤቶች ፥ የታክሲ መቆሚያ ሥፍራዎችና የትራፊክ መብራቶችን አጠ

ናሁና መዘገብኳቸው ። በስንት ሰዓት ለዘረፋ በመኪና እንደምንወጣ ፣ ጉዞው ምን ያህል ሰዓት እንደሚፈጅብን ፣ መኪናችንን የት እንደ ምናቆም ፣ ዘረፋው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መከናወን እንደሚገባው ሁሉ ጸፍኩኝ ። ሱቁ ለሥራ ወዲያው እንደ ተከፈተ የሚዘረፍ መሆኑን ስለ ወሰንን ፣ በዚሁ መሠረት የሰዓት አጠቃቀም ዕቅዴን አሰፈርኩ ። የማምለጫ መኪናውን እኔ ራሴ በመንዳት ውጭ ልጠብቃቸው እንደምችል ወቀድኩ ።

ዕቅዴን በማንበብ ሳወጣ ሳወርድ ፣ ስጨምርና ሳስተካክል ቆየሁ ። ይህን የምሠራው በመደበኛ ቤቴ ውስጥ ሲሆን እንዳጠናቀቅሁ ለመ ጽሐፌ እንዲረዳኝ በማስታወሻዬ ላይ በጥንቃቄ እንድም ሳላስቀር መዘገብኩት ።

ሐሙስ ለት ማታ ከሚስተር ጂርቪስ ጋር እራት ለመብላት ቀጠሮ ስለ ነበረኝ መለባበስ ጀመርኩ ።

ከጂርቪስ ጋር በቀጠሮአችን ሰዓት ተገናኘንና እራት ለመብላት አንድ ጣሊያን ምግብ ቤት ገብተን እራት አዘዝን ። የጂርቪስ አስተ ዛዘዝ የቤቱ ባለቤት ያስመስለዋል ። ምክንያቱም የአስተናጋጅ ኃላፊ እኛ ጋ ብቻ ይሄ ይሻላል ያ ሲል ከወሥር ደቂቃ በላይ አሳልፏል ።

ራታችንን እየበላን በመጠኑ መጠጣት ስጀምር ፣ እሱ ግን ከምግቡ ጋር መጠጡንም እየተቻኮለ በመገንጨት ላይ ነበረ ።

ከበላንና ከጠጣን በኋላ ፣ ሒሳቡን ለመክፈል የአስተናጋጆችን ኃላፊ ጠርቶ ሲጠይቀው ፣ በአክብሮት ሒሳቡ መከፈሉን ነገረው ።

«ሚስተር ስሚዝ የሚባሉት ናቸው ሒሳቡን የከፈሉት ።»

«ስለዚህ ለሚስተር ስሚዝ ረሾም ዕድሜ እመኝለታለሁ ። ለመሆኑ ጓደኛህ ነው ?» አልኩት ።

«ጓደኛዬ አይደለም ። የሱቃችን ደንበኛ ነው ። የመሐጃ ሰዓታ ችን ደርሶአል ። ምሽቱን ለማሳለፍ ዳንስ ቤት ይሻላል ወይስ ቲያትር ቤት ?»

«ዳንስ ቤቱንና ቲያትሩን በዕረፍት ቀን እናድርገው ፣ ጥዋት ሥራ ገቢ ስለ ሆንክ ጸጥታ ያለበት ቦታ ሔደን ቁጭ ብለን ብንጨዋት ይሻላል ።»

«በጣም ጥሩ ነው ። ትልቅ ሰው መሆንሽን ያወቅሁት በመጀ መሪያ ያየሁሽ ሰት ነው ። እኔ የምመርጠውን ቦታ ትቀበያለሽ ?»

«እቤትህ ልትለኝ ነው ?»

ብልጣ ብልጥ ፊቱ በደስታ አበራ ። ለአስተናጋጁ ጉርሻ ሰጠና ወጣን ።

ቤቱ በምሥራቅ በኩል በሐያ አንደኛው መንገድ ከመዝናኛ ስፍራ አጠገብ ነው ። ቤቱ አነስተኛ ቤተ-መንግሥት ሲመስል ሁለት መኝታ ቤት ፣ ሁለት መታጠቢያ ቤትና አነስተኛ አዳራሽ የሚያክል ሳሎን አለው ። የቤቱ ዕቃ በጣም ቆንጆ ነው ። ከዕብነ በረድ በተሠራ ጠረጴዛ ፣ በተሸከርካሪ ሶፋና በተለያዩ ጌጣጌጦችና ሥዕሎች ሳሎኑ የተሞላ ነው ። ሚዩዚያም እንጂ መኖሪያ ቤት አይመስልም ።

ጂርቪስ በእንደዚህ ዓይነት ቤት ውስጥ ይኖራል ብዬ አልገመትኩም ። የዚህ ዓይነት ቤት ሊኖረው የሚችል የኢውዮርክ ከተማ ሎተሪ የደረሰው ሰው መሆን አለበት ።

ማድነቅ ስለ ነበረብኝ በጣም ቆንጆ ቤት እንደ ሆነ ገለጽኩለት ፤ ደስ አለው ። ማድ ቤቱ የሚያስገርም ነው ። ማንኪያና ሹካው ሣህኖቹ ከብር የተሠሩ ናቸው ።

«የራስህን ምግብ ማዘጋጀት ትወዳለህ ?» አልኩት ።

«በጣም ደስ ይለኛል ። በሌላ ቀን ስትመጪ ሠርቼ አበላሻለሁ ። ያን ጊዜ ችሎታየን ታደንቂያለሽ ።»

«በጣም ደስ ይለኛል ።»

ወደ ሳሎን ሐዲን ብራንዲ መጠጣት ጀመርን ። ያመጣን መኪና እንዲቆይ ስለ ተነገረው ብዙም እንደማንቆይ ይመቼአለሁ ።

እየተጫወትን መጠጥ ስንጠጣ ፣ ይቅርታ ብሎኝ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ። ብጠብቅ ብጠብቅ ቀረብኝ ። ተጣራሁ ፤ መልስ የለም ። ደነገጥኩ ። ልብ ድካም አለበት ወይስ ምንድነው?

'መኝታ ቤት የገባው ልብሱን አወላልቆ ሊጠብቀኝና ስሐድ ሊይዘኝ ይሆን?' በማለት ለመሮጥ እንዲያመቸኝ ጫማየን አድርጌ መኝታ ክፍሉ ገባሁ ። ከነልብሱ እግሩን እንኳ አልጋ ላይ ሳያወጣ ተኝቶ ያን ኮራፋል ። ጫማዎቹን አወላለቅሁና እንሥቼ አልጋ ላይ ሳወጣውም አይሰማም ። ክራባቱንና የሸሚዙቹን ቁልፍ ፈታትቼ በደንብ አስተኛሁት ። የሳሎኑን በር ቆልፌ ስመለስ ሁሉ አልተንቀሳቀሰም ።

መታጠቢያ ቤት ሐጄ የመድኃኒት ማስቀመጫ ሣጥኑን ከፍቼ አየሁ ። የዐይን ጠብታዎች ፣ የተለያዩ ቀለምና ቅርፅ ያላቸው እንክ

ብሎችና የተወሰኑ ለእንቅልፍ የሚረዱ መድኃኒቶች አሉበት ። እንደ ነበረ ዘጋሁና ወደ መኝታ ቤቱ ተመለስኩ ። አሁንም ዝም ብሎ ያን ኮራፋል ። ወደ ቁም ሣጥኑ ሐዲኩና ከፈትኩት ፣ ከእንግሊዝና ከጣሊያን አገር የተገዙ የተለያዩ ልብሶች ሞልተውበታል ። ከላይ ያለውን መሳቢያ ስስበው በአልማዝና በወርቅ ሰዓቶች ተሞልቶአል ። ዘጋሁና የታችኛውን መሳቢያ ስስበው የስፖርት ዕቃዎችን አየሁኝ ። የከፈትኳቸውን ሁሉ እንደ ነበሩ መዘጋታቸውን አረጋገጥኩ ። ምንም ያነሣሁት ነገር የለም ። የመጨረሻውን መሳቢያ ስከፍተው ያለበት ሹራብ ብቻ ነው ። በእጄ የሹራቡን ዓይነት ለማወቅ ስነካ ከሹራቡ ሥር አንድ ሌላ ነገር መንካቴ ታወቀኝ ። ዞር ብዬ ጂርቪስን አየሁት ። ተኝቶአል ። የነካሁትን አወጣሁት ። ፓስፖርት ነው ። ወደ ትራስጌ መብራት ወስጄ ሳየው የጂርቪስ ፎቶ የተለጠፈበት ሆኖ ፣ የሆላንድ ፣ የጣሊያንና የእስራኤል አገር ማኅተም ተደርጎበ ታል ። ሌላው በት ክክል የቀረበ ሲሆን ስሙ ግን አንቶኒዮ ሮሲ ይላል ። ፊርማውንም አየሁት ። አንድ ጣሊያናዊ የአሜሪካ ስም ቢጠቀም ምን አለበት ? እንዲያውም ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የጌጣጌጥ ሱቅ ኃላፊ በመሆኑ ከአንቶኒዎ ይልቅ ጂርቪስ የሚለውን ስሙን ደንበኞቹ ሊወዱት ይችላሉ ብዬ ገመትኩ ። የቀረኝ ጂርቪስ ከተኛበት አጠገብ ያለውን መሳቢያ ማየት ነው ። ልይ ፣ ልተው እያልኩ አመነታሁ ። ጂርቪስን ሳየው የሚንቀሳቀስ ባለመሆኑ ቀስ ብዬ ሳብኩት ። ትልቅ ሽጉጥ ተቀምጠበታል ። መልሼ ዘጋሁና በድጋሚ የከፈትኳቸውን ሁሉ መዘጋታቸውን በማረጋገጥ መብራቶችን አጠፋፍቼና የዋናውን በር ዘጋግቼ ወደሚጠብቀኝ መኪና ሐዲኩ ።

የደንብ ልብስ በለበሰ ሹፌር አሽከርካሪነት ቤቴ ስደርስ ሾፌሩን መሐድ እንደሚችል ነገርኩት ። «ሚስተር ጂርቪስ እቤትዋ እስክትገባ ጠብታት ብሎኛል» ሲለኝ ምን ችገረኝ በማለት ትቼው ወደ ቤቴ ገባሁ ።

በዚያ በጣሊያን ምግብ ቤት የበላሁትን ምግብ እያሰብኩ እንቅልፍ ይዞኝ ሐደ ።

ዓርብ ዕለት በቀጠሮአችን መሠረት ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ ጃክ ከፍል ተሰበሰብን ። የዲክ የዛሬው አለባበስ የተለየ ነው ።

ጃክ እንደ ድሮው ፊገግታ አይታይበትም ። በዝምታ መጠ ቀድቶልን ቁጭ አለ ።

«እሺ ! በጉዳዩ ትስማማበታለህ ወይስ አትስማማበትም ?» አልኩት ።

«ለሁለት ቀን ሱቁን በአካባቢው ሆኜ አይቸዋለሁ ፣ ውስጡንም

ለመመልከት ችያለሁ ። ሒሳቤን ከመናገሬ በፊት ግን እንዴት ለመ
ፈጸም እንደ ታቀደ መስማት እፈልጋለሁ » አለኝ ።

ያዘጋጀሁትን ዕቅድ በዝርዝር መግለጽ ጀመርኩኝ ።

«እኛ ሦስታችን ከምንቀጥራቸው ሁለት ሰዎች ጋር ማለትም
አምስታችንም በኔ ቮልፈርነት ወደ ሱቁ እንሒድና ከሱቁ ትንሽ ራቅ
ብለን እንቆማለን ። አራታችሁ ትወጣላችሁ ። እኔ ሞተር ሳላጠፋ
እጠብቃችኋለሁ ። ልክ ሲከፈት ወደ ሱቁ በመግባት ሁለት ሰዎች
ወደ ጓዳ ይሒዱና ከውስጥ ያሉት ሠራተኞች የጓዳውን በር የመዝጋት
ዕድል እንዳያገኙ በፍጥነት እነሱን ያስራሉ ። የቀሩት ኃላፊውንና
ሠራተኞችን መሬት እንዲተኙ አስገድደው ያስራሉ ። እንዳይጮሁ
አፋቸውን በፕላስተር ማጣበቅ ያስፈልጋል ። ተላላኪውም ካለ እሱ
ንም እንደዚሁ ማሰር ። ከዚያም በፍጥነት ንብረቶችን መሰብሰብና
መውጣት ፣ ስትወጡ እኔ መኪናውን አስጠግቼ መጫድ . . .»

ጆክ አቋርጦኝ ፣ «ደደብ !» ሲል ሰደበኝና ፣ «ይሄ የሕፃን ልጅ
ሥራ ነው ። አንች እስከምትጠጊ በሩ ይዘጋና ሁላችንም በቁጥጥር
ሥር እንውላለን ። አንቺ ባልሽው መንገድ ካደረግነው ዕድለኞች
ሆነን ባንሞት እጃችን በሰንሰለት ከመታሰር አይድንም» አለ ።

እኔና ዲክ ተያየንና «እንሒድ» ተባባልን ።

ለመጫድ እንደ ተነሣሁ ፣ «አልሰማማበትም ካልክ መተው
ትችላለህ» ብየው ሁለታችንም ስንንቀሳቀስ ፣

«አንቺም አንተም ዝም በሉና ቁጭ በሉ ! አልሰማማብትም
አላልኩም ! ዕቅዳችሁ ግን ብላሽ ነው ። የድሮ ፍቅረኛሽ በዚህ ሥራ
ልምድ እንደ ነበረው ነግረሽኝ ነበር ። በዚህ ዓይነት መንገድ ሞከ
ሮት ከሆነ መሞቱ ትክክል ነው » አለ ።

«አንድ ወር ሙሉ የለፋሁበት ዕቅድ ነው ። ስሕተቱ ምንድ
ነው ?» በማለት በቁጣ ተናገርኩ ።

«ቀስ በይ አትጩኺ ! ቢያ ! ረጋ በይና ምን ስሕተት እንዳለበት
እነግርሻለሁ ። በመጀመሪያ ደረጃ ሱቁ ከፍተኛ ንብረት ያለው ሆኖ
የሠራተኛ ቁጥር ግን አነስተኛ ነው ። ስለዚህ በቀላሉ መዘረፍ የሚ
ችል ነው ። ከሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት እንዳለበት ቢያ
አልነገረችህም ?» ብሎ ዞር በማለት ዲክን ተመለከተና ፣ «ብዋቂ
አንድ ሚሊዮን ብር ወይም ከዚያ በላይ . . . ጓዳስ ያለው ምን ያህል
ይሆናል? አይታወቅም ። ብዙ ንብረት ሊኖር ይችላል ። በዚህ ተስማ

ምተናል ። የሚገኘው ንብረት ከፍተኛ ሲሆን ሊደርስ የሚችለው አደጋ ትንሽ ነው ። የታጠቀ ዘበኛ ፣ የመቆጣጠሪያ ቴሌቪዥን የለም።»

«ስለዚህ በዝርፊያው ተስማምተሃል ?» አልኩት በመቻኮል ።

«እስማማለሁ ፥ ግን ባንች ዕቅድ አይደለም ። በመጀመሪያ ደረጃ ለአምስት ሰው አንድ መኪና ብቻ አይበቃም ። ሁለት መኪና ያስፈልጋል ። ሱቁ በር ሲደርሱና በመጨረሻም ሲሔዱ ለሚያያቸው ሰው እንኳ ግራ ያጋባሉ ።»

«ጥሩ ! ይሄን ሐሳብህን እቀበላለሁ ፤ በዚህ ዓይነት ተጨማሪ ሰው ሊያስፈልገን ነው ።»

«ትክክል ! ከአንድ ሰው ሌላም ተጨማሪ ሰው ያስፈልገናል ። ሱቁ እንደ ተከፈተ ዝም ብለን ወደ ውስጥ መግባት አንችልም ። ምና ልባት ተዘዋዋሪ እግረኛ ፖሊስ ወይም ባለመኪና ቢመጣስ ?»

«የመምጣት ዕድላቸው በጣም አነስተኛ ነው ።»

«ፖሊሶች እንዴት እንደሚሠሩ በውቃለሁ ። የተወሰነ ሰዓትና ቦታ የላቸውም ። እኔ የምለው ቢሆንስ? እኛ ውስጥ እንዳለን ቢመጡ አንቺ ብቻሽን እየተታኮስሽ ልታቆሚያቸውና አካባቢውን ጦር ሜዳ ልታስመስይው ነው? ቢያ የማይሆን ነው ። ጥራት ያላቸው ብዙ ሰዎች ያስፈልጉናል ።»

«ምን ዓይነት ሰዎች ?»

«ይሄውልሽ ለሁለት ቀን ቦታውን ባየሁበት ጊዜያት ሱቁን የሚያጸዱ ፥ ከመክፈቻው አንድ ሰዓት ቀደም ብለው በትልቅ መኪና እንደሚመጡ አስተውለሻል ?»

«አዎ! ሦስት ሰዓት ላይ የሱቁ ኃላፊ በሩን ይከፍትላቸውና ገብ ተው ከሠላሳ እስከ ዐርባ አምስት ደቂቃ ያህል ቆይተው ሲወጡ በሩ እንደ ገና ይዘጋል ።»

«ሁል ጊዜ ጥዋት ጥዋት ?»

«አዎ! አንድም ቀን አቋርጠ አያውቅም ።»

«ጥሩ ነው» አለ በመደሰት ። መሠረታዊውም ጥያቄ ይሄ ነው ። መኪናው የ«ቦኖሞ የጽዳት ሥራ ድርጅት» ንብረት ነው ። ሁለቱንም ቀን እንዳየሁት ጥዋት መኪናው ከበራፉ ደርሶ ሲቆም የሱቁ ኃላፊ ወዲያውኑ በሩን ይከፍትላቸዋል ። ገባሽ? የሚመለከተው መኪናውን እንጂ ፥ መኪናው ውስጥ ያሉትን ሰዎች አይደለም ። መኪናውን እንጂ

ሠራተኞቹ እነማን መሆናቸውን አያረጋግጥም ።»

«ታዲያ መኪናውን መጥለፍ ነዋ !» አለ ዲክ ።

«ልክ ነው !» አለ ጃክ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዲክን በአክብሮት እየ ተመለከተ ። «እንግዲህ ሁለተኛውን መኪና አገኘን ማለት ነው ። መኪናው አስፈላጊ ከሆነ ከኋላው አንድ የእግር ኳስ ቡድን አባላትን ያህል ሰው ሊይዝልን ይችላል ። ፍጥነት ካለን ባለን የሰው ኃይል ሱቁ ውስጥ ያለውን ንብረት ቀርቶ ግድግዳ ላይ የተለጠፈውንም ወረቀት መውሰድ ይቻላል ። መኪናው እንደ ቆመ የሱቁ ኃላፊ በጽዳት ሠራ ተኞቹ ማንነት እንኳን ቢጠራጠር ፍጥነት ካለን በሩ ሳይዘጋ መግባት እንችላለን ።»

«ተቃውሞ አለኝ ! ኃላፊው መጀመሪያ ሰዎቹን እይቶ ብቻ በሩን የሚከፍት ቢሆንስ?» ስል ጠየቅኩት ።

«ይሄን ያደርጋል ። ግን የሚመለከተው ፊታቸውን ሳይሆን የለበሱትን የጽዳት ሠራተኞች ቱታ ነው ። የተለየ ልብስ የለበሰን ሰው መጀመሪያ የምታይው ልብሱን እንጂ ፊቱን አይደለም ።»

«ከዚያ በኋላስ ?» አልኩ በመዳከም መልክ ።

«በሩ እንደ ተከፈተ የጽዳት መኪና ውስጥ ከፊት ወንበር የተ ቀመጡት በፍጥነት ሮጠው ሲወጡ፣ ከኋላ ያሉትም ተከታትለዋቸው ይሔዳሉ ። ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ስለ ሆነ መንገደኛ ቢያያቸው የጽዳት ሥራቸውን ቶሎ ለማከናወን የሚሮጡ እንጂ በሌላ የሚጠረጥራቸው አይኖርም ። እንደገቡ ሰዎቹን በቁጥጥር ሥር ያውላሉ ። በተቻለ መጠን ከሠራተኞቹ መካከል አንዱ በወጌ ተነሣሥቶ ችግር እንዳይፈጥር ጥን ቃቄ ይደረጋል ። የምንፈልገውን ካገኘን በኋላ ፣ ሰዎች እንደ ታሰሩ በላያቸው ላይ በሩን በመዝጋት ንብረቱን ለሁለት ተከፋፍለን በተ ለያየ አቅጣጫ እንሔድና በመጨረሻ በትክክል ለመከፋፈል እንገና ኛለን ። ምን ይመስላችኋል ?»

እኔና ዲክ ተያየንና ፣ «ምን ታስባለህ? ዲክ» አልኩት ።

«መኪናውን ለመጥለፍ እንዴት እንችላለን ?»

«በጣም ቀላል ነው ! ንብረትነቱ የቦኖሞ የጽዳት ሥራ ድርጅት ስለ ሆነ ፣ ድርጅቱ የሚገኝበትን ቦታ ካገኘን መኪናው መንቀሳቀስ የሚጀምርበትን ሰዓት እናውቃለን ። የመኪናው ጉን ቁጥር ዐሥራ አራት ስለ ሆነ መከታተል እንጀምራለን ። እርግጥ ጊዜ ይወስዳል እንጂ ፣ የት የት እንደሚሔድ ለማወቅ ቀላል ነው ። ሱቁ ከመድረሱ በፊት መኪናውን እንጠልፈዋለን ።»

«ሾፌሩና ረዳቱ መኪናው ሲጠለፍ ለፖሊስ አመልክተው እን ያዝም ወይ ?»

«ልክ ነሽ ! በዚህ ዓይነት ከነሰዎቹ መኪናውን እንጠልፍና አስረን ከኋላ እናስቀምጣቸዋለን ። ከጨረስን በኋላ ሰዎቹ ታፍነው እንዳይሞቱ ለፖሊስ ስልክ ደውለን እንነግራለን ።»

«አንድ ነገር ያሳስበኛል ። እርግጠኛ ነህ ኃላፊው ሰዎቹን ሳይ ለይ ልብሳቸውን ብቻ ተመልክቶ በሩን ይከፍታል ?» ስል አሁንም ጠየቅኩት ።

«እሺ !» አለ በማንሓጠጥ መልክ ። «እንዳልሺው በሩን ከመክ ፈቱ በፊት በመስታወት ቢመለከት ፡ የሚያያቸው እፊት የተቀመ ጡትን ሁለቱን ነው ። ታዲያ እዛው ውስጥ ሆኖ ፡ 'ምንድን ናችሁ ? የተለመዱት ሠራተኞች የት ሔዱ?' ብሎ ሊጠይቅ ነው? አይጠይቅም ። ቢጠይቅም በሩን ከፍቶ በመውጣት ይሆናል ። የድርጅቱን ልብስ የለበሱና የጽዳት ዕቃ የያዙ መሆናቸውን ሲያይ ደግሞ አይጠረጥርም።»

«ስማ ጃክ» አልኩት ፡ «በዕቅዳችን መሠረት ለመፈጸም ከሁለት ሳምንታት በላይ አለን ፤ ስለዚህ በዚህ ብዙ እንጨነቅ ። እኔና ዲክ ለሚቀጥለው ሳምንት ከሦስት ሰዓት ጀምሮ የጽዳት ሠራተኞቹ ሲመጡ እንመለከታለን ። እንዳልከው ኃላፊው መኪናውን ብቻ አይቶ በሩን የሚከፍትና የማይከፍት መሆኑን እናያለን ። እንደምት ለው ከሆነ ባንተ መገንድ እንቀጥላለን ፤ የተለየ ነገር ካለ ሌላ ዘዴ እንፈልጋለን ።»

«የእግዚአብሔር ያለህ ! ምን ማለትሽ ነው ? አሁንስ አረጀሽ መሰለኝ ? ለምን ዕድላችንን እኔ ባልኩት አንሞክርም ? ጊዜ ለምን እናጠፋለን ?»

«አላስፈላጊ ችግር ውስጥ መግባት የለብንም ። ጊዜ ስለ አለን አያስቸኩለንም ።»

«ጥሩ እሳሩ ፤ እኔ ግን ምን ሳደርግ ልቀይ ?»

«አንተ የጽዳት ድርጅቱ የት እንደሚገኝ ካወቅህ በኋላ ፡ የጐን ቁጥሩ ፬ሥራ አራት የሆነውን መኪና ተከታተል ። ይሄን ከጨረስክ በኋላ ከተማውን ከኔ የተሻለ ስለምታውቅ ፡ ለሥራችን የሚያስፈልጉ ነገን ሰዎች መልምል ። ይሄን ማድረግ ትችላለህ ?»

«ምንም ችግር የለም ።»

«ሌላው እነዚያን አገኛቸዋለሁ ያልካቸውን ሰዎችስ አገኘህ?»

«አግኝቻለሁ ፣ ጫፍ ጫፉን ነግሬአቸዋለሁ ። ግን በትክክል ጉዳዩ ምን እንደ ሆነ አይለዩም ። ለማንኛውም ዝግጁ ናቸው ሰዎቹ ፣ የሚያስቡ አይደሉም ፣ አድርጉ የተባሉትን ያደርጋሉ ። አፋቸውም ጥብቅ ነው ።»

«መኪናውን የምንጠልፍ ከሆነ ሌላ የሰው ኃይል አሁንም ሊያስፈልገን ነው ።»

«ችግር የለም ። ከተማው በሙሉ በሥራ አጥ የተጥለቀለቀ ስለ ሆነ የምንፈልገውን ያህል ሰው ማግኘት እንችላለን ።»

«ለመሆኑ እንዴት ነው የምንከፍላቸው ? በጥሬ ገንዘብ ወይስ ከንብረቱ ማካፈል ?» በማለት ዲክ ጥያቄ አቀረበ ።

ጃክ ከመቀመጫው ተነሥቶ፡ «ይሄ እንኳ በጓላ የምንወስነው ነው» ብሎ መጠጥ ቀዳልን ። ሁሉቱም ብርጭቆአቸውን ከፍ አድርገው ዲክ «ለመልካም ውጤት !» ጃክም፡ «ለመልካም ዕድል !» አሉ ። እኔ ግን ዝም አልኩ ።

ከዚያም ዲክን ለየት ባለ ሁኔታ ተመለከተው ። ዲክ መጠጡን ጨለጠና ከመቀመጫው ተነሥቶ «ከሰው ጋር ቀጠሮ አለኝ» በማለት ዞር ብሎ ለጥቂት ጊዜ ተመለከተኝ ። ከጃክ ጋር ምሽቱን እንዴት እንደምናሳልፈው እያብሰለሰለ ደህና እደሩ ብሎ ወጣ ።

«ምንም አይልም» በማለት እንደ ገና መጠጥ ቀዳና ፡ «ጥሩ ሰው መሆኑን ዐውቃለሁ ብለሽኛል ። ደግሞም ደደብ አይደለም ። ስለ መኪና ጠለፋም ያውቃል ፡ ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር ጓደኛ መሆን አልፈልግም ። አብሬ ለመሥራት ግን እችላለሁ ። ችግር ቢመጣ አሁንም የሚቋቋም አይመስለኝም » አለኝ ።

«በበኩሌ እንደሚቋቋም ሙሉ በሙሉ አምናለሁ» አልኩት ።

«ከልብሽ ከሆነ ጥሩ ነው ። መተኛት ትፈልጊያለሽ ?»

«አዎ» ብዬው አብረን ተኛን ። ጃክን ወደ ወንጀል በመምራቴ እያዘንኩ ፡ አልጋ ላይ እንደልቡ እንዲዝናና አደረኩት ።

ከሰኞ ጀምሮ ላሉት ሦስት ቀናት ማለት ሰኞን ራሱን ፡ ሮብና ዐርብን ቢያን ሆኜ በሰቱ አካባቢ የጅዳት መኪናውን ተመለከትኩት ። ግክሰኞና ሐሙስ እውነተኛዋን ጂኒን ሆኜ ቡና ቤት ውስጥ ተቀምጬ አየሁት ። እንዲያውም ማስታወሻ ሁሉ ያዝኩ ። ከአምስቱ በአራቱ ቀናት ልክ ጃክ እንዳለው ሆነ ። በሌላው ቀን ግን መኪናው ሲመጣ በራ አልተከፈተም ። ሠራተኞቹ ወርደው በራን ካንኳኩ በኋላ ነበር

የተከፈተው ። ኃላፊው ውስጠኛው ክፍል ሥራ በዝቶበት ሊሆን ይችላል ። ማን ያውቃል ?

ዕቅዳችን ከመኪናው መምጣት ፡ ከሱቁ በር መከፈትና ካለ መከፈት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፡ ይሄን አጋጣሚ መመዝገቤ እንደ ቀላል ነገር የሚታይ አይደለም ። ለመጽሐፌም ጥሩ ነው ። ሌላው ትምህርት ያገኘሁት ትላልቅ ወንጀሎች ሁሉ እንደ ከፍተኛ ጦርነት በሰዓት የሚመሩ መሆናቸውን ነው ።

በዋናው ማስታወሻዬ ላይ ይሄንን ሁሉ አስፍሬ ስጨርስ፡ ለወኪሌ ለሶል ፋበር ስልክ ደውዬ አዲስ መጽሐፍ በመጻፍ ላይ እንደምገኝና በጥር ወር እንደማደርሰው ነገርኩት ።

«የኔ ቆንጆ ደስ የሚል ዜና ነው ። አልዶ እንደሚፈልገው እውነትነት አለው ?» ሲል ጠየቀኝ ።

«ሙሉ በሙሉ» በማለት አረጋገጥኩለት ።

«ማለቴ መጨረሻ ያለው ታሪክ ጥሩ የሆነ ?»

«አንተ ደግሞ ሰው አታምንም ! ጊዜው ሲደርስ ታየዋለህ ።»

ዐርብ ለት ማታ ምስታችንም ከፋንጮ ቡና ቤት ጆርባ ተገናኘን ። ከኛ ቀደም ብሎ ጃክ ደርሷል ። የተዳከመና የከፋው ይመስላል ።

«እሺ እንዴት ነው ?» አልኩት ።

«የጽዳት ድርጅቱ በሃምሳ አራተኛው መንገድ ላይ ነው የሚገኘው ። ከሃምሳ በላይ መኪናዎች አሉት ። የጮን ቁጥሩ ዐሥራ አራት የሆነውን መኪና ለማግኘት ሁለት ቀን ፈጅቶብኛል ።»

«መኪናውን ተከተልከው ?»

«ችግሩ እሱ ነው ። በየቀኑ የሚሔድበት ቦታ አንድ ዓይነት አይደለም ። የሚገርም ነው» አለ ራሱን በማወዛወዝ ።

ዴክ ቀበል አደረገና ፡ «የጽዳት አገልግሎት የሚሰጠው ድርጅት ብዙ ደንበኞች ስለአሉት አንድ መኪና ሁል ጊዜ እንዴት አንድ ቦታ ይመድባል ብለህ ታስባለህ? ለምሳሌ የጮን ቁጥር ዐሥራ አራት እዚህኛው ሱቅ የሚመጣው በአንድ ሳምንት ልዩነት ሲሆን ፡ ይህ መኪና ሌላ ቦታ ሲሔድ በምትኩ ለአንድ ሳምንት ሌላ መኪና ይመጣል ። ስለዚህ መኪናው ሰኞ ሲመጣ ካየነው ሳምንቱን ሙሉ የሚመላለሰው እሱ ብቻ ይሆናል ማለት ነው » አለው ።

ጃክ የዲክን አገጭ መታ መታ እያደረገ ፡ «ልክ ነህ ፤ ጥሩ ጭንቅላት አለህ ። እንዴት በፊት አላሰብኩትም ?» አለ ።

«አሁን ማድረግ የሚገባን በሳምንቱ ውስጥ የትኛውን ቀን መጠቀም እንዳለብን እንወስንና የጉን ቁጥሩ ዐሥራ አራት መኪናን እንቅስቃሴ እናጥና» አለ ዲክ ።

«ወርብ ቀን ቢሆን ለኔ ይስማማኛል ። አንተስ ጃክ?» አልኩኝ ።

«ወርብ ቀን ጥሩ ነው ። ለቅዳሜው በዓል ሰዉን ክፍት ለማድረግ ወርብ ሬለት መጽዳት አለበት ። በጣም ጥሩ ስለዚህ እንጠጣ! ትክክለኛውን ቀን በመጨረሻ እንወስናለን ።»

«ለማንኛውም መኪናው ሲጠለፍ ረዳቱን ወደ ኋላ እናስገባና እናስራለን ። ሾፌሩ አጠገብ ሽጉጥ ደግኖ አንድ ሰው ይቀመጥና እንዲነዳ ያስገድደዋል ። የሰው ኃላፊ የተለመደውን ሹፌር ሲያይ በሩን ሊከፍትልን ይችላል ፤ አዲስ ረዳት ከሾፌሩ ጋር ቢያይ አይጠራጠርም » አለ ዲክ ።

«በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው !» አለ ጃክ በመደሰት ።

«የሚሰካ ይመስልሃል ?» አለው ዲክ ።

«ልክ ባንክ ያስቀመጥከው ገንዘብ ማለት ነው ። ያለ ጥርጥር ይሰካል ። ሁለቱንም ሰዎች አግኝቻለሁ ። ቡና ቤቱ ውስጥ እየጠበቁን ነው ። በዕቅዳችን መሉ በመሉ እስከምንስማማ ብዬ ዕቅዳችንን መሉ በመሉ አልነገርኳቸውም ። አሁን ልጥራቸው ?»

«ጥሩ ! ጥራቸው ። ለመሆኑ የትኞቹ ናቸው ?» አልኩት ፊቴን ወደ ቡና ቤቱ አዙሬ ።

«ቢራ ከሚቀዳበት መኻል ያሉት ይታዩሻል! ትልቁ ሄሚንግር ይባላል፡ ሰውነቱ ብረት ነው ፤ በዚያ ላይ ፊጣን ነው ። ቀጭኑ ትክክለኛ ስሙን ማንም አያውቀውም ። እንዴህ ሆሊ ጉስት ይሉታል ። ቆይ ልጥራቸው» ብሎ ሐደ ።

«ጄኒ ! ሄሚንግርና ሆሊ ጉስት ለመጽሐፍሽ ተአማኒ ገጸ ባሕርያት ይሆኑሻል» አለኝ ዲክ ።

«ማን ያምነኛል ብለህ ነው፣ መጽሐፌ ውስጥ ስማቸውን አልጠቀምበትም ።»

ሁለቱም ቢራቸውን እንደ ያዙ መጡ ። ጉስት ጃክ ጉን ተቀመጠ ፤ ሄሚ ጠረጴዛው ጫፍ አጠገብ ወንበር ሳበና ተቀመጠ ። መተ

ዋወቅ የለም ! ፈገግታ ተለዋወጥንና ትንሽ ቆይተን ስለ ከተማውና ስለ አየር ጠባዩ አወራን ። አስተናጋጅዋ ስትመጣ ጃክ ለሁላችንም አዲስ ቮድካ አምጭልን አለ ። ሐሳቡን ያው እኔ እንደምከፍለው ዐውቃለሁ ።

ሄሚ ጐር በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ፣ ቮድካው ተቀድቶለት መለኪያውን ሲይዘው እጁ ውስጥ መኖሩ አይታወቅም ። የሚገር መው ግን ፣ ከንደዚህ ዓይነት ጠረንገሉ ሰው የሚወጣው ድምፅ ቀጭን መሆኑ ነው ።

ሆሊ ጐስት ፣ ገና መብቀል የጀመረ ጠም ያለው ሲሆን አንድ የሆነ ሐሳብ ውስጥ የገባ ይመስል ጠረጴዛውን በእጁ ይቆረቁራል ።

ጃክ አስተናጋጁዋ እስክትሔድ ጠብቆ ሁለቱን በመመልከት ፤ «አሁን የተገናኘነው የጌጣጌጥ ሱቅ ለመዝረፍ ነው ። ሰባት ሠራተኞች ያሉት ሲሆን ፣ ለሥራ ከመከፈቱና ገበያው ከመድራቱ በፊት ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ ለመዝረፍ አቅደናል » ሲል ነገራቸው ።

«እንዴት ? የማስጠንቀቂያ የኤሌክትሪክ መሣሪያ የሉትም ?» አለ ሆሊ ጐስት በሚያጉረመርም ወፍራም ድምፅ ።

«ቢኖረውም መሣሪያ የያዘ ዘበኛና ቴሌቪዥን የለውም ። እኛ በምንደርስበት ሰዓት በሩ ክፍት ይሆናል ። ለገዥዎቹ ግን ቆይቶ ነው የሚከፈተው ። ስለዚህ ጌጣጌጡቹ በመጀመሪያው ክፍልና ጓዳ ውስጥ ስለ አሉ ሰብስቦ መውጣት ነው ። በጣም ቀላል ነው ። ጣፋጭ ኬክ መግመጥ ማለት ነው ።»

«እንዲህ አድርጎም ጣፋጭ ኬክ የለም ! ቢያንስ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ያስጠፍራል» አለ አሁንም ጐስት ።

«እውነቴን ነው ይሄ ዕድል ሊያመልጠን አይገባም ! »

«በዘረፋው የምንሳተፈው አምስታችን ብቻ ነን ?»

«ሌላ ሁለት ወይም ሦስት ሰው እንጨምራለን ፤ ግን አሁን ሳይ ሆን ለዘረፋው ስንቃረብ ይሆናል ።»

«ክፍያው ስንት ነው ?» አለ ሆሊ ጐስት ።

«መጀመሪያ በጉዳዩ እንስማማ ፤ በዘረፋው ለመሳተፍ ተስማም ታችኋል ?»

«መስማማት ? ምን ማለትህ ነው ? እኔ እስማማለሁ» አለ ሄሚ ጐር

«እኔ ዐሥር እፈልጋለሁ !» አለ ጐስት ።

«ዐሥር ምን ?» አለ ዲክ ።

«ከሚገኘው ንብረት ዐሥር ከመቶ»

ጃክን ተመለከትኩት ። ራሱን በመነቅነቅ ጥሩ መሆኑን ገለጸ ።

«ጥሩ ነው ለሁለታችሁ ዐሥር ዐሥር በመቶ እንሰጣለን ፤ አዲስ ለምንቀጥራቸው ሰዎች ግን መቀነስ አለበት ። አለበለዚያ ወጭው ከፍተኛ ይሆናል ።»

«ልክ ነው» አለ ጃክ ።
«ጥሩ ይሄን ቅንብር የሚመራው ማነው ?» አለ ሆሊ ጐስት ።
«እኔ ነኝ !» አልኩት ።
«አንቺ ?»
«አዎ እሷ ነች ። ጐበዝ ናት ፤ እኔም አለሁበት» አለ ጃክ ።
«እንደ ገና ማሰብ ትፈልጋላችሁ ?» አለ ዲክ ።
«ከገና በፊት ነው ። አይደለም እንዴ ?» አለ አሁንም ሂሚ ጐር ።
«ከገና ሁለት ሳምንት በፊት» አለ ዲክ ።

«ጥሩ ነው፤ ለገና በዓል ብዙ የምሰጠው ስጦታ ስለአለኝ ገንዘብ ማግኘት ይኖርብኛል ፥ እኔ በሥራው እሳተፋለሁ ።»

«እኔም አለሁበት » አለ ጐስት ።
«ጥሩ ነው» አልኩኝና ዝርዝር አፈጻጸሙን ነገርኩዋቸው ።

«በተለይ የጽዳት መኪናው በጣም ጥሩ ነው» ሲል ጐስት አድናቆቱን ገለጸ ።

«ቢያ እንደ ነገረቻችሁ ሁለት ወይም ሦስት ተጨማሪ ሰው ያስፈልገናል ። ስለዚህ እናንተም ምረጡ ። ከመዝረፋችን አንድ ቀን በፊት መኪናም እንሰርቃለን ። ስለዚህ የሚሰረቀው መኪና ባለ አራት በርና ጠንካራ ሞተር ያለው መሆን አለበት ። እንዲሁም ከዘረፋው በኋላ ንብረቱን የምንከፋፈልበትና ከመኪና ላይም የምናራግፍበት የተዘጋ ጋራዥ ብናገኝ ጥሩ ነው ። ከተከፋፈልን በኋላ መኪናውንና ሰዎቹን እዛው እንተዋቸዋለን ። ሌላ የጽዳት ሠራተኞች ቱታ ለሁላችንም ያስፈልገናል ። ፖሊሶችንም በዕለቱ ግራ ለማጋባት አንድ ቦታ ቦንብ ተጠምዷል ብለን ልንደውል እንችላለን ። አለዚያ አነስተኛ ፖስታ ቤት ፊልገን በቦንብ እናፈነዳዋለን ።»

በመገረም ጃክን ተመለከትኩትና አለቃነቴን ለማሳየት ፣ «የፊት መከለያ ፣ ጓንት እንደዚሁም የሱቁንና የጽዳት ሠራተኞችን ለማሰር የፕላስቲክ ገመድ ያስፈልገናል » አልኩ ።

«ለመሆኑ የጓዳው ሳጥን የተቆለፈ ቢሆንስ ?» አለኝ ጃክ ።

«አይቆለፍም» አልኩኝ በቁርጠኝነት ። «ከተቆለፈም ለመስ በርም ሆነ ለመቁረጥ ጊዜ ይወስዳል ፤ ድምፅም አካባቢውን ሊረብሽ ይችላል ። ስለዚህ ሣጥኑን ትተን መስታወቱ ውስጥ የተደረደሩትን ብቻ መውሰድ ይኖርብናል ማለት ነው ። ለማንኛውም አሁን የሚያ ስፈልገን ትልቅ መዶሻና ቦርሣዎች ነው ።»

ሁሉም ተያዩና ፥ «በጣም ጥሩ ነው» አሉ ።

«ንብረቱን ከወሰድን በኋላ ፥ ቶሎ ሽጠን ገንዘቡን ለመከፋፈል ጊዜ ይወስዳል ። ስለዚህ በቀላሉ ሊሸጥ የሚችል ሐብልና ቀለበት የመሳሰሉትን ለመውሰድ ፈቃደኛ ትሆናላችሁ ?» ብሎ ጃክ ሁለቱንም ጠየቃቸው ።

«ይቻላል ፤ እነኝህን ወዲያውኑ በመሸጥ መጠቀም እንችላለን» አለ ሄሚ ።

«እሺ ሌላ ጊዜ እንገናኛለን» ሲላቸው ፥ ሁለቱም መጠጣቸውን ጨልጠው በእጃቸው ሰላም ብለው ወጡ ።

«ምን ታስባላችሁ ?» አለን ጃክ ብቻችንን እንደ ቀረን ።

«ሥራውን ለመሥራት የሚችሉ መሰለኝ» አለ ዲክ ።

«ጃክ ! ለምንድነው ከተሰረቀው ንብረት ድርሻቸውን እንዲ ወስዱ የፈለግከው? ለምን እስኪሸጥ ከኛ ጋር አይቆዩም ?» ስል ጠየኩት ።

ትኩር ብሎ አየኝና ፥ «አልገባሽም ! እነዚህ ሰዎች ጉልበት ነው ያላቸው እንጂ ጭንቅላት የላቸውም ። ጌጡን ብናካፍላቸው በየቡና ቤቱ እየዞሩ ይሸጡታል ። ወዲያው ይያዛሉ ። ከዚያ በኋላ ሱቁን እን ዴት እንደ ዘረፉት ጋዜጣ ላይ ይወጣል ። በዚህም ነገሩ ስለሚረሳሳ እኛ የማምለጥ ዕድል ይኖረናል ።»

«ቆይ ! ቆይ !» አለ ዲክ ። «በፖሊሶች ባይያዙስ ምስጢሩን የሚጠብቁ ዓይነት ሰዎች ናቸው? በየቦታው ስለኛስ አያወሩም ?»

«ለዚህ ምን ጥርጥር አለው ? ከሁለቱም ጋር ብዙ ሥራ አብረን ሠርተናልና ዐውቃቸዋለሁ ። ሆኖም እነርሱ ወሬውን በሚያናፍሱ በት ወቅት እኛ ከአገር ልንወጣ እንችላለን ። ይልቅስ መጠጥ እንድ ግም ! ያሁኑን እኔ እከፍላለሁ» ብሎን መጠጥ ደገምን ።

ዲክን ለብቻዬ እሸኘዋለሁ በማለት ሒሳቡን በሙሉ እኔ ከፍዬ ተለያየን ።

☆ ☆ ☆

ለሦስት ሳምንታት ያህል ፣ ቢያ በመሆን ከጃክ ጋር ሳንለያይ አብረን ከረምን ። የዘረፋ ቀናችን እየተቃረበ ሲሔድ ፣ ካንች ጋር በመሆኔ ጥሩ ዕድል ሳያጋጥመኝ አይቀርም» አለኝ እየሣቀ ።

«ልክ ነህ» አልኩት ።

ጃክ የጽዳት ሠራተኞች ቱታ ለማግኘት ችግር አልገጠመውም ። የላውንደሪ ባለቤት የሚል መታወቂያ ይዞ ወደ ቦኖሞ የጽዳት ሥራ ድርጅት በመሔድ ስሙን ሳም ሐሪሰን ብሎ በመቀየር የላውንደሪው ባለቤት እንደ ሆነ አድርጎ አስተዋወቀ ። አዲስ ድርጅት በመሆኑ በስልክ ማውጫ ላይ እንዳልተመዘገበም ገልጾ፡ «ካስፈለገ በዚህ ቁጥር ደውለው ሊገናኙን ይችላሉ» አለው የድርጅቱን ኃላፊ ።

እኔም ከጃክ ጋር እንደ ተመካከርነው ፋንገሎ ቡና ቤት ስልኩ አጠገብ ተቀምጬ እጠብቅ ነበር ። ስልኩ እንደ ጮኸ አነሣሁትና «ላውንደሪ ቤት ነው» አልኩኝ ።

«ደህና አደራችሁ ! እናንተ ድርጅት ሳም ሐሪሰን የሚባል ሠራተኛ አለ ?»

«አዎ ! ሚስተር ሳም የድርጅታችን ኃላፊ ናቸው ። አሁን ግን ደንበኞችን ለማነጋገር ወደ ውጭ ወጥተዋል ። የሚፈልጉዋቸው ከሆነ መልእክት መቀበል እንችላለን » አልኩኝ ።

«ግዴለም ተይው» በማለት ስልኩን ዘጋው ።

ጃክ ከኃላፊው ጋር የሠራተኞችን ቱታ ለማጠብ ተስማማ ። ድርጅቱ ከዚህ በፊት ለአጠባ ከሚከፍለው ዐሥር በመቶ የሚቀንስ ስለ ሆነ ፣ ያለ ምንም ማወላወል ብዙ ቱታዎች አስረከበት ። ጥርጣሬ እንዳይኖር ቱታዎቹን በሌላ ላውንደሪ አሳጥቦ ስድስት ቱታ ብቻ በቀጥር በማምታታት አስቀርቶ ሌላውን አስረከባቸው ።

«አየሽ ምን ያህል ቀላል እንደ ሆነ ?» አለኝ ፡ ቱታዎቹን እያሳየኝ ። ወዲያው የአንድ ሰው አድራሻ ፈለገና ስልክ ደውሎ በአራት ሰዓት ላይ ለመገናኘት ቀጠሮ ተቀበለ ። በጣም ገረመኝ ። በከፍተኛ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሠሩ ሰዎች አንዳንዶቹም ከሌቦች ጋር ግንኙነት አላቸው ! የሚገርም ነው ።

ጃክን በቀጠሮው ቦታ ለማድረስ ፎርድ መኪናዬን ይዤ ስሔድ ፡ «የምገናኘው በጣም ትልቅ ሰው ነው ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የተሰረቁ ንብረቶችን ወደ ተፈለገው ቦታ በማጓጓዝና በመግዛት የታወቀ

ነው ። ታይዋለሽ» አለኝ ። እቦታው ስንደርስ ቢሮውን አይቼ ማመን አቃተኝ ። ትልቅ ድርጅት ነው ። ወደ ውስጥ ስንገባ ጸሐፊዋን አገኘ ናት ። ወፍራም ስትሆን ለሥራው ብዙ የምትጨነቅ አትመስልም ።

ጃክን እየተመለከተች ፣ «ምንድ ነው ?» አለችን ።

«ከሚስተር ኮን ጋር አውን በስልክ ተነጋግረን ቀጠሮ ሰጥቶናል ። እኔም ሞሪሰን እባላለሁ» አላት ።

«እሺ! ቆይ ልጠይቅ» ብላን ወደ ውስጥ ገባችና ተመልሳ «ግቡ!» አለችን ። ውስጥ ስንገባ በጣም ያረጀ ሽማግሌ ቁጭ ብሏል ። ክፍሉ ጠባብና በጣም ሞቃት ነው። ሰውየው ግን ደራርቦ ለብሶ ሻይ ይጠጣል ። ከፍሉ ውስጥ ከአንድ ጠረጴዛና ከአንድ ወንበር በስተቀር ምንም ነገር የለም ። አዲስ ቢሮ ገብቶ ዕቃው እስከ ሚመጣለት የሚጠብቅ ሰው ይመስላል ።

«ሚስተር ኮን ነዎት !» አለ ጃክ ፣ ሁለታችንም ገብተን እንደ ቆምን ።

ሽማግሌው ቀና ብሎ ተመለከተን ። ፊቱ ከመጨማደዱ የተነሣ የመንገድ ካርታ ይመስል መስመር ይበዛበታል ።

«ምን ልታዘዝ ?» አለ በለሆሳስ ድምፅ ።

«ሞሪሰን እባላለሁ ፤ እሷ ባለደረባዬ አውገስ ትባላለች» አለ ጮክ ብሎ ።

«እሺ !»

«ቅድም በስልክ እንዳነጋገርኩዎት አድራሻዎን የሰጠኝ ሚስተር ዊንዞ ነው ። ከፊለጉ ደውለው ማጣራት ይችላሉ ።»

«ዐውቃለሁ ምንድን ነው የምትፈልገው ?»

«በታጎሚሥ አጋማሽ ከፍተኛ ንብረት ይኖረኛል ፤ ለመግዛት ገንዘብ ሊያዘጋጁ ይችላሉ ?»

«ምን ዓይነት ዕቃ ?»
«በጣም ውድ የሆኑ ሰንቁዎች ፣ አልማዞችና ወርቆች»
«ከዋጋው ዐርባ በመቶ ይስማማሃል ?»
«አይሆንም ! ጌጣጌጦች ውድ ናቸው ፤ ስልሳ ከመቶ ከሆነ ጥሩ»
«እስቲ እናያለን !»
«ተስማምተዋል ማለት ነው ?»
«እናያለን ነው ያልኩት ፣ ጊዜው ሲደርስ ደውልልኝ ።»

«ጥሩ ነው እንዳገኘሁ እደውላለሁ»

ስንገባ ሽማግሌው ያየኝ በጨረፍታ ነው ። ልንወጣ ስንል አንቺ ልጅ ብሎ ጠራኝና፣ «ይሄ ጡትሽ እውነተኛ ጡት ነው ?» አለኝ ።

«አይደለም !» አልኩት ።

«እኔም አልመሰለኝም ነበረ» ብሎ ሻዩን መጠጣት ሲጀምር ወጣን ። በኔ በኩል ንግግሩ የተሳካ አልመሰለኝም ። ጀክ ግን እንደ ተሳካ አድርጎ ነበረ የወሰደው ። «ዋናው ነገር ሰውዬው ደስ ብሎ ታል ። ደግሞም እምቢ አላለም ። ዕቃዎችን ሳያይ እሺ አይልም ፤ ይህ ንጉም ዊንዞ ነግሮኛል» አለኝ ።

«ቢሮው ሲታይ ገንዘብ ያለው ሰው አይመስልም !»

«ሰነዶች እንዲያስቀምጥ ትፈልጊያለሽ ? ሽማግሌው የሚፈጽ ማቸውን ስምምነቶች ሁሉ በጭንቅላቱ ነው የሚመዘግበው ። እንደ ተሳካልን እንደውልለትና እንገናኛለን ፤ ያኔ ታይዋለሽ ።»

ሁለቱ ሰዎች ማለትም ሆሊ ጐስትና ሄሚ ጐር ከዘረፋ በኋላ መኪናዎችን የምንደብቅበት ጋራዥ ፍለጋ ይዞሩ ስለ ነበር፣ እነሱን ፈልገን አገኘንና ያገኙትን ጋራዥ ለማየት ሔድን ።

ሁለቱም ከመኪና ኋላ ተቀምጠው ጋራዡን አሳዩን ። ጋራዡ ከሦስት ዓመት በፊት የተዘጋ ከመሆኑም በላይ ጭር ብሏል ። ማታ ማታ በሚዘዋወሩ ዘበኞች የሚጠበቅ ሲሆን ፣ ቀን ግን ጠባቂም እንደ ሌለው ነገሩን ።

ቦታው አመቺ ሆኖ ስለ አገኘነው ተስማማንበት ።

የዚያን ዕለት ማታ ዲክ መኖሪያ ቤት ሆኜ እራት እየበላን ስለ ቱታው መግኘት ፣ ጌጡን ከሚገዛን ሰው ጋር ስለ አደረግነው ውይይትና ስለ ጋራዡም በዝርዝር ነገርኩት ።

«ጥሩ ነው ! ለመሆኑ መቼ ነው ይህ ዘረፋ ከመፈጸሙ በፊት የምንሠወርባቸው ? »አለኝ በመጨነቅ መልክ ።

«ለመውጣት ችግር አይደለም ። እንደ ነገ ሊዘረፍ እንደ ዛሬ በምናደርገው ስብሰባ ላይ መገኘት እፈልጋለሁ ። የዚያኑ ዕለት ማታ ቢያ የሚያሰጉኝን ልብሶቼንና ዕቃዎቼን ይገር እጠፋለሁ ።»

«ድንገት እኛ በሌለንበት ዘረፋውን ቢሞክሩትስ ?»

«አይሞክሩትም ! ይርብ ዕለት ጥዋት በቀጠሮ ቦታችን ሲያጡን ፈርተን የቀረን ወይም ለፖሊስ ለመናገር የሔድን ይመስላቸዋል ።

ስለዚህን ዕቅዳችን እንደ ፈረሰ ስለ ሚያውቁ ከኛ ውጭ በራሳቸው አይሞክሩም ።»

«ልክ ነው !» አለና የተመገብንበትን ሳህን ገፋ በማድረግ፡«ሰዎቹ ግን አያሳዝኑሽም ?» አለኝ ።

«ባንድ መልኩ ያሳዝኑኛል ።»

☆ ☆ ☆

የጽዳት መኪና የጮኽ ቊጥር ዐሥራ አራትን እኔና ጃክ እየተከታተልን እያለን ፡ «ቢያ ለብቻሽ ላናግርሽ እፈልግ ነበር ። አሁን ጥሩ አጋጣሚ ነው ። ከዚህ በፊት ብዙም ስለ አልተዋወቅን አላነጋሁትም ። አሁን በደምብ ተዋውቀናል ። ነገሩን ማንሣት እፈልጋለሁ» አለኝ ።

«ስለ ከፍያው ነው ?»

«አዎ ! ብዙ ወጪዎች አንዳወጣሽ እገምታለሁ ። የሚያስፈልጉንን ዕቃዎች ሁሉ የገዛሽው አንቺ ነሽ ።»

«ግዴለም አትጨነቅ ፡ ወጪው ይሄን ያህል አይደለም ።»

«ለሁለቱ ሰዎች ዐሥር ሀሥር ከመቶ ስንሰጥ ቀሪው ሰማንያ ከመቶ ይሆናል ። የሐሳቡ ባለቤትና አለቃችንም አንቺ ስለ ሆንሽ ሠላሳ አምስት ከመቶ ላንቺ ፡ ለኔ ሐያ አምስት ከመቶ ፡ ለዲክ ሐያ ከመቶ ለምን አንከፋፈልም!»

«በኔ በኩል ይስማማኛል ፤ዲክ ግን በሐያ ከመቶ የሚስማማ አይመስለኝም ።»

«በዘረፋው ዕቅድ እስካሁን ምን አስተዋጽኦ አድርጎ ነው ቅር የሚለው ?»

«በዘረፋው ዕቅድ የመጀመሪያው ተሳታፊ ነው ።»

«ይሁን ! ግን አብዛኛውን ሥራ የሠራነው እኔና አንቺ ነን ።»

«ጥሩ ! አነጋግረዋለሁ ፤ቅር ሳይለው ሐያ ከመቶ እንዲወስድ አግባባዋለሁ ።»

«ብታነጋግሪው ጥሩ ነው ። ለመሆኑ ምን ያህል ትቀራረባላችሁ?»
«ትቀራረባላችሁ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው ?»
«ማለቴ በመኻላችሁ ያለውን መቀራረብ ማወቅ አልቻልኩም ። ወንድምሽ እንዳልሆነ ይገባኛል ። ነው እንዴ ?»
«አይደለም ። እንዴት እንዲህ ልታስብ ቻልክ ?»

«አላውቅም ! አንዳንዴ ተመሳሳይ ሥራ ትሠራላችሁ ፣ አልፎ አልፎም የምትሰጡትና የምታስቡት ሐሳብ አንድ ዓይነት ነው ። በሁለታችሁ መኻከል (የወሲብ) ግንኙነት አለ እንዴ ?» ፥

«ዲክን የማውቀው እዚህ አይደለም ፣ ምዕራብ በነበርኩበት ጊዜ ነው የተዋወቅነው። ኒውዮርክ ተገናኝን፤ይበልጥ ጓደኛሞች ሆንን»

«በጣም የቅርብ ጓደኛሽ ነው ?»

«አዎ ! ብዙ ጊዜ አብረን ስለ ቆየን የቅርብ ጓደኛዬ ነው ።»

«ቢያ» አለኝ ለስለስ ባለ ድምፅ ፣ «ይህን ያህል የሚያስቸግር ሰው ስላልሆነ ምንም ሳናካፍለው ልንጠፋበት እንችላለን ። የትም ሊያገኘን አይችልም ።»

«አይሆንም ፤ ይህን አላደርገውም ።»

«ቢያንስ በሽያጩ ልናጭበረብረው እንችላለን ። በዚህ የተወሰነ ገንዘብ ሰዋተነው እኔና አንቺ ሀብታም መሆን ብንሞክርስ ?»

ፊቴን ወደ መስኮቱ አዞርኩና ወደ ውጭ እየተመለከትኩ ፣ የማለላስል በመምሰል ፣ «አስብበታለሁ» አልኩት ።

«አስቢበት ! . . . ይሄው ልሽ መኪናው መጣ ፤ሱቁ ከመድረሱ በፊት ሁለት ቦታ ይቆማል !»

በርቀት ቀስ እያልን መከተል ጀመርን ።

ከዚያ በኋላ ጀክ ሰለ ክፍያው አላነሣም ። እንደሱ ሐሳብ ዘረፋው የሚከናወን ቢሆን ሁሳችንንም ጉድ አድርጎ ሊጠፋ እንዳሰበ ገባኝ ።

በእኔ ቤት ለመጽሐፉ ስል ብቻ የማላደርገውን የዘረፋ ሐሳብ በድንገት አቋሜ ስደበቀው የሚሰማው ንዴት እየታየኝ አዝኘለት ነበር ። አሁን ግን በልኩ እኔንና ዲክን ፣ እነኛንም ሁለቱ ሰዎች አምስት ሳንቲም ሳያቀምሰን ለመጥፋት የሚያብሰለስል መሆኑን ስረዳ ፣ ‘ይህ ሁሉ ዕቅድ ቢከሽፍ ለእንደዚህ ዓይነት መጥፎ ሰው እንዴት ይታዘናል ?’ የሚል ሐሳብ አደረብኝ ።

«እንግዲህ ከመጀመሪያው ሱቅ ደረስን ፣ ስንት ሰዓት ሆነ ?»

ማስታወሻየን በማየት፡ «ልክ እንዳቀድነው ሁለት ሰዓት ከሩብ ነው ። ከመኪናው ሲወርዱ አይተኻቸዋል ። የፊቱንም ሆነ የኋላውን በር አልቆለፉትም » አልኩት ።

«እርግጠኛ ነሽ ?»

«አይደለሁም ፣ ግን ሲመለሱ እናያቸዋለን » እንዳልኩት ሲመጡ ዝም ብለው በሩን ከፍተው ገቡ ።

«እውነትሽን ነው አይቆልፉትም ፤ በጣም ዐዋቂ ነሽ ።»

«ስለዚህ ከእዚህ ከመነሣታቸው በፊት እኛ ሰዎቻችንን መኪና ውስጥ ማስገባት እንችላለን ። ሥራቸውን ጨርሰው ወደ መኪናው ለመግባት ሲመጡ እዛው እንዳለን መሣሪያ ደግሞ ግቡ ማለት ነው » አልኩት ።

ጮክ ብሎ በመሳቅ እቅፍ አድርጎ ሳመኝ ።

ኃይለኛ ቅዝቃዜ ያለበት ጥሞት ነው ። ነገር ግን ወዲያው ላብ አጠመቀኝ ። በሕይወቴ እንደዚህ ተጨንቄ አላውቅም ። ምን በማድረግ ላይ እንዳለሁ ተረዳሁት ፤ እንደማልፈጽመው ዐውቃለሁ ፣ ግን በዚህ ብቻ አልተጽናናሁም ። እንዲያውም በሰዓት የሚፈነዳ ቦንብ ያጠመድኩና ውጤቱንም የምጠባበቅ መሰለኝ ።

«ምን ሆነሽ ነው የምትንቀጠቀጪው ። በረደሽ እንዴ ?»

ጥርሴ ሁሉ እየተንቀጫቀጨ፡ «አዎ» አልኩት ።

«መኪናውን አቁሚና ሻይ እንጠጣ፡ጉዳያችን እየተቃረበ ሲሔድ እንድትታመሚ አልፈልግም ።»

☆ ☆ ☆

የገና ሰሞን እየተቃረበ በመምጣቱ፡ የከተማው ሰው በሙሉ የስጦታ ዕቃ ለወዳጅ ዘመድ ለመግዛት ወዲያና ወዲህ ይላል ። የሸቀጣ ሸቀጥና የጌጣጌጥ ሱቆች ሁሉ ከወትሮው የተለየ አሸብርቀዋል ።

በየመንገዱም የሰካራሙ ብዛትና ረብሻ ከምንጊዜውም የተለየ ነው ። በዚህ ግርግር ውስጥ አንድ የጌጣጌጥ ሱቅ ቢዘረፍ፡ ሊሆን የሚችል ስለ ሆነ መጽሐፌን እውነተኛ እንደሚያደርገውና አንባቢም እንደሚያምንበት ተረዳሁ ።

እስከ ከሰዓት በኋላ ተኝቼ ተነሣሁ ። አልጋ አንጣፊዋ መጣችና ማንጣጠፍ ስትጀምር አንድ መለኪያ ቮድካዬን ጨልጬ ወደ መደበኛ ቤቴ ለመሔድ ወጣሁ ።

እቤቴ እንደ ደረስኩ በማስታወሻዬ የያዝኩትን ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ ለመጽሐፌ አመቺ በሚሆን መልኩ እያቀነባበርኩ ሳዘጋጅ አመሸሁ ። ጽሑፌ ከማስታወሻነት ወደ ረቂቅ መጽሐፍነት ተሸጋገረ ። በዚህ ረቂቅ ውስጥ በምስጢር የያዝኳቸውን ጉዳዮች አሰፈርኩ ።

ጽሑፌን እንደ ጨረስኩ ትንሽ ስፖርት ሠራራሁና ሰውነቴን ተጣጥቤ ፒጃማዬን ለበስኩ ። መጠጥ ቀዳሁና እየጠጣሁ ስለ አዲሱ መጽሐፌ ዝግጅት የደረስኩበትን ደረጃ ለአልዶ ባይንደር ደብዳቤ ጻፍኩ ። ወዲያው ሐሳቤን ቀይሬ ደብዳቤውን ቀድጄ ጣልኩት ።

እኩለ ሌሊት ላይ ከእንቅልፌ ነቅቼ ሬዲዮ ማዳመጥ ጀመርኩ ። የተለያዩ የዓለም ዜናዎች ከተላለፉ በኋላ ፡ ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ መጣሪያ የያዙ ስድስት ሰዎች በከተማው ውስጥ ከሚታወቀው ትልቅ የጌጣጌጥ ሱቅ ቀን በቀን ፡ ግምቱ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን ንብረት መዝረፋቸው ተነገረ ።

ሬዲዮኑን ዘጋሁና ፡ ሁለት ሚሊዮን ብር . . . ስድስት ሰዎች ! እንዴት ፈጣን ቢሆኑ ነው ። ፖሊሶች የኤሌክትሪክ ማስጠንቀቂያ ውን እየሰሙ እንዴት ቶሎ መድረስ አቃታቸው ? በዚህ ዓይነት የኤሌ ክትሪክ መጣሪያዎች ዋጋ የላቸውም ማለት ነው ። በዕቅዳቸው መሠ ረት ያለ ምንም ችግር ተሳክቶላቸዋል ። እርግጠኛ ነኝ ጃክም ስለ ሳን ፍራንሲስኮ ዘረፋ ሬዲዮ ያዳምጣል ። አሊያም በነገ ጋዜጣ ላይ ያየዋል።

ለዲክ እኛ እስካልተሳተፍንበት ለመዝረፍ አይችሉም ብዬ የነ ገርኩትን እንደገና ማሰላሰል ጀመርኩ ። ቢሞክሩና ቢያዙስ ? የዘ ረፋውን ሐሳብ ያመነጨችው ቢያ የምትባል ናት ብለው ይናገራሉ ። ወዲያው ጋዜጣ ላይ ይወጣል። 'የኋላ ኋላ መያዜ ይቀራል?' እያልኩ በሐሳብ ስጥላላ ቆይቼ የእንቅልፍ ኪኒን ዋጥኩና ተኛሁ ።

ቅዳሜ ጧት ከእንቅልፌ ተነሥቼ በሬዲዮ የሰማሁትን ለማረጋገጥ ጋዜጣ ገዛሁ ። ማንበብ ጀመርኩ ፡ ስድስት መጣሪያ የታጠቁና ፊታ ቸውንም የሸፈኑ ሰዎች በሳንፍራንሲስኮ ከተማ ውስጥ ዴቨልት ክሮስ የተባለውን ዕውቅ የጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ ከምሳ ሰዓት በኋላ እንደ ተከፈተ ሮጠው በመግባት ሁለቱ በሠራተኞችና በገበያተኞች ላይ መጣሪያ ሲደግኑ ፡ አራቱ ሰዎች ምርጥ ምርጥ የሆኑትን ጌጣጌጦች በመ ምረጥ መውሰዳቸውን ሲገልጽ ፡ የኤሌክትሪክ ማስጠንቀቂያው ለፖ ሊሶች የተሰማ ቢሆንም ፡ ፖሊሶች ከመድረሳቸው በፊት ሌቦቹ በሁለት መኪና በመሆን ሊያመልጡ እንደ ቻሉ ያትትና በተለይ ከዘራፊዎቹ አንዱ ከመውጣቱ በፊት የሱቁ መዝጊያ ወደ ውጭ የሚከፈት በመ ሆኑ ፡ በሩ ቶሎ እንዳይከፈት የሚረዳ የበር ማቆሚያ ላስቲክ እበሩ ሥር ተዝናንቶ በማስገባት መሐዱን ይገልጻል ።

በዚህ ዓይነት እኛም ለመዝረፍ የተዘጋጀነው የሱቅ በር ወደ ውጭ የሚከፈት ስለ ሆነ ፡ ይህን የበር ማገጃ ላስቲክ ጃክ ሊገዛ እንደ ሚችል ገመትኩ ።

ቅዳሜ ማታ በአልቤርጎ አሳለፍኩ ። ጃክን ግን አላገኘሁትም ።

እሑድም ጃክንም ሆነ ሌሎችን ማግኘት አልቻልኩም ። ግራ ተጋባሁ ። ወደ መደበኛ ቤቴ ሒጄ ለዲክ ፥ ለላውራና ለሶልፋበር ስልክ ደወልኩ፤አጣሁዋቸው። 'ሰውን ሁሉ ምን በላው?' በሚል ግራ ተጋባሁ።

ወደ ምግብ ቤት ሔድኩና ራቴን ለመብላት ሞከርኩ ፥ አልጥምሽ ስለ አለኝ ጥየው ወጣሁ ።

መጀመሪያ ወደ ቤቴ ልመለስና ከዚያም ወደ አልቤርጎዬ ልሒድ ብዬ ወደ ቤቴ ስገባ ስልኩ ይጮኻል ፥ አነሣሁት። ሚስተር ጄርቪስ ነበር የደወለው ።

«ሦስት ቀን ሙሉ በተከታታይ ብደውል አጣሁሽ ። የት ሔደሽ ነው ?»

«ለገና በዓል አንዳንድ ዕቃዎችን ለመግዛት ወጥቼ ነበር ። ሥራ እንዴት ነው ?» አልኩት ።

«በጣም ጥሩ ነው፤ይሄን ሰሞን ገበያተኛ ሞልቷል ። አሁን የደ ወልኩት ሰኞ ማታ እቤቴ እራት እንድንበላ ልጠይቅሽ ነበር ።»

«እሺ» ብዬው ስልኩን ዘጋሁት ።

እሑድንም አልቤርጎ አደርኩኝ ። ሰኞ ጥዋት ወደ ሁለት ሰዓት ላይ ጃክ መጥቶ መተኛቴን አይቶ መመለሱን ከአልጋ አንጣፊዋ ሰማሁ።

ወደ መደበኛ ቤቴ ተመልሼ ቀኑን እዛው ዋልኩና ወደ ቀጠሮዬ ቦታ ለመሔድ ስዘገጃጅ ወደ ፀሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ስልኬ ጮኸ ። አነሣሁት ፤ ሚስተር ጄርቪስ ይቅርታም ሳይጠይቁኝ ዛሬ የሱቃቸውን ንብረት ቆጠራ ስለሚያካሒዱ ሥራ እንደ በዛበትና እንደ ማይመቸው፤ ማክሰኞ ማታ ግን እንደምንገናኝ ነግሮኝ ስልኩን ዘጋው ። ለዚህ ሰው ምን ዓይነት ይቅርታ ይደረግለታል? ማክሰኞ ማታስ መሔድ አለብኝ?

በዚያን ጊዜ ምን እንደ ሚሰማኝ ፥ ጃክንም ለሦስት ቀን እንዳ ላየሁት ፥ ስለ ሳንፍራንሲስኮ ዘረፋና ስለ በር ማቆሚያ ላስቲክ ለዲክ ለማውራት ፈልጌ ወደ ቤቱ ስልክ ብደውል የመጥራት ድምፅ ያሰማል ፤ የሚያነሣ ግን አልነበረም። 'ሰው ሁሉ ምን ሆነ? ምንድነው ነገሩ?' አልኩኝ ለራሴ ።

ማክሰኞ ለት ወደ ተለመደው ተግባሬ ተመለስኩ ። ምሳ ከጃክ ጋር በላን ። እንደ ገመትኩት ስለ ሳንፍራንሲስኮ ዘረፋ አንብቦ ስለ በር ማቆሚያ ላስቲኩም አንሥቶ የወቂ ሥራ በመሆኑ እሱም ሁለት ላስቲክ እንደ ገዛ ነገረኝ ።

ሐሙስ ለት ማታ ፣ አምስታችንም በምዕራብ ዐርባ ሰባተኛው ጐዳና አጠገብ በሚገኘው ጋራዥ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል እንድ ንገናኝ ተቀጣጠርን ።

ኰስተር ብዬ «የሚሰረቀውስ መኪና ?» አልኩት ።

«ለሱ አትጨነቂ ፤ ሁል ጊዜ አንድ ቦታ የሚያድር አራት በር ያለው ሾፍረሌት ፣ ሄሚና ጐስት አግኝተዋል » አለኝ ።

«ጥሩ ነው ተጨማሪዎቹ ሁለት ሰዎችስ የት አሉ ?»

«ዝግጁ ናቸው ፣ በሚደርሳቸው አምስት በመቶ ተስማምተዋል ። አንቺና ዲክ ዐርብ ልክ ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ላይ በጋራዡ ትገኛላ ችሁ ። ሦስታችን የተሰረቀውን ሾፍረሌትና አስፈላጊዎቹን ዕቃዎች ይዘን እንጠብቃችኋለን ። ሁለቱ ሰዎች በሚያመቻቸው መንገድ ወደ አምሳ አራተኛው መንገድ ደርሰው ይጠብቃሉ ። ሁላችንም የጽ ዳት መኪናውን እንጠብቅና ለሥራ ወደ ሌላ ሱቅ ሲደርስ አምስታ ችን መኪናው ውስጥ ገብተን ሠራተኞቹ ሲመለሱ አስገድደን እናስ ገባቸዋለን ። አንቺና ዲክ በሾፍረሌቱ ሆናችሁ ትከታተሉናላችሁ ። ለማንኛውም ሐሙስ ማታ በሰፊው እንወያይበታለን ።»

«በደንብ አዘጋጅተኸዋል !»

ሣቅ እያለ፣ «ይሄን ሐሳብ መቀበል አለብሽ» አለኝና በዚሁ ተለ ያየን ።

ከአልቤርጎው የሚጠቅሙኝን ዕቃዎች ያዝኩና ወደ መደበኛ ቤቴ ተመለስኩ ። በመጨረሻ ከዚህ ድርጊት የመለያ ጊዜዬ ስለ ደረሰ በግማሽ ልቤ እፎይ ስል በግማሽ ልቤ ደግሞ ጭንቅ ጭንቅ አለኝ ።

የጀርቪስን ቀጠሮ አስታወስኩና እንደ ነገሩ ለባብሼ ወጣሁ ።

ካፖርቴን እያወለቀልኝ ምን የመሰለ እራት እያዘጋጀሁ ነው ብሎኝ ወደ ማድቤት ተከታትለን ገባን ። ወዲያው መጠጥ ለሁለታ ችንም ቀዳና ምግብ ማብሰሉን ቀጠለ ።

«የሱቃችሁን የንብረት ቆጠራ ጨረሳችሁ ?»
«ምን ?» አለኝ ቀና ብሎ ።
«ትላንት ያልከኝን ?»
«አዎ ጨርሰናል ።»
«ከገና በፊት ቆጠራ ማድረጋችሁ የተለመደ ነው ?»

«አይደለም ፣ አልፎ አልፎ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ቆጠራ እናደርጋለን ።»

«ምናልባት የተሰረቃችሁት እንዳለ ለማወቅ ነው ?»

«እረ አይደለም ! ብዙ ጊዜ አይጠፋብንም ፣ እንዲሁ ለውስጥ ቁጥጥር ስንል ነው ።»

«የውስጥ ቁጥጥር ! ሠራተኞቹን አታምናቸውም እንዴ ?»

«አምናቸዋለሁ ! ማመንም አለብኝ ። በየወሩ ቆጠራ የምናካሂደው ምናልባት ትናንሽ ጌጦች ሊጠፉ ይችላሉ በሚል ግምት ነው።»

የምግቡ ዓይነት ተዘርዝሮ የሚወራ አይደለም ። በጣም ጣፋጭ የሆነ የጣሊያን የባህል ምግብ ነው ። ወይን ጠጅም እየተጎነጨን በልተን አበቃን ።

«ለምን አታገባኝም ?» ስል ጠየቅኩት ።

በፈገግታ «በጣም ደስ ይለኛል» አለኝ ።

የበላንበት ሳህን ሲነሣ፡«አጠባ ላግዝህ አልኩት» ግን በሙሉ ልቤ አልነበረም ።

«ሞኝ ነሽ ! ጥዋት እንዴ መጥቶ ያጥበዋል ።»

«ማን ? ፖሊሶች ?»

«ከመቀመጫው በብሽቀት ተስፈንጥሮ በመነሣት ለምንድነው ይሄን ያልሽው !» አለኝ ፊቱ ደም መስሎ ።

«እንዴ ! ምን ነካህ ? ቀልድ አታውቅም ?»

እንደ ገና ወንበሩ ላይ ቁጭ አለና ፡«ቀልድ መሆኑ ገባኝ ። ፖሊሶች አይደሉም የጽዳት ሠራተኛዬ ናት ። ምግቡ ተስማማሽ ?»

«ቅድም ነግሬሃለሁ ፡እንዴ ዛሬ በልቼ አላውቅም ። በጣም ጥሩ ነው ።» ዝም ብለን በመጠጣት ላይ እንዳለን ፡ሰውነቱ ወዲያው እየዛለ ሐዲና ፡ «አንድ ነገር ልንገርሽ ?» አለኝ ።

«ንገረኝ» አልኩት ቀና ብዬ ።

«በሕይወቴ ሙሉ የምመኘው ምግብ ቤት ለመክፈት ነበር ። ግን ማነው የሚፈልገው የሚሳካለት ?» አለና ዝም አለ ።

«ስማ ! ባለፈው ሳንፍራንሲስኮ ውስጥ የተፈጸመውን ዘረፋ ሰምተሃል ?» አልኩት ወዲያው እንቅልፍ እንደሚወስደው ዐውቄ ።

«የበላኸውን እንዲያንሸራሽርልህ ብራንዲ ላምጣልህ» ብዬ ማድ ቤት ሐዲኩና ልክ እሱ የሚቀዳውን ያህል በመለኪያ ቀድቼ ይዤለት ተመለስኩ ።

ብራንዲውን ተቀበለኝና ፈገግ በማለት፣ «ለጤናችን !» አለኝ ።

ከወንበሩ ቢወድቅ ቶሎ ለማንሣት እንድችል ጠጋ ብዬ፣ «ጀርቪስ! አንተስ ሱቄ ቢዘረፍ ብለህ አታስብም ?» አልኩት ።

ተስተካክሎ ተቀመጠና፣ «የኛ ሱቅ ለዘረፋ የሚመች አይደለም . . . አይዘረፍም ! ! » አለኝ እርግጠኛ ሆኖ ።

«ጋዜጣውን በደንብ አንብበህ ከሆነ የማስጠንቀቂያ መሣሪያ እያላቸው እኮ ነው የተዘረፉት !»

«ዐውቃለሁ ዘራፊዎች ገብተው እጅ ወደ ላይ ሲሉኝ ደወሉን ለመንካት ስሞክር ይገሉኛል ። የኛ ግን የተለየ ነው ። ሌቦቹ ሳያውቁ ፖሊሶችን እንጠራለን ።»

«ከሌላው ሱቅ የተለየ ማስጠንቀቂያ እንደሚኖራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ ።»

«ልክ ነሽ ! ጐበዝ !»

«ከሁሉ ሱቅ የተለየ ?»

«አዎ ! ሱቃችንን ታውቂው የለ ? ግድግዳው አጠገብ ያለውን ወንበር ታስታውሻለሽ ?»

«አዎ ! አስታውሳለሁ ።»

«እሱ ማስጠንቀቂያ ነው ፤ ብዙ ጊዜ ሰው እንዳይነካው እንጠነቀቃለን። ጓዳ ላሉትና በአቅራቢያው ለሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ወንበሩ እንደ ተነካ ምልክት ይሰጣል ። ዘራፊዎች እጅ ወደ ላይ ሲሉን ፣ እጃችንን ወደ ላይ አድርገን በተቻለ መጠን ወደ ወንበሩ በመጠጋት በሰውነታችን መንካት ብቻ ነው የሚያስፈልገው ። ከዚያም ወዲያውኑ ፖሊሶች ይመጣሉ ማለት ነው ።»

«በጣም የሚገርም ነው ! ግን ፖሊሶች እስከሚመጡ ሌቦች ቢሐዱስ ?»

አንገቱን ዘንበል አደረገና እንደ መተኛት ብሎ ዝም አለ ። ቆይቶም ፣ «ፖሊሶች እስከሚመጡ ዐሥርና ዐሥራ አምስት ደቂቃ ቢፈጅባቸው ነው ። ወንበሩ ሲነካ ፖሊሶችን ብቻ መጥራት ሳይሆን ዋናው በር በኤሌትሪክ ስለሚዘጋ መውጫ አይኖርም » አለኝ ።

«ጀርቪስ በጣም ጥሩ ነው» አልኩት ። አልሰማኝም ፤ ሞልጥ ያለ እንቅልፍ ወዲያው ወሰደው ።

ማድ ቤት ሔጂ ዕቃዎቹን አጣጠብኩና ካሰናዳሁ በኋላ ሁለተኛ እንደማንገናኝ በማሰብ ወደ ቤት ሔድኩ ።

ቤት እንደ ደረስኩ ለዲክ ስልክ ደውዬ በመጥራት ፡ ስለ አስገራሚው አስጠንቃቂ ወንበር ለመንገር ፈለኩና ሰዓቴን ባይ እኩለ ሌሊት በመሆኑ ትቼው በሁኔታው እየተገረምኩ ተኛሁ ።

ረቡዕ ዕለት ጥዋት ስነሣ የማታው መጠጥ ራሴን አሳመመኝ። መድኃኒት ዋጥኩና ቡና አፍልቼ መጠጣት ስጀምር ስልኬ ጮኾ ሳነሣው ጄርቪስ ነው ። «ትላንት በሰላም አቤትሽ መድረስሽን ለማረጋገጥ ነው» አለኝ ።

«ያን ሁሉ ምግብና መጠጥ አስፈጅተህ ራሴን ስለ አሳመምከኝ በጣም ጠላሁህ» አልኩት ።

«እኔንም አሞኛል» አለኝ ፡ ድምፁ ግን የጤነኛ ሰው ነው ።

«ጄኒ የእውነት ካመመሽ ኮኛክ ወይም ብራንዲ አቤትሽ አለ . . . አይደለ? ውኃም ሆነ በረዶ ሳትጨምሪ አንድ መለኪያ ደረቁን ጠጪ ፡ በሐያ ደቂቃ ውስጥ ትድኛለሽ ፡ ታደርጊዋለሽ ?»

«አዎ አደርገዋለሁ» በማለት አመሰግኘ፡ ስልኩን ዘግቼ እንዳለኝ አንድ መለኪያ ብራንዲ ቀድቼ ጠጣሁና ሰዓቴን ተመለከትኩ ። እንዲያውም ካለኝ ደቂቃ በፊት ጨመሙ እየተወኝ መጣ ። በራሴ ፊቃድ አንድ መለኪያ ቀዳሁና በደብቅ በምጽፈው ረቂቅ መጽሐፌ ላይ የማታውን ድርጊትና ከጄርቪስ የሰማሁትን ጻፍኩ ።

ሰውነቴን ተጣጥቤ ወደ አልቤርጎ አመራሁ ። እንደ ደረስኩ የጀኮን ክፍል አንኳኳሁት ፡ መልስ የለም ። አለመኖሩ ደስ አለኝ ።

ክፍሌ ገብቼ በዕቃ መያዣ ሳስቲክ የተወሰኑ ዕቃዎችን ያዝኩና ወጣሁ ። የአልቤርጎው አስተናጋጅ ቢያየኝም የምጠፋ አልመሰለውም ። እንዲያውም ዕቃዎቼን ብትዋቸው አይጐዳኝም ነበር ።

ባጋጣሚ አስተናጋጁ በዘወትር መቀመጫው ላይ አልነበረም ። ዶሎ ወጣሁና ወደ ቤቴ ሔድኩ ።

እቤቱ ደርሼ ዕቃዎቼን በመልክ በመልካቸው ማስቀመጥ ጀመርኩ ። አውቶማቲክ ቢሬታ ሽጉጤንም ከመጻፊያ ክፍሌ አወጣሁና መኝታ ቤት አንዱ መሳቢያ ውስጥ አስገብቼ ቆለፍኩበት ። ወዲያው ለዲክ ስልክ ደወልኩና፡ «እራት ለመብላት ሼዝ ሞሪስ ቤት እንገናኝ» አልኩት ።

«ጅኒ ! ለምን ወደ ተሻለ ቦታ ሔደን ጥሩ እራት አንበላም ?»

«ትላንትና ጥሩ ምግብ በልቻለሁ ። ዛሬ የምፈልገው ብዙ ላለ መብላት ነው ። ወደ ሦስት ኪሎ ያህል መቀነስ እፈልጋለሁ ። ብዙም የምነግርህ አለኝ ፤ እባክህ እሺ በለኝ? ከእራት በኋላ እኔ ቤት ተመልሰን በጣም ደስ የሚል ምሽት እናሳልፋለን ።»

«እሺ ይሁን» አለኝ በመደሰት መልክ ።

እንደ ተመኘሁትም ምግቡ ጥሩ አልነበረም ፥ ሦስት ጉርሻ ያህል እንደ ጐረስኩ ተውኩት ። በመጀመሪያ በምዕራብ ፀርባ ሰባተኛ መንገድ በሚገኘው ጋራዥ ስለ አለን ቀጠሮ ነገርኩትና «ትግኛለህ ?» አልኩት ።

«በምንም ዓይነት መቅረት የለብኝም»

«የጃክን ዕቅድ ስነግረው እየደጋገመ ፀይኑን ማሻሸት ጀመረ ።»
«ስሕተት አለው እንዴ ?»
«እንዴት ነው ሁለቱ ሰዎች በሰዓቱ የሚደርሱት ?»

«እኔ ምን ፀውቃለሁ፤ ጃክ የሚናገረው በሙሉ ልብ ነው ። ምና ልባት በታክሲ ሊደርሱ ይችላሉ ወይም መኪና ይሰርቃሉ ወይም የራሳቸው መኪና ይኖራቸዋል ።»

«ምንድነው ወይም! ወይም! አልሽ ። እኔ ነገሩ ደስ አላለኝም ። በደንብ የተዘጋጀ ዕቅድ አይደለም። እንዲያውም የጃክ ዕቅድ አይመስልም። እሱ ለራሱ ጠንቃቃ ሰው ነው። ታዲያ ይሄ ምን ይባላል? የእብድ ሥራ ነው ።»

ለትንሽ ጊዜ አሰብኩና፡ «ታውቃለህ! አንተ ልክ ነህ ። ብዙዎቹ ዘረፋዎች ከፍተኛ ጥናት ፥ ዕቅድና ማሰብ ይፈልጋሉ ። ሐሳብክን በከፊል እቀበላለሁ ። ግን ይሄ የጃክ ዕቅድ ነው ። ምናልባት ይሳካል ብሎ ገምቶ ሊሆን ይችላል። ብቻ እኛ ምን አስጨነቀን? ከሐሙስ ዕለት ማታ ጀምሮ የምናቋርጥ ስለ ሆነ ሁሉም ነገር ይቆማል ። አይደለም?»

ተያየንና «አዎ ምንም አያስጨንቅ» አልኩት ።

በመቀጠልም ከጀርቪስ ጋር ስለ አሳለፍኩት ምሽት ፥ ስለዚያ ልዩ ማስጠንቀቂያ ወንበርና ስለ ሳንፍራንሲስኮ ዘረፋ ነገርኩት ። ምንም አልተጨነቀም ።

«ስለዚህ ለመጽሐፍሽ ተጨማሪ ታሪክ አገኘሽ ማለት ነው ። ከዚህ በፊትም ስለ ስውየው ባሕሪ እንድታጠኚ ነግሬሽ ነበር ። ለመሆኑ ስለ ወንበሩ እንዴት አውጣጣሽው ?»

«ዋናው ነገር . . . ስለ ወንበሩና በሩ በኤሌተሪክ እንደሚዘጋ ለጃክ ልንገረው ወይስ አልንገረው ።»

ትንሽ ካሰበበት በኋላ፣«መንገር የለብሽም ። ብትነግሪው እንዴት ልታውቂ እንደ ቻልሽ ይጠይቅሻል ። ምን መልስ ልትሰጪው ነው?»

«ምናልባት ከኛ ተለይተው ለመዝረፍ ቢሞክሩና እዛው እንዳሉ በሩ ቢዘጋባቸውና ቢያዙስ ?»

«እና ! ቢያዙ ምን ችገረን ፤ ዝረፉ ብለን አላስገደድናቸው !»

«እኔ እንደምገምተው . . . . .»

እጄን ያዝ አደረገና፣«ጄኒ! ስለ እነሱ ወንጀል መሥራት ኃላፊነት እንደሚሰማሽ ይገባኛል ። ዕቅዱን ያወጣሽውና የሚዘረፈውን ሱቅ የመረጥሽው አንቺ ነሽ ወይም ሁለታችንም ነን ። ግን በግድ እንዲ ዘርፉ አላስገደድናቸውም ። አሁን ልክ እኛ እንደምናደርገው ማቋረጥ ይችላሉ ። በራሳቸው ሞክረው ቢያዙ የራሳቸው ስሕተት እንጂ የኛ አይደለም ። ደሞም ሰዎቹ የለመዱ ወንጀለኞች እንጂ፣ እኛ ገፋፍተን ወንጀለኛ እንዲሆኑ አላደረግናቸውም ።

ራሴን ነቀነቅኩና . . «የሕሊና ዕረፍት የማገኝ አልመሰለኝም ። የምትለው ትክክል ነው ። እነዚህ ደንቆሮዎች ቢሞክሩና ቢያዙ ወይም ከመኻከላቸው አንዱ አደጋ ቢደርስበት፣ በከፊል እኔም በራሴ ተወቃሽ ነኝ ። በሌላ በኩልም ለፖሊሶች ስለኛ መናገራቸው አይቀርም ።»

«ምን የሚናገሩት ነገር አላቸው? ቢናገሩስ የሚያውቁሽ በቢያ ነትሽ ምን እንደምትመስይ ፣ አድራሻሽ የት እንደ ነበር እንጂ ፣ ስለ እውነተኛዋ ጄኒ ሼን አይደለም ።»

«እኔንም ብሆን ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ከሚኖሩ በብዙ ሺ ከሚ ቆጠሩ ሰዎች አልለይም ። ሌላው ቀርቶ የት እንደምኖር አያውቁም ። ስለዚህ ጄኒ ምንም የሚያስጨንቀን ጉዳይ የለም ።»

ወደ ቤቴ እየተጓዝን ይህንኑ ስንነጋገር ቆይተን ፣ እቤት ከገባንና ከተኛንም በኋላ ውይይታችንን አላቋረጥንም ። በሚቀጥለው ቀን ማታ ከችግሩ የምንላቀቅ መሆኑንና እነጃክም ቢሆኑ ብቻቸውን ለመ ሞከር ይሄን ያህል እንደማይደፍሩ ነገረኝ ። ያለኝን ሁሉ አመንኩ ።

«ብቻየን መሆን ስለ አስጠላኝና አልጋየንም እንዲያሞቅልኝ አይ ደለም እንዴ አብረን እንደር ያልኩት? ስለዚህ ለምን እጨነቃለሁ አልኩና እቅፍ አድርጌው እንቅልፍ ወሰደኝ ።

ሐሙስ ጠዋት ከጃክ ጋር ተገናኘን ። ሁኔታውን እስከ መቼም አልረሳውም ። በፍጥነት ይናገራል ። ሀይኑ ሁሉ የተለየ ሆኖአል ። የደነዘዘም ይመስላል ፣ በመጠጥ ወይም በዕፅ አይደለም ። እጁንም ያርገበግባል ። እየተጠጋኝ ማታ ስለሚኖረን ስብሰባ ይነግረኝ ጀመር ።

መኪናሽን ትንሽ ራቅ አድርገሽ አቁሚ ፤ ከዚያ ከዲክ ጋር በእ ግራችሁ ልክ ሀሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ጋራዡ ድረሱ ። በዚያን ሰዓት ዘበኛው የሚዘዋወርበት ነው ። እኛ ቀደም ብለን ገብተን እንጠብቃለን ። በሩ ሲከፈትላችሁ ትገባላችሁ ፤ወዲያው ስለ ነገው ፕሮግራም ተነጋግረን እንወጣለን ፣እሺ? እሺ ?»

«ጃክ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ረጋ በል ፤ምን ነካህ? መጠጥ ልቅ ዳልህ? ትክክል አትመስለኝም ።»

ቆጣ በማለት ፣«ለመጠጡ ወደ ፊት ብዙ ጊዜ አለን ፤ መጀመሪያ ንብረቱ ይገኝ ። ቢያ ሰመሆኑ ነገ በዚህ ሰዓት ሀብታም እንደምንሆን አስበሻል ?»

«ልክ ነህ ፡ አሁን ግን ረጋ ብለህ ባይህ ደስ ባለኝ ነበር ! እስቲ ቁጭ በልና አንድ መለኪያ ቮድካ ቅመስ ።»

«እቸኩላለሁ ፡ ብዙ የምሠራው ሥራ አለኝ ። ይሁን አንድ መለ ኪያ ልጠጣ ።»

ለሁለታችንም ቮድካ በደንብ ሞልቼ እየቀዳሁ ፡«ምን ዓይነት ሥራ ነው ያለብህ ?» አልኩት ።

«ለሁለቱ ሰዎች የት እንደምንገናኝ መንገር አለብኝ ። እንዲሁም ሂሚ መዶሻ ማግኘት ስለ አልቻለ ፣ የሚገኝበትንና ቁታዎቹ ልካችን መሆናቸውን ፣ ሌላም አስፈላጊ ዕቃዎች ሁሉ መዘጋጀታቸውን ማረ ጋገጥ አለብኝ ። ቢያ ባለሱቆች ምን ዱብዳ እንደ ወረደባቸው ሳያው ቁትና ፣ አንድም ጉዳት ሳይደርሰብን ይሳካልናል ። ይሄ ከሳንፍራን ሲስኮ የበለጠ ዘረፋ ነው የሚሆነው ። አይመስልሽም ?»

«ይሆናል . . . »

ለብዙ ሴኮንዶች በትዝብት መልክ ተመለከተችና ፡«ድርሻሽን ስትወስጂ ምን ታደርጊበታለሽ ?» አለች ።

«ከዚህ አካባቢ መጥፋት ነዋ !»

«ከዲክ ጋር ?»

«ምናልባት !» አልኩት፣ ትከሻየን ወደ ላይ ከፍ በማድረግ ። «እንዲያውም አንዳንድ ዕቃዎችን ወደ እሱ ቤት እየወሰድኩ ነው ።»

«ወሙቂያለሁ ፤ዕቃ መውሰድሽን አልጋ አንጣፊዋ ነግራኛለች » አለና ሣቅ አለ ።

«ይሄ የሚያስቀይምህ አይመስለኝም ፥ ማንኛውም አይጥ የራሱ መደበቂያ ጉድጓድ እንደሚያዘጋጅ ሁሉ ፥እኔም የራሴን ማዘጋጀቴ ነው ። በዘረፋው ምክንያት አንድ ችግር ቢመጣ እዚህ መጥተው ከአንተ ጋር እንዲይዙኝ አልፈልግም ። ንብረቱን እጄ ከማስገባቴ በፊት ቤት መቀየሬ ለትልቅ ጥንቃቄ ስል ነው ።»

በመደነቅ መልክ እያየኝ ፥«ጥሩ ጭንቅላት እንዳለሽ ከዚህ በፊት ነግሬሻለሁ ። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም ይሄን ለመልቀቅ አስቤአለሁ።»

«ድርሻችንን ስንከፋፈል መሸዋወድ አይኖርም ?» አልኩት በሽሙጥ ።

እየሣቀ ጉልበቴን በጁ መታ መታ አደረገና ፥«ሸውጂሽ አላውቅም ። አንቺ ለኔ ጠቃሚዬ ነሽ ። ለአሁኑ ሁለታችንም ስለምንፈላለግ ይሄን ማሰቡ አይጠቅምም። ይሄ አያጨቃጭቀንም ፤ሐሳቡን ሁሉ ያመነጨሽው አንቺ ባትሆኚ ኖሮ እዚህም ደረጃ ባልተደረሰ ነበር ። አሁን ቸኩያለሁ ልሒድ ፤እዚህ ትቆያለሽ ?»

ለተወሰነ ጊዜ አቅማማሁና ዕቃ መውሰዴን አንዴ ስለ ዐወቀው በማለት ፥«የቀረኝን ዕቃ ወደ ዲክ ቤት እወስዳለሁ ። አንተ ለባለ አልቤርጎዎቹ ቅዳሜ እንደምለቅ ንገራቸው» አልኩት ።

«በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ። ከእንደዚህ አስቀያሚ ሰፈርና ቁንጫ ከበዛበት አልቤርጎ መለየት ያስደስታል ። አይደለም እንዴ ?»

«ልክ ነህ» አልኩት ከልቤ ።

«አዎ! ከእንደዚህ ዓይነት ኑሮ ጋር የተለማመድሽ አይመስለኝም ።»

«ድርሻህን እንዳገኘህ የምትሔደው ወደ አውሮፓ ነው ወይስ ወደ ደቡብ አሜሪካ ?»

«አልወሰንኩም ። ብቻ. . .ዘረፋው እንደ ተፈጸመ ፖሊሶች ወደ ውጭ አገር የሚደረግ የአውሮፕላን በረራ ስለሚቆጣጠሩ ፥ለትንሽ ቀን በጣም አነስተኛ በሆነ ከተማ ውስጥ አሳልፋለሁ ። በእንደዚህ ዓይነት ከተሞች አዲስ መጤዎች ተለይተው አይታወቁም ። ከዚያ በኋላ ወደ ሚያሚ በመሔድ እኔን የመሰሉ ሰዎች ሊገኙ በማይችሉበትና ሰውም በሚበዛበት ሥፍራ እቆያለሁ ፤አብረሽኝ መሔድ ትፈልጊያለሽ ?»

ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ፤ እውነትም አነጋገሩ ከምሩ ይመስላል።

«በአንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ላይ እናተኩር ። መጀመሪያ ገን ዘቡ ይገኝና ከተሳካ በኋላ እወስናለሁ ።»

«ቢያ ጥንቆላ በይው ወይም ሌላ የሚሳካ ነው » ብሎኝ ወጣ ።

እንደ ሐደ ዕቃዎቼን መሰብሰብ ጀመርኩ ። ለስሙ እንጂ የያዝ ኳቸው ሻንጣዎች ባዶ ናቸው ። እታች ስደርስ አስተናጋጁን አግኝቼ ቅዳሜ በጠቅላላ እንደምለቅ ስነግረው ፣

«ከሰዓት በፊት መሆን አለበት ፤ ከሰዓት በኋላ ከሆነ የአንድ ቀን እናስከፍላለን » አለኝ ።

«ዐውቃለሁ ።»

«በድንገት ለመልቀቅ ምን አጋጠመሽ? ሥራ እንደልብ አልሆን አለ ?»

«እዚህ ሥራ ስላላገኘሁ ወደ ቺካጐ መሔዴ ነው ።»

«ቺካጐ ምን ይገኛል ?»

«እዛ ያለው አልጋ አከራይ በቀን በቀን ሰውነቱን ይታጠባል » አልኩት ።

እንደ እውነቱ ከሆነ መሳደብ ፈልጌ አልነበረም ። ግን ቢያነቴን የምሰናበትበት ሰዓት ስለ ሆነ ፣ ይሄን ብልግና መናገር ፈለግሁ ።

እቤት እንደ ደረስኩ ለዲክ ስልክ ደወልኩለት ። «ሥራ ስለ በዛብኝ ትንሽ ደቂቃ አሳልፌ ነው የምመጣው ፤ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል እንገናኝ» አለኝ ። ቤቱ ድረስ በመሔድ በተከራየሁት ፎርድ መኪና እንደምወስደውና ከስብሰባም በኋላ ለአዲሱ መጽሐፌ ሲባል መጠጥ እንደምጋብዘው ተነጋገርን ።

በቀጠሮአችን መሠረት ዲክ ቤት ሔጄ ወሰድኩት ። አንድ ጭር ባለ መንገድ አቁሜ እሱ መኪናውን እንዲነዳ ነግሬው የቢያን ልብ ሶችም መለባበስ ጀመርኩ ። ልክ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ከሩብ ሲሆን ጋራዡ አካባቢ ደረስን ።

«ሽጉጤን መያዝ ነበረብኝ» አልኩት እየሣቅሁ ።

«ምን ያረግልሻል ። ይልቅ እዚህ ከመንቀዋለል ቶሎ ባገኝ ናቸው ።»

ጃክ እንዳለን በወሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል የጋራዡ በር ተከፈ ተልንና ገባን ። ሄሚ በሩን ከኋላችን ሲዘጋው ጨለማ ዋጠን ፣ ትንሽ ትንሽ ጭላንጭል ብቻ ይታያል ።

«እንዴት ነው ሄሚ ?» የጃክ ድምፅ ነበር ።

«መጥተዋል ።»

«እንግዲህ በሩን ጠብቅ»

ክብሪት ተጫረና ሻማ ተለኮሰ ። ጋራዡ ሰፊ ሲሆን ስድስት መኪና ሊያቆም የሚችል ነው ። ቢሮና ሁለት የመኪና ማጠቢያ ቦታ አለው ፣ መስኮቶቹ በበሩማ ወፍራም ወረቀት ተለብደዋል ።

ወለሉ በዘይት የተጨማለቀ ስለ ሆነ ፣ «እንዳትወድቁ ተጠንቅቃችሁ ወደዚህ ኑ» አለን ጃክ ። ወደ ቢሮው ገባን ። ምንም ወንበር የለውም ፣ ብዙ ቆሻሻና የቆየ ጋዜጣ ተከማችቶበታል ፣ የአይጥ ኮሽኮሽታ ይሰማል ።

«አይዞሽ እዚህ አንኖርም ። ጐስትን ታውቂታላችሁ፡ አዲሶቹን ባልደረቦቻችንን ላስተዋውቃችሁ ። ይሄ ክሊመንት ይባላል ። እስዋ ቢያ፡ እሱ ዲክ ናቸው» በማለት ሰውየውን እንድናየው ሻማውን ወደ ሰውየው ጠጋ አደረገው ። ቀጥ ያለ ቁመና ያለው ጥቁር ሰው ሆኖ መነጽር አድርጓል ። እንገቱን ዝቅ በማድረግ «ተባባሪያችሁ ለመሆን ፈቃደኛ» ነኝ አለ ።

ጃክ ቀጠለና፡ «ስማይሊ የሚባለው ይሄ ነው» ብሎ አንድ አጭር ሰውየ አሳየን ። ሰውየው ፊገግታ ያበዛል ። ከዚህ በፊትም አይቼዋለሁ ።

«እሺ እንግዲህ ለትውውቅ ከዚህ በላይ ሰዓት አናጠፋም ፣ እዚህ የምንቆየው ቢበዛ ሰዓርባ አምስት ደቂቃ ነው» በማለት ልክ ለኔ እንደ ነገረኝ ፣ እኔና ዲክ በተባለው ቦታ በመኪናችን እንደምንመጣ ፣ ጃክም የተሰረቀውን መኪና ይዞ እንደምንገናኝ ፣ የጽዳት መኪናው የሚቆምበት ቦታ ከመድረሱ በፊት ሁለቱም መኪናዎች ደርሰው በመኻሉ ቸው ለሌላ ትልቅ መኪና የሚሆን ቦታ ትተው እንደሚቆሙ ፣ አራቱ ወንዶች ተራ በተራ እየወጡ ቱታቸውን እንደሚለብሱ፡ የጽዳት መኪናው ሲመጣና ሠራተኞቹ ሲወጡ መኪናው ውስጥ እንደሚገቡ፣ ሲመለሱ ረዳቱን በማሰር ከኋላ እንዲቀመጥ አድርገው ሾፌሩ ላይ ሽጉጥ በመደገን እንዲነዳ ማስገደድና ሱቁ ሲደርሱም በሙሉ ወርደው ወደ ሱቁ እንደሚገቡ፡ እንደዚህም የጽዳት መኪና ሾፌሩንና የሱቁን ሠራተኞች እዛው ውስጥ አስረው በመተው በሩ ቶሎ እንዳ

ይከፈትጃክ ላስቲኩንበሩ ሥር እንደሚያያይዘው፥ አብዛኛው ጌዋ እኔ በምንዳት መኪና፥ ግማሹ በጽዳት መኪናው ሆኖ ወደ ጋራዡ እንደ ምንሔድ ፥ ከዚያም በሾፍረሌቱ ሆነን ወደ አልቤርነአችን እንደምን ደርስና ጃክ ከፍል ሆነን ንብረቱን ከተከፋፈልን በኋላ እንደምንለያይ ፥ ትንሽ ቆይቶ ጃክ ግን ፥ የታሰሩት ሠራተኞች ታፍነው እንዳይሞቱ ለፖ ሊሶች ስልክ ደውሎ እንደሚነግር ገለጸልን ።

«ዋያቄ አላችሁ ?»

«ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ» አለ ዲክ ፥ «ከዘረፋው በኋላ ሰባታችንም ቦርሳ ተሸክመን ወደ አልቤርነ ስንገባ አያስጠረጥርም ?»

«ለሱ አትጨነቅ ። ጌጡን በአርጊ ቦርሳ አድርገን ተራ በተራ እንገባለን ።»

«ሌላው» አልኩኝ ፥ «የፊት መሸፈኛውንና መደሻውን የት እና ደርገዋለን ?»

«ከጋራዡ ከመውጣታችን በፊት የለበስነውን ተታ እዛው ስለ ምንተወው በየቱታው ኪሶች እናደርገዋለን ።»

«ሁለቱ ሰዎች በሰዓቱ መድረሳቸው ምን ያህል አስተማማኝ ነው?» አለ ዲክ ።

«ችግር የለም፤ በሰዓቱ ይገኛሉ ።»

«በተባለው ሰዓት እንገኛለን» አለ ክሊመንት ። ስማይሊም በአ ወንታ መልክ ፈገግ አለ ። ከዲክ ጋር ተያየንና ሁሉታችንም ተማባ ባን ። ጥያቄአችን ሁሉ ልክ የተጨነቀ ሰው ለመምሰል ነበር ።

«ከዚህ በፊት የፖሊሶችን ትኩረት ለመቀየር ያሰብከው እን ዴት ሆነ?» አልኩት ።

«በደንብ ተዘጋጅቷል ፥ አንድ ጓደኛዬ ለፖሊሶች ሦስት ሰዓት ከሩብ ላይ ደውሎ አይሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ላይ ፈንጂ መጠመዱን ይነግራቸዋል ። ፖሊስ እየተንጋጋ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ሲጓዝ አንድ ሱቅ ውስጥ ለሚሮህ ማስጠንቀቂያ ማን ይጨነቃል ብለሽ ነው ?»

እኔም ሆንኩ ዲክ ሌላ ጩሳብ ለመሰንዘር አልቻልንም ። ሁላች ንም ቆመን ተፋጠጥን ።

ጃክ ሻማውን መሬት ላይ አስቀመጠ ።

«ጥሩ ነው እንግዲህ፤ ሁሉም በጥንቃቄ ስለ ታቀደ ፡ በቀጠሮአችን ሰዓት ጥቃት እንገናኝ» አልኩኝ ።

«ቆይ አምስት ደቂቃ አስን ፤ መጀመሪያ አንቺና ዲክ ትወጣላችሁ፤ ከዛ ሁላችንም ተራ በተራ እንወጣለን ።»

የተባለው ደቂቃ ደረሰና እኔና ዲክ ልንወጣ ስንል ጃክ ፡ «በቀጠሮ አችን ለመገናኘት ያብቃን» አለ ።

ዞር አልኩና ለጥቁሩ ጃክ እጄን አወዛውገፍለት ወጣን ። በመ ንገዳችንም ከአንድ ሰዓት በኋላ እቤቱ ገብቼ እንደማርፍ እያሰብኩ ፡ የቢያን ልብሴን መኪና ውስጥ አመላልቄ ለወጥኩኝ ። ወደ ሼባ ሞሪስ ቡና ቤት ሐደን በዘረፋ ጨዋታ ለመጨረሻ ጊዜ የምንለያይበትን ቀን ለማስታወስ ቮድካ አዘን መጠጣት ጀመርን ።

«አራቱ ሰዎች አለንበት ቦታ ድረስ እየመጡ ቱታ እንዴት ይለ ብሳሉ? አይገርምም!» አለ ዲክ ።

«ምን እሱ ብቻ ፡ የተሰረቀ ንብረት ተሸክመን ወደ አልቤርጎ መጣባታችንስ? የፊለገውን ያህል አሮጌ ቦርሳ ቢሆንም ያስጠረጥራል።»

ብቻ እውን የኛ ችግር አይደለም ፡ ዝም ብለን እንጠጣ ተባባ ልን ። መጠጡ ግን አልጠጣ አለን ። ቡና ቤቱ ቀስ በቀስ ባዶ እየሆነ ሲሔድ ሞሪስ ዝም ብሎ ያስተውሰናል ።

«ሞሪስ ቮድካ ድገሙን» አልኩት ።

የመዝጊያ ሰዓት ስለ ደረሰ አልቀዳም አለን ። ሐሳባችንን ከፈ ልንና ስንወጣ ሞሪስን ወደኔ ሳብ አርጌ ጉንጩ ላይ ሳም አደረኩት ።

ዲክና እኔ ተቃቅፈን ስንሔድ፡ አነዚያ ደደቦች ምን ያህል ከፍተኛ ችግር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ እንኳ ቅንሽም አለማሰባቸው የሚ ያሳዝን ቢሆንም ፡ ዋናው ነገር ግን ይሄ ዘረፋ የሚፈጸም አለመሆኑ ነው ተባባልን ።

ወደ ቤቱ ለመግባት ደረጃውን ወጣንና በሩን ለመክፈት ስሞ ክር አቃተኝ ። ዲክ ቁልፉን ቀዳብሎ ከፍቶት ገባንና እንደ ገና በሩን ቆለፈው ። በጨለማ ውስጥ በዳበሳ ማብሪያውን አግኝቼ አበራሁት ።

ሳሎን ውስጥ ብዙ ሰው ተሰብስቧል ። «ታዲያስ!» አለን ጃክ እየሣቀ ።

ዕውቅ ደራሲዎችም ሆኑ እኔ በየመጽሐፉችን በድንጋጤ «ፊቱ ከሰል መሰለ ፤ ወይም አፉን ከፈተ» እያልን የምንጽፈው እንዲሁ ለአባ

ባል ይመስለኛ ነበር ። እንዚህ አባባሎች እውነት መሆናቸውን ከራሳችን ከአሁኑ ሁኔታ ተረዳሁት ። ዲክን ሳየው በድንጋጤ አፉን ከፍቷል ። እኔም አፌን እስከ መጨረሻው የከፈትኩት መሆኑን ወዲያው ዐወቅሁ ።

«ኑ እንጂ ቁሜ በሉ! ስማይሊ ሰምን መጠጥ አትቀዳላቸውም፣ መጠጣት የፈለጉ ይመስላሉ » አለ ጃክ ።

ስማይሊ ሰሁለታችንም ከርቫይዘር ቀድቶ መለኪያዎቹን ሰጠን።

አንድ ጊዜ እንደ ተጫነጨሁ ሁሉንም መመልከት ጀመርኩ። ጃክ ፣ ሄሚ ፣ ጉስት ፣ ክሲመንት ፣ ስማይሊና ከዚህ በፊት አይቻት የማላውቅ ትንሽ ፊት ያላት ሴትዮም አለች ። ሁሉም ፊት ለፊቴ ተቀምጠው በራሴ መጠጥ ይገባበዛሉ ።

ጃክ ሴትዮዋን ትኩር ብየ ስመለከታት አስተውሎ ፣ «አንጂላ ትባላለች ፣ የጉስት ዓይኖ ናት ፣ አይደለም አንጂላ?» አለ ወደ እርሷ እየተመለከተ ።ቅ

ራስዋን በአምንታ ነቀነቀች ። ቤቱ በጣም ይሞቃል ። እሷ ግን ደራርባ ለብሳለች ።

«አንጂላ የተለየ ችሎታ አላት ። እስቲ አሳያቸው ?» አለ አሁንም ጃክ ።

ከየት እንዳወጣችውና እንዴት እንዳደረገችው ማመን አልቻልኩም ። በደምብ የተሰለና የሚያበለጨልጭ አውቶማቲክ ጩቤ አሳየችን ።

«ከየት እንዳወጣችው አሳያችሁትም ። የኛ እንጂላ ችሎታዋ የሚያስደንቅ ነው ። አሪፍ ናት አይደል ?»

ዐይኔን ከጩቤው ላይ አንሥቼ ዙር ብዬ ስመለከት ፣ የራሴን ብሬታ ሽጥ ጥቁሩ ሰውየ ይዞት ማንም ላይ ሳይደግን ጣቱን ምላጩ ውስጥ አስገብቶ ይጫወትበታል ። ከዚህ የከፋው ጃክ አጠገብ በምስጢር ስጽፈው የነበረው ረቂቅ መጽሐፌ ተቀምጧል ። ዝም ብዬ ስመለከት ፣

«ጂኒ ሌላ ስም አጥተሽልኝ ነው ጥቁሩ ጃክ ያልሽኝ ?» አለና ጠየቀኝ ።

ዲክ ቀስ በቀስ ድንጋጤው እየለቀቀው በመሐዴ ፣ ምንድነው የምትፈልጉት ?» አላቸው ።

«የምንፈልገው . . . ግልጽ ነው ። ሁለታችሁንም እንፈልጋች

ኋለን ። ለምን እንደ ምንፈልጋችሁ ከመናገሬ በፊት አንዳንድ ማስ ጠንቀቂያዎች አሉኝ ። አንዳችሁም ለመጮህ ወይም ሌላ ነገር ብት ሞክሩ ወዮላችሁ ! አንጂላ እንዴት ፈጣን እንደ ሆነች አይታችኋል ። ከሊመንትም ከሷ የበለጠ ፈጣን ነው ። ስለዚህ እርዳታ ከማግኘታ ችሁ በፊት ሟቾች ናችሁ ።»

«ከመቼ ጀምሮ ነው ያወቅከው ?» ብዬ ጃክን ጠየኩት ።

ሁሉም ሣቁ ። «ከመጀመሪያው ጀምሮ ነዋ ! ሌባን ሌባ አይሰ ርቀውም ። እንቺ አንድ ቀሽም ተዋናይ ነሽ » አለኝ ጃክ የሹፈት ፈገግታ እያሳየኝ ።

በውስጤ የመጐዳት ስሜት እየተሰማኝ፡ «ምን ስሕተት ሠራሁ!» አልኩት በንዴት እያረርኩ ።

«እንቅስቃሴሽ በሙሉ ስሕተት ነው ፡ የምትጠቀሚባቸው ቃላ ቶች የቤት ልጅ እንጂ፡ ዱርዬ ሰው እንደማይናገራቸው ተረድተሻል! ከመቼ ወዲህ ነው ከቺካጐ የመጣች የቡና ቤት አስተናጋጅ ጨዋ አንጋገር የተማረችው! አንድ ጊዜ ቢያ ፤ ሌላ ጊዜ ጂኒ መሆንሽለ ፡ ልብስ መቀየርሽ ብቻ ነው ሌላ ሰው ያስመሰለሽ እንጂ ማንነትሽ በደ ንብ ያስታውቃል ። ሌላው ቀርቶ አካሔድሽ አንድ ነው ። ለመጀመ ሪያ ጊዜ ሳይሽ አስገረምሽኝ ። ይሄ ሁሉ መለዋወጥ ለምንድነው ብዬ እራሴን ጠየኩ ። ምናልባት የፖሊስ የምስጢር ሠራተኛ ትሆን ? አልኩኝ ። አጣራሁ አልነበርሽም ። አንተስ ?» አለ ወደ ዲክ እየተ መለከተ ፡ «አንተም ከሷ የተሻልህ አይደለህም ። ሁለታችሁም የማ ትረቡ ለማጅ ተዋናዮች ናችሁ ።»

«ይሄን ካወቅህ ለምን በፅቅዳችን ተስማማህ ?»

ራሱን በፉጨታ በመነቅነቅ፡ «ጂኒ . . . ጂኒ . . . መልሱን ታው ቂዋለሽ ። አንቺና ዲክ የማትረቡ ናችሁ ። ይሄ እውነት ነው ። ግን ጥሩ ሕልም አልማችኋል ። ትክክለኛ ዘመቻም አቅዳችኋል፤ ሱቁን በደንብ አጥንታችኋል ፤ ሁሉንም ሥራ ሠርታችኋል ፡ በመጨረሻ ጊዜ መሸሻችሁ ምን ማለት ነው! ታሾፋላችሁ!»

«እና በፅቅዱ መሠረት ልትቀጥሉ ነው?» አለ ዲክ በመደንገጥ ።

«ትንሽ የፅቅድ መስተካከል አድርገን፡ አንተም ጂኒም ሁላች ንም ሆነን እንቀጥላለን ።»

«ገደል ግባ !» አለ ዲክ በንዴት ።

ጃክ ከሊመንትን እያየ «አንጂላ !» ብሎ ተጣራ ።

ጨቤዋን አውጥታ በማፍጠጥ ተመለከተችኝ ። ከሊመንትም ሽጉጡን ጠበቅ አድርጎ በመያዝ በተወሰነ ርቀት ዲክ ላይ አነጣጠረ ።

«ሁላችንም በዚህ ዘረፋ ውስጥ አለንበት ። እኛ እንደ ተነከርን ሀት ሁሉ እናንተም ተነክራችኋል ። ለመሮጥ ፣ ለመጮህ ሞክሩ፤ ያል ቅላችኋል ።»

«እኔን አስቀሩና ጂኒን ልቀቅዋት ። ሰፖሊስ አትነግርም፤ ሁለ ታችንንም የምትፈልጉ አይመስለኝም ።»

«አስተማማኝ የሚሆነው ሁለታችሁም ከኛ ጋር ስትሆኑ ነው ፣ ለምን አላስፈላጊ ችግር ውስጥ እንገባለን?» ።

ወደ ዲክ ጠጋ ብዬ «ኤመሰግንሃለሁ» አልኩት ።

«እሺ እንግዲህ ብዙ ሰዓት የለንም ። አለና አጠገቡ የተቀመጠ ውን ረቂቂን አንሥቶ ሥራችንን እንቀጥል» ሲል ፣

«ቆይ ! ወደዚያ ከመሔዳችን በፊት ጥያቄ አለኝ ። ለምሆኑ እዚህ የምኖር መሆኔን እንዴት ዐወቅህ?» አልኩት ።

«ጂኒ ! በጣም ቀላል ነው ። በየጊዜው ወደዚህ ቤት ስትመላለሽ ተከታተልኩሽ፤ ጉስት መኪናሽን ፈትሸ ወንበር ሥር መታወቂያሽን አገኘ ። አድራሻሽን ዐወቅሁት ማለት ነው ።»

«እሺ ! ቤቱ እንዴት ልትገቡ ቻላችሁ ?»

«የቤትሽን ቁልፍ ተመሳሳይ አሠራን ።»

«ተመሳሳይ ቁልፍ? ከመቼ ጀምሮ? የት አገኘኸው?»

ተመለከተችኝና ፈገግ አለ ። ወዲያው ገባኝ ። የመጀመሪያ ለታ አብረን ያደርን ቀን እንቅልፍ ሲወሰደኝ ተነሥቶ ክፍሌን ፈትሾ እን ዳገኘውና ኮሪዶር ላይ ለሚጠብቁት ለሄሚና ለጉስት እንደ ሰጣቸው ፤ እነሱም ሌሊቱን ተመሳሳዩን አሠርተው ከእንቅልፌ ከመንቃቴ በፊት ለጃክ መልሰውለት ኖሮ እሱም መልሶ ክፍሌ ሊያስቀምጠው እንደ ቻለ ተረዳሁ ።

«በእውነት ቁልፉን እንዴትና መቼ እንዳገኘሁት እንድነግርሽ ትፈልጊያለሽ ?»

«አልፈልግም ! እንዴት እንዳገኘኸው ግምት አለሁ ።»

«መገመት ትችያለሽ ። ከዚያ በኋላ ቀን በቀን እዚህ ቤት መም ጣት ጀመርኩ ። ለመሆኑ ዕቃዎችሽ ተነካክተው እንደ ነበሩ የጠረ ጠርሽበት ጊዜ ነበር ?»

«አልነበረም ።»

«ምንም ዕቃ አልወሰድኩብሽም ። ግን ይሄን ረቂቅ ጽሑፍ በየ ዕለቱ እከታተል ነበር » አለ ጽሑፉን በእጁ መታ መታ እያደረገ ።

እቤቴ ውስጥ ያለ ፈቃድ በመግባቱና ሚስጢሮቼንም በመመል ከቱ በጣም ጠላሁት ። መንገድ ላይ እንደ ደፈረኝ ቆጠርኩት ። ወዲ ያው ጥላቻየን የሚቀንስ ነገር ተናገረ ።

የረቂቆቹን ገጾች እያገላበጠ፡«ጂኒ በጣም ጥሩ ጸሐፊ እንደ ሆንሽ ታውቂያለሽ ?»

«አመሰግናለሁ ! 'ጸሐፊዎች የማይረቡ አይምሰሉህ' አልኩት ስለ ተሞገስኩ ውስጥ ውስጡን ደስ እያለኝ ።

«በጣም ጥሩ ነው ። ወደ ፊት ብዙ መጽሐፍ መጻፍ ትችያለሽ የሚያሳዝነው ግን፡ይህ መጽሐፍ ምን ጊዜም ሊታተም አለመቻሉ ነው ።»

«ለምን ?» አልኩት በጭንቀት መልክ ።

ወዲ ዲክ ፊቱን አዞረና «ከጂርቪስ ጋር ያሳለፈችው ምሽት እን ዴት እንደ ነበረ ባትጠይቃት ኑሮ ስለዚያ ማስጠንቀቂያ ወንበርና በር ስለ መዘጋቱ እንዴት ማወቅ እንችል ነበር? እናንተም አትነግሩ ንም ነበር አይደል? ብቻ ይሄን ተዉት ። ራሳችሁን ከዚህ ስላወጣ ችሁ ብቻቸውን አይሞክሩትም ብላችሁ ነው ። አሁን ግን. . . እኛና ትልቁ ዘረፋ ልክ አንቺ እንዳቀድሽው ተግባራዊ ሊሆን ነው ።»

ሁሉም ቀደም ብለው የሰሙት ስለ ሆነ መሰለኝ ማንም ጣልቃ ገብቶ ጥያቄ አላቀረበም ። እኔና ዲክ ለመቃወም ተዘጋጀን ። እሱም በበኩሉ በደንብ ተዘጋጅቶበታል ። ያን ሰሞን ጃክ የተሰወረብኝ ለካስ ሲከታተለኝ ኖሯል ። እኔና ዲክ የተነጋገርነውን በረቂቁ ውስጥ ያሰ ፈርኩት በመሆኑ ፣ ረቂቁን ተመልክቶ የዕቅድ ለውጥም አዘጋጅቷል ። እንዲህም አለ ።

«አዲሱ ዕቅዳችን ይሄን ይመስላል ። እስከ ጠዋቱ ሁለት ሰዓት እዚህ ቤት እንቆያለን ። ከፈለጋችሁ አንቺና ዲክ እዚህ ክፍል መተ ኛት ትችላላችሁ ። ወደ ሽንት ቤት መሔድ ከፈለጋችሁ አንጂላና ክሊመንት ያጅቧችኋል ። የሽንት ቤቱ በር አይዘጋም ! የተወሰነውም ትንሽ መተኛት እንችላለን ። ከስድስታችን ሦስታችን በተራ ነቅተን እንጠብቃለን ። ከአንጂላ ጀምረን ሁላችንም መሣሪያ ይዘናል ። ጥዋት ሁላችንም ለሥራ እንዘጋጃለን ። ጂኒ ፈቃደኛ ከሆንሽ ቡና ታፈያለሽ ፤

ከልሆንሽ አንጂላ ታፈላለች ። ለዐይን መግለጫ የተፈለገውን መጠጥ እንቀምሳለን ። ልክ በሁለት ሰዓት አንጂላ ከጂኒ በኋላ ፣ክሊመንት ከዲክ በኋላ በመሆን ተራ በተራ ወጥተን ከቤቱ በስተጀርባ ወደሚገኘው የመኪናዎች ማቆሚያ እንሔዳለን ። ከዚያ እኔ ፣ ጂኒ ፣ አንጂላ ፣ ሄሚና ጐስት በጂኒ ፎርድ እንሆናለን ። ክሊመንት ፣ ዲክና ስማይሊ በዲክ ቮልስ ዋገን ትሆናላችሁ ።»

«የኔ መኪና ያለችው ከዚህ ራቅ ብላ ነው » አለ ዲክ ።

«ሌላ ብላ ! አሁን ያለችው እዚሁ ናት ፣ አምጥተናታል ። ከት ትል ያደረግሁት ጂኒ ላይ ብቻ አይደለም ። የት እንደምትኖርና እንደ ምትሠራ ፣ መኪናህን የት እንደምታቆማት ሁሉ ተከታትያለሁ ።»

«አሺ ይሁን ፣እንዴት በሩን ከፍተህ አስነሣሃት ?»

«እኔ አይደለሁም ጐስት ነው ያስነሣት ። በመኪና አከፋፈት ከፍተኛ ልምድ አለው ።»

«ጥሩ! እንግዲህ ስምንታችን ሁለት መኪና ውስጥ ሆነን ማለት ነው ፣ በዐርባ ሰባተኛው መንገድ በኩል ወደ ተሰረቀው ሾፍረሌት እንሔዳለን። አስፈላጊ ዕቃዎቻችን ጋራዡ ውስጥ ስለሆኑ፣እዚያ ደርሰን ቱታዎቹን በመልበስና አስፈላጊውን ዕቃዎች በመያዝ ሾፍረሌቱ ውስጥ እንገባና ፎርድዋንና ቮልስዋገኑን ጋራዥ እንተዋቸዋለን ። ጂኒ! ቮልስዋገኑዋን እጋራዥ ከተውናት'ሦስቱ ሰዎች በምን ይጓዛሉ፣ እንዴትስ በቀጠሮው ሰዓት ይገኛሉ' ብለሽ እያሰብሽ ነው አይደል?» ትከሻየን ነቀነቅሁና ፣«ምናልባት ሌላ መኪና ሰርቃችሁ ይሆናል አልኩት ።»

«ልክ ነሽ ! እስቲ ምን ዓይነት መኪና ሊሆን እንደሚችል ገምች? ቆንጆ አረንጓዴ ጃጉዋር ቢሆን ጥሩ አይመስልሽም?» የእኔን መኪና ነበረ ።

«አንተ ዲቃላ!» አልኩት ።

«የመኪናሽ ቁልፍ በጂ አለ ። ለዚህ ከፍተኛ ተግባር ካልተጠቀምንበት አሳፋሪ ይሆናል » አለኝ ረጋ በማለት ። ከዚያም ቀጠለና ፣

«ሁለቱ መኪኖች ተከታትለው ማድሰን ጐዳና ይደርሳሉ ። የጽዳት መኪናው እስከሚመጣ ድረስ አንቆምም ፤ እንዘዋወራለን ። በዚህ ጊዜ ቱታችን እንዳይታይ ከላይ ሁላችንም ኮት እንደርባለን ። የጽዳት መኪናው መጥቶ እንደ ቆመና ሠራተኞቹ ወደ ሱቅ ሲገቡ ፣ ሾፍረሌቱ ከፊት ፣ ጃጉዋሩ ከኋላ በመቆም መኪናውን መክል እናስገ

ባዋለን ። አምስቱ ወንዶች ከመኪናው ኋላ በር ዘኩል ገብተው አስ
ፈላጊውን የፊት መሸፈኛ ያደርጋሉ ። ለዲክ የፊት መሸፈኛ አያስ
ፈልገውም ፤ ምናልባት አርቲፊሻል ጺምና የቁስል ፕላስተር ግምባሩ
ላይ ይለጠፍለታል ።

የጽዳት ሠራተኞች ተመልሰው በሩን ሲከፍቱ ወደ ውስጥ እንዲ
ገቡ በመሣሪያ ይገደዳሉ። ከረዳቱ ጋር ሌላ ሰው ካለ አስሮ መኪናው
ወለል ላይ ማስተኛት ነው ። እኔም ሹፌሩን አስገድጄ አስገባዋለሁ ።»

«አይሳካም! መንገደኞች ይሄን ሲያዩ ይሰበሰባሉ» አልኩት ።

«በደንብ ይሠራል! ሠራተኞች መኪናው ውስጥ ከነፍሰ ገዳዮች
ጋር መሆናቸውንና ሽጉጥ እንደ ተደገነባቸው ወዲያው ያውቃታል ።
እኔ ከሾፍረሌቱ የምወጣው ሾፌሩ በሩ ጋ ሲደርስ ነው ። ከኋላው
ሽጉጥ ደግኖ ሳበገድደው ሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ሲፈጽሙ ምን
ማድረግ ይችላሉ? ምናልባት ራሳቸውን ይስቱ ይሆናል ፤ ከዚያ ውጭ
የሚያደርጉት የለም ። እንዴት እንደሚሠራ ታያለሽ ። ይሄንን እንዳ
ከናወን መንገዳችንን ወደ ሱቁ እንጀምራለን ። በዚህ ጊዜ የፖሊሶችን
ትኩረት ለማሳሳት ጓደኛየ ለፖሊሶች አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ
ቦምብ የተጠመደ መሆኑን ስልክ ደውሎ ይነግራቸዋል ። መኪናው
ሱቅ እንደ ደረሰ ጂኒ የምትነዳው ሾፍረሌት ከአንጀላ ጋር ሆናችሁ
ከጽዳት መኪናው ኋላ ትቆማላችሁ ። እሱና ሾፌሩ መጥረጊያ ይዘን
እንወጣለን ፤ የሱቁ በር እንደ ተከፈተ መኪናው ውስጥ ያሉ ሰዎቻችን
አብረውን ወደ ሱቁ ይገባሉ ። የታወቀው የበር ማዝጊ ላስቲክ ከሳን
ፍራንሲስኮ የበለጠ አገልግሎት ይኖረዋል ። ውስጥ ከገባን በኋላ በሩ
እንዲዘጋ ስፈልጋለሁ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን አንድ ሰው ለማስወጣት
የሚችል ክፍተት ይኖረዋል ። ዘረፋውም እንዳበቃ የሱቁን ሠራተኞች
በማሰርና አፋቸውን በፕላስተር በማጣበቅ እዛው ትተናቸው ቦርሳ
ዎቻችንን ሞልተን እንወጣለን። ሁላችንም እንደወጣን ከውስጥ ያስ
ቀመጥነውን ላስቲክ በማንሣት በውጭ በኩል አድርገን በሩ በደንብ
እንዲዘጋ አደርጋለሁ ። እኔ ፣ ጮስትና ሄሚ ሆነን ሾፍረሌቱ ውስጥ
ከኋላ በር እንገባለን ። ስማይሊ ፣ ክሊመንትና ዴክ የተወሰነውን ተሸ
ክመው በጽዳት መኪናው ውስጥ ይገባሉ ። መኪናውን ስማይሊ ይነ
ዳል ። በተለያየ መንገድ ቀጥለን ባዘጋጀነው ጋራዥ እንገናኛለን ።
እዛው ጋራዥ ውስጥ የጽዳት መኪናውንና ሾፍረሌቱን ትተን በፎር
ዱና በቮልስዋገኗ እንሳፈራለን ።»

«ከዚያ በኋላ ወደ አንተ አልቤርቶ እናመራለን ?» አሰ ዴክ
በማሾፍ ።

«እንደዚህ ዓይነት የቂል ሥራ ሠርቼ አላውቅም ፣ የተሻለ ቦታ አለ ፤ ጊዜው ሲደርስ ታየዋለህ ።»

«የኔ መኪና የባህል ዕቃ መሸጫ ሱቅ እንደ ቆመ ሲቀር ነው፣ ፖሊሶች በሀሥር ደቂቃ ውስጥ የጽዳት መኪናው ከየት እንደ ተጠለፈ ወውቀው ወዲያውኑ ወደ ቤቱ ሊመጡ ይችላሉ » አልኩኝ ።

ስማይሊ ለመጀመሪያ ጊዜ እየሣቀ ፣ «አዎ! ይመጣሉ! ላንቺ አላፊ ነው ፣ አይደል?» አለኝ ። ምንም የምናገረው ስለአልነበረኝ ወደ ዴክ እየተመቻቸሁ ጠጋ አልኩኝ ። ጃክ ዝም ብሎ ያየኛል ። ሄሚ ፣ ጐስትና ክሊመንት አግራቸውን ዘርግተው የተኙ ይመስላሉ ። ስማይሊ ፣ አንጀላና ጃክ እንቅልፍ አልሞከራቸውም ። ስማይሊ ጠርሙስ ውስጥ የቀረውን ኩርቫይዘር እየቀዳ ይጠጣል ። ሲያዩት ምንም የቀመሰ አይመስልም ።

«ምን ዓይነት ጣጣ ውስጥ ነው የገባነው? ለምንድነው ሁሉንም ነገር ወረቀት ላይ ያሰፈርሽው?» አለኝ ዴክ ።

በማሳዘንና በመጨነቅ መልክ፡ «እኔማ ጥሩ መጽሐፍ ይወጣዋል ብዬ ነበር» አልኩት ።

«አሳዛኝ መጨረሻ! ለመሆኑ መውጫ መንገድ ይታይሻል! ምናልባት ..... ደካማ ጐን ሆኖ ያገኘሁት...»

ጃክ ስንሾካሾክ ዝም ብሎ ያየን ነበር ፤ አቁመውም አላለንም ። «ጂኒ! ሰው ምን እንደሚያስብ ፊቱን አይቼ እንደማውቅ ታውቂያለሽ?» አለኝ ። ዝም ብዬ ተመለከትኩት ። «አሁን አንቺ የምታስቢው የማምለጫ መንገድ ነው ። የጽዳት መኪናው ሲጠለፍ ሾፍረሌቱ ውስጥ አንቺና አንጀላ ብቻ ስለምትቀሩ ዕድልሽን ለመሞከር ነው ። ወይ ትጮሂያለሽ ፣ ወይም አንጀሳን አንድ ነገር ለማድረግ ታስቢያለሽ ። ይሄ የሕዛን ልጅ ሥራ ነው ጂኒ! እንዳትሞክሪ ከልቤ እመክርሻለሁ ፤ ትገልሻለች» አለና አንጀላ ብሎ ተጣራ ።

አንጀላ አፍጥጣ ተመለከተችኝና ፣ በማንሾካሾክ መልክ ፣ «አንጀ ትሽን እዘረግፍልሻለሁ!» አለችኝ ።

«ቀልድ እንዳይመስልሽ አዳምጪት! ሰው መግደል የመጀመሪያዋ አይደለም ። ባጋጣሚ እንኳ ቢሳካልሽ ምንም አይጠቅምሽም ። ጽሑፍሽ ያለው እኛ ጋ ነው ፣ ተገድጂ ፈጸምኩ ብትይ ዕቅዱን ስለመን ደፍሽ ይህ ጽሑፍ ማረጋገጫዬ ነው ። ያዋጣሻል ?»

ያለኝን ሁሉ አብሰለሰልኩት ። ለኔም ሆነ ለዴክ መውጫ የለንም ። ዕድሉ ሁሉ የነሱ ነው ።

ጀርቪስን ይጐዱት ይሆን ብዬ አሰብኩ ። ምናልባት ስለ ጀርቪስ ፓስፖርት ብነግራቸውና ትክክለኛ ስሙ አንዶሪዮ ሮሲ መሆኑን ቢያውቁ ምን ለውጥ ያመጣል? ጃክ እንደ ሆነ ስለ ውሸት ስሞች ስለ ሚያውቅ ምንም አይመስለውም ።

ዐይኔን ስገልጠው የጧት ፀሐይ ክፍሉን አስውቦታል ። የግራ ትከሻየን ከብዶኝ ዞር ብል ዲክ ራሱን እላየ ላይ አሳርፎ እንደ ተኛ ነው ።

አንጀላ ፡ ጐስትና ስማይሊ ደስተኛው ተኝተዋል ። ሄሚና ክሊመንት ተነሥተዋል ፡ ክሊመንት በእጁ ሽጉጡን ይዞ ዐይን ዐይኔን ይመለከታል ። ጃክ ይተኛ ፡ ይንቃ ማወቅ አልቻልኩም ። በድንገት አንድ ነገር ለመሥራት ብሞክር ተስፈንጥሮ ሊነሣ እንደሚችል ገመትኩ ።

ክሊመንትን ተመለከትኩትና ፡ «ምንድነው ልብስህ ላይ የተጻፈው?» አልኩት ።

ልብሱን ተመልከቶ ፡ «እንበሳ ያለበት ጫካ ውስጥ ስትገቢና በሕይወት መመለስ ስትፈልጊ እንደ አንበሳ መልበስ አለብሽ ። ገባሽ?» አለኝ ።

«እቤት! የማይረባ ሙከራ ነው ፡ አይሠራም?» አልኩት ከምሬ ።

«በእውነት አይሠራም ብለሽ ታምኛልሽ?» አለ አሁንም ልብሱን እያየ ።

«እኔም ራሴን በልብስ ለመለወጥ ሞክሬ አልተሳካልኝም ።»

«ችሎታ የለሽማ! እኔ ግን ባህሉን ፡ አነጋገሩንና አካሔዱን ፀውቅ በታለህ ፡ የትም ቦታ እንደልቤ መግባትና መውጣት ችግር አይሆን ብኝም ።»

«አዎ! መልክህንም ቀለም ከተቀባኸው ምናልባት ይሳካል ።»

ሽጉጡን ቀስ እያለ ወደኔ ደገነው ።

ጃክ ዐይኑን በግማሽ ከፈተ አድርጎ ፡ «ክሊመንት! ረጋ በል በማ ዴት ስሕተት እንድትፈጽም ነው የምትገፋፋህ ። አልገባህም?» አለው ።

«ገባኝ... ገባኝ» አለና ሽጉጡን ወደ መሬት በመመለስ ፡ «ለዚህ ነው በጥዋት የምትለክፈኝ » አለ ።

ጃክ ከተኛበት ተነሣና ፡ «ትንሽዋ ሴት ወይዘሮ ወደ ማድቤት እንሒድ» አለኝ ። እምቢ ለማለት አሰብኩ እምቢ ብል አንጀላ ቦምቡን ታፈላለች ፤ እና ምንም ላይሰጡን ይችላሉ በማለት ቀስ ብዬ የዴንን ራስ ከትከሻዬ አንሥቼ ወንበሩ ላይ አመቻችቼ አስተኛሁትና

ተነሥቼ ማድቤት ሐድኩ ። የቡና ጀበናውን ውሃ ሞልቼ ምድጃው ላይ ጣድኩት ።

ጃክ እንቅስቃሴዬን ሲከታተል ቆይቶ ፣ «ቆንጆ ቤት አለሽ» አለኝ ። መልስ አልሰጠሁትም ።

«አሁንም የማምለጫ መንገድ እያሰብሽ ነው፣ ለምሳሌ የፈላ ውሃ ፊቴ ላይ በመገልበጥ በቀላሉ ማምለጥ እችላለሁ ብለሽ አትሞ ከሪ ። ከሊመንትን ለማናደድ የሞከርሽው ዘዴ የሚያነቅ ነው ።»

«ሌላ ዘዴ እሞክራለሁ» አልኩት ፊቴን ከሱ አዙሬ ።

«ምናልባት ትሞክሪ ይሆናል ። ያንችና የዲክ ግንኙነት ምንም ሊገባኝ አልቻለም ። አንዳችሁ ብታመልጡና ወደ ፖሊስ ብትሔዱ ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ቢኖር አንዳችሁ ከኛ ጋር መሆናችሁን ነው ።»

«ይገባኛል » አልኩት ። ጥቂሩ ጃክ ምን ያህል ብልጥ እንደ ሆነ ዐወቅሁ ። በመኻከላችን ስላለው ግንኙነት ምንም ዕውቀት የለ ውም ፤ ግን እኔም ሆንኩ ዲክ አንዳችን አንዳችንን እደጋ ውስጥ ለመ ጣል እንደማንፈልግ ዐውቆታል ።

ቡናው እንደፈላ ጃክ ጠራቸውና ሁሉም ተራ በተራ እየመጡ ወሰዱ ። ለራሴና ለዲክ ቡና ቀድቼ አጠገቡ ተቀመጥኩ ። ጃክ እያየን ጠጣን ። ቡናችንን እሰክንጨርስ ጠብቆ ሰዓቱን ተመለከተና ፣ «ጄኒ ሰውነትሽን ባለመታጠብሽ አዝናለሁ ። ሁላችሁም እንዴት እንደ ምትወጡ ዐውቃችኋል ። ችኮላ አያስፈልግም ፤ ረጋ ብለን ወደ ሥራ እንደሚሔድ ሰው ነው መሔድ ያለብን ። ባጋጣሚ የምናገኘውን ሰው በትሕትና ሰላም ማለት ነው ። ጥያቄ የሚጠይቅ ሰው ካጋጠመ እኔ መልስ እሰጣለሁ ። ከቤቱ አጠገብ ከደረስን በኋላ ፣ ሁለት ሁለት እየሆንን ወደመኪናው ማቆሚያ እንሔዳለን ፤ ሁላችሁም ዝግጁ ናችሁ?» በሉ እንግዲህ ትርዒታችንን ውጭ እናሳይ» ብሎ ረቂቁን ይዞት ተነሣ ። የሚረሳው መስሎኝ ነበር 'ዲቃላ!' አልኩኝ በልቤ ።

ሁላችንም ከቤት ወጣን ። እግሬን ብርክ ያዘኝ ። ልቤም በፍጥ ነት ይመታ ጀመር ። የምወድቅም መሰለኝ ። 'ይሄ ነገር እውነት ከሆነ በዚህ ውስጥ መሳተፍ አልፈልግም' አልኩኝ ለራሴ ። ሆኖም ተሳታ ፊም ተመልካችም ሆንኩ ።

ትልቁ ገርፊያ

ምን እንደማደርግ የማላውቅ ብሆንም ፥ የታዘዝኩትን ሁሉ ፈጸ ምኩ ፤ በሚነገረኝ መንገድ መመራት ጀመርኩ ። ከዚህ በፊት የማው ቃቸው መንገዶችና ቤቶች ሁሉ አዲስ ሆኑብኝ ። በማያውቀው አገር የሚጓዝ መንገደኛ ሆንኩ ። 'ሁሉንም ነገር ማስተዋልና መከታተል ይኖርብኛል' በሚል አሰብኩና የጃክንና የሌሎችን ሁኔታ አስተዋልኩ። የሚሠሩትን መጻፍ ባልችልም በአዕምሮዬ መቅረፅ አለብኝ ። ወዲያው ራሴን በራሴ «ጸሐፊዋ በሥራ ላይ» አልኩት ።

ሌቦች ሁሉ ትኩረታቸው በሥራቸው ላይ ነው ። በፎርዱ መኪና ውስጥ በኔ ነጂነት አንጂላ ፥ ጃክ ፥ ሄሚና ጐስት አሉበት ። አንጂላ የምትመለከተው እኔኑ ብቻ ነው ። ሌሎቹ ግን፥ በሁሉም አቅጣጫ አንገታቸውን እያዞሩ የመኪናውን ብዛትና የትራፊክ መብራቶችን ይቆጣጠራሉ ። በመጽሐፌ ውስጥ የመዘገብኩት የጭንቀት ዓይነት ከእውነተኛው ጭንቀት ጋር ሲተያይ አነስተኛ ነው ።

እንደ ሞኝ ያስቆጥረኝ ይሆናል እንጂ ፥ የፈለገው ነገር ይምጣ ይህ ዘረፋ ትክክለኛ ታሪክ ስለሆነ 'ራሴን ተቆጣጥሬ መከታተል አለብኝ' የሚል እምነት እያደረብኝ መጣ ።

እኔና ዲክ ከነዚህ ሰዎች በአስተዳደግና በትምህርት እንበልጣ ቸዋለን ። ከነሱ ጋር የሚያገናኘን ምንም መንገድ አልነበረም ፥ የበ ታቾቻቸን ናቸው ። ለመጻፍ የነበረኝ ጉጉት እንደዚህ ያለ ችግር ውስጥ ከተተኝ ። እነዚህ ወንጀለኞች በተንኰለኝነታቸውና ለሰው ሕይወት ደንታቢስ በመሆናቸው ፥ እኛ ለነሱ የበታች ሆነን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉን ።

በሕይወቴ አንድም ጊዜ ከሌቦች ጋር እገናኛለሁ የሚል ሐሳብ አልነበረኝም ፤ አሁን ግን ሳልወድ ትልቅ ተባባሪ ሆንኩ ።

እኛ ከመድረሳችን በፊት ሌላው መኪና ቀድሞን ጋራዥ ደርሶ ኖሮ በሩ ተከፍቶልን ገባን ። ጋራዡ ውስጥ የኔና የዲክ እንዲሁም የተሰረቀው ሾፍረሌት መኪና ቆመዋል ።

ያለምንም ግራ መጋባትና ንግግር ሁሉም ወደ የሥራው ተሰ ማራ ። ወንዶች ዲክንም ጨምሮ የጽዳት ሠራተኞች ቱታ ለበሱ ። ለቀጭኖቹ ለዲክና ለጐስት እንዲሁም ለአጭሩ ስማይሊ የሚስማማ ቱታ በመገኘቱ ጃክን አደነቅኩት ።

የቮልስዋገኑዋን ሰሌዳ በዘይትና በወፈር መለወስ ጀመሩ ። «ብዙ እታድርጉ! እንዴ ቍጥሩ ላይ ብቻ ይሁን » ብሎ ጃክ ተናገረና ጦር ሜዳ ወታደሮችን ይዞ እንደሚሔድ ሃምሳ አለቃ መያዝ የሚገባቸውን ዕቃዎች ሁሉ መያዛቸውን አንድ ባንድ ተቆጣጠረ ። ለራሱ አርቲ ፊሻል ጺም ለጥፎ በመኪና መስተዋት ተመለከተ ። በድጋሚ ሰዎቹን ተመልክቶ ሰዓቱን አየና ፡ «እሺ! ንግታችሁን አድርጉና መኪናዎቹን አለፍ አለፍ እያላችሁ ፋቅ ፋቅ አድርጓቸው» አለ ። የበሩን ፡ የኋላውንና ሌላውንም የመኪና ክፍሎች ቀለም ፈገፈጉዋቸው ። «በቂ ነው ፤ የመሔጃ ጊዜያችን ደርሶአል» አለ ጃክ ።

«እኔ ፡ አንጀላ ፡ ጄኒ ፡ ሄሚና ጐስት ከሾፍሌቱ እንግባ ፡ ጄኒ መኪናውን ስለምትነጂ ንጉት አድርጊ ፡ ሌሎቻችሁ በጃጉዋሩ ሁኑና ዲክ ይንዳ ፡ እንቀጥል እንግዲህ!» ብሎን ከጋራዡ ወጣን ። ትእዛዙ ጥብቅ ነው ።

አንጀላ አጠገቤ ተቀምጣ ሾፍረሌቱን መንዳት ጀመርኩ ። የያዘችው ጩቤ ጐኔን አልፎ አልፎ ነካ ያደርገኛል ። ከአንጀላ አጠገብ ጃክ ተቀምጧል፤ጐስትና ሄሚ ከኋላ ናቸው ። በመስተዋት ስመለከት ዲክ ጃጉዋሩን እየነዳ ይከተለናል ። እኛ ወደፊት ቀጠልን ። የኔ መጽሐፍ ግን ሕልም ሆነ ። ማዲሰን ጐዳና ስንደርስ ጃክ 'ዕድሌ ወደ መጨረሻ እያማረ ነው ያለኝ ትክክል ባይሆንስ? እሱ እንዳቀደው ዘረፋው ባይሳካ?' እያልኩ አሰብኩ ። እስካሁን ግን ፡ ምንም ያጋጠመን ነገር የለም ፡ ከቤት ስንወጣ አንድም ሰው አላገኘንም ። ቱማርተኞችና ሌቦች ያሰቡት እንደሚሳካላቸው በደመ ነፍስ ያውቁ ይሆን?

በትእዛዝ መልክ«ፍጥነትሽን ቀንሽ ፡ ጃጓሩ ይድረስብን»አለኝ ።

ትእዛዙን ተቀብዬ ፍጥነቴን ቀነስኩና አጠገባችን ሲያርስ ወደ ከተማው ማቋረጫ መንገድ ድረስ ሔጄ ወደ ግራ ታጥፌ ጉዞአችንን ቀጠልን ። በተቻለ መጠን የትራፊክ መብራቶችን እየተቆጣጠርኩ በጥንቃቄ ነዳሁ ።

«ጐበዝ ልጅ! ጥሩ አነዳድ ነው በዚህ ቀጥይ» አለኝ ።

ሃምሳ ሦስተኛው መንገድ ደረሰን ። የጽዳት መኪናው አልመጣም ። «ቀስ በይና ወደ ቀኝ ዙሪ» አለኝና ወደ ቀኝ ዞሬ በደቡብ በኩል ወደ ሃምሳ አራተኛው መንገድ ሔድን ። እንደገና ተመልሰን ወደ ሃምሳ ሦስተኛው መንገድ ገባን ። ጃጓሩ ይከተለናል ፤ አሁንም የጽዳት መኪናው አልመጣም ። ጃክ ሰዓቱን ተመልክቶ ያለምንም ጭንቀት «ትንሽ ደቂቃ ዘግይቷል» አለ ። አነጋገሩን አደነቅሁት ። እንደገና ዙረታችንን ጀመርን ። የሥራ መግቢያ ሰዓት እየተቃረበ ስለሆነ መን

ገዱ በመኪና ተሞልቶአል ። እንደ ገና ስንመለስ የጽዳት መኪናው መጥቶ ከባህል ዕቃ መሸጫው ሱቅ አለፍ ብሎ ቆመ ።

መኪናውን ያቆሙት ከሱቅ ሆነው ለመመልከት በሚያመች ቦታ ላይ ነው ። «ተሳክቶልናል!» አለ ጃክ በመደሰት መልክ ። ከመ ኪናው ፊት ሒጂና ቁሚ! ከዚያ ወደ ኋላ አምስት እርምጃ እስኪቀርሽ ድረስ ተጠጊ» አለኝ ። እንዳለኝ አደረኩና በመስተዋት ተመለከት ኩኝ ። ዲክም ከጽዳት መኪናው በኋላ ጀጉዋሩን አቆመ ።

«በጣም ጥሩ ነው! አሁን የምንጠብቀው...» አለና ዝም አለ ። ለዐሥር ደቂቃ ያህል ያለምንም እንቅስቃሴ በጸጥታ ቁጭ አልን ። በአጠገባችን የፖሊስ መኪና አለፈ፤ዘወር ብለው እንኳን አላዩንም ። በእግሩ የሚጓዝ ፖሊስማ አይታይም ።

ጃክ ወደ ኋላ ወንበር ፊቱን አዞረና፡«ሰዓት ደርሶአል!» አላቸው ። ራሳቸውን ነቀነቁና ረጋ ብለው በመውጣት የጽዳት መኪናውን የኋላ በር ከፍተው ገቡ ። መስተዋቴን አየሁ ። ዲክ ክሊመንትና ስማይሊም ከመኪናው ወርደው ገቡ ። የመኪናው በር ተዘጋ ።

«በጣም ቆንጆ! ጂኒ ልትኮሪ ይገባል ። ልክ እንዳቀድሽው ሊሆን ነው ።»

መልስ አልሰጠሁትም ። መኪናው ውስጥ ሰዎቹ የፊት መከለያ ቸውን እንደሚያደርጉና በገዛ ሽጉጣም ዲክ ላይ እንደሚደግኑበት ዐውቅ ነበር ።

«ሠራተኞቹ መጡ !» አለ ጃክ በድንገት ።

ዞር ብዬ አየሁ፡ምስኪኖች! ሾፌሩና ረዳቱ መጥረጊያ ይዘው እየተሳሳቁ ከሱቅ በመውጣት ላይ ነበሩ ።

«የኔ ተራ ነው» ብሎ በሩን ከፈት አደረገና ዐይን ዐይኔን እየ ተመለከተ፡«አንጂላ ችግር ከፈጠረችብሽ ግደያት!» አለ ። እንደዚህ የጐደጐደ ዐይን ወደ ፊት የማይ አይመስለኝም ።

ጃክ ሠራተኞቹ ልክ መኪናው ጋ ደርሰው በሩን ሲከፍቱ ጠብቆ ሽጉጡን ደገነባቸው ። ድንጋጤያቸው ይታያል ። ወደ መኪናው እን ዲገቡ በእጁ ገፋ አደረጋቸው ። ያለምንም ጩኸት ገቡ ። ተሳካ ማለት ነው ።

አንጂላ ምን እንደሚፈጸም አታይም ፤ የምታየው እኔን ብቻ ነው ። ጩቤዋም ከጐኔ ለአፍታም ዞር አላለም ።

«አንጀላ! ሰምን?...» ስል አቋረጠችኝና ፣

«አፍሽን ዝጊ! የተባልሽውን ብቻ አድርጊ ። አንድ ነገር ብት ተነፍሺ እወጋሻለሁ» አለችኝ ።

ያለችውን ሁሉ ከመፈጸም ወደ ኋላ እንደማትል ዐውቄ ዝም አልኩ ። ሁሉም ሰው እንዲያውቅልኝ የምፈልገው ለሕይወቴ ስለ ፈራሁና ስለ ተገደድኩ የምፈጽመው እንጂ ፣ አሁን በመሠራት ላይ ለሚገኘው ወንጀል ሕጋዊ ተጠያቂ አለመሆኔን ነው ።

እንደ ገና በመስተዋቱ ተመለከትኩ ፤ የጽዳት መኪናው ሾፈር ቦታውን ይዞአል ። አጠገቡ ጃክ ተቀምጧል ። ሰዓቴን ተመለከትኩ ። ሁለት ሰዓት ከሃምሳ ሦስት ደቂቃ ነው ። ዝም ብለን ቆምን ። ሁለት ሰዓት ከሃምሳ ሰባት ደቂቃ ሲሆን ፣ የጽዳት መኪናው ሞተር አስነሥቶ ጉዞ ጀመረ ። በአጠገባችን ሲያልፍ ሾፈሩን በጨረፍታ አየሁት ፣ ፊቱ ዐመድ መስሎአል ፤ ለማልቀስም የከጀለው ይመስላል ።

ወዲያው የአንጂላ ጩቤ ልብሴን አልፎ ሰውነቴን ጠቅ አደረ ገኝ ። ሞተሩን አስነሥቼ የጽዳት መኪናውን ተከተልኩት ። በመኻላችን ሌላ መኪና እንዳይገባ በደምብ ተጠጋሁት ። ጉዞ እንደ ጀመርን የፖሊስ መኪኖች የአደጋ ምልክትና ጩኸት እያሰሙ በአጠገባችን አለፉ ። እነዚህ የተጠመደ ቦንብ ፍለጋ የሚሔዱ መሆናቸው ነው ። ይሄ ዲቃላ ተጫወተባቸው ።

ወደ ሃምሳ አምስተኛው መንገድ አመራንና ብንደን በርግና ልጆቹ የጌጣ ጌጥ መሸጫ ሱቅ ስንደርስ የጽዳት መኪናው ቆመ ። ከመኪናው ኋላ ሌላ መኪና ስለ ቆመ ትንሽ ራቅ ብዬ መኪናውን አቆምኩ ።

ሾፌሩና ጃክ መጥረጊያ ይዘው ከመኪና ወረዱ ። ጃክ አንድ እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ ሽጉጡን ይዞአል ። እበር ደርሰው ትንሽ እንደ ቆሙ የሱቁ በር መከፈት ጀመረ ። የጽዳት መኪናው የኋላ በር ወዲያው ተከፈተና አምስቱም አንገታቸውን አቀርቅረው በፍጥነት ተራምደው ሱቁ ውስጥ ገቡ ። በሩ ከኋላቸው ተዘጋ ። በዐይኔ ያየሁት ይሽንን ነው ። በኋላ ዲክ እንደ ነገረኝ ፣

በሩ እንደ ተከፈተ ጃክ ሾፌሩን ገፍትሮ ወለል ላይ ጣለውና ጄርሺስ ግራ እንደ ተጋባ በፍጥነት ሽጉጡን አውጥቶ ደገነበት ። ሌሎቹም መሣሪያዎቻቸውን በሠራተኞች ላይ ደገኑ ።

ሂሚና ጐስት በቀጥታ ወደ ጓዳ ሮጠው በመግባት ውስጥ የነበሩትን ሁለቱን ሠራተኞች እየገፈተሩ አምጥተው ሱቁ መኻል አቆሙ

ዋቸውና እያሰሩ መሬት አስተኝተው አፋቸው ላይ ፕላስተር መለጠፍ ሲጀምሩ፣ጀርቪስ«በጣም ከፍተኛና አደገኛ ስሕተት ነው የምትሠሩት» አላቸው ። ማንም የሰማው የለም ። ሁሉም መሣሪያ ይዘዋል ። ከሁለቱ ሠራተኞች ኮት ኪስ ውስጥም የሬዲዮ መገናኛ ተገኘ ።

ጐስት የታሰሩትን ሰዎች ሲጠብቅ ሌሎች ወደ የሥራቸው ተሰማሩ ። ጌጣጌጡ ሁሉ ተሰባስበው በተያዙት ተጣጣፊ ቦርሣዎች መሞላት ጀመሩ ። አንዳንድ ጌጦች ከነመያዣ ፓኬታቸው ተሞሉ ። ዲክ የሞሉትን ቦርሣዎች እየዘጋ በአንድ በኩል ያስቀምጣል ። ጃክ በየጊዜው ሰዓቱን እየተመለከተ በፍጥነት ጌጣጌጥ ከመደርደሪያው ላይ ይለቅማል ።

«ሥራ አምስት ፡ ሰዓር ፡ አምስት እንሒድ ካለ በኋላ አንድ ደቂቃ ቆዩ አለና የተሰበሰቡትን ፀሥራ አራት ቦርሣዎች ተመልክቶ ፡ «ለሽከም የሚመጡ አይደሉም ፡ በጣም ይከብዳሉ» አለ ። ክሊመንት «ቀላል ነው ሄሚ አራቱን ያዝ! » ሲል አዘዘ ።

«ስማይሊ ፡ ክሊመንትና ዲክ መጀመሪያ ውጡና የጽዳት መኪናው ውስጥ ግቡ ፡ ሄሚና ጐስት ቀጥላችሁ ሾፍረሌቱ ውስጥ ግቡ ፡ በሩን እንደ ዘጋሁ እክተላችኋለሁ ። መሮጥ የለም! በሉ ሒዱ!»አላቸው። ክሊመንትና ዲክ ሁለት ሁለት ቦርሣ ይዘው ወጡ። ስማይሊም በአንድ እጁ ሁለቱን ቦርሣ ይዞ አንድ እጁን ኪሱ ውስጥ በመክተት ተከተላቸው ። በፍጥነት ተራመዱና የመኪናውን የኋላ በር ከፍተው ቦርሣዎቹን ይዘው ገቡ ። እስማይሊ ተመለሰና የመኪናውን የፊት በር ከፍቶ የሾፈሩን ቦታ ያዘ ። ጩኸትና ግርግር የለም ፤ መንገደኛም ዞር ብሎ አላያቸውም።ሄሚ አራት ፡ ሆሊ ጐስት ሁለት ቦርሣ ተሸክመው በፍጥነት እኔ ወዳለሁበት መጥተው ቦርሣውን በመስኮት በኩል ወርውረው ከኋላ ገቡና ሞተር አስነሺ በደቂቃ ውስጥ ይመጣል አሉኝ ። ሞተሩን አስነሣሁትና ሁላችንም ወደ ሱቁ በራፍ ተመለከትን ። ጃክ ከሱቁ ወጥቶ የያዘውን ሁለት ቦርሣ በሩ ሥር አስቀመጠና ጫማውን እንደ ሚያስር ሰው ጐንበስ ብሎ ላስቲኩን በራፉ ላይ ሲያስቀምጥ አየሁት ። ሁለቱን ቦርሣ አንሥቶ ወደኛ መምጣት ሲጀምር ፡ ከዚህ በፊት ከእኛ ቸው ጋር በሰንሰለት የተያያዘ ቦርሣ እየያዙ ሱቁ ውስጥ ከሚገቡት መካከል ከአንዱ ጋር ፊት ለፊት ተገናኙ ። ጃክ ይቅርታ እንደ ማለት ፈገግ ብሎ አለፈና ወደ መኪናችን ተጠጋ ። ሄሚ የኋላውን በር ከፍቶ ቦርሣውን ከጃክ ተቀበለ ። ጃክ የፊቱን በር ከፍቶ ገባና፣«ዮፊ ከዚህ!» አለኝ ። ተስፈንጥሬ ስነሣ አንጂላ ወደ ኔ ተጠጋችና የጩቤዋ ጫፍ ነካ አደረገኝ ።

ይሄ ሁሉ ሲሆን ትኩረቴ ከጃክ ጋር ከተገናኘው ሰውዬ ላይ ነበር። ሰውየው ሱቁን መልከት አድርጎ ፊቱን ወደኛ አዙሮ በአንድ እግሩ በርከክ አለና ወደ ግራ ጐኑ እጁን ላክ በማድረግ ሽጉጥ ሲያወጣ የጽዳት መኪናው መንቀሳቀስ ጀምሮአል ። ረጋ ብሎ አነጣጠረ ። የሽጉጡ አቅጣጫ በቀጥታ እኔ ላይ መሆኑ ታየኝ።ወዲያው የጽዳት መኪናው የኋላ መስታወት ተከፈተና የጥቁር ሰው እጅና ሽጉጥ አየሁ ። ተተኩሶ የሱቅ መስተዋት ረገፈ።ጥይቱ ያለፈው ከተንበረከከው ሰውየ አናት ትንሽ ከፍ ብሎ ነው ።

«የሞተ ! ቀሽም !» አለ ጃክ ።

ሰውየው በደረቱ ለጥ አለና ። እንደ ገና በጽዳት መኪናው ላይ አነጣጠረ።ሦስት የተኩስ ድምፅ ሰማሁ። ከጽዳት መኪናው ወጥቶ የነበረው ጥቁር እጅና ሽጉጥ ወደ ውስጥ ተመለሰ ።

አሁን አካባቢው ሁሉ ሽብር ሆነ ፤ የመኪናውና የሰው ጩኸት ተደበላለቀ።የጽዳት መኪናው እፊቱ የነበረችውን መኪና በመግጨት ከመንገዱ አስወጥቶአት በፍጥነት ይጓዝ ጀመር ። የመኪናው የኋላ በር ሙሉ በሙሉ ተከፈተና ክሊመንት ቆሞ ይተኩስ ጀመር።መንገደኛው ሁሉ ከለላ ፍለጋ ሲሯሯጥ ከመንገደኞቹ አንዱ በተረጋጋ ሁኔታ ከኪሱ ረዥም ሽጉጥ አውጥቶ በሁለት እጁ በመያዝ ምላጩን መሳብ ጀመረ ። ሰውየው ሲታይ የተኩስ ልምምድ ላይ ያለ ይመስል ነበር ። በኋላ ግን፡ በጋዜጣ ላይ እንዳየነው ከሚስቱ ጋር ተቃጥሮ እሷን ለመጠበቅ የወጣ ፖሊስ መሆኑን ዐወቅን ።

የጽዳት መኪናው እየበረረ መንገዱን ቀጠለ ። እኛም ተከትለነው ረብሻው ወደ መረጋጋቱ ሲጠጋ፡«የተጐዳ ሰው አለ?» ብሎ ጃክ ጠየቀን ። እኛ መኪና ውስጥ የተጐዳ ሰው አልነበረም ። በኔ በኩል ግን ቀዳዳ አየሁ ። ሄሚም ቀዳዳውን በመገረም እያየ በወፍራም ጣቱ ቀዳዳውን እየነካካ ሳቀና ፡«ትንሽ ነበር የቀረው» አለ ።

የጽዳት መኪናው ቀድሞን ጋራዥ ደረሰና ስማይሊ በሩን ከፍ ቶልን ገባን ። ወዲያው በሩ ተዘጋ ።

ጃክ ከሾፍረሉቱ ወጥቶ አርቲፊሻል ዲሙን እየላጠ ወደ ጽዳት መኪናው ተጠጋና ጥይት የበሳሳውን ቀዳዳ ተመልክቶ «ጥሩ ተኳሾች ናቸው ፣ ማነው የተመታው» አለ፡«ረዳቱ ነው! የዳን መሰለህ ወዲያው ነው የሞተው! ክሊመንትም ሁለት ጥይት አግኝቶአል፡ አንዱ ከባድ ነው ፣ ወደ ...»አለ ስማይሊ ።

«እስቲ እንየው» አለ ጃክ ።

የመኪናው በር ሲከፈት ጠጋ ብየ ተመለከትከ።የመኪናው ወለል በደም ተጨመላልቋል።ረዳቱ እንደ ታሰረ ወለሉ ላይ ተዘርግቷል ። ዲክ እግሩን አጣምሮና በቦርሳ ተከቦ ፣ ፊቱ በመድ መስሎ ተቀምጦ አል ። ሰውነቱ ይንዘፈዘፋል ። ክሊመንት ራሱን ዲክ እግር ላይ አንተርሶ ተዘርግቷል ። ዲክ አንዱን ቦርሳ አነሣና ክሊመንትን አን ተርሶት ተኝሥቶ ቆመ ። የክሊመንት ዐይን እንደ ተጨፈነ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል ።

ጃክ «የወሻ ልጅ!» በማለት መኪናው ላይ ወጥቶ ወደ ክሊመ ንት ጐንበስ ብሎ አንድ ነገር ተናገረ ። ምን እንዳለ ግን አልሰማሁም ። ወረደና መኪናውን ደገፍ ብሎ ቆመና በረኸሙ ተነፈሰ ። ሲጋራ አው ጥቶ ለኮሰ ።

«ሆስፒታል መሔድ አለበት !» አልኩኝ ።

ሁሉም በመገረም ተመለከቱኝ ። «የሚድን ቢሆን ኖሮ እንወስ ደው ነበር ፣ ግን ዋናው የደም ሥሩ ተበጥሶአል ፤ አይተርፍም » አለ ጃክ ።

እንባና እልህ እየተናነቀኝ ፣ «አንተ ምን ታውቃለህ?» አልኩት።

«ዐውቃለሁ ! የሚድን ቢሆን አንቺና ዲክ ሆስፒታል እንድ ትወስዱት አደርግ ነበር ። ከዐሥርና ከአምስት ደቂቃ በላይ አይቆ ይም ፤ ውጪና ራስሽ ተመልከቺው ።»

መኪናው ላይ ወጣሁና የዲክን ትከሻ ተመርኩዤ ተመለከት ኩት ። ዲክ እንባ እየተናነቀው ፣ «ጄኒ መሞቱ ነው» አለኝ እየተን ቀጠቀጠ ።

ጐንበስ ብዬ አየሁት ። ደሙ እንደ ውሃ ይፈሳል ፣ ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ፣«አይዞህ ትድናለህ ፣ ወደ ሆስፒታል እንወስድሃለን ፣ ካንድ ሳምንት በኋላ ጤነኛ ሰው ትሆናለህ» እያልኩ ደጋግሜ ነገርኩት ።

ከንፈራ ሲንቀሳቀስ አይቼ ለመስማት ጆሮዬን ወደ አፉ አስጠ ጋሁት ። የሰማሁትን ማመን አልቻልኩም ፣ እነዚህ ሰዎች በሞት ጣር ተይዘውም ደህና ቃል አይወጣቸውም? «ደደብ ! » ብሎኝ እግሩን እጥፍ ዘርጋ አደረገና ጸጥ አለ ። ዝም ብዬ ከመኪናው ወረድኩ ፤ ሁሉም ቱታቸውን አውልቀዋል ። ጃክ መኪናውን ተደግፎ ሲጋራ ያጨሳል ።

«አሁን ደስ አለህ፣ ሞቷል» አልኩት ።

«ይሄ ሁሉ አንቺ ያቀድሽው ነው » አለኝ ምንም ሳይጸጸት ።

ዲክ ከመኪና ሲወርድ አይቼ ወደሱ ሐድኩ ። ቱታው በደም ተጨመላልቆአል ።

መሐረቡን አውጥቶ ለመጥረግ እየሞከረ፡«ጂኒ! በሕይወቱ ሙሉ እፊቱ ሰው ሲሞት አይቼ አላውቅም ነበር» አለ በአዘኔታ ።

ሁሉም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ጃክን ዝም ብለው ማየት ጀመሩ ።

«ችግሩ ...» አለ ጃክ ።

«ችግሩ በረፋ ብቻ ሳይሆን የነፍስ ግድያም ተፈጽሟል» አልኩት ።

«አፍሽን ዝጊ! ምን ማድረግ እንዳለብን ላስብበት» በማለት ጮኸብኝ ።

«የክሊመንት መሞት በጣም ትልቅ እንቅፋት ሆነብን። ከዘረፋው በኋላ እሱ ቤት ለመፈንድ ነበር ያቀድኩት ። አሁን እንግዲህ ዕቅዱ ከሱ ጋር ሞተ ። ከዚህ ቶሎ መውጣት አለብን ። እና የምንፈልገው ...» በማለት ጃክ አንገቱን ዞር አድርጎ ዲክን ተመለከተና ፡«አንተ ቤት ይሆናል » አለው ።

«ለምን ተብሎ ዲክ ቤት፣ ለምን እኔ ቤት እንሒድም፣» አልኩኝ ።

«አይሆንም! ብዙ ሰው የጽዳት መኪናውን አይቶታል፤መኪናው ከተነሣበት ጀምሮ በየቦታው የሚቆምበትን ፖሊሶች መመርመር ይጀምራሉ ። ያንችን ሽጣር ሲያገኙት በቀጥታ እቤትሽ ሊሔዱ ይችላሉ ። እስካሁንም እቤትሽ ደርሰው እየጠበቁሽ ሊሆን ይችላል ።»

«አመሰግናለሁ! ስላ ታስብልኛለህ!» አልኩት ሆዴ እየተቃጠለ።

«አንቺን ቢያጡ ጓደኞችሽንና ዘመዶችሽን ይጠይቃሉ ። ከት ንሽ ጊዜም በኋላ የዲክን እድራሻ ሲያገኙ ወደሱ ቤት መሔዳቸው አይቀርም ። ግን እንዳንቺ ቤት እዚያ ቶሎ አይደርሱም ። እስከዚያ እኛ ከዲክ ቤት እንወጣለን ። ደግሞም አመቺ ነው ። አይደለም እንዴ ዲክ፧»

ዲክ መልስ ሳይሰጥ ዝም አለ ።

ቦርሳዎቹን በቮልስዋገኑና በፎርዱ ውስጥ አስገቡና ፡«እኔ ቮል ሱን እነዳለሁ ። ጂኒና አንጀላ ከኔ ጋር ትሆናላችሁ ፤ስማይሊ ፎርዱን ትነዳለህ፤አብሪውህ ዲክ ፡ ሂሚና ጐስት ይሆናሉ» ብሎ ጃክ ከፎርዱ ውስጥ ረቂቅ መጽሐፌን አውጥቶ ወደ ቮልሱ ገባና እንሒድ አለ ።

ጃክ እንዳለው የዲክ ቤት አመቺ ነበር ። ወዲያ ወዲህ የሚል ሰው አላጋጠመንም ።

ዲክ አሁንም ድንጋጤው አልለቀቀውም፤ከኪሱ የቤቱን ቁልፍ አውጥቶ ሰጠ ። አንጂላ አሁንም ከኔ አጠገብ አልተለየችኝም ። ዲክንም ስማይሊ አጅቦታል ።

ተራ በተራ ቦርሳዎቹን ይዘን እቤት ውስጥ ገባንና በሩ ከውስጥ ተቆለፈ ። ሁሉም የድካም ስሜት ያለበት ስለሆነ በአቅራቢያው ባገኘው ወንበር ላይ ቁጭ አለ ።

ጃክ ዲክን «መጠጥ ካለህ ስጠን» ብሎ በትሕትና ጠየቀው ። ዲክ አንድ ጠርሙስ ቮድካ አምጥቶልን መጠጣት ጀመርን ።

«ዛሬ የልደት በዓላችን ነው ፤ ምን እንዳለን እንይ እስቲ...» በማለት ጠረጴዛ ላይ ያለውን መጽሐፍና ጋዜጣ ወደ መሬት ጥሎ አንዱን ቦርሳ አነሣና ቀስ ብሎ ዘረገፈው ። ሁላችንም ወደ ጠረጴዛው ተጠግተን ጌጣጌጦቹን በአንክሮ እየተመለከትን አደነቅን ።

ለተወሰነ ሰዓት ጌጦቹ የተሰረቁና የሁለት ሰዎች ሕይወትም ያለፈባቸው መሆኑን እረሳሁት ።

ጃክ አንድ የአበባ ቅርፅ ያለበት አንባር አነሣና በከበሬታ ጐንበስ ብሎ ለአንጂላ ሰጣት ።

አምባሩን ተቀበለችና የእውነት የተሰጣት መሆኑን በመጠራጠር፡ «እመሰግናለሁ» አለች ። ስጦታው ሳያስገርማት አልቀረም ።

«ለኔስ» ብዬ ልጮህ ምንም አልቀረኝም ። አፍሬ ካፈ መለስኩት።

እስማይሊ ወደ ጠረጴዛው እየተጠጋ ፡ «ምን ያህል ይሆናል ብለህ ትገምታለህ ጃክ?» አለው ።

ጃክ ወደ ጠረጴዛው እየተመለከተ ፡ «አንተስ ምን ያህል ትገምታለህ?» ሲል በጥያቄ መለሰለት ።

«ቢያንስ ሩብ ሚሊዮን።»

«አዎ! በትንሹ ይሆናል ወይም ይበልጣል ። ግን በሩብ ሚሊዮን እንያዘው » በማለት ሌላውን ቦርሣ አንሥቶ ዘረገፈው ። ይሄ ጌጣጌጥ ከነፓኬቱ ከጓዳ የተለቀመው መሰለኝ ፡ ልክ ልጆች ለልደት በዓላቸው የተገዛላቸውን ስጦታ ለማየት እንደሚጓጉ እኛም ለማየት ተሰባሰብን ። የተለያየ ቅርፅና ቀለም ያላቸው በአልማዝ የተሠሩ ሐብሎች ፡ ቀለበቶችና አምባሮች ሲሆኑ ፡ በጣም አንጸባራቂ ናቸው ። ሁሉም አፉን

ከፍቶ በመደነቅ ሲመለከት ከቆየ በኋላ፡ ወይናችን ጌጡ ከወጣበት ፓኬት ላይ ወረፋ ።

ፓኬቱ ላይ፡ «ዴቨልት ብሮስ ሳንፍራንሲስኮ» የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል ።

ጐስት በመገረም አንዱን ፓኬት አንሥቶ፡ «ምንድነው ይሄ?» በማለት ጠየቀ ።

«ረጋ በል ፡ ያየነው አንዱን ቦርሣ ነው ። ይሄ ብቻ ከሆነ ብንደን በርግና ልጆቹ የተበደሩት ወይም መቋቋሚያ የተሰጣቸው ሊሆን ይችላል ። እስቲ ሌሎችንም እንይ!»

ለዐሥራ አምስት ደቂቃ ሁላችንም በገመታ ቦርሣዎቹን እየከፈትን ማየት ጀመርን። የመደናገጥም ሁኔታ ስለ ነበር፡ አንዳንድ ጌጦች በየወለሉ ሲወድቁ ለማንሣት የሞከረ አንድም ሰው አልነበረም ።

በመጨረሻ ሁሉም ቦርሣ ተዘረገፈና እርስ በርስ ዝም ብለን መተያየት ጀመርን ። ይሄ ጌጥ ከሳንፍራንሲስኮ የተዘረፈ መሆኑ ገባን ።

ጃክን ተመለከትኩት፤ ዝም ብሎ ከንፈሩን ይነክሳል ። ምን እንደሚያስብ ማወቅ አልቻልኩም ።

ስማይሊ የተቆለለውን ጌጥ እየተመለከተ ፡ «በሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ሽፋን ዘረፋ የሚያካሒድ የሌቦች ድርጅት !» አለ ።

ዲክ ወደ ኔ ዞረና ፡ «ጆኒ! እነዚያ ከእጃቸው ጋር በሰንሰለት የተያያዘ ቦርሣ ይዘው ከሱቁ የሚገቡና የሚወጡት አሻሻጮች አይደሉም ማለት ነው ?»

«መሆኑ ነው ፤ እስካሁን አላወቅም ነበር ። እነዚህ ሰዎች ከተለያየ አገር የሚዘረፈውን ጌጥ በቦርሣ የሚያመላልሱ ሳይሆኑ አይቀርም» አልኩት ።

ስማይሊ ፡ «የሌቦች ድርጅት! በመጨረሻ... በመጨረሻ...» እያለ ፈገግታውን አቆመና፡ «የዚህ ዓይነት ትልቅ ዘረፋ የሚያከናውን ካለሌቦች ድርጅት ሌላ የለም» አለ ።

«እውነትም ያለምንም ጥርጥር ትልቅ ስሕተት ሠርተናል» አለ ጃክ ።

«ምን? ማነው እንደዚህ ያለህ?» አልኩት ።
«ጆርቪስ !»
«አንቶኒዮ ሮሲን ! ማለትህ ነው ?»

«ማን?» አለኝ ስማይሊ በመጠራጠር ።
«የሱቁ ኃላፊ እውነተኛ ስሙ አንቶኒዮ ሮሲ ነው» አልኩት ።

እስማይሊ በድንጋጤ ፊቱ ዐመድ መሰለና ፥ «አንተ ታውቅ ነበር?» ብሎ ጃክ ላይ አፈጠጠበት ።

ጃክ ትከሻውን ነቀነቀና ፥ «በመጽሐፍዋ ረቂቅ ውስጥ ስሙን አይቼው ነበር» አለ ።

«ታዲያ ለምን አልነገርከንም?»

«እንደዚህ ይሆናል ብዬ መቼ ገመትኩ ። ስሙን ሳይ ምንም አልመሰለኝም ።»

«ወይኔ! ወይኔ! ሁላችንም አልቆልናል ፤ ሚኞች ነን ። አንቶኒዮ ሮሲ ቀላል ሰው መሰለህ? ድርጅቱን አናግተነዋል ። ጉድ አደረግከን፣ አንተ ደደብ!» ብሎ እስማይሊ ጮኸበት ።

«አሁን ንብረቱን ማሸሽ እንችላለን ፤ ለትንሽ ደቂቃ ታገሠኝ ። በዚህ ሥራ ከታወቀው ሚስተር ኮን ጋር ተነጋግሬአለሁ» ብሎ የዲ ክን ስልክ አንሥቶ ደወለ ።

«ሃሎ! ሳም ሞሪሰን ነኝ ፥ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ተነጋግረን ነበር» አለና ወዲያው፥«ምን? ምን? ቆይ! ቆይ...» ስልኩን ዘግቶ የሐዘን ፊገግታ እያሳየ ፦ «ከዚህ በፊት እንደማያውቀኝና ሊያወቀኝም እንደማይፈልግ» ነገረኝ ብሎ ዝም አለ ።

እስማይሊ ወደ ጌጡ ቀረብ ብሎ፥«ይሄው ነው ። እኔ ከዚህ ጌጥ ውስጥ የምፈልገው የለም ፤ ሁሉም የናንተ ነው ። ለተወሰነ ጊዜ በሕይወት መኖር ስለምፈልግ ።

ከዚህ ውጭ መሆኔን ዕወቁት » አለ ።

«አዎ! ውጭ ለመሆን ትችላለህ» አለ ጃክ በሽሙጥ ።

«አሳምሬ እወጣለሁ» አለ ስማይሊ ፥ የውሸት ሳቅ እየሳቀ ። «በቀላሉ እወጣለሁ ፤ ግርግር አልፈልግም» ብሎ እንደገና ፈገግ አለና ከጃኬቱ ኪስ ሽጉጡን አወጣ ። ማንም አልተንቀሳቀሰም ። ሁላችንም ክው አልን ።

«በምንም ዓይነት መንገድ መውጣት አትችልም ። ከወጣህ በኋላ ለድርጅቱ ጠቁመህ ልታስፈጅንና አንተ ሕይወትህን ልታድን? በምንም ዓይነት የማይሞከር ነው» በማለት ጃክ ወደ ስማይሊ ጠጋ አለ ። የሁሉም ትኩረት ጃክ እንቅስቃሴ ላይ ነበር ። ምናልባት ይሄ

እንዲሆን ሆን ብሎ ያሰበው መሰለኝ ፣ ምክንያቱም ስማይሊ ጃክ ላይ በማተኮር ላይ እንዳለ የተንቀሳቀሰው ሄሚ ነበር ። ጃክ... «ሄሚ ፈጣን ነው» ብሎ ከዚህ በፊት የነገረኝ ለካ እውነት ነው ።

ሄሚ በአንድ እጁ ሽጉጥ የያዘውን የስማይሊን እጅ ይዞ ወደ ራሱ ጠመዘዘው ። ሁለቱም ተጣብቀው ተፋጠጡ ፤ አንዳችንም ለመገላገል ዕድል ሳይገጥመን ሽጉጡ ሦስት ጊዜ ተተኮሰ ። ሲመን የመጽሐፍ አሳታሚው ድርጅት እርታዒ መሣሪያ ሲተኮስ «ካቻው» አይልም ያለኝ እውነቱን ነበር ። አሁንም የመሣሪያው ድምፅ «ባንግ» ! ወይም «ብላም» ! አላለም። በሁለቱ ወፍራም ሰዎች መካከል የተተኮሰው መሣሪያ ድምፅ «ደፍ !» የሚል ነው ።

ሄሚ የያዘውን እጅ ለቀቀና ዘወር አለ ። ስማይሊ ለትንሽ ጊዜ ቆም አለና ዐይኑ እየተገለባበጠ ቤቱን በሚነቀንቅ ድምፅ ወለሉ ላይ ወደቀ ። ወዲያው ሰውነቱ ዝርግት ብሎ ሁለት ጊዜ ፈርገጥ ፈርገጥ አለና ጸጥ አለ ።

ጃክ ሬሳውን በእግሩ ሁለት ጊዜ ረገጠና ፡ «ይሄ ከሃዲ ! እንደሱ ሐሳብ ቢሆን ኖሮ ሸጠን ነበረ» አለ በንዴት ።

ይሄን ሁኔታ ሳይ ራሴን መሳት ነበረብኝ ። ግን ባለፈው አንድ ሰዓት ውስጥ ሦስት ሰው ሲሞት ማየቴ ስለ ነበረ ምንም አልመሰለኝም ። እርግጠኛ ነኝ ።

ሆን ብየ አይመስለኝም ። በወይኔ እያየሁ ፡ በጆሮዬ እየሰማሁ የሽጉጡ ድምፅ ዝም ብሎ ጩኸት ብቻ...የሚፈስ ደም ሁሉ ፡ ቀይ ፈሳሽ ነገር ። ሬሳ ሁሉ ፡ አሻንጉሊት መሰለኝ እንጂ ፡ የሰው ውድ ሕይወት እየጠፋ አልመሰልሽ አለኝ ።

«ሄሚ! በጣም ጥሩ ነው ያደረከው ፤ አመሰግናለሁ» አለ ጃክ በመደሰት መልክ ። «ምንም አይደለም! ድሮም ይሄን ሰው አልወደድኩም ፡ ከዚህ በፊትም ደደብ ብሎ ሰድቦኝ ነበር» አለ ሄሚ ።

ጃክና ጐስት ሬሳውን ተሸክመው አንድ ክፍል አስገብተው በሩን ዘጉት ።

ጃክ ቮድካ ቅድቶልን መጠጣት ጀመርን ፤ አንድም ሰው ወደ ተቆለለው ጌጥ ፊቱን ያዞረ አልነበረም ። ለማንኛችንም የተቆለለው ጌጥ ምናችንም አልመሰለንም ። አሁን ጭንቀቱ ሕይወትን የማዳን ሐሳብ ነው ።

«አዳምጡኝ !» አለ ጃክ ፡ ራሱን ወደ ጣራው ቀና አድርጎ ኮር ኒሱን እየተመለከተ ። «በአሁኑ ሰዓት ከከተማው የምንወጣ ስለሚ

መስላቸው ፣ የከተማው ኬላ በሙሉ ቁጥጥር ይደረግበታል ። ስለዚህ በፖሊሶች ታጥረናል ማለት ነው ። ከሁሉም መጥፎውና የሚብሰው የተሰረቀው ድርጅት እንቅስቃሴ ነው ። የፖሊሶቹ በድርጅቱ ዐይን ሲነጻጸር ይሄን ያህል የሚያሠጋን አይደለም ። ድርጅቱ በየሥርቻው እኛን ለማፈላለግ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ያሠማራል ። እንደምገምተው አለቤርጎአችን ደርሰው እዚህ ቤት ለመምጣት ሁለት ቀን ይፈጅ ባቸዋል...»

አቋረጥኩትና በመገረም ፡ «እንዴት ሊያደርጉት ይችላሉ ?» አልኩኝ ።

«በጣም ቀላል ! የጋራዡ ዘበኛ የክሊመንትንና የረዳቱን ፊሳ ያገኛል ። ለፖሊስ ይነግራል ። ፖሊሶች ስለ ክሊመንት መረጃ ካሰ ባሰቡ በኋላ ስለኔ ያውቃሉ ። ፖሊሶች ዐወቁ ማለት ድርጅቱ ዐወቀ ማለት ስለ ሆነ፣ ባንድ ጊዜ ለስዎቻቸው ያሰራጩታል ። ለሚጠቁማ ቸው ሁሉ ገንዘብ ይሰጣሉ ። አሁን የሚሻለው መለያየቱ ነው ። ስድስታችንም በአንድ ላይ የምንጓዝበት ምንም መንገድ የለም ። ጐስት ምን ታስባለህ ?»

ጐስት ወለሉን በእግሩ እየቆረቆረና ጣቱን እያንቋቋ ወደ አንጂላ ዞረና በስጋንኛ ቋንቋ ለተወሰነ ጊዜ ተነጋገሩ ። ፊታቸው ላይ ፍር ሃትና ጭንቀት ይታይበታል ። «ሁለታችን ወደ ስፓንሽ ሑርለም መሔድ ስለምንችል እንለያችኋለን» አለ ።

ጃክ ያለምንም ጭንቀት ፡ «አዎ ትችላላችሁ» አላቸው ። ያለመ ጨነቁ ለኔም እፎይታ ተሰማኝ ።

«አንተና አንጂላ ጥሩ የመደበቂያ ቦታ አግኝታችኋል ። ወደ ፊትም ጥሩ ዕድል ይገጥማችኋል » አለና ወደ ተቆለለው ጌጥ ፊቱን አዙሮ ፡ «በሰምምነታችን መሠረት የሚደርሳችሁን ክፍያ እርሱትና የምትፈልጉትን ያህል ውሰዱ ፤ እንደኔ ከሆነ አነስተኞቹንና በቀላሉ ሊሸጡ የሚችሉትን ጌጦች ብትወስዱ ይሻላችኋል ።»

ልክ እንደ ተመከሩት ቀለበት ፡ ሐብልና የጆሮ ጉትቻዎችን ብቻ መረጡና አንጂላ በቦርሳዋ ስትሞላ ጐስትም በኪሱ አጨቀ ።

«ጃክ ! በጣም ጥሩ ነው ። ልክ እንዳልከን ተሳካልን» አለ ጐስት።

«አዎ ጥሩ ዕድል ነው ፤ መልካም የገና በዓል ይሁንላችሁ ! ጌጣ ጌጡን ስትሸጡ ተጠንቀቁ ፤ ከቆሙት መኪናዎች አንዱን ትፈልጋለህ?»

«አያስፈልገንም ፤ በእግራችን እንሔዳለን» አለና ወደ ሄሚ ተጠ

፥«ላንተም መልካም ዕድል እመኝልሃለሁ ። ለራስህም ተጠንቀቅ» አለው ።

«ምን? አሃ! እሺ መልካም ዕድል» አለ ። አንጂላም ዐዋቂ ሰዎች ናችሁ ብሳን ከቤቱ ወጡ ።

ጃክ በሩን መልሶ ቆለፈና ፥«ጐስት ጐበዝ ነው በጥንቃቄ በየቦታው ይሸጠዋል፤ይሳካላቸዋል ። ሄሚ! አንተስ መለየት ትፈልጋለህ?» አለው ።

ሄሚ የያዘውን መሰኪያ እየተመለከተ ፥«ችግር የማይፈጥር ከሆነ ካንተ ጋር መቆየት ይሻለኛል » ሲል መለሰለት ።

«ከፈለግህ በኔ በኩል ችግር የለም» ብሎ አጠገቡ ካለው ወንበር ላይ ድካም በተሞላበት ስሜት ቁጭ አለ ። ጉልበቱ ሁሉ የተሟጠጠ ይመስላል ። ሰምን ያህል ጊዜ ያለዕረፍት ሊቆይ እንደሚችል አላውቅም ። ከዚህ ሁሉ ነጻ ካልሆነ የሚያርፍ አልመሰለኝም ። ለነገሩ ነው እንጂ ፥ መጀመሪያስ ቢሆን መቼ ነጻ ሰው የሚባል ነበረ?

ቮድካውን እየጠጣ ፊቱን በመሰኪያ ጋርዶ እኔንና ዲክን ተመለከተንና ፥«እናንተ ቀራችሁ ። የተወሰኑ ምርጫዎች አሉአችሁ ። እኔና ሄሚ ወደ ይቡብ ሚያሚ እንሬዳለን ። እዚህ ካገኙን አለቀልን ማለት ነው፤ ስለዚህ ከኛ ጋራ መሔድ ትችላላችሁ ። ሌላው ምርጫችሁ እዚህ ቀርታችሁ ፥ በሰው መሞት ፥ በመኪናና በጌጣጌጥ ዝርፊያ ተጠያቂነት ዕድላችሁን መሞከር ነው ። ይሄን ከወሰናችሁ እኛ ከዚህ ወጥተን ለመሔድ የሚያስችለንን ያህል ጊዜ ለማግኘት አጥብቀን እናስራችኋለን ፤ ከወጣን በኋላ እስራችሁን በትግል ተላቃችሁ እንደልባችሁ በመጮህ ፖሊስ ጠርታችሁ እጃችሁን መስጠት ትችላላችሁ » አለን ።

«መጽሐፌን ትተውልኛለህ ?» ስል ጠየቅኩት ።

«አልተውልሽም ። ይህ መጽሐፍ ለኔ ኢንሹራንሴ ነው ። ከሁለት አንዱን ተነጋግራችሁ ለመወሰን ከፈለጋችሁ ፥ እኔና ሄሚ የማንሰማችሁ ጥግ ቦታ ሆናችሁ ተነጋገሩ ። ከዚህ ክፍል ውጭ ግን አይቻልም ።»

ከዲክ ጋር ተያየንና ወደ መስኮቱ ተጠጋን ፥ ጃክና ሄሚ ካሉበት አልተንቀሳቀሱም ። እግራቸውን አንፈራጠው ዐይናቸውን አሽልበዋል። ሰዎቹ ምን ያህል ፈጣን እንደሆኑ ስለአየሁ ወደ በሩ ለመሮጥ አልሞከርኩም ።

«ዲክ! ምን ታስባለህ! ምን ማድረግ አለብን?» አልኩት ።

«ምን ዐውቃለሁ! የኛ ሁኔታ በሕግ ዐይን ሲታይ እንዴት ይሆን!»

«ትልቅ ችግር ነው ። እኔ የሕግ ባለሙያ አይደለሁም ፤ እንደሚታየኝ ከሆነ እዚሁ ቀርተን ተገደን የፊጸምነው መሆኑን ለፖሊስ ማስረዳት ነው ።»

«አሁን የምትይኝ እውነትሽን ነው?» አለ በንዴት ።

«አዎና! እኔ በጩቤ ፣ አንተ በሽጉጥ ተገደን ያደረግነው ነው ። ግን 'ፖሊሶች ለዐሥራ ሁለት ሰዓት በቁጥጥር ሥር ሲያውሉአችሁ ዕቅዳቸውን ለማደናቀፍ ለምን አልጮኻችሁም ? ወይም በድንጋጤ እራሱን እንደሳተ ሰው አልሆናችሁም' ብለው ይጠይቁናል ። ተገደን ያደረግነው መሆኑን ለማሳመን በጣም አስቸጋሪ ነው ። ከሁሉ አስቸጋሪው ደግሞ የኔ መጽሐፍ ነው ። ጀክም ከእጁ የሚለየው አይደለም ። ድንገት በፖሊሶች ቢያዝ የዘረፋው ዋና መሪዎች እኛ ስለመሆናችን በመረጃነት መጽሐፉን ይጠቀምበታል ። ለዚህም ነው ኢንሹራንሴ ነው ያለኝ ።»

«አንቺ መጽሐፍ ለመጻፍ ያደረግሽው ጥናት እንጂ ፣ ለመዝረፍ ሆን ብለሽ ያሰብሽው አይደለም።»

«ዲክ ይሄ የድሮ ወሬ ነው ። በየጊዜው በወንጀል ሥራ የሚያዙ ሁሉ ጸሐፊ ስለሆንኩ ለጥናት ብዬ ነው እንጂ ፣ ለመዝረፍ አይደለም እያሉ እንደሚናገሩ ታውቃለህ! እኔ የአውነቴን ጽሑፉ ጥናት መሆኑን እነግራቸዋለሁ ። መጽሐፉን ሲያነቡት ዘረፋው ያተኮረው በአንድ ሱቅ ላይ መሆኑን ፣ ለሦስት ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት እንደሆነ ያውቁታል ። ከዚያ ምን የሚሉኝ ይመስልሃል ? የሚያምነኝ አይኖርም ፣ ይስቁብኛል ፤ ቢሆንም...»

«ጄኒ! እኛ ወንጀለኞች አይደለንም ። ከዚህ በፊትም ወንጀል ሠርተን አናውቅም ። ሰላማዊ ዜጐች መሆናችን ስለሚታወቅ ፣ ለዘረፋ ምንም ፍላጐት እንዳልነበረን ማሳመን ይቻላል።»

«ያልከው ሊሆን ይችላል ። ግን ገበዝ ዓቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ በዘረፋው የተሳተፍንበትን ምክንያት ሲያስረዳ ፣ ዘረፋውን ያካሔድ ነው ፣ ምን ያህል ዐዋቂ መሆናችንን ለማሳየት ፣ ወይም ለዝና ስንል የፊጸምነው ጀብዱ አስመስሎ በማቅረብ ፍርድ ቤቱን ሊያሳምን ይችላል ። ግን ሌላው ቢቀር ወንጀለኛ መሆናችንን ለማሳመን መጽሐፉ ፖሊሶች እጅ ከገባ መጽሐፉ ራሱ በቂ ማስረጃ ይሆናል ።»

«ስለዚህ እጃችንን ለፖሊሶች ብንሰጥ ከተጠያቂነት እንድንም ነው የምትይው ?»

«ይሄን አላልኩም ። እኔ እንደማስበው ከሆነ፡ለተወሰነ ጊዜ ከዚህ ጠፍተን ከተዘረፈው ንብረት ተጠቃሚ ካልሆንን ፡ ዘረፋውን ለመፈጸም ፍላጐት እንዳልነበረን ሊያረጋግጥልን የሚችል የሕግ ጠበቃ ካገኘን በኋላ ፡ እጃችንን ብንሰጥ በቀላሉ በማስጠንቀቂያ ሊያልፉን ይችላሉ ። ይሄን ዕድል መሞከር ትፈልጋለህ?»

ዝም ብሎ ሲያየኝ ቆየና ፡ «ጂኒ አንቺ ማድረግ ያለብሽን አድርጊ ። እኔም ማድረግ የሚገባኝን እደርጋለሁ ። ማለቴ ሁለታችንም የሚያስተማምን ነገር መፈጸም የለብንም ። ካልተስማማን መለያየት እንችላለን» አለኝ ።

በመጨረም ተመለከትኩትና ፡ «አዎ! በማትፈልገው ነገር ውስጥ እንድትገባ አልፈልግም ። ራስህን እንዴት ማዳን እንዳለብህ የምትወስነው አንተ ነህ ።»

«ሲጋራ አለሽ?» ብሎ ጠየቀኝ ። ወደ ጠረጴዛው ሔጄ ሲጋራና ክብሪት አንሥቼ ወደ ዳክ ስመለስ ጃክ ፊቱን ወደኔ አዙሮ ምን እንደ ማደርግ ተመለከተኝ ።

«የሚገርምሽ የድዳት መኪናው ላይ ጥይት እንደ በረዶ ሲፈስበት ወለሉ ላይ ለጥ ብዬ ተኛሁ ። አጠገቤ ታስሮ የተኛውን ረዳት ተመለከትኩት።እንዴት ደስ የሚል ወጣት ልጅ ነበር! ወዲያው በጥይት ተመታና ሞተ ። ከዚያም ጋራዥ ከደረስን በኋላ ፡ አጠገቤ ክሊመንት ሞተ ። እዚህም ከደረስንና ጌጡን ካየን በኋላ ስማይሊም ሞተ...»

«እና? ምን ለማለት ነው የፈለከው?» አልኩት ጤነኛነቱ እያጠራጠረኝ ።

«ሕይወቴን ሙሉ ምን ዓይነት ሰላማዊ ኑሮ እንደ ኖርኩና ወደ ፊትም ጥሩ ኑሮ እንደሚገጥመኝ ነበር የማልመው ። አሁን ግን ሌላ ሆነ ።»

ዝም ብየ ተመለከትኩት ። የሚለው ሁሉ ለራሱ ትርጉም አለው ። ባጋጠመው ችግር እንደ ተደናገጠ ይሰማኛል ። ይሄ ችግር ሲያጋጥመው የሚጋፈጥ አልመሰለኝም ነበር ። አሁን ግን ድንጋጤው አመለካከቱን ለወጠው ።

ከዚህ በፊት አይቶት በማያውቀው ኑሮ ውስጥ ለመግባት ፈቃደኛ መሆኑን ተረዳሁት ። ድሮ ስለ ጉብዝና ፡ ፍርሃት ፡ ፍቅርና ጥላቻ

ምንም ዕውቀት የነበረው አልመሰለኝም ። ቃላቱን የሚያውቃቸው በመዝገበ ቃላት መጻፋቸውን እና ፍቺአቸውን ነው ። አሁን ግንባኑሮ ውስጥ ምን እንደ ሆኑ ለማየት የጓጓ ይመስላል ።

«እርግጠኛ አይደለሁም እንጂ ፣ ወደ ፊት በደምብ ስረዳው እነ ግርሻለሁ ።»

«ጃክን ትወደዋለህ እንዴ ?»

መልስ ሳይመልስልኝ ሲቆይ ያልሰማኝ መስሎኝ ነበር ። ትክ ብሎ አየኝና ግራ በመጋባትና በመጨነቅ መልክ ፣ «እኔ እንጃ! ምናልባት እወደው ይሆናል ። ግን በትክክል አላውቅም» አለኝ ።

«እና ከሱ ጋር ትሔዳለህ?»

ራሱን በመነቅነቅ «እም» አለኝ ።

«እኔም እሔዳለሁ ።»

«ጂኒ! ለኔ ብለሽ መሆን የለበትም ።»

«አይደለም ! እኔም የራሴ ምክንያት አለኝ ።»

«ምን ዓይነት ምክንያት ?»

«አንደኛ ይሄን መጽሐፍ ለመጻፍ ብዙ የደከምኩበትና ጊዜም ያጠፋሁበት ስለ ሆነ ፣ መጽሐፉን መልሼ እጂ ለማስገባት ጥረት ሳላ ደርግ መሰየት አልፈልግም። ሁለተኛ ደግሞ ፣ የዚህን መጨረሻ ማየት እፈልጋለሁ ።»

«ምን? ዕብድ ነሽ !»

«አይደለሁም አሳታሚዬ ሶልፋበር፣ አንባቢያን እውነተኝነት ያላቸውና መጨረሻቸውም የሚያምር መጽሐፍ ማንበብ ይፈልጋሉ ብሎኛል። ይሄ ወንጀል በምን ዓይነት እንደሚፈጸም እግዚአብሔር ይወቀው። እስካሁን የፈጸምኩት ሁሉ ስሕተት ነው ። ስለዚህ ወደ ኋላ ማለት የለብኝም። አብሬ እጓዛለሁ። ከዚህ ሌላ የሚሰማኝ ፣ የሰው መሣሪያ መሆን አልፈልግም ። ጃክ አሁን መሣሪያው አድርጎ እየተጠቀመብን ነው ። ስለዚህ አብሬ ቆይቼ ሊጠቀምብኝ እንደማይችልና ባዘጋጀው ወጥመድ ራሱን ለመያዝ የምችልና የማልችል መሆኔን ማየት እፈልጋለሁ ።»

«ቅደም ተከደጂ ነው እያልሽ ስትናገሪው የነበረው ሐሳብሽ ሁሉ በኖ ጠፋና የዘረፋው ሙሉ ተባባሪ ልትሆኚ ነው?»

«ድሮም ቢሆን ሕገ ወጥ ሥራዎችን እቃወማለሁ ።»

«ከሦስት ወራት በፊት ተቃውመሽ ቢሆን ጥሩ ነበር» አለና ጠጋ ብሎ ጉንጬን ሳም አረገኝ ።

ወደ ጀክ ተመለስኩና፣«ካንተ ጋር አብረን እንሔዳለን» አልኩት።

ጀክ በረሸሙ በእፎይታ ተነፈሰና ፣ «ይህ አጋጣሚ በሕይወቱ አይቼው የማላውቀው ረሽሞና ትልቅ ቁማር ነው ። በጣም ጥሩ ! አሁን በአሸናፊነት ለመውጣት ጥረት ማድረግ ይቀረናል » አለን ።

«እውነት እንነጋገርና እዚህ መቅረት እንፈልጋለን ብንልህ ኖሮ እትቃወመንም ነበር?» ስል ጠየቅኩት ።

«በምንም ዓይነት አልቃወምም ።»

አላመንኩትም ፤ አንዱ ምክንያት ከጀክ ጋር ለመሔድ የወሰንኩትና ለዲክም ያልነገርኩት ንምቢ ብለን ብንቀር ሁለታችንንም ይገለናል በሚል ፍርሃት ነው ።

ጀክ ክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየተንጐራደደ ፣«የአንድ ቀን ወይም የሁለት ቀን ጊዜ ይኖረናል። እዚያ ክፍል ውስጥ ያለውም አስከሬን እስከ ሁለት ቀን አይሸተም ። አስተማማኝ የሚሆነው ዛሬ ማታ ከዚህ ብንወጣ ነው ። ሞስታችንም መንገድ ላይ ብንታይ ፣ ጥሞት ያዩን ቱታ ለብሰን ስለ ሆነ የሚለየን የለም ። ችግሩ ያንቺ ብቻ ነው ።»

«የኔ ችግር ምንድነው?»

በመናደድ መልክ ፣«መኪናሽን እንዳገኙት ወደ ቤትሽ በመሔድ ፎቶግራፍሽንና ስለ ጠቅላላው አቋምሽ ከጐረቤቶችሽ ወይም ከጓደኞችሽ ጠይቀው በነገው ዕለት በየቴሌቪዥኑና በየጋዜጣው ትታያለሽ ። ስለዚህ እንደ ገና ወደ ቢያነት መለወጥ አለብሽ ።»

«ወደ ቢያነት መለወጥ አልፈልግም ። ለዚያውም የቢያ ዕቃዎች ሁሉ ያሉት እቤቱ ነው ።»

«ይሄ ችግር አይደለም ። ወደ ከተማ ወጥቼ አንቺን ሊለውጥሽ የሚችል ልብስና ቀይ አርቲፊሻል ጸጉር እገዛለሁ ።»

«ቀይ ጸጉር አልወድም ።»

«ይሄን ደደብ ሞንቅላትሽን ትንሽ አስቢበት! እቤትሽ ሲሔዱ የቢያን አርቲፊሻል ጸጉር ያገኙታል።ስለዚህ ከበፊቱ የተለየ ጸጉር ነው የሚያስፈልግሽ ። ከከተማም እስክንወጣ ሆቴል መመገብ ስለማንችል ለስንቃችን የሚሆን ምግብ መግዛት አለብኝ ።»

«ለዕቃና ለምግብ መግዣ ገንዘብ ከየት ታመጣለህ?» አልኩት ። በጥርጣሬ ፈገግ አለና በጣቱ የተቆለለውን ጌጥ እየነካ፡ «የተወሰነ ቀለበትና ሐብል መሸጥ ይቻላል ። ፖሊሶች ስለ ጠፉት ጌጦች ዓይነት አስኪያውቁ ድረስ እኛ ካገር እንጠፋለን ። ዲክ ! እኔ እንደ ወጣሁ ልብስህን ቀይር ፤ የለበስከው በደም ተጨማልቋል ፤ ሌላው ! ቦርሳ አለህ?»

«ሁለት የቆዳ ቦርሳና አንድ የመንገድ ሻንጣ አለኝ ።»

«ጥሩ! ጌጦቹ እንዳይንጠባጠቡ ፎጣና የተወሰነ ሽሚዝ ከቦርሳዎች ውስጥ አድርጉና በሙሉ ክተቱዋቸው ። በትንሽ ሰዓት ውስጥ እመለሳለሁ ። የስልክ ቁጥርህን እወስዳለሁ ። ምናልባት ችግር ካጋጠመኝ ለመደወል እሞክራለሁ ። ሁለት ጊዜ የናንተ ስልክ እንደ ጮኸ እዘጋና እንደ ገና ስደውል ታነሳላችሁ ። ሌላ ስልክ ቢደወል አታንሡ ፤ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን አትክፈቱ ፤ በሩንም ለማንም አትክፈቱ ። ፎርድዋን መኪና ይገዛ እሔድና ነዳጅ እሞላለሁ ፤ ወደ እኩለ ሌሊት ስለምንሔድ እስከዛ ከፈለጋችሁ መተኛት ትችላላችሁ ።»

«ጆክ ! ወዴት ነው የምንሔደው ያልከው?» አለ ሄሚ ።

«ወደ ደቡብ ሚያሚ»

«አይሳካልንም !» አልኩት ።

«ይሳካል ! ሞተንም ሆነ በሕይወት ኖረን ሳይሳካ አይቀርም» ብሎኝ ወጣ ።

ሽ ሽ ት

በሊንኮን ድልድይ በኩል ኒውጀርሲ ከሚባለው ቦታ ከደረስን በኋላ ጉዞአችንን ወደ ደቡብ አመራን ። ከኋላ ወንበር ዲክና ሄሚ ተቀምጠው ያንቀላፋሉ ። መኪናውን የምነዳው እኔ ስሆን ፡ አጠገቤ ተቀምጦ ጆክ የመንገድ ካርታ ያገላብጣል ።

«አንድ ጊዜ እንኳ ለመተኛት አትሞክርም?» አልኩት ሁኔታው አሳዝኖኝ ።

«የመተኛ ጊዜ ሲደርስ እተኛለሁ ። እንደዚህ መንገዱ በመኪና ሲሞላ አንዴት ደስ ይለኛል መሰለሽ » ብሎኝ ዝም ተባባልን ።

አዲስ የተገዛልኝን ልብስና አርቲፊሻል ጸጉር አድርጌ ስታይ ሌላ ሰው እመስላለሁ ።

«በመንገዳችን ከምናገኘው ሱቅ ለኔ፣ ለሄሚና ለዲክ ልብስ፣ እንዲሁም ካገኘን ቦርሣና ምግብ በተጨማሪ እንገዛለን» አለኝ ።

«ጃክ! ለመሆኑ የሚሳካልን ይመስልሃል?» አለ ሄሚ ከእንቅልፉ እየተነሣ ።

«ያለ ጥርጥር ይሳካልናል ።»

ኒው ጀርሲ ደርሰን ወደ ደቡብ ስናመራ ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ሆኖአል ። ከሱቁ የተዘረፉት ጌጦች በዲክ ቦርሣዎች ተሞልተዋል ። የንብረቱን ዋጋ ጃክ ሲገምት ሦስት ሚሊዮን ይሆናል ብሎአል ። ግምቱ ትክክል እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም ። ከመኪናው መቀመጫ ሥር ከሱቁ ሠራተኞች የተወሰዱት ሦስት ሽጉጦች ፣ የኔ ፣ የጃክ ፣ የሄሚ ፣ የስማይሊና የክሊመንት ሁሉ አንድ ላይ ተቀምጠዋል።

«በነዚህ መሣሪያዎች አንድ አገር መውረር እንችላለን» አለ ጃክ እየሳቀ ።

«መሣሪያዎችን ከመደበቅ ይልቅ ለምን በኪሳችን አንይዛቸውም?» ብዬ ጠየኩት ።

«ባጋጣሚ ፖሊሶች መንገድ ላይ ቢያስቆሙንና ትንሽ እንኳ ቢጠረጥሩን ፣ እኛን ከመኪና አስወርደው ይፈትሹን ይሆናል እንጂ መኪናውን አይበረብሩትም ። ጥርጣሪያቸው ከጨመረ የመፈተሻ ፈቃድ ከፍርድ ቤት ስለማይዙ፣ መጥሪያ ወረቀት ሰጥተውን ይሔዳሉ ። ስለ ዚህ ሽጉጥ ታጥቆ መገኘቱ አደገኛ ይሆናል ። ለመኮንት ወደ አል ቤርጎ ስንገባ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል ። መንገድ ላይ ግን ሰላማዊ ዜጋ መስለን መታየት አለብን » አለኝ ።

ጃክ የሚሰጠኝን ትዕዛዝ እየተቀበልኩ ፣ ፍጥነቴን እየጨመርኩና እየቀነስኩ መንዳት ጀመርኩ ።

«አሁን ችግሩ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ ፖሊሶች ወይም የብን ደንበርግ ድርጅት ሰዎች በክሊመንት ሞት ምክንያት እኔ ከሚያሚ የመጣሁ መሆኔን ያውቁና በየመንገዱ ጥበቃ ያደርጉ ይሆናል » አለ ጃክ ።

«ለምን ታዲያ በባቡር ወይም በአውሮፕላን ስመሔድ አንሞ ክርም ?»

«ይሄን እርሺው! ዘረፋው በተካሔደ በአንድ ሰዓት ውስጥ የባ ቡርና የአየር ጣቢያዎች በሙሉ ይጠበቃሉ ። አሁን የሚያስቡት በመ ኪና እንደምንሔድ ስለሆነ ፣ ዋና ዋና መንገዶችን አልፎ አልፎ ብቻ

እየተጠቀምን ብዙ ጊዜ በአቋራጭ መንገዶች ጉዞ እንቀጥላለን ።»

«ግንዛቤስ?» አልኩት ።

በእጁ ጉልበቴን መታ ፣ መታ አደረገና ፣ «ጥሩ ጭንቅላት አለሽ። ያንቺን የዱቤ መቀበያ ካርድ ብንጠቀምበት ፣ እዚህ ቦታ ደርሰናል እያሉ መናገር ይሆናል ። ስለዚህ ሳናበዛው ከተማ እየገባን አነስተኛ ጊጣጌጦችን እየሸጥን የሚያስፈልገንን እንገዛለን ። ጥርጣሬ ውስጥ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ አለብን ።»

«ዕቃ ልንገዛ ስንሔድ መኪናችንን ቢፈትሹትስ?»

«ከፈተሹት ጌጡን ያገኙታል ። ታዲያ ምን ለውጥ ያመጣል ብለሽ ነው? ቅድም እንዳልኩት በቂ ጊጥ በኪሳችን ይዘን ስለምንሔድ ያለንን ይዞ መጥፋት ነው ። ይልቅ አሁን ከመንገዱ እንውጣና ወደ ከተማ ገብተን የሚያስፈልገንን ዕቃና ምግብ እንግዛ ፤ ተመልሰን አል ቤርጎ ፈልገን እንተኛለን ፣ ጉዞአችንን ነገ ማታ እንጀምራለን ።»

«ሁል ጊዜ ማታ ማታ ብቻ ነው መጓዝ የለብን ?»

«ቀን ፣ ማታ ፣ ጥዋት እንደ ተመቸን ፣ ዋናው ነገር አንድ ቦታ ብዙ መቆየት የለብንም ። ፖሊሶችንም ሆነ የድርጅቱን አባላት መቅደም መቻል አለብን ።»

«እርግጠኛ ነህ ! አሁን እየተከታተሉን ነው ?»

«ፖሊሶችም ሆኑ የድርጅቱ አባላት እየተከታተሉን ነው ፤ አትጠርጥሪ ይሄን ማመን አለብሽ ።»

«ስለ አንተ ቀደሞስ ሚያሚ መኖር የሚያውቁ ከሆነ ለምን አሁን ወደ ሚያሚ እንሔዳለን ?»

«ታዲያ ወዴት እንሔድ ?»

«ወደ ምዕራብ አትላሜ» ስል አስተያየቴን ሰንዘርኩና ፣ «ለምሳሌ ቺካጐ ፣ ሎስ አንጀለስ ፣ ወይም ሌላ የማንጠረጠርበት አካባቢ ።»

«ጥሩ አይደለም! ፖሊስ ማለት ወታደር ማለት ነው ። በየከተማውና በየኬላው ላሉት ሠራተኞቻቸው በሬዲዮ መልዕክት ያሳውቃሉ ። የድርጅቱም አባላት በየቦታው የሚገኙ ስለ ሆነ አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ ሁሉም መንገድ እደገኛነቱ እኩል ስለ ሆነ ፣ የማውቃቸውና የምተማመንባቸው ሰዎች ወደ አሉበትና ወደ እማውቀው አገር መሔድ ይሻላል ። ከዚህ ሌላ ግን ፣ ይህን ሁሉ ንብረት እዚህ መሸጥ አለመቻላችን አይገርምሽም ? »

«በጣም ይገርመኛል ! ሚስተር ኮንም ፈቃደኛ አልሆነም፤ኢን ሹራንሶችም የሚቀበሉን አይመስለኝም ።»

«እዚህ አገር የሚቀበለን የለም ። ወደ ሚያሚ የምንሔድበት አንዱ ምክንያት ይሄው ነው ። እዛ ከደረስን በኋላ፣ አውሮፕላን ተከ ራይተን ወደ አንዱ ውጪ አገር መሔድ እንችላለን ።»

«ለምን ኒው ኢንግላንድ አይሆንም፣ ወይም ቦስተን ቤተሰቦ ችህ ጋ ብንሔድ የምታምናቸው ሰዎች ይኖራሉ ።»

«ቦስተን ቤተሰቦቼ ጋ ! ?» አለና ከት ብሎ ስቆ፣ «ከዚህ በፊት የነገርኩሽን አምነሻል ማለት ነው ። ቦስተን ቤተሰብ የለኝም ። ውሸ ቴን ነው ፤የተወለድኩት ጆርጂያ ውስጥ ሲሆን ፤የደኃ ገበሬ ልጅ ነኝ » አለኝ ።

አየሁትና ፣«አሁንስ ምን ማመን እንዳለብኝ ነው ያልገባኝ!» ስል በነገር ገሸም አደረግሁት ።

«ማመን ያለብሽ ሰዎች የሚሉትን ሳይሆን የሚያደርጉትን መሆን አለበት ።»

ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ እንቅልፍ ያልወሰደኝ እኔ ብቻ ነበርኩ ። በዚህ በተሰረቀ መኪና ሽጉጦችና ሦስት ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ንብረት ይዤ የምጓዝ መሆኔን መጽሐፌ ውስጥ ብጽፈው ደስ ባለኝ ነበር ። ግን ማን ያምነኛል?

'አሁን አልቤርቶ ብናገኝ እንዴት ነው የምንኮሞው? አራታችንም እራት ክፍል እንጠይቃለን? ታዲያ ማን ከማን ጋር ሊተኛ ነው?' እያ ልኩ ሳብሰለስል ቆየሁ ። ወደ ፊላደልፊያ መታጠፊያ ምልክት ሳይ ጃክን ቀስቅሼ አስነሣሁት ።

ወደ መንገዱ መታጠፊያ ዞርንና እኔና ጃክ አልቤርቶ በዐይናችን መፈለግ ጀመርን ። ሁለቱ ከኋላ ተቀምጠው ያንኰራፋሉ ።

ብዙ አልቤርቶዎች ካለፍን በኋላ ፤ጃክ የሚፈልገውን ዓይነት አገኘን ። የአልቤርቶው ስም ፍሎው ማርስ ነው ። የ « ሀ » ቅርፅ ያለው አሮጌ ቤት ሲሆን ፣ ለኛ ተስማሚያችን ነበር ።

ጃክ ሞተሩን አታጥፊ ብሎኝ ወረደና ወደ መመገቢያው ሔዶ ከአ ምስት ደቂቃ በኋላም ተመልሶ «ከውስጥ የተግናኙ አራት አልጋዎች ያሉ በት ሁለት ክፍሎች አግኝቼ ፣ ተመዝግቤና ከፍዬ መጥቻለሁ» አለኝ ።

«በትክክለኛ ስማችን ነ» አልኩት ።

«ታሾፈያለሽ? ጉርሻ ስለ ተሰጣቸው ምንም ጥያቄ አላቀረቡም ።»

«እንዴት እንዴት ሆነን ነው የምንተኛው ?»

«አንቺና ሄሚ አንዱ ክፍል ፣ እኔና ዲክ ሌላው ክፍል እንተኛለን ፤ ስለ ምንም አትጨነቂ፤ ሄሚ ትልቅ ሰው ነው አትፍሪ ።»

«ማን ያንኰራፋል ።»

«በጣም ይተነፍሳል እንጂ አያንኰራፋም ። አንቺም ስለ ደከመሽ ምንም አትሰሚም። ይሄ የቀልድ ወይም የጨዋታ ጊዜ አይደለም። ለዛሬ ለሁላችንም የሚያስፈልገን ጥሩ እንቅልፍ ብቻ ነው ።»

«ልክ ነህ ጃክ» አልኩት ።

ኪሱን ፈታተሸና ከተዘረፈው ጌጥ ውስጥ ያገኘሁት ነው አለና ቀለበት አውጥቶ ጣቴ ውስጥ አጠለቀልኝ ። በመገረም ሳየው ፣ «ሰዎች ሲያዩሽ ባለትዳር ትመስያቸዋለሽ፤ ከአሁን ጀምሮ አድርጊው» አለኝ ።

«እና ቀለበቱን ሳደርግ ተጋብተናል ማለት ነው ?»

ፈገግ ብሎ ፣ «ደስ ትይኛለሽ ! አሁን ሔደን እንተኛ » አለኝ ።

ቦርሳውንና መሣሪያችንን ይዘን ወደ ክፍላችን ገባን ። በሌሎቹ ክፍሎች መብራት አይታይም ። እንደ ገባን በሩን ዘጋግተን ተኛን ።

ጃክ እንዳለው ሄሚ ትልቅ ሰው ነው ፤ አልጋው ላይ ጋደም እንዳልኩ ወዲያውኑ እንቅልፍ ስለ ወሰደኝ ሲያንኰራፉ አልሰማሁም ። ቅዳሜ ጧት እምስት ሰዓት ላይ ከእንቅልፌ ስነሣ፣ ሄሚ አልጋው ላይ የለም ። ሌላኛው ክፍል ዲክና ጃክም የሉም ። መኪናዋንም ከቆመችበት ሥፍራ አጣኋት ። ጥለውኝ ጠፍተዋል ብዬ ትንሽም አልተጨነቅኩም ። ለእንድ ጥሩ ነገር ሔደዋል ብዬ በመገመት መታጠቢያ ቤት ገብቼ በሙቅ ውኃ ሰውነቴን ታጥቤ ጥርሴን ልፍቅ ብፈልግ የጥርስ ብሩሽ አለመያዜ ትዝ አለኝ ። ልብሴን ለባብሼ ስጨርስ በሩ ተንኳኳ ።

«ማነው?»

«ዲክ ነኝ ።»

በሩን ከፍቼ አስገባሁት ሁለታችንም ተያየን ።

«እንዴት አደርሽ?»

«የሰላም እንቅልፍ ወስዶኝ ነው ያደርኩት ። አንተስ?»

«ቅዠት ይኖረዋል ብዬ ነበር ፤ ግን ምንም ሳላውቀው ነው የነጋው ።»

«ወዴት ነው የሔዱት?»

«ጃክ እንደ ነገረኝ፣ ከሄሚ ጋር ሆነው አካባቢውን ለማየት ነው ። እኔም አብሬአቸው ልምጣ ብላቸው አንተ ንብረቶቹን ጠብቅ ብለውኝ ሔዱ ። ጄኒ ከፈለግን ለመጥፋት እንችላለን ።»

«መጥፋት ትፈልጋለህ?»

«አልፈልግም ። አንቺስ?»

«እኔም አልፈልግም ። ለምን አካባቢውን ለማየት እንደ ፈለጉ ጃክ ነግሮሃል?»

«ብዙም አልነገረኝ ። ብቻ ጃክ ዕቃ ለመግዛት ዝርዝራቸውን ይጽፍ ነበር ።»

«ከዕቃ ዝርዝር ውስጥ የጥርስ ብሩሽ ቢኖርበት እንዴት ጥሩ ነበር» አልኩት ።

ከሰዓት በኋላ ጃክና ሄሚ ሁለት አዳዲስ ቦርሣዎች ይዘው መጡ ። ቦርሣዎቹ ከምግብ አንሥቶ እስከ አነስተኛ ምላጭ ሳይቀር ይዘዋል ።

«ሽርሽር የምንሔድ ሰዎች እንመስላለን ፣ ጋዜጣ ገዝታችኋል?» አልኳቸው ።

«አዎ !» አለና ጃክ ጋዜጣውን ሰጠኝ ።

በመጀመሪያ ገጽ ላይ ወጥተናል ። ርዕሱ የአንድ ሚሊዮን ብር ንብረት ዘረፋ ይላል ። ዝርዝሩ እንደሚለው የኒውዮርክ ፖሊሶች ክትትል በማድረግ ላይ ናቸው ነው ።

«አንድ ሚሊዮን? ማንን ነው የሚያታልሉት?» አልኩ ።

«ፖሊሶችን ነው ። ብንደነበርግና ልጆቹ የዘረፉትን የሁለት ሚሊዮን ብር ንብረት እንደ ገና እንደ ተወሰደባቸው ለመግለጽ የሚፈልጉ ይመስልሻል? የሚያስቅ ነው ። ብዙ ጊዜ የማስበው ሴባን ሌባ አይዘርፈውም ነበር ። አሁን ግን ተዘራረፉ ። ማክዶናልድ ሆቴል ቤት እዚሁ በቅርባችን ስለ ሆነ ምሳችንን እንብላ ።»

ከብዙ ሰዓታት በኋላ ፣ ሆቴል ውስጥ ስንበላ የመጀመሪያችን መሆኑ ነው ። ወደ ጥግ በኩል ተቀምጠን ምግብ አዘዝን ። ከየምግቡም ዓይነት ድጋሚ እንዲቀርብልን አደረግን ። ጃክ ይሄን ቦታ የመ

ረጠው ከውጭ የሚመጣውን ለመቆጣጠር ነው ። ምናልባት ሴባን ሌባ ሲዘርፈው ማየት አስቂኝ ይሆን ?

ምግባችንን በልተን ከጨረስን በኋላ ፣ ቡና እየጠጣን እያለ ጄክ ምን ያህል ብር በኪሳችን እንዳለን ጠየቀን ። እኔ መቶ ብር ፣ ዲክ ዐርባ ብር ፣ ሄሚ ስልሳ አምስት ብር እንዳለን መለስንለት ። ከዚህ በተረፈ ጃክ ኒውዮርክ ከጌጣጌጥ ሽያጭ ያገኘው ሁለት ሺ ብር እንዳለን ታወቀ።

«በቂ ገንዘብ የለንም ። ስለዚህ ገንዘብ ለማግኘት ዛሬን እዚህ እንውሳለን፤ ገንዘብ የምናገኘው እንደዚህ ነው...»

ቀስ እያለ በዝርዝር ምን እንደምናደርግ፤ ነገረን ።

«ወደ ፊላደልፊያ ከተማ እንገባና ፎርዳችንን የመኪና ማቆሚያ ቦታ አቁመን ጌጣጌጥ በመያዝ በእግራችን ወይም በታክሲ ወደ ተለያየ ቦታ እንሔዳለን ።

«ዲክ ከወርቅ የተሠሩ ሰዓቶችን ይዞ በየሱቆቹ አለፍ አለፍ እያለ አንዳንድ ሰዓት ይሸጣል ። ሲሸጥ ሰዓቱ የአያቱ እንደ ነበረና በውርስ እንዳገኘው ፣ አሁን የሚሸጥበት ምክንያት ገንዘብ ስለ ፈለገ ብቻ መሆኑን ይገልጻል ።

«ዲክ ! ይህን መፈጸም ትችላለህ ?»

«እችላለሁ ።»

«አዎ ትችላለህ ! ለምን ለመሸጥ እንደ ፈለክ ባለሱቆቹ ካልጠየቁህ በስተቀር አትንገራቸው ።»

«ስሜን ከጠየቁኝስ ?»

«የሚጠይቁህ አይመስለኝም ። ከጠየቁህ ንገራቸው ።»

«በስንት ብሸጠው ጥሩ ይሆናል ?»

«አምስት መቶ ስትላቸው ይስቁብሃል ፣ ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ውረድ፤ ከዛ ያነሰ ከጠየቁህ ዝም ብለህ ውጣ ። አይለቁህም ። ሰዓቱ ላይ ያለው ወርቅ ከዚያ በላይ ዋጋ እንዳለው ያውቃሉ ።»

«ጄኒም የጋብቻ ቀለበቶችና አምባሮች ይዘሽ ወደ ተለያዩ ሱቆች ትሔጂያለሽ፤ ባለሱቆቹ ሲጠይቁሽ ከባልሽ እንደ ተፋታሽና የድሮ ባልሽን ሊያስታውሱሽ የሚችሉትን ንብረቶች ለመሸጥ እንደ ፈለግሽ ንገሪያቸው ። በምን ያህል እንደሚገዙሽ ራስሽ ጠይቂአቸው ። ሲነግሩሽ በግማሽ ጨምረሽ ንገሪያቸው ። ወዲያው ይገዙሻል ፣ ግልጽ ነው ?»

«ግልጽ ነው ። አንድ ሱቅ ሁለት ቀለበት መሸጥ እችላለሁ ?»

«ለምን አትችይም? ብዙ ሴቶች ከአንድ ቀለበት በላይ አላቸው ። ጉበዝ ስለ ሆንሽ ሁሉንም ራስሽ ተወጭው ።»

«ለምን ጠየቅሽ አትበለኝና አንቲና ሄሚስ ምን ታደርጋላችሁ?»

«ከፍተኛ የሆኑ ጌጦችን በመግዛት የቡና ቤት ባለቤቶች የታወቁ ስለሆነ ፡ ሄሚ ብዙ አልማዝ ያላቸውን የወንድ ቀለበቶች ወስዶ በየ ቡና ቤቱ ሊሸጥ ይችላል ። እኔም በግብግና በሠርግ ወቅት የሚደ ረጉ ትላልቅ አምባሮችና ጌጦችን ወስጄ እሸጣለሁ ።»

«እንደዚህ ዓይነት ጌጥ ማን ይገዛሃል?» አልኩት በመገረም ።

«ሴተኛ አዳሪዎችና የነሱ ደላሎች ይገዙኛል ። ጌጡን ሲየዩት ምራቃቸው ይመጣል ። ስለዚህ ከየት እንዳመጣሁት እንኳ አይጠ ይቂም ። አንድ የማውቀው ቦታ ስለ አለ ወደዚያ እሔዳለሁ ። አሁን ወደ አልቤርጎአችን እንመለስና መንገዳችንን እንቀጥል ።»

ጃክ ለፈላደልፊያም ሆነ ለሌሎቹ ከሁምች ባዕድ አይደለም ። መኪናችንን ብዙ ሱቆች ወደሚገኙበት አካባቢ አቆምንና ተመል ሰን በዚሁ ቦታ ሀሥራ አንድ ሰዓት ላይ አንድንገናኝ ተቀጠርን ። ከሠላሳ ደቂቃ በላይ የዘገየ ሰው ቢኖር ግን ፡ እንደ ተያዘ ስለሚገመት ፎርዱ በቦታው ላይ እንደማይጠኝ ተስማምተን ለመሔድ ተዘጋጀን ።

ጃክ እኔና ዲክ ወደ ከተማው የሚያስገባውን ታችኛውን መንገድ እንድንይዝ ነገሮን ታክሲ አሳፈረን ። የያዝኩት የእጅ ቦርሳዬ በጌጥ ተሞልቶአል ። የዲክም ከሷ እንደዚሁ ። ታክሲ ውስጥ እንደ ገባን ዲክ ዙሪያውን እያየ ፈገግ ሰፊ አየሁት ። ምን ያህል ጉበዝ እንደ ሆነ ለመሞከር ጉጉ መሆኑ ከፊቱ ማወቅ ይቻላል ። ባለፉት ጊዜያት ቀዝ ቃዛና ረጋ ያለ፡ ብዙም ደስታ የሚታይበት ሰው አልነበረም። ካለፉት ሐያ አራት ሰዓት በኋላ ግን ደስተኛ ሆኖአል ። እንደ እውነቱ ከሆነ በወንጀለኛነቱ የተደሰተው ዲክ ብቻ አልነበረም ። እኔም እየተደሰ ትኩ ነኝ ። ምናልባት ሌሎች ወንጀለኞችም ይህ የነጻነት ስሜት ይሰ ማቸው ይሆናል ።

በአሁኑ ሰዓት እብደቴን ኢየፋጠንኩ መሔዴ ይሰማኛል ። ቀደ ም ሲል የነበረኝ ባሕሪ ፡ እውነተኛነትና ሞራል ሁሉ ሙልጭ ብሎ ከ ውስጤ ጠፍቶአል ። በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ ለመቀጠል እ ንደ ምችል ለማየት እፈልጋለሁ ። ይህን ሁሉ ስፈጽም አስፈላጊ ከ ሆነ ለመዋሸት ፡ ለመሥረቅ ፡ ለማጭበርበርና የሰው ሕይወት ለማጥፋት ወደ ኋላ አልልም ። ይህ የሥልጣኔ ዓለም እውነቱ ውሸት ፡ ጥቁሩ ነጭ ፡ ነጩ ጥቁር በመሆን እየተገለባበጠ ነው ።

በቁም እንደማያልም ሰው መጀመሪያ እግሬ ወደ መራኝ ሱቅ ገባሁ ።

«አቤት የኔ ወይዘሮ ! ምን ልታዘዝ?» አለኝ ባለሱቁ ።

«የግራ ጣቴን እያሳየሁት ይሄን ቀለበት መሸጥ እፈልግ ነበር» አልኩት ።

ጣቴን በእጁ ያዝ አድርጎ ተመለከተና 'ልየው' በማለት ከጣቴ በቀላሉ አወጣው ። ሰፍቶሻል አለኝ ።

«አዎ ብዙ ከስቻለሁ ።»

«ሊሆን ይችላል !» ሲል ፥ ሱቁ ውስጥ የነበረችው ሴትዮ ፥ «ይሄ አንተንም ሊያጋጥምህ ይችላል» አለችው ።

«ዝም በይ !» አለና ወደ ገንዘብ መክፈያው ገብቶ መነጽሩን አደረገና የጠረጴዛውን መብራት አብርቶ ቀለበቱን መመርመር ጀመረ። መመልከቱን ሳያቋርጥ ፥ «ለምን ለመሸጥ ፈለግሽ?» አለኝ ።

«ከባለቤቴ ጋር ስለ ተፋታሁ ነው ። ያ አውሬ የገዛልኝ ጌጥ ሁል ጊዜ እሱን እንዲያስታውሰኝ ስለ ማልፈልግ ነው » አልኩት ።

«ይደበድብሽ ነበር?» አለችኝ ሴትየዋ እንደ ማዘን ብላ ።

«ሊታመን በማይችል ሁኔታ» አልኩዋት ።

«ሰምተሃል !» አለችው ወደ ሰውዬው እያየች ።

«አዎ ሰምቻለሁ » አለና ቀለበቱን በጣቱ እያሻሸ ፥ «ይሄም ሊያጋጥም ይችላል» አላት ። ወደ እኔም ዞር ብሎ «ለዚህ ትንሽ ቀለበት ምን ያህል ትፈልጊያለሽ?» አለኝ ።

«በድፍረት አምስት ሺ ብር» አልኩት ።

«አምበት ሺ?» ብሎ ጮኸ !

«የፈታሁት ባሌ ገዛሁት ያለኝ በዚህ ዋጋ ነው ።»

«እሺ ብሎሽ ይሆናል ። ይሄኔ ከአንድ ሺ ወይም ከአንድ ሺ አም ስት መቶ ብር በላይ አልገዛውም ፤ እመኚኝ ። እኔ ስምንት መቶ ብር ልገዛሽ እችላለሁ ።»

«ስምንት መቶ ብር? በምንም ዓይነት በስምንት መቶ አልሸ ጥም ። ቀለበቴን መልስልኝ ።»

«ቆይ እንጅ ረጋ በይ ፣ አትቆጪ ! እንደምታይው ሱቂ አነስ ተኛ ናት ። በዛ ላይ ብዙ ወጭዎች ስለ አሉብኝ ችግር ላይ ነኝ ። ምና ልባት አንቺ እንዳልሽው የድሮው ዋጋ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል ። በአሁኑ ጊዜ ቢሸጥ ዋጋው አነስተኛ ነው ።»

ይሄን ሁሉ የሚለፈልፈው ቀለበቱን ለመግዛት መጓጉቱ መሆኑ ገባኝ ። በዋጋው ትንሽ ስንከራከር ቆየን ። እሱ ቀስ እያለ ዋጋውን ከፍ ሲያደርግ ፣ እኔም ዝቅ እያረኩ በአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ብር ተስማማን ። «ብሩን የምፈልገው በጥሬ ነው» አልኩት ።

ፈገግታው እየጠፋ ሔደና ፣ «በጥሬውስ እስቲ ሱቁን በደምብ ተመ ልከቺው ፤ ይሄን ያህል ገንዘብ በመሳቢያዬ ውስጥ የማስቀምጥ ይመ ስልሻል ! ቼኮቹ በባንክ የሚታወቁ ስለ ሆነ ቼክ ልስጥሽ ።»

«ቼኮችህ በባንክ ተቀባይነት እንደሚኖራቸው እገምታለሁ ። ገንዘቡን የምፈልገው አሁን ነው ። ባንክ ቤቶች በአሁኑ ሰዓት ዝግ ናቸው ። እስከሚከፈቱ መቆየት አልፈልግም ። ዛሬውኑ ወደ ሚያሚ ተጓዥ ነኝ ።»

«ይሄን ያህል ገንዘብ በእጇ የለም ፤ አዝናለሁ !»

«ምን ያህል ገንዘብ አለህ?» አልኩት ። ትልቅ ስሕተት ነበረ ።

«ወደ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር የሚያህል አይጠፋም ።»

እሺ ብዬ ተቀበልኩና ስወጣ ሰውየውና ሴትየዋ እበር ድረስ እየሸኙኝ ሚያሚ መልካም ዕድል እንዲያጋጥመኝ ተመኙተውልኝ ተለያየሁ ። እንዳጭበረበሩኝ ዐውቄዋለሁ ።

የመጀመሪያ ሽያጭ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር በማግኘቴ እን ዴት ጀክ እንደሚደሰት አሰብኩ ። በሌላው ሐሳቤ ፣ በሌብነት ውስጥ የተሳተፍኩት እኔ ብቻ ሳልሆን ባለሱቆቹም መሆናቸው ገረመኝ ። ለምን የተሰረቁ ይሁኑ አይሁኑ ሳያጣሩ ይገዛሉ ። ምናልባት ጌጡ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያወጣላቸው ገምተው ይሆናል ። በመኻሉ በፖ ሊስ ቢያዙስ ፣ የሚገርም ነው ።

ሁለተኛው ሱቅ እንደ መጀመሪያው ቀላል አልነበረም ። የገዛ ሀበትን ደረሰኝ ማቅረብ ባለመቻሌ ሰድበው አባረሩኝ ። አንዳንዶ ቹም 'ብትፈልጊ በዚህ ዋጋ ሽጪ ፤ ኤለዚያ ተይው እያሉ' የሰጡኝን መቀበል ጀመርኩ ።

ሌሎች ሱቆችም ጥሬ ገንዘብ የለንም ቼክ ውሰጅ ብለውኝ ሳን ስማማ ቀረን ።

በመጨረሻ የገባሁበት ሱቅ ባለቤት ወጣት ሲሆን፡ እራሱ በራ ነው ። ቀለበት አውጥቼ አሳየሁት ፤ ተመለከተና የጠየኩትን ዋጋ ከፍ ሎኝ «ከዚህ ሌላ የሚሸጥ ጌጥ ካለሽ በከፍተኛ ዋጋ ለመግዛት ፈቃደኛ መሆኔን በደስታ እገልጽልሻለሁ» አለኝ ።

«ሳገኝ እሞክራለሁ» ስል መለስኩለት ።

«ሌላ ጊዜ ተመልሰሽ እንደምትመጪ ተስፋ አደርጋለሁ ።»

«እሞክራለሁ» አልኩት ። በልቤ ሁለታችንም ሌቦች ነን ብየ አሰብኩ ።

የእግር ጉዞ ስለ በዛብኝ ደከመኝ ። አሁን ወደ ሰባት ቀለበት ሽጪ አምስት ሺ ብር አግኝቻለሁ ። ሰዓቴን ሳይ ፀሥር ሰዓት ተኩል ይላል። የቀጠሮአችን ሰዓት ሳይደርስ መመለስ ፈልጌ ታክሲ ተሳፈርኩ ። በቀጠሮ ቦታችን ስደርስ ዲክ መኪናችንን ተደግፎ ሲጋራ ሲያጨስ አገኘሁት ። እንዳየኝ ፡ «እንዴት ነው?» አለኝ ፈገግ ብሎ ።

«ወደ አምስት ሺ ብር አግኝቻለሁ ።»

ፈገግታውን ቆም አደረገና ፡ «እኔ ሁለት ሺ ብር ነው ያገኘሁት ፡ በኔ ቤት ብዙ መሰሎኝ ነበር ።»

«እንዲያውም አንተ ጥሩ ሸጠሃል ፤ እኔ የያዝኩት ጌጥ ቢያንስ ከዐሥር ሺ ብር በላይ ማውጣት ነበረበት» ብዬ አጽናናሁት ።

በዚህ ሥራ እስካሁን ያገኘነውን ልምድ እያነጻጸርን ስንጨዋወት ፡ ጃክና ሂሚ ከአንድ ታክሲ ሲወርዱ አየናቸው ። እንደ ተሳካላቸው ያስታውቃሉ ። አረማመዳቸው ሁሉ የመዝናናት ነው ።

«እንዴት ነው ጥሩ ቀን አሳለፋችሁ?» አሉን ጃክ እየጣቀ ።

የሁለታችን ተዳምሮ ወደ ሰባት ሺ ብር ሆኖአል » አልኩት ።

«በጣም ጥሩ ነው ፤ ከምጠብቀው በላይ አግኝታችኋል፤ እኔና ሂሚም ደህና አግኝተናል ። የወሰድነውን በሙሉ ሸጠናል ። አስፈላጊ ቢሆን እንደ ገና መጥተን ጌጥ መውሰድ እንችል ነበር ። ግን በዚህ ከተማ ከዚህ በላይ መሸጡ መንሰፍሰፍ ይሆናል ብለን ተውነው ።»

«ስንት አገኛችሁ ?»

«ወደ ሐያ ሺ ብር ያህል አግኝተናል ። እንዴት ደስ የሚል የደ መወዝ ቀን ነው ! ነገ እሑድ ስለ ሆነ እናርፋለን ። አሁን መኪናችንን ነዳጅ እንሙላና መንገድ ከመቀጠላችን በፊት ጥሩ ምግብ ቤት ፈል ገን ትንሽ እንዝናና» አሉን ። በዚህ ተስማማን ።

የዕቃና የልብስ መሸጫ ሱቆች ክፍት ስለሆኑ ሠላሳ ደቂቃ እንዲ ፈቀድልኝ ጠየኩ ። ተፈቀደልኝ ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ወደ ፎርዱ ስመለስ ቅባት ፣ ሽሚዝና ሹራ ቦች ተሸከሜ ነበር ። በመዘግየቴ የተናደዱ መስሎኝ ነበር ። እነሱ ግን፣ ውስኪያቸውን እየጠጡ ስለ ጠበቁኝ ፣ መዘግየቴን ያስታወሱት አልመሰለኝም ። ወዲያው ወደ አልቤርጎአችን ሔድን ።

ወንዶቹ ተጣጥበውና ጺማቸውን ተላጭተው እኔም አዲስ ልብ ሴን ለባብሼ ወደ ምግብ ቤት ለመሔድ ተነሣን ።

«ስሙ !» አለ ዲክ ። «ዛሬ ማታ መንገዳችንን የምንቀጥል ከሆነ ፣ ንብረታችንን ለምን መኪና ውስጥ አናደርግምን ምናልባት ምግብ ቤት አንድ ችግር ቢያጋጥመን ፣ ንብረት ፍለጋ ወደዚህ ከመምጣት ይልቅ በመኪናችን ተሳፍረን ወደምንፈልገው መሔድ እንችላለን ።»

ጃክ ሲያስብ ቆየና ፣ «በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው» ብሎ «ዕቃችንን እናውጣና እንጫን» ብሎን የያዝነውን ዕቃ በሙሉ ጫን ።

ጃክ ከኋላ ወንበር ተቀመጠና ክላክስ እንዳደርግ ነገረኝና አደ ረግሁ ። የአልቤርጎው አስተናጋጅ አጠገባችን እንደደረሰ መሔዳ ችን ነው አለው ። ቁልፉን እየመለሰ ፣ «ሰለ እንክብካቤያችሁ ከልብ እናመሰግናለን ።»

«እኔም የናንተ ዓይነት እንግዳ በማስተናገዴ ደስ ይለኛል ፣ ሌላ ጊዜ ስትመጡ የበለጠ እንክብካቤ ይጠብቃችኋል ።»

ልክ እንደ ሚታመን ሰው ፣ «መመለሳችን አይቀርም» አለው ጃክ ።

«እዚህ አካባቢ ጥሩ ምግብ ቤት የት እንደሚገኝ ልትጠቁመን ትችላለህ ?»

አስተናጋጁ ፣ ያለ ምንም ማሰላሰል ፣ «ከዚህ ሠሥራ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው የቱም ምግብ ቤት ጥሩ ነው ። ከዋናው መንገድ ወደ ግራ ስትታጠፉ ታገኙታላችሁ» አሰን ። አመሰግነን መንገዳችንን ቀጠልን ።

በተባለው አካባቢ ስንደርስ ምግብ ቤቱን አገኘነው ። ብዙ መኪና ሊያቆም የሚያስችል በአስፋልት የተሠራ ሜዳ ያለው ትልቅ ምግብ ቤት ሆኖ አስተናጋጆቹ ነጭ ሙሉ ልብስ የለበሱ ናቸው ።

ሁላችንም አንድ ዓይነት ምግብ አዘን መብላት ጀመርን ። ምግቡ በጣም ጥሩ ባይሆንም፣ ብዙም መጥፎ አይደለም። መጠጥ በመጠጣት ላይ እንዳለን በመኻሉ ይቅርታ ጠየኩና ወደ ሽንት ቤት ሔጄ ተጸዳድቼ

ስመለስ ወደ ቡና ቤት ውስጥ ተመለከትኩኝ ። ሳሎኑ በጠጭዎች ተሞልቶአል ። ቡና ቤቱ ግድግዳ ላይ ያለውን መስተዋት ሳይ ከዚህ በፊት ያየሁትን ሰው የሚመስል ሰው ቁጭ ብሎአል ። ለመቆም ምንም አልቀረኝም ፣ ቆሜ ዝም ብዬ በመስታወቱ ብመለከት በቀጥታ ሊያየኝ ስለሚችል ፈጠን ብዬ ወደ ቦታየ ተመለስኩ ። ቁጭ እንዳልኩ የአፍ መጥረጊያ ወረቀት እንደሚያነሣ ሰው ወደ ጀክ ጠጋ ብዬ በፈገግታ ፡ «ወደ ኔ ጠጋ ብለህ እየሣቅህ ተጫወት፣ ወደ ሌላ ቦታ አትይ፣ ችግር ሳይገጥመን አይቀርም » አልኩት ።

አንድ እጁን ትከሻዬ ላይ ጣል አደረገና የተቀመጠበትን ወንበር ወደ ኔ አስጠግቶ ፡ «ሁለታችሁ ዝም ብላችሁ መጠጣችሁን ጠጡ፣ ወደ እኛ አትመልከቱ ፣ ሌላውንም አትዩ » አላቸው ።

ይሄ ሲናገር በመሣቅና በመጫወት ሲሆን ፡ ከሩቅ ለሚመለከት ሰው የፍቅረኞች ጨዋታ ይመስል ነበር ።

«ጀኒ ምንድን ነው ?» አለኝ ።

«ወደ በሩ ጋ ያለ ራሰ በራ ወጣት ይታይሃል ?»

ጀክ ሲጋራ ከኪሱ አወጣና ክብሪቱን ጫረው ። ሆኖም ሲጋራውን ሳያቀጣጥል ዐውቆ አጠፋውና እንዳጐነበሰ ወደ ነገርኩት አቅጣጫ ተመለከተና ፊቱን ወደ እኔ መልሶ ፡ «አየሁት» አለኝ ።

«ታውቀዋለህ ?»

«አላውቀውም ። ማን ነው ?»

«በመጨረሻ ሰዓት ቀለበት የገዛን ባለሱቅ ነው ። የሚገርመው የጠየኩትን ዋጋ ያለ ምንም ክርክር ከፍሎኝ ሌላም ካለኝ እንዳመጣ ጠይቆኛል» አልኩት ።

ረጋ አለና ፡ «ገባኝ ... ገባኝ» አለ ።

ሄሚና ዴክ መጠጣቸውን ዝም ብለው የሚጠጡ ይምሰሉ እንጂ የምንነጋገረውን ያዳምጣሉ ።

«አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ። ምናልባት እዚህ ቀጠሮ ይኖረዋል ወይም ቅዳሜ ምሽትን ለመዝናናት ፈልጎ መጥቶ ሊሆን ይችላል » አለ ዴክ ።

«እሺ ባክህ ! እንዴት የፊላደልፊያ ጌጣጌጥ ባለንብረት የቅዳሜን ምሽት ለመዝናናት ሲል እዚህ ድረስ ብቻውን ሊመጣ ቻለ! አጋጣሚ ሊባል ነው፣ ጀኒ ከሱት ከወጣሽ በኋላ ምን አደረግሽ?»

ያደረኩትን እያሰብኩ ፣ «የመጨረሻዬ ሱቅ ስለ ነበር ፣ ሁለት ሕንፃዎችን በእግሬ አልፌ ታክሲ ተሳፈርኩና ወደ ቀጠሮአችን ቦታ መጣሁ ።»

«ሱቁ ውስጥ ብቻውን ነበር ?»

«ይሄን ማወቅ ያስቸግራል ። ሊኖርም ላይኖርም ይችላል ። የሱቁ ጓዳ በመጋረጃ የተጋረደ ስለሆነ ፣ እዛ ውስጥ ሰው ሊኖር ይች ላል። እኔ ግን ያየሁት እሱን ብቻ ነው ።»

«ነገሩ አላማረኝም ! ይሄ ሰው ስለ ጠረጠረሽ ተከታትሎናል ።»

«አዝናለሁ ! ጃክ» አልኩት ።

«ያንቺ ስሕተት አይደለም የራሴ ጥፋት ነው ፤ የሚከተላችሁ ሰው መኖር አለመኖሩን እንድታረጋግጡ መንገር ነበረብኝ ።»

እየተንሾካሾክ ፣ «አሁንም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ። ሰውየውን እንደ ጠረጠርነው ላይሆን ይችላል፤እርግጠኞች አይደለንም አለ» ዲክ።

«ላይሆን ይችላል! ላይሆን ይችላል ! ሁሉም ነገር ላይሆን ይች ላል ። አሁን የምናደርገው ፣ ለአስተናጋጁ ሒሳባችንን እንዲያመጣ ጠይቄ ከጥርሻ ጋር መክፈል ነው ። ከዚያ ሁላችንም እንነሣለን ፤ ስንወጣ እየተገናኘንና እየተሣሣቅን መሆን አለበት ፣ ገባችሁ ! ልክ በሩን ስን ወጣ ሄሚ በአመቸህ በኩል ትታጠፍና በሩን ማየት በምትችልበት ቦታ ተደበቅ ። እኛ መኪናችን ውስጥ እንገባለን፤ ሰውየው ወዲያው ከወጣ በለው! ቶሎ ካልወጣ ዲክ እንዳለው አጋጣሚ ነው። ገብቶሃል?»

«አዎ ! ገብቶኛል ፣ ልግደለው?»

ዲክን እየሁት ። ፊቱ በድንጋጤ ዐመድ መስሎ ሰውነቱ ሁሉ ይንቀጠቀጥ ጀመር ። መንቀጥቀጡ እንዳይታይ ከለልኩት ። ጥሩ ቀን አሳልፈን ውለን አሁን ይሄ ችግር ተጋረጠብን ።

«አይሆንም... አትግደለው ፣ እስካሁን የደረሰብን ችግር ይበቃ ናል ፣ ሌላ ችግር ውስጥ መግባት የለብንም ፤ ቀስ ብለህ እንዳይሞት ምታው ፣ ልክ ድሮ እንደምታደርገው ዝረፈውና ራሱ መኪና ውስጥ ለማስገባት ሞክር ። ሰዎች ቢያዩም የሰከረ ይመስላቸዋል ። ይህን ባደረክ በአምስት ደቂቃ ውስጥ የፈለገው ችግር ይኑር ተመልሰን ወደ አንተ እንመጣለን ። ገባህ?»

«ገብቶኛል ! ችግር አይኖርም ።»

«ጥሩ ! ሁላችሁም ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ዐውቃችኋል ። ስንወጣ ወደ ሰውየው አትመልከቱ ፤ ሞራሽ መኖሩንም እርሱት » አለና አስተናጋጁን ጠርቶ ሒሳቡን ከጉርሻ ጋር ሲከፍል ሁላችንም ተነሥተን እየሣቅንና እያወራን ወደ በሩ ሔድን ።

ከመግቢያው በር ስንወጣ ሦስታችንም በፍጥነት እርምጃ ወደ ፎርዱ ሔድን ። ዲክ በሩን ከፈተልንና ገባን ። ሄሚ የት እንዳለ አይታይም ።

«ስንት ሰዓት ነው?» አለን ጆክ ።

ከፊት ወንበር የተቀመጠው ዲክ ሰዓቱን ወደ ዐይኑ አስጠግቶ እያየ «አንድ ሰዓት» አለው ።

«ጥሩ ! ሰዓትህን ተመልከትና አንድ ሰዓት ከአምስት ሲሆን ንገረኝ» አለው ።

ጆክ መኪናዋን አንቀሳቅሶ በዝግታ እየነዳ ወደ ዋናው መንገድ ተጓዘን ።

«አንድ ሰዓት ከአምስት ሆነ!» ሲል ዲክ ፣ ጆክ መኪናዋን ወደ ምግብ ቤት በፍጥነት አዙሮ መንዳት ሲጀምር፣ ሄሚ ወደኛ ሲመጣ አየነው ። የኋላውን በር ከፈትኩለትና ገባ ። ጆክ መኪናዋን እንደ ገና ወደ ዋናው መንገድ አዙሮ ነዳና ዋናውን መንገድ ያዝን ።

«ልክ እንደ ነገርከኝ ቦርሳውን ፣ ሰዓቱንና የዱቤ መቀበያ ካር ዱን ይገፍአለሁ » አለ ሄሚ ።

«በዚህ ዓይነት ወደኛ ነበር የሚመጣው?»

«አዎ ! መኪናው ውስጥ ለመግባት እንደ ወፍ ይበር ነበር ። መኪናው ውስጥ ሳይገባ ቀድሜ መታሁት ፤ እስካሁን አይነግም ፤ ትንሽ ይተኛል ።»

«ጥሩ ሥራ ነው ! ሄሚ ።»

«ይህች ምናላት ብለህ ነው ቀላል ሥራ ናት ። ቁም ነገሩ አሁን ሁሉም ነገር ሰላም መሆኑ ነው » አለ ሄሚ ።

«ወይኔ ! ይሄን የውሻ ልጅ መግደል ነበረብን » ሲል ጆክ ነገሩ ከለፈ በኋላ ቆጨው ። እንደ ቀልድ የተጀመረና ሁሉንም በአሸናፊ ነት የተወጣነው የመሰለን ነገር አሁን መልኩን ቀይሮ ወደ ባሰ ችግር ውስጥ እየገባን ሔድን ። በየቦታው አደገኛና ከባድ ጠላት እንደ ሚጠብቀን ዐወቅን ።

«በጣም የሚያስጠላና የሚያናድድ ነው ። እኛ እንደ ሆነ አንዴ ተሳክቶልናል ። ለምን አይተዉንም፣ ለምን ይከታተሉናል?» አለ ጃክ በንዴት ።

ይሄ የሁሉም ወንጀለኞች ስሜት ሳይሆን አይቀርም ። የዘረፉ ዕቅዳችንንና ጉብዝናችንን አስመስክረናል ። ለምን ታዲያ ይወነጅሉናል? ፖሊሶችም ፣ ሕጉም ፣ ራስዋ ሕይወትም በትክክል ለኛ አል ቆመልንም ማለት ነው?

የመኪናችንን ፍጥነት ቀነስ አድርገን ወደ ደቡብ ጉዞአችንን ጀመርን ። አንድም የሚናገር ሰው አልነበረም ። ዝም ብሎ መጓዝ ስለ አሰጠላኝ ፣ «ሰውየውን ገድለነው ቢሆንም ፣ ምንም ጥቅም አል ነበረውም ። ቀደም ብሎ ስልክ ደውሎ ለአንዱ ተናግሮ ይሆናል » አልኩኝ ።

«ግምትሽ ትክክል አይደለም ። ቀደም ብሎ ለሰው ነግሮ ቢሆን ኑሮ ብቻውን ሳይሆን ቢያንስ ከአራት ሰው ጋር ይመጣ ነበር ። አሁን ከእንቅልፉ ሰነቃ ወዲያው ይናገራል ።»

«የሌቦቹ ድርጅት አባል ይሆን እንዴ?»

«ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ፖሊስ እንዳልሆነ እርግጠኛ ነኝ» አለ ዲክ ።

ሁላችንም ዝም ብለን የየራሳችንን ሐሳብ ማብሰልሰል ጀመርን ። የወደፊቱ ጉዞአችን ታየኝ ። በየምግብ ቤቱ ስንገባ የሚከታተለን ሰው መኖር አለመኖሩን ሁል ጊዜ ማየትና መጠርጠር እንዳለብን ተሰማኝ ።

«ሄሚ ! የምትከታተለን አንተ ብትሆንና የት እንደ ታየን ብት ጠቆም ወዴት ይሔዳሉ ብለህ ትገምታለህ?» አለ ጃክ ።

«ወደ ባልቲሞር ! እገምታለሁ ። አይመስልህም?»

«ልክ ነህ የሚገምቱት ባልቲሞርን ነው ። ስለዚህ ባልቲሞር ለመድረስ የቀረን ትንሽ ስለ ሆነ ፣ ለዛሬ ወደ ዊልሚንግተን ተጠግተን አድረን ነገ ከሰዓት በኋላ በባልቲሞር እናልፋለን ። ማታ ወይም ጥዋት ባልቲሞር አለመኖራችንን ካወቁ ወደ ዋሽንግተን ይሔዳሉ ።»

«ጃክ ! የእብድ ሐሳብ ሊሆን ይችላል ! ግን ፖሊሶችም ሆኑ ድርጅቱ ወዴት እንደምንሔድና የት እንደምንቆም የሚገምቱና የሚከታተሉን ከሆነ ለማደናገር ወደ ኒውዮርክ ለምን አንመለስም፣ ይሄን የሚገምቱ አይመስለኝም» አለ ዲክ ።

«አይሠራም ! ኒውዮርክ ውስጥ ብዙ ተመልካችና ወሬኛ ሞል ቶበታል ። የትስ መደበቅ እንችላለን? ጌጣጌጡን እንዴት መሸጥ ይቻ ላል? ይህን ማድረግ ካልቻልን ከተማ ውስጥ መቀመጡ ምን ይጠቅ ማል? ከኒውዮርክ ወደ ሌላ አገር ለመውጣትም አንችልም ! ስለዚህ ሚያሚን የመሰለ አስተማማኝ ቦታ አናገኝም ።»

በደቡብ ዊልሚንግተን የሚገኘውን ወንዝ እንዳለፍን ከአገር አገር አቋራጭ የሆነውን መንገድ ዘጠና አምስትን አየነው ። ጃክ ካሳለፍናቸው ቀኖች ወይም ሰዓታት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲደሰት አየሁት ።

«ተናፋቂውና ተወዳጁ መንገድ ዘጠና አምስት ! እንግዲህ ወደ ቤታችን እያመራን ነው» አለን ።

ከዘጠና አምስተኛው መንገድ ታጥፈን ተስማሚ መኝታ ፍለጋ በስተምሥራቅ ኢልክቶን መካል ስሙን የማላስታውሰው አልቤርጎ አገኘን ። እንዲያው ለስሙ ለማረፊያ የሚሆን ነው ። በውስጥ የሚ ገናኙ ክፍሎችን ተከራየን ።

«አንቺ ከኔ ጋር ትተኝያለሽ ፣ ዲክና ሄሚ አንድ ላይ ይተኙ » አለኝ ጃክ ።

ማንም የተቃወመ የለም ።

መግቢያና መውጫችንንና ለማምለጫ አመቺ የሆኑትን ሥፍራ ዎች ሁሉ በጥንቃቄ አየናቸውና ቦርሳዎቻችንንና ሽጉጦቻችንን ይዘን ወደ ክፍላችን ገባን ።

«በአሁኑ ጊዜ ሁኔታዎች የተለዋወጡ ስለሆነ ፣ ከዚህ ሳንወ ጣም ሆነ መንገድ ላይ እነዚህን መሣሪያዎች መያዝ አለብን።አንቺና ዲክ መሣሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ታውቃላችሁ?» አለን ጃክ ።

«መማር እንችላለን» ሲል ዲክ መለሰ ።

«አዎ ትችላላችሁ ። ሄሚ ያሳያችሁ ፣ ቀላል ነው ፣ ሄሚ መጠ በቂያውን አላቅና ስጣቸው ፣ ከዚያ በኋላ ማለምና ምላጩን መሳብ ነው ።»

ወደ መኝታችን ከመሔዳችን በፊት መሣሪያዎቹን ተቀበልንና እንዴት መጠቀም እንዳለብን ሄሚ ያሳየን ጀመር ።

መጠበቂያውን ወደ ታች ታደርጉና መምታት ወደ ምትፈልጉት ታልማላችሁ ። ከዚያ ምላጩን መሳብ ነው ። መሣሪያውን ጠበቅ

አድርጋችሁ መያዝ አለባችሁ ። አለዚያ ስትተኩሱ ከጃችሁ ይወድቃል ። ሌላው ድምፁ አስደንጋጭ እንደሚሆን ከአሁኑ ማሰብ አለባችሁ » አለን ።

«ሲያዩት ቀላል ይመስላል» አልኩኝ ።

«አዎ ! ቀላል ነው ፣ መተኮስ ስትጀምሩ ትለምዱታላችሁ» አለን ።

ከዚያ በኋላ እኔና ጃክ አንድ ክፍል ውስጥ በተለያየ አልጋ ላይ ተኛን ።

ዝም ብዬ ቆየሁና፣ «ጃክ ! እንቅልፍ ወሰደህ?» አልኩት ።

«መተኛት አልቻልኩም ፣ ብዙ ነገር እያሰብኩ ነው ፣ ፎርዱዋን መኪና መለወጥ አለብን » አለኝ ።

«ለምን?»

«ፎቶግራፍሽ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ ሲወጣ ፣ መኪና አከራዮቼ መኪናቸው እንዳልተመለሰላቸው ለፖሊስ ይናገራሉ ። ስለዚህ መኪናዋ ትታወቃለች ማለት ነው ። የተከራየሽው በመደበኛ ስምሽ ነው ፣ አይደለም?»

«ነው ። »

«ስለ ምትታወቅ ባልቲሞር እንደ ደረስን ሌላ መኪና ፈልገን እዚያው እንተዋታለን ።»

በጨለማ ሲጋራ ሲያቀጣጥል አየሁትና እኔም አቀጣጠልኩ ።

«ጃክ ! አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ ። ለምንድነው ስማይሊን እዚህ ውስጥ ያስገባኸው? ከዚህ በፊት ዕዳ አለብኝ ስትል አልነበረም?» አልኩ ፣ የዚያ የምስኪን ሰው አሟሟት እየታየኝ ።

«አዎ ! ለነበረብኝ ዕዳ ስል አስገባሁት ። በቅርቡ ብዙ ንብረቶች አግኝቼ ዕዳየን እንደምከፍለው ስነግረው ፣ እውነቴን መሆኑን በቅርብ ለመቆጣጠር እንዲመቸው ለመሳተፍ ፈለገ ። ምንም ማድረግ ስለ አልቻልኩ አስገባሁት ። ይሄ የውሻ ልጅ አያምነኝም ነበር ። ብቻ ዋጋውን አግኝቷል ። የማያምኑኝን ሰዎች በጣም እጠላቸዋለሁ » አለኝ ።

'እኛስ እናምነው ይሆን?' እያልኩ አሰብኩ ። ሲጋራችንን አጨስን እንደ ጨረስን እንቅልፍ አልወስድሽ አለኝ ። ጃክ ሲገላበጥ ተሰማኝና የተናገረ መስሎኝ ፣ «ምንድነው ጃክ?» አልኩት ።

ለራሱ የሚናገር ይመስል ፥ «ዕድሜዬን በሙሉ ያሳለፍኩት እዚር ቤት ነው ፣ የዐሥር ዓመት ልጅ ሆኜ ነው የጀመርኩት ፥ ሆዴን ለመሙላትና ልብስ ለማግኘት ምን መሥራት እንዳለብኝ ተማርኩ ፥ ትሰሚያለሽ?»

«እሰማሃለሁ ።»

«እኔ አውሬ አይደለሁም ፥ ጭንቅላት አለኝ ። ሌላ ሰው መሆን ነበረብኝ እንኚ ሕይወቴን በሙሉ በውንብድና የማሳልፍ ሰው አል ነበርኩም ። ጥሩ ጭንቅላት እንዳለኝ ዐውቃለሁ ። እና ከእዚር ቤት በተለቀቅኩባቸው ጊዜያት ውስጥ ራሴን መለወጥና ማሻሻል ነበረ ብኝ ። አልሆነም ! እንደ ገና ወደ እዚር ቤት መመላለስ ዕድሌ ሆነ ። ምን ዓይነት ሕይወት ነው? ሌላው ከሁሉም የባሰው ደግሞ ሉብነቱ ከኔ ጋር አብሮ የተፈጠረ ይመስል አልለቅህ ብሎኝ ፥ ፀሐይ ሆኖብኝ መቅረቱ ነው ። መቼ ነው ከዚህ የምላቀቀው ? ራሴን በራሴ እያጠ ፋሁት ነው ። ሁል ጊዜ የሚጨንቀኝ ይሄው ነው ። ምናልባት ይህ የመጨረሻው ሆኖ ጥሩና ንጹሕ ሰው እሆን ይሆን?»

«ሚያሚ ከነሀብታችን ደርሰን ወደ ፊት ስለ ምናሳልፈው ጥሩ ሕይወት እያሰብክ ነው?»

«አዎ ! አንቺስ ምን ታስቢያለሽ?»

መልስ አልሰጠሁትም። ያለ ዕረፍት ሲገላበጥ ይሰማኛል፤ መስኮቱን ስመለከት ከውጭ ባለው ጭቡራት አማካኝነት በረዶ ሲጥል አየሁ ።

«ጃክ ! አንተ ጋ መጥቼ ልተኛ» አልኩት ።

«ጥሩ ነው ፤ ኪሐሳብ ይገላግለናል» አለኝ ።

እሑድ ለት ምንም የምንሠራው አልነበረንም ። ምናልባት ወደ ውጭ ስንወጣ ሻንጣችን ቢሰረቅ በሚል ጌጣጌጦችን ተከፋፍለን ይዘናል ። ሄሚ መኣረያዎቹን እየወለወለ ፥ «ጃክ ! ጥይት እንደሚያ ስፈልገን ታውቃለህ?» አለው ።

«አዎ ዐውቃለሁ፤ ወደ ደቡብ እየተጠጋን ስንሔድ ያለ ምንም ጥያቄ በቀላሉ ጥይት ልንገዛ እንችላለን ። ለመንገዳችን አሁን ያለው አይበቃም?»

«ይበቃናል ።»

ከሰዓት በኋላ ሙኝታ ከፍላችን ውስጥ ሁላችንም ቁጭ ብለን ቮድካ እየጠጣን የእግር ኳስ ጨዋታ በቴሌቪዥን እንመለከት ነበር ።

በረዶ መጣሉን አቁሟል፤ መንገዳችንን መቀጠል እንዳለብን ዕንወቅ እንጂ እንሒድ ለማለት የሞከረ አልነበረም ። የእግር ኳስ ጨዋታው እንዳበቃ ዜና ተጀመረ ። ፓኪስታን ስለ ደረሰው ድርቅ ፣ ፖላንድ ውስጥ ስለ ተከሰከሰው አውሮፕላን ፣ ቦምቤ ውስጥ በተነሣው እሳት ሳቢያ ስለ ሞቱት ሰዎች ከአተተ በኋላ፣ በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ በሚገኝ አንድ ሥጋ ቤት ውስጥ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ተገድለው በፖሊሶች መገኘታቸውንና ሰዎቹ ከመገደላቸው በፊት በአሰቃቂ ሁኔታ ስለ ተገረፉ፣ የሚጾቹን ማንነት መለየት እስካሁን እንዳልተቻለ ተናገረ።

ጃክ ከመቀመጫው ረጋ ብሎ ተነሣና ቴሌቪዥኑን ዘግቶ ወደ መስኩቱ በመሔድ ወደ ውጭ መመልከት ጀመረ ።

«ጃክ ! አዳመጥክ?» አለ ሄሚ ።

«አዎ ! »

«እንማን ይመስለሃል?»

«አንጄላና ጐስት ናቸው፤ አልተሳካላቸውም» አለ ዲክ በመገረም።

«ስለኛ ተናግረው ይሆናል ብለህ ነው የተገረምከው» ብሎ ጃክ ዲክ ላይ አፈጠጠበትና ፣ «አትገረም ! ይናገራሉ ! ራስህ ፣ እኔም ወይም ሌላውም ቢሆን እንደዚያ ሲሠቃይ ዝም አይልም ። አሁን ስለ ጠቅላላው ሁኔታችን ታውቋል ። ስለዚህ ይሂን መኪና ወደዚያ መጣል አለብን» አለ ።

ረጋ እንዲል አስቤ ፣ «ባለፈው ጊዜ ጐስት ጐበዝ ነው ይሳካ ለታል ብለኸኝ ነበር ። እንዴት ሊያገኙዋቸው ቻሉ?» አልኩት ።

«ምን እውቃለሁ ! ምናልባት አንጄላ ለአንድ ዘመድዋ ስጦታ አበርክታ ይሆናል ። ስጦታውን ያገኘች ሴት እየዞረች ለጓደኞችዋ ታሳያለች ። በዚህ መንገድ ሊነቃ ይችላል ። ሌላም የሚታወቅበት ብዙ መንገድ ሊኖር ይችላል ። የውሻ ልጅች ! ጐስት ያለ ምንም ዱላ የጠየቁትን ይነግራቸው ነበር ። እኔም ይህን እንደሚያደርግ ዐውቃለሁ ። ሆን ብለው ነው የጐዱዋቸው? ለምን እንደሆነ ዐውቃችኋል?»

«ስለጐስት እንደምንሰማ ወይም ጋዜጣ እንደምናነብ ስለ ሚገምቱ። ለእኛ ምን እንዳዘጋጁልን መግለጻቸው ነው ። ከዚህ ጉድ መውጣት ትፈልጋላችሁ? ብትመለሱ አልቃወምም ። እኔና ሄሚ ንብረቱን ተከራፍለን እንለያያለን ። እናንተ ፖሊስ ጠርታችሁ ዕድላችሁን መሞከር ትችላላችሁ » አለን ።

ዲክና እኔ ተያየን ።

«አይሆንም ! አንተ የተንከርከበትን ያህል እኛም ተንከረንብ ታል ። ስለዚህ አሁን ወደ ኋላ የምናፈገፍግበት መንገድ አይኖርም » አለ ዴክ ።

«ይሄ የራሳችሁ ምርጫ ነው ። በሉ ዕቃችንን እንጫንና መንገዳ ችንን እንቀጥል ፤ ቦታውም ደስ አላለኝም ።»

ዴክ መኪናውን ወደ ባልቲሞር መንገድ ሲነዳ ሄሚ አጠገቡ ፣ እኔና ጃክ ከኋላ ተቀምጠናል ። ዘጠና አምስተኛውን መንገድ በመያዝ ወደ ባልቲሞር አመራን ።

«ባልቲሞር እንደ ደረስን ሌላ መኪና ማግኘት አለብን ። ገንዘ ብም ያስፈልገናል ፤ ወደ ደቡብ ዋሽንግተን ከደረስን የትም ሆቴል ሳናርፍ ከፈለግን ሚያሚ መድረስ እንችላለን » አለ ጃክ ።

«ለኔ በጣም ደስ ይለኛል ፤ ያለ ዕረፍት መጓዝ ጥሩ ነው» አልኩኝ።

ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ «ትላንት ማታ ለብዙ ቀን የሚያስፈልግ ሽን ያህል ዕረፍት ስለ ወሰድሽ ነው?» አለኝ በማንሾካሾክ ። ይህን ሲለኝ ከፊታችን የሚመጡትንና በኋላ ያሉትን መኪናዎች እያስተ ዋለ ነበር ።

ከቤቱ ከወጣንበት ሰዓት ጀምሮ ከእጁ ሰለ አልተለየው መጽ ሐፉ አነሣሁለት ። «ስማኝ ጃክ ! መጽሐፌን መያዝ ለምን እንደ ፈለክ ገብቶኛል ። ለዚህ ምንም ተቃውሞ የለኝም ። እኔ የምፈልገው መጽ ሐፉን እንድትሰጠኝ ሳይሆን ያለፍናቸውን ችግሮችና ደስታዎች ለመ ጻፍ ስለምፈልግ ነው ። ምንም የሚጐዳህ ነገር የለውም ። ሌላው ቢቀር በየቀኑ የተደረጉትን ድርጊቶች ብጽፍና ባጋጣሚ እንኳን ብን ያገ፡ ጃክ አስገድዶን ወይም ተጠልፈን ነው ብንል ተቀባይነት ስለ ማይኖር፡ አንተን ከወንጀሉ ነጻ ሊያደርግህ ይችላል። መጽሐፉን እንደ ፈለክ ያዘው ። እኔ ግን የየዕለቱን ድርጊት ልጻፍበት ። በእጅ የሚያዝ የጽሕፈት መኪናና ወረቀት ብቻ ነው የሚያስፈልገኝ ። ሆቴል ስና ርፍ ልጠቀምበት እችላለሁ ። ሆቴል ሳናርፍ መጓዝ እንደሚያስፈ ልገን ካመንክበትም መኪና ውስጥ ታይፕ ማድረግ እችላለሁ ።»

«የጽሕፈት መኪናው የማይታሰብ ነው ። አንደኛ ጭነት መጨ መር ነው። ሁለተኛ አልቤርጎ ውስጥ ስትተይቢ አጠገባችን የሚገኝ ክፍል ድረስ ድምፅ ስለ ሚሰማ ችግር ይፈጥርብናል ።»

«እሺ ! የጽሕፈት መኪናውን የማላገኝ ከሆነ እርሳስና ወረቀት እገዛና የየለቱን ድርጊት እጽፋለሁ» አልኩትና በዚህ ተስማማን ።

በምሥራቅ ባልቲሞር በሚገኝ አንድ አልቤርጎ አደርን ። በዚህ አልቤርጎ እኔና ዲክ አብረን አንድ ክፍል ፣ ጃክና ሄሚ በሌላኛው ክፍል ተኛን ።

መኝታችን ላይ ሪረፍ እንዳልን ፣ «ይሄ ሰውዬ ሆን ብሎ የሚያደርገው ይመስልሃል?» አልኩት ዲክን ።

«ምኑን ነው ሆን ብሎ የሚያደርገው ?»

«አንድ ቀን ከሄሚ ፣ አንድ ቀን ካንተ ፣ አንድ ቀን ከሱ ጋር እንድተኛ የሚያደርገኝ ? የቡድኑ ፍቅረኛ አድርጎ ቆጥሮኝ ነው እንዴ?» አልኩት ። እየሣቀ ፣ «ሆን ብሎ የሚያደርገው አይመስለኝም ! ደግሞስ ምን ለማግኘት ?» አለኝ። እኔ ምንህውቂ ጃክ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ በግዴለሽነት የሚፈጽም ሰው አይደለም ። መኝታችንን በየጊዜው መለዋወጥ የፈለገበት የራሱ የሆነ ተንኮል አቅዶ ሊሆን ይችላል» አልኩት ።

«ጸሐፊነትሽን አሁንም አልረሳሽውም ?»

«መርሳት አልችልም ዲክ ! ጃክን ትወደዋለህ ?»

«አዎ ! የተግባር ሰውና የሚፈልገውን ማድረግ የሚችል በመሆኑ እወደዋለሁ ፣ አደንቀዋለሁም ።»

«አሃ ! አንተ አልጋ ላይ ይሻላል ፣ ወይስ እኔ አልጋ ላይ እንተኛ?»

«ምን ለውጥ ያመጣል ?»

ዲክ አልጋዬ ላይ መጥቶ ከተኛም በኋላ ዝም ማለት አልቻለም ። ማውራቱን ቀጠለ ። የሚያጋጥሙኝ ወንዶች ሁሉ አልጋ ላይ ወሬ ይወዳሉ ።

«ምን እንደ ነካኝ ዐላውቅም ። በዘረፋ ውስጥ መሳተፌና ፖሊሶች መሸሸ ፣ ስለ መሣሪያ አጠቃቀም ማወቄ ሁሉ እኔ የፈጸምኩት ሳይሆን በሌላ በማላውቀው ሰው የተፈጸመ ነው የሚመስለኝ ። እኔ ራሴ የፈጸምኩት መሆኔን ማመን አልቻልኩም ፣ ጄኒ ! ሰው እንዴት ማንነቱን ሳያውቀው ይኖራል ?» አለኝ ።

«የምትለውን ሁሉ እየፈጸምን ነው ። ተደስተህበታል ?»

«እንደ ገና እንደ መወለድ እቆጥረዋለሁ ። ባለፉት ሰዓታት ሁሉ የተደናገጥኩበትና ግራ የተጋባሁበት ጊዜ ነበር ። ይሁንና አስደናቂም ፣ አስገራሚም ነው ። ጃክና ሄሚ ስለ ግድያ ሲያወሩ ለነሱ መሬው

አዲስ አይደለም ። የለመዱት ነው፤ ለኔ ግን አዲስ ነው። አሁን ግን ለመድኩት ።»

«እንተ እንደምታስበው እኔም አስባለሁ ። ለምንድነው ይህን ሁሉ የምፈጽመው? ለመጽሐፍ ብዬ ነው እንዳልል መጽሐፉ በእጄ ገብቷል ። ከዚህ ሁሉ ጣጣ መራቅ ሲገባኝ አርቲፊሻል ጸጉር አድርጌ ሕይወቴን ለማዳን እየሸሸሁ ነው ። ለምን? ... እንዳንተው ባለፈው ሕይወቴ የተሰላቸሁና አሁን ያለሁበትን ሁኔታ እንደ ቲያትር ስለ ቆጠርኩትና ስለ ወደድኩት ይሆን ?»

«ምናልባት ይሆናል .»

«ወይም አንተ እንደ ምትፈልገው እኔ ለምንም ቦታ ብቁ መሆ ኔን ማወቅና ማረጋገጥ ፈልጌ ይሆን? ባለፉት ጊዜያት የምጽፋቸው መጽሐፎች ሁሉ ሕልምና ውሸት ነበሩ ። አሁን ግን፣እውነትነት ያለው መጽሐፍ የምጽፍ ስለ ሆነ፣ ምን ያህል ተግባራዊ ማድረግ የምችል መሆኔን ለማየት በመጓጓቴ ይሆን ?»

«መጽሐፍሽ እስካሁን የደረሰበት ደረጃ በጣም ጥሩ ነው ።»

«አመሰግናለሁ !»

በማግሥቱ ሰኞ ዕለት ምሳ ሰዓት ላይ ተሰብስበን አዲስ መኪና ስለሚገኝበትና ፎርዱን ስለምንሸጥበት ዘዴ መወያየት ጀመርን ።

«ስለ መኪናው ጉዳይ እኔና ሄሚ እንጨርሳለን » አለን ጃክ ።

እኔ ግን ለማወቅ በመጓጓት ፣ «እንዴት ልታደርጉ ነው የቆመ መኪና ልትሰርቁ ?» አልኩኝ ።

«መሰረቅ አያስፈልግም» አለ ፊቱን በመጨምደድ ፣«ያገለገለ መኪና ከሐቀኛው ሳም ወይም ከሐቀኛው ጆን ለመግዛት እንሞክራ ለን » አለና በመቀጠል ፣«ሰምን መሰለሽ ሐቀኛ የተባሉት? አሮጌ መኪና የሚሸጡ ሰዎች ብዙውን ጊዜ እውነት ለመናገር ፣ በሐቅ ለመ ናገር የሚል ታል ስለ ሚያበሩና የሚገዛው ሰው ማነው? ምንድነው ብለው ጥያቄ ሳይጠይቁ ገንዘብ ላይ ብቻ ስለ ሚያተኩሩ ሐቀኞች ተባሉ ። እኔና ሄሚ ፎርዱን መኪና ይዘን ሔደን የሚሸጥ መኪና እን ፈልጋለን ፣ አንቺና ዴክ ሱቅ ሐዳችሁ ኦንዳንድ ዕቃዎችን ገዛሁ » አለን ።

ከአስተናጋጇ እርሳስ ተወሽ የሚያስፈልጉንን የዕቃዎች ዓይ ነት ዝርዝር ጻፍኩኝ ። ለመጽሐፌ አገልግሎት የሚውል እርሳስና ወረቀት በመጀመሪያ መዘገብኩ ። ወንዶቹ ሹራብ የውስጥ ሱሪና

ካልሰ. አስመዘገቡኝ ። ለራሴ የጡት መያዣም ጸናኩና ወረቀቱን ቦርሳዬ ውስጥ ማስገባት ስጀምር መጠጥና ደረቅ ምግብ እንዳልረሳ ጃክ አስታወሰኝ ። እንደ ገና መዘገብኩ ። ወደ አልቤርጎአችን ተመልሰን ዕቃችንን ጫንን ። እኔንና ዲክን ሱቅ አደረሱን ። ዲክ ከመኪናው ወጥቶ ልከተለው ስል፡ ጃክ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣ «ከዲክ ጋር ያሳለፍሽው አዳር እንዴት ነበር?» አለኝ ።

«ካንተ ጋር ካሳለፍኩት የበለጠ ነበር » አልኩት ።

እየሣቀ፣ «አንቺ ውሻ» አለኝና ተሰናየን ።

የምንፈልጋቸውን ዕቃዎች ለመግዛት ሦስት ሰዓት ፈጅብን ። የገዛነውን ዕቃ ይዘን ወደ መንገድ ዳር ሔድንና እንጃክን መጠባበቅ ጀመርን ።

«ሠላሳ ደቂቃ ያህል ጠብቀን ካልመጡ ከዚህ አካባቢ መጥፋት አለብን ፡ ምናልባት ጥለውን ጠፍተው ሊሆን ይችላል » አልኩት ።

«በምንም ዓይነት ጥለውን አይሔዱም ፡ ጃክ እመለሳለሁ ካለ ይመለሳል ።»

«ታምነዋለህ ?»

«እሱም መታመን ይፈልጋል ።»

«አሃ ! ይሄንንም ዐውቀሃል?» አልኩት ፡ ፀይን ፀይኑን እያየሁት ።

«አዎ ! እንዲያውም እኛው ልሽሽ መጡ !» አለኝ ራሱን በመነቅነቅ ጭምር ።

በግምት ሦስት ዓመት ያገለገለች ፔዣ ጃክ እየነዳ ፡ ሄሚ በኩራት መልክ አጠገቡ ተቀምጠ አጠገባችን አቆሙ ። የመኪናዋ ቀለም ትንሽ ተጫጭሮአል ። እንዲያውም ተግልብጣ እንደ ገና ተቀጥቅጣ የተቃናች መሆኗ ይታወቃል ። ሆኖም ከሩቅ ሲያዩዋት ደህና ትመስላለች ።

ጃክ ከመኪናዋ ወርዶ የገዛነውን ዕቃ እየጫነ ፡ «ስለ ቀለምዋ ምንም አያስጨንቅም ፡ አዲስ መኪና የተመልካችን ዐይን የሚስብ ስለሆነ አያስፈልገንም ። ይሄን አሮጌ መኪና ማንም ዞር ብሎ የሚያየው የለም ። ዋናው ነገር የሞተሩ አዲስነት ነው ፡ ከመግዛታችን በፊት ሞክረንዋል ፡ ጠንካራ ነው » አለን ።

«ስትገዙ ምንም ችግር አላጋጠማችሁም ?»

«ምንም አላጋጠመንም ። ጃክ እንዳለው የሸጠልን ሰው ስሙ 'ሐቀኛው ፔርሲ' ነው ። መኪናው ላይ ከተለጠፈው ዋጋ አምስት መቶ ብር ቀንሰን ሰጠነው ። ተስማማ» አለ ሄሚ ።

«እውነተኛ ስምህን ነገርካቸው እንዴ ?» አለ ዲክ ።

«አዎ ! የመንጃ ፈቃዴን ማየት ስለ ፈለገ ነግሬዋለሁ ፣ ሌላው ግን ለጉዞአችን አመቺና አቋራጭ የሚሆነን መንገድ ጠይቄው ነግሮ ኛል ። ምናልባት የሚከታተሉንን ለጊዜው ግራ ለማጋባት የምንችል በት መንገድ አግኝተናል ።»

መኪናችንን አስነሥተን ወደ መንገድ ዘጠና አምስት ደቡብ አመራን ። ሄሚ መኪናዋን ሲነዳ አጠገቡ ዲክ ተቀምጦአል ።

«ፎርድዋን መኪና የት ጣላኋችት ?» ብዬ ጃክን ጠየኩት ።

«አንቺ ስለ ወንጀል አጸያፍ ልምድ አለሽ! ጥሩ ጥሩ መጽሐፍ ጽፈሻል ። እንደ ጸሐፊነትሽ አንድ መኪና እንዳይገኝና ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ ትፈልጊያለሽ እንበል ! እንዴት ነው ይህን ተግባራዊ የምታደርጊው ?»

«ምን ዐውቃለሁ ። ምናልባት ሰው ወደማይገኝበት አካባቢ ወስጄ አቆመዋለሁ ። ወይም ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ አስገብቼ ዕን ጨት እላዩ ላይ ከምሬ እደብቀዋለሁ ። አለዚያም ታርጋውን ነቅዬ ወንዝ ውስጥ እጥለዋለሁኝ፤ ሰው የማያየኝ ከሆነም መኪናዋን እንዳለ ወደ ገደል ገፍቶ መጣል ። ይህን የመሰለ ብዙ መንገድ አለ ።»

«ባልሽው ሁሉ መንገድ ማጥፋት ይቻላል ። ግን አድካሚና አደገኛም ቢሆን አንቺ ባልሽው በጥቂት ቀኖች ውስጥ ከተደበቀበት ቦታ ይገኛል ። እኛ ያደረግነው ፣ እኔ ፎርድዋን ፣ ሄሚ ፔገሮዋን እየ ነዳ ከመንገድ ወጣንና ዕቃችንን ወደ ፔገሮዋ ጫንን ። አደገኛ ሌቦች ወደ ሚገኙበት ሠፈር ድረስ ሔደን ወደ ጥግ ቦታ ፎርድዋን አቁሜ በሩን ሳልቆልፍ ከመኪናዋ በመውረድ ፔገሮዋ ውስጥ ገባሁና መን ገዳችንን ወደ እናንተ ቀጠልን ።»

«ነገ ጥዋት ፎርድዋን ያቆምንበት ቦታ ብንሔድ የምናገኘው ሻንሲዋን ብቻ ነው ። መጀመሪያ ጐማውን ይወስዳሉ ፣ ቀጥሎ ባት ሪውን ፣ ካርቡሬተሩን ፣ የነዳጅ መያዣውን በቀላሉ አውልቀው ይወ ስዱታል ። የሰፈሩ ጐረምሶችም የመኪናዋን ወንበር ለመገናኛ ክበ ባቸው ያረጉታል ። የተረፈውን ቀፎ አሮጌ የመኪና መለዋወጫ ሻጮች

ይዘውት ይሔዳሉ ። ምናለፋሽ ከዐሥራ ሁለት ሰዓት በኋላ መኪ
ናዋ የለችም ። የምትፈለገው መኪና እንዳትገኝና ከምድረ ገጽ ለማ
ጥፋት ዘመናዊ ዘዴው ይሄ ነው ።»

በመንገድ ዘጠና አምስት ስንዝዝ ቆይተን ወደ ዋሽንግተን ከተማ
ዳርቻ ተጠጋን ። በየመንገዱ የማያቸው ከተሞች ሁሉ በእየሩ ጠባይ
ምክንያት የደበዘዙ ይመስላሉ ።

ራታችንን ፍሬደሪክስበርግ ተብሎ በሚጠራው ምግብ ቤት
በልተን መንገዳችንን ቀጠልን። አሁን መኪናዋን የምነዳው እኔ ስሆን፤
ዲክ አጠገቤ ተቀምጧል ። ነዳጅ ለመሙላት ማደያ ቆምን ። ነዳጅ
እስከሚሞላ ጃክ ከመኪና ወረደና በረዶና መጠጥ ገዝቶ ተመለሰ ።
ወደ ደቡብ ሪችመንድ ስንቀጥል የአየሩ ጠባይ የተሻለና ደስ የሚል
ነበር ።

ጃክ የመጠጥ ጠርሙስ ከፍቶ የምንፈልገውን ዐይነት በኩባያ
ቀዳልንና እየጠጣን መንገዝ ጀመርን ። ወደ ሪችመንድ ልንደርስ ስንል
እግራችንን ለማፍታታትና መንዳቱንም ለመቀያየር ጥግ ቦታ አቁመን
ከወረድን በኋላ ትንሽ ተዝናናን ።

ወደ መኪናችን አቀማመጣችንን ለውጠን ገባን ። ጃክ መኪናዋን
እየነዳ ሲሆን ፣ ሄሚ አጠገቡ ተቀምጧል ። እኔና ዲክ ከኋላ ነን ።
የገዛሁትን ወረቀት በማንሣት ለመጻፍ ፈልጌ ፣ በቂ ብርሃን ስለሌለ
ተውኩት ።

መንገዳችንን ወደ ደቡብ ቀጠልን ። «ሮኪማውንት ስንደርስ
አልቤርጎ ፈልገን እንተኛለን ። አለዚያም መንገድ ላይ መኪና
የማይበዛ ከሆነ መንገዳችንን እንቀጥላለን» አለን ጃክ ።

እኔና ዲክ ከኋላ ተቀምጠን ማንቀላፋት እንደ ጀመርን ፣ ጃክና
ሄሚ ቀስ ብለው ሲያወሩ ትንሽ ትንሽ ይሰማኛል ። ትንሽ ቆይቼ
የመኪናዋ ፍጥነት ሲቀንስና ወደቀኝ ሲታጠፍ ተሰምቶኝ ከእንቅልፌ
በመባነን ፣ «የት ደረስን?» ብዬ ጠየኩ ።

«ሮኪ ማውንት ደርሰናል ። እኔና ሄሚ ወርደን ሽንታችንን እዛ
መሸናት ፈልገን ነው የቆምነው» አለ ሽንት ቤቱን በእጁ እያመለከተ ።

«እኔም መሸናት እፈልጋለሁ» ስል ዲክም እየተንጠራራ «እኔም
አለ» መኪናችንን ጥግ አቁመን ወደ ሽንት ቤት ለመሔድ እንደጀመ
ርን ሄሚ ቆም አለና ጃክ ይታይሃል ብሎ ወደፊት ለፊታችን አመለ
ከተ ። ወደአመለከተው ቦታ ሁላችንም ተመለከትን ። «ጌምስኮክ»

የሚል ስም የተለጠፈበት ቡና ቤት አየን ። ተመልሰን ወደ መኪናችን ገባንና ወደ ቡና ቤቱ ሔደን ቆምን ።

በመኪናው ማቆሚያ ቦታ ብዙ መኪናዎች ፣ ሞተር ብስክሌቶችና የትራክተር ጋሪዎች ቆመዋል ። ወደ ቡና ቤቱ ተመለከትን ፣ የሙዚቃም ድምፅ ውጭ ድረስ ይሰማል ።

«በጣም የሚያስደስተን ቦታ ሳይሆን አይቀርም» አልኩ ።

«እኛን ሊያስደስተን የሚችል ቦታ ከሆነ ጥሩ ነው ። የመኪናችንን በር እንቆልፍና ጌምስክክ ምን ያህል ሊያዝናናን እንደሚችል እንይ» ብሎን ጃክ ወደ ቡና ቤቱ ገባን ።

ክፍሉ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለውና ጣውላ ቤት ሲሆን ፣ ብዙ መንበር የለውም ። አብዛኛው ሰው ባንኮኒ ተደግፎ ይጠጣል ። የተወሰኑ መንበሮችና ጠረጴዛዎች ጥግ ላይ ይታያሉ ። የክፍሉ መሻል ለመደነሻ እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ ይምሰል እንጂ ባዶ ነው ።

ቡና ቤት ውስጥ ዐይን የሚስብ ምንም አዲስ ዕቃ የለም ። መብራቱ ደብዘዝ ቢሆንም ፣ እያንዳንዱ ቁልጭ ብሎ ይታያል ። ግድግዳው ላይ የምግብ ዝርዝር ከነዋጋው ተለጥፎአል ። ሜድቤቱ እዛው አጠገባችን ሳይሆን አይቀርም ። ቡና ቤቱ ውስጥ ሆኖ ምግብ እየተዘጋጀ መሆኑ ይታወቃል ። በርካታ ወንዶችና ሴቶች ግማሾቹ ተቀምጠው ሌሎቹ ደግሞ ቆመው ይጠጣሉ ። ተክታትለን ስንገባ ሁሉም ወሬአቸውን አቋርጠው እኛን መመልከት ጀመሩ ። ገብተን እንደ ተቀመጥን ጨዋታቸውን ቀጠሉ ።

አብዛኛዎቹ ወንዶች ፊታቸው የገረጣ ገበሬዎች ፣ የሕንፃ ሠራተኞችና የስልክ መስመር ጠጋኞች ይመስላሉ ። ሴቶቹ እውነት ለመናገር እኔን ቢያ ፍላጎደርን ይመስላሉ ። ሁሉም አርቴፊሻል ጸጉር ፣ ትልቅ የጠቆ ማስያዣና ረዥም ተረከዝ ያለው ጫማ ያደረጉ ሆነው ፊታቸውንም የተለያየ ቅባት ተቀብተዋል ፤ ባጠቃላይ ሲተኛ አዳሪዎች ይመስላሉ ።

በግምት ዕድሜዋ ከዐሥራ አምስት ዓመት የማይበልጣት አስተናጋጅ ልትታዘዘን መጣች ። እንደ አኳሆኗ በሥራው ላይ የብዙ ጊዜ ልምድ ያላት ይመስላል ።

መጠጥ አዘዝናትና ልታመጣልን ስትመለስ ሁላችንም በዐይናችን ተከተልናት ። ሱሪና ጃኬት የለበሰች ሲሆን ፣ ሆድ የሚባል ያላት አይመስልም ፤ ዳሌዋም ኩራ ያለና ስትሔድ ይንቀጠቀጣል ። የልጅትዋ አቋም የወንድ ዐይን የሚማርክ ነው ።

«እንደምገምተው ጥሩ ገበያ ሳይኖራት አይቀርም ፤ ሄሚ እን ዴት ነው?» አለ ጃክ ።

«አዎ ጥሩ ናት! ወደ ሚያሚ ከኛ ጋር መሔድ ትችል እንደሆነ ልጠይቃት እንዴ?»

«አይሆንም! እንደዛ ማለቴ አይደለም ። እንዳትጠይቃት ቦታ የለ ንም» አለ ጃክ በፍጥነት አሳጋገር ።

«እንዳልክ! ብቸኝነቱ እየተሰማኝ ነው»

«ሄሚ! ብቸኛ እንደሆንክ ይገባኛል ። ለአንድ ወይም ለሁለት ቀን ታገሥ ፣ ከዚያ በኋላ ወደ ሚያሚ ስንጠጋ ብቸኛ አትሆንም ፣ እሺ?»

«እሺ!»

አስተናጋጅዋ ተመልሳ መጠጣችንን ስታቀርልብን ሽንት ቤት የት እንደሆነ ጠየቃት ፤ በማድቤቱ ውስጥ አልፎ እንደሚገኝ ነገረ ችው ።

«አካባቢውን ማየት ስለምፈልግ ፣ መጀመሪያ እኔ ልሒድና ልመል ከት ፣ ስመለስ ተራ በተራ እናንተም ታዩታላችሁ» ብሎን ጃክ ወደ ማድቤቱ ሔደ ። ሌሎችም ወንዶችና ሴቶች እንዲሁ በማድቤቱ ይመላለሱ ።

ወዲያው ተመለሰ ። ወንበሩ ላይ ሀረፍ አለና ፣ «የወንዶችና የሴ ቶች ሽንት ቤት የተለየ የለም ። ሽንት ቤት የሚል ጽሑፍ አለ ፣ ያንን ተመልከተሽ አፍንጫሽን ይዘሽ መግባት ትችያለሽ» አለኝ እየሳቀ ።

ያለን ሁሉ እውነት ነው ። የአካባቢ የጤና ተቆጣጣሪዎች እንዴት እንዳላዩት የሚገርም ነው ። ሽንት ቤቱ ከመሙላቱ የተነሣ በቅርብ ሀይነምድሩ ይታያል ። የሚገርመው ልቡና ቤት ተስተናጋጆች ሁሉ «ከሽንት ቤት ስትወጡ እጃችሁን መታጠብ አትዘንጉ» የሚል ማስ ታወቂያ መለጠፉ ነው ። ማስታወቂያው ጥሩ ነበር ፤ ግን ውኃ ሆነ ሳሙና የለም ። መታጠቢያው ሣህን አጠገብ የተንጠለጠለው ፎጣም ከመቆሸሹ የተነሣ ቆርጥዶአል ።

በጓሮ በኩል ወደ ውጭ የሚያስወጣ ትንሽ መነገድ አለው ። በማድቤቱና በሽንት ቤቱ መካከል ሁለት የስልክ መነጋገሪያ ሣጥኖች አሉ ። ከስልኮቹ አጠገብ ሽቶ ፣ ሲጋራ ፣ ማበጠሪያና ፣ ሽንት ቤት ወረ ቀት የሚሸጥ በጣም ትንሽ ሱቅ ይገኛል ።

የማድ ቤቱ ንገር ሌላ ነው ፣ ሽታው የምግብ ፍላጐትን ያባብሳል ግን ውስጡን ሲመለከቱት የከሰል ማስቀመጫ መጋዘን እንጂ ማድ ቤት አይመስልም ። ምግብ አብሳዩ ከወገቡ በላይ ራቁቱን በላብ ተኑ ክሮ እጠባቡ የሚቀቀለውን ሥጋ በዕንጨት ማማሰያ በመላስ መረቁን ቀመስ እያደረገ መልሶ ማማሳያውን ብረት ድስቱ ውስጥ ይከተዋል ። ይህን እያዩ ከዚህ ቤት ለመመገብ መሞከሩ ሲያስቡት ያጥወለውላል ።

ሄሚና ዳክም በተራቸው የጓሮውን ሁኔታ ተመልከተው መጡና መጠጥ ደገምን ። አስተናጋጅዋ መጣችና ምግብ መብላት የምንፈልግ መሆናችንን ጠየቀችን ።

«መብላት እንፈልጋለን ፤ ግን እዚህ አይደለም ። ሒሳባችንን ንገራን» አለ ጀክ ።

የመጠጡን ሒሳብ በወረቀት ላይ አሰበችና ነገረችን ። ጀክ ከኪሱ ገንዘብ አወጣና ሒሳቡን ከጉርሻ ጋር ከፍሎ ተነሣን ።

ሄሚ ቀደም ብሎ ወደ በሩ በመሔድ በሩን ከፍቶልን ወጣን ። የሰማይ ከዋክብት ጥርት ብለው ይታዩ እንጂ ጨለማ ነው ። ቆም ብዬ ከዋክብትን አየሁ ።

«ጀክ! ወደቀኝ ተመልከት» አለ ሄሚ ቀስ ብሎ ።

ሁላችንም ወደአሉን ቦታ ተመለከትን ። በኛ ትይዩ ከቆመ መኪና ግራና ቀኝ ሁለት ሰዎች እጃቸውን ኪሳቸው ውስጥ ከተው ቆመዋል ። ዝም ብለን ቆመን ስንመለከት ፣ ዐይናችን ላይ የመኪናው መብራት በራብን ። ወዲያውኑ በስተግራ በኩል ከቆሙት መኪናዎች ተመሳሳይ መብራት አበሩብን ። መብራቱን በእጁ ከዐይኔ እየከለልኩ ለማየት ጣርኩ ። ካፖርት የለበሱ ሦስት ሰዎች ቆመዋል ።

«ሳትቸኩሉ ፣ ሳትሮጡ ወደውስጥ ተመለሱ» አለን ጀክ ።

ወደ ጌምስኮክ ተመልሰን ገባን ። ጀክ ከቡና ቤቱ መጨረሻ ወደ ሚገኘው ቦታ መራንና ተቀመጥን ።

አስተናጋጅዋ ፣ ወደኛ መጥታ ጠረጴዛውን እየወለወለች፣ «እንደ ገና ተመለሳችሁ?» አለችን ።

«አዎ! ለመንገድ አንዳንድ ለማለት ፈለግን ። ደብል ደብል ፎድካ ቅጅልን»

«ታዛኘ ነኝ» ብላ መጠጡን ልታመጣልን ሔደች ።

ቀስ ብዬ በመንሾካሾክ መልክ «ጀክ! እነማን...» ስለው አጭር ጠኝ ፣

«እፍሽን ዝኒ» ብሎ አፈጠጠብኝ ።

«ለምን በጓሮ በር አንሞክርም?» አለ ዲክ ።

ጥርሱን ብልጭ አደረገና፡«በጓሮ በኩል የማይጠብቁን መሰለህ? ሰዎቹን እንዲህ ቀላል አረካቸው? በዚህ ዐይነት ሥራ ብዙ ልምድ ያላ ቸው ናቸው ። አታምነኝም አይደል? ካላመንክ ለመውጣት ሞክርና ታገኘዋለህ» አለ ጃክ ።

አስተናጋጅዋ፡መጠጣችንን አምጥታ እፊታችን አስቀመጠችልን ። ጃክ የመጠጡን ሒሳብ አውጥቶ ከጉርሻ ጋር ከፈለና አስተናጋጅዋ እስ ክትሔድ ሁላችንም ዝም አልን ። ጃክ አንድ እጁን ጠረጴዛ ላይ አሳ ርፎ ፊቱን በማዞር ቡና ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች አንድ በአንድ ተመለከታቸውና ፡

«እዚህ ውስጥ የነሱ ሰው ያለ አይመስለኝም ፡ በዚህ እርግጠኛ ነኝ ፣ እስክንወጣላቸው ይጠብቁናል እንጂ እዚህ ድረስ መጥተው ሊይ ዙን አይፈልጉም» አለ ።

«መኪናችንን! መኪናችንን ሳይለዩዋት አይቀሩም ፤ ታዲያ ለምን የበሩን ቁልፍ ወይም መስተዋቱን ሰብረው ጌጡን አይወስዱትም» አልኩ በጭንቀት ።

«ጌጡን ብቻ የሚፈልጉ ይመስልሻል? እስቲ ትንሽ አስቢ? በመ ጀመሪያ ደረጃ የሚፈልጉት እኛን ነው ።»

«ስማ ጃክ! ምናልባት ፖሊሶች ሊሆኑ ይችላሉ» አለ ሄሚ ረጋ ብሎ ።

«በምንም ዐይነት ፖሊሶች አይደሉም ። እነሱ ቢሆኑ ኖሮ በርከት ብለው እናያቸው ነበር ። እነዚህ የድርጅቱ ሰዎች ናቸው»

«በምን ተአምር መኪናችንን ሊያውቁት ቻሉ?»

«ሐቀኛው ጂርሲ ነግሮአቸው ሊሆን ይችላል» አለ ዲክ ።

«ይሆናል ወይም ፎርድዋን ጥለናት ስንሔድ ያየ ሰው የፔገርዋን ታርጋ መዝግቦት ይሆናል ፡ ወይም ከባልቲሞር ጀምሮ ተከታትለውን ይሆናል ። አሁን ስለዚህ መጨነቅ ጥቅም የለውም ። ማሰብ ያለብን ይህን ከበባ እንዴት ሰብረን መውጣት እንደምንችል ነው ።»

«ጃክ ወደ ጓሮ በር ወጥቼ ብተኩስ... ታውቃለህ አይደል ሰውን ባስደነግጠው ውጭ የሚጠብቁትም ሆኑ እዚህ ውስጥ ያሉት ለማየት ወደ ጓሮ ሲወጡ እናንተ...» አለ ሄሚ ።

ጃክ አቋረጠውና እጁን ሄሚ ላይ አሳርፎ ፡«አመሰግናለሁ ሄሚ አያዋጣም! ወዲያው መተኮስ እንደ ጀመርክ ባንድ ጥይት ያስቀሩሃል፡ ደግሞስ ምን ጥቅም አለው? ምንም ቢሆን የመውጫውን በር አይለቁልንም ። አሁን ዝም ብላችሁ እንዳልተጨነቀ ሰው እየጠጣችሁ ተዝናኑ ፡ ተጫወቱ» አለን ።

እንዳለን ለመሆን ሞከርን ። ምንም ችግር እንደሌለብን ሁሉ እየ ተሳሳቅን አወራን ። ቀስ ብዬ ወደ ውጭ በጨረፍታ ተመለከትኩ ። ቅድም በርተው የነበሩት የመኪና መብራቶች ጠፍተዋል ።

«ስማ ሄሚ ቅድም በጓሮ ወጥቼ ልተኩስ ማለትህ ብዙ ጩኸትና ግርግር ልፍጠር ማለትህ ነው አይደል?»

«ልክ ነህ ወጥቼ ልሞክር?»

«አይደለም፤ያልከውን እያሰላሰልኩ ነበር ። አሁን የምናደርገው እንደዚህ ነው ፡ ጂኒ ዝርዝር ሳንቲም አለሽ?»

በራሴ የአምንታ ምልክት አሳየሁት ።

«ጥሩ! እኔና አንቺ ቀስ ብለንና እየተዝናናን በማድ ቤቱ በኩል ወደ ጓሮ ወጥተን በቀጥታ ወደ ሰልኩ እንሔዳለን ። አንቺ ልክ እንደ ፈራና እንደ ተጨነቀ ሰው በመምሰል ለእሳት አደጋ መከላከያ ትደ ውይና ጌምስኮክ በእሳት መያያዙንና እውስጡ ያለነው ሰዎችም ለመ ውጣት እንዳልቻልን ትገልጪያለሽ ። አስታውሺ! ስትናገሪ በጭንቀ ትና በእንባ የተዋጠ ሰው መምሰል አለብሽ»

«ይሽን ማድረግ እችላለሁ » አልኩት ።

«እንደምትችይ ዐውቃለሁ ። ያለን ዕድል ይሽው ነው ፤እኔ ደግሞ ሌላውን ስልክ በመጠቀም ወደ ፖሊስ እደውልና ሦስት መሣሪያ የታ ጠቁ ሰዎች ቡና ቤት ውስጥ ያሰውን ሰው በሙሉ ግድግዳ እስደግፈው እየዘረፉ ስለሆነ ቶሎ እንዲደርሱ እነግራቸዋለሁ ። ከተሳካልን በአ ምስት ወይም በሠር ደቂቃ ውስጥ አካባቢው በግርግር ድበልቅልቁ ይወጣል ። ሄሚ! ሁለታችሁ እየጠጣችሁ እዚሁ ትጠብቁናላችሁ ። ከዚህ ቦታ እንዳትንቀሳቀሱ ፤እኛ ሽንታችንን ለመሸናት እንደ ወጣን ቁጠሩት» በይ ተነሽ ትርዒታችንን እንጀምር» ብሎኝ ተነሣን ።

እንዳለኝ ፊት ፊት በመሔድ ወደኋላ መለስ እያልኩ እያወራሁና እየሳቅሁ በማድቤቱ አልፈን ስልኩ ቦታ ስንደርስ፤የማይሠራ የሚል ተጽፎበት ሳይ በድንጋጤ ክው ብዬ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ ። ጃክ ፈጠን ብሎ ትከሻዬን ያዝ አርጎ ወደ ስልኩ ተመልክቶ ፡

«ለመውደቅ ሞክሪያትና ደሽን አንገትሽን ቁንጥሼ ነው የም ጥለው» አለኝ በሚያስፈራራ ድምፅ ።

ትከሻዬን ጠበቅ አርጎ እንደያዘኝ ወደሌላኛው ስልክ ወሰደኝ ፤ ይሽኛው አይሠራም የሚል ምልክት የለውም ።

«በይ እንዳልኩሽ ደውይ ፡ ስምሽን ከጠየቁሽ አትንገሪያቸው ፤ ዝም ብለሽ አልቅሺ» አለኝና ወደ ውስጥ አብሮኝ ገብቶ በሩን ዘጋው። እንደ መሰለኝ ወንድና ሴት አንድ የስልክ ቦታ ውስጥ አብሮ መታየት በጌምስኮክ ቡና ቤት አዲስ አይደለም፡ ዞር ብሎ የተመለከተን ሰው አል ነበረም ።

እጄን እያላበኝ ሳንቲሙን ጨምሬ ቁጥሩን ማሠር ጀመርኩ ። ሦስት ጊዜ እንደጠራ

«ምን እንታዘዝ» የሚል የሴት ድምፅ ሰማሁ ።

«እሳት አደጋ መከላከያ ነው? ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ቶሎ ድረሱልን ፡ ማለቃችን ነው ፡ ነደድን ፡ እባካችሁ...»

«አንድ ጊዜ... አንድ ጊዜ ከሚመለከተው ጋር ላገናኝሽ» አለችና ከአንድ ወፍራም ድምፅ ካለው ወንድ ጋር አገናኘችኝ ።

«ይሂ...» አለና ሲጀምር ፡

ስልኩን ወደአፌ በደምብ አስጠግቼ «እሳት! እሳት! አሠቃቂ ነው ፡ ሰዎች እየተቃጠሉ ነው ፡ ቤቱ በሙሉ...»

«የት ነው? ከየት ነው የምትደውይው?» ብሎ ጮኸ ።

«ከጌምስኮክ ነው ፤ ዘጠና አምስተኛው መንገድ አጠገብ ካለው» ብዬ ማልቀሴን በመቀጠል፡ «ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ቶሎ ድረሱልን ፡ ቤቱ በሙሉ ተያይዞአል ፡ ሰዎችም እየተቃጠሉ ነው ። መውጫም የለንም...»

«ስምሽ ማነው?» ብሎ ጮኸ ።

«እባካችሁ ድረሱልን አልኩት» የፍርሃት ልመና እያስመሰልኩ።» «እሳቱ እየተወረወረ ነው ። ማድቤቱም ነደደ ። እንዲሁም...»

ጃክ እጄን ሰዶ ስልኩን ዘጋው ።

«በጣም ጐበዝ» ይሽን ያሀል ትሆኛለሽ ብዬ አልጠበቅሁሽም ነበር። በጣም ጥሩ ነው ፤ በይ ነይ ውጭ፤እኔ ደግሞ ዕድሌን ልሞክር» አለኝና ወደ ውጭ ሳብ አርጎኝ ተከተለ ።

ያለምንም መርበትበት ሳንቲሙን ጨመረና ስልኩን ደወለ ። ጠጋ ብዬ ማዳመጥ ጀመርኩ ። አፕሬተሯን አግኝቶ በአካባቢው ከሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ጋር አገናኘችው ።

«ስሙ! ወንበዴዎቹ ሲሰሙኝ ስለሚችሉ ከዚህ በላይ ጮክ ማለት አልችልም። ጌምስኮክ ቡና ቤት ታውቁት የለ? ጥሩ! መሣሪያ የታጠቁ ሦስት ሰዎች ሰውን ግድግዳ አስደግፈው እየዘረፉ ነው! አዎ! አሁንም አሉ ፤ ተጠንቀቁ እንዳታስጨርሱን መሣሪያ ይዘዋል ፣ ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ፣ ቶሎ ድረሱልን ፣ የኔ ስም...» ወዲያው ስልኩን ዘጋው ።

የሚገርመው ስልኩ የመለሰለትን ሳንቲም አልረሳም ፣ አንሥቶ ኪሱ ከተተው ።

«እንዴት ነው? ጥሩ ነው?» አለኝ ።

«በእኔ በኩል ጥሩ የሠራሁ ይመስለኛል» አልኩት ።

እጇን ያዥኝ አለኝና ተያይዘን በማድቤቱ በኩል ስናልፍ ፣ «ቅድም በመፍራቱ ይቅርታ አድርግልኝ?» አልኩት ።

«ይኸ ያለ ነው ፣ ምንም አይደለም»

ቦታችን ደረስንና መጠጣችንን አንሥተን መጠጣት ጀመርን ። «እንዴት ነው?» አለ ዲክ ቀስ ብሎ ።

«ጥሩ ነው! ዕድላችን ካማረ በቀላሉ መውጣት እንችላለን ። አሁን የምናደርገው እንደዚህ ነው... የእሳት አደጋውን መኪና ድምፅ ስትሰሙ መጠጣችሁን ትጨልጣላችሁ ፤ ከዚያ በኋላ በመነሣት ወደ መስኮቱ ተጠግተን እየተሳሳቅንና እያወራን እንቆማለን ። ቀድሞ የሚመጣው የፖሊስ ሆነ የእሳት አደጋ መኪና እስከሚቆም ድረስ ጠበቅን ሰዎቹ ወርደው ወደ ቡና ቤቱ ማምራት ሲጀምሩ እንወጣለን ። ከወጣን በኋላ ፡ ሁኔታው አመቺ መሆኑን አይተን ወደ መኪናችን እንሔዳለን ። ሂሚ ከኛ ቀድመህ መኪናውን ትከፍትና ሞተር አስነሥተህ ትጠብቀናለህ። እኛ መኪና ውስጥ እንደገባን አቅጣጫህን ወደ መንገድ ዘጠና አምስት አርገህ ወደ ደቡብ ትታጠፋለህ...»

«ወደ ሰሜንም ሆነ ወደ ደቡብ ብንሔድ መከተላቸው አይቀርም፤ ስለዚህ ወደፊት ከምንሔድ ለምን ወደ ኋላ አንሔድም?» አለ ዲክ ።

«ወደኋላ ብንመለስ የሚጠብቀን ብዙ አደጋ ይኖራል። የማምለጫ ብቸኛ መንገዳችን ዝም ብሎ ወደፊት መጓዝ ነው ። ሂሚ እንዴ መኪና ውስጥ የመግባት ዕድል ካገኘን በፍጥነት መጓዝ አለብህ ፤ መንገድ

የሚዘጋ መኪና ካጋጠመህ በጐን በኩል ገጭተህ ለማለፍ ሞክር እንጂ እንዳትቆም።»

«በዚህ አትጠራጠር፤ እንዴት ማለፍ እንደምችል አሳይሃለሁ» አለ ሄሚ ።

እኔና ጃክ ስልክ ያወለን ከተመለስን በአምስት ደቃቂ ውስጥ ከሩቅ የእሳት አደጋ መከላከያ መኪና የአደጋ ድምፅ እያሰማ ሲመጣ ሰማንና መጠጣችንን ጨልጠን ተነሣን ። እየተሳሳቅንና እያወራን ወደ መስኮቱ ተጠግተን ቆምን ። የአደጋ ምልክቱ ድምፅ እየቀረበ መጣ ።

«የእሳት አደጋ መኪና ነው ፣ ፖሊሶቹን ቀደሚቸው ማለት ነው!» አለ ጃክ ።

ከመኪናው የሚመጣው ጩኸት እየተጠጋን ሲሔድ ፣ ቡና ቤት ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ ከወንበሩ እየተነሣ ግማሹ በመስኮት ሲያይ ግማሹም ወደ ውጭ መውጣት ጀመረ ።

ጆሮ የሚያደነቁረው የአደጋ ድምፅ ከቡና ቤቱ ውስጥ የሚወጣ ይመስላል ። መኪናው ወደ ቡና ቤቱ ተጠግቶ ሲቆም ፣ የአደጋ ምል ክት የሆነው ቀይ መብራት ብልጭ ድርግም ሲል በመስኮት በኩል ይታያል ። መኪናው እንደ ቆመ ወደ በሩ ሮጥን። በመስኮት ይመለከት የነበረው ሰው ሁሉ ተከትሎን ወደ ውጭ ወጣ ።

ውጭ ሦስት የእሳት አደጋ መኪናዎች ቆመዋል ። ግማሾቹ ሠራተ ኞች የውኃ መርጫ ላስቲካቸውን ሲዘረጉ ፣ ሌሎች ደግሞ አነስተኛ መጥረቢያና በእጅ የሚያገለ የእሳት ማጥፊያ ቆርቆሮ ይዘው ከመኪና ወረዱ ። ሌላ የአደጋ ጩኸትም ወዲያው ተሰማ። ሁለት መኪና ፖሊሲ ችን ይዞ ደረሰ ። ከጌምስኮክ የወጣው ሰው በር ላይ ቆሞ ወዴት እንደሚ ሔድ ግራ የተጋባ ይመስል እርስ በርሱ መተራመስ ጀመረ ።

ጃክ ወደ ግራና ቀኝ ተመልክቶ፣ «አሁን ነው ማምለጫችን!» አለ። ሄሚ ከፊቱ ያገኘውን ሰው ሁሉ እየገፈተረ እኛ ከኋላ ተከትለን መሮጥ ጀመርን ። ጃክ ከኋላዬ ሆኖ ትከሻዬን ይዞ ወደፊት እየገፋኝ መኪናችን ጋ ደረሰን ። ሄሚ በሩን ከፍቶልን ሁላችንም ገባን ። በሩን እንኳን ሳንዘጋ ሄሚ መኪናዋን በፍጥነት አስነሣ ፣ የቆመውን የእሳት አደጋ መኪና ለመግጨት ምንም ያህል አልቀረውም ። ወደ ጌምስኮክ የሚያመራ ሦስተኛ የፖሊስ መኪና ጋርም ፊት ለፊት ለመጋጨት ምንም አልቀረንም ነበር። ሆኖም የሄሚ መኪና የመንዳት ችሎታው ከፍ ተኛ ስለነበር ሳንጋጭ ተረፍን። ወደ መንገድ ዘጠና አምስት ስናመራ ከፊታችን ያገኘነውን መኪና ሁሉ በጥሩንባ እያስደነበርን፣ መንገድ

እያስፀቅን በከፍተኛ ፍጥነት ተጓዝን ። ሄሚ ወደፊት ብቻ እየተመለከተ መንዳቱን ቀጠለና የሚያሚን መንገድ ተያይዘነው፣ ወደ ኋላችን ዞር ብለን የተከተለን መኪና መኖሩን ለማረጋገጥ አየን ። አንድም የተከተለን መኪና አልነበረም ።

ጃክ እንደ ማሉቀስም ፡ እንደ መሳቅም እየቃጣው ፣ «አመለጥን... አመለጥናቸው!» አለ ።

ስለ ጅማንነታችንና ስለ ችሎታችን ለአምስት ደቂቃ ያህል እየሳቅን፣ እየቀለድን ስናወራ ቆይተን ሁላችንም ጸጥ አልን ። እጇ ከኔ ቁጥር ውጭ ሆኖ ይንቀጠቀጣል ።

«ጃክ ብርዱ ይሁን ድንጋጤው አልገባኝም ፡ ሊያመኝ ነው መሰለኝ መጠጥ ካለ ልትሰጠኝ ትችላለህ?» አልኩት ቀዝቀዝ ባለ ድምፅ ።

ከኔ ጋር ከኋላ ተቀምጦ ስለነበር ወደኋላ ዞር ብሎ ከዕቃ ማስቀመጫው ብራንዲ አውጥቶ በፕላስቲክ ኩባያ አፉ ድረስ እየሞላ፣ መጀመሪያ ለሄሚና ለዴክ ከዚያ ለኔ ሰጥቶን መጠጣት ጀመርን ። «ሄሚ በፍጥነት በመሔዳችን ምክንያት አንዱ እንዳያስቆመን ከአሁን በኋላ ፍጥነትህ ከስል ፤ አይብለጥ» አለው ።

እስካሁን ፍጥነታችን ከሰባና ከሰባ አምስት መካከል ባለው ነበር ። ሄሚ የመኪናችንን ፍጥነት ሲቀንስ ሰዓቱ ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖአል ። መንገዱ ግን በመኪናዎች ተጨናንቋል ።

«ለስመአብ! ሰው ሁሉ ወደ ሚያሚ ነው እንዴ የሚጓዘው!» አልኩኝ በመሣቅ ። አንድም ሙሉስ የሰጠ ሰው አልነበረም ። የጨለማውን ጉዞ በገምታ ተያያዝነው ። እንቅልፌ የመጣ ቢሆንም፣ ለመተኛት ፈራሁ ።

«እንዲህ ግምት ሊሆን ይችላል ። እርግጠኛ ነኝ ቡና ቤት ውስጥ ገንዘብ ሲቀበል የ፤ በረው ሰውዬ ጠቁሞብን ሳይሆን አይቀርም ። መጀመሪያ እንደገባን እዬና ጂኒ ተራ በተራ ወደ ሽንት ቤት ስንሔድ ሰውየው ወደ ጓሮ ወጥቶ ስልክ መደወሉን ልብ ብለኸኋል?»

ማንም ያየ አልነበረም ።

«ምናልባት ወጥቶ ስልክ ደውሎ ይሆናል ፣ ግን ከመኻከላችን ያየ ሰው የለም ማለት ነው » አለ ጃክ ።

«ጃክ እንዴት ሊሆን ይችላል ፣ ሰውዬው መኪናችንን ሳያይ በምን ምክንያት ጠርጥሮ ሊጠቁመብን ይችላል?» አለ ዴክ ።

«ልክ ነህ መኪናችንን አላየም ። መኪናዋን ባያያትም ፣ እኛን አይቶናል ። ይሽን ልል የቻልኩበት ምክንያት የሌቦቹ ድርጅት ስለኛ እንቅስቃሴ ለማወቅ ለየቡና ቤቱ፣ ምግብ ቤቱና አልቤርጎዎች ባለቤቶችና በየወኪሎቻቸው አማካኝነት ይጠይቃሉ ። ስለዚህም ከድርጅቱ ወኪል አንዱ ጌምስኮክ በመሔድ ለባለቤቱ ትንሽ ጉርሻ ቢጤ ይሰጥና ሦስት ወንዶችና አንድ ሴት በመሆን አብረው የሚጓዙ ሰዎች እንዳየህ በዚህ ስልክ ቁጥር ደውልልን ብሎ ስለሁኔታችን ይገልጽለታል ። እርግጠኛ ነኝ፣ አንጂላና ጐስትም በዚህ ዓይነት መንገድ ነው ሊያዙ የቻሉት ። ከዚያም እኛ ያልንህ ሰዎች ከጋጠሙህና ከደወልክልን ኪፍተኛ ገንዘብ እንሰጥሃለን ብሎ ቃል ገብቶ ይሔዳል ። እንግዲህ የቡና ቤቱ ባለቤት በዚህ መልክ ተጠቅሞ ነው ጉድ ሊሠራን የሞከረው ።» ፥

ትንሽ አሰብኩና ፣ «በሌላ በኩል የቡና ቤቱ ባለቤት መኪናችንን እንዳላየ እርግጠኛ ነኝ ። ምክንያቱም ከቡና ቤቱ ርጠን ስንወጣ ፣ መኪናችን አጠገብ አንድም ሰው አልነበረም ። መኪናችንን ዐውቀዋት ቢሆን ኖሮ ፣ እኛን ብቻ ሳይሆን መኪናዋንም ይጠብቁዋት ነበር ። ሌላው ማረጋገጫ ያልተከተሉንም በየትኛው ዐይነት መኪና እንደ ምንጓዝ ስለአላወቁ መሰለኝ» አልኩ ።

«እርግጠኛ ነኝ ፣ በመጨረሻ ስናመልጥ ምን ዐይነት መኪና እን ደያዝን አይተዋል » አለ ዲክ ።

«ሊያዩንም ላያዩንም ይችላሉ ፣ በእንደዛ ያለ ግርግር ውስጥ የእ ሳት አደጋውና የፖሊስ መኪኖች ጩኸት በተደበላለቀበትና ሰዎችና መኪና በሁሉም አቅጣጫ በተንቀሳቀሱበት ፣ ያን በመሰለ ጨለማ ውስጥ መኪናችንን መለየት አይችሉም ። ብታምኑም ፣ ባታምኑም ይቺ መኪና አልታወቀችም ። ሰዎቹም ራሳቸው ሰላማዊ የነበረው ቦታ በአ ጭር ጊዜ ውስጥ ድብልቅልቁ ሲወጣ ሳይደናገጡ ይቀራሉ ብላችሁ ነው » አለ ጀክ ።

«ለምንድነው ዝም ብለህ በአእምሮህ የመጣልህን ሁሉ ትክክል አድርገህ የምትናገረው?» አልኩኝ በበኩሌ ።

«ጀኒ መጽሐፍሽን አንብቤዋለሁ ፤ ታዲያ 'የመጣልኝ ሐሳብ ሁሉ ትክክል ነው' እያልሽ አሰብ ነበር ብለሽ ለምንድነው የጻፍሽው?» ሲል እኔኑ መልሶ ጠየቀኝ ።

«እንደኛ የማትረሳው ነገር የለም ማለት ነው ! መጽሐፌ ላይ ማስፈሬን እንዴት አስታወስክ? ጥሩ! ዋናው ነገር አንተ ባልከው ይሁን፣ ወይም በሌላ መንገድ ተከታትለውን ዐውቀውን ነበር ። ዋናው ነገር ለጊዜውም ቢሆን አምልጠናቸዋል ፣ አሸናፊዎች ነን» አልኩት ።

«ከዚህ በፊትም አሸንፈናቸዋል ፣ ወደፊትም ድሉ የኛ ነው ። ከዚህ ቀደም እንደሚሳካልን ነግሬያችሁ አልነበረም፣ እውነቱን ነው የምላችሁ ። ብዙውን ጊዜ አንድ ነገር እንደሚሳካልኝ ስረዳ ፣ ቶሎ እንዲሆን ስለምጓጓ ሁሉንም ነገር ትቼ ስለጉዳዩ ብቻ እያወጣሁና እያወረድኩ ፣ ቀና የሆነውን መንገድ ቶሎ እወስናለሁ ። ይቺን መኪና ከገዛን በኋላ እንዴት አርገን በሌላ መኪና መለወጥ እንዳለብን ሳሰላስል ነበር ። አሁን ግን ሳስበው መኪናዋን መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም ። ለቀኛው ፔርሲም አልተናገረም ፣ ፎርዱዋንም ትተን ስንሔድ ያየን ሰው የለም ። ስለዚህ ይቺ መኪና ስለአልታወቀች አስ ፈላጊ ናት ።»

ምናልባት ከሱ ሐሳብ የተሻለ ማቅረብ አቅቶን ሊሆን ይችላል ። የተናገረውን የተቃወመ ሰው አልነበረም ።

ሁሉንም ውሳኔና አስተያየት ለጃክ መተው ትልቅ ዕረፍት ነው ። ወዴት እንደምንሔድ ፣ መቼ እንደ ምንሔድ ፣ የት ማረፍ እንዳለ ብንና እንዴት መሆን እንዳለብን የሚወስንልን እሱ ብቻ ሆኖአል ።

«ሄሚ ወደ ራሴይ ሔደን መኝታ ቦታ ስለ ምንፈልግ ወደ ግራ ታጠፍ ። የዛሬ መንገዳችንን ሰጊዜው እናቆማለን ። ነገ በተመቸን ሰዓት ተነሥተን ወደ ምሥራቅ በመምጣት ጉዞአችንን በስሚዝ ዋና መንገድ በኩል አድርገን እንቀጥላለን» አለ ጃክ ።

በታዛዥነት መልክ ፣ «እሺ ጃክ!» አለ ሄሚ ።

ዊልሰን አካባቢ ስንደርስ ወደ ምዕራብ ታጠፍንና በመንገድ ቁጥር ሁለት መቶ ሠላሳ አራት ተጉዘን ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ራሴይ ደረስን ። መንገዳችን ረዥምና በተገኘው አልቤርጎ ስለ ምንተኛ ንጽሕናው አስተማማኝ እንደማይሆን መገመቴ ትክክል ነበር ። አሁን በያዝነው መኝታ ክፍልም ችግሩን ስለ ሚያውቁ ነው መሰለኝ፣ የቁንጫ መግደያ መርዝ የያዘ አነስተኛ የታሸገ ቆርቆሮ በየክፍሉ አስቀምጠዋል ። እኔ ከጃክ ጋር አንድ ክፍል ውስጥ ተኛሁ ። ደግነቱ ጃክ አልጋ ላይ እንደ ደረሰ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው።እና ሲያንኮራፉ አልሰማሁትም እንጂ ፣ ማንኮራፋት ቢጀምር ኖሮ የቁን ጫውን መድኃኒት አፉ ላይ ለመርጨት ተዘጋጅቼ ነበር ።

በማግሥቱ እስከ ቀትር ድረስ ሁላችንም ተኝተን ተነሣንና ቁር ሳችንን ለመብላት ወደ ምግብ ቤት ሔድን ። ወደ ደቡብ በምናደር ገው ጉዞአችን ውስጥ ካስደሰቱኝ ነገሮች መካከል፣ ጥሩ ምግብ ቤት የምንመገብ ከሆነ አስተናጋጆዎቹ ከፈገግታ ጋር እንዴት አደራችሁ እያሉ የምንጠጣውን ቡናና ሻይ ሲቀዱልን ማየቱ ነበር ።

ሆዳችን ሞልቶ ቁጭ ብለን ሀሐይ ስንሞቅ ቆየን ። ሁሉም ነገር ሰላማዊ ይመስላል ።

ቀኑን ገሞ ብለን ተቀምጠን ከምንውል ጌጣጌጥ እንሸጥ ብለን ወደ መኝታ ክፍላችን ተመለስንና የጌጣጌጥ ቦርሳዎችን ከፍ ተን ተመለከትን። በቀላሉ የሚሸጡት ትናንሾቹ ጌጦች ጥቂት ሲሆኑ ሌሎቹ እነስተኛ ከተማ ለመሸጥ የሚያስቸግሩ ትላልቅ ጌጦች ብቻ ሆነው አገኘናቸው ።

ጀክ ከቀሩት እነስተኛ ጌጦች ውስጥ የተወሰኑትን መርጠ ኪሱ ከተተና፡«እነዚህን ለመሸጥ እሞክራለሁ ። ሦስታችሁም እዚህ ትጠ ብቁኛላችሁ ። ወደ ውጭ አትውጡ ፡ ቴሌቪዥን ማየት ትችላላችሁ ፡ መጠጥም ጠጡ ፡ መኪናዋን ይዤ ስለ ምሔድ እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት እመለሳለሁ ። በዐሥራ አንድ ሰዓት ካልተመለስኩ መያዜን ተረድታችሁ ከዚህ አካባቢ በተቻለ መጠን ለመጥፋት ሞክሩ» አለ ።

«ጀክ !» አልኩት ለመናገር እያወላወልኩ ።

«ምነው ?»

«አንድ ያልነገርኩህ ነገር አለ ። ምክንያቱም እርግጠኛ አል ነበርኩም ነበር ፡ አሁን ግን ብነግርህ ጥሩ መሰለኝ ።»

«ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ምንድን ነው?»

«ታስታውሳለህ! መጀመሪያ ከጌምስኮክ ስንወጣ በስተቀኝ በኩል ቆሞ የነበረው መኪና መብራት ሲያበራብን ሁለት ሰዎች መኪናው አጠገብ ነበሩ ። ወዲያው በስተግራ ቆሞ የነበረው መኪና ሲያበራ ብን መብራቱን ለመከላከል ሀይኔን በእጄ ከልዬ ስመለከት ሦስት ሰዎች ቆመው አየሁ ። እንደሚኖር ገምቼ ሲሆን ይችላል ፡ ከቆ ሙት መካከል አንዱን ሰው የማውቀው መሰለኝ ። አጭር ወፈር ያለና ካፖርት የለበሰ ሲሆን ፡ እንደ አለባበሱ ከሰሜን የመጣ ይመስላል ። ፊቱን ግን ለማየት አልቻልኩም ። ብቻ እሱ መሰለኝ ።»

ወዲያውኑ «ጆርሺስ! የሱቱ ኃላፊ?» አለኝ ።

«አዎ ! አንቶኒዮ ሮሲ»

«አንቶኒዮ ሮሲ ! እርግጠኛ ነሽ?»

«መብራቱ ዐይኔ ላይ ስለ በራ ሙሉ በሙሉ አይቼዋለሁ ለማ ለት አስቸጋሪ ነው ። በጨለማ ውስጥ በጨረፍታ ነው ያየሁት ፤ ሳየው እሱ መሰለኝ ።»

ለጥቂት ደቂቃ የታችኛው ከንፈሩን ወደ ላይ በመለጠጥ ሲያስብ ቆየና ፣ «ሊሆን ይችላል ። ግን በጣም ይደንቀኛል ፣ ማለቴ እንዴት ዝም አሉት? እኛን ከገባንበት ገብቶ እንዲይዝ በመፍቀዳቸው ሰውየው ዕድለኛ ነው ።»

«እንዴት ነው ዕድለኛ የሆነው?»

«ምክንያቱም ፣ ዘረፋው ወዲያው እንደ ተፈጸመ ሊገድሉት ይገባ ነበረ ። አንቺን ራት እንደ ጋበዘሽና ሰክሮም ብዙ ምስጢር እንዳወጣ ያውቃሉ ።»

«ራት እንደ ጋበዘኝ እንዴት ያውቃሉ?»

«አይ ጂኒ ! እሱ ትንሽ አስቢ ! በአሁኑ ጊዜ ፎቶግራፍሽ በየ ቦታው ተበትኖአል ። ከጂርሺስ ጋር እዚያ ምግብ ቤት አብራችሁ ገብ ታችኋል ። አልገባሽም? ይሄን መጽሐፍሽ ላይ ጽፈሽዋል ። ስለዚህ እዚያ ያሉት አይተውሻል ማለት ነው ። ይሄን ሁሉ ካወቁ በኋላ ሰውየው በዘረፋው ውስጥ እጁ ይኖርበታል በሚል ገምተው ምንም ሳይጠይቁት ይገድሉት ነበር ። ግን ይህ ሳይሆን የሌቦች ድርጅት እኛን እንዲ ፈልገን ዕድል ሰጥተውታል ። በጣም ዕድለኛ ነው ።»

«እንዴት እኛን ብቻ እንዲፈልግ ትላለህ? ጌጣጌጡስ?»

«አነርሱ የሚፈልጉት ጌጣጌጡን ይመስልሻል» በርግጥ ይፈ ልጉታል ። በመጀመሪያ ደረጃ ከጌጡ በላይ የሚፈልጉት ግን እኛን ነው ። በምንም ዓይነት መንገድ ጌጡን ይዘን እንድንጠፋ አይፈል ጉም ። ይሄ ለነሱ መጥፎ ወሬ በየቦታው ያስነግሩባቸዋል ። እንደ ገናም በሌላ ቡድን ዘረፋ ይቃጣባቸዋል ። ይህን ሁሉ ለመከላከል እኛን ይዘው መቀጣጫ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ ። ለዚህ ነው አንቶኒዮ ሮሲ የሚከተለን ። እጁ እስክንገባ ድረስ የትም ይሁን የትም አይለቀንም ። ይሄን ካላደረገ ያግሞ ለራሱ ሕይወት ያሠጋዋል ። በሉ ልሒድ ብሎን ወጣ ።

እንደ ውጣ ቤሩን ቆለፍንና ጃክ እንዳለን መጠጥ እየጠጣን ቴሌ ቪዥን ማየት ጀመርን ። በኋላም ሄሚና ዲክ ተቀምጠው ማንቀላፋት ሲጀምሩ የገዛሁትን ወረቀትና እርሳስ ይዤ መጽሐፌን ከወቅቱ ጋር ለማመሳሰል ቶሎ ቶሎ መጻፍ ጀመርኩ። ዐሥር ሰዓት ሲሆን አውን ስለ አለንበት ሁኔታ ገልጬ ጽሑፌን አቆምኩ ።

ወደ መታጠቢያ ቤት ሔጄ ሰውነቴን ታጠብኩና ልብሴን ለባ ብሼ እነ ዲክን ቀሰቀስኳቸው ። ጃክ እንደ መጣ ለመንገር እንድንችል ዕቃዎቻችንን ሁሉ አዘጋጀን ።

ጀክ በዐሥራ አንድ ሰዓት ካልተመለስኩ ከዚህ በተቻለ መጠን ለመጥፋት ሞክሩ ብሎናል ። ግን ምንድነው የምናደርገው በኔ በኩል ምን ማድረግ እንደሚገባን አላውቅም ። በሕይወቴ በሰው ሐሳብ ተመርቼ አላውቅም ። ይህ የመጀመሪያዬ ነው ። በአሁኑ ጊዜ በማላ ውቀው ሕይወት ውስጥ በሰው መመራቴ አልከፋኝም ። ከብዙም ችግር አውጥቶኛል ። በዚህም ተደሰቼበታለሁ ። ሆኖም ይህ ሰውዬ ቢሞት ወይም ቢያዝ ምን ማድረግ እንዳለብን ስለ ማናውቅ ‘ምን ሊውጠን ነው?’ የሚለው ሐሳብ አእምሮዬን በጠበጠው ።

ጀክ ግን፡ ካለው ሰዓት በፊት ቀደም ብሎ በጁ ትንሽ ካርቶን ይዞ ፊቱ በድንጋጤ ተሞልቶ መጣ ። እንደ ደረሰም፡ «ሁሉንም አዘጋጅተሃል ! ጥሩ! አሁኑኑ መንገዳችንን እንቀጥል !» አለን ።

ሁላችንም ተመለከትነው ።

«ጀክ ! ምንድ ነው? ሁኔታህን ሳየው የሆንከው ነገር አለ ። ምን አጋጠመህ ?» አልው ዴክ አጠገቡ ከሰው ወንበር ዘርፈጥ ብሎ ቁጭ አለና እግሩን ወደ ፊት እየዘረጋ ። «እየሁት ... ያን የውሻ ልጅ አየ ሁት ። ጀኒ ግምትሽ ትክክል ነው» አለ ጮርነን ባለ ድምፅ ።

«አንቶኒዮ ሮሲን ?»

«እዎ ከሆቴል ቤት ሲወጡ አየሁዋቸው ። ተመስገን ነው እኔሱ ሳያዩኝ እኔ አየሁዋቸው ።»

«እነሱ ስትል ምን ማለትህ ነው? ስንት ናቸው ?»

«አንቶኒዮ ሮሲና ሌሎች ሁለት ሰዎች !»

«አብረውት ያሉ ሰዎች እንዴት ያሉ ናቸው? ጠባቂ ይመስላሉ ?»

«እንደዛ ነው የመሰለኝ ...» አለና ፈገግ ብሎ፡ «አንቶኒዮ ሮሲ ቶሎ ሊይዘን ባለመቻሉ የሌቦች ድርጅት እየተጠራጠረው ሳይሔድ አልቀረም ። እንዲይዘን ፅድሉን ሰጥተውታል ፡ ግን ራሱም ቢሆን እንዲያመልጣቸው አልፈለገም ። ስለዚህ ነው ጠባቂ የመደቡበት » አለ ።

«እዚህ ራሴይ ምን ይሠራል? ማለቴ እንዴት ሊመጣ ቻለ? ወደ ዚህ ስንመጣ የተከተለን መኪና አልነበረም » አልኩ ።

«እንዲሁ ባጋጣሚ ነው ። ከዋናው መንገድ ገባ ብለው የሚገኙ ከተሞችን ሁሉ ያስሳሉ ። እኛ ባለንበት ከተማ እሱ መገኘቱ አጋጣሚ ነው ። ምንም የሚያሠጋን አይደለም ።»

ሁላችንም ዝም አልን ።

«በሉ መንገዳችንን እንቀጥል» ብሎን ወደ መንገድ ዘጠና አም ስት ተመልሰን በስሚዝ ፊልድ በኩል ወደ ምዕራብ አመራን ። ጃክ መኪናዋን ይነዳል ። ዲክም አጠገቡ ተቀምጦአል ። እኔና ሄሚ ከኋላ ወንበር ተዘናንተን ቁጭ ብለናል ። ጊዜው የደስታ ባለመሆኑ ንግግር በመኻላችን የለም ። በየጊዜው ወደ ኋላዬ ዞር እያልኩ መኪና የተከ ተለንና ያልተከተለን መሆኑን አያለሁ ። በዚህ መኪና ውስጥ ጉድ ሠርታው በመሸሽ ላይ የምትገኘውን ሴት ለመግደል የሚቋምጥ ሰው በሐሳቤ ይታየኛል ።

ወደ ምሽቱ አካባቢ በፋይተቪል በኩል ወደ ለምበርተን እመ ራን ። መጪውን በዓል ምክንያት በማድረግ ይመስላል መንገዱ ሁሉ በየቦታው ዕቃ ለመግዛት በሚጓዙ ሰዎች ተሞልቶአል ። በሰውና በመኪና ብዛት የተነሣ ይሄን ቦታ ለማለፍ ከሦስት ሰዓት በላይ ፈጀ ብን ። ፈርሞንት አካባቢ ስንደርስ ከዋናው መንገድ ወጣ ብለን ራታ ችንን ቶሎ በልተን እንደ ገና ዋናውን መንገድ ይዘን ጉዞአችንን ቀጠ ልን ። አሁን መኪናውን የሚነዳው ዲክ ሲሆን፣ ጃክ አጠገቡ ቁጭ ብሎ የመንገድ ካርታ ለማንበብ ይሞክራል ።

«ጃክ የራሌይ ጌጥ ሽያጭ እንዴት ነበር? ተሳካልህ?» አልኩት።

በጁ የያዘውን የመንገድ ካርታ አጣጥፎ ከፊት አስቀመጠና ወደኔ ፊቱን ከፈገግታ ጋር አዙሮ፣ «አይከፋም የተወሰኑ ሺ ብሮች አግኝቻለሁ » አለኝ ።

«ካርቶኑ ውስጥ ያለው ምንድ ነው? ምን ገዝተህ ነው ?» ስል መልሼ ጠየቅኩት ።

«ሚያሚ ስንደርስ አዲስ መታወቂያ ፣ ለብቻችን የሚወስደን አውሮፕላን ሁሉ መከራየት ያስፈልገናል።ይህን ለማድረግ ካለን ትላ ልቅ ጌጦች ውስጥ አንዱን ቆርጠን ጉቦ መስጠት አለብን ። ለነዚህ ወጭዎች ያሉን አነስተኛ ጌጦች በቂ አይደሉም ። ይሄን መኪና ከገ ዛን በኋላና ራሌይ ውስጥ ጌጥ ሸጠን ያለን ገንዘብ ከዐሥራ አምስት ሺ ብር አይበልጥም ። ይሄ ደግሞ በቂ አይደለም ። ስለዚህ ትላልቆቹን ጌጦች ለመቁረጥ ካስፈለገን ብዬ የመቁረጫ መሣሪያ ገዝቻለሁ ። ይሄም ዕቃ ጠንካራና ወፍራም ሽቦ መቁረጫ ፣ ማለስለሻ ሞረድ ፣ አነስተኛ የጌጣጌጥ ማቅለጫ የኤሌክትሪክ መሣሪያ ያጠቃለለ ነው ። በነዚህ ዕቃዎች ያለንን ጌጣጌጥ እያቀለጥንና በምንፈልገው መጠን ቆራርጠን በየትም አካባቢ መሸጥ እንችላለን ። ይህን ካደረግን በኋላ ፣ ከዚህ ቦታ የተሰረቀ ነው ብሎ የሚገምት አንድም ሰው የለም ።

በጌጣጌጥ ሥራ ውስጥ ደግሞ፣ ዘመናዊው የሌቦች ዘዴ የተሠረቀን ጌጥ እቅልጦ በሌላ ቅርፅ መሸጥ ነው ።»

በመደነቅ ተመለከትኩትና፣ «ጃክ ! ለመሆኑ በሕይወትህ ሙሉ ሕጋዊ የሆኑ ሥራዎችን ሠርተህ ታውቃለህ ?» አልኩት ።

«ይህን ያህል አይደለም» አለኝ ።

ይህን ካለኝ በኋላ በሕልም ዓለም ውስጥ እንዳለሁ ገመትኩት ።

ደቡብ ካሎሪና ስለ መድረሳችን እርግጠኛ አልነበርኩም ። ለካስ ደርሰን ኖሯል ። መንገዱ ቀጥ ያለና መጨረሻ ያለው አይመስልም ። ከር ቢሆን ዓለምን ሁለት ጊዜ ሊያጥፋት ይችላል ብዬ አሰብኩ።ዝም ብለን ብቻ መጓዝ ሆነ ። ቀን በሌሊት ሲተካ ከመንዝ በስተቀር ምንም ሥራ ሳንሠራ ሲያልፍ ማየት ብቻ ነው ። ከፊታችን የመኪና መብራቶች የተለያየ ቀለም እያፈለቁ ይታዩናል ። በአቅራቢያችንም የእርሻ መኪና ጩኸት ይሰማል ። የስፖርት መኪና የያዙ ጐረምሶች ከት ራፊክ ደንብ ውጭ እየነዱ ያልፋሉ ።

ሁሉንም እንቅስቃሴ እያየሁ ነው ። ግን በትክክል ምን በማድ ረግ ላይ እንደምገኝ አልገባኝም ። ቀደም ሲል በዘረፋው ተሳታፊና ተመልካች ነበርኩ ። አሁን ከዚህ ለየት ያለ የቀዘቀዘ ስሜት ይሰማኝ ጀመር ። ተሳታፊ ሳልሆን ተመልካች እንደ ሆንኩ ራሴን ቆጠርኩት።

ዲክ እየነዳ ጉዞአችንን ወደ ደቡብ ቀጠልን፤ ወደ ማሪዮን ሐይቅ አካባቢ ስንደርስ ፡

«ምን ያህል ነዳጅ አለን ?» ብሎ ጃክ፡ ዲክን ጠየቀው ።

«ወደ ሩብ ያህል የሚሆን» አለ ዲክ የነዳጅ መቆጣጠሪያውን እያመለከተ ።

«ወደ ሳቫና ለመድረስ ቸኩዬ ነበር ። አመቺ የሆነ ቦታ ስታገኝ አቁምና ዕንረፍ በጣም ደክሞኛል ። ጂኒስ አልደከመሽም ?» አለኝ ።

«በጣም ደክሞኛል ... ጃክ ! የትንኝ መድኃኒት የማያስፈልገው ንጽሕናው የተሟላ አልቤርጎ ብናገኝ ደስ ይለኛል ። በተለይ በእን ደዚህ ዓይነቱ አልቤርጎ ለአንድና ለሁለት ቀን ብናርፍ ችግር የሚ ያስከትል አይመስለኝም ። እንዲያውም ጉዞአችንን የሚከታተሉ ከሆነ አንድ ቦታ በመቆየታችን ምክንያት ግራ ልናጋባቸው እንችላለን ።»

«ትክክል ነሽ ፤ ጥሩ አልቤርጎ ፈልገን ትንሽ እንዝናናለን ። ሄሚ ! በሐሳቡ ትስማማለህ ?»

ሄሚ መልስ አልሰጠም ። ራሱን ትከሻዬ ላይ አሳርፎ እያን ኮራፋ ተኝቶአል ። ራሱን ትከሻዬ ላይ በማሳረፉ ቅር አላለኝም ። ሄሚ የሚገርም ሰው ነው ። አርቆ የሚያስብ አይሁን እንጂ ጉልበታም ነው ። ከዛ ዊቺ ወደ ተባለ ቦታ ታጠፍን ።

«ለምን ወደዚህ አዞርክ ?» ብሎ ጃክ ዲክን ጠየቀው ።

«ስሙ ደስ ስለ አለኝ ነው» ብሎ መለሰለት ። ጃክ ሣቅ አለና «በል እንደ ፈለክ» አለው ።

የከተማው ሰም ለዲክ ደስ ይበለው እንጂ ጥሩ አልነበረም ። ለማሽ ሰዓት ያህል አልቤርን ፍለጋ ዞርን ። አንድም ቦታ ማግኘት አልቻልንም ። አልቤርነምቹ በሙሉ ተይዘዋል ። እንደ ገና ወደ ዋናው መንገድ ገብተን ወደ ደቡብ ሪጅላንድ ሔድን ። እዚህም አል ቤርነው ሁሉ ተይዞአል ። እንደ ገና መንገዳችንን ቀጥለን ጀርጂያ ጠረፍ በሚገኘው ሐርዲሺሌ ደርሰን አለጋ አገኘን ።

የተከራየነው ክፍል ካለፉት በሙሉ በጣም የተሻለና ዘመናዊም ነው ። በየክፍሉ አነስተኛ ማቀዝቀዣ ያለ ሲሆን ፥ የመታጠቢያ ውና የአልጋው ንጽሕናም በጣም ጥሩ ነው ።

ምዝገባችንን አጠናቅቅንና ዕቃችንን ይዘን ወደ አራተኛው ፎቅ ወጣን፤ከጃክ ጋር አንድ ክፍል ይዘናል ። ዕቃችንን በየክፍሉ ካስቀመ ጥን በኋላ ጃክ ለሐያ ደቂቃ ያህል ወደ ውጭ ወጣ ። ወዴት እንደ ሔደ አላወቅሁም ። እሱ እስኪመለስ ሰውነቴን በሙቅ ውኃ ታጥቤ የመ ኝታ ቤቱን መብራት አጠፋሁና አልጋው ላይ በጀርባዬ ተኛቼ እዝናና ጀመር ። በእውነቱ ከሆነ ከመድከሜ የተነሣ መንቀሳቀስ አቅቶኛል ።

ጃክ ወደ ክፍሉ ገብቶ በሩን ሲዘጋና ልብሱን ሲያወልቅ ተሰ ማኝ ። ዐይኔን በመጠኑ ገርበብ አድርጌ ስመለከት፡ ሰውነቱን በመታ ጠብ ላይ መሆኑን አየሁ ። ሙሉ በሙሉ እንቅልፍ አልወሰደኝም ፥ ወይም ሙሉ በሙሉ አልነቃሁም ። የምተኙት ስለ መሆኔም እርግ ጠኛ አይደለሁም ፤ ማሰብም አልቻልኩም ።

ጃክ ታጥቦ ሲጨርስ አልጋዬ ውስጥ ገብቶ ተኛ ። ምንም አል ተቃወምኩም ፤ ያለኝን ሁሉ አድርጌያለሁ ፥ ሰውነቴ ዝም ብሎ እየ ታዘዘ እንጂ፡ እያወቅሁ ያደረኩት ምንም ነገር አልነበረም ።

ከእንቅልፌ ስነቃ ጃክ አራሱ አልጋ ላይ ተኝቶአል ። ከሕልም ዓለም ወጥቼ ማሰብ ጀምሬያለሁ ። ሰውነቴን ተጣጥቤ ልብሴን ስለ ብስ ሁሉ አልነቃም ። ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሔጄ የሄሚንና የዲክን ክፍል አንኳኳሁ ። መልስ የለም ።

ወደ ታች ወደ ቡና ቤት ስመርድ ቁርሳቸውን ሲበሉ አገኙዋቸው ። ወንበር ሳብኩና አጠገባቸው ተቀምጨ እነሱ የሚበሉትን አዝዤ በላሁ ። ምግባችንን በልተን እንደ ጨረስን ቡና መጠጣት ጀመርን ። ምስተኛውን ሲኒ ስንጠጣ ጃክ መጥቶ ተቀላቀለን ። እሱም የሚፈልገውን ቁርስ በላና ወደ ውጭ ወጥተን በእግራችን መሄደር ጀመርን ። ሁኔታችን ሁሉ ሰላማዊ ያመስል ጀመር ። በመሸሽ ላይ የምን ገኘው ሰላም ለማግኘት ስለ ሆነ ፡ የከተማው ሁኔታም ይህን ሊያበስር ልን የተዘጋጀ ይመስላል ።

ከተማው ብዙ ሱቆች ፡ ሰፊ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ፡ ሲኒማ ቤቶች ፡ ሆቴሎች ፡ መሥሪያ ቤቶችና የግል መኖሪያ ቤቶች የሞሉ በት ነው ።

እንደ መሰለኝ፡ከመሻል የተወሰኑ ቤቶች ከተሠሩ በኋላ እያደገና እየሰፋ የመጣ ከተማ ነው ። ምክንያቱም የቤቶቹ ቅርፅ ተመሰሳይ ሆኖ በየፎቆቹ መካከል ክፍት ቦታ አለ ። እንዲያውም የከተማው ቤት በሙሉ በአንድ መሐንዲስ የተሠራ ይመስል ተያይዘው የተሠሩ ፎቆች ቍጥር እነሰተኛ ነው ።

«በጣም ጥሩ ከተማ ነው ። ቀሪውን ሕይወታችንን እዚህ ከተማ ውስጥ መኖር እንችላለን ። የዕቃ መደብር ፡ ቡና ቤት ፡ ምግብ ቤት ፡ ፖስታ ቤት ፡ ሲኒማ ቤትና ነዳጅ ማደያ የመሳሰሉትን ይዤ ከተማ ከያዘ ፡ ከዚህ በላይ ምን ያስፈልገናል ?» አለ ዴክ ።

አዎ ! ዴክ እንዳለው ጥሩ ከተማ ነው ። ሆኖም ለትንሽ ጊዜ ላመዝናናት እንጂ ፡ ለረዥም ጊዜ መደበቂያነት በቂ አይደለም ።

አራታችንም ጥሩ የመዝናኛ ጊዜ አሳለፍን ። የእየሩ ጠባይም ተስማሚ ነው ። ቀን ቀን ፀሐያማ ሲሆን ፡ ማታም ይህን ያህል ብርድ የለውም ። ደስ ሲለን ሲኒማ ቤት እየሔድን እናመሻለን ። ጥሩ ምግብ ቤት እንመገባለን ። ከየሱቆቹ እየተዘዋወርን አንዳንድ ዕቃዎችንም እንገዛለን ። አንዳንዴም እየጠጣን ዘረፋው በደንብ እንዴት ሊታቀድ እንደ ቻለና እንደ ተሳካ እናወራለን ። ነለ ወደፊቱ ግን ምንም አና ነግም ።

ጃክ ከአልማዙቹ ውስጥ የተወሰኑትን መርጦ በገዛው መሣሪያ እንዴት መቁረጥ እንደ ሚቻል እያየን ። ከአብል ጋር የተያያዙትን በቀላሉ ማላቀቅ ይቻላል ። እሱማዙን ለመቁረጥ ግን ፡ በጣም አስቸጋሪ ሆኖ አገኘነው ። ሆኖም ከረዥም ሰዓት ልፋት በኋላ የተወሰኑትን ለመቁረጥ ቻለ ። ጃክ የመቁረጥ ተግባሩን ሲያከናውን ረጋ ብሎና ጥበብ በተሞላው ሁኔታ ነው ። አንዳንዴ በተደጋጋሚ በማጉደጉና

መልሶ በማቅናት ሲቆርጥ፣ አልፎ አልፎም በመዶሻው እየቀጠቀጠ የተወሰኑትን ቅርፃቸውን ለወጠ። ቆርጦና አስተካክሎ ሲጨርስ፣ «ደህና ነው ከበፊቱ ቅርፃቸውን በተቻለ መጠን ለመቀየር ተሞክሮ አለ። ለመሸጥ ምንም አያስቸግሩም፤ የተሰረቁ መሆናቸውን ማንም አያውቅም» አለን የተቆራረጡትን እየሰበሰበ።

ሁለቱን ቀን በሰላም ካሳለፍን በኋላ፣ ጃክ ጋዜጣ ይዞልን መጣ። በጋዜጣው ላይ በኒውዮርክ ከተማ በስተምሥራቅ ማንሐተን አካባቢ በሚገኝ አንድ ቤት ውስጥ ማንነቱ የማይታወቅ ሰው ተገድሎ መገኘቱን የሚገልጽ ዜና ተመለከትን። ቤቱ የዲክ ቤት ነው። ጋዜጣው ላይ ግን፣ ቤቱ የዲክ መሆኑ አልተገለጸም። ሆኖም ፖሊሶች የሚቹንም ሆነ የቤቱን ባለቤት ለማወቅ ከትጉል ላይ መሆናቸውን አስፍሮአል።

«አሁን እንግዲህ ስምህን፣ እንደዚህም በጠቅላላው ስለ አቋምህ ወዘተ ፎቶግራፍህንም በትነውታል ማለት ነው» አለ ጃክ፣ ዲክን አፍጥጦ እየተመለከተ።

«እና? ታዲያ ምን ይሁን?» አለ ዲክ።

ከሰዓት በኋላ ምሳችንን እንደ በላን ጉዞአችንን መቀጠል እንዳለብን ወሰንን። ጥቁሩ ጃክ በየጊዜው ከኛ የሚለይበት ምክንያት የገባኝ አሁን ነው። ለካስ የመግቢያና የመውጫ መንገዳችንን በየ ጊዜው ይመለከት ኖሮአል! መኪናችንን አልቤርጎ በር ከማቆም ይልቅ በከተማው መሃል ከሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ መተው አስተማማኝ እንደ ሆነ አምኖአል።

መኪናዋን አስተማማኝ ቦታ ነው ያቆምናት። መኪናዋን ለይተው ወሰዱ የቆመችበትን ቦታ ቢያዩ እንኳን፣ እኛ የት እንዳለን መረዳት አይችሉም። ሁል ጊዜም ቢሆን፣ ወደ መኪናዋ ከመሔዳችን በፊት የሚጠባበቁን ሰው መኖር አለመኖሩን መጀመሪያ ማረጋገጥ አለብን ብሎ ጃክ አስረድቶናል።

ጃክ የሚያቀርበው ሐሳብ ሁሉ ትክክል መሆኑን እንድናረጋግጥ ጥለት ስለ ሚፈልግ፤ ሐሳቡ ትክክል መሆኑን እኛም ገልጸንለታል። እኔና ዲክም ሰውየው እንዲታመን እንደ ሚፈልግ ቀደም ሲል ተረድተናል።

ወደ ምሽቱ አካባቢ፣ አቅራቢያችን ከሚገኘው ምግብ ቤት እራታችንን በላንና ዕቃዎቻችንን ለማዘጋጀት ወደ ክፍላችን ሔድን። ጌጦቻችንን በሁለት ቦርሳዎች፣ ልብሶችንን ደግሞ በሦስት ሻንጣዎች እደረግናቸው። ጊዜው ወደ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተጠግቶአል።

ጃክ ከፈገግታ ጋር፡ «እንግዲህ ጉዞአችንን እንጀምር ። መጀመሪያ እኔ ልውጣና አካባቢው ሰላም መሆኑን አረጋግጬ መኪናዋን ወደዚህ አምጥቼ ዕቃችንን እንጭናለን ። መኪናዋን ይዤ አልቤርጎ ስደርስ ዕቃውን ይዛችሁ ውረዱ ፤ ከዐሥር ደቂቃ በላይ አልቆይም » ብሎን ወጣ ።

አነጋገሩስ ጥሩ ነበረ። ግን ዐሥር ደቂቃ ሳይሞላው በሁለት ደቂቃ ውስጥ ተመለሰና ፡ «ችግር መጣ... ይሄ የውሻ ልጅ !» አለ ።

«ጃክ ! ምን...ድን... ነው ?» አልኩት ተደናግጬ ።

የውሸት ፈገግታ አሳየኝና ... «ወሽማሽን አየሁት ። ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ሆኖ አልቤርጎ ያከራየንን ሰው ሲያነጋግሩ አየሁዋቸው » አለኝ ።

«እዚህ መሆናችንን እንዴት ሊያውቅ ቻለ ?» ብዬ ጮኽኩ ።

«እኔ ምን ዐውቄ ! ይሄ የሴት ልጅ ! ሁላችንም ካልሞትን የሚለቀን አልመሰለኝም» አለ ጃክ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍርሃትና ጭንቀት እየታየበት ።

ዝም ብለን መተያየት ብቻ ሆነ ። የሁላችንም ፊት በንዴት ከስሎአል ። «እክፍላችን ድረስ ይመጡ ይሆን እንዴ ?» አለ ሄሚ ።

«አይመስለኝም ! በአልቤርጎ ውስጥ ረብሻ እንዲነሣ አይፈልጉም ። ዙሪያውን ከበው ስንወጣ አንድ ባንድ ሊለቅሙን የሚጠብቁ መሰለኝ ፡ ሁኔታቸውን ለማወቅ ቀላል ዘዴ አለ...»

ስልኩን አንሥቶ ደወለና አልጋ አከራዩን አነጋገረ ።

«ሳም ሞሪሰን ነኝ ። የፈለገኝ ሰው ነበር? አሃ ጥሩ ነው ። ውጭ እንጠብቃለን ነው ያሉት? ጥሩ ! እመጣለሁ ። አመሰግናለሁ » ብሎ ስልኩን ዘጋና «ልክ እንደ ገመትኩት ውጭ ተደርድረው ይጠብቁናል » አለ ጃክ ።

«ሦስት ብቻ ናቸው ?» አለ ሄሚ ።

«ያየሁት እነሱን ብቻ ነው ። ምናልባት ሌላም ሰው ሊኖር ይችላል ። ባይኖር እንኳ አንቶኒዮ ሮሲ ይዤን ጊዜ ስልክ ደውሎ ብዙ ሰው ጠርቶአል ።»

«ፖሊሶችንና የእሳት አደጋዎችን እንደ ገና መጥራት አንችልም ?» ብዬ ጠየኩ ።

«ሁለት ጊዜ አይሠራም ። ለዚህም ዝግጁ ሆነው ይጠብቁናል ። ከግርግሩ እስክንወጣ ዝም ብለው ጠብቀው በቀላሉ ይይዙናል ። ቦታው በጣም ሰፊ ስለ ሆነ እንደ ጌምስኮክ አመቺ አይደለም» አለኝ ።

ጃክ እክፍሉ ውስጥ ይንኮራደዳል ፥ የኛም ሀይን እሱ ላይ በርፎ አል ። መፍራቱ ኣይታወቀኝም ፤ እንዲያውም አልፈራሁም ። ለማ ምለጥ ተሰፋ ያለን ይመስለኛል ፥ ሁሉም እንደኔ የገመቱ መሰለኝ ።

«መጣሪያችንን ይዘን እየተኮሰን ብንወጣስ፣ ማሉቱ በቂ መሣሪያ አለን ። ምናልባት ከመኻከላችን አንድ ወይም ሁለት ሰው ማምለጥ ይችላል » አሰ ሄሚ ።

«ይሄ ራስን መግደል ማለት ነው ። ይህን አልቤርን ከመከራ የታችን በፊት የመውጫ በሮችን አይቻቸዋለሁ ። ማታ ማታ መውጫዎቹ ላይ ትላልቅ መብራት ይበራባቸዋል ።እነሱ ከጨለማው በኩል ሆነው እኛ እየተኮሰን ስንወጣ በቀላሉ ሊያስገቡን ይችላሉ » አሰ ጃክ ።

እንደ ገና ጸጥታ ሆነ ።

ጃክ መንኮራደዱን አቆመና ዲክ ወደ ተቀመጠበት ወንበር ሔዶ ቁልቁል ዲክን እየተመለከተ ፥ «እሺ ! የኮሌጅ ተማሪ ! ጥሩ ጭን ቅላት አለህ ፥ ይሄን ዐውቃለሁ ። ከዚህ በሰላም ለመውጣት ምን ማድረግ ነው ያለብን ?» አሰው ።

«በጓሮ በር በኩል ብንሞክር ?» አለ ዲክ ቀስ ብሎ ።

«ዙሪያውን ከበውናል ።»

«በምድር ቤቱስ? ወደ ምድር ቤት የሚወስዱት ደረጃዎች የማ ገኙት በጓሮ በር በኩል ነው ። የጀኒን ልብሶች ለብሰን ተመሳስለን ለመውጣት ብንችል» አለና ወዲያውኑ... «አይ ተዉት ፥ ይሄም አይ ሠራም » ሲል ራሱን አወዛወዘ ።

«ልክ ነህ አያዋጣም ! ምናልባት እኔ በሌላ ለመውጣት ስሞ ክር ፥ ምስታችሁ በሌላ በር ለማምለጥ ብትሞክሩ ፥ ሁሉም እኔ ላይ ትኩረት ሊጥሉ ስለሚችሉ...» አለን ጃክ ።

«በእንደዚህ ዓይነቱ ሙያ በጣም የሠለጠኑ ናቸው አይደል ?» ሲል ዲክ ጥያቄ አቀረበ ።

«አዎ ! በጣም የሠለጠኑ ናቸው» አለ ጃክ በምሬት ።

«ይህ ከሆነ ፖሊሶችን ጠርተን መጥተው እንዲይዙን ማድረግና እጃችንን መስጠት ነው» አሰ ዲክ ።

«እና? በግድያ ወንጀልና በዘረፋ ተከሰን እስክንሞት ድረስ እስር ቤት መግባትን ይህ እንዲሆን ትፈልጋለህ?»

«እኔ በፍጹሉ አልፈልግም» አልኩኝ ጣልቃ ገብቼ ።

«እስቲ ቆይ !» አለና ዲክ ግምባሩን አኰሳተረ ። ሁላችንም በጸጥታ ተመለከትነው ። ከዚያም በሁለት እጁ ዐይኑን ሲያሻሽ ቆየና ፡ «ይቅውላችሁ ፡ ይሄ ከሐቅ ጋር የተያያዘ ነው ። ወደ ታች ወርደን ወደ ውጭ መውጣት አልቻልንም ፡ አይደል? ታዲያ ወደ ታች ካል ቻልን ለምን ወደ ላይ ወደ ጣሪያው አንሞክርም ?» አለን ።

ጃክ በፍጥነት ዲክ አጠገብ በርከክ ብሎ ጉንፏሙን ሳም አደረገና፡ «ጥሩ ጭንቅላት እንዳለህ በደምብ ዐውቃለሁ ። በጣሪያው በኩል መሞከሩ ያዋጣል ። ዲክ አብረን ሔደን እንመልከት ። ሄሚ ከጀኒ ጋር እዚህ ቆዩ ፤ በሩን ለማንም አትክፈቱ፤ ስንወጣ ቆልፉት ። እኛም ተመልሰን በሩን ስናንኳኳ የምትከፍቱት ፡ ሦስት ጊዜ ቶሎ ቶሎ ፡ ከዚያ ቆየት ብሎ ሁለት ጊዜ ሳንኳኳ ብቻ ይሆናል » ብሎት ተያይዘው ወጡ ።

ከሔዱ ዐሥራ አምስት ደቂቃ ሆናቸው ። እኔና ሄሚ ቁጭ ብለን ሲጋራ በላይ በላዩ እናጨሳለን ። የመንገድ ልብሳችንን ለብሰናል ። ዕቃዎቻችን ሁሉ ተዘጋጅተዋል ፤ ሄሚ አንዱን ሻንጣ ከፍቶ ተጨማሪ ሽጉጥ ጃኬት ኪሱ ውስጥ ከተተ ። እኔም መውሰድ ይኑርበኝ አይኑርብኝ እላወቅሁም ። ስለዚህ ተውኩት ። ስለ ጀኒ ሹን ማሰብ ጀመርኩ ።

ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ የጃክን ምስጢራዊ የበር ማንኳኳት ሰማን። ሦስት ጊዜ በፍጥነት ኪ. ኳ. ኳ አለና ጥቂት ዐረፍ እንደ ማለት ብሎ ሁለት ጊዜ ኳ...ኳ ሲል ሄሚ አንድ እጁን ከኪሱ ሳያወጣ በሩን ከለላ አድርጎ ከፈተላቸውና ገቡ ። የሁለቱንም ፊት ተመለከትኩት ፤ የደስታ ወይም የጭንቀት ገጽታ አይታይባቸውም ።

«መቼም ... እስቲ ዕድላችንን እንሞክር » አለ ጃክ ።

«ምን ማለትህ ነው? በጣም ጥሩ ዕድል ነው » አለ ዲክ ።

«በጣም ጥሩ ነው የሚለውን እንኳን ተዉው ! እንዲያው ዕድላችንን እንሞክር ። ሁኔታው እንደዚህ ነው ፡ ለአደጋ ጊዜ መውጫ ተብሎ በተዘጋጀው በር በኩል የብረት መሰላሉን ተጠቅመን ወደ ጣሪያው እንወጣለን ። ይህ በጣም ቀላል ነው ። ከዚህኛው ሕንፃ ቀጥሎ የሚገኘው ሕንፃ ጥቂት ከፍ የሚል ፡ ምናልባትም ከሦስት ጫማ የማይበልጥ ርዝመት ያለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት አለ ።

ዲክ! ከሦስት ጫማ ይበልጣል?» ሲል ጃክ ገለጻውን አቋርጦ ጠየቀው ።

«ወደዚያው ገደማ ነው፤ከሦስት ጫማ የሚበልጥ አይመስለኝም»

«ጥሩ ! በሁለቱ ሕንፃዎች መካከል ክፍት ቦታ አለ ። ከሥር የሚታይ ምንም ነገር የለም ። እኔና ዲክ ወደ መሥሪያ ቤቱ ዘለን አይተነዋል ፤ ምንም አያሠጋም ። እንግዲህ አሁን መሥሪያ ቤቱ ሕንፃ ላይ ስንዘል ማንም ሰው ሳይሰማን ደረስን እንበል ። ችግሩ እንግዲህ እዚህ ላይ ነው። ሲኒማ ቤቱ ከመሥሪያ ቤቱ ሕንፃ ዝቅ ያለ ሆኖ በመ ኻከላቸው የአምስት ወይም የስድስት ጫማ ርቀት አላቸው ። ስለዚህ በዚህኛው ሕንፃ ያለውን ርቀት ወደ ጐን ብቻ ሳይሆን ወደ ታችም መዝለል ይኖርብናል ። ገባችሁ? እዚያ ከደረስን በኋላ መመለሻ የለም ፤ በርግጥ ይህን ቦታ ዘለን አልሞከርነውም ።»

በመገረም መልክ ፥ «ከሲኒማ ቤቱ ጣሪያ አለፍ ብሎ ወደ ታች የሚያስወርድ መሰላል ባለበት ቦታ ላይ በር ኦይተናል እኮ ! ወደ ኋላ መመለስ ባንችል በዛ በኩል ወደ ሲኒማ ቤቱ መውረድ እንችላለን» አለ ዲክ ጣልቃ ገብቶ ።

ጃክ የንዴት ፈገግታውን እየሳየ ፥ «ይሄን ሁሉ ዕቃ ተሸክመን ነው በሲኒማ ቤት ውስጥ የምንሔደው ?» አለ ።

እኔም በዚያን ጊዜ ጌጣጌጥና ልብስ የሞላንባቸውን ሻንጣዎች ተመለከትኩና ፥ «እና ታዲያ ይሄን ሁሉ ዕቃ ይዘን ልንሔድ ነው ?» አልኩት ግራ በመጋባት ።

«ጥለነው እንሔዳለን ብለሽ ታስቢያለሽ ?» አለኝ ።

«ዕቃዎቻችንን ተሸክመን ወደ ጣሪያው ከሔድን ፤ በኋላ መጨረሻ በኩል ወደ ጣሪያው የሚወስደውን ደረጃ እንወጣለን ። በኮሪደሩ ፥ በሊ ፍት የማንወጣው ምናልባት ሰው እንዳያጋጥመን በመሥጋት ነው » አለ ጃክ ።

ከዚያም ጃክ ከፊት ፥ ቀጥሎ እኔ ፥ ዲክና ሄሚ ከኋላ ተከታተ ልን ። ሄሚ ሁለቱን ሻንጣ በአንድ እጁ ፥ በሌላው እጅ ደግሞ ሽን ጡን አውጥቶ ይዞአል ። ወደ ጣሪያው መውጫ ስንደርስ ፥ ጃክ ፊቱን ወደ እኔ አዙሮ፣ «በሩ የሚከፈተው ወደ ውጭ ነው ። ለሌባ እንዳይመች የሚቆለፈው ግን ከውስጥ ነው ። በጣም አሪፎች ናቸው ። እኔና ዲክ ለመመልከት ስንመጣ እንዳይዘጋ ቁልፉን ሰብረነዋል ። ክፍቱንም የተውነው ፥ ምናልባት ይህ መንገዳችን እንዳሰብነው የማይሳካልን ከሆነ ተመልሰን በዚሁ በር ስለ ምንገባ ነው » አለኝ ።

ጣሪያው ላይ ወጣን ። ብርዱ ኃይለኛ ነው ። ሰማዩ ጥርት ብሎ ፣ ከዋክብት ልቅም ብለው ይታዩ እንጂ ጨረቃ ግን አልወጣችም ። ጣሪያው ላይ የተዘረጉት ቧንቧዎች እንዳያደናቅፉን ተጠንቅቀን ጃክ እየመራን ወደ ጣሪያው መጨረሻ ሔድን ። ቀጥሎ የሚገኘውን ሕንፃ ተመለከትኩት ። «እንደ እኔ ከሆነ በነዚህ ሕንፃዎች መካከል ያለው ርቀት ከሦስት ጫማ በላይ ነው » አልኩኝ ።

«አይደለም ፤ በቀላሉ የሚዘለል ርቀት ነው ። ዲክ ! ምን ያህል ቀላል እንደ ሆነ ዘለህ ለጂኒ አሳያት» አለው ጃክ ።

ዲክ ቦርሳዎቹን መሬት ላይ ቁጭ አደረገና የኮቱን ቁልፍ በመ ፍታት ወደ ኋላ መለስ ብሎ ወደ ፊት ተንደረደረና ዘለለ ። በአየር ላይ ሆኖ ኮቱ እንደ ጃንጥላ ተወጠረ ። እዚያኛው ጣሪያ ላይ ሲያርፍ ቶሎ መቆም አልቻለም ። ሁለት እርምጃ ወደ ፊት ከተንደረደረ በኋላ ቆመና ፊቱን ወደ እኛ አዙሮ በፈገግታ እያየኝ ፣ «አየሽ? ምን ያህል ቀላል እንደ ሆነ ። በይ ያንቺ ተራ ነው ዝለይ» ከጣሪያው ጫፍ ወደ ኋላዬ አፈገፈግሁ ፤ በመሻከሉ ያለው ርቀት ከፍተኛ ሆኖ ታየኝ ።

«ወደ ታች አትመልከቺ ! ዝም ብለሽ ሮጠሽ ዝለይ» አለኝ ።

«መዝለል አይሆንልኝም ።»

«ትችያለሽ ። በጣም ቀላል ነው ። ምን ያህል ጠንካራ እንደ ሆንሽ መጽሐፍሽን አንብቢዋለሁኝ ፤ ትችያለሽ » አለኝ ጃክ ።

«አልችልም !»

«ዝለይ ነው የምልሽ ! ጭቃ ቦታ ቢሆን ኑሮ ይሽኔ ትዘሺ ነበር» አለኝ ንዴት እየያዘው ።

«ጭቃ ያለበት ቦታ ይሄን ያህል አይርቅም» አልኩት ።

«ደደብ ትዘሊያለሽ ዝለይ ! አለዚያ ሄሚ ተሸክሞ እንዲወረ ውርሽ አደርጋለሁ ።»

ግልቀስ ጀመርኩ ፤ «እውነቴን ነው የምልህ መጽሐፌ ውስጥ ያልጻፍኩት ነገር ኦለ ። ከፍተኛ ቦታዎችን በጣም እፈራለሁ ፤ ወደ ታች ማየት አልፈልግም ፤ እታች ምን እንደ ሚጠብቀኝ ዐውቃለሁ ። መዝለል አልችልም ፤ እዚህ ተዉኝና እናንተ ሒዱ ፤ ግዴለም እዚህ ሆኜ ዕድሌን ልጠብቅ ።»

ብስጭት ብሎ «የወሻ ልጅ !» አለኝና እጆቹን ወገቡ ላይ አሳ ርፎ በረዥሙ ተንፍሶ ዝም ብሎ ቆመ ። ሁላችንም ምንም ሳንነጋገር

ዝም ብለን ቆየን ። እኔ ከፍርሃቴ የተነሣ ሰውነቴ ሁሉ መንዘፍዘፍ ጀመረ ።

«ምነው፣ ምን ነካችሁ፣ ዝለሉ እንጂ» አለ ዲክ እዛኛው ሕንፃ ላይ ሆኖ በቀስታ ድምፅ ።

«ሂሚ ዕቃዎቹን ወደ ዲክ ወርውራቸው » አለ ጃክ ።

በዚህ ጊዜ ከጣሪያው ጫፍ በተቻለ መጠን ወደ ኋላዬ ራቅ ብዬ ቆምኩ ። የሰውነቴ መንቀጥቀጥ አሁንም አልተወኝም ። ሂሚ ዕቃዎቹን ሁሉ ለዲክ ወርውሮ ጨረሰ ። ጌጣጌጡና ዕቃዎቻችን ከዲክ ጋር እዛኛው ሕንፃ ላይ ሆነው የቀረነው እኛ ሦስታችን ብቻ ነን ።

«ማዶለም ለኔ አታስቡ እናንተ ሒዱ» አልኳቸው ፣ ትተዉኝ ይሒዱ ብዬ ሙሉ በሙሉ ተማምኜ ።

«አሁን አፍሽን ዝጊ ! ሂሚ ያንን በር አስኪ እንሞክረው !» ብለው ሲሒዱ ተከተልኳቸው ። በሩን ተመለከቱት ። በሩ ሁለት አንኾ ያህል ውፍረት ያለው የብረት መዝጊያ ነው ። ጃክ ማጠፊያው ያለበትን ቦታ በእጁ ነክቶ አየውና «ሂሚ ! ከማጠፊያው ለመገንጠል የምትችል ይመስልሃል ?» አለው ።

ሂሚ በሩን ሙሉ በሙሉ ከፈተና ማጠፊያዎቹን በማየት ፣ «ከባድ ሳይሆን አይቀርም ፣ ግን ኃይል ልሞክረው» ብሎ ሁለት እጁን አጣምሮ በሩን ያዘና ወደ ላይ ወደ ታች ይነቀንቀው ጀመር ። የላይኛው ማጠፊያ መንጫጫት ጀመረ እንጂ ፣ በሩ ከማጠፊያው መሰበር አልቻለም ። «ቆይ ልርዳህ» አለና ጃክ እጁን ሂሚ እጅ ውስጥ በማስገባት ኃይላቸውን አስተባብረው በሩን ለመገንጠል ያወዛውዙት ጀመር ። በከዋክብቱ ብርሃን ፊታቸውን ላይ ጥረሳቸውን ነክሰው ሥራቸው ተግተርትሮ ይለፋሉ ።

ትንሽ እንደ ቆዩ የብረት ሲጢጥታ ተሰማኝ ፣ የላይኛው ማጠፊያ ከሲሚንቶው ሲላቀቅ ሁለቱም ወደ ኋላ ለመውደቅ ተንገዳገዱ ። አሁን በሩ የላይኛው ማጠፊያ ለቆ የቀረው ሁለተኛው ማጠፊያ ብቻ ነው ። ሂሚ እንደ ግና ለብቻው የቀረውን ማጠፊያ ለመገንጠል ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ ይወዘውዘው ጀመር ። ከትንሽ ውዝወዛ በኋላ የተለመደው ሲጢጥታ ተሰምቶ በሩ ከሲሚንቶ ተላቀቀ ። የተገነጠለውን በር ሂሚ ተሸክሞ ዲክ ወደ አለበት ሕንፃ ሲወስደው እኔና ጃክ ተከተልነው ።

«ሂሚ ቶሎ ብለህ አስተኛው፤ በሩ ሲገነጠል እታች ያለው አልጋ አከራይ ሳይቀር ሰምቶት ይሆናል» አለ ጃክ በችኮላ አነጋገር ።

ሄሚ በሩን ከአልበርሪው ጣሪያ ላይ በቁመቱ አሳረፈና ዲክ ወደ አለበት ሕንፃ ቀስ እያለ ያስተኛው ጀመር ። ዲክ ያለ ምንም ፍርሃት በርከክ ብሎ የበሩን ጫፍ ለመያዝ እጁን ዘርግቶ ተቀ በለውና ከሕንፃው ጣሪያ ላይ አሳረፈው ። እንደ ገና ቀስ ብለው በጠፍጣፋው እንዲቀመጥ አደረጉት ። በሩ ከሰባት ጫማ በላይ ርዝማኔ አለው ። በያንብ ሲያስተኙት በሕንፃው መካከል የነበረው ከፍት ቦታ ሙሉ በሙሉ ተሸፈነ ። እንዲያውም በሁለቱም በኩል ጉርፍ አለው ።

«የብረት ድልድይ ተሠራ ማለት ነው ፤ እጄን ያዥና ዐይንሽን ጨፍነሽ ተከተይኝ ። ይህን ካላደረግሽ ገፍትሬ ወደ መሬት እጥል ሻለሁ» አለኝ ጃክ ።

እንዳለኝ አደረግሁ ። ዐይኔን ጨፍኜ በሩ ላይ ወጣሁ፤ መንገዳገድ ሞከረኝ። ግን በእጁ ጠበቅ አድርጎ ይዞኛል ። ከበሩ በላይ የምጓዘው ጉዞ በጣም ረዘመብኝ። ከሙቶ ዓመት በኋላ ይመስለኛል፣ «ዐይንሽን ግለጭ» ያለኝ ። ዐይኔን ስገልጥ በመሥሪያ ቤቱ ጣሪያ ላይ ደርሼ ዲክ እጄን ይዞ ቆሞአል ። ሄሚ በበሩ ላይ በፍጥነት ተሻገረ ። እኔና ዲክ የተወሰነውን ዕቃ ስንሸከም፣ ዲክ ሄሚን እየረዳው በሩን ወደ መሥሪያ ቤቱ ሕንፃ ገፍትተው ካቆሙት በኋላ ፣ ሄሚ በጭንቅላቱ ተሸክሞት ወደ ሲኒማው ቤት ጣሪያ ሔድን ። እንደ መጀመሪያው ዲክ አሁንም ዘለለ ። የአሁኑ ዝላይ እንደ በፊቱ ቀላል አልነበረም ። ዲክ ዘሎ ጣሪያው ላይ ሲያርፍ ወደቀና ትንሽ ተንከባሎ ጉልበቱን እያሻሸ ቆመ ። ሦስቱም በሩን ተጋግዘው በሕንፃዎች መካከል አጋደሙት ። የበሩ ርዝመት ሙሉ በሙሉ በመ'ካል የነበረውን ርቀት ገጠመው ።የሲኒማ ቤቱ በማ ጠሩ ምክንያት አሁን የተዘረጋው ድልድይ ወደ ቁልቁል ነው ። እኔም እንደ ገና ዐይኔን ጨፍጌና የጃክን ወገብ ግጥም አድርጌ ይዤ ቀስ ብሎ እየመራኝ ሲኒማ ቤቱ ጣሪያ ላይ ዐረፍኩ ። ሄሚም በፍጥነት ተሻገረ ።

«በሩን እዚህ ልተወው ወይስ እንሥቼ ልጣለው ?» አለ ሄሚ ።

ጃክ ወደ በሩ ተመለከተና ፣ «ከጣልከውማ በአካባቢው ያለ ሰው ሁሉ ይሰማል ። እዚህ ተወው ፣ ከዚህ በኋላ ምንም ጥቅም የለውም ። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሕንፃም በጣም ዝቅተኛ ስለ ሆነ፣ መገለልም ሆነ በበሩ መጠቀም አንችልም » አለው ።

ከሲኒማ ቤቱ ጣሪያ ወደ ታች የሚያስወርድ መሰላል ወደ አለ በት ሔድን ። ልክ እንደ መጀመሪያው ይሄኛውም የብረት መዝጊያ አለው ። በሩ ግን፣ ከውጭ በቁልፍ ተቆልፎአል ። ጃክ ክብሪት ጭሮ ወደ በሩ ተጠግቶ ተመለከተና፣ «መግባት እንኳን እንችላለን ። ደረጃ ውንም ለመውረድ ግፋ ቢል ከሠላሳ ደቂቃ በላይ አይፈጅም ። ግን

ይሄን ያህል ሰዓት ማቃጠል የለብንም ። ይሄ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ስለ ሆነ፡ አራታችንም ይሄን ሁሉ ዕቃ ተሸክመን በአዳራሹ ውስጥ መውጣቱ አደገኛ ነው ። ስለዚህ የእሳት አደጋ በተነሣ ጊዜ ለማም ለጫ የተዘጋጀ የብረት ደረጃ ስለ ሚኖር የት እንዳለ እንፈልገው » አለን ።

ወንዶቹ ከሕንፃው አካል ውጭ ተያይዞ የሚገኘውን ደረጃ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ፡ እኔ በተቻለ መጠን ከጣሪያው ጫፍ ርቄ መኻል ላይ በመቆም እመለከት ነበር ። ሄሚ ደረጃውን አገኘውና ጃክን ጠራው ። ደረጃው ጠመዝማዛና ሲረግጡት ወዲያ ወዲህ ቢልም ከሕንፃው ግድግዳ ጋር የተያያዘና ብረት ስለ ሆነ፡ ለመውረድ የሚያ ስፈራ አይደለም ።

ጃክ የተወሰኑ ደረጃዎችን ወደ ታች ወርዶ ተመለከተና ተመልሶ ወደኛ በመምጣት፡ «ደህና ነው ። የመጨረሻው ደረጃ ሲያረስ ትንሽ መዝለል ያስፈልጋል ፤ ሄሚ ቅደም ! ከዛ ጂኒ ፡ እኔ እቀጥላለሁ ፤ ዴክ ደግሞ ትኩተለኛለህ ። ሁላችሁም ዕቃዎቹን ተሸከሙ» አለ ።

በዚህ መልክ መውረድ ጀመርን ። እኔ አንድ ቦርሳና በትከሻዬ ትንሽ ሻንጣ አንጠልጥዬ በአንድ እጄ የደረጃውን ብረት ጠበቅ አድ ርጌ ይዤ ጉልበቱ እየተንቀጠቀጠ፡ እያንዳንዱን ደረጃ ቀስ ብዬ ስወ ርድ ፡ ሄሚ መጨረሻው ደረጃ ላይ ኖሮ ዘሎ ሲወርድ ደረጃው ተወዛ ወዘ ። ጠበቅ አድርጌ ይዤ ስለ ነበር አልወደቅሁም ። ሄሚ መሬት እንደ ደረሰ ሻንጣዎቹን መሬት አስቀምጦ ደረጃውን በሁለት እጁ ጠበቅ አድርጎ ይዞልን ቶሎ ቶሎ ብለን ወረድን ።

ትንፋሻችንን ሰብሰበንና ወደ ፊት ትንሽ ራመድ እንዳልን በሁ ለቱ ሕንፃ መካከል ባለው ክፍት ቦታ ደረስን ። የቦታው ስፋት ምናል ባት ከአምስት ጫማ በላይ አይሆንም። ሁለት ሰዎች ገመን ለገመን መሔድ የሚችሉበት ስፋት ይኑረው እንጂ፡ለመኪና በጣም ጠባብ ነው። በየሕ ንፃዎቹ ጫፍ የተንጠለጠሉት መብራቶች መንገዱን በደንብ ስለሚያ ሳዩ ለመጓዝ ችግር የለውም ።

ጃክ ወዲያና ወዲህ ሬቱን እያዞረ አካባቢውን ተመለከተና ፡ «የመኪና ማቆሚያ ሥፍራ ከዚህ በጣም ቅርብ ነው ። በዚያ በኩል ሒዱ» አለን በሹክሹክታ ፡ አቅጣጫውን በአገጩ እያሳየን ።

ሄሚ ሁለቱን ሻንጣ በአንድ እጁ ይዞ እየመራን መንገዳችንን ቀጠልን ። ከኋላ ሁላችንም እንደ ሰለፈኛ መስመር ገብተን እንከተ ላለን ። ማምለጣችን መሆኑን ማመን አቃተኝ ። ከአንቶኒዮ ሮሲና ከአጃቢዎቹ ማምለጥ የመሰለ ምን ትልቅ ነገር አለ? እውነት ከሆነ ጥሩ ነው ።

ሄሚ መውጫው አካባቢ ሲደርስ ሐያ ጫማ ርቀት ሲቀረው፡በሚ ታየው የመንገድ መብራት መኻል አንድ ሰው ብቅ አለ ። እኛን እያየ ዝም ብሎ ቆሞአል ። ሳየው ረዥምና ሰውነቱ ደልደል ያለ ወፍራም ሹራብ የለበሰ ሲሆን ፣ ባርኔጣ በማድረጉ ምክንያት ፊቱን መለየት አልቻልኩም ። ሽጉጥ መያዙን ግን አረጋግጫለሁ ።

ወዲያው ሄሚ «አ !» ሲል የሰማሁት መሰለኝ። መንገዱን ግን እንደ ቀጠለ ነው። ይህ እየተፈጸመ ነው ብሎ መጸፍ ብዙ ጊዜ ይፈጃል ።ድር ጊቱ ሲፈጸም ግን ደቂቃም አይፈጅም ። ሄሚ አንዱን ሻንጣ ጥሎ ፣ ሌላውን ሻንጣ በቁመቱ በመያዝ ደረቱን ከልሎበት ወደ ሰውዬው በፍጥነት መራመድ ጀመረ ። እንደገና «አ !» ሲል ሰማሁት ። ሁሉም ነገር ፈጣን ሆነብኝ ። ሰውየው ጋ ሲደርስ ትንሽ ሲቀረው ቦርሳውን ወደ ፊት ወረወረውና አጯን ከኪሱ አውጥቶ ሲዘረጋው የተኩስ ድምፅ ሰማሁ ። ያሁኑ ድምፅ ከፍተኛ ነው ፣ የተተኮሰው ጥይት ሄሚን ይም ታው ወይም በሻንጣው ውስጥ ይለፍ ማወቅ አልቻልኩም ። ዐወቅሁ ዐላወቅሁ ምን ለውጥ ያመጣል? ሄሚ መመታቱን ዐወቅሁ ። ትንሽ ቆም ካለ በኋላ ወደ ፊት ወደቀና እየተንከባለለ ከኪሱ ሽጉጥ ለማው ጣት ይሞክራል ። ረዥሙ ሰውዬ ግን ፣ ሄሚ የወረወረው ሻንጣ ላይ አንድ እግሩን አሣርፎ ቆሞአል ። በተከታታይ የተተኮሰ ሁለት የጥይት ድምፅ ሰማሁ ። .

ወዲያው ሄሚ ከወደቀበት ተነሥቶ ሰውየውን አነቀውና ሁለቱም መሬት ወደቁ ። ሰውየው ሄሚን ለማስለቀቅ ይሞክራል። ጃክ በትከሻው ገጨኝና ፣«በዛ በኩል መኪናዋ ጋ ሒዱ! ሩጡ!» ብሎ ጮኸብን ።

እኔና ዲክ የያዝነው ቦርሳ ከጉልበታችን ጋር እየተጋጨ ሮጥን ። እንዴት እንደ ሆነ አላውቅም እንባዬ ይወርዳል ፣ ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ ስመለከት ጃክ የያዘውን ሻንጣ መሬት ጥሎ ሽጉጡን አውጥቶ በመ ያዝ ሄሚና ሰውየው ወደ ሚታገሉበት ሮጠና ጉንበስ ብሎ ወደ ሰው የው ጆሮ ሽጉጡን አስጠግቶ ተኮሰው ። በዚህ ጊዜ የተሰማኝ ድምፅ ደጉ የሚል ሲሆን ፣ በመብራቱ ውስጥ የሆነ ነገር ሲበተን ታየኝ ።

ጃክ ወደ ሄሚ ጠጋ ብሎ ተመለከተና ሄሚ የጣለውን ቦርሳ ያዘና ራሱ የጣለውን ሻንጣ ለማምጣት ወደ ኋላ ሮጠ በማንሣት ወደ እኛ እየሮጠ ፦

«ሩጡ ! ሩጡ !» እያለ አምባረቀብን ።

ዲክ ሮጠና ጠፋብኝ፤እኔ ግን መሮጥ አቅቶኝ ዝም ብዬ ቆምኩ ። ጃክ ዐይኑን አፍጥጦና ጥርሱን አግጦ አጠገቤ እስኪ ደርስ ድረስ መን ቀሳቀስ አልቻልኩም ። ከያዘው ሻንጣ አንዱን ተቀበልኩና ከዚያ

አስቃቂ ቦታ ለማምለጥ ሮጥኩ ። ጃክ መታጠፊያ ቦታ ላይ ሲደርስ ጠራብኝ ። ለመጨረሻ ጊዜ ዞር ብዬ ወደ ኋላ አየሁ ።

ሁለት ሽጉጥ በሁለት እጁ የያዘ ሰው በመጣንበት መንገድ በመ ብራቱ ትይዩ ሲመጣ አየሁ ። ማን እንደ ሆነ ወዲያው ዐወቅሁት ።

'ብተኩስ እመታት ይሆን ወይስ እስታት' እያለ ከራሱ ጋር በሐሳብ እንደ ሚሟገት ሰው ፡ ሽጉጡን ደግሞ በቀጥታ ይመለከታል ።

ወደ ታች ተመለከትና ጐንበስ ብሎ ሽጉጡን ሄሚ ላይ አስጠ ጋው ። ወዲያው 'ቡም ' የሚል ድምፅ ሰማሁ ።

ጃክ ከየት እንደ መጣ አላወቅም፤ ባለው ኃይል እጁን ጥብቅ አድ ርጎ እየገፈተረና እየገሠተ ይዞኝ ሲሮጥ ፡ አያለቀስኩ «ጃክ ! ሄሚ ሞተ ?» አልኩት ።

«እና ምን ይሁን ? ደደብ ! ዕርፈሽ ሩጭ» ብሎኝ ሩጫችንን ቀጠልን ።

የት እንዳለን አላወቅም፡ ዝም ብዬ ሞኪናዋን እነዳለሁ ። ዲክ ከፊት አጠገቤ ተቀምጦአል ። ጃክ ከኋላ ወንበር ተቀምጠ የመንገድ ካርታ ሳያይ ወዴት መታጠፍ እንዳለብኝ የትዕዛዝ መዓት ያወርደው ጀመር ።

ምዕራፍ ምጸተኞች

በመንገድ ሀሥራ ሰባት በኩል ወደ ቀኝ ታጥፌ ልክ መኻል ልደ ርስ ስል ፡ ጃክ ወደ መንገድ ሰማኒያ ሁለት ታመሪያለሽ ፡ እዛም እንደ ደረስሽ ወደ ቀኝ ትታጠፊያለሽ ፡ ከዚያ ወደ ምዕራብ ሄንስቪል ትሔጂያለሽ ፡ ከዚያ በደቡብ ምዕራብ ጂሳፕ በኩል ወደ ፎልክስቶን ፡ እንደ ገና ወደ ጃክሶንቪል አድርገን መንገድ ዘጠና አምስት ትገቢያ ለሽ ። ብዙ ጊዜ ይወስድብኛል ። ነገር ግን እነሱ በየመንገዱ ባሉት ከተሞች ሁሉ እያቆሙ ስለ ሚፈልጉን ፡ በዚህ ጉዞአችን የትም ሊያ ገኙን አይችሉም» አለ ።

እንደ እኔ ከሆነ አንዮኒዮ ሮሲ ገሃነም ብንገባም ተከትሎን ይገ ባል እንጂ ፡ የትም ቦታ ብንሔድ ፈልጎ እንደሚያገኘን አልተጠራ ጠርኩም ።

ሄሚ እንደ ሞተና ወደ ሰሜን ሳቫና ከመድረሳችን በፊት ጃክ መኪ ናዋን እየነዳ ልክ የመኪና አሽቅድድም ተወዳዳሪ ይመስል ከተማዋን በጨከት በጥበጠን ወጣን ። እንደዚህ ዓይነቱ የሰውና የመኪና ብዛት

ባለበት ከተማ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት ምንም አደጋ ሳናደርስ መውጣት በመቻላችን የጃክን የመኪና መንዳት ችሎታ አደነቅኩት ።

ከከተማው ወጥተን ዋናውን መንገድ ይዘን በፍጥነት መጓዝ ጀመርን ። ወደ ሰሜን ሳቫና አካባቢ ስንደርስ ፀረፍ አልን ። ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው እኔ መኪናዋን መንዳት የጀመርኩት ። ጃክ ከኋላ ወንበር ተቀምጦ ስለ ነበር ፥ ለሁላችንም ብራንዲ ቀድቶልን እንጠጣለን ።

ዲክ ፍርሃቱንና ደንጋጤውን ለመርሳት የተሰጠውን ብራንዲ በሁለት እጁ ጥብቅ አድርጎ ይዞ ይጠጣል ። ሁኔታዬን ከዲክ ጋር ላስተያየው ከሱ የበለጠ አልደነገጥኩም ። እሱ ሞራሽ ፈሀአል ። እኔ ተደናግጬ በነበረበት ወቅት የሆነውን ሁሉ እንዲነግረኝ ጃክን ጠየኩት ። እሱም ለካ ይሀን ብራንዲ ከልክ በላይ ጠጥቶ ኖሮ ለምጠ ይቀው መልስ ሳይሰጠኝ ዝም ብሎ ብቻውን ያወራል ።

«ያን የመሰለ ጥሩ ሰው አጣን ። እንደ መሰለኝ ከሆነ ሄሚን የገደለው ብንደንበርግና ልጅቱ መሸጫ ሱቅ ያየሁት ሰውዬ ነው።እኔም ጭንቅላቱን ብትንትኑን አውጥቼለታለሁ ። ገንበስ ብዬ ሳየው ነፍሱ አልወጣችም ። በሦስት ጥይት ስለ ተመታ አይተርፍም ። ለዚህ ነው ትቼው የሔድኩት ።»

«አንቶኒዮ ሮሲ ፥ ሄሚን ሲገድለው አይቻለሁ» አልኩት ።

«አዎ ! ሊሆን የሚችልና የምገምተው ነው» አለኝ ።

«ገበገ ሰው ነበር» ብዬ ማልቀስ ጀመርኩ ።

«አዎ በጣም ጥሩ ሰው ነበር ፥ ምን ያደርጋል ገለበት እንጂ ጭንቅላት አልነበረውም ።»

«ጃክ ! ቤተሰብ አለው ?» ብሎ ዲክ ጠየቀ ።

በግዴለሽ መልክ ፥ «ቤተሰብ ይኑረው አይኑረው አላውቅም » አለ ጃክ ።

ባለማዘኑ ምክንያት ልጮህበት አሰብኩ ። ግን ምን ጥቅም አለው ። እራሱ ቢሞትም የሚያዝንለት ሰው የለም ። እሱም ይሄን ስለ ሚያውቅ አይጨነቅም ።

የሄሚን ሞት ለመርሳት ይሁን ወይም ስለሚከታተሉን ሰዎች እያሰበ መሆኑን ማወቅ አልቻልኩም እንጂ ፥ ከኋላ ወንበር ተቀምጦ ይሄን መጠጥ ዝም ብሎ ይጠጣል ። አንዱን ጠርሙስ ብራንዲ ለብቻው ጠጥቶ ጨረሰና መስታወቱን ዝቅ አድርጎ በመስኮት ወረወ

ረው ። ጠርሙሱ ሲሰባበር ከትከት ብሎ በመሣቅ እንደ ገና ግማሽ ጠርሙስ ቮድካ አውጥቶ መጠጣት ጀመረ ።

ያለ ምንም ንግግር በጸጥታ ተጓዝን ። ወደ ደቡብ ሳቫና ስንደርስ ፣ ጃክ ድምፁን ከፍ በማድረግ እየተኮላተፈ ይናገር ጀመረ ።

«የሚያሥቀው ነገር ... ምን እንደ ሆነ የሚያሥቀው ታውቃላችሁ? ሄሚ ከጥይት ለመከላከል ደረቱን ጋርዶበት የነበረው ሻንጣ በልብስ የተሞላ ስለ ነበር፣ ጥይቶቹ በልብሱ አልፈው ሊመቱት ቻሉ። ሻንጣው አጠገቤ ነው፣ ጥይቶቹ የገቡበትና የወጡበት ቀዳዳ ይታያል። ይሄን ሻንጣ መጣል አለብን ። ሄሚ የጌጣጌጥ ሻንጣውን ይዞት ቢሆን ኖሮ ጥይቶቹ አልፈው አይመቱትም ወይም ሻንጣው ውስጥ ከገቡ በኋላ አቅጣጫቸውን ይለውጡ ነበር ። ገባችሁ? ልብስ የተሞላበት ሻንጣ መያዙ በጣም መጥፎ አጋጣሚ ነው ። ሁኔታው ይሄን ይመስላል ... ማለቴ የመጥፎ ዕድል አጋጣሚ» አለና ዝም አለ ።

በፊት መስታወት ስመለከተው፣ እግሮቹን ወደ ጐን ዘረጋና ራሱን ወንበር ላይ አስደግፎ ተኛ ። እርግጠኛ ነኝ እንቅልፍ ወስዶታል ።

በየት በኩል መሔድ እንዳለብኝ፣ የት ስደርስ መታጠፍ እንደ ሚኖርብኝ የነገረኝ ሁሉ ጠፋብኝ ። መንገድ ሰማንያ ሁለትን ይዤ ወደ ደቡብ ምዕራብ አመራሁ ። በመጨረሻ እኔና ዲክ የመገናኛ ሥፍራ የሚል ምልክት አየንና መንገዳችንን መሳታችንን ዐወቅነው ።

እየተንሾካሾክን 'ጃክን እንቀስቅስና ትክክለኛውን መንገድ ይምራን ወይስ እንተወው' ተባባልን ። ግን ምንም ጥቅም አልነበረውም ። አንደኛ ሰዓቱ ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖአል ። ሁለተኛ እኔ በጣም ተዳክሜአለሁ ፣ ዲክም ጉልበቱን እንዳመመው ዐውቄአለሁ ። ይሄ ሁሉ ችግር እያለ ያለ የሌለ ኃይላችን እስኪያልቅ ድረስ መጓዝ ሞኝነት ነው በሚል ሐሳብ አልቤርጎ ፍለጋ ጀመርን ። አልቤርጎ ለማግኘት ወደ ዐሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ አገኘን ። ያገኘነው ክፍል ጽዳት የሚወራ አይደለም ። በዚህ የድካም ወቅት ደግሞ ንጽሕና የሚያስጨንቅ አልነበረም ።

ዲክ ከመኪናው ወርዶ አልጋ አከራዩን ሰውዬ በመቀስቀስ በውስጥ ሁለት ክፍል ያለው አንድ ቤት ተከራየ ። እኔና ዲክ እየተጋገዝን ዕቃዎቻችንን ወደ ክፍሉ አስገባንና ጃክን እንደ ምንም ጐትተን ከመኪና በማውጣት ደግፈን ወደ ክፍሉ አስገብተን አልጋ ላይ አሳረፍነው ።

«በቃ ተይው፤ እኔ ልብሱን አውልቄ አስተኛዋለሁ» ስለ አለኝ መጽሐፌንና የሚያስፈልጉኝን ልብሶች ይዤ ወደ መኝታዬ ሔድኩ ።

ሽሽት ከጀመርን ጊዜ አንሥቶ ለብቻዬ ስተኛ የመጀመሪያዬ ይሁን አይሁን ማሰታወስ አልቻልኩም ። እልጋዬ ላይ ከማረፌ በፊት አርቲ ፊሻል ጸጉሬንና ልብሴን አወላለቅሁና የውስጥ ሱሪና ጡት ማስያዣ ብቻ እንደ ለበስኩ ተኛሁ ። መጥፎ ጠረን ይሸተኛል ። መጥፎው ጠረን የሚሸተው ከእኔ ይሁን ከክፍሉ ማወቅ አልቻልኩም ።

ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት እንቅልፌን ሳልጨርስ ፣ ከክፍሌ አጠገብ የቆሻሻ መጫኛ መኪና ትናንሽ ቆርቆሮዎችን ሲጭን ጩኸቱ ቀሰቀሰኝ ። ቆሻሻውን ጭኖ መኪናው በጩኸት ከሔደ በኋላ ፣ ለመተኛት ብሞክር እንቅልፍ አልወስድሽ አለኝ ። ተነሣሁና የሬሳ ሳጥን በም ታክል ግንዳ ውስጥ ሰውነቴን ተለቃልቄና ንጹሕ ልብስ ለብሼ ከክ ፍሉ ወጣሁ ።

ፀሐይ በደመና የተሸፈነች ትሁን እንጂ ሙቀት አለ ። አካባቢ ውን ቃኘሁት ። ለጥ ባለ ሜዳ የተለያየ ቅርፅና መልክ ያላቸው እዚ ህም፣እዚያም የተሠሩ ቤቶች ያሉባት አነስተኛ መንደር ናት ።

መኪናችን ማታ ክቆምንበት ቦታ ቆማለች ፣ ወንዶቹ አሁንም እንደ ተኙ ናቸው። አልጋ ወደ እሚያከራዩበት ክፍል ሔድኩ ። ጠረ ጴዛው ላይ ሁለት እጆችዋን አሳርፋ የጥፍርዋን ቆሻሻ በስንጥር እያ ወጣች የተቀመጠች ወፍራም ሴትዮ አገኘሁ ። ቁመትዋ ከእኔ አነስ ቢልም፣በክብደት ግን የእኔ እጥፍ ትሆናለች ።

«እንዴት አደርሽ ቆንጅት ! ይሄን ደስ የሚል ሞቃት ቀን እን ዴት ታይዋለሽ?» አለችኝ። አነጋገርዋ ለስለስ ያለና ደስ የሚል ሲሆን፣ የጀርጂያ ሰው ትመስላለች ።

«የሚጠጣ ቡና ባገኝ የበለጠ ደስ የሚል ቀን ይሆናል» አልኩ ዋት ከፈገግታ ጋር ። «ይቻላል ፤ ለአንድ ሲኒ ቡና ከሁለት ኬክ ጋር ሠላሳ አምስት ሣንቲም ትከፍያለሽ ።»

«አሺ አንድ ቡናና ኬኩን ስጪኝ»

ከኤሌክትሪክ የቡና ማፍያ ቡናውን እየጨመቀች ፣ «ወተትም ከፈለግሽ አለኝ» አለችኝ ።

«ቡናውን ለብቻው ነው የምፈልገው ። ጥቁር ቡና በጣም እወ ዳለሁ ።»

«ልክ ነሽ ፣ ጥቁር ቡና ቆንጆ ነው፤ በስኳር ይሁን ወይስ እንዲሁ?»

«እንዲሁ ይሁንልኝ ።»

ቡናውን በፕላስቲክ ኩባያ ቀዳችልኝና ኬኩን በለስላሳ ወረቀት እየጠቀለለች፣ «ከጓደኞችሽ ጋር ወዴት ነው የምትጓዙት?» አለችኝ፣ ለዛ ባለው አነጋገር ።

«ወደ ደቡብ» አልኩዋት ።

«በዚህ ዓመት ብዙ ሰው ወደ ደቡብ እየተጓዘ ነው ፣ እርግጠኛ ነኝ፣ ወደ ሚያሚ ነው የምትሔዱት» አለችኝ ።

«አዎ ! ግምትሽ ትክክል ነው ።»

«እኔና ሽማግሌዬ በዚህ ዓመት ወደ ሚያሚ ለመሔድ አስበናል ። ባለፈው ዓመት ሔደን ነበር ። ለመሆኑ ከአሁን በፊት ታውቂዋለሽ?»

«አላውቀውም ።»

«ማየት አለብሽ ፣ በጣም ቆንጆ ከተማ ነው ፣ አያምልጥሽ» በማለት ኩስተር ብላ መከረችኝ ። እጅ ለእጅ ተጨባበጥን ።

ደስ የሚል ስሜት ከውስጤ እየተሰማኝ ቁርሴን ይዤ ወደ ክፍሌ ሔድኩ ። ቡናውንና ኬኩን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጬ ወንበር ስቤ ተቀመጥኩና ከቦርሳዬ ውስጥ ወረቀትና እርሳስ አውጥቼ ቡናዬን ፉት እያልኩና ኬኩን እየገመጥኩ፡ መጽሐፌን ከድርጊቱ ጋር እኩል ለማ ራመድ ቶሎ ቶሎ መጻፍ ጀመርኩ ።

ቁጭ ብዬ መጻፍ ከጀመርኩ ሁለት ሰዓት ሳያልፈኝ አልቀረም ። ሱቆች በብዛት የሚገኙበት ሐርዴቭል አካባቢ መድረሳችንን በመጻፍ ላይ እንዳለሁ የክፍሌ በር ተንኳኳ ። ከመክፈቴ በፊት እነማን እንደ ሆኑ ለማረጋገጥ የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ አድርጌ ተመለከትኩ ። ጃክና ዴክ በናና ኬካቸውን ይዘው ቆመዋል ። ከፈትኩላቸውና ገቡ ። ዴክ አሁንም ትንሽ ያንዘላል ። ሆኖም ሁለቱም ጥሩ እንቅልፍ የወሰዳቸው ይመስላሉ። አልጋዬ ላይ ዐረፍ አሉና ቡናቸውን መጠጣት ጀመሩ ።

«ወደ ጂሳኒ የሚገነጠለውን መንገድ ስለ ሳትነው ነው ወደዚህ የመጣነው» አልኩት ።

«ምንም ችግር የለውም ። እንድናርፍ ማድረጋችሁ ትክክል ነው ። ወደ ዋናው መንገድ ለመድረስ በቀላሉ ሁለት ወይም ሦስት አቋራጭ መንገድ አይጠፋም ። ለዚያውም ለመሔድ ካስፈለገን ነው» አለ ጃክ ።

ትኩር ብዬ ተመለከትኩትና ፣ «ካስፈለገን? ... ምንድነው የም

ትለውጣ ሚያሚ ቶሎ ለመድረስ ተጣድፊሀ ነበር ። አሁን ደግሞ ለመ ዘግየት የፊለከው ለምንድነው ?» አልኩት ።

«አዎ ! አሁንም ሚያሚ ቶሎ ለመድረስ አፈልጋለሁ ። ሆኖም በተዳዩ ከዲክ ጋር ተነጋግረንበት ለአንድ ሳምንት ያህል ይዜ ሁሉ ችግር በረድ እስኪል ወደ ገጠር ገብተን ብንቆይ የተሻለ ሆኖ አግኝ ተነዋል ። ለአንድ ሳምንት አንድ ቦታ ሊያስቀምጠን የሚችል ገን ዘብ አለን ።»

«የምንቆይበት ቦታ ጆርጂያ እንደ አሚሆን ተስማምተናል ። ጃክ እንዳለኝ ከሆነ ጆርጂያን እንደ እጁ መዳፍ ስለ ሚያውቀው ፣ ለጊዜው የምናርፍበት ቤት ሊያገኝ እንደሚችል ነግሮኛል» አለ ዲክ ፣ ቀጠል አደረገና ።

«ምን ታስቢያለሽ? ማለቴ ስለ ቆይታችን ...» አለኝ ጃክ ።

«እንደ ተረዳሁት ፣ ከጃክ የወንበዴ ቡድን በሕይወት ያለነው ሦስት በመሆናችን ምክንያት ፣ መሪያችን ከማዘዝ ይልቅ ሐሳባችንን መቀበል መርጠአል መሰለኝ» አልኩኝ በማሾፍ ። እንደ እውነቱ በመንገድ ዘጠና አምስት ነጠላቶቻችን እየተከታተሉን ከመሸሽ ይልቅ ለአንድ ሳምንት አንድ ቦታ መቀመጡ ጥሩ መስሎ ታየኛና ትከሻዬን በመነቅነቅ ጭምር«እንደ እኔ ከሆነ ጥሩ መሰለኝ ። ግን ለአንድ ሳም ንት ያለ ምንም ችግር ለንቆይበት የምንችል ቤት የት ነው የምናገ ኘው ?» አልኩት ።

«እንደ እኔ ከሆነ ወደ ፎይክሮስ ተመልሰን በምዕራብ በኩል ወደ አልባኒ እንሔዳለን ። እዚያ አካባቢ ያሉ መንደሮችን በደምብ ስለማውቃቸው ፣ ማረፊያ ቦታ በቀላሉ ማግኘት እችላለሁ» አለን ።

«እንደዚያ ዓይነት ገጠር ውስጥ ከመግባታችን በፊት በመንገ ዳችን ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ጥሩ ምግብ ቤት ገብተን መመገብ ይኖር ብናል ። አይመስልህም ጃክ ?» ፣

«ግንም ጆርጂያ ውስጥ ፊለሳ ሊያገኘን ስለ ማይችል የፈለግነን ማድ ረግ እንችላለን ። እና እንዳልሺው በፊለግነው ምግብ ቤት ገብተን ለአ ንድ ሳምንት የሚሆነንን የምንችለውን ያህል ጥሩ ምግብ እንበላለን ።»

ጃክ መኪናዋን እየነዳ መጀመሪያ ወደ ፎይክሮስ ከዚያም ወደ ሰሜን ፊታችንን በመመለስ እንደ ገና ወደ ምዕራብ አልማ አቅጣጫ ዞርን ። አጠገቡ ሆኘ መንገዱ እንዳይጠፋን ሞቢል ያዘጋጀውን የመ ንገድ ካርታ እመለከታለሁ ። ግን አራት የነበሩት መንገዶች ወደ ሦስትና ከዚያም ወደ ሁለት መንገድነት እየተለወጡ መጡ ። እነዚ

ሀን መንገዶች እንደ ጨረስን ወደ ኩረኩንች መንገድ ገባን ። ለጥ ያለ ሜዳ እስከምናገኝ ድረስ እየተንገጫገጭን ተጓዝን ። ሜዳው ከደረስን በኋላ መንገጫገጩ ቀርቶ ከፍተኛ አቧራ ከኋላችን እያስነሣን ወደ ፊት መንገዳችንን ቀጠልን ።

በየመንገዳችን የነዳጅ ማደያ ፣ አነስተኛ ሽቀጥ መሸጫና ቡና ቤት ብቻ ያላቸው ትናንሽ መንደሮች አጋጥመውናል። በነዚህ መንደሮች የሚታዩት ሰዎች ወንዶቹ ያረጀ ቱታ ፣ ሴቶቹ ደግሞ የተበጫጨቀ ልብስ የለበሱ ሲሆን ፣ አንዳንዶቹ በአህያና በበቅሎ የሚገሠቱ ጋሪዎችን እየነዱ ወደ ፊት ይጓዛሉ ። መሬቱን ሲያዩት ሙልጭ ብሎ ከመበላቱ የተነሣ አፈሩ አልቆ ሸክላው ብቻ ቀርቶአል ። ሰዉም እንደ መሬቱ የተጐሳቆለ ነው ።

የኛ ፔጆ መኪና በነዚህ መንደሮች ስታልፍ ፣ ልክ ከሌላ ክፍለ ዓለም የመጣን ይመስል ወዋቂውም ሆነ ሕፃኑ ቆመው በመደነቅ ይመለከቱናል ። ፀሐይ በቅጥታ እኛ ያለንበት አካባቢ ብቻ ብርሃንዋን ያሳረፈችበት ይመስል የመቀቱና የፀሐዩ መንቀልቀል 'ንግዚአ' የሚያሰኝ ነው ።

ወደ ጀክ ዞር ብዬ ተመለከትኩት ። ፊቱ በደስታ ተሞልቶአል ፤ አልፎ አልፎም ወዲያና ወዲህ እየተመለከተ ፈገግ ይላል ። እንደ ገመትኩት ከሆነ ጭልጥ ያለ በረሃ ውስጥ በመግባት አስተማማኝ ሰላም ለማግኘትና ከሚከተሉን አደገኛ ጠላቶች ለመራቅ አመቺ ቦታ በሐሳቡ የሚያማርጥ ይመስላል ።

ይህ ብቻ ይሆን የሚያስደስተው ፣ አልመሰለኝም ። ምናልባት ከብዙ ጭንቀት ፣ መከራና ችግር በኋላ ወደ ሚያውቀውና እንደ ቤቱ ከሚቆጥረው አገር መመለሱ ሳይሆን ይቀራል ፣ እርግጠኛ ነኝ ይሄን እያሰበ ነው ። ወደ ፊት በተጓዝን ቁጥር አልፎ አልፎ በየመንገዱ መኻል የተቦረቦሩ ጉድጓዶች ውስጥ ገብተን ስንላተም ፈገግ የሚለውና በመጠኑም ለመሣቅ የሚሞክረው ወደ ድሮ ቦታው መመለሱን እያስታወሰ መሆን አለበት ።

ዳዱሮ እዚህ በነበርኩበት ጊዜ በአነስተኛ የጭነት መኪና ፣ በየማድቤቱ የሚዘጋጅ ጥራቱ ውኃ የመሰለ የአልኮል መጠጥ እየጫንኩ በየደንበኞች ቤት እየሠርኩ እሸጥ ነበር ። መጠጡ በየከተማው ከሚገኘው አልኮል መቶ በመቶ የሚበልጥ ሲሆን ፤ በጣም ኃይለኛ ነው። ስትቀምሱት ጉሮሮ እያቃጠለ ይወርዳል ። ታዲያ መጠጡን የሚያዘጋጁት ሰዎች በተገኘው ዓይነት ጠርሙስ እየሞሉና ቆርኪ እየከደኑ ይሰጡናል ። እኛም ወስደን መሸጥ ነው ። የሚገርመው ጠርሙስ

ለማግኘት ችግር ስለ ሆነ ፡ መጠጡን ጠጥቶ የጨረሰ ሰው ከፊለጊ ሰጠ ርሙስ አንድ ብር ፡ ለቆርኪው ደግሞ ሁለት ሣንቲም ማስመለስ ይች ላል» አለና ጃክ ፊጊግ አለ ።

«ይሂን ሥራ ስትሠራ ዕድሜህ ሰንት ነበር ?» አለ ዲክ ።

«አ ! በጣም ልጅ ነበርኩ ። ምናልባት ዐሥራ ሦስት ወይም ዐሥራ አራት ዓመት ቢሆነኝ ነው ። እዚህ አካባቢ ያንን ዓይነት መጠጥ እያስጫኑ ሕፃናትን መኪና ማሰነዳት የተለመደ ነው ። ለምን መሰለህ መጠጡ አደገኛ ከመሆኑ የተነሣ እንዳይሸጥ የተከለከለ ስለሆነ ነው ። ስንነዳ ፖሊሶች ቢያገኙን የሚያደርጉት ምን መሰለህ ? ትንሽ ገራር ፈው ይለቁናል ። ለዚህ ነው ትልልቆቹ ሰዎች ተቀምጠው ሕፃናትን መኪና የሚያስነዱት ።»

ወደ በርሃው ውስጥ እየገባን ስንሔድ የጃክም የአነጋገር ዘይቤ እየተቀየረ መሔዱን ተገነዘብኩ ። አነጋገሩ መሰወጥ ብቻ ሳይሆን ፤ አንዴ ኒውዮርክ ሰው ፈጠን ብሎ ይናገር የነበረው ሰውየ ረጋ ብሎና እያንዳንዱን ቃል ጫን እያለ መናገር ጀመረ ። አሁን እንግዲህ እኛ ወደ ማናውቀው ውጭ አገር ውስጥ ገብተናል ። ሾፌራችን ጃክም የአነ ጋገሩ ዘይቤ እየተቀየረ በመሔዱ ከሌላ ሰው ጋር የምንገገ መሰለኝ ።

በእነዚህ አነስተኛ መንደሮች የተገነዘብኩት ብዙዎቹ ወንዶች የአካል ጉዳተኞች ናቸው ። አንድ እጅ ያሳቸው ፡ ጣታቸውን የተቆ ረጡ ሕፃናት ፡ በአርቲፊሻል እግር ወይም በእንጨት ምርኩዝ የሚ ሔዱ ሰዎች በብዛት ይታያሉ ። የነዚህ ሰዎች አካል ጉዳት ከምን የተ ነሣ እንደ ሆነ ጃክን ጠየኩት ።

«ዘመናዊ የእርሻ ቦታ በየገጠሩ ውስጥ ስላለ እዚያ የሚሠራ ሁሉ አንድ እደጋ ይደርስበታል ። ወደ ገጠሩማ ብትገቡ ብዙ ቆራጣ ታያ ላችሁ ። እኔም ከዚህ አካባቢ ለመውጣት ትልቅ ምክንያት የሆነኝ ይሄው ነው ። ትንሽ ቆይቼ ቢሆን ኖሮ አካለ ጉዶሎ የመሆን ዕድል ያጋጥመኝ ነበር ።»

በመጨረሻ ካለፍናቸው መንደሮች በመጠንም ሆነ በዓይነት ለውጥ የሌለው መንደር ደረስን ። «ዊተር ጆርጂያ ማለት ይሄ ነው ። እዚህ አካባቢ ሳምንቱን ብናሳልፍ ጥሩ ነው» አለን ።

«ካለፍናቸው መንደሮች የተለየ አይደለም ፡ ለምን ይሂን ቦታ መረጥክ ?» አልኩት ።

«አንዳልሽው ከሌሎች መንደሮች የተለየ አይደለም ፡ እኔም የመረጥኩት በዚሁ ምክንያት ነው ። የዚህ ዓይነት ከመቶ በሳይ ተመ

ሳላይ መንደሮች አሉ ። ሁሉንም ዐውቃቸዋለሁ ። የነዚህን ከተሞች ካርታ የሠራው ሰው ዊተር ረስቶ ካርታ ላይ አላሰፈራትም ። እና ለኛ ተስማሚ ናት ። አነስተኛ ቢሆኑም ነዳጅ ማደያ ፣ የሽቀጣ ሽቀጥ መደብር ፣ ባንክ ቤት ፣ ምግብና መጠጥ ቤት አላት » አለኝ ።

«አልቤርነስ ?» አለ ዲክ ።

«እዚህ ማን ይመጣልና ነው አልቤርነ የሚያስፈልገው ። በዚች ሙንደር የሚያልፍ እንጂ የሚያርፍ መንገደኛ የለም ።»

«ታዲያ አንድ ሳምንት በሙሉ የት እንቆያለን ?» አልኩት ።

«አሁን የምንፈልገው የሚከራይ ቤት ነው ። ቢቻል ባልዋ የሞተባት ወይም ፈት የሆነች ሴት ቤት ብናገኝ ጥሩ ነው ። እዚህ አካባቢ የሚገኙ ቤቶችን የሚያከራዩ ከሆነ በየበራቸው ላይ ቱሪስቶችን ለአንድ ቀን ፣ ለአንድ ሳምንት ወይም ለአንድ ወር እናስተናግዳለን የሚል ማስታወቂያ ይለጥፉበታል ። የቤታቸው ንጽሕናም ይሄን ያህል የሚያስጠላ አይደለም ። ዘመናዊ የቤት ዕቃ ግን የላቸውም» አለንና የሚከራይ ቤት ፍለጋ ጀመርን ።

ከዋናው መንገድ ወደ ቀኝ በሚታጠፍ መንገድ ላይ የሚከራይ ቤት እንዳለ የሚገልጽ ምልክት አየንና ምልክቱን ተከተለን ወደ ውስጥ በመግባት አንድ ትልቅ ቤት ደረስን ።አንዲት ሴትዮ ወደ ኋላና ወደ ፊት በሚወዛወዝ ወንበር ላይ ሆና ሙቀቱን ለመከላከል በማራገቢያ ፊትዋን እያራገበች በረንዳ ላይ ተቀምጣለች ። ጃክ የመንገዱን ጠርዝ አስጠግቶ መኪናዋን አቆመና ሞተሩን አጠፋ ። ወደ ዲክ ፊቱን አዙሮ ፣ «ሄሚ ባርኔጣ ነበረው ፣ ተመትቶ ሲወድቅ ግን ባርኔጣ አላደረገም ነበረ ። ስለዚህ ከኋላ ይኖራልና ፈልገህ ስጠኝ» አለው ። ዲክ ሻንጣዎቹን እያመሰቃቀለ ፈለገና አረንጓዴ ቀለም ያለው ሰፊ ባርኔጣ አውጥቶ ለጃክ ሰጠው ። ጃክ ተቀበለውና ዐይኑን እስኪሸፍነው ድረስ ገቅ አድርጎ አጠለቀው ።

«ሁላችንም መኪናዋን እዚህ ትተናት እንወርዳለን ። ለአካባቢው እንግዳ መሆናችን እንዲታወቅ ግራና ቀኝ እየተመለከትን ተዝናንተን ወደ ሴትየዋ እንሔዳለን ። ሁለታችሁ ከኔ ቢያንስ ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ቀረት ብላችሁ ተከተሉኝ ። ዲክ እግርህ ከሚያስነክስህ በላይ ለማን ከስ ሞክር ። ከሴትየዋ ጋር የምነጋገረው እኔ ነኝ ። እናንተ ዝም በሉ » ሲል ጃክ፣ «ታዲያ ባርኔጣ ምን ሊያደርግልህ ነው ያደረከው ?» አልኩት በመመናጨቅ መልክ ፤

«ማውለቅ እችላለሁ» አለኝና ፣ «ይልቁኑ የሚወራረደኝ አለ ?» አለን በድንጉት ።

እኔና ዲክ ተያየንና በመገረም፡ «ምን ዓይነት ወርርድ!» አልኩት።

«የምወራረዳችሁ የሴትየዋ ስም አፖል ፡ ፔርሲ ፡ ሮዛ ፡ ሚኒ ወይም ቻራቲ መሆን አለበት ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ካልሆነ ዐሥር ብር እከፍላለሁ ።»

«እኔ እወራረዳለሁ ፤ የሴትየዋ ስም እንተ ከጠራኸው ውጭ ከሆነ ዐሥር ብር ለእኔ ትሰጠኛለህ ካልሆነ እኔ እሰጥሃለሁ» አለ ዲክ ።

«እሺ እስማማለሁ ። እንሒድ ።»

ለሙቀቱ ብለን የመኪናችንን መስኮት ትንሽ ዝቅ አድርገን በሩን ቆለፍንና ረጋ ብለን ወደ ቤቱ ተጓዝን ። በረንዳ የተቀመጠች ው ሴትዮ ከወንበሩ ጋር መወዛወዙን ሳታቆም ወደ እሷ የምንሔድ መሆኑን በውቃ ፊትዋን በማራገቢያ እያራገበች ጠበቀችን ። እየተጠ ጋናት ስኑሔድ ዕድሜዋ በማምት ወደ ስልሳው የሚጠጋ ፡ ረዥምና ወፍራም መሆኗን መለየት ቻልኩ ። የለበሰችው ልብስ ዘመኑ ያለፈ በት አሮጌ ሲሆን ፡ ከረዥም ካልሲ ጋር ጫማ ተጫምታለች ። ጫማው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ወታደሮች ያደርጉት የነበረ የጦር ሜዳ ጫማ ነው ። የሆነ ነገር ታሳምጣለች ። ማስቲካ ወይም ትንባሆ ይሆናል ስል ገምቼ ነበረ ። ግን በኋላ እንደ ተረዳሁት የምታላምጠው በአካባቢው ልዋርስ ንጽሕና ይጠቅማል ብለው የሚያምኑበት ቅጠል ሆኖ አገኘሁት ። ሴትየዋ አጠገብ ልንደርስ ሁለት እርምጃ ሲቀረን ጃክ እንድንቆም ምልክት አሳየንና ቆምን ። ጃክ ወደ ፊት ራመድ ብሎ አንዱን እግሩን ደረጃው ላይ አሳርፎ ባርኔጣውን ከራሱ እያነሣ «እንደ ምን ዋሉ» አለ በራሱም ጭምር ጉንበስ ብሎ ።

ራስዋን በመነቅነቅ ሰላም አለችውና ፡ «በዚህ ዓመት መቀቱ ኃይለኛ ነው » አለች ።

«አዎ ! በጣም ይሞቃል ። ስሜ ሳም ሞሪሰን ይባላል ። ይቺ ቆንጆ ሴት ባለቤቴ ናት ፤ ስሟ ቤትሪስ ይባላል ። ይሄኛው ደግሞ ወንድሜ ዲክ ሪቻርድ የሚባለው ነው ። የመጣነው ከማኮን ነው ። ያውቁታል? ለአንድ ሰምንት ያህል ወደ ደቡብ ፍሎሪዳ ጭሣ ለማጥ መድ ነበር የምንሔደው ። ግን ዛሬ ቀዋት ዲክ እግሩን ወለም አለው። ሲያነክስ አይተውት የለ? ዶክተር አይቶት አያሠጋውም ፤ ግን ማረፍ አለበት ብሎታል » አለና ጃክ ትውውቁን ጨርሶ ፡ ቀጠል በማድ ረግ ፡ «ዓሣ ለማጥመድ የሚያስችለን ስለ አልሆነ ፀረፍ ብለን ዲክ እስኪሻለው ለመጠበቅ ወሰን ። ስለዚህ ነው ማረፊያ ቤት ፍለጋ ወዲ ያና ወዲህ የምንንከራተተው ። እና እርሶ ዘንድ አንድ ክፍል ለኔና ለባ ለቤቴ ፡ አንድ ደግሞ ለዲክ የሚሆን ክፍል ለተመሰኑ ቀናት ፡ አምን

ቢበዛ ለአንድ ሳምንት የሚከራይ ይኖረዎት እንደ ሆነ ለመጠየቅ ነው፣ ምንም ችግር አንፈጥርም ። ብዙ ስንሠራ የከረምን ስለ ሆነ ሰላማዊ ዕረፍት ብቻ ነው የምንፈልገው ፣ ምንም አይሥጉ » አለ ። ሴትዮዋ ወንበሩ ላይ ተቀምጣ መወዛወዙንና ፊቱዋን ማራገቡን አላቆመችም ። ምንም መልስ ሳትሰጥ ከጃክ ጋር ለረኾም ጊዜ ዐይናቸውን ከአንዳቸው ላይ ሳይነቅሉ ተፋጥጠው ይታያዩ ጀመር ። ቦመኻላቸው ያለው ጸጥታ ለዘለዓለም የሚቀጥል ይመስላል ። እንደዚህ ጭልጥ ባለ ባላገር የተለመደ ሳይሆን አይቀርም ። በእካባቢው የወፍ ፣ የመኪናና የአውሮፕላን ድምፅ አይሰማም ።

የጃክና የሴትዮዋ መፋጠጥ አሁንም እንደ ቀጠለ ነው ፤ ሲያዩዋቸው ሁለቱም በዐይናቸው የሚነጋገሩ ይመስላሉ ። «ሳም ሞሪሰን ነው ያልከኝ ?» አለች ከዚያ ከብዙ ጸጥታ በኋላ ።

«አዎ ! ሳም ሞሪሰን ነው ያልኩዎት ። የተወለድኩትና ያደኩት እዚያው ማኮን ነው ። ባለቤቴና ወንድሜ ግን ፣ የሚኖሩት ሰሜን ማኮን ነበረ» አለ ፣ ልክ ማኮን የተወለደ ሰው ፣ ከሰሜን ማኮን ሚስትና ወንድም መኖሩ የተለመደ ይመስል ።

ሴትዮዋ መረዳትዋን ለማሳየት ራስዋን ነቀነቀችና ፣ «ለያንዳንዳችሁ በቀን ዐሥር ብር ትከፍላላችሁ ። ይሄ ክፍያ ጥዋት የምትበሉትን ቁርስ ይጨምራል ። ምሳና ራታችሁን ከተማ መብላት ትችላላችሁ ። ሐክሲ ምግብ ቤት ብዙም ጥሩ ምግብ ማዘጋጀት ባይችልም ሆዳችሁን ሊሞላ የሚችል ታገኛላችሁ ። በተረፈ እዚህ በምትቆዩበት ጊዜ ሁሉ እክፍላችሁ ውስጥ ምግብ ማብሰልና ሳሎን ውስጥ ከባድ አልኮል ያላቸው መጠጦች መጠጣት አይፈቀድም ። ምናልባት መጠጣት ከፈለጋችሁ ክፍላችሁ ውስጥ ሆናችሁ ልትጠጡ ትችላላችሁ ። ይሄን አልታወሙም ። በረዶ ከፈለጋችሁ ፍሬጅ ውስጥ አለ ። ቴሌቪዥን ማየት ከፈለጋችሁ ሳሎን በመምጣት ማየት ትችላላችሁ » አለችን ።

ጃክ የተጠየቀውን ዋጋ ለመክፈል ቦርሳውን ከኪሱ እያወጣ፣ «በጣም እናመሰግናለን ፣ ወንድሜ ቶሎ የሚድን ስለ ሆነ ብዙ ቀን የምንቆይ አይመስለኝም ። ይቅርታ ያድርጉልኝና ስምዎ ማነው ?» አላት ።

«ሮዛ ሲፈንስ» እባላለሁ ። ከበስተኋላዬ ዲክ ሲያጉረመርም ተሰማኝ ።

«መኪናችሁን በጓሮ በኩል ከሚገኘው የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ማቆም ትችላላችሁ ፣ ሰፊ ቦታ አለ ። የኔ አሮጌ መኪናና የዶሮዎች

ቤት ብቻ ነው ያለበት ፤ ምንም ችግር አይኖርም ።»

«እናመሰግናለን ! ክፍያውን በቅድሚያ ለማጠናቀቅ ባለቤትዎ ይኖራሉ ?»

«ሚስተር ሲፈንስ ከሞተ ቆይቷል» አለችው ።

ጃክ ራሱን ወደ መሬት አቀርቅሮ ፣ «በጣም አዝናለሁ ፣ ቢሆንም ከሞት የሚቀር ሰው ስለማይኖር ፣ የሰማይ ቤታቸው የደስታ እንደሚ ሆን » አላት ።

«እኔም እንዳንተው ሲፈንስ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገባ እገምታለሁ» አለች ።

የቤት ዕቃዎቹ ዘመናዊ ባይሆኑም ፣ ሊኖሩ የሚገባቸው የዕቃ ዓይነቶች አሉበት ። ቤቱ ከሌሎቹ ቤቶች የተለየና ታሪካዊ ይመስላል ። በተለይ የክፍሎቹ መስፋት ፣ የጣሪያው ርዝማኔ ፣ የበሮቹና የመስ ኮቶቹ መተለቅ ፣ የወለሎቹ ማንጸባረቅ ፣ የወንበሮቹና የአልጋዎቹ ከመጠን በላይ ትልቅ መሆን ፣ የግድግዳዎቹ መንጣት ፣ ከሃምሳ ዓመት በፊት በመካከለኛ ያረጀ ይኖሩ የነበሩ የአሜሪካኖችን ኑሮ የሚያሳዩ ናቸው ።

ሁሉም ነገር ንጹሕና አንጸባራቂ በመሆኑ የተለየ ስሜት ተሰም ቶኝ አልቅሽ አልቅሽ አለኝ ። ምክንያቱም ይህ ፣ ቤት ማለት ምን እንደ ሆነ እንዳስታውስ አድርጎኛል ።

ባለፉት ቀኖች በማደሪያነት ያሳለፍኳቸው አልቤርጎዎች ሰጊ ዜው ለመሸሸጊያነት የተጠቀምንባቸው እንጂ ፣ ቤት ናቸው ተብለው የሚጠሩ አልነበሩም ። ይህኛው ቤት ግን ፣ ሰላም የሰፈነበትና አስተ ማማኝ ደህንነት የሚታይበት መስሎ ታየኝ ። ከዚያ ሁሉ ግርግርና ሩጫ ፣ ከድንጉጥኛ ሞት ሰጊዜውም ቢሆን ወጥተን እፎይ ያልንበት ነው ። ያም ሆኖ ቤቱ ሰላምና ጸጥታ የሰፈነበት መስሎ ይታየን እንጂ ባለፉት ቀናት የነበረብንን ሜንቀትና ችግር ሙሉ በሙሉ ያላቀቀን አይደለም ። ችግራችንን በመጠኑም ቢሆን ለመርሳት ግን እገዛ አድ ርጎልናል ።

ወደ ተፈቀደልን ሁለት ክፍሎች ዕቃዎቻችንን ተሸክመን ፎቁን ወጣን ። ከኛ ክፍል አጠገብ ሦስት የመኝታ ክፍሎች ያሉ ቢሆንም ፣ ባዶ ናቸው ። ላሉት ክፍሎች በጋራ መጠቀሚያ የሚሆን መታጠቢያ ቤትና ሽንት ቤት አለ ።

ጃክ በኋላ እንደ ነገረን ፣ ወይዘሮ ሮዛ ደረጃዎቹን መውጣት ስለ ሰለቻት ፣ መኝታ ቤቷን ወደ ምድር ቤት አዛውራለች ። «በሰምንት

አንድ ጊዜ እላይ ያሉትን ክፍሎች የምታጸዳ አንድ ጥቁር ሴትዮ ትመጣለች» አለንና ሆን ብሎ ዲክን እየተመለከተ ፡ «ስለ ወይዘሮ ሮዛ እንደ ምናገር ገብቶሃል?» አለው ። «ዋናው መናጢ ነህ ! ለመሆኑ የሴት የዋን ስም እንዴት ልታወቅ ቻልክ ?» አለ ዲክ እየሣቀና የውርርዱን ዐሥር ብር እያወጣ ።

ጥቁሩ ጃክ እየሣቀ ዐሥር ብሩን ተቀብሎ ኪሱ ከተተና ፡ «ጅሎ ! ይሄ የተወለድኩበትና ያደኩበት አገር ነው ። የሴቶቹን ስም ከጠቃቀስ ኩልህ ውጭ እንደማይሆን ዐውቃለሁ» አለው ።

በመገረም ፡ «ያንተም እናት ስም ከዚሁ ተመሳሳይ ነው?» አልኩት ።

«አይደለም ! የናቴ ስም ተመሳሳይ አይደለም» አለኝ ።

ሁላችንም አንዱ መኝታ ክፍል ውስጥ ገባን ። ክፍሉ በጣም ሰፊ ነው ። እስካሁን ግን ፡ ማን ከማን ጋር እንደ ሚተኛ አልተነጋገር ንም ። በርግጥ ሦስታችንንም ለየብቻችን የሚያስተኛ በቂ ክፍል አለ ። በዚህ ማቃለል ይቻላል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም አልተጨነኩም ፡ በሁኔታው ግን ተገርሜያለሁ ።

በቅርብ ካገኘሁት አንዱ ወንበር ላይ ቁጭ ስል ጃክና ዲክ አልጋው ላይ ዐረፍ አሉ ። አልጋው ተንጫጫ ። ጃክ በመገረም በእጁ ፍራሹን መታ መታ አደረገና ፡ «የማር ፍራሽ ነው ፡ ድምፁ ከእንቅልፍ ካልቀሰቀሰን ጥሩ መኝታ ነው ። በዚህም መወራረድ እችላለሁ ፡ ሣሩን ገዝታ ጨርቁን ራስዋ ሴትየዋ ናት የሰፋችው» አለን ።

«ለመሆኑ እንዴት ነው ያን ያህል ሰዓት ዝም ብላ ስትመለከትህ ቆይታ ቤቱን ለማከራየት ፈቃደኛ የሆነችው ? ምን ብታስነካት ነው ?» አለ ዲክ ።

«ለምን ትኩር ብላ እንዳየችን ገብቶሃል ? ሴትየዋ በሽሽት ላይ መሆናችንን ዐውቃለች ።»

«እንዴት ልታውቅ ትችላለች? እንደ እኔ ከሆነ የነገርካት ምክን ያት ሁሉ አሳማኝ መስለኝ ።»

«እስቲ ረጋ ብለሽ ትንሽ አስቢ ። በአቧራ የተሸፈነች ፔጆ መኪና ይዘን ነው የመጣነው ። የምንሔደው ወደ ፍሎሪዳ ነው ብለ ናል ። ከማኮን ወደ ፍሎሪዳ የምንሔድ ከሆነ ይሄን ሁሉ ጠመዝማዛ መንገድ መምጣት አስፈላጊ እንዳልሆነ ታውቃለች ። አሮጊትዋ ደደብ አትምሰልሽ ። ሽሽት ላይ እንዳለንና ለጊዜው መደበቂያ ቦታ እንደምንፈልግ ዐውቃለች ።»

«ታዲያ ለምን ..... » ብዬ መናገር ስጀምር ፡

«ገንዘቡን ፈልጋ ይሆናል ወይም ለተወሰነ ቀን ብቻዋን ከምት ሆን ከሰው ጋር መሆኑን መርጣ ይሆናል ። ብዙ ምክንያት ይኖራታል ። ትኩር ብላ ስታየኝ ስለ ማንነታችን ዐውቃለች ። ዶሎ መወሰን ግን አልሆነላትም ። በመጨረሻ ግን ፡ ጥሩ ገንዘብ ሲኖረን እንደሚችል በማመኑና የጠየቅችንን ያህል መክፈል እንደምንችል ስላወቀች ለአንድ ሰው ዐሥር ብር ጠየቀችን ። እርግጠኛ ነኝ ፡ መደበኛ ኪራዩ ከአምስት ብር አይበልጥም ።»

«ታዲያ ካወቀች ልታወራ አትችልም ?» አለ ዴክ በመረበሽ መልክ ።

«አታወራም ። ስለኛ ትወቅ እንኳ ጉዳይዋ አይደለም ። እኛ በደንብ ከተንከባከብናትና ጠባያችን ካማረ ዝም ትላለች ። በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ብዙዎቹ ስለ ራሳቸው ሥራ እንኳ ስለ ሌላ ሰው የሚጨነቁ አይደሉም ። ተማርን ያሉና ከተማ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ናቸው ሰውን የሚያጋልጡ ። በዚህ ክልል ያሉ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ጠባይ የለባቸውም ። ሴትዮዋ ትልቅ ሰው ናት ። በሕይወትዋ ብዙ ነገር አይታለች ፤ ስለዚህ የሚያስጨንቅ አይደለም ። ይልቅስ እዚህ ቁጭ ከምንል አካባቢውን እንመልከት ። በዚህ አካባቢ የምናየው እርሻ የሴትዮዋ ነው ። ብዙ ጭሰኛም አላት ። ከዚህ ትንሽ ሔድ ብሎም የውኃ ምንጭ እንዳለም ነግራኛለች ። ብናየው ጥሩ ነው» አለንና ተነሣን ።

ወደ እርሻው ቦታ እየተዘናናን ተጓዝን ። ቀኑ የተራዘመና ዕድሜአችንን በሙሉ በዚህ ቦታ የምንኖር መስሎ ተሰማኝ ። ስማዩ ላይ ምንም ደመና አይታይም ፡ ፀሐይዋ የወጣችው ስዚህ ሥፍራ ብቻ ይመስል መቀቱ በጣም ከፍተኛ ነው ።

እርሻው መኻል ገብተን በጸጥታ ቆም አልንና ጃክ በእጁ ወደ ሚያመለክተን ቦታ አየን ። ከኛ ራቅ ብሎ አንድ ትልቅ ጥቁር አሞራ ሊያርፍ ካለ በኋላ ፡ እንደ ገና ሽቅብ ወደ ላይ ወጥቶ ዛፎች ወደ አሉበት አመራ ።

«የዛፎቹ መጨረሻ ይታያችኋል? እዛ ከደረስን በኋላ እንመለሳለን ። ዴክ ! እግርህ እንዴት ነው ?» አለው ።

«ለሞት አያሠጋኝም ፤ ከተማ ውስጥ መድኃኒት ቤት ካለ ባለ ሳስቲኩን ፋሻ ገዝቼ አስርበታለሁ ።»

«ካላገኘህም ወይዘሮ ሮዛ በጨርቅ ታስርልሃለች ። የገጠር ሲቶች ማንኛውንም በሽታ የማከም የተፈጥሮ ችሎታ አላቸው » አለ ጃክ ።

ጃክ በሩቁ ካሳየን የባሕር ዛፎች አካባቢ ስንደርስ ፣ ከወገብ በታች ብቻ የሚያሰምጥ ሰፋ ያለ ምንጭ አየን ።

«ምንጩ ከወንዝ ጋር የሚቀላቀል ነው ?» ብዬ ጠየቅኩ ።

«እኔ እንጃ ከወንዝ ጋር የሚቀላቀል አልመሰለኝም ። ምናልባት ዝም ብሎ ፈሶ ሜዳ ውስጥ ሰርጎ ገብቶ ይቀር ይሆናል ። ብዙዎቹ በዚህ አካባቢ የሚገኙ ምንጮች እንደዚሁ በየሜዳው ሰርገው ገብተው የሚቀሩ ናቸው» አለኝ ።

ጃክ አካባቢውን ወዲያና ወዲህ ተመለከታቸው ። ከኛ በስተቀር የሰው ዘር አይታይበትም ፣ ጃክ ልብሱን ማወላለቅ ጀመረና ፣ «መግባቴ ነው!» አለን ።

«እዛ ውስጥ? ጭቃ ሞልቶበታል እኮ !» አልኩት በመገረም ።

ልብሱን ማወላለቁን እንደ ቀጠለ ፣ «ይሁና ቀዝቃዛ ስለሆነ ደስ ይለኛል ። ሕፃን በነበርኩ ጊዜ በምኖርበት አካባቢ የዚህ ዓይነት ምንጭ ስናገኝ ፣ ዋና እንለማመድበት ስለ ነበር ለትዝታውም ስል አሁን መዋኘት አለብኝ» አለኝ ።

ዲክ ተመለከተኝና ቁጭ ብሎ ልብሱን አወላለቀ ። እኔም ቁጭ አልኩና ሲጋራየን አቀጣጥዬ ሁለቱም ምንጩ ውስጥ ሲንቦጫረቁ ተመለከትኩ። ውኃው ውስጥ እንዳንዴ እየዘለሉ ፣ ሌላ ጊዜም ውስጥ ለውስጥ ሲዋኙ በፈገግታ ካስተዋልኩዋቸው በኋላ ሲጋራየን አጥፍቼ ልብሴን አወላልቄ ከድፍርሱ ውኃ ውስጥ ገባሁ ።

ከጠበቅሁት በላይ ይቀዘቅዛል ። አንድ ሁለት ጊዜ ከተንቦጫረቅሁ በኋላ ፣ በረዥሙ ተነፈስኩና በጀርባዬ በመንጋለል ዝም ብዬ ተንሳፈፍኩ ።

እንደ መሰለኝ ለሠላሳ ደቂቃ ያህል ውኃው ውስጥ ቆይተናል ። ጭቃ የተሞላበት ውኃ ቢታጠቡበትም ፣ ዕድፍ የሚያጠራ አይመስለኝም ነበር ። አሁን ገብቼበት ስወጣ ግን ሙልጭ አድርጎ እንደ ሚያስለቅቅ አየሁት ። ውኃው ያጠበልን ቆሻሻችንን ብቻ ሳይሆን ጭንቀታችንንና ፍርሃታችንንም ጭምር ነበር ። እርስ በርሳችን እየተላፋን ከተጫወትን በኋላ ፣ ከውኃው ወጥተን ሜዳው ላይ ጐን ለጐን በመተኛት ፀሐይ መሞቅ ጀመርን ።

ይህ ጊዜ በዚህ ዓይነት መልኩ ለዘለዓለም ቢቀጥል በጣም ደስ ይለኝ ነበር ። ለቦታው ምስጋና ይግባውና ጭንቀታችን ሁሉ እልም

ብሎ ጠፋ ። በዚች ሰዓት የሚሰማን የፀሐዩ ሙቀትና በሥቃችን መካከል ያለው መቀራረብና ጓደኝነት ብቻ ነው ። ሁላችንም በየአስ ምሮአችን ይህን የምናሰላስል መሰለኝ ። ምክንያቱም አንዳችንም ለመናገር አልሞከርንም ።

ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ፡ ተነሥተን እላያችን ላይ የተጣበቀውን አፈር አራግፈን ልብሳችንን ለባበስንና ያለ ምንም ንግግር ወደ ወይ ዘሮ ሮዛ ቤት መንገዳችንን ቀጠልን ። ከቤት ስንገባና ያረጀውን መው ጣት ስንጀምር ፡ ጃክ መምጣታችንን ለማሳወቅ ይመስል ፡ «ተመልሰን መጥተናል !» አሳት ። ሲትየዋ ግን ፡ ምንም መልስ አልመለሰችም ። ያረጀውን በመውጣት ክፍላችን ከደረስን በኋላ ፡ ሰው ነታችን ላይ ያለ ውን አፈር ለማስለቀቅና በፀሐይ የጋለውን ገላችንን ለማቀዝቀዝ መታ ጠቢያ ቤት በተራ እየገባን ታጠብን ።

ወደ ዋናው መኝታ ቤታችን ገብተን በሩን ቆለፍንና ግማሽ ጠር ሙስ ቮድካ በማውጣት እየተቀባበልን ከነጠርሙሱ ጠጣንና ልብላ ችንን አወላልቀን አንድ ላይ ተኛን ።

ሥስታችንም አንድ ላይ እንደጉተኛ የገፋፋን የወሲብ ፍላጐት አልነበረም ። በመኻላችን ያለው ግንኙነትና መቀራረብ አሁን ባለን በት ደረጃ እንድንገኝ አስገድዶናል ። እስካሁን ብዙ ችግርና ደስታ ዐጋራ አጋጥሞናል ። ምናልባትም ተመሳሳይ ፍርሃት ይዞናል ። በማ ንኛውም መልኩ ይሆን ተደስተንበታል ። የማስታውሰው በመኻላችን ያለው መቀራረብ አንዳችን አንዳችንን እንድንንከባከብ ረድቶናል ። ከሁለት ወንዶች ጋር በአንድ አልጋ ላይ በመተኛቴ ቅር አያሰኘኝም ። ወደ ፊትም አልጸጸትም ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ሥስታችንም እንቅልፍ ወሰደን ። ሰውነታችን ድቅቅ ብሎ ከእንቅልፋችን ተነሣን ። ከፍላ ችን መቀዝቀዝ በመጀመሩ መምሸቱን ዐወቅን ። ራታችንን መብላት ያለብን በመሆኑ ፡ ራት ለመብላት ወደ ከተማ እንደ ምንወጣ ለወይ ዘሮ ሮዛ ነገርናት ።

«ጥሩ ምግብ ለመብላት ከፈለጋችሁ ሐክሲ ምግብ ቤት ተመገቡ» አለችን ።

እኛም ወይዘሮ ሮዛ በነገረችን መሠረት ሐክሲ ምግብ ቤት ሔድን። ሐክሲ ምግብ ቤት ከጌምስኮክ ጋር ተመሳሳይ ነው ። የሁለ ቱንም ቤቶች ፕላን አንድ መሐንዲስ የሠራቸው ይመስል የቤቱ መመ ሳለል ብቻ ሳይሆን የውስጥ ዕቃዎቻቸው ሁሉ አንድ ዓይነት ናቸው ። ሌላው ቀርቶ ሽታው እንኳን ሳይቀር አንድ ነው። ልክ እንደ ጌምስኮክ አዲስ ሰው በጣላ ሱፐር ውስጥ ሲያወሩና ሲጫወቱ የነበሩ ሰዎች ጨዋ

ታችውን ቆም አድርገው አዲስ የመጣው ሰው ወንበር ይዘ እስኪቀመጥ የመመልከት ልምዱም ሐከሲ ምግብ ቤት አለ ። ስንገባ ሁሉም ተመ ለከቱንና ቦታ ስንይዝ የግል ጨዋታቸውን መጫወት ቀጠሉ ።

አስተናጋጅዋ ወደኛ መጣችና ፡ «እንደምን አመሻችሁ ፤ እን እባላለሁ ፤ ምግብ ፡ መጠጥ ወይስ ሁለቱንም ላቅርብላችሁ» ብላ እየተዝናናች ጠየቀችን ።

«ሁለቱንም እንፈልጋለን ፡ መጀመሪያ ግን ጉሮሮአችንን እንዲ ያረጥብልን ቮድካ አምጪልን ፤ የምግብ ዝርዝር ካላችሁ የምንበላ ውን ምግብ እንምረጥ» አላት ጃክ ።

«የምግብ ዝርዝር አለን ። አካባቢያችን ይሆን ያህል ገጠር መሰ ለህ እንዴ? ለጥያቄዬ መልስ አልፈልግም» አለችንና ወዲያው የውሻ ጆሮ የሚያክክሉ ሦስት ወረቀቶች ጥላልን ሔደች ። ወረቀቶቹ በዘይት የተጨማለቁና ከማስታወሻ ደብተር ላይ የተቀደዱ ሲሆኑ ፡ የምግብ ዝርዝር በእጅ ተጽፎባቸዋል ። ወረቀቶቹን ለመውሰድ አሰብኩ ፡ ግን በወረቀቶቹ መጨረሻ መስመር ላይ ይሄን የምግብ ዝርዝር ወረ ቀት መውሰድ የተከለከለ ነው የሚል ተጽፎበታል ።

እን መጠጣችንን ይዛልን መጣችና ፡ «መብላት የምትፈልጉትን ምግብ እስካሁን አልወሰናችሁም?» አለችን ።

«የዓሣው ሾርባ እንዴት ነው ?» አልኩዋት ።

«በጣም ጣፋጭ ነበር ። ግን በአሁኑ ሰዓት ማግኘት ላያስቸግር አይቀርም ።»

«የሥጋውስ ሾርባ እንዴት ነው ?» አለ ጃክ ።

«የቲማቲም ሾርባ ይሻላችኋል ፡ በጣም ጥሩ ነው ።»

«ኮተሌቲውስ ?» አለ ጃክ ።

«ባሪሬ በልቶዋለሁ ፡ በጣም ጥሩ ነው ።»

«ቅመም አለው ?» አለ ዲክ ።

«አዎ! በመጠኑ አለው ።»

ሦስታችንም ሾርባውንና ኮተሌቲውን እዘን መመገብ ጀመርን ። ሰለ ራበን ዝም ብለን በላን እንጂ ፡ እን እንዳሰብን ምግቡ ጥሩ አልነበ ረም ። የሚገርመው ከምግብ በኋላ የቀረበልን ቡና ቀዝቃዛ ነው ። መጠጡ ግን ጥሩ አገናንቶናል ። ሁለት ሁለት በደግምን ቊጥር እን ዳንድ ዙር በባለቤቱ ተጋበዝን ። ለእንግዳ መቀበያ መሆኑ መሰለኝ ። ጥሩ ባህል ነው ።

አን ሰመጨረሻ ጊዜ መጠጥ ልቅቀዳልን ስትመጣ ፡ «ባንኩኣው ውስጥ የቆመው ሐክሲ ነው ?» ብሎ ጃክ ጠየቃት ።

«አይደለም ፡ ሐክሲ ብልጥ ነው ። ቤቱን ሽጦልን ለተሻለ ሥራ ወደ ካሊፎርኒያ ሔዶአል ። የድሮ ስሙን መለወጡ አስፈላጊ ሆኖ ስለ አላገኘነው ነው እሁንም በሐክሲ ስም የሚጠራው ።»

«የቡና ቤቱ ባለቤት ባልሽ ነው ?»

«እሱ የሚለው እንደዛ ነው ። ስለዚህ አዎ ባሌ ነው » አለች እየሣቀች ።

ጃክ ከመቀመጫው ተነሥቶ ወደ ባንኩኣው በመሔድ ከሰውየው ጋር ተጨባበጠ ። ራሳቸውን ጥምመው ለትንሽ ጊዜ ካወሩ በኋላ ፡ ጃክ ገንዘብ አውጥቶ ሲሰጠው ተመለከትኩ ። ይሽን የገንዘብ ስጦታ ያየሁት እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም ።

ጃክ ወደኛ ተመለሰና ፡ «አንን እየተመለከተ ይዘነው የምንሔደው ድድስት የቀዘቀዘ በራ ልታዘጋጂልን ትችያለሽ» አላት ።

«በደስታ ! ሌላስ ?» አለች ከፈገግታ ጋር ።

«ለአሁኑ ከበረው በስተቀር አንፈልግም ። ምግባችሁ ጥሩ ነው ፡ ስለ ሙሉተንማይሽ በጣም እናመሰግናለን ።»

«ውሽታምም ቢሆን ፡ መልክ መልካም ወንድ ንወዳለሁ» አሰች ገና ያለብንን ሒሳብ ነግራን ፡ «ገንዘቡን ለሰውየው ስጡት ፡ እኔ ስቀበል ደስ አይለውም ፡ ይዛብኝ ትጠፋለች ብሎ ያስባል» አለችን ።

ጃክ የተባለውን ገንዘብ ለሰውየው ከፈለና ቢራችንን ይዘን ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት መንገዳችንን ቀጠልን ።

«ጥሩ ሰዎች ናቸው» አለ ዲክ ።

«አዎ ! ብዙዎቹ ጥሩዎች ናቸው ። ጥቂቶቹ ደግሞ ልክ ሌላው ቦታ እንደሚገኙ መጥፎ ሰዎች ናቸው » አለ ጃክ ።

«ከባንኩኣው ጀርባ ቆሞ ለነበረው ሰውዬ ገንዘብ ስትሰጠው አይቼሃለሁ» አልኩት ።

«አይተሻል ? አዎ ! እኛን የሚጠይቅ ሰው ከሎጣ በፍጥነት ወይዘሮ ሮዛ ቤት ስልክ እንዲደውልልኝ ጉርሻ ሰጥቼዋለሁ ።»

«ሰውየውን ታምነዋለህ ?» አለ ዲክ ።

«ምንም ምርጫ የለንም ። አለን እንዴ ? ሰውየውን ሳየው ይሄን

ያህል ተንኰለኛ አይመስለኝም ። አሁን ይሄን እንርሳውና እንዝናና ። ያ የውሻ ልጅ ይሄን ጊዜ በየቦታው ስለኛ በመጠየቅ ላይ ነው ።»

ወይዘሮ ሮዛ በረንዳዋ ላይ ስትንጐራደድ አየናት ። ጃክ መኪና ችንን ከቤቱ አጠገብ አቆማትና ወረደን ። ዲክ ከሐከሲ ቡና ቤት ያመጣነውን ቢራ ተሸክሞ ሁላችንም ወደ ቤት ገባን ።

«ደህና አመሹ ወይዘሮ ሮዛ ! ዛሬ ጨረታዋ ደምቃ ወጥታለች ፣ ጥሩ ምሽት ነው» አለ ጃክ ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ ።

«አዎ ! ደስ የሚል ምሽት ነው ። ሳሎን መቀመጥ ከፈለጋችሁ በቂ ወንበር አለ» አለችን ። ባለችን መሠረት በየወንበሩ ላይ ቁጭ አልን ።

«ሲጋራ ባጨስ አይረብሽዎትም ?» አልኩኝ ።
«ምንም ችግር የለም ፣ እኔም አጨያሽ ነኝ ።»

ለወይዘሮ ሮዛ በቅድሚያ ሲጋራ ሰጠሁዋትና ሁላችንም አውጥተን ማጨስ ጀመርን ። ሴትየዋ እንደ አባባልዋ መደበኛ አጨያሽ አይደለችም ። ጭሱን ወደ ውስጥ መሳብ ሲገባት ወደ ውጭ እፍ ትለዋለች ። «የቀዘቀዘ ቢራ ይዘን ስለ መጣን አብረውን ቢጠጡ» ብሎ ጃክ ጠየቃት ። ምንም አላቅማማችም ። አራታችንም ቢራችንን እየጠጣንና ሲጋራችንን ቡልቅ እያደረግን ፣ የባጡን የቆጡን ማውራት ጀመርን ።

ከትንሽ ጊዜ ጨዋታ በኋላ ፣ ወይዘሮ ሮዛ ስለ ሕይወትዋ እንድትነግረን በተዘዋዋሪ መንገድ ጠየቃት ። የሕይወት ታሪኳን እንድትነግረን መጠየቁ አስቸጋሪ አልነበረም ። እንዲያውም ሴትየዋ ታሪኩዋን ለመናገር ይህን አጋጣሚ ስትጠብቅ የቆየች ትመስላለች ።

ሴትየዋ ጀርጂያ ከተማ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከሲፈንሰን እንደተዋወቀችውና ለመጋባትም ወዲያው ተስማምተው የሷን ቤተሰብ ለማየትና ለመተዋወቅ አላባማ አብረው መሔዳቸውን ፣ ከዚያም ተመልሰው እንደ ተጋቡና ፣ በዚሁ ቤት ውስጥ ከሲፈንስ እናት ጋር አብረው እንደኖሩ ፣ ከአማቲቱም ጋር በየጊዜው ይጣሉና ይጨቃጨቁ እንደ ነበር አወራችልን ።

«ሙቼም ያለፈ ነው ፣ ቢሆንም አማቴን በክፉ ማንሣት የለብኝም» አለች ። ሴትዮዋ አንዴ ወሬ ከጀመረች የምታቆም አትመስልም ። ሁለተኛው ቢራ ሲሰጣት በደስታ ተቀብላ ሁለት ጊዜ ተጐነጨችና የጀመረችውን ታሪክ ለመጨረስ አፉዋን በሁለቱም እጆችዋ ጠረገች ።

ከባልዋ ስድስት ልጆች ወልዳ እንደ ነበርና የመጀመሪያው ወንድ ልጅዋ ገና ከመወለዱ፥ ሁለተኛዋ ሴት ልጅዋ ደግሞ፥ ዐተወለደች በሦስት ዓመትዋ በብርድ በሽታ እንደ ሞቱባትና የመጨረሻውም ወንድ ልጅ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጦር ሜዳ ሔዶ የት እንደ ገባ ሳይታወቅ መቅረቱን አጫወተችን ። እንደዚሁም የቀሩት ሦስት ሴቶችም ባል እያገቡ ጥለዋት እንደ ሔዱና አልፎ አልፎ በገና በዓል እየመጡ እንደሚጠይቁዋት ነገረችን ። ምንም መልስ ሳንሰጥ በዝምታ አዳመጥናት ።

«ስለ ራስዎ ዘመዶች አላወሩልንም» አለ ጃክ ።

«የኔ ዘመዶች? ግማሹ ሞቶአል፥ ግማሹም ወደ ተለያየ አገር ሔዶአል ። ከዘመዶቼ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ሁሉ ተቋርጦአል » አለችው ።

«በአሁኑ ዘመን ይሄ የተለመደ ነው ። ሁሉም ከየዘመዱ እየተራራቀ ነው» አለ ዲክ ።

«ሊሆን ይችላል ፤ በኔ በኩል ግን ሰው ከዘመዱ ተለያይቶና ተራርቆ መኖሩ በጣም ያሳዝነኛል ። ያደኩበት መንደር፥ ቤተሰቦቼና ባለቤቴ ሁል ጊዜ በሐሳቤ ይታዩኛል ። በአካል መተያየት የሚባል ነገር ግን አብቅቷል ። ሌላው ቢቀር ይጽፉልኝ የነበረው ደብዳቤ እንኳን በአሁኑ ጊዜ ቀለሙ እየደበዘዘ ወደ መጥፋቱ ደረጃ ተቃርቧል ። ፎቶግራፎቻቸውም ቀለማቸውን እየለወጡ ነው ። በርግጥ ማንም ሰው በነበረበት ሥፍራ አይቆይም ። ቀደም ሲል ስም ትልቅ ነገር ነበር ። ሰዎች ማን መሆንህንና የማን ቤተሰብ እንደ ነበርክ ያውቁ ነበር ። ጊዜ እየተራዘመ ግማሹ ሲሞት፥ ሌላው መኖሪያውን ሲቀይር መጠሪያ ስም ዋጋውን እያጣ ሔደ ። ይሄ እያሳዝናችሁም ?»

«ወይዘሮ ሮዛ ፥ ይሄ አዲስ ነገር አይደለም ፥ ጊዜ እየተለወጠ ፥ አሮጌው በአዲስ እየተተካ፥ የሰዎች የአኗኗር ዘዴ እየተለወጠ የሚሔድ ስለሆነ ወደድንም ጠላንም አዲሱን ነገር መቀበል አለብን» አልኩ ።

ኩስተር ብላ፥ «አንቺ ወጣት ስለሆንሽ ዘመናዊውን ልትቀበይ ትችያለሽ ። እኔ ግን አልቀበልም ፥ መቀበልም የለብኝም ። እንደእኔ ፍላጐት ቢሆን ኑሮ ልጆቼ ከኔ ሳይርቁ አጠገቤ ሆነው ይህን ያለኝን መሬት እያለሙ ቢቀመጡና የልጅ ልጆቼን እያሳደግሁ ብኖር ደስ ባለኝ! ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለመሆኑ እንደተመኘሁት ሊሆን አልቻለም ። ያም ቢሬ በዛና እንቅልፍ እንቅልፍ አለኝ ። ይቅርታ አድርጉልኝና እናንተ እስከ ፈለጋችሁት መጫወት ትችላላችሁ» አለችንና ብድግ አለች ።

ሁላችንም ተነሣን። ዲክ መንገድ በመልቀቅ ያዝ አድርጎ መራት ። ፈገግ አለችና ፣ «የማረጋግጥላችሁ፣ እቤት ውስጥ ምንም ቁንጫ ስለሌለ ጥሩ እንቅልፍ ይወስዳችኋል ፣ በሉ ደህና እደሩ» ብላን መኝታ ቤትዋ ገብታ በሩን ዘጋች ።

ወንዶቹ ወደ ቀድሞው ወንበራቸው ተመልሰው ሲቀመጡ፣ እኔ ወይዘሮ ሮዛ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ ። ወንበሩ አሁንም እንደሞቀ ነው ። ፀይኔን ከደንኩና ወደፊት ወደኋላ ተወዛወዝኩ ። ማንም ባይናገር ደስታዬ ነው። ባጋጣሚም ማንም አልተናገረም። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ቢራችን በማለቁ ወደ መኝታ ክፍላችን ተያይዘን ገባንና በሩን ቆለፍን ። የወይዘሮ ሮዛ ማንኰራፋት አለንበት ድረስ ይሰማል ። ጫማችን ሲፈሀ ሰምታ እንዳትንቀሳቀስ ያለምንም ንግግር ቀስ ብለን ወደ አልጋችን አመራን ። የዛንለት ማታ ሥስታችንም እራቁታችንን ሁነን አንድ ላይ ተኛን ። ሁለቱም ወንዶች እቅፈውኝ መተኛቴ ደስ አለኝ ። ሌላ ጊዜም ቢሆን ብቻዬን መተኛት አልፈልግም ። የሣሩ ፍራሽ እየተንኰሻኰሸ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ ። ባላለፍነው ጊዜያት ውስጥ ቀኑ ብሩህ ሌሊቱ ጨረቃማና ደስ የሚል በመሆኑ ሁላችንም በብዙ ነገሮች ተለውጠናል ። በውስጣችን የሚሰማን ነገር አለ ። ምን እንደሆነ ግን አላወቅነውም ።

የየቀኑ እንቅስቃሴያችን በጣም ውሱን ነው ። አንድ ላይ እንተኛለን ። የልብስ ሻንጣዬ በሌላኛው መኝታ ቤት ተቀምጦአል ። በጥዋት ተነሥቼ አልጋውን እንዳተኮተብት አስመስዬ ልብሱን አመሰቃቅለዋለሁ ። ይህ ሁሉ ወይዘሮ ሮዛ ሥስታችንም አንድ ላይ የምንተኛ መሆናችንን እንዳታውቅብን የምናደርገው ነበረ ።

ጥዋት ጥዋት በሁለት ሰዓት ከመኝታችን ተነሥተን ልብሳችንን በመለባበስ ፣ ቁርሳችንን ከወይዘሮ ሮዛ ጋር ለመብላት ወደ ምግብ ቤት እንሔዳለን ። ሴትየዋ የምታቀርብልንን ቁርስ ጥርግ አድርገን የምን በላ በመሆኑ ትደሰትብታለች ። ከቁርስ በኋላ መኪናችንን ይዘን ለወይዘሮ ሮዛ የሚያስፈልጋትን የምግብ ዓይነትና ለኛም የሚያስፈልጉንን አንዳንድ ዕቃዎች ለመግዛት ወደ ሱቅ እንሔዳለን ። ብዙ ጊዜ ከሱቅ መልስ የወይዘሮ ሮዛን ማቀዝቀዣ ቢራ እንሞላዋለን ።

በሁለተኛው ቀን ቆይታችን፡ ከከተማው ነዋሪዎች ጋር መተዋወቅ ችለናል ። በሱቆች ፡ በነዳጅ ማደያዎችና በመጠጥ ቤቶች በተዘዋወርን ቁጥር ከምናገኘው ሰው ጋር ሰላምታ እንለዋወጣለን ።

ሐክሲ ምግብ ቤት ስንገባ ሁልጊዜም አንድ ሳንድዊች አዘጋጅታ ትጠብቀናለች ። ሁሉም በዚህ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች ለኛ ጥሩ ሆኑልን ።

ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት ደርሰን የገዛነውን ዕቃ ካስቀመጥን በኋላም ለንድዊችና ቢራችንን በመያዝ ወደ ምንጩ ሐደን ጭቃ ውስጥ ስንቦ ራጨቅ እንውልና ቢራችን መቀዝቀዝ ሲጀምር ከሳንድዊች ጋር እያጣ ጣምን ምሳችንን እንበላለን ።

በተለመደው ፕሮግራማችን አንድ ቀን የገዛነውን ዕቃ ካስቀመ ጥን በኋላ፡ ወደ ምንጩ ከመሔዳችን በፊት ጃክና ዲክ ሳንድዊችና ቢራ ውን ፡ በዚያ ሄሚ እራሱን ለመከላከል በተጠቀመበት ቀዳዳ ቦርሣ ውስጥ ከተው ያዙና ወደ መዋኛችን ተጓዝን ። እንደ ደረስን ጃክና ዲክ ጉድጓድ ፈልገው ቦርሣውን ጣሉት ። ከሰዓት በኋላ ወይዘሮ ሮዛ ቤት እንደ ተመለስን እኔ መጽሐፌን ከአቋረጥኩበት በመነሣት ጸፍ ኩና እሁን ከምንገኝበት ሁኔታ አደረስኩት ።

ጃክና ዲክ ፡ የኛን ፔጀና የወይዘሮ ሮዛን ፕሴይማውዝ መኪና አጠቡ ። መኪና አጠባቸውን እንደ ጨረሱ ልብሶቻችንን እና ጌጣጌ ጡን በአራት ቦርሣ አደረጉት ። በሚቀጥለው ቀን ጃክና ዲክ እኔን ወይዘሮ ሮዛ ቤት ትተው ለመኪናችን ነዳጅና አስፈላጊውን የመኪና ዘይት ለመሙላት ወደ ከተማ ሔዱ ። ከተማ መልስ ጃክ ሊያዝናቸው መሣሪያዎች የሚበቃ ጥይትና ለመሣሪያዎቹ መወልወያ የሚሆን ዘይት ይዞ መጥቶ ሁለቱም ወንዶች ለአንድ ሰዓት ያህል መሣሪያዎ ቹን እየፈታቱ ሲመለሙለ ቆዩ ።

ሌላው ከከተማ ይዘውት የመጡት ንጹሕ ውኃ የመሰለ ሁለት ጠርሙስ መጠጥ ነበር ። ይህ መጠጥ ጅርጅያ ውስጥ በየቤቱ የሚዘ ጋጅ መሆኑን ጃክ ነገረኝ ። ከመጠጡ ትንሽ ቀመስ ሳደርገው ጉሮሮ ዬን አቃጥሎኝ ሲወርድ ተሰማኝ ። እርግጠኛ ነኝ ፡ ይኽ መጠጥ መዶ በመዶ አልኮል እንጂ የእህል ዘር ያለበት አይመስለኝም ።

የዛን ቀን ማታ ከሐክሰ ምጣብ ቤት የተለመደውን ቢራችንን ይዘን በመመለስ ፡ ከወይዘሮ ሮዛ ጋር እየተጫወትን ከጠጣን በኋላ ለመተኛት ተሰነባብተን ወደ ክፍሳችን ተመለስን ።

መኝታ ክፍላችን ከተመለስን በኋላ ፡ ወንዶቹ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብለው ቀን ይዘውት የመጡትን መጠጥ መጠጣቱን ተያያዙት። እኔ ግን ስቀምሰው ስላቃጠለኝ መጠጣት አልፈለኩም ። ጠርሙሱን እን ዳገባደዱ ወደኋላቸው ፍንግል ፍንግል ፡ ብለው እንቅልፋቸውን ተያያ ዙት ። ጫማቸውን አወላለቅሁና አያተሸትኩ አልጋ ላይ አወጣ ቸው ። ልብሳቸውን ለማውለቅ በሚመቻሉ ከንለብሳቸው ንዲተኙ ትቼ ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቻዬን ለመተኛት ወደ ሌላ ከፍል ሔድኩ።

ጠዋት መኝታ ክፍላቸው ስገባ ነቅተው ማን ብዙ እንደ ጠጣና

ማን ቶሎ እንደ ሰከረ ጉራቸውን ይነዛሉ ። በተለይ የዲክ ይሽን ያህል መለወጥ አስገረመን ። ሦስታችንም አንድ ላይ በመሆናችን ዲክ እየ ተለወጠ ሔደ ። መለወጡ ውስጣዊ ብቻ ሳይሆን ውጫዊም ነው። ቀድሞ ከነበረው ቅጥነት አሁን የባሰ ቀጥኖአል ። ግን ጥንካሬ ይታይ በታል ። ፊቱም በፀሐዩ ምክንያት ወደ መጥቆሩ ነው ። በተለይ ዐይኑ ወደ ውስጥ ተሰርጉዷል ።

መለወጡ በጣም ግልጽ ነው ። ድሮ አርምጃ ለመውሰድ ዝግ የሚልና ጭምት ነበር ። አሁን ግን፡ ወሲብ እንድናደርግ የሚገፋፋኝ ፡ መኪናውን የሚነዳውና ፡ ሐክሲ ምግብ ቤትም ትዕዛዝ የሚሰጠው እሱ ሆኖአል ። እንዲያውም የወደፊት ጉዞአችን ምን ሊሆን እንደ ሚገባው ሐሳብ ሁሉ ያቀርብ ጀመር። የወሳኝነት ጠባይ እየተላበሰ መጣ። በመገረምና በመደነቅ ተመለከትኩት ። ከዚህ በፊት የማላውቀው አዲስ ሰው ሆነብኝ ።

እኔና ጃክ ብቻችንን በሆንበት ሰዓት፡ በዲክ ላይ ያየሁትን ለውጥ አንሥቼ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ጠየኩት ። የተለመደ ፈገግታውን እያሳየኝ፡ «ለምን በደንብ እያወቃት ነው ። በዚህ መድረክ ውስጥ የሱ ሚና ምን እንደሆነ ለማወቅ ዕድሉን እየሞከረ ነው» አለኝ ።

መለወጡን ከወደደው በኔ በኩል ምንም ቅር አይለኝም ። እኔስ ብሆን ምን ያህል ተለውጫ ይሆን? ማወቅ ግን አልቻልኩም ።

የቆይታችን ቀናት እንደ ጥሩ ሕልም ወርቃማ ሆኑ ። የምናሳል ፈውም እያንዳንዱ ሰዓት ባለፉት ጊዜያት ያጋጠመንን መከራ እንድ ንረሳ ረዳን ። እርግጥ ምን ጊዜም ቢሆን በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ ያለን ስለመሆናችን መረጃዎች እንፈልጋለን ። ማሳደዱ ጋብ ስላለ አቁ ሚል ማለት እንዳልሆነም እናውቃለን ።

የዚህ ዓመት ግና እሑድ ለት የሚውል በመሆኑ ፣ርብ ለት ነዳጅ ማደያ አጠገብ ከሚገኘው ሱቅ ለግና በዓል የሚሆን ጽድ ገዛንና ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት ይዘነው ገባን ። ወይዘሮ ሮዛ ለጽዱ ማስጌጫ የሚሆን ጌጣጌጥ ለኖሪት እንደሚችል እርግጠኞች ነበርን ። ምክንያቱም እንደ ወይዘሮ ሮዛ ዐይነት ሰው፡ በአንድ የገና በዓል የተገዛን ጌጣጌጥ ጊዜው አልፎበታል ብላ የምትጥል አይደለችምና ።

የዛን ቀን ሐክሲ ምግብ ቤት አምሽተን ተመለስንና የገና ዛፋች ንን አስጊጠን እንደ ጨረስን ራሳችንም ያዘጋጀነውን ዛፍ እየተመ ለከትን ፡ ለበዓሉ ዋዜማ የገዛነውን ወይን ጠጅ መጠጣት ያዝን ። እየጠጣን አንዳንድ ቀልዶችን በመደባለቅ ያለፈውን ዓመት የገናን በዓል እንዴት እንዳሳለፍነው ተራ በተራ ተረከን ። የገናን በዓል እንደ

ዚህ ባለ ሞቃት አካባቢ ማሳለፉ የመጀመሪያዬ በመሆኑ ሁሉም ነገር አዲስ ሆነብኝ ። እንዴትስ ተብሎ በገና ለት ምሽት ዕራቁቴን ሁለት ወንዶች መኻከል የሣር ፍራሽ ላይ ልተኛ?

የምጠጣው ወይን ጠጅ ትካዜዬንና ትዝታዬን አስረስቶኝ መዝ ናናትና መጫወት ቀጠልኩ ። ወይዘሮ ሮዛ ደስ እንዲላት የገና በዓልን በማስመልከት በልጅነታችን የምንዘምረውን መዝሙር ዘመርን ። ወይዘሮ ሮዛ በዚህ የበዓል ዋዜማ ምሽት በጣም ተደስተች ። ለመተኛት ከፍላችን ሔድንና አልጋችን ላይ ጋደም ብለን በሹክሹክታ ስለ መንገዳችን ጉዳይ ተነጋገርን ። የበጎሉን ቀን አብረን እንድናሳልፍ ወይዘሮ ሮዛ ጠይቃን ስለነበር ፣ በዓሉን እዚህ ውለን ሰኞ ዕለት ለመሔድ ወሰን ። በአሁኑ ሰዓት ለወጪ የሚያስፈልገንን ያህል ብር ይዘናል። ጃክ እንዳለን ከሆነ ወደ ሚያሚ የሚወስደውን ቀጥታ መንገድ ተከትለን ከምንሔድ በአጻራሮ መንገድ ሔደን ረቡዕ ወይም ሐሙስ ሚያሚ መድረስ እንደምንችል ነው ።

ባሳለፍናቸው ቀኖች ምንም ችግር ያላጋጠመን በመሆኑ፣ ወደፊትም ችግር ይገጥመናል ብለን ስለአላሰብን የጃክ ሐሳብ ጥሩ ሆኖ አገኘነው ። ቅዳሜ ጥዋት ቁርሳችንን ከበላን በኋላ ፣ ለወይዘሮ ሮዛ የሚሰጥ ስጦታ ለመግዛት ከተማ ወጣን ። ከተማዋ ትንሽ በመሆንዋ የምንፈልገውን ዐይነት ዕቃ ለመግዛት ባንችልም፣ እኔ የአልጋ ልብስ ወንዶቹ ሽቶ ገዙላት ።

የከሰዓት በኋላውን የዋና ፕሮግራማችንን ለመሠረዝ ስለ ተስማማን፣ የገዛነውን የስጦታ ዕቃ ለመስጠት በቀጥታ ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት ሔድን ። ሰዓቱ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሆኖአል ። ወደ ቤት ገብተን ወደ ክፍላችን የሚወስደውን ደረጃ ስንወጣ ወይዘሮ ሮዛ ማድ ቤት ሆና «ሚስተር ሲመንስ» ብላ ተጣራች ።

ጃክ ደረጃውን ወርዶ ማድቤቱ ሲደርስ፣ «ሚስተር ሲመንስ ፣ ከሐከሲ ቡና ቤት ስልክ ተደውሎልህ ነበር» ስትለው ሰማን ። በዚህን ጊዜ ዲክ ዐይኑን አፍጥጦ ተመለከተኝና ዕቃዎቹን እናዘጋጅ አለኝ ።

ጃክ ደረጃውን ወጥቶ እክፍላችን ገብቶ ከቦርሣው ውስጥ ሁለት ሽጉጥ አወጣና አንዱን በጃኬቱ ኪስ ፣ ሌላኛውን በወገቡ ሽጦ ዕቃ ማዘጋጀቱን እየረዳን፣ «ሁለት ሰዎች ሐከሲ ቡና ቤት ሔደው ስለእኛ ሲጠይቁ እንደነበር ነው ሰውዬው የደወለልኝ። እንደ አለባበሱ ከሆነ ሰዎቹ የአንቶኒዮ ሮሲ ሰዎች አልመሰሉኝም ፖሊሶቹ ናቸው» አለና ፣ «እንዲያውም አንደኛው የክልሉ ፖሊሶች አዛዥ ሳይሆን አይቀርም»

ሲል አከለበት ። ይሀን ሲነግረን ለብዙ ጊዜ ረስቸው የነበረው ፍርሃት ተመልሶ መጣብኝ ።

«ሰውዬው እንዳለው ከሆነ ምንም ነገር ስለኛ አልነገራቸውም»

«ሊነግራቸውም ላይነግራቸውም ይችላል ፤ ሆኖም ከከተማ ሰው አንዱ ይነግራቸዋል ። በዚህ እርግጠኛ መሆን አንችልም ።»

«የሁለታችሁንም ፎቶግራፍ ይዘዋል ፣ በአጠቃላይ ስለኛ ሁኔታ በደምብ ዐውቀዋል» አለ አሁንም ጃክ ።

«ግን እንዴት እዚህ ድረስ ሊከተሉን ቻሉ?» አልኩኝ ።

«እኔ ከሚያሚ የመጣሁ መሆኑን በማወቃቸው ወደዚሁ ይሔዳል ብለው ገምተው ነው»

«አንተም ፣ እኛም የፈጸምነው ልክ እነሱ እንደ ገመቱት ነው ። ብቻ ወይዘሮ ሮዛ ቤት መሆናችንን ያወቁ ይሆን?» አለ ዲክ ።

«ይኸን አትጠራጠር ፤ እስካሁን አንዱ ነግሮአቸው ይሆናል»

«ለምን ብለው ያጋልጡናል? ምን አደረግናቸው?» አልኩኝ ።

«ሽልማት ለማግኘት ፣ ወይም መኪና ይዘን እንደ ልባቸን ገን ዘብ ስንረጭ አይተው በመቅናት ፣ ወይም የሚደርስብንን ነገር ለማየት በመጓጓት ። ብዙ ምክንያት ሊኖር ይችላል» አለን ጃክ ትከሻውን እየነቀነቀ ።

«ከዋናው ከተማ የመጣና የክልሉ የፖሊሶች ኃላፊ ነው ሲሉኝ? ግን እኮ ሁለት ብቻ ከሆኑ ብቻቸውን ሊይዙን አይሞክሩም ። የሰው ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል» አለ ዲክ ።

ጃክ ዲክን በእንክሮ ተመለከተና ፣ «ብዙ ነገር እየተማርክ ነው። በሙያው እንደ ሠለጠነ ሰው ማሰብ ጀመርክ? ልክ ነህ ብቻ ሊይዙን አይሞክሩም ። ስለዚህ የሚፈልጉትን የሰው ኃይል እስኪ ያሰባስቡ ድረስ የተወሰነ ጊዜ አለን ። ሁሉም ዕቃ ተዘጋጀ? በጣም ጥሩ! እናንተ ቦርሣዎችን ይዛችሁ በር ላይ ጠብቁን ፤ እኔ መኪናዋን ላምጣ» ብሎን ወጣ ።

ቦርሣችንን እኔና ዲክ ተሸክመን ደረጃውን ስንወርድ ወይዘሮ ሮዛ የሚድቤቱን በር ተደግፋ ዝም ብላ ትመለከተናለች ። ጃክ መኪናዋን ወደበሩ ድረስ አስጠጋና ወርዶ ቦርሣዎችን እየተሸከመ ወደ ውጭ አውጥቶ መኪናው ውስጥ አስቀመጠና ተመልሰን ወደ ቤት ገባን ።

«ወይዘሮ ሮዛ የገናን በዓል አብረን ብናሳልፍ ደስ ይለን ነበር ፤ አሁን ግን ከመሐድ በቀር ሌላ ምርጫ የለንም ፣ እና መሐዳችን ነው» አለ ጀክ ፊገግ ለማለት እየሞከረ ።

«አዎ! ይገባኛል ፤ ለመቆየት የሚያስችል ምርጫ ያላችሁ አልመሰለኝም» አለችን ።

«ወይዘሮ ሮዛ ለገና በዓል ያዘጋጀናት አነስተኛ ስጦታ አለችን ። ስለ አስተናገዱን በጣም እናመሰግናለን» አለ ዲክ ።

«ያሳዩንን መልካም ትብብርና ደግነትዎን ምንጊዜም አንረሳውም» አልኩኝ እኔም በበኩሌ ።

ለስጦታ ያዘጋጀነውን አወጣንና በእጃችን ይዘን ቆምን ። «ሳሎን አስቀምጡት» አለችን ፊትዋ በሐዘን ተሞልቶ ።

እንዳለችን ሳሎን ወስደን ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥነውና ወደ ውጭ ወጥተን መኪናችን ውስጥ ገባን ። ጀክ የመኪናውን ሞተር አስነሥቶ መንገዳችንን ቀጠልን ። ወደኋላ ዞር ብዬ ስመለከት ወይዘሮ ሮዛ እጆችዋን አጣምራ ልክ ምስል መስላ ቆማለች ።

ጀክ ወደግራ መታጠፍ ሲጀምር፣ «በከተማ ውስጥ ነው እንዴ የምንሔደው?» አለ ዲክ ።

«አዎ! አቋራጭና በፍጥነት ለመንዝ የምንችለው በከተማው ውስጥ ሰናልፍ ነው ። ምናልባት መንገዱን ዘግተው ካልጠበቁን» ሲል ጀክ መለሰለት ።

ወደከተማው በፍጥነት እየሔድን ሳለ ቢድንገት ጀክ ፍሬን በመያዙ መኪናዋ ወደ አንድ ወገን ዘንበል አለችና ከብዙ መንሸራተት በኋላ ቆመች ። በግምት ከአምስት መቶ ሚትር ርቀት ላይ አንድ የግልና የፖሊስ ጅፕ መኪናዎች መንገዱን በ«V» ቅርፅ ዘግተው ቆመዋል ። በመኪናዎቹ ኋላ ጠመንጃ የያዙ ሰዎች ይታያሉ። ከመንገዱም በስተቀኝና በስተግራ ያለው ክፍት ቦታ ለመኪና የማያመችና የድንጋይ ክምር የበዛበት ነው። ጀክ የመኪናዋን መሪ እየጠመዘዘ ወደ ፊት ወደኋላ ፣ ወደፊት ወደኋላ ከተንቀሳቀሰ በኋላ አዙሮ ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት ተመለሰን ። ሴትየዋ እንደምንመለስ እርግጠኛ ሆና መሰለኝ ስንሰናበታት በነበረችበት ቦታ ቆማ ነው ያገኘናት ።

ከወይዘሮ ሮዛ ቤት በስተቀኝ በሚወስደው መንገድ ወደ ሦስት መቶ ሚትር ርቀት ላይም ሁለት ትራክተሮች መንገዱን ዘግተው መቆማቸውንና ሁለት ሰዎች ከሁዋላ እንዳሉ አየን ።

«ተከበናል» አልኩኝ ።

«ተጨማሪ ሰው ፣ መኪናና የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያ ካገኙ በኋላ ወደኛ ለመምጣት አስበው ነው ። በእርሻው እናቋርጥና አጥሩን ጥሰን እንሒድ» አለ ዲክ ።

«ከዚያ በኋላስ? ዋናው መንገድ ለመግባት ቢያንስ አምስት ኪሎ ሜትር መጓዝ አለብን። ሜዳው ደግሞ ድንጋያማ ሲሆን እንደገና መንገዱን ዘግተው ሊጠብቁን ይችላሉ» አለ ጃክ ።

የኋላ ማርሽ አስገባና ወደኋላ መጓዝ ጀመረ ። ዝም ብሎ ለመጓዝ እንጂ ምን ማድረግ እንዳሰበ ራሱም አያውቀውም ።

«ዝም ብለን ትራክተሮች ባሉበት በኩል እንሒድና ልንደርስ ስንል «በስተቀኝ ያለው ቦታ ሊያሳልፈን ስለሚችል በፍጥነት አልፈን ወደ መንገዱ እንግባ» አልኩት ።

ጃክ በረጅሙ ተነፈሰና ፣ «በጣም ጥሩ ሐሳብ ነው ፤ ወይ ይሳካል አለዚያም ያው ነው» በማለት ፈገግ ብሎ ፣ «ጂኒ እወድሻለሁ አንተንም ዲክ...ዕድላችንን እንሞክር...» አለን ተራ በተራ እያየን ።

«ቆይ እስቲ አንዴ መኪናውን አቁመው» አለ ዲክ ።

መኪናውን ጃክ አቆመና ሁለታችንም ዲክን አየነው ። ዐይኖቹን ገርበብ አድርጎ ወዲያው ወዲያው ሲተነፍስ ቆየና ዐይኑን አፍጥጦ እየተመለከተ፣ «ብዙም ዕድል የሚኖረን አይመስለኝም። ግን እንሞክር ካልን ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት እንመለስና መኪናዋን ከፍለንም ይሁን ወይም ነጥቀን እንውሰድ ። ከዚያ ዕቃችንን በርሷ መኪና እንጫንና ጂኒ መኪናዋን ትንዳ፣ ጃክ ከኋላ ወንበር ተኛ። ቆይ! ሌላ ሐሳብ... ጂኒ ከወይዘሮ ሮዛ ልብሳቸውን ትዋሽና ትለብሺያለሽ ገባሽ? የወይዘሮ ሮዛን ልብስ ለብሰሽ አሮጌውን መኪና ስትነጂና ሰው አጠገብሽ አለመኖሩን ሲመለከቱ ሴትየዋን ትመስያቸዋለሽ ። በዚህን ጊዜ እስከ ምትጠጊያቸው ድረስ ዝም ይሉሻል እንጂ አይተኩሱብሽም ። እነሱ የሚጠብቁት ሁለት ወንዶችና አንዲት ሴት በፒጆ መኪና ውስጥ ነው፣ ገባችሁ? ወደ መንገዱ በፍጥነት ስትሒጂ ከፍተኛ አቧራ ስለሚነሣ አቧራውን ከሶላ አድርጌ ከኋላሽ ፒጆውን ይዤ እከተልሻለሁ ። በዚህን ጊዜ የሚያዩት ፕሌይማውን እንጂ የኔን ...ፒጆ አይደለም ። ስለዚህ ፍጥነትሽን ሳትቀንሽ አጠገባቸው ልትደርሽ ጥቂት ሲቀርሽ ትንሽ ወደጐን ዘር ብለሽ ሞተር ሳታጠፊ ታቆሚያለሽ ። ለኔ ግን ማለፊያ የሚሆን ቦታ መተው አለብሽ፣ ገባሽ? አንቺ ልክ እንዳቆምሽ በፍጥነት መንገዴን ቀጥዬ ዘግተው የቆሙትን መኪናዎች በመግጨት

መንገድ አስለቅቃቸዋለሁ ። መንገዱ መለቀቁን እንዳየሽ ጊዜ ሳታጠፊ ነዳጅ እስከ መጨረሻው ሰጥተሽ ታልፊያለሽ ። ምን ታስባላችሁ?»

ሁላችንም ዳጥ አልን ። ጃክን ተመለከትኩት። ፊቱን ወደ መስኮቱ አዙሮ ይመለከታል ።

«ጥሩ ሐሳብ ነው ፤ ግን አንድ የማልስማማበት ነገር አለ» አለ ጃክ ።

«ምንድነው?» አለ ዲክ ።

«እኔ ፔጆውን መንዳት አለብኝ ። አንተ ከጄኒ ጋር ከኋላ ሆነ በር መደበቅ አለብህ» አለ ጃክ ።

«በምንም መንገድ ሊሆን አይችልም ። ሐሳቡን ያመነጨሁት እኔ ነኝ ። የራሴን ዕድል መሞከር አለብኝ» አለ ዲክ ኮስተር ብሎ ።

«ሳንቲም እንወርውርና ከሰው ወይም ከአንበሳ የወጣለት ይንዳ ። እኔ ሰው መርጫለሁ» ብሎ ከኪሱ አወጣና ሊወረውር ሲል ፥ ዲክ ቶሎ አለና ፥

«አይሆንም ሌቦ! አንተ አትወረውርም ፤ ጄኒ አንቺ ወርውሪ» አለኝ ። ከጃክ ተቀብዬ ወደ ሰማይ ወረወርኩና በእጄ ሸፍኜ ቀስ ብዬ ስገልጸው አንበሳ ወጣ ። በጣም ጥሩ ነው ። እንደ ተመኘሁት ሆነ ። ዕድላችንን እንሞክር ፥ እንሒድ!» አለ ዲክ በመደሰት መልክ ።

ወደ ወይዘሮ ሮዛ ቤት በፍጥነት መኪናዋን እየነዳን ልክ በራፉ ላይ ስንደርስ ወይዘሮ ሮዛ በሩን ከፍታ ወጣች ። እንደ መሰለኝ ከሆነ በመስኮት ሆና ስትመለከተን ቆይታለች ።

«እናንተ ዝም በሉ ፥ እኔ ላነጋግራት» አለ ጃክ በመንሾካሾክ ።

ሦስታችንም የበሩን ደረጃ ስንወጣ ተመለከተችንና ስንጠጋት ፥ «አንድ ሌላ ሰው ከፖሊስ ጣቢያ ደውሎ ሊያነጋግርህ እንደሚፈልግ ነግሮኝ ነበር ። ግን መሐዳችሁን ነገርኩት» አሉችን ።

«ወይዘሮ ሮዛ መኪናዎን በጣም እንፈልጋታለን ። እባክዎ ይስጡን ። እርስዎን ችግር ውስጥ የሚከትዎት አይደለም ። ቢፈልጉ ከሒድን በኋላ መኪናዬን አስገድደው ወሰዱብኝ ብለው ለፖሊሶች መንገር ይችላሉ ። ደህና ገንዘብ ለመኪናዋ እንከፍላለን ፥ እባክዎ ይርዱን» አለ ጃክ ።

በሐዘኔታ ተመለከተችውና ፥ «ቁልፉን ላምጣላችሁ ፥ ገንዘባችሁን ግን አልፈልግም» ብላ ወደ ውስጥ ገባች ።

አምስት ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ቁልፉን አመጣችልንና ዕቃችንን ወደ ፕሌይማውዙ ውስጥ አስገባን ። እኔም ወደ ወይዘሮ ሮዛ ጠጋ ብዬ ልብስ እንድትሰጠኝ ጠየኩዋት። ለምን እንደ ፈለኩት ሳትጠይቀኝ የጠየኩትን ዓይነት ሰጠችኝና መኪናው ውስጥ ለበስኩት። ለሁለተኛ ጊዜ ከወይዘሮ ሮዛ ጋር ለመሰነባበት ሦስታችንም ቆምን ።

«ወይዘሮ ሮዛ እንዴት ብለን እንደምናመሰግንዎት አላውቅም ። ያደረጉልን ትብብርና እርዳታ ከፍተኛ ነው ። መኪናዎን በቅርብ ቀን ውስጥ በተቻለ መጠን እንመልሳለን ። ይኸን ቃል እንገባልዎታለን ። ለራስዎ የሚሆን ገንዘብ እንደማይፈልጉ ወውቃለሁ ። ግን ለድሆች የሚመፀውቱትና ለቤተክርስቲያን የሚሰጡት ገንዘብ እንስጥዎት?» አለ ጃክ ።

«ኑሺ ለቤተክርስቲያንና ለድሆች ስል ገንዘቡን እቀበላለሁ ። የሰጣችሁኝን ለድሆች መጽውቼ ለናንተም እጸልያለሁ » አለችን ።

«ወይዘሮ ሮዛ በጣም አመሰግናለሁ» አልኩና ጠጋ ብዬ ጉንጭ ዋን ሳም አደረኩት ። ወንዶቹም እኔን አይተው ሳምዋት ። ጃክ የገን ዘብ ቦርሳውን አውጥቶ አንድ ሺ ብር ቆጠረና አጣጥፎ ሴትዮዋ እጅ ላይ ጣል አደረገላት ።

እኔና ጃክ ወደ ፕሌማውዛችን ፡ ዲክም ወደ ፔጀው ስንገባ፡ «እን ግዲህ ቅድም የነገርኩሽን አትርሺ ። በተቻለሽ መጠን ከመቆምሽ በፊት ለኔ ክፍት ቦታ መኖሩን አረጋግጪ ። ይህን ካረጋገጥሽ በኋላ ስትቆሚ ወይዘሮ ሮዛ መስለሻቸው መንገዱን በትንሹም ቢሆን ከፈት ያደርጋሉ ። ይኸን ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየበረርኩ መኪናዎቹን ገጭቼ አልፋለሁ ተከተይኝ» ብሎ ዲክ ሲነግረኝ ፡ የነባኝ መሆኑን እራሴን በአምንታ ነቀነቅሁ ። ፊቱን ማየት አልደፈርኩም ። ሳየው እንደማለቅስ ስለ ሀወቅሁ ወደ ሰማይ ተመለከትኩ ።

«መኪናዎቹን ገጭተህ እንዳለፍክ በተቻለህ ፍጥነት ከመኪናው ውጣና ተመልሰህ ወደኛ መኪና እራጥ ። የተኩስ ሽፋን እሰጥሃለሁ ። የኋላውንም በር እከፍትልሀና ትገባለህ» አለው ጃክ ።

«ጥሩ ነው ፡ ብቻ ተጠንቀቁ!» አለ ዲክ ።

ወደየመኪናችን ገባን ። የወይዘሮ ሮዛን መኪና ያዝኩ ። ጃክ ከኋላ ወንበር እንደ መተኛት ብሎ ሁለቱን ሽጉጦች አውጥቶ በእጁ ሲይዝ በመስተዋት ተመለከትኩት ። ዲክም ፔጀዋን ይዞ ተከተ ተለን ። መንገዳችንን ስንቀጥል ወይዘሮ ሮዛ ቆማ ትመለከታለች ። እጇንም ደህና ሁኑ በሚል ያወዛወዘች መሰለኝ ። እርግጠኛ ግን አይደ

ለሁም ። እንዲሁ በሐሳቤ ገምቼ ይሆናል ። ጃክ ከኋላ ወንበር ተኝቶ የትእዛዝ መዓቱን ያሻርጐደጉደው ጀመር ።

«ፍጥነትሽ ከዐርባ አይብለጥ ፣ የተዘጋው መንገድ እስከምንደርስ ድረስ መሪውን ወደግራ ወደቀኝ እየጠመዘዝሽ ንጂ ፣ መንገዱ በሙሉ በአቧራ እንዲሸፈን ማድረግ አለብሽ ፣ አንድ ጊዜ ፍጥነትሽን ቀነስ አንዴ ጨመር አድርጊ ፣ መንገዱን በሙሉ መያዝ አለብሽ ፣የሚነሣው አቧራ ዲክን መሸፈን አለበት ፣ በግምት ሠላሳ ጫማ ያህል ሲቀርሽ ፍሬን ያዢ ፣ መንገዱ እንደሚያንሸራትት ዐውቀሽ ለዚህ መዘጋጀት አለብሽ ፣ በተቻለ ፍጥነት መቆም ሞክሪ ፣ ወዲያው ወደ ግራ ታጠፊ ፤ ገባሽ? ወደግራ! ዲክ ሊያልፍበት የሚችል ቦታ መኖሩን ማየት አለ በት ። እና እዚህ ተኝቼ የርሱን ማለፍ ማየት ስለማልችል አንቺ ወዲ ያውኑ ትነግሪኛለሽ ፣ ወይም በጩኸት አሰሚኝ ፣ ያንቺን ጩኸት እንደ ሰማሁ ፣ በሩን እከፍትና ሰዎቹ ላይ ተኩስ እከፍታለሁ ። በምትሰሚው ጩኸት እንዳትደነግጪ ። ዝም ብለሽ ነዳሽን እርገጪና ወደፊት ቀጥይ ። ዲክ መኪናውን አቁሞ ወደኛ ሲሮጥ መኪናውን ታቆሚና ዲክን ትጠብቂያለሽ ፤ ከዚያ በኋላ...»

«በቃህ! የምትነግረኝ ሁሉ በዛብኝ ። እኔ በራሴ መንገድ ልሞክ ረው ተወኝ!» አልኩት በጩኸት ። ለትንሽ ጊዜ ጸጥ አለና... መናገር ሲጀምር ድምፁ ከወትሮው የተለየና ለስለስ ያለ ነበር ። «አዎ ልክ ነሽ ፣ በሚስማማሽ መንገድ ቀጥይ» አለኝ ።

ወደፊትና ወደኋላ በመስተዋት እየተመለከትኩ መንገዴን በመ ቀጠል ለጃክ ሁኔታውን መንገር ጀመርኩ ። «... በግምት ሃምሳ ሜትር ርቆ ዲክ እየተከተለን ነው ። ከፍተኛ አቧራ ስለአለ በደምብ ለማየት አስቸጋሪ ነው ። ወደ መጨረሻው መታጠፊያ ልንደርስ ነው ። አሁን ደርሰናል ። ቀጥታውን መንገድ ይዘናል ። ፍጥነቴን በትንሹ ቀንሻለሁ ፣ ቀጥ ብዬ ተቀምጫለሁ ፣ ወይዘሮ ሮዛን እንድመስላቸው ወደፊተኛው መስተዋት ተጠግቻለሁ ፣ ተዘጋጅ! ወደግራ ልታጠፍ ነው ፣ አዩን! ከመኪናዎች ኋላ ቆመዋል ፣ እጃቸውን እያርገበገቡ ቁሚ እያሉኝ ነው ፣ ፍጥነቴን ቀንሻለሁ ፣ ቁጥር ልቆጥር ነው አምስት... አራት... ሦስት... ሁለት... አንድ አሁን ነው!»

መሪውን በፍጥነት ወደ ግራ ጠመዘዝኩትና ፍሬኑን ባለ ኃይሌ እረገጥኩት ። መኪናው መንሸራተት ጀመረ ። ወደ ጉድጓድ ይዞኝ ሔደ ። እንደ ምንም ታግልኩና መለስኩት ። ፍሬኑን ግጥም አድርጌ ስለያዝኩት ፍጥነቱ እየቀነሰ እየቀነሰ መጣና ቆምኩ ።

ወዲያው ፔጀው በከፍተኛ ድምፅ በጣም ተጠግቶኝ አለፈ ።

በጨረፍታ ዲክን ተመለከትኩት ። መሪው ላይ ጐንበስ ብሎአል ። ፊቱ ላይ የመደንገጥ ወይም የመረበሽ ምልክት አይታይበትም ። ዲክ በቀጥታ መኪናውን ወደ ጂፑ ሲያመራ ከኋላ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ሸሹ ። አንዱ ዘሎ ወደ ጉድጓድ ሲገባ አየሁት ። እኔም ፕሌይማውዙን አንቀሳቅሼ መንገዱን ስይዝ ፡ ጃክ ከተኛበት ተነሥቶ የኋላውን በር መስኮት በማውረድ በሁለቱም ሽጉጦች መተኮስ ጀመረ ።

ፔጀው ጂፑን በስተቀኝ በኩል ጨረፍ አርጎ ሲገጨው የሰማሁት ድምፅ ጆሮ የሚያደነቁር ነው ። ጂፑ እንደ ኳስ ወደ አየር ላይ ጉኖ መሬት ሲያርፍ መገለባበጥ ጀመረ ። ፔጀዋም ገጭታ ካለፈች በኋላ አንዴ ወደቀች ፡ አንዴ ወደግራ በመጣችበት ፍጥነት ሔደችና መገለባበጥ ጀመረች ። የተከፈተውን መንገድ መልክት አልኩና በፍጥነት አለፍኩ ። ጃክ የኋላውን በር ሙሉ በሙሉ ከፍቶ ይተኩሳል ። የጠመንጃው ድምፅና የሰዎች ጩኸት ይሰማል ። አካባቢውም በአቧራ ተሸፍኖአል ።

ሲገለባበጥ ከነበረው ጂፕ የብርቱካን ቀለም የመሰለ እሳት ቡልቅ ብሎ ከወጣ በኋላ አንዴ ተያያዘ ።

የተዘጋውን መንገድ እንዳለፍኩ ፍሬኑን በመርገጤ ከብዙ መንሸራተት በኋላ ለመቆም ቻልኩ ። ዘወር ብዬ ስመለከት ፔጀዎ በጐንዋ ጋደም ብላለች ። ጃክ ከመኪናው ወርዶ እየተኮሰ ወደ ኋላ ዲክን ለማነጣት ይሮጥ ጀመር ። ወዲያው የፔጀዋ በር ተከፈተና ዲክ ሲወጣ አየሁት ። ያንከሳል ።

ከቦርሳዬ ውስጥ ሽጉጤን አወጣሁና ከመኪና ወርጄ በሁለት እጄ ጠበቅ አድርጌ በመያዝ መንገዱን ዘግቶ በቆመው መኪናና በሰዎቹ ላይ መተኮስ ጀመርኩ ። ጃክ ዲክ ጋ ለመድረስ ትንሽ ቀርቶታል ። ዲክ ለጃክ እጁን ሲዘረጋለት የጠመንጃ ድምፅ ተሰማ ። ዲክ ወደ ላይ ጓነና ወደ መሬት በመውደቅ ተንከባለለ ። ጃክ ለአንድ አፍታ ቆም ብሎ ተመለከተና ፊቱ በድንጋጤ ዐመድ መስሎ እየሮጠ ወደኔ ተመለሰ ። እኔም በደመ ነፍስ ጥይቱ ያለቀበት ሽጉጥ ይገር ምላጩን እየደጋገምኩ እስብ ነበር ።

ጃክ አጠገቤ እንደ ደረሰ ወደ መኪናው ውስጥ ገፍቶ አስገባኝና በነጂው ቦታ ራሱ ተቀምጦ ዶሎ ማርሽ በማስገባት መንገዳችንን ቀጠልን ። ከኋላችን የጥይት እሩምታ ይተኮስብናል ። በከተማው ውስጥ ስናልፍ በመንገድ ላይ የሚገኝ ሰው ሁሉ እየተሯሯጠ መንገድ ይለቅልን ነበር ። ከተኛሁበት ወንበር ቀና አልኩና በደምብ ተስተካክዬ ተቀመጥኩ ።

ጃክ መኪናውን እየነዳ እየደጋገመ መሪውን በእጁ በመደብደብ «ብሩህ መንገድ የምትቀይስልን ጓደኛችን የት ሔድክ?» እያለ ማንጐራጐር ጀመረ ።

አሁን ሙሉ ለሙሉ መለወጤን ዐወቅሁት ። እንዴት እንደ ተለወጥኩ ገባኝ ። እስካሁን ሰነት ድረስ የድርጊቱ ተራኪ እንጂ ተሳታፊ አልነበርኩም ። በዚህ ዘረፋ እንቅስቃሴ ምን ላይ እንደ ደረስን ከመ ግለጽ ባሻገር በእንቅስቃሴው ውስጥ ይኸን ያህል የጐላ ሚና አልነበረኝም ። በዚህ ሰዓት ግን ፣ ከዘራፊው ቡድን ጋር በማበር በጅርጅያ አነስተኛ ከተማ ውስጥ በሕግ ተወካዮች ላይ መሣሪያ መዝዤ ተታኩሻለሁ። እውነቴን ነው የምላችሁ፡ ሕገ ወጥ መሆኔን የተረዳሁት አሁን ነው ። ምናልባት ሰውም ገድዬ ሊሆን ይችላል ።

«ዕድሜው ስንት ይሆናል?» አለኝ ጃክ ወደ እኔ አየት አድርጎ ።

«ሠላሳ ሁለት ፣ ሠላሳ ሦስት ፣ ወይም ሠላሳ አራት ሊሆን ይችላል ።»

በመገረም ፣ «እንዴት አታውቂም?» ሲል መልሶ ጠየቀኝ ።

«አላወቅም!»

«ውሸታም!» አለኝ ።

ስለ ዘረፋው ስጽፈው የነበረው ሁሉ አላረካሽ አለኝ ። እንደ መሰለኝ ከሆነ ስለ ዲክ ፣ ሄሚ ፣ አንጂላ ፣ ክሊመንት ፣ ስማይሊ ፣ ሆሊጐስትና አንቶኒዮ ሮሲ እንዲሁም ስለ ጃክና ስለራሴ የጸፍኩት ታሪክ ሙሉ በሙሉ እውነተኛ አልመስለኝ አለ ። ስለዚህ ሰዎች ሊነገር የሚገባውን እውነተኛ ታሪክ አልጸፍኩም ። የጸፍኩትን እንደገና ሳነበው ፣ በሁሉም ውስጥ የነበረውን ብልጥነት ፣ ቅራኔና ሽኩቻ ሳስታውስ ፣ የየአንዳንዳቸውን ሰብዕና ለመገምገም የነበረኝ ችሎታ አነስተኛ ሆኖ አገኘሁት ። በኔ በኩል ያየሁት ደንቆሮነታቸውን ፣ ጭካኔያቸውንና ለዘረፋ ያላቸውን ችሎታ ብቻ እንጂ ፣ እውነተኛ የሕይወት ታሪካቸውን ለማወቅ ባለመሞከሬ አዘንኩኝ ።

«የትውልድ አገሩ የት ነው?» አለኝ ጃክ ።

«ከአሐዩ እንደ መጣ ነግሮኝ ነበር»

«በሕይወት ያሉ ቤተሰቦች አሉት?»

«እናቱና አክስቱ በሕይወት አሉ ። ስለ አባቱ ግን ተናግሮ አያውቅም ። እንደ መሰለኝ አባትየው ጥሎአቸው ሌላ ቦታ ሔዶአል ወይም ሞቶ ይሆናል ። ራሱ ስለአልነገረኝ እኔም አልጠየቁትም ።»

«ስለዲክ ብዙ የምታውቂው የለም ማለት ነው!» አለኝ በወቀሳ መልክ ።

በመገረም ፡ «አዎ! ስለሕይወት ታሪኩ መጠየቅም አልፈለኩም ነበር ። ምክንያቱም መናገር ቢፈልግ ኑሮ ሳልጠይቀው ሊነግረኝ ይችል ነበር። አልነበረም!» አልኩትና በመቀጠል ፡ «እኔ እንደምገምተው ዲክ የሰውን ታሪክ ለመስማት የማይጓጓና የራሱንም የማይናገር ዝምተኛ ሰው ነበር ። ይህም ጠባዩ ነው ብዬ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኜ ለመ ናገር ባልደፍርም ፤ ምናልባት ስለራሱ የማይናገር ዝምተኛ ሰው የም ወድ መስሎት ሊሆን ይችላል ፡ ስለማንነቱ ያልነገረኝ ። እኔም ብሆን ስለራሴ የሕይወት ታሪክ የነገርኩት አይመስለኝም» አልኩኝ ።

ያም ሆኖ ጀክ ያለው እውነቱን ነበረ ። ስለዲክ ማንነት ብዙ ማወቅ ነበረብኝ ። በጥይት ተመትቶ ሲወድቅ አይቼአለሁ ። ተመልሶ ቢመጣና አልጋ ላይ ራቁታችንን ተኝተን ዐይን ዐይኑን እየተመለከ ትኩ በሹክሹክታ ስለማንነቱ ብጠይቀው እርግጠኛ ነኝ ይመልስል ኛል ።

«አርቆ ማሰብ የሚችል ጥራት ያለው ሰው ነበር» አለ አሁንም ጀክ በቁጭት ።

«አንተም ጥራት ያለህ ሰው ነህ» አልኩኝ ላጽናናው ።

«አይደለሁም! እንዳልሆንኩ ዐውቀዋለሁ!» አለኝ በሐዘኔታ ።

አሁን በመናገር ላይ ያለሁት እንደ ጂኒ ሼን አይደለም ። እንደ ቢያ ፍላንደር ነው ። ጂኒ ሼን ስደተኛ ፡ ወንጀለኛና በጣም የምትፈለግ ናት ። ሆኖም በቢያ ፍላንደርነቴ ፍርሃትን ፡ ወንጀለኝነትንና ጭካኔን እየተላበስኩና እየተዋሐድኝ መጥቶአል ።

የብንደንበርግና ልጆቹን ጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ ለዘረፋ ሳጠና የተሰማኝ ነገር ነበር ። ይኸውም እኔ የጎበረተሰቡ ጠላት እንደ ሆንኩና እያንዳንዱም ሰው እኔን ለማጥፋት እጁን እንደ ዘረጋብኝ ሳስብ በጣም እጨነቅ ነበር ። አሁን ግን ፡ በተግባር ላይ ሲውል መጨነቁ ቀረና ከተያዘበት ወጥመድ ለማምለጥ መውጫ ቀዳዳ እንደሚፈልግ አውሬ ሆንኩ ። የተገነዘብኩት ቢኖር ሕይወቴ ባላሰብኩት መንገድ መለወጡ ነው ። ከዚህ በኋላ ወደ ድሮ ንጹሕ ሕይወቴ ለመመለስ የሚ ያስችለኝ ዕድል ሁሉ ተዝርግቶአል ።

«በጣም የሚደነቅ ጓደኛ ነበር»
«አዎ! ይገባኛል»
«እጅግ በጣም ትልቅ ሰው ነበር»

ዲክን እያስታወሰ ብዙ ነገር መናገር ፈልጎአል ፤ ወደ ቢያ ፍላ ንደርነት የተለወጠችው ጄኒ ሼን ግን አልፈለገችም ። የሞቱትን ሰዎች ሁሉ ረስታ ወደፊት በሕይወት ለመኖር ትፈልጋለች ።

የጥይት በረዶ እየወረደብን ካመለጥን በኋላ፡ዊተር ከተማን ትተን ወደኋላ በመመለስ አቋራጭ መንገዶችን እየፈለግን ተጓዝን ። የወይ ዘሮ ሮዛ ፕሌይማውዝ ሬዲዮ የሌላት መሆኑን ያወቅነው ብዙ ከተጓ ዝንና ከተረጋጋን በኋላ ነው ።

ፋርጐ አካባቢ ስንደርስ ከመንገድ ወጣ ብለን መኪናዋን ተውና ትና አንድ ሽፍሮሌት ፒክ አፕ ቁልፉ እሞተሩ ማስነሻ ላይ እንደ ተን ጠለጠለ አግኝተን ሰረቅን ። መኪናው ሬዲዮ ስለአለው በየሰዓቱ የሚ ተላለፈውን ዜና ማዳመጥ ጀመርን ። ስለኛም ብዙ ተብሎአል ። እነሱ እንደሚሉት የሚከታተለን ቡድን እንደ ተንቀሳቀሰና በአጭር ጊዜ ውስጥም በቁጥጥር ሥር ሊያውሉን እንደሚችሉ ነው ።

መንገዳችንን በመለወጥና ወደ ቀኝ በመታጠፍ፡ወደ ሰሜን ተጉዘን ፍሎሪዳ ገባን። ሾፍሬሌቱን ፒክ አፕ ፡ መኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ትተን ወደ ጃክሲንቬል በሚሔድ አውቶቡስ ተሳፈርን ። ጃክሲንቬል ወደ ምሽቱ ላይ በመድረሳችን አልቤርነ ፈልገን አደርን። በማግሥቱ ጠዋት አሮጌ መኪና ወደሚሸጥበት ሔደን ከዐሥር ዓመት በላይ ያገለገለ ዶጅ ገዛንና ነዳጅ ሞልተን እንደገና ወደ ደቡብ በማምራት ወደ መን ገድ ዘጠና አምስት ተጓዝን ።

የመጨረሻው ጉዞ

ከአንዱ ወደ ሌላው መኪና ለውጥ ባደረግንበት ጊዜ ሁሉ ፡ ዕቃ ዎቻችንን ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ያሸጋገርን ስለሆነ ፤ ከኋላችን በቦታው ስለ መቆየታችን የሚገልጽ መረጃ አልተውንም ። በጉዞአ ችን ላይ ምንም አልተነጋገርንም ። የዲክን የልብስ ሻንጣ ሳይቀር ይዘነ ዋል ። ጃክሲንቬል ባመሸንበት ወቅት ክፍት የመድኃኒት ቤት በመፈ ለግ የጸጉር ቀለምና አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶች ገዛን ። የጃክን ጸጉር ቀለም ከቀባነው በኋላ ፡ ቀለሙ እስኪይዝ ከአንድ ሰዓት በላይ ፈጀ ። የዐይኑንም ሽፋል አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ያለበት እንዲመስል ቀባ ሁት ። የዐሐይ መነጽር ፈልገን ገዛንና አደረግን ።

በማግሥቱ ጠዋት ቅዱስ አውጐስቲን ስንደርስ ጃክ በተለያየ ቀለም የተዥጐረጐረ የስፖርተኛ ቁምጣ ሱሪ ፡ ነጭ ካልሲ ፡ ጫማና በደረቱ ላይ የደን ሥዕል ያለበት እጀ ጉርድ ሸሚዝ ገዛ ። የገዛቸውን ልብሶች በሚለብስበት ወቅት ሆን ብሎ ሸሚዙን ከሱሪው በላይ አደረገው ።

ይሽ አለባበስ በክልሉ የሚታዩትን ቱሪስቶች ለመምሰል ብቻ ሳይሆን በወገቡ የሻጠውን ሽጉጥ ለመደበቅ ነበር ።

የቢያ ፍላንደርን ፎቶግራፍ እንደማያገኙ እርግጠኛ ነን ። የቢያን ፎቶ ባያገኙም የጂኒ ሼንን ፎቶግራፍ እያራቡና ባሉት የፖሊስ ሠዓሊ ዎች እያሣሉ ወደየቦታው ይበትኑታል ። ስለዚህ ቢያን የሚያስመስለ ኝን አለባበሴንና ጸጉሬን መለወጡ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም ።

ለተጨማሪ ማሳሳቻ ጃክ አሮጌ ካሜራ ገዝቶ ዘለበቱን አንገቱ ውስጥ አስገብቶ ደረቱ ላይ አንጠለጠለው ። እኔም የእጅ ቦርሣዬን ትቼ በአካባቢው የሚሸጠውን የቃጫ ቦርሣ በትከሻዬ አንጠለጠል ኩት ።

ያለፈውን ምሽት በደይቶና ካሳለፍን በኋላ ፡ የገና በዓል ማለፉን አስታወስን ። በማግሥቱ ጠዋት ሁለታችንም ተለያየንና ለገና በዓል ስጦታ የሚሆን ዕቃ ገዛን ። ለጃክ የኤሌክትሪክ የጺም መላጫ ገዛ ሁለት ። እሱም በተራው በአካባቢው የተሠራ የሞና ልብስ ገዛልኝ ። በተለዋወጥነው የገና በዓል ስጦታ ተደስተን ተሳሳምን ።

ያገና በዓል ሳናውቀው ቢያልፍም ፡ ማለፉን ካወቅን በኋላ ግን ከጃክ ጋር የተለዋወጥነው ስጦታና የመዝናኛ ምሽት በጣም አስደስቶ ኛል ። ቀጥተኛውን መንገድ ከመያዝ ይልቅ ወደ አርላንድ ታጠፍንና አሮጌውን ዶጅ መኪና ሸጠን ሁለት ዓመት ያገለገለ ሲትሮይ መኪና ገዛን ።

መኪና ስንሸጥና ስንገዛ ጃክ፡ በትክክለኛ ስሙ መጠቀሙ የግድ ነበር ። ይሽም የት ቦታ እንዳለን ለሚከታተለን ክፍል እንዲያውቅ የሚረዳ ቢሆንም ፡ በየትናንሹ ከተማ መግባታችንን እንጂ የት እንደ ምንሔድ ግራ ሳይገባቸው አይቀርም ። ይህም እኛ ሚያሚ ቱሉ ለመድ ረስ ሲያስቸለን እነሱ ግን ብዙ ቀን ይወስድባቸዋል ።

ሚያሚ ከደረስን በኋላም ከተማው ትልቅ በመሆኑ ፡ የመደበቂያ ሥፍራ እንፈልግና ነገሩ ከተረጋጋ በኋላ ወዴት መሔድ እንዳለብን ወደፊት እናስባለን ። ደቡብ ፍሎሪዳ ከመድረሳችን በፊት መኪናች ንን ሸጠን ሌላ መግዛትም እንችላለን ። ጥሬ ገንዘብ እንኳ ከአምስት ሺ ብር በላይ አለን ። ገንዘብ በተጨማሪ ቢያስፈልገን ጥቂት ጌጦች መሸጥ ይቻላል ።

ወደ መንገድ ዘጠና አምስት እንደገና ተመለስንና በደቡብ ቬሮ መዋኛ ሥፍራ በኩል በማለፍ ፓልም መዝናኛ ስንደርስ አልጋ ያገን ። ጥሩ ራት ከበላን በኋላ ወደ ዳንስ ቤት ሔድን ። መደነሱ ደስ ባይለኝም

ቮድካችንን እየጠጣን ተመለከትንና ወደ መኝታ ክፍላችን ተመልሰን እንደ ነገሩ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጸምን ። ዲክ ከሞተ በኋላ የወሲብ ግንኙነት ስናደርግ ይህ የመጀመሪያው አይደለም ። ያሳለፍነው ጭንቀት ከእእምሮአችን ስለአልጠፋና አሁንም እንደሚያጋጥመን ስለም ናስብ፡ ግንኙነቱ እንዲሁ መኖራችንን ለማስታወስ እንጂ ስሜታችን የቀዘቀዘ ነው ።

ጄክ ስለቤተሰቡ ፡ በወጣትነቱ ዘመን ስለፈጸማቸውና በጉልምስና ዘመኑም ምን ያደርግ እንደነበር እንዲነግረኝ ጠየኩት ። ይህን ለመጠየቅ የደፈርኩት 'ይኸ ሰው እንደ ዲክ በድንገት ሳይሞት ማንነቱን ማወቅ አለብኝ' በሚል ስሜት ተገፋፍቼ ነበር ።

ሆኖም ታሪኩን ሲናገር ግራ ያጋባኛል ። እንዳንዴ ስለ ገጠመኞቹ ከማውራት ወደ ኋላ ይላል ። ሊነገር የማይገባውንም ይገልጽልኛል ። እና የጄክ የሕይወት ታሪክ እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር ይቸግረኛል ። ከዚህ በፊት ሰዎች ስለራሳቸው የሚያወሩትን ሁሉ ተጠራጠሪ ብሎ ኛል ፤ ይኸ ከሱ የተማርኩት ነው ።

ስለ ታሪኩ ሲያወራ እንዲህ አለኝ ። «...ብዙ ጊዜ ትላልቅ ቡና ቤቶችን ቆም ብዬ ወይም የበረንዳዎችን ብረት ተደግፌ የሚያስተናግዱ ትን ወንዶችና ሴቶች እመለከታለሁ ። እንደማስበው እነዚህ ሰዎች ከኔና ካንቺ ምንም የተለዩ አይደሉም ። እንደኛው ይበላሉ ፡ ይጠጣሉ ፡ ይጸዳዳሉ፤ የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ እንደ ማንኛውም ሰው ቀናቸው ሲደ ርስ ይሞታሉ ። አንዳንዴ ሳያቸው ግን ለየት ይሉብኛል ። አነጋገራ ቸው ፡ አለባበሳቸውና አካሔዳቸው በጠቅላላ ኑሮአቸውን ስመለከት ከሌላው ሰው የተለዩ መሆናቸው ይገባኛል ። ለምን መሰለሽ? ሰው እንደ መደቡ ይለያል ።»

«አየህ! ሰዎች ከሌላ ሰው የሚለዩበት ምንም መንገድ የለም ። የተለወጠብህ እነሱ ገንዘብ ስለአላቸው ፡ አንተ ግን ገንዘብ ስለሌለህ ነው» ስል አቋረጥኩት ።

«አዎ! ምናልባት ይሆናል ። ግን የተወሰኑትን ስትመለከቺ ገን ዘብ ስለአላቸው ብቻ ልዩ ፍጡር አይደሉም ። ማለቴ ለምሳሌ አንድ ጥሩ ኮርማ ተመልክቺና ስለአወላለዱ አጥኚ ። ትልቅ መሆን የቻለው ባለንብረቱ በሚሰጠው ምግብ ብቻ አይደለም ። መጀመሪያ ከዘሩ ጥራት ያለው በመሆኑ ነው ። በርግጥ ይህን ግዙፍነት ለመጠበቅ ምግብ የሚያስፈልገው ሲሆን፡ ምግቡን ለመግዛት ግን ገንዘብ ያስፈ ልገዋል ። ዋናው መነሻው ግን ገንዘብ አይደለም ። ጥራት ካለ ከዚሁ ጋር ተከታትሎ ገንዘብም ይመጣል ። በዚህ ዓለም ትልቁ ነገር ክደህና

መደብ መወለድ ነው ። እና እዛ ቦና ቤት እንደልባቸው የሚገናኙት ከደሀና ቤተሰብ የመወለዳቸው ጉዳይ ነው ።»

«ይኸ እንኳን በአጋጣሚ ከደሀና ቤተሰብ በመወለዳቸው ነው»

«ልክ ነሽ! በዚህ እስማማለሁ ። የሚታወቁት ከሌላው በበለጠ ሠርተው ሳይሆን በመወለዳቸው ነው ። ገንዘብ ባለኝ ጊዜ አስፈላጊውን ልብስ ለብሼ ወደነዚህ መዝናኛዎች ብቅ እል ነበር ። በዚህ ቦታ ማሳየት ስለሚኖርብኝ ሥነ ምግባርም ዐውቃለሁ ። ጥሩ ጉርሻ ስትሰጪያቸው ደሀና ወንበር ላይ እንድትቀመጭና ጥሩ መስተንግዶም እንድታገኚ ያደርጉሻል ። በዚህን ጊዜ ራስሽን ከሌሎች ጋር እኩል የሆንሽ አድርገሽ ትቆጥሪ ይሆናል ። ግን አይደለም ። እነዚያ ከደሀና ቤተሰብ የተገኙ ሰዎች ብቅ ሲሉ አንቺን ይረሱሽና እነሱን ማስተናገድ ይጀምራሉ ። እነዚህ ሰዎች ለአስተናጋጆቹ ምንም ጉርሻ ባይሰጡዋቸውም እንኳ እግራቸውን ለመሳም ምንም አይቀራቸውም። ለምን መሰለሽ፣ ሰዎቹ ምርጥ መሆናቸውን በማወቃቸው ነው»

«እሺ! አሁን እንተኛ»

ለትንሽ ደቂቃ ዝም ብሎ ቆይቶ ፡ «የሚሳካልኝ አይመስለኝም » አለኝ ።

«ይሳካልሃል! ነገ ሚያሚ እንገባለን» አልኩት ።

«ሚያሚ ስለመግባታችን አይደለም» አለኝና ማንቀላፋት ጀመረ ። በማግሥቱ መኪናችንን አስነሥተን ወደ ሚያሚ ጉዞአችንን ቀጠልን። ጃክ ሚያሚ ለመግባት እንዳልቸኮለ ሁሉ እየተቃረብን ስንሔድ ዝግ ማለት ጀመረ ። መንገድ ዘጠና አምስትን ይዘን ዝም ብለን ሚያሚ መግባት ስንችል፡ ብዙ መኪና በሚበዛበት መንገድ ቁጥር አንድን ተከትለን መጓዝ መረጠ ። እንዳንድ ኪሎ ሜትር በተጓዝን ቁጥር በትራፊክ መብራት እየተያዝን መቆም የግድ ሆነ ።

ቁርሳችንንና ምሳችንን ለመብላት ባረፍንበት ምግብ ቤት የሚቀር ብለትን ምግብ እንዲሁ ላመሉ እየነካካ ይተ ክዝ ጀመር ። ለምን እንደሚተክዝ ጠየኩት ። ዝም ብሎ ራሱን እየነቀነቀ መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም ።

ምናልባት ሚያሚ ምን እንደሚጠብቀን ገምቶ በፍርሃት ይሆን ወይስ ንብረቱን ለብቻው ይዞ ለመጥፋት አስቦ ይሆን? ምናልባትም እንዴት ሊገለኝ እንደሚችል እያቀደ ሊሆን ይችላል ብዬ ተጠራጠርኩ።

አያችሁ! የወንጀለኝነት ባሕሪን እየተለማመድኩት መሔዴን ! የወንጀለኝነት ሙያ አለመተማመንንና ጥርጣሬን ያስተምራል። ቀን

በምንገዛበት ወቅት ሽጉጤን ከቦርሳዬ አልለየውም ። ስተኛም እትራሴ ሥር አስቀምጠዋለሁ ። የያዝኩት ሽጉጥ ከአጐት ሳም የገዛሁት ነው።

በቦካ ራቶን በኩል ስናልፍ፣ ጃክ «ጂኒ፣ ሚያሚ ሊጠብቁን ስለ ሚችሉ በቀጥታ ወደእዛ ከመሔድ ለምን ከአቅራቢያው ከተማ ሆነን አዲስ መታወቂያ እናሠራም ። ከዚያም ከሚያሚ የሚያወጣን አውሮ ፕላን ለመፈለግ ብቻ ወደ ከተማው ብቅ እያልን ብንመለስስ? ይህን ካረግን ሊደርስብን የሚችለውን ችግር መቀነስ እንችላለን» አለኝ ።

ለጥቂት ጊዜ በጥሞና አሰብኩና፣ «ነገሩ አሳማኝ መስሎ ታየኝ፣ ጥሩ ነው ። የትኛው ከተማ ውስጥ እንድንቆይ አሰብክ?» አልኩት ።

«ፖምፓኖ የባሕር ዳርቻ ካለው መዝናኛ ቦታ ቢሆን ጥሩ ነው። አካባቢውን በደንብ ዐውቀዋለሁ ። ወደ ሚያሚ ለመሔድ ከዐርባ አምስት ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ይፈጃል ። ሰዓቱ የሚወሰነው በመን ገድ ላይ እንደሚገኘው የመኪና ብዛትና ማነስ ነው ። እዚያው እባሕሩ ዳርቻ ከሚገኙት አልቤርጎዎች ከአንዱ አልጋ እናገኛለን»

«በጣም ጥሩ ነው ። የዕረፍት ጊዜአችንን ፀሐይ እየሞቅንና እየ ዋኘን እናሳልፋለን ።»

«ይቻላል ፣ ብቻ በባሕር ላይ መዋኘት ብዙም አልችልም። ትንሽ እንደ ሔድኩ ይደክመኛል ። ሆኖም የባሕሩን ዳርቻ እወደዋለሁ ። በተ ለይ ማታ ጨረቃ ስትወጣ እንዴት ደስ የሚል መሰለሽ ፤ ጨረቃዋ ከሰማይ የወጣች ሳትሆን ከባሕሩ ውስጥ የወጣች ትመስላለች ። ማመን አትችይም ፡ በጣም ቆንጆ ናት ። ልክ ፖስት ካርድ ላይ የምታይውን ታያለሽ ።»

ወደ ግራ በመታጠፍ በአትላንቲክ ቦልቫርድ በኩል አልፈን ወደ ሐይቁ አመራን ። የመሸጋገሪያ ድልድዩ በባሕር ላይ የተሠራ በመ ሆኑ፡ ድልድዩ ተነሥቶ አንድ መካከለኛ መርከብ እስክትሻገር ድረስ ለዐሥር ደቂቃ ያህል ቆምን ።

«በመርከብዋ ላይ ላሉት አራት ሰዎች ተብሎ እነሱን ለማሳለፍ ከአራት መቶ በላይ መኪና መቆም አለበት?» አልኩት ።

«የመርከብ ባለቤቶች ስለሆኑና ገንዘብም ስለአላቸው ይህ መብታቸው ነው ። አይመስልሽም?» ሲል መለሰልኝና ፡ «አሁን እኛ የምንሔድበት ቦታ ሪፐስ ይባላል፡ ለተወሰኑ ጊዜያት ቆይቼበታለሁ ። ቤቶቹ የተሠሩት ውኃው ደር ላይ በመሆኑ ደስ ይላል ።

«ሪፐስ አካባቢ በሜዳው ላይ ፈረስ የሚጋልቡና ለዋና የሚመጡ ብዙ ሴቶች ስለሚኖሩ ፡ እነርሱን ለማማገጥ ትላልቅ ሰዎች በብዛት ይመጣሉ » አለኝ ።

«እንደዚህ ሰው የሚበዛበት ከሆነማ ለኛ ጥሩ መቀመጫ ነው» አልኩት ።

«እኔም ይህን ገምቼ ነው ። የተሟላ ዕቃ ያለው መኝታ ክፍል አንፈልጋለን ። እንዲያውም ብዙዎቹ አልቤርጎዎች ማቀዝቀዣና የቡታጋዝ ምድጃ አላቸው ። ብዙውን ጊዜ ውጭ እንመገባለን ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘነው ቁርሳችንን ብቻ እዚያው ክፍሉ ውስጥ አዘጋጅተን መብላት እንችላለን» አለኝ ።

የሪፐስ አካባቢ ቤቶች እውነትም በባሕር ዳርቻ ላይ የተሠሩ ናቸው ። ቤቶቹ በሙሉ ነጭ ቀለም የተቀቡና የሚያንጸባርቁ ሆነው ፤ ከባሕሩ ያላቸው ርቀት ከሃምሳ ጫማ አይበልጥም ። ቤቶቹ በሙሉ የ«ሀ» ቅርፅ ያላቸው ሲሆኑ ሰው ሠራሽ የመዋኛ ስፍራም አላቸው ። ትልቅ ባሕር እዛው እያለ ሌላ የመዋኛ ቦታ ማዘጋጀት ማስፈለጉ ለምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ።

ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ፡ ሁኔታውን ስረዳ ግን በባሕር ዳርቻ የተሠሩ መዝናኛዎች ሁሉ ሰው ሠራሽ መዋኛ እንዳላቸው ገባኝ ። እነዚህ መዋኛዎች ከባሕሩ በበለጠ ለተጠቃሚው ለየት ያለ አገልግሎት እንደሚሰጡ አየሁ ። ተመስገን ወደ ክፍላችን ለመሔድ ወደ መመዝገቢያው ቢሮ ከጃክ ጋር አብረን ሔድን ።

«ሚስተር ሞሪሰንና ሚስ ሞሪሰን ሙኖሪያ እድራሻ ኒውዮርክ» ብሎ ጃክ ተመዘገበ ። ፎርሙን የሚያስሞላው የተሞላውን አየና ወደኛ ቀና ብሎ እየተመለከተ ፡ «ሚስተር ሞሪሰን አንድ ቀን አንድ ሰው ስለ እርስዎ ሲጠይቅ ነበር» አለው፡ ያለምንም ጭንቀት በመዝናናት መልክ።

«መቼ ነበር?» አለው ጃክ ።

«ቆይ እስቲ ማስታወሻዬን ልመልከት» ብሎ አጠገቡ የነበረውን ወረቀት ካገላበጠ በኋላ ፡ «ትላንት አይደለም ፤ ከትላንትና ወዲያ» አለ።

«ሙሉ ልብስ ከነከራባቱ የለበሰ አጠር ያለ ወፍራም ሰው ነው?» አለ ጃክ ።

«አዎ ልክ ነዎት! ጓደኛዎ እንደሆነ ገልጾልኝ አልጋ መያዝዎን ጠየቀኝ ።»

«እዚህ እንደምሆን ነግሬው ነበር ። በመኪና ብልሽት ምክንያት በቀጠሮአችን ቀን መገኘት አልቻልኩም ። እደወልለታለሁ » አለና ወደ ተከራየነው ክፍል ሔደ ። የተከራየነው ክፍል ምድር ቤት ሲሆን የክፍሉ ዕቃዎች ሁሉ የተሟሉ ናቸው። ትልቅ የመስታወት መስኮት ስለ አለው መጋረጃው ሲገለጥ አካባቢውን ሁሉ ለማየት የሚያስችል ነው ።

«አንቶኒዮ ሮሲ፡ እዚህ ቦታ ስለመኖራችን ጠይቆ ከሔደ በኋላ የኛ እዚህ መቀመጥ ችግር እያመጣም?» አልኩት ።

«ምንም ችግር አያመጣም ። ይቺን አካባቢ የጠየቀ ስለሆነ ተመ ልሶ የሚመጣ አይመስለኝም ። ስለኛ ካልጠየቀቤት ቤት ይልቅ የጠ የቀበት በት ዳግመኛ ላለመምጣቱ ይበልጥ አስተማማኝ ነው » አለና መለሰልኝ ። ግምቱ ትክክለኛ መሰለኝ ።

በጣም ብዙ ሐሳብ በአእምሮዬ ይጉላላ ጀመር ። ስለ መለወጤም ብዙ ተመራመርኩ ። ነገሮች ጉንዴት እንደሆኑና እንዴትስ መሆን እን ዳለባቸው አወጣሁ፡ አወረድኩ ።

እንደ መሰለኝ፡ ከዚህ ቀደም አይቼው የማላውቀው ዓለም ውስጥ ገብቻለሁ ። በፊት ያሳለፍኩት ሕይወት የገጠመኝ ኑሮ ሳይሆን በምክ ንያት ላይ የተመሠረተ ነበር ። ለምገለገልባቸው ዕቃዎችና ለቤት ኪራይ እከፍላለሁ ፡ ለመኪናዬ ነዳጅ እሞላለሁ ፡ በፈለግሁት ሰዓት የወሲብ ስሜቴን አረካለሁ ፡ መጽሐፍ ለመጻፍ ወደ ፈለኩበት ቦታ እጓዛለሁ ፡ ወደ ቲያትር ቤት በመሔድ እዝናናለሁ ፡ ጓደኞቼን እጠይ ቃለሁ ። ይህን ሳደርግ ውዬ በማግሥቱ ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ፡ በአን ጻራዊ መልኩ ዓለም የተለወጠች አትሆንብኝም ። በእኔ ግምት ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ ቋሚና እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ የሚቀጥል መስሎ ነበር የሚታየኝ ። በደንቆሮነቱ ይሁን ወይም በየዋህነቱ አላውቅም ። እንደኔ ሐሳብ የሰው ልጅ ኑሮው ከዚህ ውጭ አይደለም ። ነብረተሰቡም የተደራጀው ይህን የመሰለውን ኑሮውን ለመምራት ይመስለኛል ። ነገር ግን ፡ አሁን ያለሁበት ሁኔታ አስተማማኝ አልሆነም ። በዕድል መወጣት ወይም አደጋን መጠበቅ የወንጀለኛው ዓለም ሥርዓት መሆ ኑንም ሳስበው ጭንቅ ይለኛል ። ብቻ የዚህኛውን ዓለም ምንነት ለመ ግለጽ በጣም ያስቸግረኛል ።

ምናልባት ተሳክቶልን ከነንብረታችን ከዚህ አገር መጥፋት እንችል ይሆናል ። ወይም አይሳካልንም ። ከጃክ ጋር ብዙ ጊዜ አብረን ከኖርን ልንጋባ ወይም ላንጋባ እንችላለን ። ጥሎኝም ሊጠፋ ወይም ሊገድለኝ ይችላል። በዚህ አዲስ ዓለም ጥርጣሬ ትክክል ነው። እና የተገነዘብኩት በሥርዓት ያልተገዛ ሕይወት ውስጥ እንዳለሁ ነው ። ለመኖር በጣም አዳጋች ነው ።

ከትክክለኛው አኗኗር ሥርዓት ውጭ ለመኖር የሚደረግ ጥረት ሁሉ ብዙ አደገኛ ሁኔታዎች ሊያስከትል ይችላል ። በመሆኑም ወደ ፊት ይገኛል ተብሎ ከሚቋመጥለት ደስታ ይልቅ ስለ ተጨባጩና ዕለታዊ ኑሮ ምኞት ማድላቱ ይመረጣል ። ስለወደፊቱ አጥብቄ ብና

ስብም ምናልባት ምን ጊዜም የማንደርስበት ሊሆን ይችላል ። ስላለፈው ማሰላሰልም በዳመና የተጋረደን ነገር ለማየት እንደ መሞከር ነው ። ዋናው ቁም ነገር ሕይወትን ለአንድም ቀን ቢሆን ማቆየት ስለሚቻል በት ከመዘየዱ ላይ ነው ።

ይ'ቸንኑ ሐሳቤን እያብሰለሰልኩ በዚህ ቦታ መቀመጥ ከጀመርን ሁለት ሳምንት ሆነን ። ሁልጊዜ ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ከእንቅልፋችን እንነቃለን ። ደስ ካለን ቁርሳችንን መኝታ ክፍላችን አዘጋጅተን እንመገ ባለን ። አልያም ወደ ውጭ ወጥተን ሆቴል እንበላለን ።

ከሆቴላችን በወጣን ቁጥር በኒውዮርክ ከተማ ታትመው የሚወጡትንና በአካባቢው የሚታተሙትን ጋዜጦች እንገዛና ወደየሱቆቹ ብቅ እያልን የሚያስፈልጉንን ሽማግሎን ወደ ክፍላችን እንመለሳለን ። እስካሁን ባነበብናቸው ጋዜጦች ላይ ስለኛ ምንም ወሬ የለም ። ቴሌቪዥንም መወራቱ ቆሟል ። ጋዜጣውም ሆነ ቴሌቪዥኑ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ስለ ተፈጸሙ ወንጀሎች ፣ በአገሮች መካከል ስለተነሡ ግጭ ቶች ፣ ስለ ውሃ ሙላትና ስለ አውሮፕላን አደጋ የሚያወሱ ናቸው ።

ወደ ጠዋቱ አራት ሰዓት ሲሆን ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሔደን ፣ እኔ ስዋኝ ጃክ ጉርድ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪውን ለብሶ ጃንጥላ ያለበት መቀመጫ ፊልጎ ይቀመጣል ። እኔም በሙቀት ከምሰቃይ በሚል አርቲ ፊሻል ጸጉሬን አውልቂ ከላስቲክ የተሠራ የጸጉር መሸፈኛ አጠልቃ ለሁ ። ሙቀቱ እየበረታ ሲሔድ ከመዋኛው አወጣና ፎጣዬን መሬት ላይ አንጥፌ በደረቴ እተኛለሁ ። ጃክ በዚህን ጊዜ በቅባት ሰውነቴን ያሸለኛል ። በተደጋጋሚ ይህንኑ የማደርግ በመሆኑ ሰውነቴ እያማረ ነው ። አልፎ አልፎ በዚሁ የመዝናኛ ሥፍራ ምሳ የምንበላ ቢሆንም ፣ ብዙውን ጊዜ ግን ፣ ጂን በቶኒክ እንጠጣለን ። ከሰዓት በኋላም ለተወሰነ ቀን ለመንሸራሸርና አካባቢውን ለማየት ከመጡ ቱሪስቶች ጋር እንጫ ወታለን ። ጨዋታችን ብዙውን ጊዜ ቁም ነገር የሌለውና ፍሬ ከርሥኪ ነው ።

የፀሐይ ብርሃን እየቀነሰ ሲሔድ ወደ መኝታ ክፍላችን ተመልሰን ለማንቀላፋት እንሞክራለን ፣ ወይም የወሲብ ፍላጐታችንን እናረካ ለን ። ወደ ምሽት ላይ ከእንቅልፋችን እንነሣና ሰውነታችንን ተጣጥ በንና ልብሳችንን ለባብሰን ራት ለመብላት እንወጣለን ። በየጊዜውም የምንበላበትን ምግብ ቤት እንለዋወጣለን ። ከራት በኋላ ወደ ቡና ቤት ወይም ዳንስ ቤት ሔደን የሚያስፈልጉንን መጠጥ ከጠጣን በኋላ እኩለ ሌሊት ከመድረሱ በፊት ወደ ክፍላችን እንመለሳለን ።

እንደሚሰማኝ ከሆነ ምንም የማያሳስብ ኑሮ ነው ። በተለይ ስዋኝ ቆይቼ ሰውነቴን በቅባት እየታሸሁ ፀሐይ መሞቴ አእምሮዬ ስለም

ንም እንዳይጨነቅና እንዳያስብ ረድቶኛል ። በዚህም ደስተኛ ሆኛ ለሁ ። ሪፐስ በቆየንባቸው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ወደ ሚያሚ መቼ እንደምንሔድና ስለመንገዳችን ምን እንደምናመቻች በተደጋጋሚ እጠይቀው ነበር ። የሚሰጠኝ መልስ ግን ፣ «በቅርቡ እንሔዳለን» የሚል በመሆኑ መጠየቁን አቆምኩ ። የገንዘብ ችግር ስለሌለብን ቶሎ መሔዱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም ። ›

በሌላ በኩል ቶሎ ወደ ሚያሚ አለመሔዳችን ዋናው ምክንያት እኔ እንደ መሰለኝ ከሆነ ሁለታችንም የነበረብን ሥጋትና ፍርሃት ከውስጣችን ሙልጭ ብሎ እስከሚጠፋ ድረስ ለመጠበቅ ነበር ። በየቀኑ በመዋኘቴና ፀሐይ በመሞቄ ምክንያት የሰውነቴ ቀለም ወደ ቡና ዓይነት እየተለወጠ ነው ። ጄክም አዞ ፀሐይ ለመሞቅ ከባሕር ወጥታ ጥላና ከለላ እንዲሆናት ድንጋይ ሥር እንደምትተኛ ሁሉ ፣ ጀንጥላ ያለበት መቀመጫ ላይ መቀመጡ የዘወትር ተግባሩ ሆኖአል ።

ሁልጊዜ ወደ ፈረስ ግልቢያ ቦታ ሔዶ ለመጋለብ ፣ ቁማር ለመጫወት ይፈልጋል ፤ ግን ሔዶ አያውቅም ። እኔም ለብቻዬ ወደ ሱቅ ሔጄ ዕቃ ለመግዛት እፈልጋለሁ ፤ ግን ለመሔድ የያዘኝ ምን እንደሆነ አላውቅም ። ብቻ ዝም ብሌን እንደዚሁ ፍላጐታችን ምን እንደሆነ ሳናውቀው ተቀምጠናል ። ብቻ ሁልጊዜ ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነቃ በሕይወት በመኖራችንና ሕይወታችንም ለአንድ ቀን በመራዘሙ ውስጥ ውስጡን እንደሰትቦታለን ።

አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፋችን እንደ ተነሣን ጄክ የገንዘብ ቦርሳውን ሲመለከት የነበረን ገንዘብ በጣም ትንሽ መሆኑንና ተጨማሪ ገንዘብ በጣም እንደሚያስፈልገን ተረዳ ። ኦስካሁን ወጪ ብቻ እንጂ ገቢ ስለሌለን ገንዘባችን እያነሰ መምጣቱ የሚያስገርም አይደለም ። ስለዚህ ጄክ በሚቀጥለው ቀን ወደ ሚያሚ መሔድ እንዳለበት ወሰንን ።

በዚህም ጉዞ መሔድ በሚገባው ሰዓትና የጉዞ ስልት ላይ ተወያየንና ጌጣጌጡ እዚሁ ከኔ ጋር እንዲቆይና ጄክ ብቻውን እንዲሔድ ፣ ሆኖም ሊያስወጣን የሚችል ሰው ወይም ቡድን ካገኘ ምን ያህል ልን ከፍላቸው እንደምንችል ለሚያጠናልን ሰው የሚሰጠው አንድ አልማዝ እና እያለቀ የሔደውን ገንዘብ ለመተካት ከትልልቆቹ ጌጦች በመቁረጥ ለሽያጭ የሚሆን ወርቅ ብቻ እንደሚይዝ ተስማማን ።

«ቢበዛ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት እመለሳለሁ ። አስታውሽ! ይህ የመጨረሻው ሰዓት ነው ። እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ካልመጣሁ ወይም ካልደወልክልሽ እንደ ተያዝኩ ዐውቀሽ ጌጣጌጡን ይዘሽ ከዚህ መጥፋት ነው » አለኝ ።

«መጥፉት አለብሽ? እንዴት ነው የምጠፋው? የትስ ነው የምሔ ደው?»

«በታክሲ፡ በአውቶቡስ፡ በባቡር ወይም በእግርሽ ሒጂ። ማድረግ ያለብሽን አድርጊ ፡ ብቻ ከዚህ አካባቢ መጥፉት አለብሽ ። ምክንያቱም እንቶኒዮ ሮሲ ከያዘኝ እንደምናገር ታውቂያለሽ ፤ አይደለም?» አለኝ ዐይን ዐይኔን እያየ ።

ለመሳም ተጠጋሁትና ፡ «ዐውቃለሁ! ግን ዕድልህ እያማረ መም ጣቱን ቀደም ሲል የገለጽክልኝ ስለሆነ፡ በተባለው ሰዓት እንደምትመ ለስ እርግጠኛ ነኝ » አልኩት ።

«ልክ ነሽ ፡ ያለምንም ችግር እመለሳለሁ» በማለት ጂን ቀዳና ለመጠጣት ወደ አፉ ካስጠጋ በኋላ ወደ እኔ እየተመለከተ ፡ «እኔ በቀ ላሉ የምሞት ሰው አይደለሁም ። ይኸን ታውቂ የለ?» አለኝ ። አትኩሬ ተመለከትኩት ። ቀለም የተቀባውን ጸጉሩን ወደኋላው በደምብ አስ ተኝቶ አበጥሮታል ። ጺሙም ለማደግ አቀምቅሟል ። ከዚህ በፊት የሚያውቁት ሰዎች ቢያዩት ቶሎ የሚለዩት አይመስለኝም ።

ጸጉሩንና ጠቅላላ ሁኔታውን ስመለከት ከዲክ ጋር ተመሳሰሉብኝ ። ወንድማማች መሆን ነበረባቸው ። የዛን ሰት ማታ ለሽያጭ የሚሆኑ ጌጣጌጦችን ስንቆራርጥና ዋጋቸውንም ስንተምን አመሸንና በጊዜ ተኛን ። የግብረ ሥጋ ግንኙነታችን ካለፉት ጊዜያት የተለየና መጀመ ሪያ ስንገናኝ እንዳደረግነው በሙሉ ስሜትና ፍላጐት የተመሠረተ በመሆኑ አድቅቆኛል ብል ማጋነን አይደለም ።

በማግሥቱ ጠዋት ጀክ ይዞት ከነበረው ገንዘብ አብዛኛውን ለኔ ተወልኝና ይዞት እንዲሔድ የተስማማሁትን ትልቅ አልማዝ በመሐረቡ ጠቅልሎ በጀኬቱ የውስጥ ኪስ፡ የሚሸጡትን ደግሞ ሱሪው ኪስ ውስጥ አስቀመጣቸው ። አንድ ሽጉጥ በወገቡ አንዱን ደግሞ ከመኪናው የፊት ወንበር ሥር ደበቀው ። የመሔጃው ሰዓት ሲደርስ እንደ ማመ ንታት ብሎ ቀም አለ ።

«ምን ፈለግህ?» አልኩት ።

«ስሚ ምናልባት ስልክ እደውልልሽና ጌጣጌጦቹን ይዘሽ አንድ የሆነ ቦታ እንድትመጪ እነግርሽ ይሆናል ፤ ገባሽ?»

«እሞ ገብቶኛል ።»

«እና ስልክ በምደውልልሽ ሰዓት ተገድጄና መሣሪያ ተደግኖብኝ ሊሆን ይችላል ። በምደውልልሽ ጊዜ ጀን ወይም ጂኒ ብዬ ከጠራሁሽ

ሰላም መሆኑን ታውቂያለሽ ። ግን ቢያ ብዬ ከጠራሁሽ ተገድጄ መሆኑን እንድታውቂ ፤ ገባሽ!»

የገባኝ መሆኑን በአወንታ ራሴን ነቀነቅሁ ። ምጥምጥ አድርጎ ላመኝና ፈገግ በማለት ፥ «እንገናኛለን» አለኝ ።

«በማንኛውም ሰዓት እጠብቅሃለሁ» አልኩትና ሔደ ።

ወደ መዋኛው ሥፍራ ሔድኩና በተቻለ መጠን ከሚዋኙ ሰዎች ራቅኩና ፎጣዬን መሬት አንጥፌ በመተኛት ይገርመው የነበረውን ወይን ጠጅ መጠጣት ቀጠልኩ ። ስለምንም ጉዳይ ለማሰብ አልፈለኩም ። ሁለት የተለያዩ ሰዎች ሊያነጋግሩኝ ሞክረው መልስ ስለአልሰጠሁዋቸው ሌላ ፍለጋ ትተውኝ ሔዱ ።

ቀኑ ፀሐያማ በመሆኑ ሙቀቱ ከፍተኛ ነው ። መሬት ላይ እንደ ተጋደምኩ ሙቀቱ በጣም ይሰማኛል ። በዚህ ቦታ ራቂቴን ብተኛና የፀሐዩ ሙቀት ሰውነቴ ውስጥ ዘልቆ ቢገባ ደስ ባለኝ ነበር ። ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ወደ መኝታ ክፍሌ ተመለስኩ ። ስለአላበኝ ነላቤን ጠረን ለማጥፋት በሙቅ ውሃ ታጥቤ እንደ ጨረስኩ ስስ ልብስ በመልበስ ጀክን ታይፕ እንዲገባልኝ ጨቅጭቄው የገዛኋትን ታይፕ ጠረጴዛው ላይ አድርጌ በእጅ ስጽፈው የነበረውን መጽሐፌን በታይፕ መምታት ጀመርኩ ።

የምጽፈው ሁሉ በደመነፍስ ነው ። ለምን እንደምጽፈው አላውቅም ፤ ጽሑፌም ፖሊሶች እጅ ቢገባ ከፍተኛ ችግር የሚያመጣብኝ ነው እንጂ ጥቅም የለውም ። መጻፍ የፈለጉት የድሮ ኑሮዬን ስለሚያስታውሰኝ በመሆኑና ያስፈውን መልሼ ስለማላገኘው በታሪክነቱ ለማስቀመጥ ነው ።

እንደ እውነቱ ከሆነ እንደ ሄሚ መንገድ ላይ ሙሞት ወይም እንደ ዲክ ገጠር ውስጥ ወድቆ መቅረት አልፈልግም። ምን እንደፈጸምኩና ምን እንደ ደረሰብኝ ሳልጽፍ መሞት የለብኝም ። ይህ መጽሐፍ ለኔ የመጨረሻ ኑዛዜዬ መሆን አለበት ። ታይፕ ማድረጌን እንደ ጨረስኩ ገጾቹን አስተካክዬ በእንዱ ሻንጣ ውስጥ ከተትኩትና ቆልፌ ቮድካ በበረዶ እየጠጣሁ ጀክን መጠባበቅ ጀመርኩ ።

ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሞላ ፥ ጀክ ባለኝ ሰዓት ላይመለስ ቢቀር ምን እንደማደርግ አሰብኩ ።

በተለያየ ሻንጣ የተቀመጠውን ጌጣጌጥና ልብስ በሁለት ወይም በአንድ በትከሻ በሚያዝ ሻንጣ በማካተት ፥ ታክሲ ጠርቼ ወደ አንዱ አይሮፕላን ጣቢያ እሔድና ትኬት ቆርጬ ወደ ሆነው አገር እሔዳ

ለሁ ። የትም ደሁን የትም ብቻ ከዚህ አካባቢ ቶሎ መሔድ አሰብኝ ። ገንዘብ እያለቀብኝ ከሐዲያ ከጌጣጌጦቹ እየቆረጥኩ እሸጣለሁ ። ስሜንና አለባበሴን እቀይርና አዲስ ኑሮ……

ያለሁበት ክፍል በር ቁልፍ ሲኮፈት ተሰማኝና ቀና ስል ጃክ ሲገባ አየሁት። ፊቱ ገርጥቷል፤ ከመቀመጫዬ እንዴት እንደ ተነሣሁ አላውቅም ፣ እያለቀስኩ አንገቱ ላይ ተጠመጠምኩበት ። ሁለታችንም ተያይዘን ልንወድቅ ምንም አልቀረንም ።

«የክርስቶስ ያለህ! ረጋ በይ እንጂ ! በሰላም ተመልሻለሁ» አለኝ ። «ቀኑን ሙሉ ምንም ምግብ ስለአልበላሁ በጣም ርቦኛል» አለኝና ምግብ ለመብላት ተያይዘን ወደ ምግብ ቤት ሔድን ። የቀረበልኝን የምግብ ዓይነት ለፀመል ያህል ትንሽ ቀመስኩሰት ። ጃክ ግን የቀረበ ለትን ጥስቅ አድርጎ በላው ። ያለንበት ምግብ ቤት በጣም ብዙ ሰው የበዛበትና ጩኸትም ያለበት በመሆኑ፡ የግል ጉዳያን ለመነጋገር አመቺ አልነበረም ።

በዚህ ምክንያት፡ ወደ ዐረፍንበት ክፍላችን ተመለስንና ብራንዲና አ ምባውሃ ይዘን ወደ መዋኛው ሥፍራ በባዶ እግራችንወጣን። በመዋኛው ቦታ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ሰዎች የሚታዩ ቢሆንም ፡ ለኔ እንደ መ ሰለኝ በዚህ አካባቢ ያለነው ሁለታችንና መዝናኛ ሥፍራው ብቻ ነው ። ጨረቃዋ በማማሸ ወጥታለች ። ጃክ ከዚህ በፊት እንደነገረኝ ጨረቃዋ ከሰማይ የወጣች ሳይሆን ከባሕሩ ውስጥ የወጣች ትመስላለች ። ባሕሩ አልፎ አልፎ በሚነፍሰው ነፋስ እየተናወጠ ዳር ዳሩ በዐረፋ ሲሞላ ይታያል ፤ በነፋሱ ኃይል የሚረጨው ውሃ አንዳንዴ እኛንም ነካ ያደ ርገናል ። የሚገርመው በዚህ ሰዓት መጠነኛ ብርድ መኖሩ ነው ። ሆኖም የምንጠጣው ብራንዲ እያሞቀን ስለሆነ ብርዱ ይሸን ያህል አልተሰማንም ። የምንረግጠው አሸዋም መሞቱ አልቀነሰም ። የተፈጥሮው ሐይቅ ፡ ሰማዩ ፡ ዳመናውና ተበታትነው የሚታዩት ኮከ ቦች ደስ ይላሉ። ምን ያደርጋል! በአካባቢያችን ሰዎች አሉ እንጂ፡ ለየት ባለ መልኩ እንዝናናበት ነበር ።

«በጉሀዬ ጥሩም መጥፎም ሁኔታዎች አጋጥመውኛል ። መጀመ ሪያ መጥፎውን ሁኔታ ልንገርሽ» አለኝ ጃክ ።

«አዎን ይሻላል! ቀጥል» አልኩት ።

«ከዚህ በፊት ለማንኛውም ጉዳይ እተማመንባቸው የነበሩት ሰዎች ዛሬ ልተማመንባቸው አልቻልኩም ። ለተወሰኑት ስልክ ብደው ልሳቸው ማንነቴን እንዳወቁ ጆሮዬ ላይ ስልኩን ዘጉብኝ ። መንገድ ላይ ያገኘሁዋቸው ጥቂቶቹ ደግሞ ሲያዩኝ ጆርባቸውን አዞሩብኝ ።

ለመነጋገር ፈቃደኛ ሆነው የተገኙትም ከኔ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የተቋረጠና ሁለተኛም እንዳላናግራቸውና አጠገባቸውም እንዳልደርስ አስጠነቀቁኝ ። ከሁኔታቸው እንደተረዳሁት ከሆነ የነአንቶኒዮ ሰዎች ስለ ፈጸምኩት ድርጊት በየቦታው ወሬውን አዳርሰውታል ። በዚህ ዓይነት ሥራ ታዋቂ ናቸው ። 'ጃክን እንዲያመልጥ የረዳ ማንኛውም ሰው ጉልበት ጉልበቱን እየተሰበረ ዕድሜውን በሙሉ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ያሳልፋል' የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል ። እግሩን ተሰብሮ የሚኖረውም ዕድለኛ ነው ። እንደሚሉት እግር ብቻ ሰብረው አይተዉም ። ቅጣታቸው ብዙውን ጊዜ ሞት ነው ። በመሆኑም ፊታቸውን ባዞሩብኝ ሰዎች ላይ መፍረድ አልችልም ። ብዙዎቹ የቤተሰብ ኃላፊዎችና ባለ ብዙ ልጆች ናቸው» አለና ዐረፍ ካለ በኋላ ፣ «ሌላው ፣ አይሮፕላን የሚያከራዩትንም ሰዎች አንጋግሬ ነበር ። ማንም ሰው ወደ ፈለገበት ለመሔድ ከጠየቀና አስፈላጊውን ገንዘብ ከከፈለ ያንገዙ የነበሩትም እነኝሁ ሰዎች ከአንቶኒዮ ደህና ጉርሻ አግኝተዋል መሰለኝ ፣ ሊያነጋግሩኝ አልፈለጉም ። ምን አለፋሽ አንቶኒዮ ሮሲ በደረሰበት በሙሉ ይሽን ሁሉ ሲያቀናጅ በመከረሙ ሁሉም በንኪኪ የሚጋባ ቁምጥና የያዘኝ ይመስል የሚጠጋኝ ሰው አጣሁ » ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ ።

«ጌጣጌጦችን ብንመልስላቸውስ?» አልኩት ።

«ካሁን ወዲያ ወደኋላ መመለስ አይቻልም ። ከጌጡ በበለጠ የፈለጉት ሕይወታችንን ነው ።» አለኝ ።

«እሺ ፣ ጥሩውስ ዜና ምንድነው? ለመስማት በጣም ቸኩያለሁ» አልኩት ። ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆም አለ ። እኔም ተጠግቼው ቆምኩና ብራንዲያችንን ፋት እያልን ጨረቃዋን ተመለከትናት ።

«ጥሩው ዜና ለሽያጭ ከወሰድኩት ግማሹን ገፍጨ ሐያ ሺ ብር አግኝቻለሁ»

በለሆሳስ ድምፅ ፣ «ጥሩ ነው» አልኩት ።

«ስለዚህ በገንዘብ በኩል ችግር የለብንም ማለት ነው ። ግን የት እንደ ሽጥኩት ታውቂያለሽ? የኩባ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ነው። ሚያሚ በሙሉ ከተለያየ ሀገር የመጡ ሰዎች የሞሉባት ናት ። የኩባ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከደቡብ አሜሪካም የመጡት አያሌ ናቸው ። ቦታው እንደልብ ገንዘብ የሚታፈስበት ነው ። እንደ ገመትኩት ብልጥ ብልጦቹ ከሀገራቸው ገንዘብ እየዘረፉ ሲነቃባቸው አምልጠው ወደዚህ የመጡ ናቸው ። እዚህ ከመጡ በኋላ ሐሺሽ በመሸጥ የበለጠ ሀብታም እየሆኑ ነው ። በየሰዓቱ የተለያዩ ዕቃች ሽያጭ እጅ በእጅ ይካሔዳል ። ምክ

ንያቱም በዚህ ዓይነት ንግድ የተገኘ ገንዘብ በቀላሉ ለማጥፋት ወይም ባንክ ለማስቀመጥ ስለማይችሉ፡ ጌጣጌጡን በፈለኩት ገንዘብ መሸጥ ችያለሁ ። ጥሬ ብር ከመያዝ ወርቅ ይዞ የትም መሔድ ስለሚቻል አነስተኛ ወርቅ በብዙ ገንዘብ ይገዛሉ » ሲሉኝ፡ በአንድ ምሽት ጄር ቪስ አንቶኒዮ ሮሲ ከመሆኑ በፊት ወርቅና አልማዝ እንደ ተፈለገው የትም አካባቢ ለመውሰድ ቀላል እንደሆነ የነገረኝ ትዝ አለኝ ።

«ሌላውና ጥሩ ደስ የሚለው ፡ በዚህ አካባቢ ያሉ ነጋዴዎች የራሳ ቸው ድርጅት ያላቸውና ራሳቸውንም የቻሉ በመሆኑ የማንም ድርጅት ተጽዕኖ የለባቸውም » ሲል ቀጠለና በተጽዕኖ ባይሆንም ፡ አልፎ አልፎ ከሌላ ድርጅት ጋር ስምምነት ሊኖራቸው ይችላል ። ይሁንና የደቡብ አሜሪካ ነጋዴዎች ሥራቸው ሐሺሽ በመሸጥ በመሆኑ፡ ሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ የሌቦች ድርጅት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለ ም» ሲል አስረዳኝ ።

«እና ታዲያ ፡ ከነዚህ ሰዎች ጋር መዋዋል እንችላለን ብለህ ትገም ታለህ?» አልኩት ።

«እንደምገምተው ከሆነ እንችላለን ። አማኑኤል ጋርቪያ ከሚባል ሰው ጋር ተገናኝቼአለሁ ። ስሙ በኛ አገር ጆን አስሚዝ እንደሚባለው ነው ። የያዝኩትን አልማዝ ሳሳየው ወዲት ፈጠ ምራቁን ቶሎ ቶሎ ዋጠ ። ከሚያሚ ሊያወጣን የሚችል አይሮፕላን ፡ ፓስፖርትና ቪዛ ፡ እንደዚሁም በምንሔድበት ጥርጣሬ የማያስከትል አዲስ መታወቂያ እንደምንፈልግ ነግሬዋለሁ ። እና እንጓለኝ ከሆነ ከራሱ ሰዎች ጋር በጉዳዩ ከተነጋገረ በኋላ፡ የተጠየቀውን ሁሉ ለማሟላት እንደሚችል ገልጾልኛል ።»

«ያሳየኸውን አልማዝ ብቻ ነው የሚፈልጉት ወይስ ሌላ ተጨ ማሪ ገንዘብ?»

«ከአልማዙ ሌላ ገንዘብ ይፈልጋሉ ። ሁለት መሆናችንን ከመና ገሬ በፊት አንድ መቶ ሺ ብር ጠየቀኝ ። ሁለት መሆናችንን ካወቀ በኋላ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር አለኝ ፡ ሃምሳውን ሺ አስቀንሰን በሁለት መቶ ሺ ብር መስማማት እንችላለን ።»

«አማኑኤል ጋርቪያ ያልከውን ሰው ታምነዋለህ?»

«በዚህ ዓይነቱ ሥራ ውስጥ አስቸጋሪው ነገር ይኸ ነው ። የፈለ ግሽውን ነገር ለማግኘት የግዴታ አንዱን ሰው ማመን አለብሽ ። ይኸን ሐሺሽ አጫሽ አላምነውም ፡ በታይው ይገርምሻል! እንደሴት በሽቶ

ታጥቧል ። ሆኖም በአሁኑ ሰዓት ያለን አማራጭ ከዚህ ሰው ጋር መዋ
ዋል ነው ።»

«ታዲያ በምን ተስማምታችሁ ተለያያችሁ?»

«ጋርቪያ የጠየቅነውን ሁሉ ማሟላት መቻል አለመቻሉን ከጓደ
ኞቹ ጋር ይነጋገርበታል ። የሚሳካላቸው ከሆነ ፡ ዋጋውን ለመነጋገር
በሰጠኝ ስልክ ቁጥር እየደወልኩ እጠይቀዋለሁ ። በየቀኑ ከሰዓት
በኋላ ሚያሚ ስልክ እደውልና ፓኮን እንዲያቀርብልኝ እጠይቃለሁ ።
ገና ተነጋግረው ካልጨረሱ ፓኮ ወጥቶአል ይሉኛል ። በጥያቄዬ
መሠረት ከተሳካላቸው የመጨረሻ ዋጋና እንዴት እንደሚያስወጡን
ለመነጋገር ፓኮ በስልክ ይቀርብና ሚያሚ መቼ መምጣት እንዳለብኝ
የት እንደምንገናኝ ይነግረኛል ።»

«ሁለት መቶ ሺ ብር እንኳ በጣም ብዙ ነው» አልኩኝ ጣልቃ
በመግባት ።

«ልክ ነሽ ፡ ብዙ ነው! ሆኖም ቦርሣችን ውስጥ ከሁለት ሚሊ
ዮን ብር በላይ የሚያወጣ ንብረት እንዳለን መርሳት የለብሽም ። እነ
ሱም ቢሆኑ የምንሰጣቸው ብር በሙሉ ትርፋቸው አይደለም ። መታ
ወቂያ ለሚያዘጋጀው ፡ ፓስፖርትና ቪዛ ለሚፈቅደው ፡ ለአይሮፕላን
ኪራይ ለመሳሰሉት ይከፍላሉ ። ምክንያቱም ሁሉም ጉርሻ ማግኘት
ያለበት ስለሆነ ፡ ሁለት መቶ ሺው ይሄን ያህል ብዙ አይደለም ። በተ
ለይ ደግሞ ፡ ከፖሊሶችና ከአንቶኒዮ ሮሲ እጅ ለማምለጥ የምንከፍ
ለው ከፍያ አይጐዳንም ።»

«ስለጥሩ ሐሳብህ ሲባል እንጠጣ» አልኩና የያዝኩትን ብራንዲ
ጨለጥኩት ።

ጃክም የራሱን ብራንዲ ጨለጠና የኔን ብርጭቆ ከጂ ላይ በመው
ሰድ ፡ የራሱንም ጨምሮ እስከ ቻለው ድረስ መዶ ባሕሩ ወረወረው ።
በጨረቃውም ብርሃን ብርጭቆዎቹ ባሕር ላይ ሲያርፉ ውሃው ተፈና
ጥቆ ባሕሩ ጸጥ አለ ።

«ሁኔታዎችን ስትገመግም የሚሳካልን ይመስልሃል?»

ፊቱን በቁጭት ክስክስ አድርጎ «ይሳካል! መሳካትም አለበት»
አለኝና ወደ ተለመደው ኑሮአችን ተመለስን ። ቁርስ በልተን ወደ
መዋኛው ሐይን እንጠጣለን ፤ ሲመሽ ራታችንን በልተን የወሲብ
ፍላጐታችንን አርክተን እንተኛለን ። ግን ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ ወደ
ሚያሚ ስልክ ይደውል ነበር ። ለአምስት ቀናት ያህል በተደጋጋሚ
ከሰዓት በኋላ ስልክ ደውሎ ፓኮን እንዲያቀርቡለት ጠይቆ ፓኮ ወደ
ውጭ የወጣ መሆኑንና መልዕክትም እንዳልተወ ሲገልጹለት ሰነበቱ ።

በስድስተኛው ቀን የተለየ መልስ መጣ ። ጃክ በስልኩ እየተነጋገረ ወረቀትና እስክሪፕቶ እንድሰጠው በምልክት ጠየቀኝ ፣ ሰጠሁት ። እስቲ ኦድራሻውን እንደገና ደግመልኝ እያለ በሰጠሁት ወረቀት ጻፈና «አዎ! ገብቶኛል፣ በጣም ጥሩ!» ሲል ቆይቶ ስልኩን ዘጋውና በወረቀት ላይ የተጻፈውን አድራሻ እየተመለከተ ፣ «እንደሚሉት ከሆነ የጠየቅነውን ሁሉ ማሟላት እንደሚችሉ ነው ። እና ነገ ወደ ሚያሚ እሔዳለሁ » ኦለኝ ።

«አብሬህ መሔድ አለብኝ?»

«አስፈላጊ አይደለም ፣ ያሁኑ ቀጠሮ ከኛ ምን ምን ነገሮችን እንደሚፈልጉና የምንከፍላቸው ገንዘብ ሪንት ሊሆን እንደሚገባው ፣ ስለምንሔድበት ቀን ለመነጋገር ስለሆነ አንቺ አታስፈልጊም» አለኝ ።

«ጌጣጌጦችን ይዘህ ትሔዳለህ?»

«ለምን? አንቺ ጋ ትቼው ነው የምሔደው ።»

«ስትመለስ የሚከተልህ ሰው መኖር አለመኖሩን አረጋግጥ»

በንቀት መልክ ተመለከተችኝና ፣ «አባቴ ያሳደገኝና ያስተማረኝ ደደብ እንድሆን አይደለም» አለች ።

የዚያን ለት ማታ ከፍተኛ ዝናብ ይጥል ጀመር ። በጠዋቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ዝናቡ የሚቀጥል መሆኑንና መኪና በመንዳት ላይ የሚገኙ ሰዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አስታወቀ ። ጃክ ወያ ሚያሚ የሔደው ዝናብ እየጣለ ነው ። የሚያስፈልገን የምግብና የመጠጥ ዓይነት ከፍላችን ውስጥ ስለአለ ፣ በዚህ ዶፍ ውስጥ ወደ ውጭ የምወጣበት ምክንያት አልነበረም ።

ቁርስ አዘጋጅቼ በላሁና እንደገና መጽሐፌን ታይፕ አድርጌ ጨረስኩ ። አሁን መጽሐፌ ካለንበት ሁኔታ ጋር የተስተካከለ ሲሆን ፤ ወደ አራት መቶ ስልሳ ሁለት ገጽ ደርሶአል ። ቢያስፈልግ በፖስታ ቤት በኩል ለአሳታሚ ድርጅት መላክ እችላለሁ ።

የምፈልገው አንድ ኮፒ ብቻ በመሆኑ ረቂቁን በሙሉ ቀድጄ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጣልኩት ። የእንቁላል ሳንድዊች አዘጋጅቼ ከበላሁ በኋላ ፣ በላዩ ላይ አንድ ቢራ ጠጣሁና የቦርሳዎቼን ዕቃ የአንዱን በአንዱ ማካተት ጀመርኩ ። የዲክ ልብሶችና እንዲሁም የሂሚናነበሩ ጥቃቅን ዕቃዎችን አንድ ላይ በአንድ ቦርሳ ውስጥ ጨመርኩት ።

በዚህ አካባቢ ስንዘዋወር የተመለከትኩት አሮጌ ልብስ መሸጫ ቦታ ስለአለ ፣ ይህንን ቦርሳ እዛ ወስደን ብንጥለው በጥቂት ደቂቃ ውስጥ

አንዱ እንደሚያነሣው አሰብኩና ለብቻው አደረኩት ። እንግዲህ የቀራን የእኔንና የጃክን ልብስ የያዙ ሁለት ሻንጣዎችና ጌጣጌጡ ያለበት አንድ ሻንጣ ብቻ ናቸው ። ሽጉጦቹን በፎጣ እየጠቀለልኩ በትከሻ በሚንጠለጠሉ ሁለት ሻንጣዎች አስቀመጥኳቸው ።

ይህን ሁሉ ካደረግሁ በኋላ ሰውነቴንና ጸጉሬን ታጥቤ የእጅና የእግር ጥፍሬን እየሞረድኩ ለሶልፋበር ፡ ለአልዶ ባይንደርና ጓደኛዬ ስልክ ልደውል ብዬ አሰብኩ ። ግን ስልካቸው ሊጠለፍ ይችላል ። ባይጠለፍስ ደውዬ ምን ልላቸው ነው ? ይሽ ሁሉ ሐሳብ ጃክ እስኪመለስ ድረስ ጊዜውን ለማሳለፍ የሞከርኩት ነው ።

ከዚህ የተለየ ሐሳብም አለኝ ። ጊዜውን ለማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ለመጨረሻ ጊዜ ለመጓጓዝ በዝግጅት ላይ መሆኔ ተሰምቶኝ ነበር ።

ዝናቡ እየበረታ ከመሐሉም በላይ ሰማዩ በዳመና ተውጦ ቀኑ ሊገባ ደድና ሌሊቱ ሊተካ ተቃርቧል ። እስካሁን ድረስ ጥሩ የሰላም ሰረፍት በማሳለፋችን የነበረን ጭንቀትና ፍርሃት በመጠኑም ቢሆን የለቀቀን ስለ ሆነ ጉዞአችንን መቀጠል አለብን ። አንቶኒዮ ሮሲም ሆነ ፖሊሶች እኛን እጃቸው ውስጥ እስክ አስገቡ ድረስ ሪረፍት ስለሌላቸው ፡ በየቦታው ፍለጋ ላይ እንደሚሆኑ አያጠራጥርም ። እንደ አሁኑ አንድ ቦታ ዝም ብለን ከተቀመጥን በቅርቡ ወይም ትንሽ ቆየት ብለው ሊይዙን ይችላሉ ። እኛን ለመያዝ በጣም ቀላል ስለሆነ ማድረግ ያለብን መደበቅ ሳይሆን መሸሽ ነው ።

ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ተኩል ሲሆን ፡ ጃክ በዝናብ ብስብስ ብሎና ፊቱ ገርጥቶ ጥርሱን በብርድ ምክንያት እያንቀጫቀጨ እክፍሉ ውስጥ ገባና ምንም ሳይናገር በዝናብ የበሰበሰውን ልብስ አወላልቆ ሰውነቱን በሙቅ ውሃ መታጠብ ጀመረ ። ታጥቦ እስኪወጣ ትኩስ ቡና አዘጋጀሁለት ። ታጥቦና ለባብሶ ሲወጣ ትኩሱን ቡናና ብራንዲ ሰጠሁት ። ሁለቱንም በጣም እንደ ተጠማ ሰው ቶሎ ጨለጠው ።

ሁለታችንም በጸጥታ ገመን ለገመን ቁጭ ብለን ፊታችንን ወደ መስኮቱ አዙረን የሚዘንበውን ዝናብ ተመለከትን ። ከዝናቡ ጋር የሚነፍሰው ነፋስ ድምፅ የሚያስቅስ ሕፃን ልጅ ይመስላል ። አልፎ አልፎ የሚሰማው የነጐድጓድ ጩኸት ከፍተኛና አስደንጋጭ ነው ።

ጃክን ስመለከተው መንቀጥቀጡን ያቆመ ቢሆንም ፡ በድጋሚ የተቀዳለትን የቡና ሲኒ በሁለት እጁ ግጥም አድርጎ ይዞአል ። በውሃ የተነከረው ጸጉሩ ግንባሩ ላይ ወርዶ ተኝቷል ። ፊቱም የገረጣ መሆኑ ያስታውቃል ። ያ ደፋርና ጀግና ሰው የደከመና የተሰላቸ ይመስል እጁን ጠረጴዛው ላይ አሳርፎ አንገቱን ወደ ጠረጴዛው ደፋ አደረገው ።

«እርቦህ ከሆነ የሚበላ ልስጥህ?» አልኩት ጠጋ ብዬ ።

«ከነዚያ ወንበዴዎች ጋር የዶሮ አሮስቶና በሚያቃጥል ቅመም የተሠራ ሩዝ በልቻለሁ ። የቅመሙ ማቃጠል ለነሱ ምንም አልመሰላቸውም ። እኔ ግን ከመቃጠሌ አልፎ ላብ በላብ ነው የሆንኩት ። አሁንም የቅመሙ ማቃጠልና ጣዕም ከአፌ አልጠፋም » አለኝ ።

«የት ቦታ ነው የበላኸው?»

«በኮስታ ሪካኖች መንደር አንድ ጉራንጉር ውስጥ በሚገኝና ከጓሮው አነስተኛ ምግብ ቤት ካለው ግሮሰሪ ነው ። በአካባቢው ብዙ ሰው ይበዛበታል ። ግን ከግሮሰሪው አንድም ሰው ዕቃ ሲገዛ አላየሁም ። ለስሙ የተከፈተ ሲሆን ፥ የግሮሰሪው ትልቁ ሥራ ሐሺሽ የሚያጨሱ ሰዎችን ማስተናገድ መሰለኝ ፥ ማን ያውቃል? ማታ ማታ የሚያጨሱበትና የሚገናኙበት ሊሆን ይችላል ። ብቻ በዚህ አካባቢ ምንም የማይደረግ ነገር ያለ አልመሰለኝም?»

«የሔድክበትንስ ጉዳይ እንዴት አደረክ?»

ወደኔ ዞር ብሎ ተመለከተኝና ፥ «እሱም ለራሴ በደምብ ባውቀው ጥሩ ነበር ። እነሱ የሚፈልጉት ለአማኑኤል ጋርቪያ ያሳየሁትን አልማዝና ሌላ ተመሳሳይ አልማዝ እንድሰጣቸው ነው ።»

«የእግዚአብሔር ያለህ! ጃክ! ይኸ ማለት እኮ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ነው ።»

«እንዳልሽው በሕጋዊ መንገድ ለሚገዛው ሰው ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ሊሆን ይችላል ። የኛ ክፍያ ግን ፥ በሕገወጥ መንገድ መሆኑን አትርሺ ፥ ቢሆንም ካለን ንብረት አኳያና ካለብን ችግር ጋር ሲነጻጸር ይኸን ያህል አይደለም ።»

ጃክ ያለኝ ሐቅ ቢሆንም ፥ ሌሎች የኛን ጭንቀትና ፍርሃት መጠቀሚያ ለማድረግ መሞከራቸው አናደደኝ ። «እሺ ይህን ከፍለን የምናገኘው ምንድነው?» አልኩት በቁጭት ጭምር ።

«ፓስፖርትና ቪዛ ፥ የቺካጐ ነዋሪነት መታወቂያ ፥ መንጃ ፈቃድና ከዚህ የምንወጣበት አውሮፕላን ።»

«ወዴትኛው አገር ነው የምንሔደው?»

«ኮስታሪካ ቢሆን ምን ይመስልሻል?»

ጥቂት አሰብኩና ፥ «ስለዚህች አገር እንዲሁ ወሬ ሰምቻለሁ ፥ ግን የት እንደምትገኝ አላውቅም » አልኩት ።

«በመካከለኛው አሜሪካ ውስጥ በኒካራጉዋና በፓናማ መካከል የምትገኝ አገር ናት ።»

«እና ኮስታሪካ ያለምንም ችግር መኖር እንችላለን?»

«እነሱ የሚሰጡን መታወቂያ ትክክለኛ ከሆነና የመኖሪያ ፈቃ ዱንም በየጊዜው ካሳደሱልን ችግር አይገጥመንም ። እንደሚሉት ከሆነ እዚያ የሚገኙ ባለሥልጣኖች በጃችን ሥር በመሆናቸው ችግር አይኖርም ብለውኛል ።»

«ከሚያስፈልገው በላይ ሰዎቹን እያመንክ አይመስልህም?» ስል ጥርጣሬ እየገባኝ ጠየኩት ።

«ምን ምርጫ አለን?» ብሎ አጉረመረመ ።

«ኑሺ! ታዲያ የጠየቁህንና ያሉህን በሙሉ እሺ አልካቸው?»

«አይ ሁሉንም አይደለም ፡ ለብዙ ሰዓት ተጨቃጭቀንበታል ፡ ሰዎቹ በጣም አደገኞች ናቸው ። ከአማኑኤል ጋሪቪያ ጋር ሁለት ሰዎች ነበሩ ። ከነዚህ ሰዎች ጋር ለመነጋገር የተስማማሁት ቀን በመሆኑ እንጂ ማታ ቢሆን አልሞክረውም ። ጭቅጭቃችን እየተካረረ ሲመጣ አንደኛው ሰውዬ ከኪሱ ትልቅ ጩቤ አውጥቶ የጥፍሩን ቆሻሻ በጩቤው እያጸዳ ትኩር ብሎ ይመለከተኝ ነበር» አለኝና ከሠልጠኑና ከጥሩ ሰዎች ጋር መነጋገርን የመሰለ ቆንጆ ነገር የለም ፤ ሰዎቹ አውሬዎች ናቸው » ሲል አስተያየቱን አከለበት ።

«እርግጠኛ ነኝ ፡ ሽጉጥህን ዝግጁአድርገህ እንደ ነበር!» አልኩት በመገረም ።

«አድርገህ ነበር ብቻ! ከኪሴ አውጥቼ ከጠረጴዛው ሥር ጭኔ ላይ አስደግፌ በእጄ ይዠው ነበር ። ለየት ያለ እንቅስቃሴ ባይ ኖሮ እመኚኝ ። ሦስቱንም መሞታቸውን ሳያውቁት እንደ ተቀመጡ እጨር ሳቸው ነበር ። ጋርቪያም ይሽን ፀውቆ ነው መሰለኝ ጩቤውን ኪሱ እንዲከት ነገረው ።»

«ብዙ ያጨቃጨቃችሁ ምኑ ነው?»

«መጀመሪያ አውሮፕላን ላይ ከመውጣታችንና መታወቂያዎቹን እኛን ከማስገባታችን በፊት ሁለቱንም አልማዞች እንድንሰጣቸው ጠየቁ ። እኔ ደግሞ ከመሐዳችን በፊት አንዱን አልማዝ ለመስጠት ሌላውን ደግሞ ኮስታሪካ በሰላም ስናርፍ ለወኪሎቻቸው እንደምሰጥ ነገርኳቸው ። ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ጋርቪያ ተስማማ ። ሌላው ደግሞ ፓስፖርቱንም ሆነ ሌላውን መታወቂያ ለመስጠት ከኔ ጋር መገኘት

ያለበት ጋርቪያ መሆን እንዳለበት አስታወቅሁ ። ይህንንም ያደረግ ኩት ሊፈጠር የሚችለውን ችግር ለመቀነስ ነበር ። ሆኖም በሰነዶቹ ላይ ፊርማ የሚፈርምበትም ሰው መኖር ግዴታ መሆኑ ስለ ተገለጸ ልኝ፡ ከጋርቪያ ጋር ሌላ አንድ ሰው እንዲኖር ተስማማሁ ። በመጨረሻ ብዙ ያጨቃጨቀን የመገናኛ ቦታችን የት ይሁን የሚለው ነበር ። ጋርቪያ የመረጠው እዚያው ምግብ ቤት ግሮሰሪው በሚዘጋበት እኩለ ሌሊት እንድንገናኝ ነበረ። እኔ ግን እብድ አይደለሁም፤ በእንደዚህ ዓይ ነት ቦታ የምገኘው ። እና አይሆንም አልኩኝ ። ሦስቱም በስጋኒኛ ሲያወሩ ቆዩ ። አስጋኒኛ ቋንቋ በመጠኑ ባውቅም በጣም በፍጥነት የሚ ናገሩ በመሆኑ አንድም ቃል መስማት አልቻልኩም። ወዲያው ንግግራ ቸውን አቆሙና በገልደን ሾርና በሶኒ ደሴት መካከል በሚገኝ በአንድ በፊራረሰ ሆቴል ቢሆንስ ብሎ ጋርቪያ ሐሳቡን አቀረበ። እንደ መሰለኝ ቦታው የባሕር ዳርቻ በመሆኑ ፡ ሐሺሽ የሚጭኑበትና የሚያራግፉበት ቦታ ነው ።

«በገልደን ሾርና በሶኒ ደሴት መካከል ! ትቀልዳለህ?»

«ለምን እቀልዳለሁ! ስሙን የጠሩልኝ እንዳዛ ብሉው ነው ። እና ዛሬ ከሰዓት በኋላ አካባቢውን እመለከትና የተስማማኝ ከሆነ ደውዬ እነግረዋለሁ ። ከዚያም ስምምነቱ ተግባራዊ እንደሚሆን ነግሬያቸዋ ለሁ ። አማኑኤል ጋርቪያ የፊራረሰውን ሆቴል በየት አቅጣጫ ሔጂ እንደማገኘው በምልክት ነግሮኛል» አሉኝ ። እንደ ተነገረው ሆቴሉን ለመፈለግ ወጣ ። ሆቴሉ በምሥራቅ ሚያሚ የባሕር ዳርቻ ፀሥር ኪሎ ሜትር አካባቢ ርቆ የሚገኝ ሲሆን ፡ ጀክ ግን ለሁለት ጊዜ በሆቴሉ አጠ ገብ እያለፈ ለብዙ ደቂቃዎች ያህል ሲፈልግ ቆይቶ በመጨረሻ ጊዜ ነበር ያገኘው ። ከዚያም ሆን ብሎ ለአንድ ሰዓት ያህል መኪናውን እየነዳ ያልታሰበ ችግር ቢፈጠር ማምለጫ የሚሆን አቋራጭ መግቢያና መውጫ መንገዶችን በደምብ አጠናቸው ። መኪናውን ወደ ፊረ ሰው ሆቴል አስጠግቶ በማቆም ወደ ሆቴሉ ገብቶ እያንዳንዳቸውን ክፍሎች በእግሩ እየዞረ ተመለከተ ። እንደ ነገረኝ ከሆነ «ቤቱ የፍሎሪዳ መሬት መንቀጥቀጥ በተነሣበት በፀሥራ ዘጠኝ መቶ ሐያዎቹ ውስጥ የተሠራ ነው ። ከመኻል ትልቅ ቡና ቤት ያለው ሆኖ በገንና በገኑ ለአልቤርጎነት የተሠሩ ክፍሎች ነበሩት ። እነዚህ አልቤርጎ ዎች በአሁኑ ጊዜ ፈራርሰዋል ።

በመኻል የሚገኘው ትልቁ ቡና ቤት ብቻ ጣራው ተበላስቶ በርና መስኮቶቹም ወላልቀው ይታያሉ ። የቤቱ ወለል በዕብነበረድ የተሠራ ቢሆንም ተሰነጣጥቋል ። ፀሐይና ዝናብ የተፈራረቁበት በመሆኑ ድሮ የነበረው ነጭ ቀለም ወደ ቢጫነት ተለውጦአል ።

የአጥሩ በር ከብረት የተሠራና በሰንሰለት ታስሮ የተቆለፈ ነው ። በበሩም ላይ ፣ «ያለ ፈቃድ እዚህ ቤት ውስጥ ገብቶ የተገኘ ሰው በሕግ ይቀጣል» የሚል ጽሑፍ ተለጥፎበታል ። ሆኖም በግራና በቀኝ የሚገኘው የሽቦ አጥር ብዙስፍራ የወጣ በመሆኑ ፣ የአጥሩን በር ለመክፈት ሳያስፈልግ ወደ ቤቱ በተፈለገው አቅጣጫ መግባት ይቻላል ። ይህ እየታወቀ የአጥሩ በር በቁልፍ መቆለፉ አስቂኝ ነው ። ትልቁ ቤት ውስጥ የአካባቢው ወጣቶች የሚዝናኑበትና ፊሽሽም የሚያጨሱበት ስለመሆኑ አንዳንድ ምልክቶች ይታያሉ ።

«ሦቱሉ በአራት ሐክታር መሬት ላይ የተሠራ ሲሆን፣ ከመሩረሱ በፊት የአትክልት ቦታና የመዝናኛ ሥፍራ እንደ ነበረው ምልክቶቹ አሉ ። ባሕሩ በጣም ቅርብ በመሆኑ ማዕበል በሚነሣበት ወቅት ውሃው እቤቱ ላይ እንደሚረጭ በግድግዳዎቹ መቀረፍ ይታያል ። በአሁኑ ጊዜ ፍርስርሱ የወጣው ሕንፃ ከጥቅም ውጭ በመሆኑ አልፎ አልፎ ሣር በቅሎበታል ። ከፍርስራሹ የተረፉ ሽክላዎችም እንደ ተወሰዱ ግልጽ ነው ።»

የቤት ውስጥ ጉብኝቱን እንደ ጨረሰ ከቤቱ ሲወጣ በተሰበረው መስኮት ወፎች እየበረሩ ሲወጡና ሲገቡ መመልከቱንም ነግሮኛል ። ወደ ባሕሩ ዳርቻ የአረጀና ንጉዱ የበሰበሰ ከጀልባ ወደ መሬት መሸጋገሪያ ድልድይ መኖሩንም ተመልክቷል ።

«እርግጠኛ ነኝ ጋርሺያ እና ጓደኞቹ ሰሐሺሽ ማራገፊያነት ቦታውን ይጠቀሙበታል ። ይኸውም እንደ መካከለኛ መርከብ ከጠረፍ ተነሥታ ወደ መካከለኛውና ደቡብ አሜሪካ ስትጓዝ የጠረፍ ጠባቂዎች ሊፈትሿት አይችሉም ። ምክንያቱም ዓለም አቀፍ የባሕር መንገድን ሳትሰቅ ስለምትጓዝ ነው ። ስለዚህ አነስተኛ ጀልባዎች ሌሊት ወደ መርከቡዋ በመሔድ የተጫነውን ሐሺሽ አውርደው ጀልባ ላይ ይጭናሉ ። እንደዚህ ሰው በማይታይበት ቦታ በጀልባ የመጣውን ሐሺሽ በመኪና እየጫኑ ወደሚፈለግበት ቦታ ለመውሰድ አመቺና አስተማማኝ ሥፍራ ነው » አለኝ ።

«እና ታዲያ ቦታው ምን ያህል አስተማማኝ ነውን» ስል ጠየኩት ። ትከሻውን ነቀነቀና ፣ «ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ ነው ። ቦታው ጥሩ ሆኖ ያገኘሁት ወደ ቤቱ ለመግባት የሚያስችል ከአንድ ጠባብ መንገድ በስተቀር ሌላ ባለመኖሩ ነው » አለኝና ፣ «ማድረግ የሚኖርብን ከቀጠሮአችን አንድ ወይም ሁለት ሰዓት በፊት እቦታው ተገኝተን እያንዳንዱን ክፍል በመፈተሽ የተደበቀ ሰው መኖር አለመኖሩን እና ረጋግጣለን ። ቤቶቹ ባዶ መሆናቸውን ካረጋገጥን በኋላ ከቤቱ ወጥተን በርቀት ቦታ ላይ ሆነን አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር ቤቱን እናያለን ።

አንድ መኪና ብቻ ከመጣና ሁለት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ካየን ወደእ ነሱ እንሔዳለን ። እቤት ውስጥ ከገባን በኋላ፣በሰባራው መስኮት በኩል ይህንኑ መንገድ አንዳችን በየጊዜው መመልከት አለብን ። ሌላ መኪና የሚመጣ ከሆነ እንወጣለን ።»

«ከወጣን በኋላስ?» አልኩት ።

«ወደዚያ ስንሔድ የሚያስፈልገንን መሣሪያ እንይዛለን። የሚያጋ ጥመን አነስተኛ ሰው ስለሆነ በቀላሉ ማምለጥ ነው ።»

«እሺ! ለምሳሌ ጋርቪያ የጠየቀውን አልማዝ ስንሰጠው ቃል በገ ባው መሠረት ፓስፖርታችንንና መታወቂያችንን ይሰጠናል እንበል ። ግን መቼ ነው ወደ ተዘጋጀው አውሮፕላን የምንሔደው?»

«ያለኝ አልማዙን ከሰጠሁት በኋላ አስፈላጊው ወረቀት እጃችን ይገባል። ከዚያም ወደ ተዘጋጀው አውሮፕላን መቼ መሔድ እንዳለብን ይነግረናል ።»

በመጮህና ግራም በመጋባት ፡ «ጃክ! በብዙ መንገድ ሊያጭበረ ብረን ይችላል» አልኩት ።

«በብዙ? ምን በብዙ ብቻ! በመዓት መንገድ ጉድ ሊሠራን ይችላል እንጂ! የሚያመጣልን ወረቀት እንኳን በከፍተኛ ባለሙያዎች ይቅርና በማንም ተራ ሰው የተጭበረበሩ መሆናቸው በቀላሉ ሊደረስባቸው የሚችሉ ሊሆን ይችላል ። ጋርቪያና አብሮት የሚመጣው ሰውዬ እቤት ውስጥ እንደገቡና ወረቀት ሳይሆን መሣሪያ አውጥተው በመደገን አል ማዙን ሊነጥቁን ወይም መንገድ ሳይ ሰው እንዲጠብቀን አድርገው ሊያስይዙን ፡ ወይንም አውሮፕላኑ ኮስታሪካ ሲደርስ አየር ማረፊያው ቦፖሊሶች ተከቦ ስንወርድ ሊያሳስሩን ይችላሉ ። ጂኒ! ሊያደርጉት ከፈ ለጉ በጣም ቀላል ነው ። እና አሁንም ቢሆን ቦታው የተስማማኝ መሆ ኑን ለጋርቪያ ደውዬ ስለ አልገለጽኩለት ከቀፈፈኝ ስምምነቱን ማቋ ረጥ እንችላለን » አለኝ ።

የትኛው መንገድ እንደሚሻል ለብዙ ሰዓት አሰብኩ ። መንገዳችን ሁሉ አደጋ የበዛበትና አማራጭም የጠፋበት ሆነ ።

«ቀደም ሲልም ነግሬሻለሁ ። የምትፈልጊ ከሆነ ከጌጣጌጡ ግማሹን ይዘሽ በፈለግሽው መንገድ መሔድ ትችያለሽ ። በኔ በኩል ምንም ቅሬታ የለኝም » አለኝ ጃክ በሀዘታዬ እያዘነ ።

«ካንተ መለየት አልፈልግም ። ግን ይሽ የኮስታሪካው መንገድ ከልተሳካልንስ ምንድነው የምናደርገው?» አልኩት ።

«የምናደርገውን የምናደርገውማ ሽሽታችንን መቀጠል ነው ። ምናልባት ከአንዱ ግዛት ወደሌላኛው ግዛት እንጓዛለን ። ምን ጊዜም አንቶኒዮ ሮሲንና ፖሊሶችን አንድ እርምጃም ቢሆን መቅደም አለብን ። ሁልጊዜ የሚከታተሉን ስለሆነ አንድ ቦታ መቀመጥ የለብ ንም ። በጉዟችን ላይ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥመን እንደ ተለመ ደው ከጌጡ ላይ እየሸረፍን በየከተማው እንሸጣለን ። ይሽን ነው የምትፈልጊው አይደል?»

«አልፈልግም ፡ ይሽን የመሰለ ኑሮ ከዚህ በኋላ ለመኖር አልሻም ። ይሽን ዕድል መሞከሩ ዋጋ የለውም ። ዝም ብለን ጉዞ ከቀጠልን ጊዜው ይርዘም እንጂ ፡ ሮሲም ሆነ ፖሊሶች እጅ መውደቃችን አይቀ ርም። ስለዚህ ለጋርቪያ ደውልና መስማማታችንን ንገረው» አልኩት ።

በእጁ ጉንጩን መታ መታ እያደረገ ፡ «ሁሉም ነገር እንዳሰብነው ይሳካልናል ፡ አትጨነቂ» አለኝ ።

«የግድ መሳካት አለበት!» አልኩት ።

ጀክ ሚያሚ ስልክ ደወለና የተወሰኑ ዐረፍተ ነገሮችን ተናግሮ ስልኩን ዘጋው ። ቀኑ ማክሰኞ ስለሆነ ሐሙስ ዘጠኝ ሰዓት ለመገናኘት ተስማሙ ። የረቡዕ ቀን ለፓስፖርትና ለመታወቂያ እንዲሁም ለመንጃ ፈቃድ የሚሆን ፎቶግራፍ ለማዘጋጀት እንድንችል የተደረገ ነው ። የተጠየቅነውን አልማዝ ከሰጠን በኋላና አስፈላጊውን መታወቂያዎች እጃችን እንዳስገባን ጋርቪያ ወደ ኮስታሪካ በሚያጓጉዘው አውሮፕላን የትና መቼ እንደምንሳፈር እንደሚነግረን በድጋሚ ገልጸልኛል » አለኝ ። በዚህም ስምምነት እንደ ተፈጸመ፡ የመብላት ፍላጎት ስላልነ በረን አንድ ጠርሙስ ቮድካ መጠጣት ጀመርን ። እንደኔ ከሆነ ሁለታ ችንም እንዳንያዝ በጣም ፈርተናል ። ለዚህም ነው ከምግብ በፊት የም ንጠጣው ።

ጋርቪያ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ሊከደን ሲሞክር ፡ ከሚደርስ ብን አደጋ እንዴት ማምለጥ እንደምንችል የተሰያዩ ሐሳቦችን በማቅረብ ተወያየንባቸው ። በእኛ በኩል ጋርቪያን ለማታለል ምንም ሐሳብ የለ ንም። የኛ ፍላጐት ሁሉም ነገር በሰላም እንዲያልቅ ነው። በመጨረሻም እኩለ ሌሊት ላይ አእምሮአችንም ሆነ ሰውነታችን በመድከሙ ተታ ቅፈን ተኛን ። ከውጭ ዝናቡ በኃይል ሲዘንብና አልፎ አልፎም የነጐ ድጓድ ድምፅ እየሰማን እ”ቅልፍ ወሰደን ።

በማግሥቱ ጠዋት የነጐድጓድ ጩኸትና ብልጭታ የቆመ ቢሆንም ሰማዩ ደመናማ ከመሆኑም በላይ ብርዳማ ነበረ ። አልፎ አልፎም የዝናብ ጠብታ ይወርዳል ። በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ መኪናዎች የፊት

መብራታቸውን እያበሩና የዝናብ መጥረጊያቸውንም ያለ ዕረፍት እያ ሠሩ በዝግታ ይጓዛሉ ።

የሄሚንና የዲክን ልብሶች ከነሻንጣው አሮጌ ልብስ የሚሸጥበት ቦታ ያለምንም ችግር ጣልንና ወደ ፎቶግራፍ አንሺ ቤት ሔድን ። እስኪደርቅ ቆየን ።

ፎቶግራፋችንን ከተቀበልን በኋላ፣ ወደ ሱቆች በመሔድ ኮስታ ሪካ ላይገኝ ይችል ይሆናል ያልናቸውን አስፕሪን ፣ ቫይታሚን ፣ የውሃ ማጣሪያና የተለያዩ ቅባቶች ገዛን ። ስለ ኮስታሪካ ያለን ዕውቀት በጣም አነስተኛ በመሆኑ ፣እዛ እንደ ደረስን የት አካባቢ መኖር እንደምንችል ፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መሟላት አለመሟላታቸውን አናው ቅም ። ጉዞአችን ወደማይታወቅ አገር እንደሚጓዝ ስደተኛ ሰው ግራ የተጋባ ነው ።

ወደ ምሽት ላይ ዕቃችንን ማዘገጃጀት ጀመርን ። በጣም የሚያስ ፈልጉንን ልብሶች ብቻ በመምረጥ በሻንጣችን ስንይዝ ፣ ለጋርቪያ የሚሰጠውን አልማዝ ለብቻ፣ ተመሳሳይ ዋጋ አለው ብለን የገመት ነውን ሌላ አልማዝ በተለየ ቦታ አስቀመጥነው ። በዚህም ጊዜ ነበር ከጃክ ጋር አስከፊና መሪር ጥል የተጣላነው ። ካቀረቀረበት ቀና አለና በሚቀጥለው ቀን ሐሙስ ጋርቪያ በቀጠረን ቦታ ስንሔድ ልብሳ ችንን እና ጌጣጌጡን ይዘን መሔድ አለብን » አለኝ ።

«ይህ የሞኝ ሥራ ነው ። ንብረታችንን በሙሉ ይዘን ሔደን አንድ ችግር ቢፈጠር ባዶአችንን ልንቀር ነው ። ማድረግ ያለብን መሣሪያና ለመስጠት ቃል የገባነውን አንዱን አልማዝ ብቻ ይዘን መሔድ ነው ። ምናልባት እንደ ዕቅዳችን ሁሉም ነገር ከተሳካ ወደ ሆቴላችን ተመል ሰን ዕቃዎቻችንን በመጫን አውሮፕላኑ ወደሚነሣበት ቦታ እንሔዳ ለን» አልኩት ።

«ስሚ! ከሪፕስ እስከ ቀጠሮአችን ቦታ ድረስ ቢያንስ የሁለት ሰዓት መንገድ ነው ። ለጋርቪያ አልማዙን ከሰጠነው በኋላ አሁኑኑ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ሒዱ ቢለንስ ምን ልንሆን ነው? እዚህ ተመልሰን ዕቃችንን የምናነሣበት ሰዓት አይኖረንም» አለኝ ።

«እንደዚህ ከሆነ እንቀራለን ። ስምምነቱም ይፈርሳል ፣ ቢያንስ የሁለት ሰዓት ጊዜ ሊኖረን እንደሚገባ መናገር አለብህ ።»

«የክርስቶስ ያለህ! አውሮፕላኑ በተመደበለት ሰዓት የሚበር ሕጋዊ መሰለሽ? እነሱ አውሮፕላን ይነሣል ባሉን ሰዓት መገኘት አለ ብን! ይህ ካልሆነ ቀረን ማለት ነው» አለኝ በንዴት ፊቱ ተኮማተሮ ።

እኔም እንደሱ በንዴት ቱግ ብዬ ፡ «ይህ ከሆነ አሁንም አንሔድም፡ ንብረታችንን ተሸክመን ወስደን እጃቸው ላይ መጣል የለብንም! ይህ ጭልጥ ያለ ደደብነት ነው ፡ እዚያ መሔድ ያለብን...»

«ይኸን እናደርጋለን ፡ ይኸን አናደርግም የማለት ሥልጣን ማን ለጠሽ?» አለኝ በመኻል አቋርጦ። «እዚህ ደረጃ የደረስነው በኔ ሐሳብ እንጂ ባንቺ አይደለም» ሲልም ጨመረበት ።

ከውስጥ የተሰማኝን ፡ ገንፍሎ «ደደብ! አንተ የሠራኸው ሥራ ሁሉ ብላሽ ነው! እያንዳንዱ ፖሊስና ሮሲ የት እንደምትገባ እያወቁ ሚያሚ ድረስ ይዘኸን የመጣኸውና ሄሚና ዲክ እንዲገደሉ ያደረከው አንተ ነህ! ሚያሚ ስትገባ እንደ አንድ ንጉሥ አቀባበል ይደረግልኛል ብለህ አልመህ ነበር ። የሚያውቁህ እንኳን ዐይንህ ላፈር አለህ» አልኩት ።

«ለናንተ ብዬ ነው መከራዬን ያየሁ እንጂ ፡ ብቻዬን ብሆን ኖሮ የማይሳካልኝ መሰለሽ? ደደብስ አንቺ ነሽ ! እንደ አራስ ልጅ አንቺን መንከባከብ ነበረብኝ ። የዐሥር ዓመት ልጅ በቀላሉ የምትዘለውን ጣሪያ መገለል አቅቶሽ እሹሩሩ እያልኩ እድሽን ይዤ ማሻገር ነበረ ብኝ! አንቺና ዲክ እንቅፋት ሆናችሁብኝ እንጂ ፡ እናንተ ባትኖሩ ኖሮ እስካሁን ድረስ ወደ ፊለኩት አገር መሔድ እችል ነበር ። ምን ያደርጋል እኔም ደደብ ነኝ ። ሁለታችሁን እዚያው ኒውዮርክ አንዶኒዮ ሮሲ እንክብካቤ እንዲያደርግላችሁ መተው ነበረብኝ ። እስካሁን ለኔ ችግር ፈጣሪዎቼ ናችሁ እንጂ የሰጣችሁኝ ጥቅም የለም ። አሁን ደግሞ የኛ ሴት ወይዘሮ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ ልትነግሪኝ ትሞክ ሪያለሽ? ዐይንሽን ማየት ነው የጠላሁት» አለኝ እንደ ተኰሳተረ ።

ስማ! በዚህ መልክ ወደ ቀጠሮ ቦታ የምትሔድ ከሆነ ወዲያው እንደምትሞት ዕወቀው ። ቁጥል ሒድ! በመሞትህ ትንሽም ቅር አይለኝም! ጭንቅላት የሌለህ ስለሆነ ቁጥል! አሁንም ጌጡን ይዘህ ሒድና ለጋርቪያ ያለኝ ጌጥ ይኸው ነው ፤ የሚቢታህ መሰለኝ በለውና ጉንበስ ብለህም እግሩን መሳም አትርሳ! እኔ ግን ከዚህ ውጭ መሆኔን ዕወቅ! ደደብ ነህ! ገባህ?» ብዬ ጮኩበት ።

ሁለታችንም በንዴት ሰውነታችን እየተንዘፈዘፈ ተፋጠን ቆምን ። እንዳችን እንኳን ሌላ ቃላት መነጋገር ብንጀምር ጉሮሮ ለጉሮሮ መተናነቃችን አይቀርም ነበር ። ይኸንን ሁለታችንም ዐውቀነዋል መሰለኝ ትንፍሽ አላልንም ። ጀክ ፊቱን ከኔ አዙሮ እጁን ኪሱ ከተተና ወደ መስኮቱ በመሔድ የሚዘንበውን ዝናብ ይመለከት ጀመር ። እኔም አጠገቤ ከነበረ ወንበር ዘፍ ብዬ እግሬን ዘርግቼ ተቀመጥኩና በንዴት

በሚንቀጠቀጠው እጄ ሲጋራ አቀጣጥዬ ማጨስ ጀመርኩ ። ምን እንደ ማስብ ማወቅ አልቻልኩም ። በተቻለ መጠን ራሴን ለመቆጣጠር ሞከርኩ ። የሠራነው ሁሉ የእብድ ሥራ ነው ፤ ለማልቀስ ባለ መሞከሬ ራሴን በራሴ አመሰገንኩት ፤ ኩራትም ተሰማኝ ።

ጀክ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ ይናገራል ። የሚለውን ግን በደንብ መስማት አልቻልኩም ። ከጥቂት ጊዜ ዝምታ በኋላ ግን «ባለፉት ሳምንታት ወይዘሮ ሮዛ ቤት ፣ እኔ አንቺና ዴክ ሆነን ያሳለፍነው ጊዜ በመራራ ሕይወቴ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም የተደሰትኩበት ጊዜ ነበር» አለኝ ።

ሲጋራዬን በመተርከሻው ላይ አጠፋሁና ተነሥቼ ወደ ጀክ ሔጄ ትከሻውን ያዝኩና ወደ ራሴ አዙሬው ዐይን ለዐይን ዝም ብለን ስን ተያይ ከቆየን በኋላ ፣ «እኔም እንደዚሁ ፍጹም ደስተኛ ነበርኩ። ከዚህ በኋላ የፈለገው መጥፎ ነገር ቢመጣም ፣ያሳለፍነው ጥሩ ጊዜ የሚይረሳ ነው ። እና የምናስታውሰው ትዝታ አለን» አልኩት ።

እዎ ልክ ነሽ ፤ የምናስታውሰው ጥሩ ጊዜ ግጥሞን ነበር » ብሎኝ በረዥሙ ተነፈሰና፡«እንቺ ባልሽው መንገድ ወደ ቀጠሮአችን እንሒዳለን ። ጥዋት አንዱን አልማዝ ብቻ እንውሰድና አውሮፕላኑ እኛ በፈለግነው ሰዓት መነሣት እንዳለበት እንነግራቸዋለን ። የማይሰሙ ከሆነ ገደል ይግቡ ፣ ይተዉት!» አለኝ ።

«የፈለከውን ማለት ትችላለህ ፤ በምትለው ሁሉ እስማማለሁ ። አሁንም አለቃው አንተ ነህ» አልኩት ደስ እንዳለው ።

ሐሙስ ጠዋት ዝናቡ መዝነቡን ያቆመ ይሁን እንጂ ከፍተኛ ጉም አለ ። በቅርባችን የሚገኘውን ባሕር እንኳ ማየት አልቻልንም ። ጠዋት ቁርሳችንን ለመብላት ወደ ከተማ ስንወጣ ፣ በወደፊቱ ኑሮአችን ዐይን ብሩህ ተስፋ በምናገኝበት ወይም በምናወጣበት በዚያን ቀን አንድ ትልቅ ፔሲካን ወፍ በጭቃና በደም ተለውሶ መንገድ ላይ ወድቆ አየነው ።

ወደ ክፍላችን እንደ ተመለስን፣ ወደ ቀጠሮው ቦታ ይዘነው የምን ሔደውን መሣሪያ ጀክ እየወለወለ አስፈላጊውን ጥይት አጐረሰው ። አንድ ሽጉጥ በወገቡ ፣ አንዱን በጀኬቱ ኪስ ሦስተኛውን መኪናው ውስጥ ሲያደርግ ፣እኔ ደግሞ አንድ ሽጉጥ በገናብ ልብስ ኪሴ ፣ አንደኛውን በቦርሳዬ ያዝኩ ።

«ጄኒ! መተኩስ የሚያስፈልግሽ ከሆነ... ብቻ አስፈላጊ አይመስ ለኝም ፣ ግን ካለብሽ የያዝሽውን ሽጉጥ ከኪስሽ ለማውጣት ጊዜ አት

ፍጂ ። ሽጉጡ እኪስሽ ውስጥ እንዳለ ወደምትፈልጊበት ቦታ አልመሽ ምላጨን ሳቢው ። ጃኬቱ ሊታጠል ይችላል ፣ ቢሆንም የሚያሠጋ አይ ደለም » አለኝ። ከዚያም «ልክ እንደዛ እንደ ደረስን እጅሽን እኪስሽ ውስጥ አስገብተሽ ሽጉጡን መያዝ አለብሽ ፤ ገባሽ?» ሲል አስጠነቀቀኝ ።

«ገብቶኛል » አልኩት ።

ከሰዓት በኋላ ጃክ መኪናዋን እየነዳ ወደ ቤንዚን ማደያ ሔድንና ነዳጅ ሞልተን ወደ መንገድ ቁጥር አንድ ተጓዝን ። በመንገድ ላይ ያሉት መኪናዎች የፊት መብራታቸውን እያበሩ በዝግታ ይጓዛሉ ። ከጐልደን ሾርስ በታች ስንደርስ ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶችን ማለፋ ችንና ወደ ምሥራቅ መጓዛችንን እንጂ ፣ የት እንዳለን ማወቅ አልቻል ኩም ። ያለፍንበት መንገድ ሜዳማና ምንም የሚታይ ነገር የለውም ።

«መንገዱን ዐውቀሽዋል? አልተሳሳትክም?»

«አትጨነቂ ፣ በደንብ ዐውቀዋለሁ ።»

እውነትም ዐውቆታል ። በመጨረሻ ወደ ግራ ታጠፍንና አንድ መንገድ ብቻ ወደ አለው አቅጣጫ ገቦ ጀመርን ። መንገዱ በአስፋልት የተሠራ ቢሆንም ፣ አገልግሎት መስጠት ያቋረጠና አልፎ አልፎ የተ ሰነጣጠቀ ግርም የበቀለበት ነው ። መታጠፊያውን መንገድ እየተከ ተልን ዝግ ብለን እንደ ተጓዝን ከበስተቀኝ በኩል በሽቦ የታጠረና የፈራረሰ አጥር ተመለከትኩኝ ።

«ይኸውልሽ ወደዚህ ቦታ መግቢያም ሆነ መውጫው ይኸ መን ገድ ብቻ ነው » አለኝ ጃክ ።

ወደቤቱ መግቢያ ደረስንና መኪናችንን አቁመን ፣ «ተመልከቺ» አለኝ ፣ ወደ ቤቱ እያሳየ። በዚህ በጭጋግ ውስጥ ቤቱ እርቃኑን የቆመ ትልቅ ጭራቅ መስሎ ይታያል ። ቤቱ በዕድሜው የገፋና የፈራረሰ በአሁኑ ጊዜም የቆሻሻ መጣያ መሆኑን ብቻ ነው መግለጽ የምችለው ። ወፎች ሲገቡና ሲወጡ ይታያሉ ። ከመፈራረሱ በፊት ምን ያህል ደስ ይል እንደ ነበርና ብዙም ሰዎች ለመዝናናት እንደሚመጡ ለመገመት ሞከርኩ ። ግን ግምቴ ትክክል መሆኑን እጠራጠራለሁ ። ምክንያቱም ቤቱ ድሮ በነበረበት ሁኔታ ላይ ስለማይገኝ ነው ።

«ለኛ ተስማሚ የሆነ ማረፊያ አዘጋጅተውልን ይሆን?» አልኩ እየ ሳቅሁ ።

«እንሒድና እንመልከት!» አለኝ ።

ከመኪናችን ወረድንና ኮቴአችን ከሩቅ እንዳይሰማ በጥንቃቄ ተራመድን ። ሆኖም የኮቴአችን ጩኸት ለራሳችን ይሰማን ነበር ። እቤቱ ከመድረሳችን በፊት ጫማዬ በሰበሰ ። ያልፈረሰውን ግድግዳ እየተጠጋን ያረጀውን መውጣት ስንጀምር በጣም የሚገማ ነገር ሸተተኝ ።

«በስመ አብ» አልኩኝ ፣ በዚያ ትንፋግ ታፍኜ ።

«ውስጥ ስንገባ ይብሳል ፣ አፍንጫሽን በእጅሽ ይዘሽ በአፍሽ ለመተንፈስ ሞክሪ» አለ ሲያሾፍብኝ ። በአንድ በተሰበረ በር በኩል ወደ ውስጥ ገባን ። ልክ ጃክ እንደ ነገረኝ የቤቱ ክፍሎች በሙሉ በቆሻሻ ተሞልተዋል ። ወደ አራተኛው ክፍል ስንደርስ ጣሪያው ተነሥቶ ሰማዩ ይታያል ። እክፍሉ ውስጥ ስንገባ የነበራት ወፎች በረሩ ። የዐይጥ ድምፅም ይሰማል ። ትንሽ እባብም ከተቆለለው ድንጋይ ውስጥ ተኝቶ አየሁኝ ። የሁሉም ክፍሎች በር የተሰበረና ደህናውም ተነቅሎ የተወሰደ ስለሆነ ፣ በጸጥታ እየተዘዋወርን ውስጣቸውን ተመለከትነው ። ጃክ እንደ ገለጸው ሐሺሽ አጫሾች በዚህኛዎቹ ክፍሎች እንደተጠቀሙባቸው አንዳንድ ምልክቶች አሉ ።

ከትልቁ ቤት በስተኋላ ወደሚገኘው ክፍል ሔድን ። ክፍሉ ሰፋ ያለ ሆኖ እንደሌሎቹ ክፍሎች በርም መስኮትም የለውም ። እክፍሉ ውስጥ ሆኖ መንገዱን በደምብ ማየት ይቻላል ። የራሳችንንም መኪና ቆማ አየናት ። «የምንገናኘው እዚህ ክፍል ውስጥ ነው ። የምነጋገረው እኔ ብቻ ነኝ ። ማለቴ መናገር የምትፈልጊው ነገር ካለ መናገር ትችያለሽ ፣ ሆኖም ዐይንሽ ከመንገዱ መለየት የለበትም ፣ መኪና ወይም ሰው ካየሽ ትነግሪኛለሽ ።»

«ችግር የለም ! መንገዱ ላይ ለየት ያለ ነገር ካለ እጮኻለሁ ።» አልኩት ።

«በጣም ጥሩ!» አለና ሰዓቱን ተመልክቶ ፣ «ከአንድ ሰዓት በላይ ያለን ስለሆነ እንውጣና ወደዚህ የሚመጡት እነማን እንደሆኑ የምናይበት ቦታ እንፈልግ» አለኝ ።

መኪናችንን አስነሣንና ወደ መጣንበት መንገድ ተመልሰን ትንሽ እንደተጓዝን የሚያቋርጥ የጠጠር መንገድ በማግኘት ወደ ውስጥ ገባን ። ካለንበት ራቅ ብሎ የመኖሪያ ቤቶች ይታያሉ ። መኪናችንን አቆምንና ሲጋራ አውጥተን በማቀጣጠል እያጨስን መጠባበቅ ጀመርን ። ጃክ አርቆ የሚያሳይ መነጽር ይዞአል ። ግን ምንም ጥቅም የለውም፤ መነጽሩ በዚህ ጉም ውስጥ ከዐሥርና ከዐሥራ አምስት ሜትር ርቀት በላይ አያሳይም ። ደግሞም እኛ ከአስፋልቱ መታጠፊያ የገባነው ርቀት አነስተኛ

በመሆኑ ሆቴሉን ያለመነጸር ማየት እንችላለን ። በጭጋግ ተሸፍነን ሲጋራችንን እየጨስን በሹክሹክታ አወራን ። ጃክ ስለኔ ሕይወት ቡትለ ይም የት ቦታ እንደ ተወለድኩ ፣ እንዴ ኖርኩና በሕፃንነቴም ስለ ጐበኘ ሁዋቸው ሥፍራዎች እንድነግረው ጠየቀኝ ።

በአብዛኛው ማወቅ የፈለገው ካደግሁ በኋላ እንዴት እንደኖርኩ ፣ የወላጆቼ መኖሪያ ቤት ምን እንደሚመስልና ስንት ክፍሎች እንዳሉት ፣ የአሽከሮቻችንና የመኪናችን ብዛት ስንት እንደሆነ፣ ስለ ተማርኩበት ትምህርት ቤት ፣ ቤተሰቦቼ ለኔ ልብስ መግዣ ምን ያህል ገንዘብ እን ዳወጡ ፣ ለገና በዓል የሚሰጡኝ ስጦታ ምን ዓይነት እንደሆነ ነው ።

ጥያቄው ምንም አላስገረመኝም ። ሀብታሞች የሚኖሩትን ኑሮ ለመኖር የሚመኝ በመሆኑ ይህን ለማወቅ ጓጉቶአል ።

ከዚህ በፊት በትላልቅ ሆቴሎች ያያቸው ሰዎች ሻምፓኝ እየ ጠጡ ሲሳሳቁና እስተናጋጁዋም በፈገግታ ስታስተናግዳቸው የተመ ለከተ በመሆኑ፣ 'ሕይወት ማለት ከዚህ ውጭ አይደለም' የሚል እምነት ተቀርፆበታል ። ይኸ ደግሞ እሱም እንዳለው ገንዘብ ስለአላቸው ብቻ ሳይሆን በሰዎች መካከል ልዩነት እንዲፈጠር ያደረገው የየመደቡ ጀርባ ልዩነት ጭምር ነው ።

የጠየቀኝ ስለማያውቀው ሕይወት በመሆኑ ራሴን ሳላኩራራ ገንዘብ ካለው ቤተሰብ የተወለደ ሕፃን የልጅነት ጊዜው ምን እንደሚ መስል ፣ ለማንኛውም ጉዳይ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች በሌሎቹ ዐይን በጨዋነትና በደግነት እንደሚታዩ ፣ ኑሮአቸው የአማረና በሕልማቸው የሚያልሙትን ሁሉ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን ስነግረው ፣ ፈገግ እያለ አገላለጼ የገባው መሆኑን ለማሳየት ራሱን በአዎንታ ያወዛውዝ ነበር ።

በርግጥ የምነግረው ሁሉ ከዚህ በፊት ያልገመተውን ወይም ይሆ ናል ብሎ ያላሰበውን አይደለም ። በዚህ ዓይነት ኑሮ ውስጥ አይደግ እንጂ ፣ ገንዘብ ካለ ኑሮ ምን እንደሚመስል በደምብ ያውቃል። ግን ኑሮ ውን ከኖሩት ሰዎች አንደበት መስማቱን ፈልጐት ነው ።

ከዘጠኝ ሰዓት ጥቂት ደቂቃ አለፍ እንዳለ ድምፅን ከፍ አድርጎ «መኪና እየመጣ ነው» አለና ወንበሩ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ ።

ሁለታችንም በመስኮት በኩል መመልከት ጀመርን ። አንድ ረዥም ጥቁር ካዲላክ መኪና በአስፋልቱ መንገድ ቀስ እያለ ተጉዞ ታጠፈ ።

«መኪናው ውስጥ ስንት ሰዎች ይታዩሻል?»

«ከፊት የተቀመጡ ሁለት ሰዎች?»

«አዬም ያየሁት ሁለት ሰዎች ነው ። እንከተላቸው» አለኝ ።

የመኪናውን ሞተር አስነሣና ወደ ሆቴሉ ወደሚወስደው አስ ፋልት መንገድ ታጠፍን ። ከፊታችን ያለፈው ካዲላክ አይታይም ። ወደ ሆቴሉ ልንደርስ ስንል ሆቴሉ በር ላይ ቆሞ አየነው ። ሁለቱም ሰዎች ከመኪናው ወርደው ወደ ሆቴሉ በመግባት ላይ ናቸው ።

ጃክ በመደሰት መልክ፡ «አጭሩ ሰውዬ ጋርቪያ ነው ፡ እርግጠኛ ነኝ ረዥሙ ሰው ፓስፖርት የሚያዘጋጀው ሳይሆን አይቀርም ። ሆቴሉ ውስጥ እስከሚገቡ እንጠብቅ » አለ ።

ሁለቱ ሰዎች ወደ ውስጥ መግባታቸውን እንዳየን ፡ ጃክ መኪና ውን በፍጥነት እየነዳ ከካዲላክ አለፍ ብሎ ወደ ፊት ፡ ወደ ኋላ ከተን ቀሳቀሰ በኋላ የመኪናውን ፊት ወደ መጣንበት አዙሮ አቆመ ። ሞተ ሩን በማጥፋት የመኪናውን ቁልፍ እዛው እንደ ተንጠለጠለ በመተው ወረድን ።

ፈገግ አለና ፡ «ምናልባት በፍጥነት ከዚህ ቦታ መሔድ ካለብን የመኪናውን በር አለመቆለፉ ጥሩ ነው» አለኝ ። እንዳለውም በሩን አልዘጋነውም ።

ወደ ካዲላክ ሐዲን አየን ፡ ውስጡ ባዶ ነው ። የዕቃ ማስቀመ ጫውን የኋላ በር ጃክ ለመክፈት ሞክሮ ቁልፍ ነው ።

«በዚህ በኩል ችግር የለም! ወደ ውስጥ ልንገባ ነው ፡ ተዘጋጅ ተሻል ?» አለኝ ።

«ተዘጋጅቻለሁ ።»

አውንም በፈገግታ ተመልከቶኝ ሳብ አድርጎ ከንፈሬን ሳመኝና «ማሽነፍ ወይም መሸነፍ» አለኝ ።

«ትክክል !»
«እንሒድ» አለኝ ።

በፈራረሰው አጥር ገብተን ወደ ሆቴሉ አመራን ። ሁለታችንም የቁኝ እጃችንን ኪሳችን ውስጥ ከተነዋል። ለሚያየን ሰው ነፍሰ ገዳዮች እንመስላለን ። ጃክ ቆም አለና አካባቢውን ተመለከተ ። የሚታይ አሳሳቢ ነገር የለም ። «የነገርኩሽን አስታውሺ ፡ መንገዱን መመል ከት አትርሺ ፡ እኔ በምንጋገርበት ጊዜ ከፊት በኩል የተሰየ እንቅስ ቃሴ ካለ የተኩስ ሽፋን ለኔ እየሰጠሽኝ ለመሮጥ ተዘጋጂ ።»

የገባኝ መሆኑን ራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ ። ወዲያው ሽንቱ የመጣ መሰለኝ ።

ቀደም ሲል ከመረጥነው ክፍል ሳይሆን ፣ ሌላ ክፍል ውስጥ እየ ጠበቁን ነው ። ጋርቪያ የዝናብ ልብስ በልብሱ ላይ ደርቧል ። ያደረ ገው ጫማ በቢጫና በጥቁር ቀለም የተሸፐሎረሎረና ረሸም ተረከዝ ያለው ነው ። ኰሌታው ትልቅ የሆነ ሸሚዝ የለበሰ ሲሆን ፣ ሰፊ ክራ ቫት አስሮአል ። ጸጉሩን በቅባት ለጥ እስኪል አበጥሮአል ። በሁለ ቱም እጆቹ ትንንሽ ጣት ላይ የአልማዝ ቀለበት አስሮአል ፣ ለመሣቅ ፈገግ ሲል ያስተከላቸው የወርቅ ጥርሶች ያንጸባርቃሉ ። ጃክ ያለው እውነቱን ነው ። ሰውየው ሽቶ የተቀባ ብቻ ሳይሆን ታጥቦበታል ማለት ይሻላል ። ገና እክፍሉ በር ስደርስ ነው የሸተተኝ ። ረሸሙ ሰውየ ፓስፖርት የሚያዘጋጀው ሳይሆን አይቀርም ። ጥቁር ኮትና ሱሪ ፣ የቆሸሸ ሸሚዝ ለብሶ ጥቁር ክራቫት አስሮአል ። ሲያዩት የመ ቃብር ቦታ ኃላፊ ይመስላል ። ረሸም ፊት ያለው ሲሆን ፈንጣጣ በልቶታል ። እኛን በቀጥታ ማየት የፈራ ይመስል ዐይኑን ወዲያና ወዲህ ያንከራትታል ። ዐይን አፋር መስሎኝ ነበር ። ያለማየቱ በመ ፍራቱ ምክንያት ይመስላል ፣ በጣምም እንያ ተጨነቀ ያስታውቅ በታል ። የወረቀት ቦርሣ የያዘው እጁ ይንቀጠቀጣል ።

ከመኻላችን ለመተዋወቅ የጠየቀ አልነበረም ። ጃክ ቀደም ሲል የመረጥነውን ክፍል በእጁ እያመለከተ ፣ «እዛኛው ክፍል እንሒድ» አለ ።

«ለምን እዚህ አይሆንም» አለ ጋርቪያ ። ድምፁ በጣም ወፍራም ነው ።

«በጣም ግልጽ ቦታ ስለ ሆነ ነው» በማለት ጃክ ንግግሩን አሳ ጥሮ ወደ ክፍሉ ሲያመራና ሲከተሉት ፣ በተቻለ መጠን ከሰዎቹ ራቅ ብዬ ጥግ ጥጉን ተከተልኳቸው ።

እክፍሉ ውስጥ ከገባን በኋላ ፣ መንገዱን ለማየት በምችልበት ጥግ ቦታ ሆንኩና መንገዱንም ፣ እነሱንም መመልከት ጀመርኩ ። ሽጉጤን እኪሴ ውስጥ እንዳለ ጠበቅ አድርጌ ይገፍዋለሁ ። ጣቴን ግን ምላጩ ውስጥ አላስገባሁም ። ጃክ አሁንም ቀኝ እጁን ከኪሱ አላወጣም ።

ጋርቪያ የለበሰው የዝናብ ልብስ ሲታይ ምንም መሣሪያ እንዳል ያዘ ያስታውቃል ። ሰላማዊነቱን እንድናውቅለት ሁለቱንም እጆ ቹን ወደ ኪሱ ለመክተት አልሞከረም ።

«አልማዙን ይዛችኋል ?» ብሎ ጠየቀ ።

«አዎ ይዘናል ። እናንተስ ወረቀቶቹን አዘጋጃችሁ ?» አለ ጃክ ።
«ጆ ! አሳየው» አለ ጋርቪያ ።

ሦስቱም ተጠጋግተው ቆሙ ። ረዥሙ ሰውዬ ከቦርሣው ውስጥ አውጥቶ ሲሰጥ ሲል ከመደናገጡ የተነሣ አንድ ወረቀት መሬት ላይ ወደቀበት ። ቶሎ ለማንሣት ሞከረና በይቅርታ መልክ ፈገግ ብሎ ያዘጋጃቸውን ወረቀቶች ለጃክ ሰጠ ።

ወደ መንገዱና ወደ በሩ ተመለከትኩ ። ከቆሙት ሁለት መኪኖች ሌላ በአካባቢው ምንም አይታይም ።

ጃክ ሽጉጥ የያዘበት እጁን አውጥቶ ወረቀቶቹን በጥንቃቄ መመርመር ጀመረ ። ሰዎቹ እርምጃ ለመውሰድ ቢፈልጉ ከዚህ ሰዓት ሌላ የተሻለ አማራጭ አያገኙም ። ሰዎቹን በጥንቃቄ ተመለከትኳቸው ፣ ምንም እንቅስቃሴ አላሳዩም ፣ ጃክ ወረቀቶቹን ሲመለከት ዝም ብለው በትዕግሥት ያዩታል ።

ፓስፖርትና ቪዛውን ፤ የመታወቂያ ካርዱንና የመንጃ ፈቃዱን እያገላበጠ መመልከቱን ሳይጨርስ ራሱን ቀና አደረገና ወደኔ አየት በማድረግ ፤ «መንገዱ ሰላም ነው ?» አለኝ ።

ወደ መንገዱ እንደ ገና ተመለከትኩና ፣ «ደህና ነው ፣ ምንም የለም» አልኩት ።

«አንድ ደምፅ የሰማሁ መስሎኝ ነው» አለ ።
«ምናልባት ነፋሱ፡ ወይም ዝናቡ ሊሆን ይችላል» አለ ጋርቪያ ።
«ምናልባት ሊሆን ይችላል» በማለት ጃክ ወረቀቶቹን መመርመር ቀጠለ ።

«ለፓስፖርቱና ለመታወቂያዎቹ የሚሆን ፎቶግራፍ አምጥታችኋል ?» አለ ጋርቪያ ።

«አዎ ! አምጥተናል ።»

«ጥሩ ነው ፣ ጆ ማጣበቂያና ማኅተሙን ይዞአል ፣ በወረቀቶቹ ላይ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለበትም» አለ ጋርቪያ ።

ወዲያው ድምፁ አነስተኛም ቢሆን የሰው እግር ኩቴ ጓ ! ሲል ሰማሁት ። «ጃክ !» ብዬ ተጣራሁ ። ተመለከተኝ ። «የሰው ኩቴ የሰማሁ መሰለኝ» አልኩት ።

«አንዱ ክፍል የተንጠለጠለ የላስቲክ መጋረጃ ነፋስ ጥሎ ሊወድቅ ሰምተሽ ሊሆን ይችላል» አለ ጋርቪያ ።

ጃክ ትኩር ብሎ ተመለከተውና ፣ «እዚህ ቦታ አንድም የላስቲክ መጋረጃ እንደሌለ አይቻለሁ» አለው ።

ጋርቪያ ትከሻውን በመነቅነቅ ፣ «አይጥ ፣ ወይም አሞራ ሊሆን ይችላል ። እንደዚህ ዓይነት ቤት ውስጥ የተለያየ ድምፅ መስማት አዲስ አይሆንም ። እንደ መሰለኝ ትንሽ ተጨንቀሻል አደደል ? » አለ ። ሁላችንም በጸጥታ ቆመናል ። ጃክ አሁንም ወረቀቶቹን እንደ ያዘ ነው ። ያለ ምንም ጥርጣሬ ያን ጊዘ የሰው ኩቴ በቀስታ መሬት ላይ ሲያርፍ ሁላችንም ተሰማን ።

«አንተ ከሃዲ» ብሎ በመጮህ የያዘውን ወረቀት ጋርቪያ ፊት ላይ ወረወረው ።

ጋርቪያ እንዴት እንዳወጣው አላውቅም ፤ ትልቅ ጩቤ አውጥቶ ወደ ጃክ በመወደር እየተጠጋው ነው ። ጩቤው ያብለጨልጫል ፤ ጃክ ሽጉጡን ለማውጣት ኪሱ ሲገባ ጋርቪያ ወደ ፊት ሰነዘረ ።

ጃክ ወደ ኋላው ዘለል አለና ፣ «አሩጭ» አለና ጮኸብኝ ። እሳው እንደ ቆምኩ ሽጉጡን ከኪሴ ሳላወጣ ወደ ጋርቪያ አነጣጥሬ ተኮሰ ። ጋርቪያ ወደ ኋላው ተንገዳገደ ። ግን አልወደቀም ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ፓስፖርት የሚያዘጋጀው ሰውዬ ጥግ ቦታ ኩርምት ብሎ አንጉቱን በመድፋት ጭንቅላቱን ለመከላከል እጆቹን ራሱ ላይ አድርጓል ።

ጋርቪያ መመታቱ ገርሞት ይሆን እንጃ ፤ እጆቹን ዘርጋ አድርጎ ሰውነቱን ሲመለከት ፣ ጃክ ሽጉጡን አውጥቶ ሁለት ጥይት በመተኮስ ሲመታው ዐይኑ ፈጠጠና ለመናገር አፉን ከፈት ሲያደርግ በአፉና በአፍንጫው ደም ፈሰሰና ቀስ እያለ ወደ መሬት ወደቀ ።

ጃክ እጄን ያዘና ወደ ውጭ ሮጥን ፤ ከባሕሩ ዳርቻ ከቆመች ኦኔ ስተኛ ጀልባ ውስጥ በበሰበሰው ድልድይ እየተሻገሩ ሰዎች ወደ እኛ ሲመጡ አየን ።

እንደ ገና ወደ ውስጥ ገባንና በአንዱ ክፍል መስኮት ዘለን ወደ መኪናችን ሮጥን ።

ብቻዬን መሮጤን አስታወስኩና ዞር ብዬ ወደ ኋላዬ ስመለከት ጃክ በኔና በሆቴሉ መካከል ሆኖ ሁለቱን ሽጉጦች በማውጣት የፈራ ረሰውን የቤቱን ግድግዳ ተገን እያደረገ በሚመጡት ሰዎች ላይ ይተኩሳል ። የተወሰኑ ሰዎች መሬት ላይ ተንተው ወደኛ በማለም ይተኩሳሉ ።

ከዚህ በፊት ያየሁት አሜርና ወፍራም ሰውዬ ፣ ጥቁር የዝናብ ልብስ ለብሶ በሞቴሉ ጥግ ቀስ ብሎና ተረጋግቶ በተኩስ መካከል እጆቹን ኪሱ ውስጥ ከቶ ወደኛ ሲመጣ አየሁት ። ከተኩሱና ከኛ ጩኸት በበለጠ የሰውየው አመጣጥ አስፈራኝ ።

ሽጉጤን አወጣሁና ወደኛ ተዝናንቶ ወደ ሚመጣው ሰው ጥይቴ እስኪያልቅና ፣ የማለቁን ድምፅ እስክ ምሰማ ድረስ ተኮስኩ ። አሁንም ሰውየው እየመጣ ነው ።

ከቦርሳዬ ውስጥ ሽጉጤን ላወጣ ስል ፣ ጃክ ዐይኑን አፍጥጦና አፉን ከፍቶ ቶሎ ቶሎ እየተነፈሰ አጠገቤ ደረሰና ፣ «ጄኒ...» እንዳለኝ በአንድ እግሩ በርከክ ብሎ እጁን ወደ ኋላው አዙሮ ጀርባውን ዳሰሰ ። ለካስ ተመትቶ ኖሯል !

አጠገቡ ስለ ነበርኩ እንደ መገመትም ፣ እንደ መገፍተርም እያ ደረኩ አጥሩ አጠገብ ደረስን ።በተበጣጠሰው ሽቦ በኩል ስገፋው ሙሉ በሙሉ በፊቱ ስለ ወደቀ ጀርባው በሙሉ በደም መጨማለቁን ተመ ለከትኩ ።

እያለቀስኩ እንደ ምንም በእግሩ አቆምኩት ። ሚዛኑን ጠብቆ ሊቆምልኝ አልቻለም ። እጥፍጥፍ አለብኝ ። የሚተኮሰው ጥይት በጀሮአችን እያፏጨ ያልፋል ፤ በቆሙት በሁለቱም መኪኖች ላይ ጥይት ይዘንብባቸዋል ።

ጃክን የሲትሮይን የኋላ በር ከፍቼ ወደ ውስጥ ግማሽ ሰውነቱን ካስገባሁ በኋላ ፣ እግሮቹንም አጥፌ ወደ ውስጥ ገፍትሬአቸው በሩን በፍጥነት ዘግቼ ቶሎ ወደ መኪናው ገባሁ ። ሞተሩንም አስነሥቼ በፍጥ ነት አንዴ ፣ ወደ ግራ አንዴ ወደ ቀኝ መሪውን እየጠመዘዝኩ ተፈ ተለኩ ።

በጣም ከፍተኛ የሰውና የመሣሪያ ጩኸት እያሰሙ ሰዎች ወደኛ ሲሮጡ ይታያል ። ሊደርሱብኝ ግን አልቻሉም ። ከኋላ በኩል በመስ ታወት ስመለከት ቅድም ያየሁት ሰውዬ ወይ አይሮፕ ወይ አይተኩስ ዝም ብሎ ወደ ፊት ሲመጣ አየሁት ።

☆ ☆ ☆

ጃክ ራሱን ማወቅ ሲጀምር ፣ «ደህና ነሽ ?» ብሎ ጠየቀኝ ። ፈገግ ለማለት ሞከርኩና የታችኛውን ከንፈሬን በመንከስ ግምባሩን በእጄ ነካ አደረኩት ፤ ከፍተኛ ትኩሳት አለበት ።

ፎጣ አንሥቼ በቀዝቃዛ ውሃ ነከርኩና ግምባሩ ላይ አደረኩለት። ሕመሙ እየተሰማውና እያቃሰተ ፣ «በጀልባ ነው የመጡት ፣ ባሕሩንም

መቆጣጠር ይገባን ነበር» አለ ። ድምፁ ከአሁኑ ጐርናና የሽማግሌ ድምፅ መስሏል ።

ራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁና ፥ «አዎ ! በቀላሉ ገምተናቸው ነበር። ለመሆኑ ጋርቪያ በዚህ ተንኰል ውስጥ ይኖርበታል ?» አልኩት ።

ለመናገር የተቸገረ ቢሆንም ፥ «በደምብ አለበት ፥ ምናልባት ያንን ያሳየሁትን አልማዝ እንደሚሰጡት ቃል ገብተውለት ይሆናል ወይም ከዚያ የበለጠ? አየሽው አይደል ?» አለኝ ።

ማንን ማለት እንደ ፈለገ ገብቶኛል ። «ልገድለው ሞክሬ ነበር ። ያለኝን ጥይት በዚያ የውሻ ልጅ ላይ ብጨርስበትም ፥ ከምንም ሳይቆጥረው ዝም ብሎ ወደኛ ይመጣ ነበር» አልኩት ።

«በጣም ጥሩ ነው ያደረግሽው ፥ እውነቴን ነው ጥሩ ነው ፥ ከተመታው በኋላ ስለ ሆነው ሁኔታ በሙሉ ንገሪኝ» ብሎ ዐይኖቹን ጨፈነ። እንቅልፍ ቢወስደው ደስ ባለኝ ነበር ። ስለ ሆነም በጥያቄው መሠረት መናገር ጀመርኩ ።

«ዋናው መንገድ እንደ ገባሁ ወደ ሰሜን መታጠፍ ሲኖርብኝ ተሳስቼ ወደ ደቡብ ታጠፍኩ...»

ዐይኖቹን የጨፈነ ቢሆንም ፥ እንደሚሰማኝና እንደ ገባው ሰውነቱን ሲያንቀሳቅስ አየሁት ።

«መንገዱን አልዘጉብሽም ?»

«እኔም ይዘጋል ብዬ ገምቼ ነበር ፤ ግን አልተዘጋም ።»

«እንደሚይዙን በጣም እርግጠኞች ነበሩ ማለት ነው ። አልተከተሉሽም ?»

«አልተከተሉንም ፥ ለማረጋገጥ ወደ ኋላዬ እመለከት ነበር ። ምናልባት ጋርቪያ የካዲላኩን ቁልፍ እኪሱ ስለ ያዘ ከሱ እስከሚወስዱ ድረስ ጠፍቶባቸው ሊሆን ይችላል ። ዋናው መንገድ እንደ ገባሁ መጀመሪያ ወደ ደቡብ ፥ ከዚያም ወደ ሰሜን ተጉዤ ወደ ቤት በቀጥታ መጣሁ ።»

«ወደ ቤት አልሽኝ? እዚህ እስክደርስ ራሴን ስቼ ነበር ?»

«መጀመሪያ ሳይህ ግማሽ በግማሽ ራስህን ስተህ ነበር ፤ እዚህ ደርሼ ስመለከትህ... እንዴት መሰለህ ...»

የሽሙጥ ፈገግታውን አሳየኝና ፥ «በቀላሉ የምሞት ሰው አይደለሁም ። ለመሆኑ እንዴት አድርገሽ ወደ መኝታ ክፍል ልታስገቢኝ ቻልሽ ?»

«እንጉቴ ላይ እጅህን እንድትጠመጥም አደረግሁና እየተንገዳ ገድን ስንሔድ የተወሰኑ መንገደኞች አዩን ። 'ለምን እንደዚህ እስክ ትሆን ትጠጣለህ?' ብዬ ስጮህብህ፣ በሐዘኔታ ተመለከቱንና መንገዳቸ ውን ቀጠሉ ። የጨለመ ስለሆነ መመታትህን ማየት አይቻልም ነበር ።»

«ብዙ ደም ፈሰሰኝ ?»

«እንዳሰብከት አይደለም ፣ መኪናው ውስጥ በጣም ትንሽ ፈሶ ሃል» አልኩት ። ግን ውሸት ነው መኪናው ውስጥ ብዙ ደም ፈሶታል ።

«እንዴት ይመስልሻል ?»

«ይሄን ያህል የሚያሠጋ አይደለም ፤ የሚታየው ትንሽ ቁስል ነው ። ከመድኃኒት ቤት የቁስል መድኃኒት ፣ ፋሻና ፕላስተር እንዲ ሁም ሥቃይ የሚያስታግሥ ኪኒን ገዝቼ በፋሻው ካሰርኩልህ በኋላ መድኃኒቱን በትንሽ ብራንዲ አጠጥቼሃለሁ ።»

«ትንሽ ቁስል አልሽኝ፣ የት ቦታ ላይ ነው ?»

«ከጐድንህ በታች ከአከርካሪ አጥንትህ ትንሽ ወደ ግራ ካለው ወገብህ ላይ ነው ።»

«ጥይቱ ወጥቶአል ?» አለኝ በደከመ ድምፅ ።
እንዳልሰማ ሰው ዝም አልኩት ።
«ጥይቱ ወጥቷል ?» ብሎ በድጋሚ ጠየቀኝ ።

«አልወጣም ! ጥይቱ ሰውነትህ ውስጥ የቀረ ስለ ሆነ፣ ወደ ሆስ ፒታል ሔደህ ዶክተር ማግኘት አለብህ ።»

«አስፈላጊ አይደለም ። ሆስፒታልም ሆነ ዶክተር አያስፈልገ ኝም ። አሁን ጤንነት እየተሰማኝ ነው ።»

እንደ ሚለው ጤነኛ አይደለም ። መነጣት አቅቶት አልጋ ላይ እንደ ተኛ ነው ። አልፎ አልፎ ከተኛ በኋላ እንደ በረደው ሰው ስለ ሚያንዘፈዝፈው ብርድ ልብስና አንሶላ እደራርብለታለሁ ።

ትኩሳቱ በተነሣ ቁጥር ሰውነቱ በሙሉ ይንዘፈዘፍና ላብ ጥምቅ ያደርገዋል ።

ጨክ ! ሁሉም ነገር ቢቢታና ፖሊሶችን ጠርቼ እጂን ብሰጥ ፣ አንተም ሆስፒታል ገብተህ መታከም ትችላለህ» አልኩት ።

ዐይኑን ገለጥ አደርጎ አትኩሮ ተመለከተችኝና፣ «ይሄን ሁሉ ጥፋት ከፈጸምን በኋላ ነው እጃችንን የምንሰጠው፣ ጅኒ እንደዚህ አትበይ ።

ቁስሉ በቀላሉ የሚደን ነው ። ይሄን ያህል ለሞት የሚያደርሰኝ አይደለም ።»

ፈውሽትህን ነው ።»

ሃውሽቴን አያያለም ፤ ደህና እየሆንኩ ነው ፥ ብዙም ሕመም አይሰማኝም ፥ አንድ ጥያት እስከዚህም አይጐዳም ። ባይወጣም ራሱ ቁስሉ ያድናል» አለኝ በለዘጣታ አነጋገር ።

ምንም መልስ አልሰጠሁትም ።
እንደ ገና ዐይኑን ጨፈነና ፥ «ቃል ግቢልኝ ፤» አለኝ ።
«ለምኑ ነው ቃል የምገባልህ ፤»

«አኔ ይሁን ካላልኩሽ በስተቀር ፖሊስም ሆነ ዶክተር ላትጠሪ ቃል ግቢልኝ ፣ »

«እሺ አንተ ካልፈቀድክ በስተቀር ማንንም ላለመጥራት ቃል እገባለሁ» አልኩት ።

እንቅልፍ እንደ ወሰደው ፎጣው ፥ ጀኬቱ ፥ ሸሚዙ ፥ የውስጥ ሱሪው ፥ ካልሲውና ጫማው በደም ተበክሎ ሰለ ነበር አጠብኩት ። መኪናው ውስጥ ከኋላ ወንበር የፈሰሰውን ደም ሳላጥብ ተውኩት ።

ብራንዲ በብርጭቆ ቀዳሁና አልጋው አጠገብ ቁጭ ብዬ ጀኮን እየተመለከትኩ ጠጣሁ ። ቀስ እያለ ሲተነፍስ አየሁት ፤ ስለ እማያስለውና ስለ እማያንኩራራ አተነፋፈሱ ጥሩ ነው ብዬ ገመትኩ። እንዳለው ቁስሉ በራሱ ይድናል የሚል እምነት አደረብኝ ።

የዚያን ለት ማታና በማግሥቱ ምንም ማሰብ አልቻልኩም ። እውጭ የማታየው ጉም ከሰውነቴ ውስጥ የገባ ያህል ተሰማኝ ስለዶክተር ፥ ስለፖሊስና ስለመጥፋት ሐሳብ ይመጣብኛል ። አንዱንም ሳል ጨብጠው ሁሉም ሐሳቤ እልም ይልብኛል ። በምንም ነገር ላይ ማተኩር አልቻልኩም ። ገዘም ብዬ ብቻ መውደቂያውን የማያውቅ የተንፋሳስቲክ ይመስል በአየር ላይ ተንሳፍፌያለሁ ።

ግድረግ የሚገባኝን ሁሉ አደርጋለሁ ። ለራሴ ምግብ አዘጋጅቼ እበላለሁ ፤ ለጀክ አዘጋጅቼ አበላዋለሁ ፤ ሰውነቱን አጥበዋለሁ ፤ እራሴንም አጥባለሁ ፥ ያስፈለገኝን የመጠጥ ዓይነት እጠጣለሁ ፤ በሩ መቆለፉን ፥ መጋረጃዎች መጋረዳቸውን አረጋግጣለሁ ።

ይሄን ሁሉ የማደርግ ቢሆንም ፥ ምን ምን እንደ ፈጸምኩ በትክክል አላውቅም ። የጠፋችውና በደመ ነፍስ የምትንቀሳቀሰዋ ጀኒ ሼን ሆኛለሁ ።

እንደ እኔ ከሆነ ይሄን ሁሉ ሥራ የምሠራው በተፈጥሮ አስገዳጅ ነት ነው ። አልናደድም ፤ ለማልቀስም አይከጅለኝም ። ብቻ ከሚደረገው እንቅስቃሴ ራሴን በመገንጠል በሌላ ዓለም የሚኖር ሰው መሰልኩ ። ያሳለፍኳቸውን ሐያ አራት ሰዓታት ምን በማድረግ ላይ እንደ ነበርሁ ለማወቅ አልቻልኩም ።

ልክ አዲስ ሰው በአዲስ ዓለም እንደሚኖረው ሁሉ እተነፍሳለሁ ፤ እበላለሁ ፤ የተፈጥሮ ግዴታ ስለ ሆነ እተኛለሁ ።

ሐሙስ ዕለት ማታ ፡ ጃክ አልጋ አጠገብ ከምተኛበት ወንበር ላይ ቀሰቀሰኝና ፡ ብራንዲና ውሃ በብዛት አጠጣሁት ። ከዚያም ቀዝቃዛ ውሃ በጨርቅ እየነከርኩ ግንባሩ ላይ አደረኩለት ። የሆነ ነገር ይናገራል ። ግን ምን እንደ ሆነ አልሰማውም ። ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው ። መተኛቱ የጥሩ ነገር ምልክት መስሎ ታየኝ ። እንደ አሰብኩት ከሆነ ሁሉም ነገር የጥሩ ነገር ምልክት ነው ።

ጠዋት ከእንቅልፌ ስነሣ የዐሐይ ብርሃን በማየቴ ፡ ይሄም ሌላው የጥሩ ነገር ምልክት መስሎ ታየኝ ። እንደ እውነቱ ከሆነ የዐሐይ ብርሃን ሙሉ በሙሉ የታየበት ጠዋት ሳይሆን ፡ በደመናው ውስጥ ዐሐይ ብልጭ ያለችበት ቀን ነው ። ጃክ እንደ ተኛ በሩን በላዩ ላይ ቆለፍኩና ለምግብ የሚያስፈልገኝን ሸቀጣ ሸቀጥ ለመግዛት ወጣሁ ።

ወደ ሱቆች ሔጄ አስፈላጊውን ምግብና የብርቱካን ጭማቂ ከገዛሁ በኋላ ፡ በዚህ አካባቢ የሚታተመውን የማያሚ ጋዜጣ አነበብኩ ።

ሰው በማይገኝበት በፈራረሰው ሆቴል ውስጥ ስለ ተፈጸመው ተኩስና ግድያ ምንም ወሬ የለም ። በቴሌቪዥንም ምንም አልተነገረም ። እንደ አሰብኩት ከሆነ አንቶኒዮ ሮሲ ጉቦ ከፍሎ እንዳያወሩ አድርጓቸዋል ።

ጃክ ከእንቅልፉ ወደ አራት ሰዓት ላይ ነቃና በማንኪያ ዳቦ በወተት ፈትፍቼ ትንሽ ካበላሁት በኋላ ፊቱን አዙሮ ተመልሶ ተኛ ።

ምንም ጤነኛ አይመስልም ፤ ፊቱ በጣም ገርጥቷል ። ሰውነቱም እየመነመነ መጥቷል ። ያሰርኩለትን ፋሻ ለመለወጥ በደረቱ ገለበጥኩት ፡ ይደማ የነበረው በመጠኑ ቆሞአል ፤ ጥይቱ የገባበት ቀዳዳም በመጠኑም ቢሆን እንደ መድፈን ብሎ ሰማያዊ ቀለም የተቀባ መስሎአል ። የላብ ወይም የደም ሽታ ሳይሆን በጣም የሚያስጠላ ሽታ ይሸታል ።

ዐርብ ዕለት ማታ ፡ ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሞ መሆን አለበት ፤ ቶሎ ቶሎ ውሃ ጠማኝ እያለ ውሃ ፡ ወተትና ቡና በብዛት ጠጣ ። ለአራት ጊዜ ያህል ወደ ሽንት ቤት ደግፌ ወሰድኩት ።

ሽንት ቤት አብሬህ ልቆይ ብለው እምቢ አለኝ ። ስለዚህ እንደ ፈለገው ይሁን በሚል ተውኩት ። ተጸዳድቶ ሲጨርስ ወደ አልጋው ደግፌ እመስድና አስተኛዋለሁ ።

አንድ ጊዜ ሽንት ቤት ገብቶ ሲወጣ ውሃውን መልቀቅ ረስቶ ወይም አቅቶት ይሁን አልገባኝም፡የሽንት ቤቱ መቀመጫ በደም ተበክሎ አየሁት ።

ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ከእንቅልፉ እንደ ገና ነቃና ሲጋራ እንድሰጠው ጠየቀኝ ።

«ጃክ ! እርግጠኛ ነህ ማጨስ...»

ዝም ብሎ አፍጥጦ ሲመለከተኝ ፣ ሲጋራውን አቀጣጠልኩና በአጄ ይዤ በከንፈሩ አስያዝኩት ። በዚህን ጊዜ እጄን ያዝ አደረገና ወደ አፉ አስጠግቶ ሳበው ።

«እናቴን በደንብ ሳላውቃት በልጅነቴ ነው የጠፋችብኝ» አለኝ ።

«ምንም ዓይነት ንግግር አያስፈልግም ፣ ዝም ብለህ አጭስና ተኛ» አልኩት ።

«አይዞሽ ! እስከዚህም መጥፎ አይደለም ፤ በርግጥ አብዛኛው ታሪኬ የከፋ ቢሆንም ፣ ሙሉ በሙሉ አይጋለም» አለኝና እጄን ዘርጋ ሲያደርገው ሲጋራው ከእጁ ላይ ወደቀ ። ሲጋራውን ከወለሉ ላይ አንሳሁና መተርኩሻው ላይ ተርኩሼ ስመለከተው ፣ ዐይኑ ተጨፍኖ ደረቱ ድረስ የለበሰው ብርድ ልብስ ከፍና ዝቅ ሲል መተንፈሱን አረጋገጥኩ ።

«ስለ ጭቃማው ሸለቆ ንግሬሽ የለ ?» ሉለኝ ።
«አዎ ጃክ !» ነግረኸኛል ።
«አዬ ዲክ ! እንዴት ያለ ጭንቅላት የነበረው ልጅ ነበር ።»
«አዎ ጥሩ ልጅ ነበር ።»
«ኤሪኔ ወዴት ሔደ ?» አለኝ ።
«የማን ኤሪኔ ?» አልኩት ።
«ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እዚህ እልነበረም እንዴ» አለኝ ።
«አዎ ነበር ወጣ ብሎአል ፣ ቶሎ ይመለሳል» አልኩት ።

«ጋሪዎቹ ጥዋት ለሥራ ሲወጡ ማየት እንዴት ደስ ይላል ! ጉሀ ሲቀድ ፣ ጤዛ ሜዳውን አልብሶት...» መልስ አልሰጠሁትም ።

«ሕፃን በነበርኩ ጊዜ አለቅስ ነበር ። አሁን ግን ማልቀስ ምን ይጠቅማል ? ያ የውሻ ልጅ ሮሲ !»

«ምንድነው የምታወራው ?»

«እኔና ዲክ ስለ አንቺ እናወራ ነበር ። ዲክ እንደ ቢያ ስትለብሺ በጣም ደስ ይለዋል ። እኔ ግን ፥ ራስሽን ጂኒን ስትሆኝ ደስ ይለኛል ።»

«በጣም አመሰግናለሁ» አልኩት ።
«አልን አይተሽዋል ?»
«አላየሁትም»

«ፒተር ክረምቱን ለማሳለፍ ከተማ ውስጥ ነው ያለው ። እንደ ሚለው ከሆነ የካርተር ልጆችም አብረውት አሉ ። ሽሚስኪ ወደ ጠረፍ ከተማ ሔዳለች ። ሐጋስ ውስጥ እየተሳካላት ነው ። ግን ሽሚ ስኪንን ታውቂያታለሽ ?»

«እስቲ ዝም በልና ተኛ ጃክ» አልኩት ።

«እንዴት እንደ ሔደች ይገርመኛል! ብዙ ጊዜ ከሽሚስኪ ጋር ለመተኛት እፈልግ ነበር ። ሳይሳካልኝ ቀረ ። አሊስ ፥ ሌላ ብራንዲ ይፈጠልሽ ?»

«አልደግምም ፤ የጠጣሁት ይበቃኛል» አልኩት ።

«ያንን የሰይጣን ልጅ መቅበር አለብን ። ዛሬ ወደ አሬንስ የሚ ሔድ ጭነት አለብኝ ። አራግፌ ስመለስ ከአባባ ጋር ሆነን ያለብነውን እንፈጽማለን ።»

«እሺ ይሁን ፥ ጥሩ ሐሳብ ነው» አለኩት ።

«በጣም ደስ የሚል ዝርፊያ ! እጅግ በጣም ግሩም ወንጀል ! ልክ ነኝ አይደል ?»

«አዎ ልክ ነህ ።»

«አቤት ! እንዴት ደክሞኛል መሰለሽ ። ወደ ጭነት መኪናው መሔድ አለብኝ ። ከዚያ በፊት ግን ትንሽ ልተኛ ።»

«ጥሩ ሐሳብ ነው ፤ ትንሽ ተኛ» አልኩት ።

እንዲሁ የባጥ የቆጡን ሲቃዥ ቆየና እንቅልፍ ሲወስደው፥እኔም ወንበሩ ላይ ገደም ብዬ ተኛሁ ።

ከእንቅልፌ ስባንን አልጋው ጫፍ ላይ እግሩን አሳርፎ ቁጭ ብሎአል ።

«ጃክ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ተኛና ብርድ ልብሱን ልበስው ።»
«ውሃ ጠማኝ የብርቱካን ጭማቂ ስጪኝ ።»

«የብርቱካን ጭማቂውን ጠጥተህ ጨርሰኽዋል።ከፈለክ ውኾትና ቡና ፥ ቢራ ፥ ኮካ ኮላ ፥ ብራንዲ ፥ ውሃ ሞልቶልሃል ልስጥህ ።»

«የብርቱካን ጭማቂ ነው የምፈልገው ።»

ግድግዳ ላይ የተንጠለጠለውን ሰዓት ተመለከትኩት ፤ ከምሽቱ ሀለት ሰዓት ሆኖአል ።

«ጃክ ! በዚህ ምሽት የት ሔጂ ነው የብርቱካን ጭማቂ የማገኘው ?»

በመገረም ተመለከተኝ ። ሲናገር ሙሉ በሙሉ ጤነኛ ይመስላል ። «ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ክፍት የሚሆኑ የጭማቂ መሸጫዎች ድልድዩን ተሻግረሽ ታገኝያለሽ ። በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ገዝተሽ መመለስ ትችያለሽ ። የቀዘቀዘ የብርቱካን ጭማቂ መጠጣት በጣም አሰኝቶኛል ።»

«ከሔድኩ ግን ተኝተህ ትጠብቀኛለህ ?»

«ከመተኛት ሌላ ምን አማራጭ አለኝ ብለሽ ነው ?»

አልጋው ላይ ጋደም ሲል ፥ እግሮቹን አልጋው ላይ አወጣሁና እስከ አገጩ ድረስ ብርድ ልብሱን አልብሼው ጐንበስ ብዬ የደረቀውን ከንፈሩን ሳም አደረኩት ።

«አሁኑኑ የብርቱካን ጭማቂ ይዤልህ እመጣለሁ ጃክ! በጣም እወድሃለሁ !» አልኩት ።

«አዎ ትወጅኛለሽ ፥ እስቲ እንደ ገና በይው ።»

«በጣም... በጣም እወድሃለሁ !»

«እኔም በጣም እወድሻለሁ !»

ከመውጣቴ በፊት በሩ ላይ ቆም ብዬ ዞሬ ተመለከትኩት ። በቀስታ ይተነፍሳል ፤ በሩን ከኋላዬ ቆልፌ ወጣሁ ።

ሦስት ደርዘን የብርቱካን ጭማቂ ገዛሁና መኪናዬን በፍጥነት እየነዳሁ ተመለስኩ ። ከሐያ ደቂቃ በላይ አልፈጀብኝም ።

ከፍላችን ስደርስ በሩ ወለል ብሎ ተከፍቷል ።

ወዲያውኑ ዐወቅሁት ። ነገሩ እየገባኝ በደመ ነፍስ ወደ ክፍሉ ገባሁና የብርቱካን ጭማቂውን ማቀዝቀዣው ውስጥ አስቀመጥኩት ።

አልጋው አጠገብ ከሚገኘው ጠረጴዛ ላይ የተሞነጫጨረ ማስታወሻ አግኝቼ አነበብኩት ።

«የኔ ቆንጆ ፥ የኔ ጉዳይ አብቅቷል ፥ ደሜ ፈሶ እያለቀ መሆኑን ዐውቀዋለሁ። ስለዚህ ወደ ባሕሩ ዳርቻ ለመንሸራሸር

ስለ ፈለኩ ወጥቻለሁ ። ሁሉንም ንብረት ውስጂው ። ማድረግ ያለብሽን ነገር ሁሉ አድርጊ ። ከዚህ አካባቢ ጥፊ ። ጉዞሽን ቀጥይ ፡ ይሳካልሻል ። እንደ ሚሳካልሽ ምንም አልጠራጠርም ። ጂኒ እወድሻለሁ ! ከዚህ በፊት ነግሬሽ የለ ፡ እወድሻለሁ !»

ጽሑፉ ከመደምደሚያ ላይ አልደረሰም ። የተጻፈበት እርሳስም መራት ወድቋል ።

ውጭ ወጥቼ ወደ ባሕሩ ሔድኩ ። የሔደበትን ኩቴ ያየሁት መስለኝ ። ግን አይደለም ። ያየሁት የመሰለኝ በሐሳቤ የኩቴው ቅርፅ ይኖራል ብዬ ስለ ገመትኩ ነው ። ውሃው ጉልበቱ እስኪ ደርስ ድረስ ወደ ባሕሩ ገባሁ ።

ባሕሩን በጨለማው ውስጥ ትኩር ብዬ ተመለከትኩት ፡ የማየው ነገር ቢኖር የባሕሩ ማዕበል የሚያነሣውና መልሶ የሚያሳርፈው ውሃና ነጭ ዐረፋ ነው ። ጨረቃ ያልወጣች ቢሆንም አልፎ አልፎ በተቆራረጠው ደመና መካከል ከዋክብት ይታያሉ ። አንድ የሚንዝ አውሮፕላን መብራቱን ብልጭ ድርግም እያደረገ አለፈ ።

ለትንሽ ደቂቃ ያህል ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ተጋብቼ በሐሳብ ስዋልል ቆየሁና ፡ ወደ መኝታ ክፍሉ ተመልሼ ዕቃዎቹን ማዘ ገጃጀት ጀመርኩ ።

አላስፈላጊ የሆኑ ልብሶችን ተውኳቸው ። የያዝኩት ነገር ቢኖር የራሴን ልብስ ፡ ጌጣጌጦቹንና መሣሪያዎቹን ብቻ ነው ።

የጃክን ልብስ እዚያው መኝታ ክፍሉ ውስጥ መታጠቢያ ቤት አስቀምጬው ወጣሁ ።

ለወኪሌ ለሶል ፋበር የጻፍኩት ደብዳቤ

ለተወደድክው ለሶል ፋበር ፡

ምንም እንኳን ይሄ የምልክልህ የመጽሐፍ ረቂቅ ከብዙ ዓመታት በፊት በሌላ ዓለም ውስጥ ስኖር የጀመርኩት እንደ ሆነ ብታስታውስም ፡ ድሮ እንደ ምታደርገው ለሕትመት የቀረቡ ረቂቆችን የመጀመሪያ ሃምሳ ገጽና የመጨረሻውን ሃምሳ ገጽ ብቻ እንደ ምታነበው ዐውቃለሁ ።

ሆኖም ይሄኛውን ረቂቅ ዳር ከዳር ማንበብ መቻል አለብህ ። ውሸት የለውም !

ሶል ! በተቻለ መጠን መጽሐፉን አሳትመህ ለመሸጥ ሞክር ። ይህን ስልህ የገንዘብ ችግር ኖሮብኝ አይደለም ። የብንደንበርግና

ልጅቹ ጌጣጌጥና ብዙም ብር አለኝ ። መጽሐፉ እንዲሸጥ የፈለኩት መጽሐፉን ያነበቡ ሰዎች እንደ ፖሊሶች በወንጀለኛነት እንዳያዩኝና ትክክለኛ ታሪኬንም እንዲረዱልኝ ነው ።

የመጽሐፉን ሽያጭ አስቀምጥልኝ ፣ ፖሊሶች ሳያውቁ በቅላሉ መጥቼ መውሰድ እችላለሁ ።

ጃክ እንዳስተማረኝ ያለንበትን ሥርዓት በቀላሉ ማታለል መቻሉን አረጋግጫለሁ ።

ይህን ፖስታ የላኩት ኒውኦርሊየንስ እንዳለሁ ነው ። የፖስታውን ማኅተም ፖሊሶች እንደሚያዩት እርግጠኛ ነኝ ። ዋናው ነገር ግን ፡ ለአንተ ፖስታው በደረሰህ ጊዜ ከኒው ኦርሊየንስ ከአንድ ሺ ኪሎ ሜትር በላይ ርቄ መሔዴን አያውቁትም ።

ሶል ! ለጓደኛዬ ለላውሪ ስልክ ደውለህ በሕይወት መኖሬን ንገራት ። እንዲሁም ለአልዶ ባይንደርም ደውልና ከዚህ በፊት የነገረኝ ሁሉ ትክክል እንደ ሆነና እውነትም ከትክክለኛውን ሕይወት ተለይቼ የኖርኩ መሆኔን ማወቄን ንገረው ።

ሶል ይህን ጽሑፌን ወደ ፖስታ ቤት የማስገባው እግረ መንገዴን ከኒው ኦርሊየንስ ለመውጣት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ስሔድ ነው ።

ዛሬ አንድ እንግዳ ሰው ካረፍኩበት ሆቴል ድረስ መጥቶ ስለ እኔ ማጠያየቁን አስተናጋጁ ነገረኝ ። አስተናጋጁ እንዳለኝ ከሆነ ስለ እኔ ምንም የተናገረው ነገር የለም ። ግን ሰውየው ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን ስለ ማውቀው፡የአስተናጋጁ መናገር ወይም አለመናገር ለውጥ አያመጣም ።

የትም ብገባ ያገኝኛል ። ይሄንን በደንብ ዐውቃለሁ ። በሚቀጥለው ቦታ ላይ ግን ፡ ከመሸሽ ይልቅ ለየት ያለ መልክ እንዲኖረው አደርጋለሁ ።

አንባቢዎች ለማንበብ የሚፈልጉት ፡ መጽሐፍ መጨረሻው የሚያምረውን ነው ያልከኝን ታስታውሳለህ?

እኔም ይሄንን በሚያምር መልኩ መፈጸም አለብኝ ። ከሚቀጥለው አገር ስደርስ ፡ አንቶኒዮ ሮሲ እንዲያገኘኝ እደርጋለሁ ። ከዚያ በኋላ ይሄን የውሻ ልጅ እገድለዋለሁ ! ገባህ? .....

ወዳጅህ

ጆኒ ሼን

ሲመን ... ለአሳታሚው ድርጅት የሚቀርቡትን መጻሕፍት የሚገመግም ዋናው አርታኢ ነው ።

« ... ይህ ረቂቅ» አለ ወደ እኔ ጽሑፍ እያመለከተና ለመ ንካተ ...ተጠየፈ ። «ተቀባይነት የለውም ።»

«መጽሐፉን አንብበኸዋል ?»

«አይረባም ! »

«በጥቅሉ ከመነጋገር ይልቅ በምን በምን ነጥቦች ላይ ስህተት እንዳለው ለይተህ ልትነግረኝ ትችላለህ ሲመን ?»

«ደስ ይለኛል ! ለ... በገጽ ሃምሳ አራት ላይ ልጅቷ በታክሲ ሄደች ፣ ምክንያቱም ዝናብ ስለ ነበረ ነው ሲል ፣ ከሁ ለት ... በፊት ግን ቀኑ ፀሐያማ እንደ ሆነና ምንም ዳመና እንደ ማይታይ ገልጸሻል ። በገጽ ሃምሳ ሁለት ላይ ደግሞ ፣ 'ጨረቃዋ ሐብሐብ በመምሰል በሰማይ ላይ ተሰቅላለች' ብለሻል ። ይህስ ምን ማለት ነው ? ... »

«ቦቃ ! ቦቃ ! የመሰለህን የመከራከሪያ ነጥቦች አዘጋጅ ተሃል !»

« ... በጠመንጃ ተኩሶ ሲመታው ድምፁ 'ካቻው !' አለ ብለሻል ... ከመቼ ወዲህ ነው የጠመንጃ ድምፅ 'ካቻው' የሚ ለው ? ...»

ከመጽሐፍ የተወሰደ